አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሒውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ድኅረ ምረቃ ፕሮግራም

# የለቅሶ ሥርዓት ክወና በደቡብ ጎንደር ዞን

በፎክሎር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት

በለማ ንጋቱ

የጥናቱ አማካሪ ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ (ተ/ፕሮፌሰር)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ነሐሴ 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የለቅሶ ሥርዓት ክወና በደቡብ ጎንደር ዞን፤ በሚል ርዕስ ለፎክሎር ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ በለማ ንጋቱ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል

የፈታኝ ቦርድ አባላት

አማካሪ ........................................ ፊርማ ........................................

ፈታኝ........................................ ፊርማ ........................................

ፈታኝ........................................ ፊርማ........................................

ABABA ... LIBRARY

## *አጠቃሎ (Abstract)*

*የዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያት የደቡብ ጎንደር ዞን የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ማሕበረሰብ፣ የለቅሶ ሥርዓቶች ሳይጠኑ በተለያዩ ምክንያቶች ለለውጥ እየተጋለጡ መሆናቸው ሲሆን፣ ዋና ዓላማውም ተጠኚው ማሕበረሰብ ሞት ሲከሰት በጋራ የሚያከውናቸውን የለቅሶ ሥርዓቶች ክወና መተንተን ነው። ይህንንም ለማሳካት መረጃዎች ደቡብ ጎንደር ዞን ውስጥ ከሚገኙት ከደብረታቦር ዙሪያ፣ ከፋርጣ፣ ከላይ ጋይንት፣ ከስማዳ እና ከፎገራ ወረዳዎች ተሰብስበዋል። መረጃዎቹ በኢትኖግራፊያዊ የጥናት ዘዴ ከተጠኚዎቹ ጋር አብሮ በመኖር ሞት ሲከሰት የሚያከናውኗቸው ሥርዓቶችና የለቅሶ ቃል-ግጥሞች በምልከታ፣ በቃለመጠይቅ፣ በቡድን ውይይትና በሰነድ ምርመራ ተሰብስበዋል። ቪዲዮና ፎቶ ካሜራዎች፣ መቅረጸ ድምጽና የጽሑፍ ማስታወሻ መረጃዎቹን ለመሰብሰብ አገልግሎት ላይ ውለዋል። በእነዚህ ወረዳዎች የሚኖሩ ለባሕሉ የተሻለ እውቀት ያላቸው 42 መረጃ አቀባዮች በታላሚ ናሙናና በሙያ ጓድ ጥቆማ (snowball sampling) ተመርጠዋል። መረጃዎቹ ከተሰበሰቡ በኋላ ወደጽሑፍ ተቀይረው በየዘውጋቸው ተመድበዋል። ከጥናቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ከተመረጡ በኋላ ሥርዓቶቹ፣ የቀብር፣ የሀዘን እና የመታሰቢያ በሚሉት ተመድበው፤ ሞት በሥጋ ዝምድና ላይ የሚያስከትለው ውጤት፣ የእናትና አባት ሞት በልጆቻቸው፣ የልጆች ሞት በእናት አባቶቻቸው፣ የእህትና ወንድም ሞት በእህቶቻቸውና በወንድሞቻቸው፣ የሽማግሌዎችና የጀግኖች ሞት በሚኖሩበት ማሕበረሰብ በሚሉት ተደራጅተው፣ በመሰረተ ባሕል (infracultural model) የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ተተንተነዋል። የትንተናውን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ መረጃዎቹን በተለያዩ ዘዴዎች ከመሰብሰብ በተጨማሪ፣ ወደመስክ በመመለስ የጥናቱን ረቂቅ ለተመረጡ መረጃ አቀባዮች በማንበብ፣ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ የማድረግና የማስተካከል ሥራ ተሰርቷል። በውጤቱ መሰረትም፣ የለቅሶ ሥርዓቱ ከእስራኤላውያን የለቅሶ ሥርዓት ጋር የሚመሳሰልባቸው በርካታ ነገሮች መኖራቸውን ለመረዳት ተችሏል። ኢትዮጵያ የብሉይን ሥርዓት ቀደም ብላ መቀበሏና እስራኤላውያን በተለያዩ ምክንያቶች ወደኢትዮጵያ ገብተው ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ መኖራቸው ተጠኚው ማሕበረሰብ ባህላቸውን ለመውረሱ ምክንያቶች ሁነው ተገኝተዋል። በሌሎች አጥኚዎች ሙሾ፣ ፉከራና ቀረርቶ ተደርገው ከሚገለጹት የለቅሶ ቃል-ግጥሞች በተጨማሪ፣ የወየታ ቃል-ግጥም ዘውግ ተገኝቷል። በሙሾ ክወና ሴቶች ከጣሊያን ወረራ በኋላ በፎካሪዎች ተገፍተው መውጣታቸውንና በአሁኑ ሰዓት በከዋኝነትም ሆነ በታዳሚነት የማይሳተፉ መሆናቸውም ታውቋል። በለቅሦ ሥርዓቱ ከሚታዩት ለውጦች፣ ከ1960ዎቹ ጀምሮ በላይ ጋይንትና በፎገራ ወረዳዎች የቀጠሮ ለቅሶ በየሳምንቱ ቅዳሜ በገበያ ዳር እየተከናወነ እንደሚገኝና ለዚህም የኑሮ ውድነት በመንስኤነት እንደሚጠቀስ ለመረዳት ተችሏል። በአለባበስ በኩል ማቅና ድሪቶ ለብሶ ከማዘን፣ አዳዲስ ልብስ እየለበሱ ወደመውጣት፣ በለቅሶ ቃል-ግጥሞች ፉከራ በማሕበረሰቡ ጀግና የሚያስብል ስራ ላከናወኑ ከመከወን ለማንኛውም ተራ ሰው ወደመከወን መሸጋገራቸው ከሚታዩት ጉልህ ለውጦች ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሱ ሆነው ተገኝተዋል። ከመረጃዎቹ ፍከራ፣ ውሃ ለክርስቲያኖች የዳግም ልደት፣ ሰሌን፤ የድል አድራጊነት፣ የመግነዝ ጨርቅ፤ ከመከራ የመገላገልና የነጻ መውጣት፣ የመገነዣ ክር፤ የስልጣንና አገልግሎት እንዲሁም መብራት፤ ከጨለማ ወደብርሃን ዓለም የመሸጋገርና የዳግም ልደት ትዕምርታዊ ፍች ያላቸው ሁነው ተገኝተዋል። የለቅሶ ሥርዓቶቹና ቃል-ግጥሞቹ ክወና የማህበረሰቡን አንድነት የማጠናከር፣ ሀዘኑን ይፋ በማውጣት የማቅለል እና ታሪኩን የማስተላለፍ ሚና የሚጫወቱ ሆነው ተገኝተዋል። በጥናቱ ውጤት መሰረት መወሰድ የሚገባቸው መፍትሄዎችም ተጠቁመዋል።*

# Performance of Funeral Ceremonies in South Gondar Zone

## Ph.D Thesis

## Submitted Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Doctor of Philosophy in Folklore

**By: Lemma Nigatu**

**Supervisor: Dr. Fekade Azeze (Ph.D)**

## Summary of the study

From birth to death, human beings pass through a number of stages which are achieved by age and social status. Birth, circumcision, coming to age and achieving adulthood, graduation, weedding, and death are some from the life of humanbeings.

Death, which is the focus of this study, is the last rites of passage that is surrounded and accompanied by many belief-based ceremonies (Abbink 2002, 67). The motivations to study this rites of passage were emanated from internal and external causes. As a member of the studied community, I was highly impressed by the performance of oral poetries especially *musho*. Inaddition, the negligence of funeral rites in the academic area and the growing motivation of banning the performance of the ceremonies aware me that the continuity of the funeral rites are endangered. Because of these factors, I decided to study the subject matter.

In order to fill the gap in the area, investigations of related works were made in IES, Kennedy and post graduate libraries of Addis Ababa University. Though evidences have shown that the tradition of funeral oral poetry has a long history in Ethiopia (Hiruy 1910, 18 and Mahtema

Silassie 1942, 590), it is impossible to find out a well organized research paper in the topic from the above mentioned libraries. Of course, there are some theses which were done for the fulfillment of first and second degrees and some articles which were written on different ethnic funeral ceremonies. But most of these researchers did not go beyond recording the ceremonies for preservation and simple description. Moreover, these works did not describe the performances, the manner of mourning, the functions of memorial ceremonies and symbolic interpretations. This study attempets to fill this gap and contributes to the exsisting literature on funeral rites. These were the gaps the study at hand sought to fill. Performance theory and infra-cultural model were employed for data interpretation.

As performance is one of the most basic ways to study human interaction, to describe and interpret the funeral rites of the studied community, I proposed performance theory for it considers event, participants (performer and audience), setting, context, channel and meaning. According to Bauman (1984) during performance people communicate within specific situations and settings, and these communications are "performed" for certain reasons and in certain ways that have meaning to the members of folk groups and communities. To describe and interpret the community's communication, the approach is found to suit the purpose.

I used infra-cultural model for data analysis because it is an appropriate model for folklore data analysis. Alembi (2000, 22) used the term infra-culture to mean interpretation of words and actions within specific cultural contexts. This means that the messages of words and actions can only be located within the perception of the study community. In addition to this, Alembi (2000) mentions the following key features of conceptual-analytical frameworks.

a) The need for insider analysis and interpretation of works of art and a given reality of community.
b) Interpretation of oral texts within their cultural context: there is recognition in ethnopoetics that oral texts are deeply rooted in the culture and tradition of the performer.

c) Examining narrative patterns beyond mere concern with stylistic features and other formal elements of the surface structure to using these features to elucidate the theme of study.

d) Deep involvement in dialogue and interaction to understand the structural and underlying issues surrounding a phenomenon and a community.

e) Significance of the performed and given meaning. The assigning of meaning to oral texts is defined by the culture and traditions of the performer and audience.

f) Co-operative entry into the performance arena by the performer, audience and folklorist for the focused way of speaking to become a focused way of meaning (pp 23-24.

The major objective of this study is to analyze the performance of funeral rites of the people in South Gondar. The specific objectives of this study are to:

1. Interpret symbols of the funeral ceremonies.
2. Investigate and interpret the bereavement custom of the society.
3. Elaborate the memorial custom and to give symbolic interpretation.
4. Investigate the effect of death on deceased's closest relatives and his/her social members.

The results of this study have numerous benefits for different bodies. First, it disseminates the culture, philosophy and outlook of the studied society for others. It also documents the customs and funeral oral poetries of South Gondar which may help the next generation to know how their ancestors accustomed to perform ceremonies and how they express their sorrow, grief, worldview, etc. through funeral oral poetries. In addition, the study serves as a model to conduct similar studies on different nations and nationalities.

Folklorists, Anthropologists, Sociologists, Psychologists and other related fields researchers do not only benefit from the result of the study, but they are also benefited from the data. The data might be a good source for those who want to study the gradual change of the custom and funeral oral poetry in the future.

In the study, four main issues are covered. The first is the description of the performance of funeral ceremonies and interpretation of its symbolic elements. The second is the analysis of the manner of bereavement and its symbolic interpretation. The third involves the analysis and interpretation of the after death ceremonies (remembrance). The last is the analysis of effects of death both on family, relatives and the community.

These main issues were treated in eight chapters. Chapter I describe the study area and the people, and introduce the study. Chapter II discusses the review of related literature. Chapter III deals with the research methodology. Chapter IV describes and analyzes the performance of funeral rites and oral poetries: composition, classification and performance. Chapter V presents mortuary custom. Chapter VI discusses the funerary commemoration rite. While Chapter VII deals with the effects of death on the family and social relations, the last Chapter presents the conclusion about the studied community burial rites and customs.

Although various African societies are rich in funeral oral poetries, evidences confirmed that they have received very limited analysis all over the continent (Finnegan, 1970) and (Alembi, 2002). The same is true in Ethiopia. In South Gondar where this research was conducted, practicing different death related customs and performing funeral oral poetries are common. But as mentioned earlier, these customs and funeral poetries have not been given attention in the area of academic research.

Besides, in view of avoiding harmful traditional practices, the performance of funeral dirges is being prohibited in some parts of West Gojjam (which is the neighboring Zone of South Gondar) (Migbaru 2009). According to Moges (2002), in Lay Armachiho wereda politics and religion have put their negative influence on funeral ceremonies and oral funeral dirges. Getu (1974) also mentioned that in Gondar, performances relate to funeral ceremonies are diminishing from time to time and the natural performance of funeral ceremony is highly influenced because of the introduction of video recording. Berehanu (2002) also mentioned that the intervention of Ethiopian Orthodox Church, (the church and priests condemned funeral dirges as a non-Christian act and a sinful deed), has certainly contributed to endanger the *muŠho* from its previous poetic status. On top of these, as Wilce (2009, ix) mentioned "... many ... descriptions imply that local lament traditions are dead or dying."

On the one hand, banning these hardly known ceremonies and funeral oral poetries, on the other, the alarming spread of acculturation through different technological materials and the impact of politics and religion became constraint on the continuity of these orally transmitted wisdoms across generation. Thus, in addition to the researcher's interest to understand the meaning of the death related rituals, these external factors made the study unquestionably important.

I have used convenience sampling to choose the study area. I have selected some informants on the actual performance in addition to using purposive and snowball sampling techniques. I attended 16 funeral ceremonies and I interviewed 42 key informants.

To collect data, I have used Participant observation, Interviews, focus group discussion and documents analysis.

The performance perspective that forms the theoretical bases of the study requires engaging the research with the community to see their day -to -day interaction in their natural environment. According to Bryman ( 2001, X) the ethnographer involves ... in people's daily lives for an extended period of time watching what happens, listening to what is said, asking questions-in fact, collecting whatever data are available to throw light on the issues that are the focus of the research.

The researche stayed in the field for three months and eleven days and recorded what they performed and said in the natural context acting as the local people in the performance.

The researcher used interview because it is the ethnographer's most important data gathering technique. He employed unstructured and semi-structured interviews. The interviews were carried out on forty-two selected key informants. Attention was given to the composition of the interviewees. So the group was made up of people of different education, age, sex and skill of performance. Unfortunately, because of tradition females were found reluctant to take part in the interview except one. The researcher collected information from respondents in discussion about the subject matter during the above-mentioned periods of time. He also supported the interview with notes.

The study has also employed focus group discussion. The researcher conducted two focus group discussions with a member of seven and six in each. This provided a forum for in-depth discussions of issues which were raised in the interviews as well as in giving clarifications the range of perceptions and opinions found in the community.

Some documents and recorded materials both audiovisual and audio were consulted. These documents were collected from individuals who made them for personal use at their parents' funeral ceremonies.

By combining all these methods, valuable information were collected from actual performances, knowledgeable informants and resourceful persons. After assembling, the data were transcribed all as they were performed and said. Critical reading and grouping of them according to the major themes of the study were made and irrelevant data were excluded.

The analysis was made based on the meanings given by the studied community. Related information from Bible and other religious books were used to clarify and/or to support the data. The researcher also used some other research findings to show the resemblances and differences of the studied culture to other cultures and to give scientific explanations. After description of an event, material or oral poem, symbolic interpretations were given.

The collected data were grouped into four major categories. The first category incorporates data from death to burial. The second includes mourning custom. The third is about after burial memorial ceremonies. The fourth includes the effect of death on deceased's close relatives and the community around him. All are analyzed according to their order.

Ceremonies before burial were analyzed and grouped into sacred and secular categories. The religious ceremony starts immediately after the soul of the individual person has departed. If the deceased is an elder, the father of the soul (*yenefs abat*) or any priest prays *tseat nefs* from *metsehaf ginzet*. An elder member of a family or relative closes his eyes and mouth and cleans his nostrils and lips. Then, the thumbs are joined and tied together with white string. In the same way, big toes are tied together and the body rests straight. Washing of the body and shrouding is followed according to the status of the deceased. If the deceased is a monk or nun the hands are

made to lie crossed with the palms resting on the chest. If the deceased is a priest the arms are pulled to the shoulder crossed signifying that he passed his life serving God. The arms of deacons are the same to the priest but not crossed. The arms of monks and nuns pulled to the face and the toys closed the ears and the rest of the fingers put on the eyes to signify that they were ignorant for this world. The arms of the lay person stretched towards his genital and the fingers cover it to mean that I am loyal to the Ten Commandments.

Regarding to the authorization, if the deceased is a priest, a deacon, a lay person, a monk or a nun, only a priest or a man of the same status can wash and shroud the body. Women do not participate in these activities because of religion and cultural reasons.

A shroud is a piece of new cloth made of cotton. No cloth that has been washed or worn used for shrouding. In shrouding, the deceased is tied down seven times with a white string each of which is arranged to look like a cross starting on the forehead, at the neck, at the breast, at the hips, at the knees, at the ankles and ending at the middle of the feet. Having completed the shrouding the corpse is laid on a bed and covered with *Shema* or *gimja.*

The clergy stand around the coffin and chant one of the seven rituals in the house according to the age and social status of the deceased. Then, the corpse is carried by four men the two at the feet lead the way and the two at the head follow. During the procession, the corpse is expected to lie down five times for short chants but because of time constraints, it is not practiced nowadays except exceptional cases. The last chant is performed at the backyard of the church. Finally, the corpse is made to bow down by tilting the head tree times to the church by the northern gate if the deceased is male, by the southern if a female. Then, it is taken to the cemetery for burial. The corpse lowered into the grave after the priest blessed it and put on its back keeping his head to east and feet to west direction. After some priests say the last prayers (dust returns to dust), the grave digger and the nearby men closed the grave immediately.

The religious ceremony is practiced when there is a corpse. For after burial (*yeketero lekso*) and (*yemerdo lekso*) funeral ceremonies, in house and on procession prayers are not practiced by priests. If the deceased has a good social status, priests may chant and dance glorifying his works. If the deceased is a layman there might not be a religious ceremony at all.

In secular ceremonies, when someone dies, the normal life is disturbed. So that everybody around starts wailing and weeping in an organized manner. Yelling, weeping, face scratching, hair pulling and throwing one's body on the ground are common features of early death announcement. The wailing depends according to the age and social status of the deceased. If somebody has died in accident or die at young age the wailing became hysterical. However, it will be weeping for small children and natural death of old people.

After some time the elders announce everybody to stop crying and get ready to engage in some activities. Most people especially women are assigned to prepare food. Some especially young men are assigned to break the news. The announcement of death in the studied society varied in rural areas and in towns. In rural areas, whenever someone dies, the immediate families break the news to neighbors by wailing and crying. Sympathizers also would come to join them in the wailing. In rural areas, the elders assign a couple of boys into many directions to convey the death news to the far lived relatives. The bad news bearers (*tina tery*) mount the highest place early in the morning and yells out somebody's name loudly. If he answers they tell him who has died, when and where he is buried and order he to communicate the news to reach the people concerned. The receiver passes the news in the same way until it reaches to the last concerned people. In towns, there are some professional news bearers who are paid.

Meanwhile, the gathered relatives, neighbors and others, start the crying in an organized way. Experienced mourners lament *woyota* in a very special way with a heartrending voice. The gathered people weep and morn according to the relationship of the deceased. Around 2:30 am the trip to the funeral starts. In the procession, the clergy lead followed by the men who carried the corpse. Next, the family (close relatives of the deceased) relatives and neighbors follow respectively. In earlier times, when there was a short chant (*yeguzo fetehat*) elegy (*musho*) was performed in addition to *wyota* when the deceased is above 18. Nowadays, the corpse has taken to the public cemetery (*margeja*) directly from his house. The performances of *woyota* continue until the corpse is taken to the church for burial. If the deceased is honored in his social status and deeds, war songs (*qerarto*) and war recital (*fukkara*) are performed. In earlier times, to perform these oral poetries; the deceased must be a soldier, a warrior, a hard worker, a hunter or a good governor regardless of its sex. Nowadays they are performed for common persons too.

ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176

In war songs and recital, praising the personality, bravery, courage, determination, etc., of the deceased is common carrying shields; spears and guns as if performers are in real battlefield. In the studied community, females do not take part both in war songs and *musho* performance, but in woyota. In *musho* performance, three to seven men make a vertical line closing each other's shoulder. The same numbers of men in the same position make a line against them. The audience accompanies surrounding them. When a performing group sings and moves to the center in a rhythmic melody, the opposite group moves in the same fashion towards the center by saying the stanza. They sing together at the center for some time and start to move to backside. At this time, they exchange their role (the performer become accompanier and vice versa). After they performed one round they change their direction and perform in the same manner until the corpse is taken to the church for burial.

After the burial the mourners sits waiting in the *margeja* to say farewell to those who do not accompany them to the deceased's house. Each person comes to the eldest mourner says: "May God gives you strength", by touching the mourner's knee with the right hand. The elder answers: "May the strength be given to him" if the cause of the death is natural but, if the cause of death is unnatural (mostly accident), he answers: "May God keeps you from such kind of disaster." When all those who wish to leave make their farewell, the mourners move to the deceased's house and eat food.

The sacred and secular ceremonies are practiced for baptized members of the community. When newborn babies die before the first 10 days (before spray of holy water by the local priest) and before forty and eighty days for male and female (unbaptized) babies respectively they are not buried in the church yard assuming that they are not Christians. Babies below 10 days buried around the home and others outside the yard of the church. Such children are not given burial ceremonies, but hurriedly buried without much mourning. To those who committed suicide elaborate rituals are not carried out during burial.

In the funeral ceremony of close relativers, mourners especially women are plucking their hair, scratching their face, and slapping their chest while they hear the bad news. Besides, women of the descent group, especially the deceased's mother, sisters, wife and daughters wear trousers,

shirts and coats of the deceased over their shoulders. Put the dress front side back at their back, when the deceased is a woman.

After burial the deceased's close relatives and friends start practicing the mourning custom. Changing the way of dressing and abstain from comfort are the manifestations of mourning in addition to injuring the body. After returning from the burial, women from very close relatives of the deceased shave their heads. Men do not shave their mustache at least up to the $40^{th}$ or the $80^{th}$ day for male and female respectively. Women wear their dress upside down, and tie one end of their *netela* around their waists and bring the other end over their shoulders from the back at least up to the $40^{th}$ or $80^{th}$ days of commemoration depending on the sex of the deceased. Men wear *bernos* and put over their head black cape. Sometimes, both sexes tie rope on their west and wear torn out clothes and unprocessed skin under their west to show their heartbreak sorrow about the lose. Women also remove their ornaments and replace their black string with white around their necks.

Even some do not wash their body and cloth. Buttering their hair or using other ointment is also prohibited for a certain period. The very sad mourners sleep stretching a sack on the floor. They also stop from listening to music and participating in any pleasurable recreations. According to the explanation of informants, some of the mourning customs are done by the will of individuals and some are by community pressure. For example if a woman who has lost her husband does not scratch her face, the community criticizes her as if she did not feel about the death of her husband. The same is true for mothers and sisters.

The remembrance ceremony starts at the third day and ends on the $49^{th}$ year of burial. The community strongly believed that remembrance ceremonies have mutual benefits to the dead and the living. The dead can be supported by the prayers of the living and the dead can improve the efficacy of the prayers of the living. The belief of these powers helps the living and the dead, and it maintains the relationship between them and it strengthens the continuity of the tradition.

Like the mourning custom, there is also a social pressure to prepare one's remembrance ceremony. According to the explanation of informants, failing to celebrate the $40^{th}$ and $80^{th}$ day memorial ceremonies results social discrimination on the families or relatives of the deceased

individual. No one celebrates one's remembrance unless he/she celebrates his/her parents' commemoration (*tezkar*).

In funeral oral poetries, the effect of death on family and other social member of the deceased were examined. Even though parents' death has physical, social and psychological effects on children, losing a mother is a very disastrous phenomenon. Parents are also affected when their children die because they are not losing only their supporters at old age but also they lose their hopes of continuity in the line of the family. The effects of death in a community who loses elders and heroic persons are also discussed. When elders die, the community loses its mediators', sources of wisdom and teachers of experience. In the death of a hero, the community also loses its communal property and social dignity.

In general, the studied community perceives death as everlasting separation of body from life and this world. In religion, death is seen from three dimensions. The first type of death is the separation of soul from body. This would be a common experience to all human beings. The second type of death is to ignore the attractiveness of this world (sin) and live according to the words of God. These people said to be dead although their soul and body are not separated. The third and much feared death is the separation of soul from God on the Day of Judgment (exile to eternal damnation in Hill). Thus, the prime motive of every community member is to gain eternal blessing in Heaven. The longing of life after death, then, has a specifically significance role to shape earthly behavior and to give meaning for life.

In short, from the analysis of the study the following major findings are obtained.

1. There are many similarities between the studied community and Jewish funeral ceremonies.

2. A new genre of funeral oral poetry which is called *woyeta* is identified.

3. A radical change has been shown in *musho and* war song performances. Before the middle of 1930s, *musho* performer was women. Since then, women do not involve in musho performance. Likewise, before the beginning of Derg regime war songs and recitals were performed for those who were honored by the community for their bravery.

Nowadays, they are performed for any layperson regardless of his/her social status and deeds.

4. In addition to the change of funeral oral poetries, a significance change has been observed in the scene of after burial (*yeketero lekso*) funeral ceremonies. Since the middle of 1960s in *Lay gayint* and *Fogera* the above-mentioned funeral ceremonies have been taken place on every Saturday at market places due to economic reasons.

5. Performing funeral ceremonies has multi-functions. Of these, the disposal of the dead body; the safe transmission of the soul to an afterlife; strengthening of social ties in the community; and enabling of bereaved people and communities to adjust to their new roles in society are some. Even though the ceremonies have such positive functions, injuring of bodies, wasting time, investing a lot of money for *kitir lekso* festivity are its negative impacts. So, rather than banning the ceremony in general, it is advisable to differentiate harmful and useful practices in reliable studies.

6. There is a dialogue on the importance and negative side effects of studying one's own culture. From my field experience, I found studying one's own culture has many benefits. Therefore, I suggest that researchers need to give priority to study their own culture.

# ምሥጋና

በመጀመሪያ አስጀምሮ ላስፈጸመኝ አምላክ ክብር ምስጋና ይግባው። በመቀጠል በርዕስ ጉዳዩ ዙሪያ ያለኝን ሀሳብ ሳማክራቸው እንድገፋበት ከማበረታታት ጀምሮ በተገናኘን ቁጥር ሥራቸውን አቋርጠው ላጋጠሙኝ ችግሮች መፍትሄዎችን በመጠቆም፣ ለጥያቄዎቼ መልስ በመስጠትና ሥራው የተሻለ መልክ እንዲይዝ መንገዶችን በማመልከት፣ በማበረታታትና እዚህ ደረጃ እንዲደርስ ሳይታክቱ ለተጉት አማካሪዬ ለዶ.ር ፈቃደ አዘዘ ከልብ የመነጨ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ፤ ያለባቸውን የሥራ ጫና ብቻ ሳይሆን ሕመማቸውን ጭምር ተቋቁመው ረቂቅ ጽሑፉን በወቅቱ አርመውና አስተካክለው ለመመለስ ያሳዩት ብርታት እጅግ ያስመሰግናቸዋልና እግዚአብሔር እድሜና ጤና ይስጥልኝ እላለሁ።

ሙያቸውም ባይሆን የሚጠናው ባሕል አካል በመሆናቸውና ከምርምር ልምዳቸው ባካበቱት እውቀት ጥናቱን ከትልመጥናቱ ጀምሮ እስከመጨረሻው በየጊዜው በማንበብ የጻፍኩትን በማረም፣ ያልጻፍኩትን እንዲካተት እና አላግባብ የጨመርኩትን እንዲቀነስ በመጠቆም አስተማሪዬ ዶ.ር ማረው ዓለሙ ላደረጉልኝ እገዛ ምሥጋና ሲያንሳቸው ነው። ያለመሰልቼት ሥራዎቼን ደጋግመው በማንበብና ሊታመን በማይችል ጊዜ ውስጥ አርመው በመመለስ ከፍተኛ እገዛ አድርገውልኛልና እግዚአብሔር ይስጥልኝ ከማለት በቀር የምለው የለኝም።

ለዚህ ጥናት ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን መስዋዕት አድርገው የየበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያደረጉትን ሁሉ መዘርዘር ባለመቻሌ በጥቅል ልባዊ ምስጋናየን ሳቀርብላቸው በታላቅ አክብሮት ነው። በተለይ ግን፣ ቀኝ ጌታ ዜናዊ ሥቡህ፣ መሪጌታ ክፍለማርያም አለነ፣ አቶ ትዕዛዙ አያሌው፣ አቶ ደሳለኝ ታየ፣ አቶ ሞላ አየሁ፣ አቶ ታከለ ንጋቱ፣ አባ ዳምጤ ፈረደ፣ አቶ ዋለ ጎበና፣ አቶ ጸጋየ ጀንበሬ፣ አቶ ደጀን አመኑ እና አቶ ብርሃን አበበ መረጃ ከማቀበል ባለፈ ለጥናቱ መሳካት ላሳዩት የባለቤትነት ስሜትና ወንድማዊ እገዛ ምስጋናዬ ወሰን የለውም። አቶ ማንደፍሮ ፈንታ ጽሑፉን በማንበብ ለሰጡኝ ገንቢ አስተያየትና የፊደል ግድፈቶችን በማረም ላደረጉልኝ እገዛ እጅግ አመሰግናለሁ።

ጅማ ዩኒቨርሲቲ ላፕቶፕ ከመስጠት ሙሉ ደመወዝ እየከፈለ በማስተማር፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የምርምሩን ወጪ በከፊል በማገዝ፣ ትምህርት ሚኒስቴር የቤት ኪራይ፣

የመጓጓዣና የጽሕፈት መሳሪያ ወጪዎችን በመሸፈን እዚህ እንድደርስ የየበኩላቸውን ተቋማዊ እገዛ አድርገውልኛልና ሁሉንም በአክብሮት አመሰግናለሁ።

እህቶቼ ጸዳል ንጋቱና ትዕግስት አለባቸው በሌለ ጎናቸው ላደረጉልኝ የገንዘብና የሞራል ድጋፍ ምስጋናዬ በቃላት አይወሰንም። ባለቤቴ ወ.ሮ ተዋበች አበራ፣ ልጆቼ ሳምራዊት፣ ቤተልሄም፣ መንግሥቱ እና ታምራት ዘወትር ላልተለየኝ ማበረታቻችሁና ለትዕግስታችሁ ክልብ አመሰግናለሁ።

## ማውጫ


*አጠቃሎ (Abstract)* ........ i

Summary of the study ........ ii

ምሥጋና ........ xiv

መግቢያ ........ 1

የደቡብ ጎንደር ዞን መልክአምድራዊ ገጽታና የማሕበረሰቡ ዳራ ........ 1

መልካምድራዊ ገጽታ ........ 1

የዞኑ ማሕበረሰብ ዳራ ........ 5

ምዕራፍ አንድ ........ 7

1.መግቢያ ........ 7

1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ........ 7

1.2. የጥናቱ ታሪካዊ ዳራ ........ 11

1.3. የክወና ትውር (performance theory) ........ 14

1.4. የመሰረተ ባሕል ሞዴል (infracultural model) የመረጃ ትንተናና ፍከራ ዘዴ ........ 16

1.5. የጥናቱ ዓላማዎች ........ 19

1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 19

1.7. የጥናቱ ወሰን ........ 21

1.8. የጥናቱ አደረጃጀት ........ 22

ምዕራፍ ሁለት ........ 23

2. የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ (review of related literatures) ........ 23

2.1. ጽንሰሀሳባዊ መነሻዎች ........ 23

2.1.1. የሥርዓት (Ritual) ምንነት ........ 23

2.1.2. ከሞት ጋር የተያያዙ ጽንሰ ሀሳቦች ........ 25

2.1.3. ከሞት መከሰት ጋር ተያይዘው የሚፈጸሙ ልማዶች ........ 34
2.2 የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት ........ **43**
2.2.1. በአማራ ብሔረሰብ በለቅሶ ሥርዓት ላይ የተካሄዱ የዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ቅኝት ........ 43
2.2.2. ከዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ሌላ በኢትዮጵያ በቀብር ሥርዓት ላይ የተካሄዱ ጥናቶች ቅኝት ........ 48
2.2.3. በአፍሪካ በለቅሶ ቃል-ግጥሞች ላይ የተካሄዱ ጥናቶች ቅኝት ........ 51
ምዕራፍ ሦስት ........ 56
3. የአጠናን ዘዴ (Research Methodology) ........ 56
3.1. የጥናቱ ሞዴል (research Paradigm) ........ **56**
3.2. የጥናቱ ዘዴ (Research method) ........ **57**
3.3. የጥናቱ አካባቢና የመረጃ አቀባዮች አመራረጥ ........ **59**
3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........ **61**
3.4.1. ተሳትፏዊ ምልከታ (participant observation) ........ 62
3.4.2. ቃለ መጠይቅ (interview) ........ 65
3.4.3. ቡድን ተኮር ውይይት (focus group discussion) ........ 68
3.4.4 ሰነድ ምርመራ (document analysis) ........ 69
3.5. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ **71**
3.6. ሥነምግባራዊ ጉዳዮች (Ethical Issues) ........ **73**
3.7. የመረጃ አደረጃጀት ስልትና አተናተን ዘዴዎች ........ **74**
3.7.1. የመረጃ አደረጃጀት ስልት ........ 74
3.7.2. የመረጃ አተናተንና ፍከራ ዘዴ ........ 74
3.8. ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱ መፍትሔዎችና መልካም አጋጣሚዎች ........ **76**
3.8.1 ያጋጠሙ ችግሮች ........ 76
3.8.2 የተወሰዱ መፍትሄዎች ........ 77
3.8.3. መልካም አጋጣሚዎች ........ 79

ምዕራፍ አራት ........................................................................................................ 81

5. የለቅሶ ሥርዓትና ቃል-ግጥሞች ክወና ትንተና ........................................................ 81

4.1. የቀብር ሥርዓት ክወና ትንተና ........................................................................ **82**

4.1.1. እስከቀብር ድረስ የሚፈጸሙ ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች ክወና ........................................ 83

4.1.1.1. በዕለት ለቅሶ እስከቀብር ድረስ የሚከናወኑ ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች ክወና ...................... 83

4.1.1.1.1. ግንዘትና ከፈን .................................................................................. 83

4.1.1.1.2. የፍትሀት ጸሎት ................................................................................ 93

4.1.1.2. በቀጠሮና በመርዶ ለቅሶ የሚከናወኑ ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች ክወና ............................ 105

4.1.2 እስከቀብር ድረስ የሚከናወኑ ዓለማዊ የለቅሶ ሥርዓቶች ክወና ................................. 108

4.1.2.1. በዕለት ለቅሶ እስከቀብር ድረስ የሚከናወኑ ዓለማዊ ሥርዓቶች ክወና .......................... 108

4.1.2.2. በቀጠሮ ለቅሶ የሚከናወኑ ዓለማዊ የለቅሶ ሥርዓቶች ክወና .................................... 121

4.1.2.3. በመርዶ ለቅሶ የሚከናወኑ ዓለማዊ የለቅሶ ሥርዓቶች ክወና .................................... 130

4.2. የተጠኚው ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ድረሳ፣ ምደባና ክወና ............................ **136**

4.2.1. የተጠኚው ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ድረሳ .................................................. 137

4.2.2. የተጠኚው ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች አካባቢያዊ ምደባ .................................... 142

4.2.2.1 ወየታ ........................................................................................... 143

4.2.2.2. ሙሾ ............................................................................................ 144

4.2.2.3. ቀረርቶና ፉከራ ................................................................................ 145

4.2.3. የተጠኚው ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ክወና .................................................. 147

4.2.3.1. የወየታ ክወና .................................................................................. 148

4.2.3.2.የሙሾ ክወና ..................................................................................... 153

4.2.3.3. የፉከራ ክወና .................................................................................. 160

ምዕራፍ አምስት ..................................................................................................... 178

5. የሀዘን አገላለጽ ልማድ ........................................................................................ 178

5.1. በአካል ላይ የሚፈጸሙ የሀዘን መግለጫ ልማዶች ........ 179

5.2. በአለባበስ የሚገለጹ የሀዘን ልማዶች ........ 187

5.3. ሌሎች የሀዘን መግለጫ መንገዶች ........ 193

ምእራፍ ስድስት ........ 196

6. የመታሰቢያ ሥርዓት ........ 196

6.1. የሥንብት ሥርዓት ........ 198

6.2. የእዝን አቀራረብ ሥርዓት ........ 201

6.3. የቀናቀን አከባበር ሥርዓት ........ 203

ምዕራፍ ሰባት ........ 212

7. ሞት በሥጋ ዝምድናና በማህበራዊ ትስስር ላይ የሚያስከትለው ውጤት። ........ 212

7.1. የእናት ሞት በልጆች ላይ ........ 214

7.2. የአባት ሞት በልጆች ላይ ........ 222

7.3. የልጅ ሞት በወላጆች ላይ ........ 227

7.4. የእህት ሞት በወንድምና እህት ላይ ........ 232

7.5. የወንድም ሞት በእህትና ወንድም ላይ ........ 234

7.6. የሽማግሌ ሞት በማሕበረሰቡ ላይ ........ 238

7.7. የጀግና ሞት በማሕበረሰቡ ላይ ........ 241

ምዕራፍ ስምንት ........ 248

8. ማጠቃለያ ........ 248

8.2. ይሁንታ ........ 252

8.3. ትዝብቶች ........ 253

ዋቢዎች ........ 255

የአባሪዎች ማውጫ ........ 270

## የምሥል ማውጫ

ምሥል አንድ፣ ጥናቱ የተካሄደበት ዞን በኢትዮጵያና በአማራ ክልል የሚገኝበትን አካበቢ የሚያሳይ ካርታ....2

ሥዕል ሁለት፣ የካህናትን አገናነዝ የሚያሳይ፤ ሥዕል ሦስት፣ የመነኮሳትን አገናነዝ የሚያሳይ ....88

ሥዕል አራት፣የዲያቆናትን አገናነዝ የሚያሳይ፤ ሥዕል አምስት፣ የሕዝባውያንን አገናነዝ የሚያሳይ....88

ምስል ሰባት፤ በእሙሁይ አጸዱ ስመኝ ለቅሶ የጉዞ ፍትሃት ሲካሄድ (ፎቶ በለማ ንጋቱ).....101

ምስል ስምንት፣ በ29/09/04 ደብራታቦር ዙሪያ ወረዳ በዋለው በአቶ ዋለ ቸኮል የቀጠሮ ለቅሶካህናት ለቅሶውን አስቁመው ሲገስጹና የመሰናበቻ ጸሎት ሲሰጡ (ፎቶ በለማ ንጋቱ)....107

ምሥል ዘጠኝ፣ በ14/09.04 ዓ.ም በዋለው በአቶ ዓለምነው መንግሥቱ ለቅሶ ሀዘንተኞቹ አዲስ ለቅሶ ደራሾችን ሲገናኙ (ፎቶ በለማ ንጋቱ)....112

*ምሥል አስር፣ በ22/02/04 ዓ.ም ደብረታቦር ዙሪያ ወረዳ ሬሳ ከቤት ሲወጣ በር ላይ የተሰበረ ሸክላ (ፎቶ በለማ ንጋቱ)*....114

ምስል አስራ አንድ፣በ8/09/04 ዓ.ም በዋለው በእሙሁይ አዛለች ለቅሶ ሀዘንተኞቹ ወደወየ ባዩ ዙረው ድምጻቸውን አጥፍተው እያሶመሶሙ ሲያለቅሱ (ፎቶ በለማ ንጋቱ)....118

ምስል አስራ ሁለት፣ በ8/10/04 ዓ.ም ከዋለው ከወ.ሮ ጸሐይ እንግዳየሁ ለቅሶ ከፊት ለፊት የሙሾ ከጀርባ የወየታ ቃል ግጥሞች ጎን ለጎን ሲከወኑ (ፎቶ በለማ ንጋቱ)....119

ምሥል አስራ ሶስት፣ በ25/09/04 ዓ.ም ፎገራ ወረዳ የገበያ ዳር የቀጠሮ ለቅሶን የሚያሳዩ ፎቶዎች (ፎቶ በለማ ንጋቱ)....123

ምስል አስራ አምስት፣ ስማዳ ወረዳ በቀጠሮ ለቅሶ ሚቾቹን በማስመሰል ተሰርተው የቀረቡ ማስለቀሻ ምስሎች (ፎቶ ከስማዳ ባህልና ቱሪዝምና ከላይ ጋይንት የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤቶች የተገኘ)....127

ምሥል አስራ ስድስት፣ በ14/09/04 በዋለው በአቶ አለምነው መንግሥቱ ለቅሶ የወየታ ክወና (ፎቶ በለማ ንጋቱ)....150

ምሥል አስራ ሰባት፣ በ27/09/04 ዓ.ም በዋለው በእሙሃይ አጸዴ ለቅሶ የሙሾ ክወና አውራጁ ቡድን ከተቀባዩ ቡድን ጋር አማካይ ቦታ ላይ ፊት ለፊት ተገናኝቶ የሙሾውን አዝማች በጋራ ሲያወርዱ (ፎቶ በለማ ንጋቱ) ........................................................................................157

ምሥል አስራ ስምንት፣ በ27/09/04 ዓ.ም በዋለው በእሙሃይ አጸዴ ስመኝ ለቅሶ በሙሾ ክወና ከዋኙ ቡድን በስተግራ ወደ ተቀባዩ ቡድን እያረገደ ሲሄድ (ፎቶ በለማ ንጋቱ) ..................158

ምሥል አስራ ዘጠኝ፣በ9/10/04 ዓ.ም ከዋለው ከ፺ አለቃ ጌቴ የቀጠሮ ለቅሶ ከቀረቡት የፉከራ ክወናዎች ከዋኙ የሚገኝበት ቡድን አሰላለፍ (ፎቶ በለማ ንጋቱ).......................................163

ምሥል ሀያ፣ በ8/10./04 ዓ.ም በዋለው በወ.ሮ ጸሀይ እንግዳየሁ ለቅሶ ቀሚስ ለብሰው የዋሉ ፈረሶች (ፎቶ በለማ ንጋቱ) ......................................................................................166

ምሥል ሃያ አንድ፣ የቅርብ ሀዘንተኞች አለባበስ ምልከታ በተካሄደባቸው ሁለት የለቅሶ ሥርዓቶች (ፎቶ በለማ ንጋቱ)........................................................................................190

ምሥል ሀያ ሁለት፣ የሟች የቅርብ ቤተሰብና ጓደኛ የሆኑ ሴቶች ሀዘናቸውን የሚገልጹባቸው አለባበሶች (ፎቶ በለማ ንጋቱ)......................................................................................191

ምሥል ሀያ ሶስት፣ በ9/05/06 ዓ.ም አቶ ግዛቸው ደምሴ የሟች አባታቸውንና በቀኝ በኩል የሚገኙ እናታቸውን ተዝካር ባወጡበት ዳስ ቃለ መጠይቅ ሲደረገላቸው (ፎቶ በብርሃን አበበ) ...............................................................................................................................209

# መግቢያ

## የደቡብ ጎንደር ዞን መልክአምድራዊ ገጽታና የማሕበረሰቡ ዳራ

በኢትዮጵያ ከሚኖሩት በርካታ ብሔረ ብሔረሰቦች አንዱ የአማራ ብሔረሰብ ነው፡፡ የአማራ ብሔረሰብ በሀገሪቱ ከሚገኙ ሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ተቀላቅሎ ቢኖርም በአብዛኛው ሰፍሮ የሚገኘው ግን በአማራ ክልል ነው፡፡ በዚህ ክፍል በክልሉ ውስጥ ከሚገኙት አስር ዞኖች መካከል አንዱ ስለሆነውና ጥናቱ ስለተካሄደበት ስደቡብ ጎንደር ዞን መልካምድራዊና ማሕበራዊ ዳራ ማስተዋወቂያ ተሰጥቷል፡፡ ማስተዋወቂያውን መስጠት ያስፈለገው፣ በተለይ በለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ፣ ከመልካምድሩም ሆነ በአካባቢው ከተከናወኑት ጉልህ ታሪካዊ ድርጊቶችና ከማሕበረሰቡ የርስበርስ ትስስር ጋር ግንኙነቶች ያላቸው ጉዳዮች ስለሚነሱ፣ ለአንባቢ አስቀድሞ ፍንጭ መስጠት ተገቢ በመሆኑ ነው፡፡

### መልካምድራዊ ገጽታ

የደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር፣ በምስራቅ፣ ከሰሜን ወሎ፤ በደቡብ ምዕራብ፣ ከምዕራብ ጎጃምና ከባሕር ዳር፤ በምዕራብ፣ ከጣና ሀይቅ፤ በሰሜን፣ ከሰሜን ጎንደር፤ በሰሜን ምዕራብ፣ ከዋግ ህምራ፤ በደቡብ፣ ከምስራቅ ጎጃምና በደቡብ ምዕራብ፣ ከደቡብ ወሎ፤ ዞኖች ጋር ይዋሰናል፡፡ አጠቃላይ የቆዳ ስፋቱም 14,095.19 ስኩየር ኪ..ሜ መሆኑን በዞኑ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ እ.ኢ.አ (2002) የተዘጋጀው ዓመታዊ መጽሔት ይገልጻል፡፡ ደብረ ታቦር ከተማ የዞኑ ዋና ከተማ ሲሆን፣ ከባሕር ዳር 91፣ ከአዲስ አበባ 641 ኪ..ሜ ርቀት እንደሚገኝም ይኸው መረጃ ያስገነዝባል፡፡




*የኢትዮጵያ ካርታ*

*የአማራ ክልል ካርታ* *የደቡብ ጎንደር ዞንካርታ*

ምሥል i. ጥናቱ የተካሄደበት ዞን በኢትዮጵያና በአማራ ክልል የሚገኝበትን አካበቢ የሚያሳይ ካርታ

የዞኑ የመሬት አቀማመጥ፣ በምዕራብ በኩል ከሚገኙት የደራ፣ የፎገራና የሊቦ ከምከም ወረዳዎች የጣናን ሀይቅ የሚያዋስኑት የድንበር አካባቢዎቻቸው ሜዳማዎች ከመሆናቸው በስተቀር ሌላው፣ አምባ፣ ወጣ ገባና ተራራማ የመሬት አቀማመጥ የሚበዛበት አካባቢ ነው፡፡ 4,231 ሜትር ከፍታ ያለው የጉና ተራራ፣ ከከፍተኛ ቦታዎቹ መካከል በቀዳሚነት ይጠቀሳል፡፡ ከዞኑ ገንዘብና ኢኮኖሚ መምሪያ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው፣ ዞኑ አራት ዋና ዋና የአየር ንብረቶች ያሉት ሲሆን፣ እነሱም፡- 10% ቆላ፣ 51% ወይና ደጋ፣ 36% ደጋና 3% ውርጭ ናቸው፡፡ ዞኑ በዘጠኝ የገጠርና በአምስት የከተማ ወረዳ አስተዳደሮች የተዋቀረ መሆኑንም ለመረዳት ተችሏል፡፡

የዞኑ ዋና ከተማ ደብረታ ታቦር ሲሆን፣ ዙሪያውን በወይና ደጋ የአየር ንብረት የተከበበና፣ ከባሕር ጠለል በላይ 2,706 ሜ. ከፍታ በደጋማ የአየር ንብረት ክልል ይገኛል። ይህ ከተማ፣ ከጥንት ጀምሮ ለዞኑ ብቻ ሳይሆን፣ ለኢትዮጵያ በአስተዳደር ማዕከልነት ያገለገለ ታሪካዊ ከተማ መሆኑን፣ የጽሑፍና የአፈ-ታሪክ መረጃዎች ያሳያሉ። ከዞኑ ባሕልና ቱሪዝም ቢሮና የአካባቢውን ታሪክ ከሚያውቁ አዛውንቶች የተገኙት መረጃዎች፣ ከተማው እ.ኢ.አ. በ1327 በአጼ ሰይፈ አርእድ ዘመነ-መንግሥት እንደተቆረቆረ ያሳያሉ። አቶ ግሩም ሀይሉ (አባ.2፣ ቁ.6፣ ክፍ.ሀ፣ አን.1)፣ ከተማው በተጠቀሱት ንጉሥና ዘመን መመስረቱን ሲገልጹ፣ ቀኝ ጌታ መዓዛ ንጋቱ (አባ.2፣ ቁ.5፣ ክፍ.ሀ፣ አን.1) የታሪክ ድርሳናትን አጣቅሰው እ.ኢ.አ. በ1327 እና በ1332 ተቆረቆረ የሚሉ መረጃዎች ቢኖሩም፣ እ.ኢ.አ. በ1336 ከተማውን ቆረቆሩት የሚባሉት አፄ ሰይፈ አርዕድ ከነሰራዊታቸው እየሱስ ተራራ ላይ ሰፍረው እንደነበር የሚያሳይ መረጃ ከብራና መጽሐፍ ማንበባቸውን በመግለጽ፣ ከተማው በተጠቀሰው ጊዜ ክልል ውስጥ እንደተቆረቆረ ያስረዳሉ።

ከተማው ስያሜውን ስላገኘበት ሁኔታ ተቀራራቢነት ያላቸው የአፈ-ታሪክ መረጃዎች ከመኖራቸው ውጭ፣ በትክክል የሚያስረዳ መረጃ እስካሁን አልተገኘም። ቀኝ ጌታ መአዛ ንጋቱ (አባ.2፣ ቁ.5፣ ክፍ.ሀ፣ አን.3)፣ የውጭ ሀገር ሰዎች ጣና ሀይቅ ሆነው ተራራውን በማየት፣ ‹‹የእየሩሳሌምን የታቦር ተራራ ይመስላል›› በማለታቸው ስያሜውን እንዳገኘ፣ አለቃ ታደሰ የሚባሉ ታሪክ አዋቂ ሲናገሩ መስማታቸውን ገልጸው፣ እሳቸው ግን በዘመኑ የነበሩት ሊቃውንት ተሰባስበው የተራራው አቀማመጥ በእየሩሳሌም ከሚገኘው የታቦር ተራራ ጋር ያለውን ተመሳስሎ ወስደው ሳይሰይሙት እንዳልቀሩ እንደሚገምቱ ያስረዳሉ። አቶ ግሩም ሀይሉ (አባ.2፣ ቁ.6፣ ክፍ.ሀ፣ አን.1) ደግሞ፣ አፄ ሳልሳዊ ገብረ መስቀል ቦታው ላይ ሶስት ቀን ካደሩ በኋላ፣ ‹‹ይኸ እየሩሳሌም ካለው የታቦር ተራራ ጋር ይመሳሰላል›› ብለው፣ ደብረ ታቦር የሚለውን ስያሜ ሰጥተውት እንደሄዱ ይገልጻሉ። ሁለቱም አፈ-ታሪክ አዋቂዎች፣ የከተማው ስያሜ በስተደቡብ ከሚገኘው የእየሱስ ተራራ በመገኘቱና፣ የከተማው ስያሜ ከተቆረቆረበት ጊዜ አንስቶ ደብረታቦር በመሆኑ ሲስማሙ፣ ቀደም ሲል ከተማው ጁራ ይባል እንደነበር በአንዳንድ ታሪክ ጸሀፊዎችና በዞኑ ባሕልና ቱሪዝም በቀረበው መረጃ አይስማሙም። ጁራ፣ በአካባቢው የሚገኝ የአንድ ጎጥ መጠሪያ እንጂ፣ የከተማው አለመሆኑንም ያስረዳሉ።

Pankhrust (1977፣235-266)፣ ስለደብረታቦር ከተማ ታሪክ የተለያዩ ምንጮችን አጣቅሰው ባቀረቡት ጥናት፣ ከተማው በራስ ጉግሳ እንደተቆረቆረና በዘመነ መሳፍንት የነእራስ አሊ መቀመጫ በመሆን እንዳገለገለ ይገልጻሉ፡፡ አጼ ቴዎድሮስ ራስ አሊ ሁለተኛን በ1853 አሸንፈው ወደመቅደላ እስከተጓዙበት እስከ1867 ድረስ፣ ዋና ከተማቸው አድርገው እንደተቀመጡበትና፣ ታሪካዊው የሴባስቶፖል መድፍ በዚሁ ከተማ እንደተሰራ ያስረዳሉ፡፡ ከዳግማዊ ቴዎድሮስ በኋላም፣ የአጼ ዮሐንስ አራተኛ ዋና ከተማ በመሆን እንዳገለገለና፣ የጎጃሙ ገዥ ራስ አዳል፣ ‹‹ንጉሥ ተክለ ኃይማኖት›› ተብለው ዘውድ የጫኑትም በዚሁ ከተማ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በአጭሩ ደብረታቦር ከተማ በአስራ ዘጠነኛውና በሃያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ በኢትዮጵያ ከሚገኙ የክፍለ ሀገር ከተሞች አንዱ እንደነበርና በአጼ ቴዎድሮስና በአጼ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት፣ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ በመሆን እንዳገለገለ ይገልጻሉ፡፡

እኒሁ ተመራማሪ አክለው እንደሚገልጹት፣ በደብረታቦር ከተማና በአካባቢው በርካታ ታሪካዊ ጦርነቶች ተካሂደዋል፡፡ ለምሳሌ በ1842 በደጃች ውቤና በራስ አሊ፣ በ1853 በራስ አሊና በአጼ ቴዎድሮስ፣ በአምስቱ ዓመት የወረራ ዘመን (ከሚያዝያ 28/1936 - ሐምሌ 1/1941)፣ በጣሊያን ወታደሮች፣ ባስከተላቸው ባንዳዎች እና በአርበኞች መካከል የተካሄዱትን ከጉልሆቹ ውስጥ ይጠቅሳሉ፡፡ ስለአካባቢው ታሪክ መረጃ ከሰጡት መካከል አቶ ግሩም ሀይሉ (አባ.2፣ ቁ.6፣ ክፍ.ሀ፣ አን.5ና6) እንደሚገልጹትም፣ እ.ኢ.አ. በ1967 በደርግና በግራዝማች አድማሱ በላይ በተመራው የአካባቢው ጀሌ፣ እ.ኢ.አ. ከ1981-82 በደርግ ሠራዊትና በኢህአዴግ ታጋዮች መካከል የተካሄዱት ውጊያዎች በጉልህነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ከተሰበሰቡት መረጃዎች ውስጥ፣ የእነዚህን ጦርነቶች ውሎ፣ የአሸናፊዎቹን ጀግንነት፣ የተሸናፊዎቹን ድክመትና የተከሰተውን ውጤት፣ ወደኋላ ሄደው የሚጠቅሱ የፉከራ ቃል-ግጥሞች ከተለያዩ መረጃ አቀባዮች ተሰብስበዋል፡፡ ከከተማው አመሰራረትና ስያሜ ጋር የተያያዙ አፈ-ታሪኮችም በማሕበረሰቡ ውስጥ እንደሚተረኩ መረጃዎቹ ያሳያሉ፡፡ ይህም ከማህበረሰቡ ባሕልና የሕይወት ፍልስፍና የመነጨ ለመሆኑ፣ ቀጥሎ በቀረበው የማሕበረሰቡ ዳራ ውስጥ ተገልጿል፡፡

የዞኑ ማሕበረሰብ ዳራ

በ2007 በተካሄደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ መሰረት፣ በዞኑ 2,051,738 ሕዝብ ይኖራል፡፡ ከክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢ.ሮ የተገኘው እ.ኢ.አ. የ2004 መረጃ ግን፣ በዞኑ 2,238,737 ሕዝብ እንደሚኖር ይገልጻል፡፡ ከዞኑ ነዋሪዎች የአማራ ብሔረሰብ 99.7% ሲሆን፣ አማርኛ ቋንቋም በ99.7% ነዋሪዎች በአፍ መፍቻነት ይነገራል፡፡ ከአጠቃላይ ሕዝቡ 96.14% የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ሲሆን፣ 3.68% የእስልምና የቀሩት ደግሞ የፕሮቴስታንታና የካቶሊክ እምነት ተከታዮች ናቸው፡፡

የደቡብ ጎንደር ዞን፣ ከላይ መልክአምድራዊ ገጽታው በቀረበበት ክፍል እንደተገለጸው፣ በሰሜን ምዕራብ ከዋግ ሕምራ ዞን ጋር ከመዋሰኑ በስተቀር፣ ሌሎቹ አዋሳኞቹ ተመሳሳይ ማሕበረሰብ የሚኖርባቸው ዞኖች በመሆናቸው፣ የሚገለጸው ባሕል የራሱ የመሆኑን አጋጣሚ ከፍ ያደርገዋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከወረዳ ወረዳ በተለይ በቆላና በደጋ ነዋሪዎች መካከል መጠነኛ የዘየ ልዩነቶች ይስተዋላሉ፡፡ በለቅሶ ሥርዓት መከወኛ ቦታዎችና በቃል-ግጥሞች ክወና በኩልም ተራርቀው በሚገኙ ወረዳዎች መካከል መጠነኛ ልዩነቶች መኖራቸውን ከተካሄዱት ምልከታዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ ግን የአማራ ማሕበረሰብ ማሕበራዊ መዋቅር በተዋረድ የስልጣን ክፍፍል ላይ የተመሰረተ መሆኑን፣ ዋጋው እ.ኤ.አ. (2001፣VI) ይገልጻሉ፡፡ ቤተሰባዊ መዋቅሩም አባዊ ነው፡፡ በመሆኑም በማሕበረሰቡ የዕለት ተለት ማሕበራዊ ግንኙነት በእድሜ የገፉ አዛውንቶች፣ በቤተሰብ ደግሞ፣ አባቶች፣ ተጽዕኖ የመፍጠር አቅም አላቸው፡፡

የከተማው ሕዝብ በመንግሥትና በግል ሥራ የሚተዳደር ሲሆን፣ የገጠሩ በግብርና ሥራ ይተዳደራል፡፡ ገብስ፣ ስንዴ፣ አተር፣ ባቄላ፣ ጤፍ፣ ሽንብራ፣ ድንች፣ በዞኑ በስፋት የሚመረቱ ሲሆን፣ ምስር፣ ግብጦ፣ ተልባ፣ ሩዝ፣ ጓያ፣ አልፎ አልፎ ይመረታሉ፡፡ በወይና ደጋና ቆላማው አካባቢ ለሚኖረው ሕዝብ፣ የጤፍ እንጀራና የገብስ ጠላ ባሕላዊ ምግቡና መጠጡ ሲሆን፣ በደጋ ለሚኖረው ደግሞ፣ መጠጡ ተመሳሳይ ቢሆንም፣ እንጀራው ግን የገብስ ነው፡፡

በአማራ ማሕበረሰብ፣ አንድ ሰው ከእርሱ በፊት የነበሩትን ዝርያዎቹን፣ የራሱንና የመጭውን ትውልድ ዘመን የመኖር ባሕልና የሕይወት ፍልስፍና እንደሚከተል፣ ዋጋው (2001፣53)

ይገልጻሉ። ይህ ሕይወታዊ ፍልስፍናና አተያይ፣ የአሁኖቹ ትውልዶች ከቀዳሚው ትውልድ የተቀበሉትን ባሕልና ታሪክ፣ ለተተኪው ትውልድ በማስተላለፍ የድልድይነት ሚና እንዲኖራቸው እንዳደረገም በተዘዋዋሪ መንገድ ይገልጻሉ። የማሕበረሰቡ አባላት ማሕበራዊ ቦታቸውን የሚመዝኑበትን መንገድም እንደሚከተለው ገልጸውታል።

> በአማራ ብሔር ሰዎች፣ የራሳቸውን ማሕበራዊ ቦታና ክብር የሚገነዘቡት፣ የድርጊታቸውን ተገቢነት የሚመዝኑትና የዛሬ ተግባራቸውንና ውሳኔያቸውን የሚመሰርቱት፣ ወደ ኋላ የአባቶቻቸውና የእናቶቻቸው ‹‹አጥንት እንዳይወቅሳቸው››፣ መንፈስ/አምላክ ወይም ውቃቢ እንዳይረግማቸው፣ ወደፊት ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው እንዳያፍሩባቸውና እንዳይወቅሷቸው በማመዛዘንና በማሰብ ነው።

ከቀዳሚው ትውልድ ተቀብለው ለልጆቻቸው ከሚያስተላልፏቸው ባሕሎች ውስጥ፣ የለቅሶ ሥርዓቶቻቸው ይገኙበታል።

ተጠኚው ማሕበረሰብ ቀደም ካለው ትውልድ ከተቀበላቸውና ዛሬም ተግባራዊ ከሚያደርጋቸው ባሕሎች ውስጥ፣ በደስታ ተካፍሎ መብላትና በችግር (በተለይ በመከራ) ጊዜ መረዳዳት አንዱ እንደሆነ የተሰበሰቡት መረጃዎች ያሳያሉ። ቀኝ ጌታ ዜናዊ ስቡህ (አባ.2፣ ቁ.1፣ ክፍ.1.1.መ፣ አን.1-2) እንደሚገልጹት፣ ለአንድ ሰው ቀረቤታ ካለው ሰው ለቅሶ እንደመቅረት የሚያሳፍር፣ ለባለመከራውም ከዚህ የበለጠ ቂም የሚያስይዝ ነገር የለም። በደስታ ጊዜ አብሮ መብላት፣ በችግር ጊዜ መደጋገፍና በመከራ ጊዜ መረዳዳት፣ ትልቅ ዋጋ የሚሰጣቸው ማሕበራዊ እሴቶች መሆናቸው፣ በተለይ በወየታ ቃል-ግጥሞቹ በተደጋጋሚ ሲገለጹ ተስተውሏል።

# ምዕራፍ አንድ

## 1.መግቢያ

ከልደት እስከሞት ባለው የሕይወት ዘመን፣ የሰው ልጅ በበርካታ በእድሜና በማህበራዊ ደረጃ በሚገኙ ጉልህ እርከኖች ውስጥ ያልፋል፡፡ ልደት፣ ግርዘት፣ ለአቅመ አዳም/ሔዋን መድረስ፣ ጋብቻ፣ ሽምግልናና ሞት፣ ከብዙዎች የሕይዎት ሽግግሮች (Rites of passages)፣ ጥቂቶቹ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ የሌሎቹ ሽግግሮች ሁሉ መዳረሻ የሆነውና የሰው ልጅ በጋራ የሚያልፍበት የመጨረሻው ሽግግር ሞት መሆኑን Abbink (2002፣67) ይገልጻሉ፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት ይኸው የመጨረሻ የሽግግር ሥርዓት ነው፡፡ ወደዝርዝር ጉዳዮቹ ከመግባቴ በፊት ይህን ሥርዓት ለማጥናት ያነሳሱት ምክንያቶች ምን እንደሆኑ አብራራለሁ፡፡

## 1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

ለአንድ ጥናት መካሄድ የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ለዚህ ጥናት መካሄድ መነሻ የሆኑት መሰረታዊ ምክንያቶች ከውስጣዊና ውጫዊ ግፊቶች የመነጩ ናቸው፡፡ ከቀዳሚው ብጀምር፣ የጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ የተጀመረውን ትምህርት ለማጠናቀቅ ከሚያስፈልጉት ግዴታዎች ከፊሉን ለማሟላት ‹‹ምን ላጥና?››፣ ከሚሉ አማራጮች የተመዘዘ፣ ከጭንቀት የተወለደ ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ ብልጭ ብሎ የተገባበት ሳይሆን፣ አብሮ ያደገና ብልጭ ድርግም እያለ ሲብሰለሰል የኖረ ነው፡፡

ጥናቱ በተካሄደበት ማሕበረሰብ ለለቅሶ ሥርዓቶች ክንውን ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡ የሟች ቤተሰቦችና የቅርብ ዘመዶች፣ የሟች የለቅሶ ሥርዓት በደመቀ ሁኔታ እንዲፈጸም ጥረት ያደርጋሉ፡፡ የጥረታቸው ስኬት ወይም ውድቀትም ለምስጋና ወይም ለሀሜት ያጋልጣል፡፡ ስኬቶቹም ሆኑ ውድቀቶቹ በየቡናውና ሌሎችም መሰባሰቢያ አጋጣሚዎች መነጋገሪያዎች መሆናቸው፣ ያልዋልኩባቸውን የለቅሶ ክንውኖች አስደሳችም ይሁን አሳዛኝ ገጽታ ከልጅነት ጀምሮ እያዳመጥኩ እንዳድግ እድሉን ፈጥሮልኛል፡፡ ነፍስ እያወኩ ስመጣ በቅርብ ቤተሰቦችና በአካባቢ ሰው ሞት ላይ መገኘት የግድ በመሆኑ፣ ባልተሳተፍኩባቸው የለቅሶ ሥርዓቶች፣ ሲተረኩ እሰማቸው የነበሩትን ሲተገበሩ የማየትና የመስማት እድሉን አገኘሁ፡፡ ሀዘንተኞች ጸጉራቸውን በመላጨት፣ ፊታቸውን በመንጨትና አለባበሳቸውን በመቀየር ሀዘናቸውን

ስለሚገልጹባቸውና ስለበርካታዎቹ ሥርዓቶች ምንነት የማውቀው ነገር ባይኖርም፣ በለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ክወና ላይ አያቸው የነበሩት ስልት የጠበቁ እንቅስቃሴዎችና ስሜት የሚነኩ ዜማዎች ይመስጡኝ ነበር፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ለተሻለ ሕክምና ወደጎንደር ሆስፒታል ተልካ በዚያው ስለቀረችው እህቷ እንደወጣች መቅረትና ስለሰው አገር አፈር እያነሳች እናቴ ታንጎራጉራቸው የነበሩት ቃል-ግጥሞች፣ በሰው አገር ስለመሞት አስከፊነትና ሞት በስጋ ዝምድና ላይ ስለሚያስከትለው ጉዳት በልጅነት መንፈሴ ውስጥ አንዳች ስሜት ትተው አልፈዋል፡፡ እንዲሁም በአካል ለማላውቀው አያቴ በኋላም ለእናት አባቷና ለአባቴ ‹‹ሙት ደረቅ አይበላም›› በሚል ብሂሏ፣ ሙት ዓመታቸውን (እርሷ ቀናቀን ትለዋለች) እየጠበቀች በጸሎት ስማቸውን ማስነሳቷ፣ ‹‹ለሟች ዘመዶቻችን፣ ይህን ሳታቋርጥ ወጪውን ሸፍና ለምትዘክራቸው እናቴ፣ በዝግጅቱ ለሚሳተፉት ተባባሪዎች ‹‹ከምርቃት ያለፈ ጠቀሜታው ምን ይሆን?›› የሚለው ጥያቄ በውስጤ ይመላለስ ነበር፡፡

በዚህ ላይ በስራ ምክንያት በቆየሁባቸው ሌሎች አካባቢዎች (ማሕበረሰቡ ተመሳሳይ በሆነበትም ጭምር)፣ በተለይ በሙሾ ክወና፣ በከዋኞቹ ጾታና በወየታ ስያሜ ባደኩበት አካባቢ ከለመድኩት የተለየ አከዋወንና ስያሜ ያለ መሆኑን ማየቴ በትውልድ አካባቢዬ የተለየ ባሕል መኖሩን የምገነዘብበትን እድል ፈጠረልኝ፡፡ የልዩነቶቹን መንስኤዎች ምንነት የማወቅ ጉጉትም አደረብኝ፡፡ በ2002 ዓ.ም ለኮርስ ማሟያ የፎክሎር የመስክ ጥናት ወደጎንደር ዙሪያ ወረዳ ተጉዤ የመስክ ቆይታየን ሳገባድድ እግረ መንገዴን እናቴን ለመጠየቅ ጎራ ባልኩበት የትውልድ መንደሬ፣ አንድ ዘመዴ በመሞቱ ከ25 ዓመት በኋላ በለቅሶው ሥርዓት ላይ የመታደም አጋጣሚ ተፈጠረ፡፡ ከላይ በጠቀስኳቸው ምክንያቶች ቆስቋሽነት፣ በዚያ ለቅሶ ላይ የሥርዓቶቹንና የለቅሶ-ቃልግጥሞቹን ክወና አደነዋሪዎቹ በዘልማድ ከመተግበር፣ በባለሙያ ዐይን ወደማየት መሸጋገር እንዳለብኝ ከምወስንበት ደረጃ ደረስኩ፡፡ ከመስክ መልስ ስላጋጠመኝ ሁኔታና በውስጤ ስለሚመላለሰው ነገር ለመምህሬና አማካሪዬ ለዶ/ር ፈቃደ ሳጫውታቸው፣ በፒ.ኤች.ዲ ደረጃ የሚሰሩ ጥናቶች በድንገት የሚመረጡ መሆን እንደሌለባቸውና አጥኚው ለርዕሰ ጉዳዩ ያለው ፍቅር ትልቅ ቦታ እንደሚሰጠው ጠቁመው፣ እንድቀጥልበት ጣል ያደረጉልኝ ምክር በሀሳቤ እንድገፋበት አበረታታኝ፡፡ በእነዚህ ውስጣዊ ግፊቶች ከመጨረሻው ውሳኔ ላይ ከመድረሴ በፊት

ግን፣ ለውጫዊ ሁኔታዎችም ቦታ መስጠት እንዳለብኝ በመገንዘብ፣ ‹‹ይኽ ነገር እስከምን ድረስ ተጠንቶ ይሆን?›› የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በኬኔዲ፣ በቋንቋዎች ጥናትና በድኅረ ምረቃ አብያተ መጻሕፍት በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ የተካሄዱ ጥናቶችን መቃኘት ጀመርኩ፡፡

ከቅኝቴም የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ትኩረት ተሰጥቷቸው አለመጠናታቸውን ከሀገር ውስጥ የምግባሩ (2009) እና የብርሃኑ (2002) ጥናቶች እንደሚገልጹ ተረዳሁ፡፡ በአፍሪካ ያለውን ሁኔታ ለመገንዘብ ካገላበጥኳቸው ድርሳናት መካከልም Finnegan (1970፣147) ለአፍሪካ የሀዘን እንጉርጉሮ ቃል-ግጥሞች (elegiac poetries) በጽሑፍ የቀረቡትን ያህል ትኩረት ባለመስጠቱ፣ የአጥኚዎችን ቀልብ እንዳልሳቡ መግለጻቸውንና Alembi (2002፣51) የአፍሪካም ሆነ የአውሮፓ ቃል-ግጥም ተመራማሪዎች፣ በለቅሶ ቃል-ግጥሞች ላይ ያካሄዱት ትንተና በጣም ውስን መሆኑን ማረጋገጣቸውን ተገነዘብኩ፡፡

ጥናቱን ለማካሄድ የሚያስችል በቂ ውጫዊ ምክንያት መኖሩን በመረዳት ቅኝቴን ሳጠናክር፣ ከሞት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሥርዓቶችና ቃል-ግጥም ክወናዎች፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጎጅ ባህላዊ ድርጊትነት ፈርጆ እንዳይከወኑ የመከልከል አዝማሚያ በመንግሥት በኩል እየታየ መሆኑን ከምግባሩ (2009) ጥናት ተገነዘብኩ፡፡ የላይ አርማጭሆ ወረዳ የቀብር ስርዓትና፣ በሥርዓቱ ላይ የሚካሄዱ የቀረርቶና የፉከራ ቃል-ግጥሞች፣ በሀይማኖታዊና ፖለቲካዊ ተጽዕኖዎች ምክንያት ነባር ይዘታቸውን እያጡ መሆናቸውንም ከሞገስ እ.ኢ.አ. (2002፣3) ጥናት ለመረዳት ቻልኩ፡፡ በጎንደር ከተማ የለቅሶ ሥርዓት ላይ ጥናታቸውን ካካሄዱት ከጌጡ (1989) የጥናት ውጤት ደግሞ፣ የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔው በጊዜ ሂደት እየቀነሰ መምጣቱንና የቪዲዮ ቀረጻ በመደበኛ ክዋኔው ላይ ጫና እያሳደረ መሆኑን የሚጠቁሙ መረጃዎችን አገኘሁ፡፡

በእነዚህ ላይ በማሕበረሰቡ ውስጥ በሚኖሩት የማያቋርጡ ለውጦች፣ ሥርዓቶቹም ሆኑ ቃል-ግጥሞቹ ለለውጥ የሚገዙ በመሆናቸው፣ የሥነቃሎቹ ሥነ ጥበባዊና አውዳዊ ለዛ እየደበዘዘና እየተለወጠ መሄዱ የማይቀር እውነታ መሆኑን የጌቴ (2002) ጥናት ሲያስገነዝብ Geest (2006፣486)፣ ከ1969-73 በነበረው የጊዜ ክልል ጋና ውስጥ የሚገኙ የኩዋሁ ማህበረሰብ አባላት፣ በቀብር ዙሪያ ሲያከናውኗቸው የተመለከቷቸውን አፈጻጸሞች ከአሁኑ (2006) ጋር ሲያነጻጽሯቸው፣ በብዙ መንገድ ስርነቀል ለውጥ ማየታቸውን እና Wilce (2009፣IX)፣ በየአካባቢው የሚገኙ የሀዘን እንጉርጉሮ ልማዶች እንደሞቱና በመሞት ላይ መሆናቸውን

የገለጹባቸው ጥናቶች በጊዜ ሂደት የሥርዓቶቹን ለለውጥ መጋለጥ አይቀሬነት የሚያጠናክሩ ሁነው አገኘኋቸው። ከእነዚህ በተለየ መልኩ ደግሞ፣ Sanka Confidence (2010) የሲሳላ ወጣቶችና አብዛኞዎቹ ጋናውያን፣ የለቅሶ ቃል-ጥሞች ለማህበረሰቡና ለሀገሪቱ ዋጋ እንዳላቸው ሳይሆን፣ ሟችን ለመሰናበት ብቻ የሚቀርቡ ድግግሞሾች አድርገው በመመልከት የውጭውን ዓለም የቀብር ሥርዓት ተግባራዊ ወደማድረግ መሸጋገራቸውንና ወጣቶችም የቃል-ግጥሞቹን ክወና ለመከታተል ፈቃደኛ አለመሆናቸውን የገለጹበት የጥናት ውጤት የውጪው ተጽዕኖ የሚያስከትለውን ለውጥ እንድገነዘብ መነሻ ሆነኝ።

በአጠቃላይ በአጉል ባህል ሰበብ በለቅሶ ሥርዓቶቹና ቃል-ግጥም ክወናዎቹ ላይ የተጀመረው ክልከላ፣ የሀይማኖት ተቋማት ውግዘት፣ ቴክኖሎጂው እያስከተለ ያለው ተጽእኖ፣ የውጪውን ባሕል የመውረስ አባዜና የዲያስፖራው በተለያዩ ምክንያቶች ከባህሉ የሚያፈነግጡ ሥርዓቶችን መከተል፣ ወይም በነባሩ ሥርዓት ያለመሳተፍ ፍዝ ተመልካችነት፣ ለነባሩ የለቅሶ ሥርዓት ባህል መሸርሸር የየራሳቸውን ድርሻ እያበረከቱ መሆናቸውን ለመገንዘብ ቻልኩ። ከቅኝቶቼም፦

1. የለቅሶ ሥርዓት በአፍሪካም ሆነ በኢትዮጵያ አካዳሚያዊ ትኩረት ተሰጥቶት ያልተጠና መሆኑን፣

2. በመንግሥታዊና ሀይማኖታዊ ተቋማት አማካይነት የለቅሶ ሥርዓቶቹና ቃል-ግጥሞቹ ክወና ላይ እገዳ እየተካሄደ መሆኑን፣

3. በውጭ ባሕል ተጽዕኖ፣ በአኗኗር ዘይቤ ለውጥና፣ በጊዜ ሂደት በሚመጣ ለውጥ ምክንያት፣ ነባሩ የለቅሶ ሥርዓት ባሕል በተለያዩ የአፍሪካ ሀገሮች እየተለወጠ መሆኑን ለመገንዘብ ቻልኩ።

እነዚህ ሁኔታዎች በትውልድ ቅብብሎሽ እየዳበሩ የመጡት የለቅሶ ሥርዓቶችና ቃል-ግጥም ክወናዎች ቀጣይነት ላይ እንቅፋቶች መደቀናቸውን በተጨባጭ አስገነዘቡኝ። በውስጣዊ ግፊቶቼ ላይ የእነዚህ ውጫዊ ሁኔታዎች አሳሳቢነት፣ እየተለወጡ ያሉትን ሳይረሱ ለማስቀረትና አሁን ያለውን ገጽታ ለማሳየት ላለመው ለዚህ ጥናት መካሄድ ዋና ምክንያቶች ሆኑ።

በእነዚህ ተጨባጭ አነሳሽ ምክንያቶች ላይ ተመስርቼ ርዕሰ ጉዳዩ መጠናት እንዳለበት ከወሰንኩ በኋላ፣ የጥናቱን ታሪካዊ ዳራ የሚያሳዩ መረጃዎችን ቀጥሎ በቀረበው መንገድ አሰባሰብኩ፡፡

## 1.2. የጥናቱ ታሪካዊ ዳራ

Hill እና Daniels (2008፣393) እንደሚያስረዱት፣ በልዩ ልዩ መቃብሮች ላይ የተደረጉ ሳይንሳዊ ጥናቶች፣ የሰው ልጅ ከጥንት ጀምሮ ሟቾችን የሚቀብርበት የተለያየ ልማድ ማዳበሩን ያመለክታሉ፡፡ ለምሳሌ ሳይንቲስቶች፣ ከአውሮፓ የአልፓይን ተራሮች እስከደቡብ አሜሪካ ጥልቅ ዋሻዎች፣ ከአፍሪካ በረሃዎች እስከሠላማዊ ውቅያኖስ ደሴቶች፣ ባደረጓቸው የመቃብር ጥናቶች፣ ጥንታዊ ሰዎች ስለሞት ምንነት ሀሳቦችን ሲያፈልቁ፣ የአቀባበር ልማዶቻቸው እነዚህን ሀሳቦች እንዲያንሰላስሉ ተደርገው ተካትተዋል፡፡ የአቀባበር ሥርዓታቸው፣ ቀብር የሚያከናውኑባቸው ጊዜያት፣ ሟቾች በሰላም እንዲያርፉ አብረዋቸው የሚቀበሩት ቁሶች፣ ሟች በቋሚዎች ላይ የሚኖረውን ሚናና፣ ከሞት በኋላ ሊኖር ይችላል የሚባለውንም ሕይወት አንጸባራቂዎች ሆነው ተገኝተዋል፡፡

እንደቁሶቹ ከሟች መቃብር ውስጥ ተቆፍሮ የሚወጣ ቅሪት አይኑራቸው እንጂ፣ የሰውን ልጅ ታሪክ፣ እምነት፣ በሞት ዙሪያ ያለውን አመለካከትና የወዲያኛውን ዓለም ተስፋ የሚያንጸባርቁ መረጃዎችን ከትውልድ ትውልድ በማስተላለፍ፣ ቃል-ግጥሞችም የበኩላቸውን ድርሻ እንደተወጡ አያጠራጥርም፡፡ ምክንያቱም ቃል-ግጥሞች፣ የተለያዩ ማሕበረሰቦች ልዩ ልዩ የየዕለት ሕይወታዊና ተፈጥሯዊ ጉዳዮችን ኪነጥበባዊ በሆነ መንገድ የሚገለጹባቸው፣ የውስጣዊ ስሜት መግለጫ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ Okpewho (1992፣138) እንደሚገልጹት፣ በገጠሬው የአፍሪካ ማህበረሰብ ዘንድ በዝማሬና (chants)፣ በዘፈን (songs) የሚቀርቡ ቃል-ግጥሞች፣ የዕለት ከዕለት የህይወት መግለጫ ክስተቶች ናቸው፡፡ Finnegan (1970፣147) እንደሚያስረዱትም፣ የዚህ ዘውግ አካል የሆኑት የሀዘን እንጉርጉሮ ቃል-ግጥሞች በየትኛውም የአፍሪካ ክፍል በተለያየ ቅርጽ በስፋት ይገኛሉ፡፡ Nketia (1955) በአካን ጎሳዎች የለቅሶ ሙሾዎች፣ Babalola (1966) በዮሩባ ጀግና የቀብር ቃል-ግጥሞች ላይ ባደረጓቸው ጥናቶች፣ ልማዱ ሰፊ ሽፋን ያለው መሆኑን በተጨባጭ መረጃዎች ላይ ተመስርተው አመልክተዋል፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADDIS ABABA, ETHIOPIA

በኢትዮጵያም የተለያዩ ብሔረሰቦች ከሞት ጋር በተያያዘ የሚከውኗቸው ቃል-ግጥሞች አሏቸው፡፡ ይህ ጥናት በተካሄደበት በአማራ ማሕበረሰብ፣ የለቅሶ ቃል-ግጥም ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ የሚከወን ባህል እንደሆነና እንደመሰንቆና በገና ባሉት ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች እየታጀበ ይቀርብ እንደነበርም ኅሩይ* እ.ኢ.አ. (1910፣18) ያስረዳሉ፡፡ ማኅተመ ሥላሴም እ.ኢ.አ. (1942፣590) ዓመተ ምህረቱን ለይተው ባያመለክቱም፣ የለቅሶ ሥርዓት በቀድሞ ነገስታት ዘመን የነበረውን መልክ ሲያወሱ፣ ልማዱ የቆየ መሆኑን በተዘዋዋሪ መንገድ ገልጸዋል፡፡ እ.ኢ.አ. በ1551 በጦርነት ለሞቱት አጼ ገላውዴዎስ የለቅሶ ቃል-ግጥም ተገጥሞላቸው እንደነበር ተክለ ጻድቅ እ፣ኢ.አ. (1965፣75) ዘመኑን ጠቅሰው ጽፈዋል፡፡

ሳሙኤል (1994፣39) ደግሞ፣ የለቅሶ ቃል-ግጥሞችን እድሜ ከላይ ከተጠቀሰው ቢያንስ በሁለት መቶ ዓመት ገደማ ያስረዝሙታል፡፡ የአማርኛ ግጥሞች ለመጀመሪያ ጊዜ በአጼ አምደ ጽዮን ዘመን እ.ኢ.አ. (1313-1343)፣ በጽሑፍ ሰፍረው ቢገኙም፣ እንደዘፈን፣ ሙሾና መወድስ አይነቶቹ ቃል-ግጥሞች ከዚያ ቀድመው ይነገሩ ወይም ይወረዱ እንደነበር ያስረዳሉ፡፡ Chadwiceን (ጊዜው አልተገለጸም) ዋቢ በማድረግ Finnegan (1970፣149) እንደሚያስገነዝቡት ደግሞ፣ ለሳባ ጋዲስ** የተገጠሙት የሀዘን እንጉርጉሮዎች፣ ለክፍለ ዘመናት ተጠብቀው ሲተላለፉ ቆይተዋል፡፡ እነዚህ መረጃዎች በኢትዮጵያ ልማዱ የቆየና ሰፊ መሰረት ያለው መሆኑን ያመለክታሉ፡፡

የሙሾ ቃል-ግጥሞች መቼ እንደተጀመሩ በትክክል የሚያስረዱ መረጃዎች አይገኙ እንጂ፣ ሞት በተከሰተ ቁጥር ከሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ልማዶች በቃል-ግጥሞች እያጀቡ ማቅረብ፣ ለአማራ ማሕበረሰብ እንግዳ እንዳልሆነ፣ የተጠቀሱት ምንጮች ይጠቁማሉ፡፡ ይሁን እንጂ፣ በጥናቱ አነሳሽ ምክንያት እንደተጠቆመው በዘርፉ የተካሄዱ የተሟሉና አመርቂ ጥናቶች፣ በኢትዮጵያ ጥናት፣ በቋንቋዎች ጥናት፣ በድሕረ ምረቃ፣ በኬኔዲ አብያተ መጻሕፍትና በብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጄንሲ በተደረጉ ፍተሻዎች እስካሁን አልተገኙም፡፡

---

*ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፣ እ.ኢ.አ. በ1910 ዓ.ም ‹‹የለቅሶ ዜማ ግጥም››፣ የምትል መጽሐፍ አሳትመዋል፡፡ የኅሩይ ዓላማ የለቅሶ ግጥሞቹን ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጋር ለማዛመድ ቢሆንም፣ ግጥሞቹ የተገጠሙበትን ምክንያት ከአዋቂዎች በመጠየቅ የሰጧቸው ማብራሪያዎች፣ በተሟላ መልኩም ባይሆን ፎክሎርን ከነአውዱ ለመሰብሰብና ለመተንተን የሞከሩ ቀዳሚው ኢትዮጵያዊ የሚያደርጋቸው ይመስለኛል፡፡

**እ.ኢ.አ. በ1824 ከራስ ማርየ ጋር ባደረጉት ጦርነት ተማርከው የተገደሉ ትግራይን ሲገዙ የነበሩ ንጉስ ናቸው፡፡

በዘርፉ ከተደረጉት የ‹ጥናት› ሙከራዎች፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ እንዲሁም በውጭ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍሎች ተማሪዎች የተሰሩ የመጀመሪያና የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶችና፣ በልዩ ልዩ ጉባዔዎች የቀረቡ የጥናት ድርሳናት ይጠቀሳሉ፡፡

ይሁን እንጂ፤ በጥናቶቹ መረጃዎቹ ከአውዳቸው ውጭ ተሰብስበዋል፤ ቴክስቶቹ ከክወናቸው ተነጥለው ተተንትነዋል፤ መረጃዎች በተዛባ መንገድ ቀርበዋል፤ ክወናዎችን ከመዘርዘር ባለፈ ለምን እንደሚከወኑ አልተገለጸም፤ ትዕምርቶች በአግባቡ አልተፈከሩም፡፡ እንዲሁም በለቅሶ ሥርዓት ላይ የሚከወኑ ድርጊቶች ለምን እንደሚከወኑ አልተብራራም፤ በተወሰኑ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ ሰፊ ማጠቃለያ ላይም ተደርሷል፡፡

በአጠቃላይ በአንድ የተወሰነ ቦታ የሚኖሩ የአማራ ማሕበረሰብ አባላትን የለቅሶ ሥርዓትና ቃል-ግጥሞች አጣምሮ በሚከወኑበት አውድ መሰረት የተነተነና ሞት በቤተሰብና በማሕበረሰብ ላይ የሚያስከትለውን ውጤት የመረመረ ጥናት አለመደረጉን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በለቅሶ ሥርዓት ላይ ምን ምን ልማዶች እንደሚፈጸሙና ምን ምን ተግባራት እንደሚከናወኑ የሚጠቁሙ ጥናቶች ቢኖሩም፣ ልማዶቹም ሆኑ ተግባራቱ ለምን እንደሚደረጉ የሚያብራሩና ትእምርቶችን የሚፈክሩ ሆነው አልተገኙም፡፡ ፊቃደ (2001፣60) የኢትዮጵያን የሥነቃል ጥናት ገጽታ ቀደም ካለው ጊዜ እስካሁን በቃኙበት ሥራቸው የመመረቂያ ጥናቶቹ ከአማተር አጥኚዎች እምብዛም ያልተለዩ መሆናቸውን መግለጻቸው የጥናቶቹን ፈርጀ ብዙ ክፍተቶች ይጠቁማሉ፡፡ በአጭሩ ጥናቶቹ ከሞት ጋር የተያያዙ ልማዶችንና የለቅሶ ቃል-ግጥሞችን ክወና (በተሟላ መንገድም ባይሆን)፣ ለመግለጽ ከመሞከር ውጭ፣ በክወናቸው አማካይነት ሁለቱን አስተሳስረው ፍክራዊ ትንተና በማካሄድ የመረመሩ ሆነው አልተገኙም፡፡ ከሞት ጋር ለተያያዙ ልማዶችና ለለቅሶ ቃል-ግጥሞች ፋይዳ (function) ትኩረት አለመስጠትም ከክፍተቶቻቸው ውስጥ ይጠቀሳል፡፡

ከዚህ በላይ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ በተካሄዱት ጥናቶች ያልተተኮረባቸው ክፍተቶች ተለይተው ተጠቁመዋል፡፡ ክፍተቶቹን ለመሙላት ለዚህ ጥናት ተስማሚ የሆኑ የትውርና የትንተና ዘዴዎችን መምረጥ አስፈላጊ ነበር፡፡ የተመረጡት የትውርና የትንተና ዘዴዎች፣ እንዴትና ለምን እንደተመረጡ የሚያብራራው ክፍል ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 1.3. የክወና ትውር (performance theory)

በዚህ ጥናት፣ የመረጃዎቹን ትንተና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለማቅረብ የሚያስችል/ሉ የትውር ማዕቀፍ/ፎችን (theoretical framework/s)፣ የመምረጡ ሥራ ፈታኝ ሆኖ ተገኝቷል። ፈታኝ እንዲሆን ካደረጉት ምክንያቶች ውስጥ ዋናው፣ የለቅሶ ሥርዓቶቹና ቃል-ግጥሞቹ ክወና በተለያዩ ትውሮች ሊታዩ መቻል ነው። በአንድ ወይም በሌላ መልኩ የሩቅ ግንኙነት ያላቸው ላይ ከማትኮር ይልቅ፣ ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማስገኘት ከሚያስችሉት የጥናቱ ዘዴዎች (research methods)፣ ጋር የቀረበ ግንኙነት ያላቸው ላይ በማትኮር ለማጥበብ ጥረት ተደርጎ፣ ትውሮችን የመምረጡ ሥራ በሚከተለው መንገድ ተከናውኗል።

የጥናቱን ትንተና ይመራል ተብሎ በመጀመሪያ የታሰበው ትውር ተግባራዊ አንጻር (functional approach) ነበር። Bascomን (1965) ዋቢ በማድረግ Sims እና Stephens (2005፣174) እንደሚገልጹት፣ ይህ አንጻር ለፎክሎር መተንተኛነት በዋናነት ከሚሰራባቸው ትውሮች መካከል አንዱ ሲሆን፣ የተለያዩ የፎክሎር ዘውጎች ለከዋኙ ቡድን ምን ማለት እንደሆኑና ምን ፋይዳ እንዳላቸው ለመመርመር ያስችላል። ስለሆነም የለቅሶ ስርዓቶቹንና የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹን ተግባር ለመተንተን በማስቻሉ ተመርጦ ነበር። ሆኖም ግን፣ የቴክስቶችና ክወናዎች ትርጉም በአውድ የማይለዋወጥ፣ የፎክሎር ቴክስት አንድ ትርጉም ብቻ ያለውና፣ እሱም ከሎሩ ባለቤች ይልቅ በፎክሎረኛው የሚወሰን አድርጎ የሚመለከት መሆኑ፣ ከዚህ ጥናት ሞዴልና የጥናት ዘዴ ጋር የማይጣጣም ሆኖ በመገኘቱ፣ ከእነዚህ ጋር ተጣጥሞ የሚሄድ ትውር እንዲፈለግ አስገደደ።

በተግባራዊ አንጻር የታዩትን ውስንነቶች በማቃለል የመዋቅራዊ አንጻር (structural approach)፣ በሁለት መንገድ የተሻለ ሆኖ ተገኘ። Tedlockን (1971 እና 1992) ዋቢ በማድረግ፣ Sims እና Stephens (2005፣185) እንደሚያስረዱት፣ የመዋቅራዊ አንጻር በአንድ በኩል የለቅሶ ሥርዓቶቹንና የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹን ክወናዎች ቅደም ተከተላዊ መዋቅር ለመተንተን ሲያስችል፣ በሌላ በኩል የዚሁ አንጻር አካል በሆነው ኢትኖፖኤቲክስ አደራጃጀት (ethnopoetics system) አማካይነት የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹን ቴክስቶች ቃላዊ አቀራረብ

(የድምጽ ቅላጼ፣ በአጽንኦት መነገር፣ ጮክ ብሎና ቀስ ብሎ መነገርና ድምጸት) እና እነዚህ ለአጠቃላይ ክወናው ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ለመተንተን የሚያስችል ነው።

ይህ አንጻር፣ ነገሮች ለምን እንደተባሉ ብቻ ሳይሆን፣ እንዴት እንደተባሉ ጭምር በጥልቀት ለመመርመር ማስቻሉና፣ የዚሁ አንጻር አካል የሆነውን ኢትኖፖኤቲክስ አንጻርን በመጠቀም Alembi (2002)፣ ኬንያ ውስጥ የሚገኘው የአብንዮል ማህበረሰብ በለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ አማካይነት ሞትን እንዴት እንደሚመለከተው፣ Sanka (2010) ጋና ውስጥ የሚገኘውን የሲሳላን ማህበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች በጥልቀት ለመተንተኛነት መጠቀማቸው፣ ትውሩ የለቅሶ ቃል-ግጥሞችን በተጠኘው ማህበረሰብ ትርጉም ላይ ተመስርቶ ለመመርመር እንደሚያስችል ማሳያዎች ሆኑ። ሆኖም ግን፣ የክወናው ባህላዊና ማሕበራዊ አውዶች፣ የከዋኝና ታዳሚ መስተጋብር በጥናቱ ላይ የሚኖራቸው ሚናና የክወና ማጀቢያ መሳሪያዎችን የሚያካትት ሆኖ ባለመገኘቱ፣ እነዚህን ሊያካትት የሚችል ትውር ፍለጋው ቀጥሎ፣ ከላይ ከተቃኙት ትውሮች በተሻለ ከጥናቱ ሞዴልና ዘዴ ጋር ተጠየቃዊ ትስስር በመፍጠር፣ የክወና ትውር (performance theory) የተሻለ ሆኖ በመገኘቱ፣ ለጥናቱ ትውርነት ተመርጧል።

ምክንያቱም ክወናን ከጥበባዊነቱ፣ ከመከሰቻ አጋጣሚው፣ ከመገለጫ መንገዱ፣ ከከዋኝና ታዳሚው ሚና፣ ከማህበራዊ ደንቡና ከአውዱ፣ አቅጣጫ የተመለከቱት (ፊቃደ፣1984፣1-3)፣ ዘሪሁን (1992፣22-23)፣ Bauman (1986፣3-4)፣ Kapchan (1995፣479) እና Finnegan (1992፣87) እንደሚያስረዱት፣ ከእለት ተእለት ተራ ክንውኖችና ተግባቦቶች የሚለዩት አመልካች ቁልፍ ቃላትና ጠቋሚ አካላዊ እንቅስቃሴዎች ያሉት፣ በአንዳች ማህበራዊ አሰባሳቢ ጉዳይ፣ ለጉዳዩ ተስማሚ በሆነ ጊዜና ቦታ በቋንቋ ወይም በአካላዊ እንቅስቃሴ ወይም በሁለቱም የሚቀርብ፣ ከዋኙ፣ የሚከውነው የፎክሎር ዘርፍ ከሚፈቅደው ልማዳዊ ደንብ ሳያፈነግጥ የራሱን የአቀራረብ ክህሎት ተጠቅሞ የታዳሚዎቹን ስሜት የሚይዝበት፣ ታዳሚዎቹ የሚከወነው ነገር በማህበሩ ደንብ በትክክል እየተከወነ መሆኑን እየገመገሙ የሚጠበቅባቸውን ምላሽ የሚሰጡበት፣ ልምድ በተደጋጋሚ የሚዳብርበት ድርጊታዊ ክንውን ነው። Bauman (1992፣44) አክለው እንደሚገልጹት፣ ክወና መጀመሪያና መጨረሻ ባለው ማዕቀፍ ተቀንብቦ የሚቀርብ ክንውን ሲሆን፣ ክንውኑም ከዙሪያ ገባው አውድ የሚመነጭ፣ ለታዳሚዎቹ ክፍት የሆነና፣ በእይታ ወይም በቁስ ይፋ የሚሆን ድርጊታዊ መግባቢያ ነው።

ስለሆነም የለቅሶ ሥርዓቶቹና የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ፣ በሞት መከሰት አስባሳቢነት፣ መጀመሪያና መጨረሻውን ጠቋሚ የሆኑ ቃላትን፣ ከዋኝና ታዳሚ ማሕበራዊና ባሕላዊ ደንቡን በጠበቀ አውድ ውስጥ በቅብብል የሚከውኗቸውን ድርጊቶች ያቀፉና፣ የከዋኙን ችሎታ ታዳሚዎቹ እየገመገሙ ምላሽ የሚሰጡበትን ድርጊታዊ መግባቢያ ያቀፈና፣ ልምድ በተደጋጋሚ የሚዳብርበት ከመሆኑም በተጨማሪ፣ አዳዲስ ሁኔታዎችን ለመቀበል ክፍት በመሆኑ፣ እነዚህን ለመተንተን ትውፊ ተገቢነት አለው፡፡ በተጨማሪም የጥናቱ ዘዴ በቀረበበት ክፍል እንደተገለጸው፣ መረጃዎቹ በተፈጥሯዊ መቸታቸው እየተከወኑ ባሉበት ሁኔታ፣ የከዋኝ ታዳሚን መስተጋብርና አውድን መሰረት በማድረግ እየተደረገና እየተነገረ ያለው ሁነት በቀጥታ ስለተሰበሰበ፣ በሁለቱ መካከል የጠበቀ ግንኙነት ይታያል፡፡

በዚህ ትውር መሰረትነት በኢትኖግራፊያዊ የጥናት ዘዴ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ከእነዚህ ጋር ተጣጥሞሽ ባለው የትንተና ዘዴ ማስኬድ ተገቢ ነበር፡፡ ቀጥሎ ለትንተናው የተመረጠው የመሰረተ ባሕል ሞዴል /infracultural model/ ምንነትና የተመረጠባቸው ምክንያቶች ቀርበዋል፡፡

## 1.4. የመሰረተ ባሕል ሞዴል (infracultural model) የመረጃ ትንተናና ፍከራ ዘዴ

ለትንተናው የተለያዩ ዘዴዎችን ለመጠቀም ታስቦ ነበር፡፡ ምክንያቱም Bernard (2006፣473) እንደሚያስገነዝቡት፣ ምንም እንኳ ቴክስትን ለመተንተን የተለያዩ ተዘውትሮ የሚሰራባቸው ዘዴዎች ቢኖሩም፣ ራሱን የቻለ አንድ ወጥ የቴክስት መተንተኛ ዘዴ ባለመኖሩ ነው፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ መጀመሪያ ላይ ባህላዊ ትዕምርቶችን በአንድምታ ለመፈከር፣ ፍከራዊ ትንተና (hermeneutic analysis)፣ ሰዎች በለቅሶ ወቅት የሚያደርጓቸውን የርስበርስ ተራክቦዎች ለመተንተን፣ የሀቲት ትንተና (discourse analysis)፣ እና የተጠኚው ማህበረሰብ አባላት ከሞት ጋር በተያያዘ ስለሚያከናውኗቸው ድርጊቶች ያላቸው እውቀት ከባህላቸው ጋር ያለውን ትስስር በለቅሶ ቃል-ግጥሞቻቸው ከሚጠቀሙት ቋንቋና ዘይቤ እየለቀሙ ለመተንተን፣ ግንዛቤያዊ ትንተና (cognitive analysis)፣ ተመርጠው ነበር፡፡ የAlembi (2002) እና የSanka (2010) የዶክትርና የመመረቂያ ጥናቶች ከተነበቡ በኋላ ግን፣ እነሱ መረጃዎቻቸውን ለመተንተን

የተጠቀሙበት መሰረተ ባህል ሞዴል (infracultural model) ከላይ የተጠቀሱትን የፎክሎር የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች አቅፎ ስለሚይዝ ተመርጧል፡፡

Alembi (2002፣22)፣ (infracultural model) መሰረተ ባሕል የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ በጥናታቸው የተጠቀሙት፣ ድርጊቶችንና ቃላትን በአንድ የተወሰነ ባህላዊ አውድ መፈከርን ለመግለጽ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በሌላ አገላለጽ ጽንሰ ሀሳቡ ድርጊቶችና ቃላት በተጠኚው ማህበረሰብ አመለካከት የሚበየኑበት ነው፡፡ ይህን ለማድረግ መረጃዎቹ ሲሰበሰቡና ሲፈከሩ ተመራማሪውና ተጠኚዎቹ እየተወያዩ ተጋግዘው ይሰራሉ፡፡

ከዚህ ገለጻ፣ መሰረተ ባህል ሞዴል፣ የጥናቱ ትኩረት የሆኑት ክወናዎችና ስነቃሎች ከዋኞቻቸው በሚሰጣቸው ትርጉም እሚበየኑበት፣ ተመራማሪው መረጃዎቹ በሚከወኑበት መቼት በመገኘት ብቻ ሳይሆን ምንነታቸውን ለመግለጽም ሆነ ትዕምርታዊ ትርጉማቸውን ለመፈከር ከባህሉ ባለቤቶች ጋር በጋራ የሚሰራበት የመረጃ መተንተኛ ሞዴል መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

የዚህ ጥናት ዓላማ የለቅሶ ሥርዓቶቹን ክወናዎች በተጠኚዎቹ እይታና ግንዛቤ መግለጽና መፈከር በመሆኑ፣ መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በሚከወኑበት ተፈጥሯዊ መቼት በግንባር በመገኘት ስለምንነታቸውና ትዕምርታዊ ትርጉማቸው ተጠኚዎቹን በመጠየቅ ነው፡፡ የመረጃ ትንተናውና ፍከራውም ይህንኑ መንገድ የተከተለ በመሆኑ፣ የመሰረተ ባሕል የመረጃ መተንተኛ ሞዴል ተገቢ ሆኖ ሲመረጥ፣ ከማሕበራዊ ትርጉም ግንባታ ሞዴል፣ ከኢትኖግራፊያዊ የጥናት ዘዴ እና ከጥናቱ ዓላማ ጋር እጅግ የጠበቀ ትስስር ስላለው ነው፡፡

በአጠቃላይ ይህ ሞዴል የሚከተሉት ዋና ዋና ባህርያት እንዳሉት Alembi ይገልጻሉ፡፡

ሀ. የተጠኚውን ማሕበረሰብ ባህል በተባራሪ ወሬ በተገኘ መረጃ ወይም በቢሮ ተቀምጦ ሳይሆን፣ በማሕበረቡ ውስጥ ያሉትን እውነታዎች ከውስጡ ገብቶ በመረዳት መፈከርን ይጠይቃል፡፡

ለ. ከከዋኙ ባህልና ልማድ ጋር ጥልቅ ትስስር እንዳላቸው የሚታመንባቸውን ሥነቃሎች በባህላዊ አውዳቸው ይፈክራል፡፡ ቃላትን ከዋኙና ታዳሚ በሚከወኑበት አውድ ከሚግባቡባቸው የጋራ ስምምነቶች ውጭ መጠቀም፣ ወደተዛባ ትርጉምና ወዳለመግባባት እንደሚወስድ ይገልጻል፡፡

ሐ. በጥናቱ ውስጥ የሚመረምረው፣ የትረካ ፈረሮችንና (paternes) ሌሎች ቅርጻዊ ባህርያትን ብቻ ሳይሆን፣ እነዚህን ላዕላይ መዋቅሮች የጥናቱን ጭብጥ ግልጽ ለማድረጊያነት በመጠቀም ነው፡፡

መ. በማህበረሰቡና በሚጠናው ነገር ዙሪያ ያሉ ጉዳዮችን ቅርጽና ትርጉም ለመረዳት በጥልቅ ውይይትና መስተጋብር መሳተፍን ይጠይቃል፡፡

ሠ. ትኩረት ተሰጥቶት የሚጠናው ነገር የሚፈለገውን ትርጉም እንዲያስገኝ፣ ከዋኙ፣ ታዳሚውና ፎክሎሪኛው በክወና ሜዳው በመገኘት ተባብረው መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሥራውን በራሱ እሴት ለመመዘን ክወናው በተለምዶ በሚቀርብበት ቦታ ተገኝቶ ሂደቱን መከታተልን የግድ ይላል (ገጽ፣ 23-24)፡፡

ስለሆነም በመረጃ መተንተኛ ዘዴው ለተጠቀሱት መሰረታዊ ነጥቦች ትኩረት በመስጠት፣ ይህ ጥናት የለቅሶ ሥርዓቶቹን ክወና በአውዳቸው ላይ ተመስርቶ ተጠኚዎቹ እያደረጉና እያሉ ያሉትን በተጨባጭ መረጃዎች ከማሳየቱ በተጨማሪ፣ ስለእያንዳንዱ ድርጊት ምንነትም የተጠኚዎቹን ግንዛቤ መሰረት ያደረገ ማብራሪያ ሰጥቷል፡፡ ሥርዓቶቹንና ቃል-ግጥሞቹን ለመከወን በማጀቢያነት የሚውሉ ቁሶችን ምንነት ከመግለጽ ባለፈ፣ አገልግሎታቸውንና ትዕምርታዊ ትርጉማቸውንም በተጠኚዎቹ ባሕል መሰረት አብራርቷል፡፡ እንዲሁም የሥርዓቶቹንና የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹን ማህበራዊ አገልግሎትና ባህላዊ ትርጉም በመመርመርና በመፈከር፣ በጥናት መስኩ ዙሪያ ከላይ የተጠቀሱትን ክፍተቶች ለመሙላት ጥረት አድርጓል፡፡

ከዚህ በላይ ጥናቱ ስለተካሄደበት አካባቢ መልካምድርና ማሕበራዊ ዳራ እንዲሁም ጥናቱን ለማካሄድ ስላነሳሱ በቂ ምክንያቶች መኖር ተገልጿል፡፡ የጥናቱን ትኩረት ለመወሰንም በርዕሰ ጉዳዩ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ተቃኝተውና ክፍተቶቻቸው ተለይተው፣ እነሱን መሙላት የዚህ ጥናት ትኩረት መሆኑ ተጠቁሟል፡፡ ተገቢዎቹ የትውርና የትንተና ዘዴዎች የትኞቹ እንደሆኑና እንዴት እንደተመረጡም ተገልጿል፡፡ ቀጥሎ ደግሞ፣ የጥናቱ ዓላማዎች ማብራሪያ ቀርቧል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ፣ የደቡብ ጎንደር ዞን የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ማሕበረሰብ፣ ሞት ሲከሰት በቡድን የሚያከናውናቸውን የለቅሶ ሥርዓቶችና ቃል-ግጥሞች ክወና መግለጽ ነው፡፡

በንኡስነት ደግሞ፡-

1. የለቅሶ ሥርዓቶቹንና የቃል-ግጥሞቹን ክወናዎች በመመርመር ትዕምርቶችን ይፈክራል፡፡

2. የሟች ቤተሰቦች ወይም የቅርብ ዘመዶች ሀዘናቸውን የሚገልጹባቸውን ልማዶች ይገልጻል፤ ትዕምርታዊ ትርጉማቸውንም ያብራራል፡፡
3. የመታሰቢያ ሥርዓቶቹን ምንነት ይተነትናል፤ ትእምርታዊ ትርጉማቸውን ይፈክራል፤ ማሕበራዊ ፋይዳቸውንም ይገልጻል፡፡

4. በለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ፣ ሞት በሥጋ ዝምድናና በማህበራዊ ትስስር ላይ የሚያስከትለውን ውጤት ያብራራል፡፡

ጥናቱ እነዚህን ዓላማዎች ማሳካቱ ወይም የጥናቱ መካሄድ ምን ጥቅም ያስገኛል? ባይጠናስ ምን ይቀራል? የሚሉትን ጥያቄዎች የሚመልሰውና የጥናቱን ፋይዳ የሚገልጸው ክፍል ደግሞ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ

ሞት በሰው ልጅ የሕይወት ጉዞ ውስጥ ጉልህ ቦታ ከሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው፡፡ ለማንም የማይቀር እጣ ፈንታ መሆኑ፣ የሰውን ልጅ በሙሉ ሲያሳስብ፣ የሚመጣበት ጊዜ አለመታወቁ ደግሞ፣ አስደንጋጭ ሆኖ እንዲታይ አድርጎታል፡፡ ይህን የማይቀር የጋራ እዳ፣ በቡድን ለመቋቋም የሰው ልጅ የተለያዩ የመተጋገዣ ባህላዊ ተቋማትን አቋቁሞ፣ ሞት ሲከሰት የየሚናውን ለመወጣት ደፋ ቀና ሲል ኖሯል፤ አሁንም በማለት ላይ ይገኛል፡፡

ሟችን በሚኖርበት ማሕበረሰብ ባህልና እምነት ስምምነታዊ ደንብ መሰረት ለቀብር ከማሰናዳት ጀምሮ፣ ሞት የፈጠረውን የሀዘን ድባብ ከውስጣዊ ስሜት፣ አመለካከትና እምነት በመነጨ የለቀሶ ቃል-ግጥሞች አማካይነት መግለጽ የሚከናወነው በግለሰቦች ቢሆንም፣ አስተሳሳሪው ጉዳይ ግን ቡድናዊ ስሜት ነው፡፡

ስለሆነም፣ ከፍ ብሎ በአጉል ባህል፣ በሀይማኖት፣ በፖለቲካ፣ ጊዜ በሚወልደው የአኗኗር ዘይቤ ለውጥና፣ በባህል ወረራ ምክንያት ቀጣይነታቸው ላይ አደጋ እንደተጋረጠባቸው የተጠቆሙትን የለቅሶ ሥርዓቶችና የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ማጥናት፣ አመንጫቸው ማሕበረሰብ ስለሞትና ስለደረሰበት መሪር ሀዘን ብቻ ሳይሆን፣ በዚያ ማህበረሰብ ውስጥ በግለሰቦችና በቤተሰባቸው፣ በቅርብ ዘመዶቻቸውና አለፍ ሲልም በሚኖሩበት ማሕበረሰብ መካከል ስላለው ትስስር፣ በማህበረሰቡ ዘንድ ስለሚበረታቱ መልካም ምግባራት፣ ከአሟሟት ሁኔታ ጋር ስለሚያያዙ አመለካከቶች፣ ከሞት ወዲያ አለ ተብሎ ተስፋ ስለሚደረገው ሕይወት፣ በወቅቱ ስላለው ፖለቲካዊ አስተዳደርና ተፈጥሯዊም ይሁን ሰው ሰራሽ አደጋ (ድርቅ፣ ጦርነት)፣ ተጠኚው ማህበረሰብ ያዳበረውን ጥልቅ አመለካከት፣ እምነትና ፍልስፍና ለመረዳት ያስችላል፡፡

በሌላ በኩል የለቅሶ ሥርዓትን ማጥናት፣ ተጠኚው ማህበረሰብ በኖረበት ዘመን የነበረውን ማህበራዊ ተራክቦ፣ ታሪክና አሳሳቢ ጉዳይ፣ የሚመለከቱ መረጃዎችን በወጉ ፈልፍሎ ለማውጣት ከማስቻሉም በላይ፣ ማህበረሰቡ የሚፈልገውንና የማይፈልገውን ተገንዝቦ ሊተገበሩና ወደታለመው ግብ ሊያደርሱ የሚችሉ ፖሊሲዎችን ለመንደፍ የሚያስችሉ ጠቃሚ መረጃዎችን ያስገኛል፡፡ የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹም ሆኑ ሥርዓቶቹ ሳይጠኑና ሳይቀረሱ በተጋረጡባቸው እንቅፋቶች ምክንያት እየደበዘዙና እየጠፉ ቢሄዱ ግን፣ አብሮ የሚደበዝዘውና የሚጠፋው፣ የአመንጫቸው ማህበረሰብ ታሪክ፣ የሕይወት ፍልስፍና፣ አመለካከትና በእነዚህ ላይ የታነጸው ማንነት ጭምር ነው፡፡

የዚህ ጥናት መካሄድ ዋናው ጠቀሜታም፣ የለቅሶ ሥርዓቶቹና ቃል-ግጥሞቹ መጠናትና መጠበቅ የሚያስገኘውን ጥቅምና፣ አለመጠናታቸውና እየከሰሙ መሄዳቸው፣ የሚያሳጣውን እሴት አጉልቶ ማሳየት ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ፣ ይህ ጥናት የተጠኚውን ማህበረሰብ ባህል፣ አመለካከትና ፍልስፍና፣ ለሌሎች የማስተዋወቅ ጠቃሚታ ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም ከተለያየ አቅጣጫ በሚሰነዘሩት ክልከላዎችና የአኗኗር ዘይቤ ለውጥ በሚያስከትለው ጫና ከአገልግሎት ውጭ የሚሆኑ የለቅሶ

ልማዶችንና ቃል-ግጥሞችን በመሰነድ፣ ለመጪው ትውልድ አያት ቅድመ አያቶቹ ሀዘናቸውን እንዴት ይገልጹ እንደነበር የሚያሳዩ መረጃዎችን ቀርሶ ያስተላልፋል፡፡ ወደፊት፣ ያለፈውን በወቅቱ ካለው የቀብር ሥርዓትና የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ጋር በማነጻጸር ለማጥናት ለሚፈልጉ ተመራማሪዎችም፣ በመረጃ ምንጭነት ያገለግላል፡፡ እንዲሁም በሞት ዙሪያ የሚታዩ ልማዶችን፣ ክወናዎችንና ቃል-ግጥሞችን በሌሎች ማሕበረሰቦች ላይ ለማጥናት ለሚፈልጉ እንደመነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

ጥናቱ ለሚካሄድበት ዞንና ወረዳ የባሕልና ቱሪዝም ባለሙያዎች፣ በሳይንሳዊ የፎክሎር የመረጃ አሰባበሰብ፣ አቀራረብና አተናተን ዙሪያ፣ ልምድ በመቅሰም የተለያዩ መረጃዎችን በተገቢው መንገድ ከመሰብሰብ በአግባቡ እስከመቅረስና መተንተን የሚደርስ አቅም ሊፈጥር ይችላል፡፡

እስካሁን ጥናቱ የተካሄደበትን ዞንና ወረዳዎች ከመጠቆም ባለፈ የጥናት ቦታውም ሆነ ተጠኚዎቹ የተመረጡባቸው ምክንያቶች አልተገለጹም፡፡ ቀጥሎ ይህንኑ የሚያብራራው የጥናቱ ወሰን የተገለጸበት ክፍል ቀርቧል፡፡

### 1.7. የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ የተካሄደው በደቡብ ጎንደር ዞን ውስጥ ከሚገኙ አስራ አራት ወረዳዎች በተመረጡ አምስት ወረዳዎች ነው፡፡ በእነዚህ ወረዳዎች ውስጥ የሚከወኑ ከለቅሶ ጋር የተያያዙ ሥርዓቶች (የለቅሶ ቃል-ግጥሞች፣ የሀዘን አገላለጽ ልማዶችና የመታሰቢያ ሥርዓቶች) የጥናቱ ዋና ትኩረቶች ናቸው፡፡ የሀይማኖት አባቶች ያለቦታ ገደብ የተጠየቁ ሲሆን፣ ከአጎራባች ወረዳዎች የመጡ ከዋኞችም የጥናቱ አካል ተደርገው ተወስደዋል፡፡ ጥናቱ ከዞኑ ውጪ ያሉ ክወናዎችንና ከሞት ጋር ያልተያያዙ ልማዳዊ ድርጊቶችንም ሆነ ስነቃሎችን አላካተተም፡፡

ከዚህም በተጨማሪ፣ ይህ ጥናት የተመለከተው በዞኑ ውስጥ የሚገኙ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችን ከሞት ጋር የተያያዙ ልማዶች ብቻ ነው፡፡ ጥናቱ በተካሄደበት ዞን በማሕበራዊ ዳራው እንደተመለከተው፣ ቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑ የሙስሊምና የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ቢኖሩም፣ በጥናቱ አልተካተቱም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት፣ በአንድ በኩል በሁለቱም የቀብር ሥርዓት የለቅሶ ቃል-ግጥሞች የማይከወኑ በመሆናቸው፣ በሌላ በኩል

የሚያከናውኗቸው ልማዶች በየእምነቶቹ ፍልስፍና የሚመሩ በመሆናቸውና እነዚህን ለመመርመር የውስጥ አጥኚ መሆንን ስለሚጠይቅ ነው፡፡

የጥናቱ መግቢያ ከመደምደሙ በፊት ጥናቱ በውስጡ ስላካተታቸው ክፍሎች ማስተዋወቅ ተገቢ በመሆኑ፣ በስንት ክፍሎችና ምዕራፎች እንደተደራጀና በእያንዳንዱ ክፍልና ምዕራፍ የተነሱት መሰረታዊ ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ የተጠቆሙበት ክፍል ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 1.8. የጥናቱ አደረጃጀት

ጥናቱ ስምንት ምዕራፎች አሉት፡፡ በምዕራፍ አንድ፣ ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ መልካምድር እና የማሕበረሰቡ፣ ታሪካዊና ማሕበራዊ ዳራዎች፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ ትውርና መተንተኛ ሞዴል፣ የጥናቱ ዓላማዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰንና የጥናቱ አደረጃጀት ተካትተዋል፡፡ በምዕራፍ ሁለት ደግሞ፣ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የጽንሰ ሀሳብ መነሻዎችና የጥናት ድርሳናት ተከልሰዋል፡፡ በምዕራፍ ሶስት፣ የጥናቱ ዘዴ፣ በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱ መፍትሔዎችና መልካም አጋጣሚዎች፣ እንዲሁም ስነምግባራዊ ጉዳዮች ተካትተዋል፡፡ በምዕራፍ አራት የለቅሶ ሥርዓቶቹና የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ክወናዎችና ፍከራ ቀርቧል፡፡ በምዕራፍ አምስት፣ የሀዘን አገላለጽ ልማዶች፣ በምዕራፍ ስድስት፣ ለሟች መታሰቢያ የሚከናወኑ ሥርዓቶች ተተንትነዋል፡፡ በምዕራፍ ሰባት ደግሞ፣ ሞት በሥጋ ዝምድናና በማህበራዊ ትስስር ላይ የሚያስከትለው ውጤት ተገልጿል፡፡ በምዕራፍ ስምንት፣ የጥናቱ ማጠቃለያ ቀርቧል፡፡

እስካሁን ለጥናቱ መካሄድ አነሳሽ የሆኑትን ምክንያቶች፣ ጥናቱ የተካሄደበትን ዓላማ፣ ፋይዳውን፣ እስካሁን ከተካሄዱት ጥናቶች በተለየ ያተኮረባቸውን ነጥቦችና የሚሞላቸውን ክፍተቶች እንዲሁም በውስጡ ያካተታቸውን ክፍሎች በማንሳት አጠቃላይ ጥናቱን ለማስተዋወቅ ተሞክሯል፡፡ የምርምር ስራ በንጥልነት የሚካሄድ ወይም እውቀት በአንዴ የሚገነባ ባለመሆኑ፣ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ የሚነሱ ጽንሰ ሀሳቦችን ማካተትና ቀደም ሲል የተሰሩ ሥራዎችን በስፋት ቃኝቶ የአጥኚዎቹን ጠንካራና ደካማ ጎኖች መገምገም ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም በጥናቱ በተደጋጋሚ ለሚነሱት ጽንሰሀሳቦች መነሻ መሰረት ለመስጠት ከጥናቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ጽንሰ ሀሳቦችና የክለሳ ድርሳናቱ ክፍል፣ በሚቀጥለው ምዕራፍ ቀርበዋል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## 2. የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ (review of related literatures)

በዚህ ምዕራፍ በጥናቱ ውስጥ ተደጋግመው የሚነሱ ጽንሰ ሀሳቦች (concepts) እና ተዛማጅ ጥናቶች /related literatures/ ተከልሰዋል፡፡ የጽንሰ ሀሳብ ቅኝቶቹ፣ በሞት ምንነትና አይነት፣ በለቅሶ ሥርዓቶችና ልማዶች፣ እንዲሁም በለቅሶ ቃል-ግጥሞች ላይ የተነሱ ለጥናቱ ጠቀሜታ ያላቸውን የተለያዩ ጽንሰሀሳቦች አካትተዋል፡፡ የጥናት ክለሳዎቹ ደግሞ፣ በኢትዮጵያና በአፍሪካ በለቅሶ ሥርዓትና በቃል-ግጥሞች ክወና የሚታየውን የጥናት ይትበሃል (trned) ቃኝተዋል፡፡ በእያንዳንዳቸው ላይ የተካሄደው ክለሳ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 2.1. ጽንሰሀሳባዊ መነሻዎች

በዚህ ክፍል ከርዕሰ ጉዳይ ጋር ግንኙነት ያላቸው የተለያዩ ድርሳናት ተቃኝተው ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ድርሳናት፣ የሥርዓትን ብያኔ፣ የሞትን ምንነት፣ አይነት፣ መልክ፣ በሞት ዙሪያ የሚከናወኑትን ልማዳዊ ድርጊቶችና፣ የሚከወኑትን የለቅሶ ቃል-ግጥሞች፣ የሚመለከቱ ጽንሰ ሀሳቦች ናቸው፡፡ ክለሳው መጻሕፍትን፣ የዲግሪ ማሟያ ጥናቶችንና ጆርናሎችን በጥልቀት በመመርመር ላይ ተመስርቶ የተካሄደ ነው፡፡

#### 2.1.1. የሥርዓት (Ritual) ምንነት

ስለ ሥርዓት ምንነት የሚሰጡት ብያኔዎች፣ በጣም በርካታና አሻሚነት የሚታይባቸው እንደሆኑ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ Morris (1992)፣ የሥርዓትን፣ ምንነት ሁሉም ሰው እያወቀው፣ አንድም ሰው ሊበይነው ከማይችላቸው ቃላት ውስጥ አንዱ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ (Ritual is one of those words where we all know what it means but no one can define it). በቃሉ አጠቃቀምና በክወናዎቹ አረዳድ ዙሪያ ሰፊ ልዩነቶች መኖራቸውን ደግሞ Leachን (1968) በመጥቀስ Roth (1995፣301) ያስረዳሉ፡፡ በጽንሰ ሀሳቡ ምንነትና በክወናዎቹ ዙሪያ ለሚታዩት ልዩነቶች፣ የጽንሰ ሀሳቡ ሰፊ ክስተቶችን ለመመርመር መዋል፣ (ከሽግግር ሥርዓቶች እስከቡድናዊ የገጽ ለገጽ መስተጋብሮች የሚታዩ ‹‹ህግጋትና ደንቦች››)፣ አስተዋጽኦ

ሳያደርግ እንዳልቀረ Roth (1995) በተዘዋዋሪ መንገድ ይጠቁማሉ፡፡ ክብደት የሚሰጣቸውና የሚሸፍናቸው ሰፊ ጉዳዮች፣ የሥርዓት ጽንሰ ሀሳብ እንዲዋዥቅ፣ እንዲሸራረፍና፣ በሂደትም እንዲያፈነግጥ አድርገውታል፡፡

የሆነ ሆኖ ግን፣ ሥርዓት፣ በድርጊት የተሞላና ማን ምን ማድረግ እንዳለበት በቡድናዊ ሥምምነት በሚወሰን ዘልማዳዊ ደንብ የሚገዛ፣ ተደጋጋሚነትና ትእምርታዊነት ያለው፣ ቡድናዊ ክበራ በመሆኑ ዙሪያ፣ ብዙዎቹ የዘርፉ ተመራማሪዎች ይስማማሉ፡፡

Myerhoffን (1977) ዋቢ በማድረግ Sims እና Stephens (2005፣95) እንደሚያስረዱት፣ ሥርዓቶች፣ በቅደም ተከተል የተደራጁና ዘወትር ትዕምርቶችን፣ ድርጊቶችን፣ ድግግሞሾችን ያካተቱና ምናልባትም ሥርዓቶች መሆናቸውን ለመገንዘብ የሚያስችሉ፣ መቼ እንደሚጀምሩና እንደሚጨርሱ የሚያመለክት ድንበር ያላቸው ክወናዎች ናቸው፡፡

ስለሥርዓት ምንነትሲነሳ፣ እነደነDurkheim (1912)፣ Turner (1967) እና ተከታዮቻቸው ከትዕምርታዊነቱ ይልቅ ተግባራዊነቱ ላይ ትኩረት የሚሰጡ ተመራማሪዎች እንዳሉ Marshall (2002)፣ ያስረዳሉ፡፡ ማርሻል፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ፣ አብዛኞቹ ተመራማሪዎች ስለሥርዓቶች ሲያስቡ፣ ከትዕምርታዊ ይዘታቸው ላይ አትኩረው፣ ሥርዓት፤ ሀሳብ ትዕምርታዊ በሆነ መንገድ የሚገለጽበት፣ የሚተላለፍበትና የሚጠናከርበት አንድ ተጨማሪ መንገድ መሆኑን በማሳየት ላይ እንዳተኮሩ ጠቁመው፣ እንዲህ አይነቱ አንጻር እነዚህ የተለዩ መልዕክቶች በእንዲህ አይነት የተለየ ሁኔታ ለምን እንደተገለጹ እንደማያብራሩ ያስረዳሉ፡፡ ‹‹ሥርዓት በዋናነት የመልዕክት ማስተላለፊያ መንገድ እስከሆነ ድረስ፣ ተሳታፊዎች ለሚያስተላልፉት መልዕክት እንግዳና ባይተዋር የሚሆኑት እንዴት ነው;›› በማለትም አንጻሩን ይሞግታሉ፡፡ የሥርዓትን መንገድ ለሁሉም የጋራና (most universal)፣ ጉልህ ከሆነው፣ ከክንውን ገጽታው መነሳት ጠቃሚ እንደሆነም ያስረዳሉ፡፡

Staalም (1979፣4)፣ ሥርዓት በዋናነት ክንውን መሆኑንና ክንውኑም ግልጽ በሆኑ ደንቦች መገዛቱን ጠቁመው፣ ጠቃሚው ጉዳይ የሚደረገው ነገር እንጂ፣ የሚታሰበው፣ የሚታመንበት ወይም የሚባለው እንዳልሆነ በመግለጽ የ Marshallን ሀሳብ ይጋራሉ፡፡

በSims እና Stephens (2005፣፣94)፣ የቀረበው የሥርዓት ምንነት ገለጻ፣ ከፍ ሲል ሥርዓትን ከክወናዊነቱ ወይም ከትዕምርታዊነቱ ላይ ብቻ በማተኮር ለመበየን የሞከሩትን ተመራማሪዎች ለማስታረቅ የሚሞክር ይመስላል፡፡ Stephens እና Sims፣ ስርዓት ለአንዳች ዓላማ ለምሳሌ ከአንድ ማሕበራዊ ደረጃ ወደሌላ ለሚደረግ ሽግግር፣ ከመሰረታዊ የሕይወት ምዕራፎች ወይም የቡድን ልምዶች መግባትን ወይም መውጣትን ለማስረገጥ የሚከወን እንደሆነ ያስገነዝባሉ፡፡ ልደት ለመግባት፣ ሞት ለመውጣት ጥሩ ምሳሌዎች ሲሆኑ እንደሚችሉም ይጠቁማሉ፡፡ በእነዚህ ሽግግሮች የሚተገበሩት ሥርዓቶች፣ በልማድ፣ በድርጊትና በሚስጥር የተሞሉ ሲሆኑ፣ በሥርዓቶች ከበራ ላይ የከዋኞቹ ልማዶች፣ እምነቶችና እሴቶች ተጨባጭና ክሱት በሆነ መንገድ ለቡድኑ አባላትም ሆነ ከቡድኑ ውጭ ላሉት የሚቀርቡባቸው እንደሆኑም ያስገነዝባሉ፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረቡት ሀሳቦች ለመረዳት እንደሚቻለው፣ ሥርዓት፣ በትዕምርቶች፣ በክንውኖች፣ በቅደም ተከተል በሚቀርቡ ድርጊቶች ተገንብተው፣ በቡድን ዘልማዳዊ ደንብ እየተመሩ በተደጋጋሚ በሚከወኑ ልማዶች ላይ ለተመሰረቱ፣ ለከዋኞቻቸው ቡድን አንዳች ማሕበራዊ ፋይዳ ላላቸው ከበራዎች፣ የሚሰጥ መጠሪያ ነው፡፡ ቀጥሎ ከሞት ጋር የተያያዙ ጽንሰ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

2.1.2. ከሞት ጋር የተያያዙ ጽንሰ ሀሳቦች

*ሀ. የሞት ምንነት*

ሞት ሕይወት ላለው ፍጡር ሁሉ የማይቀር የጋራ ተፈጥሯዊ እጣ ፈንታ ነው፡፡ Cederroth (1988፣39)፣ #ሕይወት በእንቆቅልሽ የተሞላች ብትሆንም አንድ ነገር ግን በእርግጠኝነት እናውቃለን፡፡ እኛ ዘላለማዊ አይደለንም፤ ይፍጠንም ይዘግይ ሁላችንም እንሞታለን፡፡$ በማለት የገለጹት ለዚህ ጥሩ ማስረጃ ይሆናል፡፡ ሞት ሕይወት ላላቸው ሁሉ የማይቀር ቢሆንም ስለ ምንነቱ ያለው አመለካከትና ብያኔ፣ እንደጋራ እጣ ፈንታነቱ በሁሉም ማሕበረሰብ ዘንድ ተመሳሳይ ሆኖ አይገኝም፡፡

ለሞት የተለያየ አመለካከትና ብያኔ እንዲኖር ከሚያደርጉት ውስጥ፣ ማህበራዊ ቡድን ወይም ሙያ ይገኝበታል፡፡ Petrieን (ጊዜው አልተጠቀሰም) ዋቢ በማድረግ Vernon (1970፣38) እንደሚያስገነዝቡት፣ በዋስትና ኩባንያዎች የሚሰጠው የሞት ብያኔ፣ በሀይማኖት ቡድኖች

ከሚሰጠው ፍጹም የተለየ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት ይመስላል ሞት፣ እንደቅጣት ፣ እንደየክብር ሽልማት፣ እንደማምለጫ፣ እንደመዝናኛ፣ እንደማህበራዊ ክብር ማጠናከሪያ፣ እንደማሕበረሰብ መቆጣጠሪያ፣ እንደኪነጥበብ ርዕሰ ጉዳይ እና እንደአፍቃሪ እየታየ የተሰጡ ብያኔዎች ይገኛሉ፡፡

የሞት ብያኔ ከባህል ባህልና ከሙያ ሙያ የተለያየ ከሆነ፣ ለሁሉም የሚሰራ አንድ ወጥ ብያኔ ለመስጠት የሚቻል አይመስልም፡፡ Bloch (1988፣15)፣ አንድ ማሕበረሰብ ስለሞትና ሕይወት የሚኖረው እምነት ከሌላው ማህበረሰብ የተለየ ስለሆነ፣ አንድ ማጠቃለያ ላይ ለመድረስ መሞከር እንደማይገባ መምከራቸው ከዚህ የመነጨ ይመስላል፡፡

Gorerን (1965) ዋቢ በማድረግ Vernon (1970፣131) እንደሚያስረዱት፣ ለሞት የሚሰጠው ብያኔ ከባህልና ሙያ በተጨማሪ፣ በሞት አይነቱ፣ በሳይንሳዊና ሀይማኖታዊ እይታ ምክንያትም ይለያያል፡፡ እውነተኛ ሳይንቲስት በሞት እንደማያምንና በሳይንስ ሞት ከውቅያኖስ አድማስ ማዶ የምትቀዝፍን መርከብ እንደሚመስል ይገልጻሉ፡፡ ከአድማስ ማዶ የተሰወረች መርከብ አትታይ እንጂ እየቀዘፈች መንዟን ትቀጥላለች፡፡ ይህም ልክ እንደነፍስ ከስጋ ተለይታ መጓዝ ነው፡፡

Bloch (1988፣12)፣ በአንዳንድ ባህሎች ሞትና ሕይወት እንደጉዞ እንደሚታዩ ያስገነዝባሉ፡፡ ይህም የሞት ጉዞ ከህይወት ጉዞ የሚቀጥል ተደርጎ እንዲታይ እንዳደረገው ገልጸው፣ ሞት የምንለው ነገር ከኒላ ጀምሮ ወደፊት የሚጓዝ የረጅም ትረካ አንድ ገጠመኝ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ Stuart እና Jun (1992፣68)፣ ቻይና ውስጥ የሚገኙ የምንሂ ቱ (Minhe Tu) ማሕበረሰቦች፣ ሞትን እንደመጨረሻ ሳይሆን ከዝንት ዓለም የሕይወት ዑደት፣ እንደያንድ ጎማ እሽክርክሪት፣ የአንድ ዙር መጨረሻ አድርገው እንደሚመለከቱት ይገልጻሉ፡፡

የሞትን ምንነት በወጥነት ለመበየን በሕይወትና ሞት መካከል ያለውን ድንበር በትክክል መለየትን እንደሚጠይቅ Vernon (1970፣50) ገልጸው፣ ከዚህ አኳያ ሞትን፣ ጣረሞት (denouement death)፣ ትኩስ ሬሳ (threshold death) እና በድን (integration death) በማለት በሶስት ደረጃዎች ከፍለው ተመልከተውታል፡፡ ጣረሞትን እንደየሕይወት የመጨረሻ ምዕራፍ፣ ትኩስ

ሬሳን እንደሞት የመጀመሪያ ምዕራፍና፣ የሁሉንም አካል ክፍሎች የተቀናጀ ሥራ ማቆምን፣ እንደሞት የመጨረሻ ምዕራፍ ወስደዋቸዋል።

እንደVernon የሞትና ሕይወትን ድንበር መለያ መስፈርት ካወጡት ውስጥ፣ Luper (2009፣50) ይገኙበታል። Luper፣ አንድ ሀኪም አንድን ሰው ሞቷል ለማለት የሚያስችሉት ሁለት መስፈርቶች እንዳሉ ይገልጻሉ። የመጀመሪያው በጤና ባለሙያዎች በክሊኒክ ውስጥ የሚረጋገጥ ሞት (Clinical Death) ሲሆን፣ ሳንባ የመተንፈስ፣ ልብ ደም የመርጨት ተግባራቸውን ሲያቆሙ የሚሰጥ ነው። Rodabough (2003፣284) እና Byrant (2003)፣ ይህ መስፈርት ለረዥም ዘመናት የተሰራበትና በጣም የተሻለው የሞትንና ሕይወትን ድንበር ጠቋሚ እንደሆነም ያስገነዝባሉ። ሁለተኛው የሞት መስፈርት የአዕምሮ ሞት ሲሆን፣ ይህ የሞት አይነት የአዕምሮ ዋና ክፍል ሊመለስ በማይችልበት ደረጃ ስራውን ሲያቆም የሚከሰት መሆኑንና፣ አንድ ሰው ‹‹ሞቷል›› ሲባል የሚችለውም፣ አዕምሮው ሲሞት መሆኑን ያስረዳሉ።

Pojmanም (1992፣158)፣ የአንድን ሰው ሞት ለመወሰን ቀደም ሲልና አሁን በሚሰጡት የሞት ብያኔዎች መካከል ልዩነቶች የሚታዩ መሆናቸውን በመግለጽ፣ የLuperን ሀሳብ ይጋራሉ። እስከሀያኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ድረስ፣ አንድ ሰው ሞቷል ተብሎ የሚወሰነው፣ የልብ ትርታው ሲቆምና እስትንፋሱ ሲቆረጥ እንደነበርና፣ ባለንበት ክፍለ ዘመን ግን የሕክምና ቴክኖሎጂ ማደግ አካልን ላልተወሰነ ጊዜ ማቆየት በማስቻሉና የሞተን ሰው የአካል ክፍል ወደጤነኛ ሰው ማዛወር በመጀመሩ፣ ለሞት እነዚህን አዳዲስ ክስተቶች የሚያንጸባርቅ ብያኔ ለመስጠት ሁኔታዎች እንዳስገደዱ ያስገነዝባሉ።

Pojman (1992፣164) አክለው እንደሚያብራሩት፣ በአሜሪካ ፕሬዘደንት የተሰየመው "Commission for the Study of Ethical Problems in Medicine and Biomedical and Behavioral Research" የተሰኘ ኮሚሽን፣ ከ1981 ዓ.ም በኋላ ለሞት ወጥ ብያኔ በሰጠባቸው አንቀጾች ፣‹‹አንድ ሰው ሊመለስ የማይችል የደም ዝውውርና የእስትንፋስ መቆም ችግር ካጋጠመው ወይም አዕእምሮው ሁሉንም ተግባሩን ካቆመ፣ ሞቷል ይባላል።›› በማለት ደንግጓል። Fineን (2005) ዋቢ በማድረግ Luper (2009፣51-52) እንደሚገልጹት፣ በአሜሪካ ሀምሳዎቹም ግዛቶች ሰዎች ሞተዋል የሚባሉት አዕምሮ ሙሉ በሙሉ ተግባሩን ሲያቆም ነው። በእንግሊዝም አንድ ሰው ሞተ የሚባለው፣ አዕምሮ ሊመለስ በማይችልበት ደረጃ ስራውን ሲያቆም ነው። ከዚህም በተጨማሪ በአሁኑ ወቅት በአሜሪካና በእንግሊዝ ለሞት የሚሰጠው ተቀባይነት ያለው

መስፈርት፣ በVernon (integration death) የተባለው በድንነት ደረጃ የደረሰውን የሚመለከት ነው።

ሳይንሳዊውና ዓለማቀፋዊው የሞት ብያኔ ይህን ቢመስልም፣ በኢትዮጵያ አንድ ሰው ሞተ የሚባለው ምዕራባውያን ከሀያኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በፊት ሲጠቀሙበት በነበረው መስፈርት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። ለምሳሌ ደስታ እ.ኢ.አ. (1962፣755) ሞተ፣ የሚለውን «ነፍሱ ከስጋው ወጣች፣ ተለየች፣ ተገደለ፣ ደበነ፣ አለቀ፣ ተጠነገደ፣ አለፈ፣ አረፈ፣ ተለየ»፣ በማለት ይፈቱታል። ስለዚህ በተጠኘው ማሕበረሰብ ዓለማዊ እይታ ከሕይወት ወደሞት የሚደረገው ሽግግር፣ በነፍስ ከስጋ መለየት ሲገለጥ፣ የመጀመሪያ መከሰቻው ደግሞ፣ የእስትንፋስ መቆም ነው። ስለሆነም፣ ሞትን በማይመለስ ደረጃ የእስትንፋስ መቆም የሚገለጥ፣ የነፍስ ከስጋ መለየት፣ ብሎ መበየን ይቻላል። በሀይማኖታዊው ደግሞ ከመረጃ አቀባዮቹ መካከል ቀኝ ጌታ ዜናዊ እ.ኢ.አ. (አባ.2፣ ቁ.1፣ ክፍ.ለ፣ አን.1-13) ሞትን ‹‹መለየት›› በማለት በይነውታል። መለየቱ በነፍስና ሥጋ እንዲሁም በነፍስና እግዚአብሔር መካከል መሆኑንም ያስረዳሉ። በመጀመሪያው መለየት፣ ነፍስ ወደፈጣሪ በመሄድ ከሥጋ፣ በሁለተኛው ወደገሀነም በመሄድ ከእግዚአብሔር እንደምትለይ ይገልጻሉ። መሪጌታ ክፍለማርያም (አባ.2.፣ ቁ.2፣ ክፍ.ለ፣ አን.1-3) በዚህ ሀሳብ ቢስማሙም ‹‹ሞት ማለት ረፍት›› ማለት እንደሆነም ይገልጻሉ። ቀጥሎ በቀረበው የሞት አይነት በተገለጸበት ክፍል፣ የሞትን ምንነት የሚያሳዩ ተጨማሪ ማብራሪያዎች ተሰጥተዋል።

## ለ. የሞት አይነቶች

የተለያዩ የሞት አይነቶች እንዳሉ መረጃዎች ያመለክታሉ። ለምሳሌ Vernon (1970፣83)፣ ከፍተኛና ዝቅተኛ ክብር የሚሰጣቸው ስላሉ፣ ሁሉም አይነት ሞት በተመሳሳይ መንገድ እንደማይታይ ይገልጻሉ። ከአሟሟት ሁኔታና ከእምነት ጋር በተያያዘ ደግሞ፣ የሚከተሉት የሞት አይነቶች እንዳሉ መረጃዎች ያሳያሉ።

በመጽሀፍ ቅዱስ ሦስት አይነት ሞቶች (ሞተ ሥጋ፣ ሞተ ሕሊናና ሞተ ነፍስ) እንዳሉ ተጠቅሷል። ሞተ ስጋ ቀላል ተደርጎ የሚታየውና ለሁሉም የሰው ልጅ የወል እጣ የሆነው የነፍስ ከሥጋ መለየት ነው። እንዲህ አይነቱ ሞት፣ ተራና እንደእንቅልፍ የሚቆጠር መሆኑም

በተደጋጋሚ ተገልጾ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ ኢየሱስ ክርስቶስ የኢያኢሮስ ልጅ ሞታ ዘመዶቿ ሲያለቅሱ ደርሶ፣ ‹‹አታልቅሱ ተኝታለች እንጂ አልሞተችም›› ካላቸው በኋላ፣ የልጅቱን እጅ ይዞ፣ ‹‹አንቺ ልጅ ተነሺ›› ሲላት ነፍሷ ወደሥጋዋ እንደተመለሰች ተገልጿል (ማቴ.9፤ ማር.5፤ ሉቃ.8)፡፡ እንደአባ መልከ ጼዴቅ (1984፣80) ገለጻ ደግሞ፣ በምድራዊ ሕይወታቸው ክርስቶስ በሰራው ሥርዓት ጸንተው የኖሩ ቅዱሳን በአካል ሲሞቱ፣ ‹‹ሞቱ›› ሳይሆን፣ ‹‹ከዚህ የስቃይ ዓለም ከጻዕሩ፣ ከድካሙ አረፉ፤ ወደሌላኛው ዓለም ተዛወሩ›› ይባላል፡፡ በዚያም ሆነ በዚህ፣ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት፣ አካላዊ ሞት እንደእንቅልፍ ቀላልና ረፍት ተደርጎ ይታያል፡፡

በዚህ እምነት ከባዱና እጅግ አስፈሪው ሞተ ነፍስ ወይም ‹‹የዘላለም ሞት››፣ ተብሎ የሚጠራው ሲሆን፣ ይህም ነፍስ ከእግዚአብሔር ስትለይ የሚከሰት ነው ይባላል (ራዕ.2፣ 11፤20፣ 6፣14፤ 21፣8)፡፡ አባ መልከ ጼዴቅ (1984፣80)፣ ይህንን ሞት የሚሞቱ ሰዎች ከቤተክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ውጭ ሆነው ፈቃደ ስጋቸውን ሲከተሉ የኖሩት እንደሆኑና፣ እንደማንኛውም ሰው ከዚህ ዓለም በመጀመሪያው ሞት ከተለዩ በኋላ፣ በትንሳዔ ሙታን ጊዜ ተፈርዶባቸው ወደሲኦል ሲወርዱ ዘላለማዊ ሞት እንደሚሞቱ ይገልጻሉ፡፡ መላከ ሰላም ዳኛቸውና ሌሎችም (1986፣11-12)፣ ከላይ ከተገለጹት የሥጋና የነፍስ ሞቶች ሌላ፣ ከሰው ሥነምግባር ጋር በተያያዘ የሚሰጡ የሞት አይነቶች እንዳሉ ይገልጻሉ፡፡ ከመልካም ሥራ ርቀው የሀጢያትን መንገድ የሚከተሉ በሕይወት እያሉ ‹‹ሙታነ ሕሊና›› እንደሚባሉና፣ እግዚአብሔርን ለማገልገል ከዓለም ሥራ የተለዩትም በዓለም ዘንድ የሞቱ ተደርገው እንደሚቆጠሩ ያስረዳሉ፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሱት በተለየ፣ በዓለማዊውም፣ ሥነሕይወታዊና (Biological death)፣ የቁም (Social death) የሚባሉ ሁለት አይነት ሞቶች እንዳሉ፣ Shneidmanን (1963a) ዋቢ አድርገው Vernon (1970፣50) ይገልጻሉ፡፡ ሥነሕይወታዊ ሞት የሚከሰተው የአካል ክፍሎች ስራቸውን ሲያቆሙ ሲሆን፣ ምልክቱም የእስትንፋስ መቆም ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የቁም ሞት ደግሞ፣ ግለሰቡ በራሱ እንደሞተ ሲያስብ ወይም ሌሎች ሙቷል ብለው ሲያምኑ እንደሚከሰት፣ Vernon (1970፣50) ያስረዳሉ፡፡ አንድ ሰው የሚኖርበትን ማህበረሰብ ማህበራዊ ደንብ ማክበር ተስኖት ከቡድኑ ሲገለል፣ ከሰዎች ጋር ግንኙነት መፍጠር ሲሳነውና፣ በራሱ ዓለም መኖር ሲጀምር፣ ‹‹የቁም ሞት ሞተ›› ይባላል፡፡

Westphalን (1984) በመጥቀስ ቴዎድሮስም እ.ኢ.አ. (2001፤153-155)፣ ሞትን ‹‹ሕይወት ባላቸው ሁሉም ፍጡራን ላይ የሚከሰትና፣ በስነምግባርና በስነልቡና ችግሮች ምክንያት በሚኖሩበት ማህበር የሚጠበቅባቸውን ለመወጣት ባልተሳካላቸው ሰዎች ላይ ብቻ የሚከሰት›› በማለት በሁለት ይከፍሉታል፡፡ የተገለጸበት መንገድ ከመለየቱ በስተቀር፣ የቴዎድሮስ የሞት ምደባ፣ ከፍ ብሎ ከተገለጹት ከሥነሕይወታዊና የቁም (ሕሊናዊ) ሞቶች ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ van Gennepን (1909) ዋቢ በማድረግ Roth (1995፤8) እንደሚያስገነዝቡት፣ ሥነሕይወታዊ ሞት በአንድ ሰው ላይ የሚከሰተው አንዴ ሲሆን፣ የቁም ሞት ግን ግለሰቡ ካንዱ ማሕበራዊ ደረጃ ወደ ሌላው ሲሸጋገር በተደጋጋሚ ይከሰታል፡፡

የአሟሟት ሁኔታን መሰረት በማድረግ የሞትን አይነት የፈረጁ ተመራማሪዎች ደግሞ፣ በሁለትና በሶስት ሲከፍሉት ይስተዋላሉ፡፡ ለምሳሌ Ogede (1995፤80) በናይጀርያዎቹ ኢግዱ ማሕበረሰቦች ላይ፣ Brookman-Amissah (1986፤78) በጋናዎቹ አካን ማህበረሰቦችና Gufler (2000፤350)፣ በካሜሩኖቹ የያምባ ማህበረሰቦች ላይ ባካሄዷቸው ጥናቶች እንዳረጋገጡት፣ ሦስቱም ማሕበረሰቦች ሞትን፣ ‹‹ጥሩ ሞት›› (good death) እና ‹‹መጥፎ ሞት›› (bad death) በማለት በሁለት ይከፍሉታል፡፡ ጥሩ የሚባለው ሞት፣ በህመምና በእርጅና ምክንያት የሚመጣ ተፈጥሯዊ ሞት ሲሆን፣ መጥፎ የሚባለው ደግሞ፣ እንደሳንባ ነቀርሳ፣ ሥጋ ደዌና የሚጥል በሽታ፣ በአጠቃላይ በማሕበረሰቡ መልካም በማይባሉ ምክንያቶች በሚመጡ በሽታዎችና በአደጋ፣ በብጥብጥ፣ ራስን በማጥፋት የሚከሰት ነው፡፡

መስፈርታቸው እንደላይኞቹ ተመራማሪዎች የአሟሟት ሁኔታ ቢሆንም፣ የሞት አይነቶችን ‹‹ጥሩ ሞት፣ መጥፎ ሞትና ድንገተኛ ሞት›› (sudden death) በማለት በሶስት የሚከፍሏቸው ደግሞ፣ Ca´tedra (2008፤77-78) ናቸው፡፡ ጥሩና መጥፎ የሚሉትን የሞት አይነቶች በስም ከላይኞቹ ተመራማሪዎች ጋር ቢጋሩም፣ በግብር የእርሳቸው ለየት እንደሚሉ ከመግለጫዎቻቸው ለመረዳት ይቻላል፡፡ በOgede፣ Brookman-Amissahና Gufler፣ የጥሩና መጥፎ ሞት መለኪያው የማሕበረሰብን ሥነምግባር በመጠበቅና ባለመጠበቅ ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ በካቴድራ ግን የሕመምተኛውን ስቃይ መነሻ ማድረጉን የሚያሳዩ መረጃዎች አሉ፡፡ በካቴድራ ጥሩ የሚባለው ሞት፣ ፈጣን፣ ሕመም የሌለበትና ሟች መሞቱን ሳያውቅ እንቅልፍ

እንደተኛ የሚሞትበት ነው። በእርጅና ምክንያት በተፈጥሯዊ መንገድ የሚመጣና፣ በልብ ድካም የሚከሰት ሞት፣ ለዚህ የሞት አይነት ጥሩ ምሳሌዎች እንደሆኑ ይጠቀሳሉ። መጥፎ የሚባለው ሞት ደግሞ፣ ለቀናት፣ ለሳምንታት፣ ለወራት ምናልባትም ለዓመታት በዘለቀ ጣር ያለበት ህመም የሚደመደም የሞት አይነት ነው። በማይድን በሽታ የአልጋ ቁራኛ ሆነው በህመም የሚሰቃዩና፣ ሞታቸውን የሚናፍቁ ታማሚዎች የሚሞቱት ሞት ሲሆን፣ ካንሰር ለዚህ የሞት አይነት ጥሩ ምሳሌ ተደርጎ ተወስዷል። ሶስተኛው የሞት አይነት፣ የተፈጥሯዊ ሞት ተቃራኒ የሆነው አሰቃቂ ሞት (tragic death)፣ የሚባለው ሲሆን፣ በውጫዊ ሀይል ወይም አደጋ የሚደርስ ድንገተኛ የሞት አይነት ነው። በተፈጥሮ አደጋዎች፣ በዘመናዊ መጓጓዣ የሚደርሱ አደጋዎች፣ በሰው እጅ መሞትና ራስን ማጥፋት፣ ለዚህ የሞት አይነት ማሳያዎች እንደሚሆኑ ተገልጿል።

በአጠቃላይ፣ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የሞት አይነቶች፣ ለሟች በሚፈጸመው የቀብር ሥርዓትና በሀዘን አገላለጽ ልማዱ ላይ የሚፈጥሩት አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖራል። ለምሳሌ አሉታዊውን ብንመለከት፣ በGufler (2000፣350) እንደተጠቀሰው፣ የያምባ ማሕበረሰብ አባላት በመጥፎ ሞት ስር ከተጠቀሱት ምክንያቶች በአንዱ ለሞተ ሰው፣ የለቅሶ ሥርዓት አያካሂዱም። ቀብሩ የሚፈጸመውም ጫካ ውስጥ በባለሙያ ነው። በሌላ በኩል በድንገተኛ አደጋና በሰው እጅ ለተገደለ ሰው የሚካሄደው የሀዘን አገላለጽ፣ በተፈጥሯዊ ሞት ከሚሞቱት የበለጠ መሪር እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። የተለያዩ ማሕበረሰቦች ከፍ ሲል እንደተገለጸው ለሞት አይነቶቹ ብቻ ሳይሆን ቀጥሎ እንደቀረበው ለሞት መከሰቻ ምክንያቶቹም ያሏቸው አመለካከቶች የተለያዩ ናቸው።

### ሐ. የሞት መከሰቻ ምክንያቶች

ማሕበረሰቦች ለሞት መንስኤዎች የሚሰጧቸው ምክንያቶች፣ እንደየባህሎቻቸውና እምነቶቻቸው ይለያያሉ። የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ በአፍሪካ በሚገኙ ልዩ ልዩ ማሕበረሰቦች፣ ለሞት መከሰት መንስኤ ናቸው ተብለው የሚታመንባቸው የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም፣ ቀደም ሲል የሞቱ አያት ቅድመ አያቶች መንፈስ ቁጣ፣ ዋናው ነው ተብሎ ይታመናል። ለምሳሌ Williamsን (1949) ዋቢ በማድረግ Alembi (2002፣118) እንደሚያስረዱት፣ በኡጋንዳ አያት

ቅድመ አያቶቻቸውን ከሞቱ በኂላ መናፍስት ሆነው ይኖራሉ ብለው ስለሚያስቡ፣ መጥፎም ሆነ መልካም ነገር የሚላከው ከእነዚህ መናፍስት እንደሆነ በጽኑ ያምናሉ። መናፍስቱ መጥፎ ነገሮችን በሕያዋን ትውልዶቻቸው ላይ የሚልኩት፣ ለእነሱ የሚገባቸውን ክብር ሳይሰጧቸው ሲቀሩ ወይም በማሕበራዊ ደንባቸው የተከለከሉ ተግባራትን ሰርተው ሲገኙ ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታ Brookman-Amissah (1986፣78) እንደሚገልጹት፣ በአካን ማሕበረሰብም፣ የአያት ቅድመ አያቶቻቸው የቀብር ስርዓት በሚገባ አለመከናወን የሚፈጥረው ቁጣ፣ በትውልዳቸው ላይ አደጋ እንዲያደርሱ ያነሳሳቸዋል ተብሎ ስለሚታመን፣ እንደአንድ የሞት መንስኤ ይወሰዳል። ከዚህም በተጨማሪ፣ በመተተኞች የሚላክ መቅሰፍት፣ ሕመምና አደጋ፣ የሞት መንስኤዎች ተደርገው ይወሰዳሉ።

Gufler (2000፣349) እንደሚያስረዱት፣ የካሜሩናዊቱ ያምባ ማህበረሰቦች ደግሞ፣ ሞትንና ከባድ ሕመምን በተፈጥሯዊ መንገድ የሚመጡ አድርገው አይመለከቷቸውም። ከዚህ ይልቅ ሞትም ሆነ ከባድ ህመም በረቂቅ ወይም ከሰው በላይ በሆኑ ወኪሎች የሚመጡ እንደሆኑ ያምናሉ። አንድ ሰው የሞተበት ምክንያት ካልታወቀ፣ ሌላ ሞት ሊከሰት ይችላል የሚል ፍራቻ ስላላቸውም፣ ሌላ ሞት እንዳይከሰት ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ ያ ሰው የሞተበትን መንስኤ ያጣራሉ።

በአጠቃላይ በአፍሪካ በበርካታ ማህበረሰቦች ለሟች ተገቢውን የቀብር ሥርዓት አለማከናወን ወይም ከማህበረሰቡ ደንብ ውጭ የሆኑ ተግባራትን መፈጸም፣ የሙት መንፈሶችን ስለሚያስቀይም ሞት ይከሰታል ብለው ያምናሉ። ሞት እንዳይከሰትም የሙት መናፍስትን ላለማስቀየምና ማህበራዊ ደንቡን ላለመጣስ ይጠነቀቃሉ። በኦርቶዶክስ እምነት መሰረት ደግሞ፣ የሰው ልጅ ሀጢያት በመስራቱ እግዚአብሔር ተቆጥቶ ሞተ ሥጋና ሞተ ነፍስ እንደፈረደበት ተገልጿል። እንደመላከ ሰላም ዳኛቸውና ሌሎችም (1986፣9) ገለጻ፣ ሞተ ሥጋንም ሆነ ሞተ ነፍስን፣ ሰው የእግዚአብሔርን ሕግ በማፍረሱ ራሱ ጎትቶ ያመጣቸው ጣጣዎች እንጂ፣ እግዚአብሔር የባህሪው አድርጎ ለሰው የፈጠረበት አይደሉም።

የሞት መንስኤው ምንም ይሁን ምን፣ የተለያዩ ማሕበረሰቦች ለሞት የሚሰጡት አካላዊና ሕሊናዊ መልክ እንደየእምነታቸውና ባሕላቸው የተለያየ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። ቀጥሎ

በአፍሪካ የሚገኙ የተወሰኑ ማሕበረሰቦች፣ ሞትን እንዴት እንደሚስሉት የሚያሳዩ መረጃዎች ቀርበዋል፡፡

*መ. መልክአ ሞት*

ሰዎች ሞትን የሚመለከቱበት መንገድ የተለያየ ነው፡፡ የሟች ማህበራዊ ቦታ፣ እድሜ፣ የጤንነት ሁኔታ፣ ለሁሉም የማይቀር መሆኑና የሚከሰትበት ጊዜ፣ ለእነዚህ የተለያዩ አመለካከቶች በመነሻነት ያገለግላሉ ለማለት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ሙሉነህ እ.ኢ.አ. (1973፣1)፣ ሞትን እያንዳንዱ ሰው ከልምድና ገጠመኙ በመነሳት የተለያየ መልክ ሰጥቶ እንደሚስለው እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> የሞትን ምንነት የማያውቅ የለም፡፡ አንዱ ትልቅና ትንሽ፣ ሀብታምና ድሃ … ወዘተ. ብሎ ከማያዳላ፣ ይግባኝ ከሌለበት ፍርድ አስተካካይ ዳኛ ጋር ያነጻጽረዋል፣ ወይ አንድ አድርጎ ያመሳስለዋል፡፡ አንዱ ከስቃይ ከመከራ የሚገላግል፣ እፎይታን፣ ጥሩ እንቅልፍን የሚቸር መልዕክተኛ ሲያደርገው፣ ሌላው ከዝች ጣፋጭ ዓለም መንጥቆ የሚወስድ ጨካኝ አረመኔ ወይም በጨለማ ሹልክ ብሎ ማንም ሳያየው ሕይወትን የሚሰርቅ ሌባ ያደርገዋል፡፡ ምናልባትም ከምድራዊ ዓለም ወደ ሰማያዊ ዓለም መሸጋገሪያ ድልድይ አድርጎ የሚገልጸው ይኖራል፡፡ እንደየገጠመኙና እንደየስሜቱ ሌላም ሌላም ይለዋል፡፡

እንደሙሉነህ ሁሉ ንጉሴም እ.ኢ.አ. (1974፣ 53) ሞትን ሰዎች ከሚገኙበት ሁኔታ በመነሳት ደግ ወይም ጨካኝ አድርገው እንደሚስሉት ይገልጻሉ፡፡ በሰዎች ሳይሆን በራሳቸው ገጠመኝ ላይ ተመስርተው ሞትን በአባትና ልጅ ፍቅር መካከል የሚገባ አረመኔ አድርገው ጌጡ እ.ኢ.አ. (1989)፣ የተመለከቱበት ገለጻ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ይሆናል፡፡ ጌጡ በጥናታቸው የአበርክቶ ክፍል ‹‹ ‹በጣም በጣም እወድሃለሁ› እያለች ስታጫውተኝ ቆይታ ንግግሯን ሳልጠግበው በአረመኔው ሞት ለተቀጠፈችብኝ ህጻኗ ልጄ … መታሰቢያ ይሁንልኝ›› በማለት ሞትን ርህራሄ የለሽ ቀሳፊ አድርገው ስለውታል፡፡

ኬንያ ውስጥ የሚገኙ የአባንዮሌ ማሕበረሰቦችን የለቅሶ ቃል-ግጥሞች የመረመሩት Alembi (2002፣139-145)፣ ማህበረሰቦቹ ሞትን ጨካኝ ፍጡር አድርገው እንደሚመለከቱት ያስረዳሉ፡፡

ናይጀርያ ውስጥ የሚገኙ የአካን ጎሳዎችን ስለሞት የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች የመረመሩት Brookman-Amissah (1986፣77) ደግሞ፣ ለአካኖች ሞት ተጨባጭና ሰዋዊ አካል ያለው ፍጡር ነው፡፡ የሞት ሰውኛ አካላዊ አሳሳልም፣ የዐይን ገበታዎቹ የጎደጎዱ፣ ማየት የተሳነው አጽምና፣ የሚሰማ ተደርጎ ቀርቧል፡፡ ምንም እንኳ ሞት ጆሮ ቢኖረውም፣ ለምህረት ተማጽኖ ቁብ የሌለው፣ በመጣ ጊዜ ‹‹አባታለም›› ወይም ‹‹እናታለም›› እያሉ ቢማጸኑት የማይምር፣ የማይደራደሩትና በቁልምጫ የማይደለል ተደርጎ ተስሏል፡፡ ይህ ጥናት በተካሄደበት አካባቢም፣ በለቅሶ ቃልግጥሞች ሞት በተለያየ መንገድ ሰውኛ ባህሪ እየተሰጠው ተገልጿል፡፡

ከዚህ በላይ ከሞት ምንነት፣ አይነቶቹ፣ የመከሰቻ ምክንያቶቹና፣ አዕምሯዊ ምስሉ ጋር የተያያዙ መረጃዎች ቀርበዋል፡፡ ቀጥሎ ደግሞ ከሞት መከሰት ጋር በተያያዘ፣ በማሕበረሰቦች የሚተገበሩ ልማዶችና ሥርዓቶች ተቃኝተዋል፡፡

## 2.1.3. ከሞት መከሰት ጋር ተያይዘው የሚፈጸሙ ልማዶች

ሞት ሲከሰት የሚፈጸሙትን ልማዶች እስከቀብርና ከቀብር በኋላ በሚሉት ጎራዎች ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ እስከቀብር ከሚፈጸሙት ውስጥ ሬሳ ማጠብ፣ መገነዝና የመቃብር አዘገጃጀት ዋና ዋናዎቹ ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡ በተለያዩ ማሕበረሰቦች ለምሳሌ በመኤን፣ በትግራይ፣ በአማራና በአባንዮሌ፣ በቀብር ሥርዓት ላይ የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚገልጹት፣ ከግንዘት በፊት ሬሳ የማጠብና በአዲስ ከጥጥ በተሰራ አቡጀዲ ወይም ሻሽ የመከፈን የጋራ ልማድ አለ፡፡ ልማዱ ለምን እንደሚፈጸም ግን ማብራሪያ አልተሰጠም፡፡

የሟችን ነፍስ ፈጣሪዋ እንዲምራት ወይም ሞት የፈጠረው ሀዘን ቀለል እንዲል፣ አስከሬን ወደቀብር ሲወሰድ በጉዞ ላይ የመጸለይ የጋራ ልማዶች መኖራቸውንም ከላይ የተቃኙት ጥናቶች ይገልጻሉ፡፡ እርድ ማከናወንም እንደዚሁ፡፡ Abbink (1990) እና Alembi (2002፣128-129) እርድ ለምን እንደሚፈጸምና ምን ትዕምርታዊ ትርጉም እንዳላው ሲያብራሩ በሌሎቹ ማብራሪያ አልተሰጠም፡፡

በመቃብር አዘገጃጀትና በሬሰ አቀባበር ከባሕል ባሕል ልዩነቶች መኖራቸውን ከእነዚሁ ጥናቶች ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለምሳሌ Gufler (2000፣356) ካሜሩን ውስጥ በሚኖሩ በታችኛው ያንባ

ማሕበረሰቦች፣ ሰዎችን በቡድን መቅበር ቀደም ባለው ጊዜ የተለመደ እንደነበር ሲገልጹ፣ በሌሎቹ በተናጠል ይቀበራል። በመዔን ሟች በሚኖርበት አካባቢ ሲቀበር በሌሎቹ በቤተ እምነቶች በተዘጋጀ የጋራ ቦታ ይቀበራል። ከሀይማኖት ጋር በተያያዘ በመኤን፣ በሀረር ሙስሊም ገበሬዎችና በሀረሪ ብሔረሰቦች ሬሳ ወደምዕራብ ዙሮ ሲቀበር፣ በትግራይና በሸዋ አማሮች ወደምስራቅ ዙሮ ይቀበራል። በያንባ ደግሞ ጾታን መሰረት በማድርግ ወንዶች ወደምሥራቅ ሴቶች ወደምዕራብ ዙረው ይቀበራሉ።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የቀረቡት ከሬሳ አዘገጃጀት፣ ከጉዞና ከአቀባበር ጋር ተያይዘው የሚፈጸሙ ልማዶች፣ የየራሳቸው ባህላዊና ሀይማኖታዊ ትርጉም እንዳላቸው ለመገንዘብ ተችሏል። እነዚህ ልማዶች የሚፈጸሙባቸው ምክንያቶች ጠቅለል ተደርገው ሲታዩም፣ ሟች በሚሄድበት ሌላ ዓለም መልካም ነገር እንዲያጋጥመው የማመቻቸት፣ የሟችን ቤተሰቦች ከሀዘናቸው የማጽናናት፣ በሞት ምክንያት የተናጋውን የማህበሩን ደህንነት የማረጋጋትና፣ በሟች ቤተሰቦችና ዘሮች ላይ የሟች ወይም ከእሱ ቀደም ሲል የሞቱት አያት ቅድመ አያቶቹ መናፍስት ተቀይመው ጥፋት እንዳያስከትሉ የመከላከል ሚና አላቸው ተብሎ በመታመኑ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል።

ከቀብር በኋላ ከሚካሄዱ ልማዶች፣ እጅን መታጠብና የእዝን እህል ውሃ ማቅረብ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከቀብር መልስ እጅን መታጠብ ከፍ ሲል በተቃኙት ጥናቶች የጋራ ልማድ መሆኑ ቢስተዋልም፣ ከAlembi ውጭ ልማዱ ለምን እንደሚፈጸም ያብራራ የለም። Alembi (2002)፣ በአባንዮሌ ማህበረሰብ በውሃ መታጠብ፣ ሁለት አይነት ትዕምርታዊ ፍቾች እንዳሉት ይገልጻሉ። ቀባሪዎቹ እጅና እግራቸውን የሚታጠቡት፣ ትኩስ የመቃብር አፈር ይዘው ወደቤታቸው ከተመለሱ፣ ሞትን ወደዚያ ቤት መጋበዝ ይሆናል ብለው ስለሚያምኑ ሲሆን፣ የሬሳውና የቀብሩ ታዳሚዎች መታጠብ ደግሞ፣ የአሮጌውን ሕይወት መጠናቀቅና የአዲሱን ሕይወት መጀመር አመልካች ተደርጎ እንደሚወሰድ ያስረዳሉ። ሬሳው ከሕያውነት ወደሙትነት፣ ሕያዋኑ ከሀዘንተኝነት ወደመረጋጋት ይሸጋገራሉ።

መላከ ሰላም ዳኛቸውና ሌሎችም (1986፣86)፣ በብሉይ ኪዳን ዘመንና በሀዲስ ኪዳን የሚደረጉት ከቀብር መልስ የእጅ መታጠብ ልማዶች፣ የተለያየ ትርጉም እንዳላቸው ያስረዳሉ።

በብሉይ ኪዳን ዘመን የሟችን አስከሬን ወይም መቃብር የሚነካ ሰው እንደርኩሰት ስለሚቆጠርበት፣ መታጠቡ ከዚያ ለመንጻት ታስቦ ይካሄድ እንደነበር ያስገነዝባሉ፡፡ በሀዲስ ኪዳን ግን፣ የክርስቲያኖች አካል በጥምቀተ ክርስትና የነጻ፣ በክርስቶስ ስጋና ደም የከበረ ስለሆነ፣ ከቀብር መልስ የሚደረገው መታጠብ በድን በመንካዝ፣ መቃብር በመቆፈር፣ አፈር በመመለስ፣ እንባ በማበስ፣ የቆሸሸ አካልን ንጽህና ለመጠበቅ ሲባል እንደሚደረግ ያስረዳሉ፡፡

ለቀስተኞቹ እጃቸውን እንደታጠቡ እዝን የመቅመስ የጋራ ልማዶች እንዳሉም መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ የእዝን እህል ውሃን ጠቃሚ የቀብር ሥርዓትነት ያጠኑት Yoder (1986፣149) በሲሎን ፣ ኢራን፣ ኢትዮጵያ፣ ናይጀርያ፣ ስዊድን፣ ፖላንድ፣ ሀንጋሪ፣ ሩማንያ፣ እንግሊዝና አሜሪካ ውስጥ የተለመደ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ምግቡ በጎረቤቶች፣ በጓደኞችና አልፎ አልፎ በሟች ቤተሰቦች እንደሚዘጋጅ ጠቁመው፣ አብዛኛውን ጊዜ የሚበላው በሟች ቤት እንደሆነና ከቀብር ወይም ከሬሳ ማቃጠል መልስ እንደሚቀርብም ይገልጻሉ፡፡ Yoder (1986፣149) van Gennepን ዋቢ በማድረግ እንደሚገልጹት፣ እዝን የመታቀፍ ሥርዓት አካል ሲሆን፣ ዓላማውም፣ የቡድኑን አባላት እርስ በርስና አንዳንዴም ከሟች ጋር ለማስተሳሰር፣ እንዲሁ ቀለበቱ በሞት የተቆረጠበትን ማሕበራዊ ሠንሰለት እንደገና ለማያያዝ እንደሆነ ያስገነዝባሉ፡፡ አይነቱ ይለያይ እንጅ በመኤን፣ በትግራይና በሸዋ ክርስቲያን አማራ ማህበረሰቦችም፣ ከቀብር መልስ እዝን የማቅረብ ልማድ እንዳለ በየማህበረሰቦቹ የለቅሶ ሥርዓት ላይ የተካሄዱት ጥናቶች ይገልጻሉ፡፡

እንዲህ አይነቶቹ ከቀብር በኋላ የሚከናወኑት ሥርዓቶች፣ በአብዛኛዎቹ የአፍሪካ ማህበረሰቦች ለሟች ብቻ ሳይሆን ለቋሚዎቹ ጭምር በማሰብ የሚፈጸሙ መሆናቸውን ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ ለምሳሌ Abbink፣ (1990) እንደሚገልጹት፣ ሟች በባህሉ መሰረት የሚያስፈልገው ተሟልቶለት ካልተሸኘ፣ ቀደም ሲል ከሞቱት የወዲያኛው ዓለም ነዋሪ ዘመዶቹ መቀላቀል ስለማይችል፣ ለብቀላ በአካባቢው በማድፈጥ ጥፋት ያስከትላል ተብሎ ይፈራል፡፡ እናም ሁሉም ነገር እንዳይጓደልበት ጥረት ይደረጋል፡፡ በክርስትና እምነት ግን ከቀብር በኋላ የሚከናወኑት ሥርዓቶች በአመዛኙ ለሟች ነፍስ ከፈጣሪ ምህረት መለመኛዎችና፣ ለራስም ክብር ማግኛዎች እንደሆኑ በፍትሃ ነገስት ተገልጿል፡፡

እስከቀብር ባለው ሥርዓት አልፎ አልፎ የሚከሰቱበት ሁኔታ ቢኖርም፣ በአብዛኛው ከቀብር በኋላ ከሚፈጸሙት ልማዶች ውስጥ የሀዘን አገላለጽ ልማድ አንዱ ነው፡፡ እያንዳንዱ ማህበረሰብ ሞት ሲከሰት ሀዘኑን የሚገልጽበት የየራሱ ልማድ እንዳለው ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ ልማዱ ሞት ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ በቀናትና በወራት ሊቋጭ ወይም ለዓመታት ሊቀጥል ይችላል፡፡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ የሀዘን አገላለጾቹ በአመዛኙ በአካል ላይ በሚወሰዱ እርምጃዎችና ከመደበኛው በሚለይ አለባበስ ይገለጻሉ፡፡

ለምሳሌ በትግራይና በሸዋ ክርስቲያን አማራ ማሕበረሰቦች፣ ሀዘንተኛ ሴቶች፣ የነጠላቸውን አንድ ጫፍ ከወገባቸው አስረው፣ ሌላውን ጫፍ ከአንገታቸው ላይ ዘቅዝቀው ያጣፉታል፣ ወይም ነጠላቸውን አጥፈው ጥለቱን ዘቅዝቀውም ይለብሱታል፡፡ ማቅ መልበስ፣ ልብስን በጥቁር ማቅለምና በተለይ በሸዋ፣ ደረትን ገልጦ፣ ቀሚስን ከወገብ በታች አሸርጦ መልበስ፣ የተለመደ እንደሆነም ይገልጻሉ፡፡

ሴቶች ብቻ ሳይሆኑ ወንዶችም ሀዘናቸውን የሚገልጹባቸው ልማዶች እንዳሏቸው እነዚሁ ጥናቶች ይገልጻሉ፡፡ በትግራይም ሆነ በሸዋ አማራ ማሕበረሰቦች፣ ወንዶችም እንደሴቶች ልብሳቸውን በጥቁር ቀለም አቅልመው ይለብሳሉ፡፡ በርኖስ ገልብጦ መልበስም ይታያል፡፡ ጸጉርን መላጨት፣ ጺምን ማሳደግ፣ ወለል ላይ መተኛት፣ ቅቤ አለመቀባት፣ ጌጣጌጥን አውልቆ ማስቀመጥ፣ ነጭ ክር ማሰርና ከዘፈን መራቅ፣ በሁለቱም ማሕበረሰቦች የሀዘን መግለጫ ልማዶች መሆናቸውንም ጥናቶቹ ያሳያሉ፡፡

እ.ኢ.አ. በ1925 በአፄ ኃይለሥላሴ በአዋጅ ከመከልከሉ በፊት፣ ሕዝቡ በአካል፣ በድርጊትና በስሜት፣ ይገለጽ የነበረውን የሀዘን ስርዓት፣ ማህተመ ሥላሴ እ.ኢ.አ. (1942፣587)፣ እንደሚከተለው አስፍረዋል፡፡

> አባት፣ እናት፣ ባል፣ ሚስት፣ ልጅ፣ ዘመድ፣ ወዳጅ፣ በሞቱ ጊዜ በተወላጆቹና በወገኖቹ ዘንድ ብርቱ ሐዘን ይደረጋል፡፡ ... መርዶውም እንደተሰማ ወዲያው በዝተት ደም እስኪወጣ ፊት ይነጫል፤ ጠጉር ይቆረጣል፣ ወይም ይላጫል፡፡ ሴቶች ክንብንባቸውን ተገልጠው ቀሚሳቸውን ይሰነጥቁና ከደረታቸው በታች አሸርጠው ምንም ትልቅ ወይዘሮ ቢሆኑ በርኖስ እንኳ ከትከሻቸው ሳያደርጉ አዕምሯቸው

እስኪጠፋ እየተንጠራሩ ዋይ ዋይ እያሉ ደረታቸውን እስኪቆስልና ደም እስኪመስል በመሪር ሀዘን እየመቱ ያለቅሳሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በተጠቀሱት ጥናት በተካሄደባቸው ማሕበረሰቦች፣ ሀዘኑ ትኩስ በሆነበት ወቅት፣ ደረት በመምታት፣ ፊትንና ጸጉርን በመንጨት፣ ደረትን በመድቃት፣ እየዘለሉ በመውደቅ፣ በአካል ላይ ጉዳት በማድረስ ሲገለጽ፣ ቆየት እያለ ሲሄድ ደግሞ፣ ውበት ሰጭ መዋቢያዎችን አስወግዶና ምቾትን ቀንሶ፣ አካልን በማጎሳቆል ሀዘንን የመግለጽ ልማድ ይታያል፡፡

በአመዛኙ በቀብር ሥርዓት አልፎ አልፎ በመታሰቢያና በሀዘን መግለጫ ልማዶች የለቅሶ ቃል-ግጥሞችን በተለያዩ መሳሪያዎች እያጀቡ ማቅረብም፣ በተለያዩ ማሕበረሰቦች የተለመደ ተግባር መሆኑን የጥናት ውጤቶች ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ Abbink (1990፣69) እንደሚገልጹት፣ በመኤን ማሕበረሰብ የለቅሶ ጭፈራ፣ ከበሮ ይመታል፤ ከእንጨት ወይም ከሚዳቆ ቀንድ የተሰራ ጥሩንባም ይነፋል፡፡ Falk (2003፣2) እንደሚገልጹትም በሽሞኝ (Hmong) ማሕበረሰብ ሞት ሲከሰት ኬይ (qeej) የተባለ የትንፋሽ መሳሪያ እየተነፋና ከበሮ እየተመታ የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹን በማጀብ ክወናውን የማድመቅ ባህል አለ፡፡

በትግራይ ደግሞ፣ አስከሬኑ ከቤት ወጥቶ ሲሄድ፣ ሴቶች የሟችን የክት ልብስ ይዘው ግራና ቀኝ እያራገቡ፣ ወንድ ዘመዶቹ ጠመንጃውን፣ ጋሻና ጦሩን፣ ባርኔጣውን፣ ይዘው እንደሚያለቅሱ ነጋ (2002) ይገልጻሉ፡፡ በአጎበር (የቀጠሮ) ለቅሶ ጊዜ ደግሞ፣ የሟች አገልጋዮች የጌታቸውን ጠበንጃ፣ ጋሻና ጦር፣ ጭራ እንዲሁም ግምጃ የተሸፈኑ ገንቦዎችንና ድስቶችን ይዘው ምስሉን እንደሚያጅቡ ያስረዳሉ፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የተገለጹትን እስከቀብር ድረስም ሆነ ከዚያ በኋላ የሚከወኑትን ሥርዓቶች ማሕበረሰቡ ልማድ አድርጎ በተዳጋጋሚና ሥርዓት ባለው መንገድ የሚከውናቸው አንዳች ፋይዳ ስላላቸው እንደሆነ የጥናት ውጤቶች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ Yoder (1986፣151-152)፣ የቀብር ሥርዓት ለሰፊው ማህበረሰብም ሆነ ለሟች የቅርብ ሰዎች፣ ጠቃሚ ሚና እንደሚጫወት ያስረዳሉ፡፡ የአንድ ግለሰብ ሞት የቅርብ ቤተሰቦቹን ብቻ ሳይሆን፣ የሚኖርበትን ማህበረሰብም እንደሚጎዳና፣ ሀዘንተኞቹ የማህበረሰቡን እርዳታ እንደሚፈልጉ ያስረዳሉ፡፡ የቀብር ሥርዓቱ መፈጸም ሀዘንተኞቹ ሀዘናቸውን እንዲቀንሱ፣ ከሟች ውጭ በሚኖሩበት ማህበረሰብ

ውስጥ መኖር እንዲችሉ ከመርዳቱ በተጨማሪ፣ በሟች ዙሪያ የሚገኙት ቤተሰቦቹ፣ ጎረቤቶቹ፣ የሰፈሩ ሰዎች፣ የሥራ ባልደረቦቹ፣ ራሳቸውን አረጋግተው ከሟች ውጭ መኖርን እንዲለምዱ ያግዛቸዋል። በማህበረሰቡና በሀዘንተኞቹ መካከል ያለው ግንኙነት፣ ሀዘንተኞቹ ብቸኛ እንዳልሆኑ እንዲሰማቸው የማድረግ ተግባር እንዳለውም ይገልጻሉ።

የቀብር ሥርዓት ክወና ቡድናዊ ጠቀሜታ እንዳለው Marshallም (2002፣360)፣ ያስረዳሉ። የቀብር ሥርዓቶች ክወናዎች ለከዋኞቻቸው የሚያስገኟቸው በርካታ ጠቀሜታዎች ቢኖሩም፣ እምነትንና (belief) አብሮነትን (belongingness) ማመንጨት መሰረታዊዎቹ እንደሆኑም ያስገነዝባሉ። ተመራማሪው አክለው እንደሚገልጹት፣ ከሥርዓት የሚመነጭ እምነት የጸና፣ አስተማማኝ፣ የማይዋዥቅና ካልተለመዱ ጥርጣሬ ፈጣሪ ነገሮች የጸዳ ነው። አብሮነቱም፣ የመፈቃቀድ፣ የመተዋወቅና የአንድነት ውህድ ነው። እምነቱ ከእውቀት፣ አብሮነቱም ከአባልነት በላይ መሆኑንም ያስረዳሉ።

Hatfield፣ Rapson እና Cacioppoን (1994) ዋቢ በማድረግ Marshall (2002፣363) እንደሚያስረዱት ደግሞ፣ በቀብር ሥርዓት ላይ ሰዎች በቡድን መሳተፋቸውና መገኘታቸው፣ የርስበርስ ስሜታቸውን እንዲጋሩና የአብሮነት ስሜት እንዲፈጥሩ ያደርጋል። Danielም (2009፣158)፣ በአንድ ሰው ላይ ከውልደት እስከሞት በሚደርሱት ነገሮች የጋራ መተሳሰቦች እንደሚንጸባረቁ ጠቁመው፣ በማሕበረሰብ ሕይወት በጣም ጠቃሚ ሚና ከሚጫወቱት አስተባባሪ ሁነቶች ውስጥ አንዱ ሞት መሆኑን ያስረዳሉ። አንድ የማሕበረሰቡ አባል ሲሞት ጉዳቱ ለሁሉም ሰው ስለሚሰማው፣ የቆየ ቂም ያላቸው ሳይቀሩ እንደሚረሱትና፣ እያንዳንዱ ሰው በሚችለው ሁሉ ስለሚተጋገዝ የቡድኑ አንድነትና ግንኙነትም እንደሚጠናከር ያስረዳሉ።

በብዙ ማህበረሰቦች የቀብር ስርዓት የሚከበረው ደግሞ ከላይ እንዳየነው ለቋሚዎቹ ብቻ ሳይሆን ለሟቾቹም የጋራ ደህንነት ሲባል ነው። ቋሚዎች ለሙታን የተለየ እንክብካቤ የሚያደርጉት፣ ለራሳቸውም እንዲደረግላቸው ጽኑ ፍላጎት ስላላቸው ጭምር መሆኑን ጥናቶች ያመለክታሉ። ለምሳሌ በመኤን ብሔረሰብ የሟችን የቀብር ሥርዓት በተገቢ መንገድ ማከናወን፣ ለቋሚም ጥቅም የሚያስገኝ ተደርጎ እንደሚታመን Abbink (1990) ያስገነዝባሉ። ስለሆነም በቀብር ሥርዓት ያልተጻፈ ሕግ መሰረት ቀብር ካልተከናወነ፣ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል ጥፋት ተደርጎ ይቆጠራል። ምክንቱያም በቀብር ሥርዓቱ ክወና የሟች ሀዘንተኛ ቤተሰቦች ከሟችና

ከአያት ቅድመ አያቶቻቸው ነፍሶችና ከፈጣሪያቸው ጋር የሚያገናኙ ተግባራትን ስለሚፈጽሙ፣ እነዚህን በተለመደው መንገድ አለማከናወን የሟችን ነፍስ ለብቀላ፣ የአያት ቅድመ አያቶቻቸውን ነፍሶችና ፈጣሪያቸውን ለቅጣት ያነሳሳቸዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ Stuart እና Jun (1992፣68)፣ የምንሂ ቱ (Minhe Tu) ማሕበረሰቦች ተገቢው ቅድመ እንክብካቤ በልዩ ትኩረት ካልተከናወነና ሟች በተገቢው መንገድ ካልተሸኘ፣ ያለምንም ጥርጥር መንፈሱ ተመልሶ በቤተሰቡ ላይ ቁጭቱን የመወጫ ጥፋትና ጉዳት ያደርሳል ብለው እንደሚያምኑ ይገልጻሉ፡፡ ስለሆነም የሟች ቤተሰቦች ከጥፋት ለመዳን፣ ከሞት ጋር ለተያያዙ አገልግሎቶችና ሥነ ሥርዓቶች፣ ከዓመታዊ ገቢያቸው በብዙ እጥፍ የሚበልጥ ገንዘብ ወጭ እንደሚያደርጉ ያስረዳሉ፡፡

Alembi (2002፣137) ደግሞ፣ የለቅሶ ሥርዓትን ፋይዳ ከላይ ከተጠቀሱት በተለየ መልኩ ያዩታል፡፡ ሞት ከምድራዊው ዓለም ወደመናፍስት ዓለም፣ ወደምውት ሕያዋን ዓለም /living dead world/፣ ወደአያት ቅድመ አያት ዓለም /ancesters world/፣ የሚደረግ ሽግግር ነው ተብሎ ስለሚታመን፣ ቋሚዎቹ ሟችን ዳግመኛ በሕይወት የማግኘትና የማየት እድል ስለሌላቸው፣ የለቅሶ ክወናው የስንብት ማቅረቢያ መንገድ በመሆን እንደሚያገለግል ይገልጻሉ፡፡ እንዲሁም የቀብርን ሥርዓት በተገቢ መንገድ ማከናወን በሟችና በቋሚ ሊከሰቱ ይችላሉ ተብለው የሚሰጉ ብቀላዎችን ከማስቀረቱ፣ ለቋሚዎቹ የወደፊት የሌላ ዓለም ጉዞ መንገድ ከማመቻቸቱና፣ ከስንብት ማቅረቢያነቱ በተጨማሪ፣ የሀዘን ክብደትን የማቅለል ጠቀሜታ እንዳለውም ያስገነዝባሉ፡፡

Hertz'ን (1960) ዋቢ በማድረግ Fishbane (1989፣66)፣ እንደሚያስረዱት ደግሞ፣ ሞት በመደበኛው መንገድ የግለሰብ በጊዜያዊነት ከማህበሩ መነጠል ቢሆንም፣ ይህ እንደማህበራዊ ክስተት ሲታይ፣ የአዕምሮ ወታወክንና መገለልን የሚያስከትል ሕመም አዘል ሂደት ነው፡፡ እንደተመራማሪው ገለጻ፣ ማሕበረሰቡ ሰላሙን የሚመልሰውና በሞት ላይ ድል የሚቀዳጀው፣ የቀብር ሥርዓቱን ሂደት በተሟላ መንገድ ሲያጠናቅቅ ብቻ ነው፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች የቀብር ሥርዓት በእንግሊዝ ማህበረሰብ ውስጥ እየተዳከመ መምጣት፣ ማህበራዊና ሥነልቡናዊ ጫና እያሳደረ መሆኑን Yoder (1986፣151)፣ በጥናታቸው ማረጋገጣቸው፣ ለዚህ ጥሩ ማስረጃ ሊሆን ይችላል፡፡ እኒህ ተመራማሪ፣ ከማህበራዊው፣ በጎ ያልሆኑ ባህርያት (maladaptive behavior) መከሰትን፣ ከስነልቡናዊው፣ ሰዎች ሀዘናቸውን የሚገልጹበት አውድ ማጣታቸው

ወይም እንዳይገልጹ መከልከላቸው፣ መፍትሄ ለማያገኝ ወይም ለረዥም ጊዜ ለሚቆይ ሀዘን እየዳረጋቸው መሆኑን ይጠቅሳሉ።

Gufler (2000፣360) እንደሚያስረዱት ደግሞ፣ በያምባ ማሕበረሰብ የቀብር ሥርዓት የሚፈጸምበት ዋና ዓላማ፣ ሟችን በሠላም በመሸኘት፣ አካባቢውን ከሞት ብክለት ለማንጻት ነው። እንደተመራማሪው ገለጻ፣ የቀብር ሥርዓት መፈጸም፣ ሟች ቂም እንዳይዝ፣ ሀብት ንብረታቸውን እንዲባርክና፣ ሲሳያቸውን ይዞባቸው እንዳይሄድ ያደርጋል።

የሚኒሶታ ዩኒቨርሲቲ የሞት ትምህርትና ምርምር ማዕከልን ግኝት ጠቅሰው Yoder (1986፣152)፣ እንደሚያስረዱት፣ የቀብር ሥርዓት ክወና የቋሚዎቹን ሀዘን ለማስረሳት ከሚያደርገው አስተዋጽኦ በተጨማሪ፣ በርካታ የቤተሰብና የጓደኛ አባላት የሚሰባሰቡበት ስለሆነ፣ ባሕላዊ እሴቶቻቸውን ከትውልድ ትውልድ ለማስተላለፍ የሚረዳ፣ ጠቃሚ የማህበራዊ ልምዶች (socialization experiences) መቅሰሚያም መድረክ ነው።

ከዚህ በላይ ከቀረቡት ሀሳቦች ለመረዳት እንደሚቻለው፣ በቀብር ስርዓት ክወና ሀዘንተኞች ሀዘናቸውን በሚገባ በመግለጽ ታፍኖ ቢቀር በአካላቸውና በስነልቡናቸው ላይ ጉዳት ሊያስከትልባቸው ይችል የነበረውን አደጋ ይቀንሳሉ። ሟችን በክብር ከመሸኘታቸው በተጨማሪ ከሙት መንፈሱ ወይም ከፈጣሪ ይላክብናል ብለው የሚሰጉትን ቅጣት ያስቀራሉ። ይህን በማድረጋቸውም የስነልቡና መረጋጋት ያገኛሉ። በቡድን ክንውኑም፣ ሀዘንተኞቹ በሚደረግላቸው የዘመድ ጎረቤት ድጋፍ፣ ብቻቸውን አለመሆናቸውን እንዲገነዘቡና ተጽናንተው ወደመደበኛው ሕይወታቸው እንዲመለሱ ያደርጋቸዋል። ኑሮ ያራራቃቸውን ቤተዘመዶች በማገናኘት፣ ትስስራቸውን እንዲያጠናክሩ፣ የጋራ ታሪካቸውን እንዲካፈሉና፣ ከአባት የቆየውን ባሕላቸውን ይዘው እንዲቀጥሉ፣ አሰባሳቢ ምክንትያት በመሆንም ያገለግላል።

እንደቀብር ሥርዓቶቹ ሁሉ የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹም፣ የተለያዩ ፋይዳዎች እንዳሏቸው ጥናቶች ያሳያሉ። ለምሳሌ የኬሪጅስታንን ኮሾክ (ሙሾ) ያጠኑት Pritchard (2011፣193) እንደሚያስገነዝቡት፣ ሙሾ፣ ጥልቅ ሀዘን የሚገለጽበትና በቋሚዎችና በሙታን መካከል

የሚደረግ ምልልስ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሙሾ፣ ስለሟች ሕይወትና ሞት፣ ከዋኙ ከሟች ጋር ስላለው ዝምድና፣ ስለሀዘንተኞቹ ሁኔታ መረጃ ያስተላልፋል፡፡

የአባንዮሌን ማህበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች የመረመሩት Alembi (2002፣51-54) ደግሞ፣ የቀብር ቃል-ግጥሞቹ የምስሎችና ትዕምርቶች ትንተና፣ የሞትን ምንነት ለመረዳት እንዳስቻሏቸው ይገልጻሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ Mooreም (1968፣57)፣ በተለያዩ የአፍሪካ ክፍሎች የሚገኙ ማህበረሰቦች፣ በቃል-ግጥሞቻቸው በሞት ዙሪያ ያላቸውን አመለካከት እንደሚያንጸባርቁባቸው፣ ስድስት ያህል የጋራ ነጥቦችን በመጥቀስ ያስረዳሉ፡፡

Sanka Confidence (2010፣196) ደግሞ፣ እንደሌሎቹ የጋና የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ሁሉ፣ የሲሳላ ማህበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞችም፣ ስነምግባራዊና ማህበራዊ እሴቶችን፣ ባህላዊ ድርጊትን፣ የንግግር ስልትን፣ ታሪክን፣ ተግባራዊ የሕይወት ትምህርትንና፣ ከእነዚህ ሁሉ በላይ መታረም የሚገባቸውን ትኩረት ሳቢ ጉዳዮች መተቸትን መሰረት ያደረጉ ትምህርቶች መስጫዎች በመሆን እንደሚያገለግሉ፣ ገልጸዋል፡፡ እኚሁ ተመራማሪ አክለው እንደሚያስረዱት፣ የሁሉም የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ተቀዳሚ ተግባር፣ ቋሚዎች ለሟቾች የተሰማቸውን ጥልቅ ሀዘን ለመግለጫነት መዋላቸው ሲሆን፣ ይህም የቋሚዎቹን ሀዘን በማስተንፈስ ከህመም የመገላገል ሚና እንዳላቸው ያስረዳሉ፡፡

እንደፌቃደ (1996) እና ብርሀኑ (2002) ገለጻ ደግሞ፣ በኢትዮጵያም የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ከሞት መከሰት ጋር ተያይዞ የመጣን ሀዘን ከመግለጫነት በተጨማሪ፣ ማሕበራዊ ብሶትንና የፖለቲካ ምሬትን ለመግለጫነት፣ ለባለስልጣናትና ለማሕበራዊ ሂስ መስጫነት ያገለግላሉ፡፡

የአልጀርያን ሀገረሰባዊ ቃል-ግጥሞች ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳ ያጠኑት Bamia (2001፣11) እንደሚያስረዱት ደግሞ፣ ሀገረሰባዊ ስነቃሎች (folk texts) ለበርካታ ታዳሚ መድረስ ባይችሉ እንኳ፣ ደራሲያቸውና በዙሪያው ያሉት አድማጮች (ታዳሚዎች)፣ ያስከፋቸውን ሀሳብ በይፋ ስለሚገልጹባቸው እፎይታ ያስገኙላቸዋል፡፡

የፊንሽን የለቅሶ ስርዓት ያጠኑት Tolbert (1990፣80) እንደሚገልጹት ደግሞ፣ ሙሾ የሟችን ነፍስ ቶንላ ወደተባለው የፊንሽ ከሪሊያን የሙታን መሬት እንድትደርስ በመምራት፣ ሕያዋኑና

ሙታኑ ከየሚገኙባቸው ዓለማት መልእክት እንዲለዋወጡ በማስቻል፣ ግለሰባዊና ማሕበራዊ የመንፈስ እርካታን የማደስ ሚና ይጫወታል።

በአጠቃላይ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች፣ ሀዘንተኞቹ በሟች መለየት ምክንያት የተሰማቸውን ሀዘን በመግለጽ እፎይታ የሚያገኙባቸው ብቻ ሳይሆኑ፣ የትናንት ታሪካቸውን የሚዘክሩባቸው፣ አስተዳደራዊ በደላቸውንና ወቅት ፈጠር ብሶታቸውን የሚተነፍሱባቸው፣ መልካም ማህበራዊ እሴቶቻቸውን የሚያስርጹባቸውና እኩዮቹን የሚያወግዙባቸው ጭምር መሆናቸውን መረጃዎቹ ያሳያሉ።

ከዚህ በላይ የተተኮረባቸውን ጽንሰ ሀሳቦች ለመግለጽ ተሞክሯል። ቀጥሎ ደግሞ በኢትዮጵያ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ምን ምን ጥናቶች ተካሂደዋል? ጠንካራና ደካማ ጎኖቻቸውስ ምን ይመስላሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች የሚመልሰው የተዛማጅ ሥራዎች ቅኝት ቀርቧል።

## 2.2 የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት

### 2.2.1. በአማራ ብሔረሰብ በለቅሶ ሥርዓት ላይ የተካሄዱ የዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ክፍል ከጥናቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው የዲግሪ ማሟያ ዲማጾችና ሌሎች ጥናቶች ተቃኝተዋል። ጥናቶቹ በሞት ላይ የተካሄደውን ምርምር ታሪካዊ ዳራ በማሳየት፣ ትኩረት የተሰጣቸውንና የተዘነጉትን ነጥቦች አመልክቶ ክፍተቶችን በመጠቆምና፣ ለዚህ ጥናት አጋዥ መረጃዎችን በማስገኘት በኩል፣ ጠቃሚ ሆነው ተገኝተዋል። ምክንያቱም ይህ ጥናት ከባዶ የጀመረ ሳይሆን በእነዚህ ላይ የተመሰረተ ነውና።

በአማራ ብሔረሰብ የሚከወኑትን የለቅሶ ሥርዓቶችና ቃል-ግጥሞች የጥናታቸው ርዕሰ ጉዳይ አድርገው ወደአካዳሚያዊ ውይይት በማምጣት፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ዲማጾች ጉልሁን ቦታ ይይዛሉ። ለምሳሌ የለቅሶ ሥርዓትንና የሙሾ ሥነቃሎችን አጣምረው በማጥናት፣ ንጉሴ እ.ኢ.አ (1974)፣ ወርቁ እ.ኢ.አ (1987) እና ሽመልስ እ.ኢ.አ (1997)፣ የለቅሶን ሥርዓት ብቻ በማጥናት ጌጡ እ.ኢ.አ (1989)፣ የለቅሶ ቃል-ግጥሞችን ኪነጥበባዊ አገላለጽ (ዘይቤ)

በማጥናት፣ ብርሃኑ እ.ኢ.አ (1973) እና ባልከው እ.ኢ.አ (1974) እንዲሁም የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹን በይዘት በመመደብ ታደሰ እ.ኢ.አ (1963) እና ማተቤ እ.ኢ.አ. (1972) ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ‹ጥናቶች› የተካሄዱት፣ ለፎክሎር ጥናት ብቻ ሳይሆን፣ ለጽንሰ ሀሳቡም እንግዳ በሆኑ የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች በመሆኑ፣ በመስኩ የሚጠቀሱት ርዕሰ ጉዳዩን የ‹ጥናታቸው› ትኩረት በማድረጋቸው እንጂ፣ በጥናት ዘዴዎቻቸው ብስለት ወይም በግኝቶቻቸው ረብ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የማይጠበቅ ነገር መፈለጉ ጊዜ ከማባከን ውጭ ፋይዳ ስለሌለው ነው፡፡ ከእነዚህ ይልቅ ቀጥሎ በቀረቡት የ2ኛ ዲግሪ ዲማጾች ርዕሰ ጉዳዩ በስፋትም ሆነ በጥልቀት በመመርመሩ፣ በቅኝቱ ጠንካራና ደካማ ጎኖቻቸው እየተጠቀሱ ተቃኝተዋል፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ኖሯቸው ከተቃኙት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ውስጥ፣ የሞገስ እ.ኢ.አ. (2002)፣ *‹‹በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ሥነ ሥርዓት፣ በሥርዓቱ ላይ የሚካሄድ የቀረርቶና የፉከራ ክዋኔ››*፣ የሀብታሙ እ.ኢ.አ (2003)፣ *‹‹ሞተን ተነሳን የሚሉ ሰዎች የሌላ ዓለም ጉዞ ተረኮች››*፣ የበሪሁን እ.ኢ.አ (2004)፣ *‹‹የሙሾ፣ የወየታና የፉከራ ግጥሞች ክዋኔና የይዘት ትንተና በደብረ ታቦር ከተማ››*፣ የማርየ (2008)፣ ‹‹*A Thematic Analysis of the oral poetry of the People of Fogera*›› እና የምግባሩ (2009)፣ ‹‹*AThematic Analysis of Funeral Dirges in West Gojjam*›› ይጠቀሳሉ፡፡

ማርየ የፎገራን ሕዝብ ቃል-ግጥም ጭብጥ በክወና ትውር ለማጥናት መነሳሳታቸውን ቢገልጹም፣ ከውስን የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ውጭ ያሉትን የውቂያና ሌሎች የሥራ ቃል-ግጥሞች፣ መጠጥ ቤት ውስጥ በቃለ መጠይቅ መሰብሰባቸው፣ የተነሱበትን ዓላማ እንዳያሳኩ እንቅፋት ፈጥሮባቸዋል፡፡ በክለሳ ድርሳናቸው ክፍል ከጥናታቸው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸውን ሥራዎች መከለሳቸው፣ የእርሳቸው ሥራ ጥናቱን ባካሄዱበት አካባቢ ቀደም ሲል ከተካሄዱ ጥናቶች በምን እንደሚለይና ከእሳቸው ጥናት ምን አዲስ ነገር እንደሚጠበቅ ማሳየት እንዳይችሉ አድርጓቸዋል፡፡ የጥናታቸውን ዘዴ ካለመግለጻቸው በተጨማሪ፣ መረጃ አቀባዮቹም ሆኑ የጥናት ቦታው በምን የንሞና ዘዴ እንደተመረጡ ያሉት ነገር የለም፡፡ ትንተናውን ከአውድ ውጭ ማካሄዳቸውም፣ ጥናታቸው በዘመኑ የዘርፉ ሳይንሳዊ አሰራር ሲለካ፣ በርካታ ክፍተቶች እንዲኖሩት በር ከፍቷል፡፡

ምግባሩም የምስራቅ ጎጃም ሕዝብ በለቅሶ ግጥሞቹ የሚያነሳቸውን ጭብጦች፣ ሟችን፣ ሞትን፣ እግዚአብሔርን፣ ማህበራዊና ፖሊቲካዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱና፣ ሌሎች የሀዘን መግለጫዎች፣ በሚሉ አምስት ዋና ዋና ክፍሎች መድበው ተንትነዋል፡፡ መረጃዎቹ ከአውድና ክወና ውጭ በመሰብሰባቸው ትንተናው ከእነዚህ ውጭ በሆኑ ደረቅ ይዘቶች ላይ እንዲመሰረት አድርጎታል፡፡ ሞገስ የለቅሶ ሥርዓቱን ከክወናው ላይ ተመስርተው መተንተናቸውና የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹንም ከሞላ ጎደል ከነአውዳቸው መሰብሰባቸው፣ በጠንካራ ጎንነት ይጠቀስላቸዋል፡፡ በጀግና ቀብር እንደማይለቀስና ሙሾ እንደማይወረድ በአንዱ የጥናቱ ክፍል ጠቅሰው፣ በሌላው ክፍል እነዚህን መተንተናቸው በጥናቱ ክፍሎች መካከል ተቃርኖ መፈጠሩን አለማስተዋላቸውን ያሳያል፡፡ በክለሳ ድርሳናቸው ያነሷቸውን ጠቃሚ ነጥቦች ለትንተናው ማጠናከሪያነት አለመጠቀማቸውም በጥናቱ ድክመትነት ይጠቀሳል፡፡

ሀብታሙ አዲስ የጥናት ርዕሰ ጉዳይ ማንሳታቸው መልካም ቢሆንም፣ የሌላ ዓለም ጉዞ ተረኮቹን በራሳቸው ባህሪ ከመመርመር ይልቅ፣ በስም እንጂ በግብር ከማይመስሏቸው የፎክሎር ዘሮች (ሚቶች፣ አፈ-ታሪኮችና ሀገረሰባዊ ተረቶች)፣ ጋር ማዛመዳቸውና ለእነዚህ በወጣው መስፈርት እንዲመዘኑ ማድረጋቸው ተቀባይነት የለውም፡፡

በሪሁን በደብረ ታቦር ከተማ የሚከወኑ የለቅሶ ቃል-ግጥሞችን፣ በሙሾ ስር ጠቅልሎ መጥራት ተገቢ አለመሆን በጥናታቸው ለማሳየት መነሳታቸው፣ የችግሩን መኖር ከመገንዘብ አኳያ መልካም ጅምር የሚባል ነው፡፡ ምክንያቱም፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ከተካሄዱት ጥናቶች ውስጥ የማርየ፣ ለመጀመሪያ ዲግሪ ከተካሄዱት ጥናቶች መካከል የወርቁ፣ ለሴሚናር ከቀረቡት ጥናቶች ውስጥ የብርሃኑ፣ በተቀራራቢ ቦታና ማሕበረሰብ ላይ ቢካሄዱም፣ ስለወየታ የለቅሶ ቃል-ግጥም ያነሱት ነገር የለም፡፡ በአማራ ማሕበረሰብ ላይ የተካሄዱት የእነታደሰና የእነጌጡ፣ ጥናቶችም ስለሙሾ እንጂ ስለወየታ የሰጡት ፍንጭ የለም፡፡ የግጥሞቻቸው ስብስቦችና ስለክወናቸው የሰጧቸው ማብራሪያዎች ሲታዩ ግን፣ ከሙሾ ይልቅ ለወየታ የቀረቡ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ጎጃምና ሰሜን ሸዋ አካባቢዎች፣ ምናልባት ከደቡብ ጎንደር ባላቸው የቦታ ርቀት ለወየታ ቃል-ግጥሞቹ ሙሾ የሚል መጠሪያ ተሰጥቷቸው ሊሆን ይችላል ብሎ መገመት ይቻላል፡፡ ቀደም ሲል ይከወኑ ከነበሩት የለቅሶ ቃል-ግጥሞች፣ የሙሾ ክወና በአንዳች ምክንያት ሲቋረጥ፣

ስያሜውን ለወየታ ቃል ግጥም አውርሶ ሊሆን ይችላል ብሎ መገመትም ይቻላል፡፡ ይህ ራሱን ችሎ መጠናት ያለበት ርዕሰ ጉዳይ ሆኖ፣ የወየታ፣ የሙሾና የፉከራ ቃል-ግጥሞች ቢያንስ በተለያየ መንገድ በሚከወኑባቸው የደቡብ ጎንደር ወረዳዎች በተካሄዱት ጥናቶች፣ ወየታን በሙሾ ውስጥ ጠቅልሎ ማቅረብና ስለምንነቱ ፍንጭ አለመስጠት፣ አንድም ለጥናቱ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በሚከወኑበት አውድ ሳይሰበስቡና በጥልቀት ሳይመረምሩ ወደድምዳሜ ከመሄድ፣ ወይም የተገኙትን መረጃዎች በአካባቢያዊ ስያሜያቸውና ባህሪያቸው ሳይሆን፣ በሌሎች ስያሜዎችና የዘውግ ባህርያት አኳያ ከማየት የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡ ችግሩ የትኛውም ይሁን፣ በሪሁን የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ በሙሾ እንደማይጠቀለሉ መረዳታቸውና ልዩነታቸውን ለማሳየት የጥናታቸው ትኩረት ማድረጋቸው፣ ከዚህ በፊት ያልተነሳ አዲስ ነገር አንስተዋልና እንደመልካም ጅምር ሊወሰድ ይችላል፡፡

ይሁን እንጂ፣ በጥናቱ የወየታ፣ የሙሾና የፉከራ የለቅሶ ቃል-ግጥሞችን ክወናና ይዘት እንዳሰቡት በተጨባጭ መረጃ አስደግፈው አንድነታቸውንና ልዩነታቸውን ለማሳየት አልቻሉም፡፡ መረጃዎቹን በተፈጥሯዊ መቸታቸው በምልከታ እንደሰበሰቧቸው ቢገልጹም፣ በሶስቱም የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ክወና፣ የከዋኝ ታዳሚን መስተጋብርና ባህላዊ አውዳቸውን መሰረት አድርገው ማሳየት ተስኗቸዋል፡፡ ስለሶስቱ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ክወናዎችም፣ እንደተመራማሪ ቅደም ተከተላዊ ሂደታቸውን እየገለጹ፣ ለምን እንደዚያ እንደሚደረጉ እየተረጎሙ ሳይሆን፣ የለቅሶ ሥርዓቱን በአጋጣሚ እንዳየ ጨዋ ታዛቢ (layman) በመንገር ነው የሚያልፏቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ በትንተናቸው ክፍል የሙሾ ቃል-ግጥሞችን አላካተቱም፡፡ የጥናታቸው ትኩረት የሶስቱን ቃል-ግጥሞች ክወናና ይዘት በመመርመር፣ በማስረጃ አስደግፎ በየራሳቸው መጠናት ያለባቸው መሆናቸውን ማሳየት ሆኖ ሳለ፣ የሙሾ ቃል-ግጥሞችን አለመተንተናቸው፣ ከተነሱበት ግብ እንዳይደርሱ አድርጓቸዋል፡፡

በመንገር በቀረበው የጥናቱ ክፍልም ከእውነታው ያፈነገጡ ሀሳቦች ተሰንዝረው ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ ስለሙሾ ባነሱበት የንድፈ ሀሳብ ክፍል፣ በሙሾ የለቅሶ ክወና የእድሜ ልዩነት እንደማይደረግና የሟች ስም እንደማይጠራ ይገልጻሉ፡፡ እርሳቸው ጥናታቸውን ባካሄዱበት ተመሳሳይ ወረዳና ዓመተ ምህረት የተሰበሰቡት የዚህ ጥናት መረጃዎች የሚያሳዩት ግን፣ በእርሳቸው ከተገለጸው የተለየ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ በተጠኘው ማህበረሰብ የፉከራ ቃል-

ግጥሞች ለጀግና ወንዶች ብቻ እንደሚቀርቡ የገለጹትም በመረጃ ላይ የተመሰረተ ግኝት አይደለም። በራሳቸው ጥናት በሌላ ቦታ፣ በሚች ባሏ ለቅሶ ላይ ከባሏ ጋር የተፎከረላትን ሚስት መረጃ ማቅረባቸው (ገጽ፣62፣64) ድምዳሜቸው የተዛባ መሆኑን ለማሳየት ያስችላል።

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ፣ በጥናቱ ከሚታዩት ጎላ ጎላ ያሉ ድክመቶች መካከል፣ ለይዘት በተመረጠው ርዕስና በሚሰጠው ትንታኔ መካከል ያለመጣጣም መታየቱ አንዱ ተደርጎ ይጠቀሳል። ለምሳሌ የወየታን ግጥም በይዘት ከከፈሉባቸው ንዑስ ርዕሶች፣ ‹‹ቁጭትን የሚገልጹ›› ተብለው ከቀረቡት ግጥሞች በሚች አለመኖር ምክንያት በሚች ቤተሰቦችና በቤተዘምድ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት የሚገልጹት አመዝነው ታይተዋል። የእነዚህ ግጥሞች ይዘት በማስገደዱ ይመስላል፣ ትንተናውም ከርእሰ ጉዳዩ አፈንግጦ ይህን ተከትሎ ተካሂዷል (ገጽ፣50)። በግጥሞቹ ያልተባሉ እንግዳ ሀሳቦች፣ በማብራሪያዎቹ ተደጋግመው ሲገለጹ ከመስተዋላቸውም በተጨማሪ፣ በጥናቱ ያልተነሱ ርዕሰ ጉዳዮች፣ በማጠቃለያው የጥናቱ ግኝቶች ተደርገው ተገልጸዋል። ለዚህ ከሙሾ ግጥሞች ትንተና የተገኙ ተደርገው የቀረቡ ግኝቶችና በኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክና ሙስሊም የለቅሶ ሥርዓቶች ላይ እንደታዩ የተገለጹት ልዩነቶች በማስረጃነት ይጠቀሳሉ (ገጽ፣73)።

በአጭሩ በበሪሁን ጥናት፣ የሙሾ፣ የወየታና የፉከራ የለቅሶ ግጥሞችን የክወናና የይዘት አንድነትና ልዩነት ለማሳየት ቢታሰብም፣ ከመንገር ባለፈ የሰበሰቧቸውን መረጃዎች ባህላዊና ማህበራዊ አውዳቸውን መሰረት አድርገው ክወናቸውን ያለማሳየት፣ ይዘታቸውን ከተነገሩበት ሁኔታ ጋር አጣጥመው ያለመተንተንና ያለመፈከር ችግሮች ጎልተው ታይተዋል።

በአጠቃላይ በሁለተኛ ዲግሪ ዲማጾቹ ተገቢ የጥናትና የመተንተኛ ዘዴዎችን የመምረጥና በርዕሰ ጉዳያቸው ዙሪያ ሰፋ ያለ ትንተና የማድረግ ጠንካራ ጎን ቢታይም፣ እንደመጀመሪያ ዲግሪ ጥናቶቹ መረጃዎችን ከክወናቸውና ከአውዳቸው ውጭ የመሰብሰብ፣ በውስን መረጃዎች ላይ ተመስርቶ ሰፊ ማጠቃለያ ላይ የመድረስ፣ ወይም መረጃዎቹ የማያሳዩዋቸውን ሀሳቦች የመጨመርና አዛብቶ የማቅረብ (በበሪሁንና በሞገስ ጥናቶች እንደታዩት) ችግሮች ይታያሉ። ይህም በአማራ ክልል በለቅሶ ሥርዓትና በለቅሶ ቃል-ግጥሞች ላይ የሚደረገው አካዳሚያዊ ምርምር፣ ያልዳበረና ዘመኑ ከደረሰበት የአጠናን ዘዴ ወደኋላ የቀረ መሆኑን ያሳያል።

ከመመረቂያ ጥናቶች ውጪ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ በተካሄዱ ጥናቶች ላይ የሚታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ደግሞ እንደሚከተለው ተገምግመዋል፡፡

### 2.2.2. ከዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ሌላ በኢትዮጵያ በቀብር ሥርዓት ላይ የተካሄዱ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ርዕስ ስር የተቃኙት በተለያዩ ማሕበረሰቦች ላይ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተካሄዱ ጥናቶች ናቸው፡፡ እነሱም የአቢንክ *(1990) ‹‹The Final Rite: Burial Among the Me'en of South-West* Ethiopia››፣ የነጋ (2002) ‹‹*The Death Custom in the Province of Tigray*›› ፣ የፋሲካ አ.ኢ.አ (1953) *«The Death Customs among the Amharas of Shewa»*፣ የአክሊሉ (2002) ‹‹*Harer Funeral Custom*›› ፣ የአንዳርጋቸው (2002) ‹‹*The Funeral Customs of the 'Kottu' of Harer*›› እና የብርሀኑ (2002) ‹‹*Mušo as a Socio-poletical Discourse Among the Amhara*›› የሚሉት ናቸው፡፡ የየጥናቶቹ ትኩረት በጥቅሉ ሲቃኝ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

Abbink (1990፣67)፣ የመኤንን ማሕበረሰብ የቀብር ሥርዓት ክወናና በክወናው ላይ የሚካሄደውን የእያንዳንዱን ድርጊት ቅደም ተከተልና፣ በለቅሶው አገልግሎት ላይ የሚውሉ መሳሪያዎችን በዝርዝር ገልጾዋል፡፡ እያንዳንዱ ድርጊት ለምን እንደሚደረግና መሳሪያዎቹ ለምን እንደሚያዙ ከማብራራታቸውም በተጨማሪ፣ ትዕምርታዊ አንድምታቸውንም ተርጉመዋል፡፡ በመኤን ማሕበረሰብ የቀብር ሥርዓትን በተገቢው መንገድ አለማከናወን የአያት ቅድመ አያት መንፈሶቻቸውን ደህንነትና ውስጣዊ ሠላማቸውን እንደሚያናጋ ስለሚታመን፣ ለቀብር ሥርዓት ልዩ ትኩረት ሰጥተው እንደሚያከናውኑም ገልጾዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የመኤን የቀብር ሥርዓት ከላም ጋር በእጅጉ የተቆራኘ መሆኑን፣ የሟች ነፍስ ስትወጣ ከሚቀርበው ወተት ጀምሮ፣ ደሟ፣ ሞራዋ፣ አንጀቷ፣ ቆዳዋና አጥንቷ፣ ያለውን ሥርዓታዊ አገልግሎትና ትዕምርታዊ ፍች በጥልቀት ተመልክተዋል፡፡

የጥናታቸው ጭምቅም፣ ከብት የማሕበር አባልነትን በማሳያነትና በዋና የቀብር ማስፈጸሚያነት እንደሚያገለግል፣ የብሔረሰቡን ደሕንነት ለመጠበቅ ሲባል፣ ለቀብር ሥርዓት በትክክል መፈጸም ልዩ ትኩረት እንደሚሰጥ፣ ለአያት ቅድመ አያት መንፈስና ለሟች ነፍስ የሚፈልጉትን ማሟላት፣ ቋሚዎቹን ከመጥፎ ነገር እንደሚጠብቅ እንደሚታመን ያስረዳሉ፡፡

በአጠቃላይ Abbink በጥናታቸው፣ በቀብር ሥርዓቱ የሚከናወኑትን ድርጊቶችና የሚያዙትን ቁሶች በመግለጽና ትዕምርታዊ ትርጉማቸውን በማቅረብ፣ ማሕበረሰቡ ለቀብር ሥርዓት ልዩ ትኩረት የሚሰጥባቸውንና ለሟች ነፍስና ለአያት ቅድመ አያቶቻቸው መንፈስ መስዋዕት የሚያቀርቡባቸውን ምክንያቶች በመመርመር፣ ያቀረቡት ገለጻና ትርጉም፣ የበሰለ ጥናት ማካሄዳቸውን ያሳያል። ጥናታቸው በዘርፉ በመረጃዎች ትንተናና ትርጎማ ዙሪያ የሚታዩትን ችግሮች ለማስወገድም ጥሩ አርአያ ይሆናል ቢባል ስህተት አይሆንም።

ነጋም በትግራይ ክፍለ ሀገር የሚፈጸመውን የቀብር ሥርዓት፣ ሕመምተኛው ሲደክም ጀምሮ እስከሰባተኛው ቀን ድረስ በቅደም ተከተል የሚፈጸሙትን ሥርዓቶች፣ ጠቀለል ባለ መንገድ ተንትነዋል። የተለያየ ማሕበራዊ ደረጃ ላላቸው የማሕበረሰብ ክፍሎች የሚፈጸመውን ግንዘት በተነተኑበት ክፍል፣ ለምን እንደዚያ እንደሚደረግ ማብራሪያ ሰጥተዋል። ከዚህ ውጭ የገለጿቸውን ሥርዓቶችና ልማዶች ስለምንነት ግን አያብራሩም። ለምሳሌ በለቅሶ ሥርዓቱ የሙሾ ቃልግጥም እንደሚከወንና የሀዘንተኞቹን አለባበስ ቢገልጹም፣ የሙሾ ቃል-ግጥሙ እንዴት እንደሚከወን ማስረጃ አቅርበው አላሳዩም። የሀዘን ልብሱ በዚያ መልክ መለበሱ ምን ትርጉም እንዳለውም አልገለጹም። አስከሬን በአዲስ ልብስ እንደሚገነዝ ከመግለጽ ባለፈ ምክንያቱን አልጠቀሱም።

እስካሁን ያየናቸው ጥናቶች በለቅሶ ሥርዓት ላይ በመካሄዳቸው በርዕስ ጉዳዩ ዙሪያ በኢትዮጵያ ያለውን የጥናት ገጽታ ከማሳየት በስተቀር፣ ይህ ጥናት ከተካሄደበት ማሕበረሰብ ውጪ ባሉ ማሕበረሰቦች ላይ የቀረቡ ናቸው። የሚከተሉት የፋሲካና የብርሃኑ ጥናቶች ግን፣ በቦታ ከመለያየታቸው በስተቀር በአማራ ማሕበረሰብ ላይ የተካሄዱ ናቸው።

ፋሲካ የሰሜን ሸዋ ክርስቲያን አማሮችን የለቅሶ ሥርዓት፣ የቀብርና የሀዘን ልማድ በማለት በሁለት ክፍለው ተንትነዋል። በቀብር ሥርዓት ከኑዛዜ አፈጻጸም ጀምሮ፣ የሟች ዜና ረፍት የሚገለጽበትን፣ በቀብር ጉዞና በቀብር ላይ የሚከናወኑ ሥርዓቶችን፣ በቅደም ተከተላቸው ዘርዝረዋል። በሀዘን ልማድ ስር ደግሞ፣ የሟች ዘመዶችና ወዳጆች ሀዘናቸውን እስከአስራ አራት ዓመት በለቅሶ፣ በጌጣጌጥ አጠቃቀምና በአለባበስ እንዴት እንደሚገልጹ ለሟች ያላቸውን ቀረቤታ መነሻ በማድረግ አብራርተዋል።

ፋሲካ ከሞት መከሰት ጋር ተያይዘው የሚከወኑ ልማዶችን በቀብር ሥርዓት በሚያከናውኗቸው ድርጊቶችና በሀዘን አገላለጻቸው ከፍለው መመልከታቸው፣ ልማዱን በተሻለ መንገድ ለመግለጽ

አስችሏቸዋል፡፡ ይሁንና፣ በቀብር ክንውንም ሆነ በሀዘን መግለጫ ልማዶቹ የሚደረጉትን ነገሮች ከመዘርዘር ባለፈ ለምን እንደዚያ እንደሚደረጉና ምን ትዕምርታዊ ትርጉም እንዳላቸው አልተረጎሙም፡፡

ከሞት ጋር ተያይዘው የሚከናወኑ ሥርዓቶች ላይ ሳይሆን ከሚከወኑት ስነቃሎች መካከል የሙሾን ማሕበረ ፖለቲካዊ ሀቲት (Socio ploetical discourse) በመመርመር ብርሀኑ (2002) ይጠቀሳሉ፡፡ እኒህ ተመራማሪ ስለሙሾ ምንነት፣ ስለከዋኞቹና ክወናው እንዲሁም ስለፋይዳው ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ ሙሾ ለማሕበራዊና ፖለቲካዊ ሒስ መስጫነት እንዴት እንደሚያገለግልም ምሳሌዎችን እየጠቀሱ አብራርተዋል፡፡

መረጃዎቹ ከተለያዩ የታሪክ መጻሕፍትና በቃል ከሚነገሩት መሰብሰባቸው በጥናቱ ላይ ክፍተቶችን አስከትለዋል፡፡ የመጀመሪያው ክፍተት አጥኚው የሙሾን ምንነት በትክክል ለመመደብ አለመቻላቸው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ አንድ ቦታ ላይ ሙሾን የእርግዶ አንድ ክፍል እንደሆነ አስረድተው (ገጽ፣1917)፣ ብዙም ሳይርቁ ሌላ ቦታ ላይ ሙሾ በእርግዶና እንጉርጉሮ እንደሚከፈል ይገልጻሉ (ገጽ፣ 1918)፡፡ ሁለተኛው የጥናታቸው ክፍተት ውስን መረጃዎችን መነሻ አድርገው ግኝታቸው ለአጠቃላይ የአማራ ማሕበረሰብ እንደሚሰራ ሰፊ ማጠቃለያ ላይ መድረሳቸው ነው፡፡

የሀረር ሙስሊሞችን የቀብር ሥርዓት አክሊሉ (2002)፣ የሀረርጌ ሙስሊም ገበሬዎችን የቀብር ሥርዓት አንዳርጋቸው (2002) አጥንተዋል፡፡ የለቅሶ ሥርዓቶቹን ሬሳ ከማዘጋጀት ጀምሮ እስከቀብር አፈጻጸሙና ከዚያም በኋላ እስከሰባት ቀናት ያሉትን ሥርዓቶችና የማሕበረሰቡን የትብብር ልማዶች ገልጸዋል፡፡ ከላይ እንደታዩት ጥናቶች በእነዚህም የእያንዳንዱን ሥርዓት ስለምንነትና ትዕምርታዊ ትርጉም ያለማብራራት ችግሮች ይታያሉ፡፡

በአጠቃላይ ከዲግሪ መመረቂያ ውጪ በቀረቡት ጥናቶች የሚከተሉት ክፍተቶች ጎልተው ተስተውለዋል፡፡ የመጀመሪያው ክፍተት፣ የጥናታቸውን መነሻ ትውርና የአጠናን ዘዴያቸውን አለመግለጽ ሲሆን፣ ሁለተኛው በለቅሶ ሥርዓቶቹ የሚደረጉትን ነገሮች በቅደም ተከተል ከመግለጽ ውጪ (የአቢንክን ጥናት አይመለከትም)፣ በዲግሪ መመረቂያ ጥናቶች እንደታየው ለምን እንደዚያ እንደሚደረግና ምን ትዕምርታዊ ትርጉም እንዳለው አለመተንተናቸው ነው፡፡ የሥርዓቶቹ ማሕበራዊ ፋይዳም አልተገለጸም፡፡

በኢትዮጵያ በሞት ሥርዓትና በለቅሶ ቃል-ግጥሞች ላይ በተለያየ ደረጃ ከተካሄዱት ጥናቶች ቅኝቶች መረጃዎችን ከአውድ ውጪ ሰብስቦ የመተንተን፣ በመረጃዎቹ የሌሉ ትንታኔዎችን በማካተትና ያሉትን በተዛባ መንገድ የመተንተን፣ የጥናታቸውን ትውሮችና የጥናት ዘዴዎች ያለመግለጽ፣ ያስተዋሏቸውን ድርጊቶች ከመግለጽ ውጪ ለምን እንደሚደረጉ ያለማብራራት፣ ትዕምርታዊ ትርጉሞችን ያለመፈከርና የሥርዓቶቹን ፋይዳ ያለመግለጽ ችግሮች ተስተውለዋል፡፡

እነዚህ ችግሮች በሌሎች ሀገሮች በርዕሰ ጉዳዩ ላይ በተካሄዱ ተመሳሳይ ጥናቶች ምን ይመስሉ ይሆን? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ፣ በዓለም ባይቻል ቢያንስ ከአፍሪካ ሀገሮች የተወሰኑትን መቃኘት ተገቢ ስለነበር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 2.2.3. በአፍሪካ በለቅሶ ቃል-ግጥሞች ላይ የተካሄዱ ጥናቶች ቅኝት

በአፍሪካ የለቅሶ ቃል-ግጥሞችን ከስነቃል ጥናት ሥራዎቻቸው አንድ አካል በማድረግ፣ Finnegan (1970) እና Okpewho (1992)፤ የአንድ ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ላይ አትኩረው ጥናት በማድረግ፣ Nketia (1955)፣ Alembi (2002) እና Sanka Confidence (2010) ይጠቀሳሉ፡፡ Finnegan እና Okpewho የአፍሪካውያንን ስነቃሎች መርምረው በመጽሐፍ መልክ ሲያዘጋጁ፣ የለቅሶ ቃል-ጥሞችንም ቦታ ሰጥተው ተመልክተዋቸዋል፡፡ ለምሳሌ Finnegan (1970፣145-166)፣ በአፍሪካ በሞት ላይ የሚገጠሙ ቃል-ግጥሞችን ጭብጥ በጥቅሉ መርምረው የሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ደርሰዋል፡፡ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች አካዳሚያዊ ትኩረት እንዳልተሰጣቸው፣ ከሌሎች ቃል-ግጥሞች ጋር ሲነጻጸሩ ክወናዊ መከሰቻቸው ዝቅተኛ እንደሆነ፣ ከዋኞቹም ተክህኖ እንደሌላቸውና፣ ለሴቶች ብቻ እንደተተው፣ በግኝትነት ገልጸዋል፡፡

የአብኔል ማሕበረሰብን የለቅሶ ቃል-ግጥሞች የመረመሩት Alembi (2002፣52-53)፣ የFinnegan ግኝቶች በትክክለኛ መረጃዎች ላይ የተመሰረቱ አለመሆናቸውን ራሳቸው ካጠኑት ማሕበረሰብ መረጃዎችን እየጠቀሱ ያስረዳሉ፡፡ ፊኔጋን በቤተመጻሕፍትና በቤተመዛግብት መረጃዎች ላይ ተመስርተው ጥናታቸውን ማካሄዳቸው፣ በእነዚህ ላልተካተቱ ክወናዎችና መረጃዎች፣ ግንዛቤ እንዳይኖራቸው እንዳደረጋቸውና ወደተሳሳተ ድምዳሜ እንደመራቸውም ይገልጻሉ፡፡

ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADDIS ABABA, ETHIOPIA

በእርግጥም ለጥናታቸው የአካንን ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች በመረጃነት ተጠቅመው ግኝቶቻቸውን ለአጠቃላይ የአፍሪካ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ማድረጋቸው ወደተሳሳተ ድምዳሜ እንደመራቸው፣ በቃል-ግጥም ክወናዎቹ የቀረቡት የዚህ ጥናት ግኝቶችም ያመለክታሉ።

Okpewhoም (1992፣156)፣ የዘመድና ጓደኛ ሞት በሀዘንተኞቹ ላይ ተስፋ ከመቁረጥ፣ በጸጋ እስከመቀበል የሚደርሱ ስሜቶችን እንደሚፈጥር ገልጸው፣ አብዛኛው የአፍሪካ ሕዝብ እነዚህን ስሜቶች በሙሾ ቃል-ግጥሞቹ አማካይነት በቀብር ላይ እንደሚገልጽ ያስረዳሉ። በተለያየ ባሕልና እምነት ውስጥ ያለውን ሰፊውን የአፍሪካ ማሕበረሰብ ትተን፣ ይህ ጥናት በተካሄደበት አካባቢ የሚኖረውን ማሕበረሰብ ብንመለከት እንኳ፣ የእስልምናና የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች በቀብር ላይ የሙሾ ቃል-ግጥሞችን አይከውኑም። በመሆኑም Okpewhoም እንደ Finnegan የተወሰኑ የአፍሪካ ማሕበረሰቦችን የለቅሶ ሥርዓቶችና ቃል-ግጥሞች ጠቅለል ባለ መንገድ በማየት፣ ግኝታቸውን የሁሉም የአፍሪካ ማሕበረሰቦች ባህሪ አድርጎ የመውሰድ ድክመት ይታይባቸዋል።

ከዚህ በላይ እንዳየናቸው ከሌሎቹ የስነቃል ዘውጎች ጋር ሳይሆን፣ የለቅሶ-ቃልግጥሞችን ራሳቸውን አስችለው በአንድ ማሕበረሰብ ላይ ካጠኑት አፍሪካውያን ውስጥ፣ Nketia (1955) ይጠቀሳሉ። እኚህ ተመራማሪ፣ የአካንን የለቅሶ ቃል-ግጥሞች፣ የመከወኛ አጋጣሚዎች፣ ማህበራዊ ፋይዳ፣ ጭብጥ፣ ስነልሳናዊ፣ ስነጽሑፋዊና ሙዚቃዊ ገጽታዎች፣ በመረጃዎች ላይ ተመስርተው በጥልቀት መርምረዋል። የዚህን ጥናት ብስለት Finnegan (1992፣145) ሲገልጹ፣ ‹‹ሌሎች የተሻሉ ጥናቶችን ለማካሄድ በማነሳሳት የሚያገለግል›› ብለውታል።

የNketia ጥናት ከFinneganና ከOkpewho ጥናቶች በጊዜ ቀዳሚ ቢሆንም፣ በአሰራር የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል። ለዚህ ደግሞ፣ በአንድ ማሕበረሰብና በለቅሶ ቃል-ግጥሞች ላይ ማተኮሩና የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹን በጥልቀት መርምሮ፣ ግኝቶቹን በመረጃዎች አስደግፎ ማቅረቡ ለአብነት ይጠቀሳል። Alembi (2002፣30) እንደሚገልጹት፣ ከ1960ዎቹ እስከ80ዎቹ በነበሩት ዓመታት ውስጥ በዘርፉ የነበረው የዕውቀት መንፈስ፣ ስነቃሎቹን በሀገር በቀል ቋንቋዎች ለቅረሳ ተግባር መሰብሰብ ላይ ያተኮረ ነበር። Nketia ከዚህ ባለፈ የቃል-ግጥሞቹን ክወናና ማሕበራዊ ፋይዳ፣ የሚያነሷቸውን ጭብጦችና፣ የቴክስቶቹን ስነልሳናዊ መዋቅር መተንተናቸው፣ በዘመኑ ከነበሩት

አጥኚዎች የቀደሙ ሊያስብላቸው ይችላል፡፡ Nketia ለአፍሪካ ፎክሎር እድገት አስተዋጽኦ ካደረጉት ተመራማሪዎች ውስጥ አንዱ መሆናቸውንም፣ Alembi (2002፣30) ይገልጻሉ፡፡

ከNketia በኋላ የአንድን አፍሪካዊ ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች በተሻለ ዘዴና በጥልቀት በመመርመር Alembi (2002) ይጠቀሳሉ፡፡ ተመራማሪው ስነቃል የአብኖል ማሕበረሰብ ስለሞት ያለውን አመለካከትና ግንዛቤ እንዴት እንደሚያሳይ በመረጃዎች አስደግፈው ለማቅረብ፣ አራት ዘርፎች ላይ ጥልቅ ትንተና ማካሄዳቸውን Sanka Confidence (2010፣19-20) ያስረዳሉ፡፡ እነሱም፡- በለቅሶ ቃል ግጥሞቹ ውስጥ የተጠቀሱ የማህበረሰቡ ማህበረ-ባሕላዊ የሞት መንስኤዎች፣ ሞት በግለሰብና በማሕበረሰብ ላይ የሚያስከትለው ውጤት፣ የክወናዎቹ ገለጻና የለቅሶ-ቃልግጥሞች ጥበባዊ ገጽታዎች ፍከራ ናቸው፡፡

አጥኚው የጥናታቸውን ውጤት በሰበሰቧቸው መረጃዎች ላይ እንዲመሰረት ማድረጋቸውና፣ የትንተናና የፍከራ ስራቸውንም በተጠኚው ማህበረሰብ ባህል ላይ እንዲወሰን ማድረጋቸው፣ በጠንካራ ጎንነቱ ይጠቀሳል፡፡ ምክንያቱም የአፍሪካ ስነቃል ጥናት በአፍሪካውያን በራሳቸው በዳበረ ትውር ባለመመርመሩ፣ በአውሮፓ ማሕበረሰቦች ላይ በተካሄዱ የመስክ ሥራዎች በተመሰረቱ ግኝቶችና ግንዛቤዎች እንዲታይ ያደረገው መሆኑን Nandwaን (1992) ዋቢ በማድረግ ያስረዳሉ፡፡ በዚህ መንገድ የተፈጠሩ የተዛቡ አመለካከቶችን ፈር ለማስያዝም ሆነ፣ የስነቃሎቹን ትርጉም በሚጠቀምባቸው ማህበረሰብ ግንዛቤ መሰረት ለመስጠት፣ Alembi ተገቢ መንገድ ተከትለዋል ለማለት ይቻላል፡፡

Sanka Confidence (2010) በዶክትርና ማሟያ ጥናታቸው፣ በላይኛው ምዕራባዊ ጋና የሚኖረውን የሲሳላ ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥም እሴቶች፣ እምነቶች፣ ክወናዎችና ጥበባዊ አቀራረቦች፣ የAlembiን ፈለግ በመከተል መርምረዋል፡፡ ለተጠኚው ማሕበረሰብ ባህላዊ እምነቶች፣ ክወናዎችና፣ የአኗኗር ዘይቤ ለውጦች፣ የክርስትናንና የእስልምናን ሀይማኖቶች እንዲሁም የምዕራባውያንን ትምህርት፣ በምክንያትነት ጠቅሰዋል፡፡ ለውጥ የስነቃሎቹም ሆነ የክወናዎቹ ሊገታ የማይችል ባህሪ ለመሆኑ ቦታ የሰጡ አይመስሉም፡፡

ከዚህ በላይ ከተቃኙት ጥናቶች፣ የአፍሪካ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ጥናት እያለፈ የመጣባቸውን ሂደቶች በገረፍታ እንደሚከተለው ያመለክታሉ። የአንድን ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ከተለያየ አቅጣጫ መመርመር በ1950ዎቹ በንክትያ ቢጀመርም፣ ከ1960ዎቹ የBabalola ተቀራራቢ ሙከራ ውጪ፣ ሌሎች ጎልተው የወጡ ጥናቶች አልታዩም። ከዚህ ይልቅ በ1970ዎቹ መጀመሪያ ላይ በFinnegan እንደተደረገው፣ የተወሰኑ ማህበረሰቦችን የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ጉልህ ባህርያት በመዳሰስ የሁሉም የአፍሪካ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ባህሪ ለማድረግ ሲሞከር ታይቷል። ከFinnegan ጥናት ከ20 ዓመታት በኋላ በ1990ዎቹ መጀመሪያ በተካሄደው በOkpewho ጥናትም፣ ብዙም የተለየ አዲስ ነገር አልታየም። እንደFinnegan የNketiaን ሥራ በምሳሌነት እያነሱ ከማቅረብና በተወሰኑ የአፍሪካ ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ጥናት ግኝት ላይ ተመስርቶ ሰፊ ድምዳሜ ላይ ከመደረሱ ውጭ፣ ለዘርፉ አዲስ ፈር ቀዳጅ የአጠናን ዘዴ የማሳየት ፍንጭ አይታይም።

የአፍሪካ የለቅሶ ቃል-ግጥም ጥናት ከፍተኛ እመርታ ያሳየው ከOkpewho ጥናት ከ20 ዓመታት በኋላ በተካሄደው የAlembi ጥናት ነው ለማለት ይቻላል። ምክንያቱም እኒህ ተመራማሪ፣ ምዕራባውያን ተመራማሪዎች በአፍሪካ ስነቃሎች ላይ ያካሄዷቸውን ጥናቶች በሰፊው ከመረመሩ በኋላ፣ ተመራማሪዎቹ የራሳቸውን ስነቃሎች መሰረት አድርገው ያዳበሯቸው ትውሮችና ያወጧቸው መስፈርቶች የአፍሪካን ስነቃል ምርምር ወደተዛባ መደምደሚያ እየመሩት መሆኑን በመገንዘብ፣ ችግሩን የሚያቃልል አዲስ መንገድ በመጥረጋቸው ነው። ይህም የአፍሪካ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ጥናት በተጠኚው ማህበረሰብ ባህልና በመረጃዎቹ ላይ ተመስርቶ በሚዳብር ትውር እንዲካሄድ በር ከፍቷል። ከዚህም በተጨማሪ፣ የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ የተለያዩ ገጽታዎቻቸው በጥልቀት ተመርምሮ ወደሚተረጎሙበት ምዕራፍ እንዲሸጋገር አድርጎታል። ስለሆነም፣ ተደጋግሞ እንደተጠቀሰው፣ ምንም እንኳ በአፍሪካ ለለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ሰፊ አካዳሚያዊ ሽፋን በመስጠቱ በኩል ብዙም መሻሻል ባይታይም፣ በጥናት ዘዴው ዙሪያ እየታየ ያለው ያሰራር ብስለት፣ የዘመኑ የጥናት ሳይንስ ወደሚጠይቀው ዘዴ እየቀረበ መሆኑን ያሳያል።

በመሆኑም በዚህ ጥናት እንደFinneganና Okpewho የተወሰኑ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ በጥናቱ ላልታዩት ሁሉ ማጠቃለያ ለመስጠት መሞከር ወደተሳሳተ ድምዳሜ እንደሚወስድ

ግንዘቤ በመጨበጡ፣ እንደ Nketia፣ Alembi እና Sanka Confidence አንድ ማሕበረሰብ ላይ ተተኩሯል፡፡ እንዲህም ሆኖ እንደNketia የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ጭብጦችና ሥነልሳናዊ ቅርጾች አይታዩም፡፡ እንደAlembi እና እንደSanka Confidence መረጃዎቹ ተጠኚው ማሕበረሰብ በሚሰጣቸው ትርጉም መሰረትነት የተተነተኑና የተፈከሩ ቢሆንም፣ በሁለቱ አጥኚዎች ትኩረት ያልተሰጣቸውን የለቅሶ ሥርዓቶችና የሀዘን መግለጫ ልማዶች ይጨምራል፡፡

ከዚህ በላይ በተካሄዱት የተዛማጅ ጥናት ቅኝቶች በኢትዮጵያ ከተካሄዱት ይልቅ በአፍሪካ በተካሄዱት ጥናቶች ከዘመኑ ሳይንሳዊ የአጠናን ዘዴ ጋር የተጣጣሙ አሰራሮች መታየታቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት ከሀገር ውስጥም ሆነ ከአፍሪካ ጥናቶች ጠንካራዎቹን በመውሰድና ከዘመኑ ሳይንሳዊ የጥናት ዘዴ ጋር በማጣጣም ከላይ የተጠቀሱትን ክፍተቶች ለሰሙላት ጥረት ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ የተገለጹትን የንድፈ ሀሳብ መነሻዎች መሰረት በማድረግ፣ በተዛማጅ ጥናቶቹ የተጠቆሙትን ክፍተቶች ለመሙላት እንዲቻል፣ መረጃዎቹን እውቀቱ ካላቸው የባህሉ ባለቤቶች በተገቢዎቹ ዘዴዎች መሰብሰብን የግድ ይል ነበር፡፡ በሚከተለው ምዕራፍ መረጃዎቹ ከእነማን፣ በምን በምን ዘዴዎች እንደተሰበሰቡና በምን መንገድ ተደራጅው ለትንተና እንደተዘጋጁ የተብራራበት የጥናቱ ዘዴ ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. የአጠናን ዘዴ (Research Methodology)

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ሞዴል (research paradigm)፣ የጥናቱ ዘዴ (research methodology)፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (data collection methods)፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች (data collection instruments)፣ የመረጃ አቀባዮቹ አመራረጥ (informant selection)፣ የመረጃው አደረጃጀትና የትንተናው ዘዴ (data organization and analysis methods) ተካትተዋል። ሁሉም በቅደም ተከተላቸው መሰረት ቀጥሎ ቀርበዋል።

### 3.1. የጥናቱ ሞዴል (research Paradigm)

ይህ ጥናት አይነታዊ ምርምር (qualitative research) ነው። አይነታዊ ምርምር ከሚከተላቸው ሞዴሎች ውስጥ ለዚህ ጥናት ተገቢ ሁኖ የተገኘው የማሕበራዊ ትርጉም ግንባታ ሞዴል (Social constructivism paradigm) ነው። ሞዴሉ የተመረጠው ለጥናቱ የሚሰበሰቡት ባሕላዊ መረጃዎች ትርጉም የሚገኘው ከባሕሉ ባለቤቶች እንደሆነ ስለታመነ ነው። Given (2008፣816) እንደሚያስረዱት፣ በዚህ ሞዴል አመለካከት ዕውቀትም ሆነ እውነታ ከማሕበረሰብ ተራክቦ የሚመነጭ፣ በግለሰቦች አመለካከት ላይ የተመሰረተና ሊለዋወጥ የሚችል ነው። Crottyን (1998) ዋቢ አድርገው Creswell (2002፣21) እንደሚገልጹትም፣ የማሕበራዊ ቡድኖች ተራክቦ መሰረታዊው የትርጉም መፈጠሪያ ተደርጎ ይወሰዳል።

Jaccard እና Jacob (2010፣9) እንደሚያስረዱት፣ በማሕበራዊ ትርጉም ግንባታ ሞዴል አመለካከት፣ እውነታ በአንድ የተወሰነ ማህበራዊ አውድና ጊዜ ላይ ተመስርቶ የሰው ልጅ አዕምሮ የሚፈጥረውና፣ በማሕበራዊ አውድ ምክንያት ሊለያይ የሚችል ነው። ከዚህም በተጨማሪ፣ በዚህ ሞዴል መርህ ተመራማሪውና መረጃ አቀባዮቹ በትርጉም ግንባታ ሂደቱ ውስጥ ተደጋግፈው መስራት እንደሚጠበቅባቸው ይታመናል። ስለሆነም፣ ተጠኚው ማሕበረሰብ በሞት መከሰት ምክንያት ከሚፈጥራቸው ተራክቦዎች የሚመነጩትን የመረጃ ትርጉሞች በማሕበረሰቡ እይታ ለመተርጎምና ለመፈከር ይህ ሞዴል ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል።

## 3.2. የጥናቱ ዘዴ (Research method)

ለማህበራዊ ሳይንስ በጥናት ዘዴነት ከሚያገለግሉት ውስጥ ለዚህ ጥናት፣ ክስተታዊ (phenomenology) እና የመሰረተ-ሀሳብ ትውሮች (grounded theory) ቀረቤታ ያላቸው ሆነው ተገኝተው ነበር። ሆኖም ግን፣ የእያንዳንዳቸው ግብ ከዚህ ጥናት ግብ የሚያፈነግጥ በመሆኑ ተትተዋል። ለምሳሌ Denscombe (2007፥80) እንደሚያስረዱት፣ የክስተታዊ ዘዴ የመጀመሪያም ሆነ የመጨረሻ ግብ፣ የተጠኚዎቹን የየዕለት ተጨባጭ ባህርያት እየተከታተሉ መግለጽ እንጂ፣ እነዚያ ባህርያት ለምን እንደሚደረጉ ምክንያታቸውን መተንተን አይደለም። የመሰረተ-ሀሳብ ትውርም፣ በመስክ በሚሰበሰቡ መረጃዎች ግኝት ላይ ተመስርቶ ትንተናውን ለማካሄድና ከመረጃዎቹ የመነጨ ትውር ለማዳበር ማስቻሉ ተመራጭ ቢያደርገውም፣ ሳያቅዱ ወደመስክ መግባትን የሚያበረታታ መሆኑ፣ ለዚህ ጥናት እንዳይመረጥ አድርጎታል። ምክንያቱም፣ በዚህ ጥናት ወደመስክ የተገባው አዲስ ትውር ለማዳበር ሳይሆን፣ ከንባብ፣ ከተመሳሳይ ጥናቶችና ከልምድ በተገኘ እውቀት፣ ምን ምን መረጃዎች፣ በምን ዘዴዎችና እንዴት መሰብሰብ፣ መደራጀትና መተንተን እንዳለባቸው ታቅዶ ነው። ወደዚህ አማራጭ እንዲገባ ለጥናቱ የተመደበው በጀት የመስክ ቆይታው ላይ የፈጠረው ተጽዕኖ በዋናነት ይጠቀሳል።

ከእነዚህ ይልቅ ከማሕበራዊ ትርጉም ግንባታ ሞዴል፣ ከክወና ትውርና ከመሰረተ ባሕል የመረጃ መተንተኛ ሞዴል ጋር ተጣጥሞ በመሄድ፣ ኢትኖግራፊያዊ የምርምር ዘዴ (ethnography research method) የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል። ምክንያቱም፣ Krüger (2008፥18) እንደሚያስረዱት፣ በአይነታዊ ምርምር የቡድኖችን የጋራ ባሕል ለመመርመር የኢትኖግራፊ የምርምር ዘዴ ተዘውትሮ ይሰራበታል። Given (2008፥288) እንደሚገልጹትም፣ ይህ ዘዴ የባህል ፍከራ ተመራማሪዎቹ ያዩትንና የሰሙትን በተጠኚው ማሕበረሰብ ማህበራዊ አመለካከት የመግለጽ ችሎታን ያካትታል። በተጨማሪም፣ Hammersleyን እና Atkinsonን (1995) ዋቢ በማድረግ Bryman (2001፥XI)፣ Savage (2006፥385) እንደሚገልጹት፣ በተጠኚዎቹ መካከል ለረዥርም ጊዜ ተገኝቶ የሚጠናውን ባህል በእለት ከእለት ሕይወት እየተከወነ ባለበት ተፈጥሯዊ አውድ በተሳታፊነት እየተመለከቱ፣ ተጠኚዎቹ የሚያደርጉትንና የሚናገሩትን በመቅረጽ፣ እየተደረገና እየተነገረ ያለውን በቀጥታ ለመግለጽ ስለሚያስችል፣ የጥናት ዘዴው ተመርጧል።

እንደGoldbart እና Hustler (2005፣16) ገለጻ ደግሞ፣ ኢትኖግራፊያዊ ምርምር በባህሪው በሰዎች (ተጠኚዎች/ ትርጉም ፈጣሪነት ዙሪያ ስለሚሽከረከር፣ ተጠኚዎቹ የሚኖሩበትን ዓለም እንዴት እንደሚተረጉሙት መረዳት ላይ ስለሚያተኩርና፣ ሰዎች ፈጥረው የሚጠቀሙበትን አንድ የባህል ዓለም መረዳትን ስለሚጠይቅ፣ የደቡብ ጎንደር ዞን የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ማህበረሰብ በሞት መከሰት ዙሪያ ስለሚያከናውናቸው ሥርዓቶችና ከሱ ጋር አያይዞ ስላዳበራቸው ልማዶች ምንነት ለመረዳት ስለሚያስችል፣ ዘዴው ተመርጧል፡፡ የሚከተሉት መሰረታዊ ባሕርያቱና ጠቀሜታዎቹም፣ ዘዴው እንዲመረጥ ካደረጉት ምክንያቶች ውስጥ ይጠቀሳሉ፡፡

ሀ. መረጃውን ከሚያውቁት ሰዎችና ከሚገኝበት ቦታ ድረስ በመሄድ በመስክ የቀጥታ ምልከታ ከቀዳማይ ምንጮች ለመሰብሰብ የሚያስችል ተጨባጭ የምርምር ዘዴ ነው (Denscombe፣2007) እና (Whitehead፣2005፣4)፡፡ የተጠኚዎቹ ድርጊቶችና ማብራሪያዎች ተመራማሪው በሚያመቻቸው አውድ ሳይሆን በዕለት ተዕለት ክንውናዊ አውዳቸው ይጠናሉ (Hammersley እና Atkinson፣2007)፡፡

ለ. በሚሰበሰቡት መረጃዎች ላይ ተመስርቶ ትውርን ለማዳበርም ሆነ ለመሞከር በመሳሪያነት ያገለግላል (Denscombe፣2007)፡፡

ሐ. በአንጻራዊነት በዝርዝርም ሆነ በጥልቀት የበለጸገ መረጃ ያስገኛል፡፡ ውስብስብና ረቂቅ እውነታዎችን ለመመርመር ያስችላል (Denscombe፣2007) ኢትኖግራፊ የባህልን ሥርዓት ለማጥናት ምሉዕ አንጻር ነው (Whitehead፣2005፣4)፡፡

መ. ከድርጊቶች ውጫው ገጽታ ጀርባ ሂደቶችና ግንኙነቶች ላይ አትኩሮ አጠቃላይ (h*olistic*) ማብራሪያ የመስጠት ጉጉት ይታይበታል፡፡ የነገሮችን ዝርዝር በተናጠል ጽንሰ ሀሳባዊ ከማድረግ ይልቅ፣ በአውድ ያስቀምጣቸዋል (Denscombe፣2007)፡፡ ኢትኖግራፊ የባህል ሥርዓትን ከውስጣዊ (emic) እና ከውጫዊ (etic) አስተያየቶች አንጻር ማጥኛ ነው፡፡ የማህበረ- ባሕላዊ አውዶች፣ የሂደቶችና የትርጉሞች ጥናት ነው (Whitehead፣2005፣4)፡፡

ሠ. ኢትኖግራፊያዊ ምርምር የባህሉ ባለቤቶች ነገሮችን በሚያዩበት ዓይን ለመመርመር በጣም ተስማሚ ነው፡፡ አጥኚው የሚመረምረውም ሆነ የሚገልጸው፣ የባህሉን ባለቤቶች የጠለቀ አስተሳሰብ ነው (Denscombe፣2007)፡፡ ኢትኖግራፊ የሰው ልጅ የዳበረ አውዳዊ ገጠመኝ በራሱ በባለቤቱ ዓለም የሚገለጽበትና የሚቀርብበት ጥናት ነው (Whitehead፣

2005፣4)።

ረ. ስነምህዳርን ባለማወክ በኩል ጥንካሬ ይታይበታል። ምርምሩ ነገሮች በተፈጥሯዊ መቸታቸው ከሚከወኑበት እንዳይወጡ የሚፈጥረው ጫና አናሳ እንዲሆን ያደርጋል።

ከዚህ በላይ በተገለጹት ጠቀሜታዎቹ የተመረጠው ኢትኖግራፊያዊ የጥናት ዘዴ፣ ከተጠኚዎቹ ጋር እ.ኢ.አ ከሚያዝያ 2004 እስከጥር 2006 ዓ.ም ባለው የጊዜ ክልል፣ ሶስት ጊዜ በተደረገ መደበኛ የመስክ ጉዞ ለሶስት ወር ከአስራ አንድ ቀናት ያህል አብሮ በመኖር ሞት ሲከሰት የሚፈጽሟቸውን ሥርዓቶችና የሚከውኗቸውን ቃል-ግጥሞች በተፈጥሯዊ መቼታቸው ከነትርጉሞቻቸው ለመሰብሰብ ተችሏል።

3.3. የጥናቱ አካባቢና የመረጃ አቀባዮች አመራረጥ

ጥናቱ በደቡብ ጎንደር ዞን መካኼዱ በመግቢያው ክፍል ተገልጿል። ይህ ዞን የተመረጠው በአመቺ የንሞና ዘዴ ነው። ጥናቱ ባህላዊ ትዕምርቶችን ፈልፍሎ ማውጣትንና የእርስበርስ ትስስራቸውን ማሳየትን ስለሚሻና አጥኚው አካባቢውን ከሌሎቹ ዞኖች በተሻለ ስለሚያውቀውና፣ ካለፈባቸው የመስክ ተሞክሮዎች ፎክሎርን በሚያውቁት ባህል ብቻ ሳይሆን፣ በሚታወቁበት አካባቢ ማጥናት የጎላ ጠቀሜታ ስላለው ተመርጧል። ለመስክ ሥራው በታቀደው ጊዜና በተመደበው በጀት ከሁሉም በዞኑ ከሚገኙ አስራ አራት ወረዳዎች መረጃ ለመሰብሰብ ስላልተቻለ፣ ከእነዚህ መካከል አምስት ወረዳዎች በታላሚ ናሙና ተመርጠዋል። ደብረታቦር ዙሪያና ፋርጣ ወረዳዎች የዞኑ ማዕከል በመሆናቸው፣ በአንድ በኩል በዞኑ የሚገኙ ነዋሪዎችን የሚወክሉ፣ በሌላ በኩል ከተሜውንና ገጠሬውን ያካተቱ የማህበረሰብ ክፍሎችን፣ ከሌሎች ወረዳዎች በተሻለ አቅፈው እንደሚገኙ በመታመኑ ተመርጠዋል። ሌሎቹ ሶስት ወረዳዎች የተመረጡት የቆላና ደጋ የአየር ንብረትን መሰረት በማድረግና ከኩታ ገጠም ወረዳዎች አንዱን በመውሰድ ነው።

ማንነትን የሚገልጽ ደብዳቤ ከዩኒቨርሲቲው በመያዝ ወደቦታው ከተሄደ በኋላ ከዞን አስተዳደር ለባህልና ቱሪዝም፣ ለመንግስት ኮሙኒኬሽን፣ ለፖሊስ መምሪያዎችና ለዞኑ ሀገረ ስብከት ጽሕፈት ቤት የትብብር ደብዳቤዎችን በማስጻፍ በየአድራሻቸው የማድረስና ግንኙነት የመፍጠር ሥራ ከተሰራ በኋላ፣ ከየመምሪያዎቹ ወደተመረጡት ወረዳዎች ደብዳቤዎችን የማድረስ፣

ግንኙነት የመፍጠርና በርዕስ ጉዳዩ ዙሪያ በየጽሕፈት ቤቶቻቸው የሚገኙትን መረጃዎች የመሰብሰብ ሥራ ተከናውኗል፡፡ ከሚመለከታቸው ሰራተኞች ጋር በመመካከርም መረጃ አቀባዮችን የማፈላለግም እንደዚሁ፡፡

ወደመስክ ሲገባ ለቁልፍ መረጃ አቀባዮች አመራረጥ ልዩ ትኩረት ተሰጥቷል፡፡ Tolken (1996፣348-49) እንደሚገልጹት፣ በፎክሎር ጥናት ከመረጃ ሰብሳቢው ወይም ተመራማሪው በላይ ለጥናቱ ቁልፉ ሰው መረጃ አቀባዩ ነው፡፡ ምክንያቱም መረጃ አቀባዩ የሚፈለገውን መረጃ በተሟላ መንገድና በትክክል ካላቀበለ፣ መረጃ ሰብሳቢውም ሆነ ተመራማሪው ምንም ያህል ጠንካሮች ቢሆኑ ጥናቱን ከእንከን ሊታደጉት አይችሉም፡፡ Tolken አክለው እንደሚገልጹት፣ መረጃ አቀባዮች የተሟላና አስተማማኝ መረጃ ባለቤቶች ከመሆናቸው በተጨማሪ፣ ለአጥኚው የካበተ እውቀት ያላቸው ባልደረቦቹ፣ የባህል ተንቀሳቃሽ ቤተመጻሕፍቱና መረዳት ለሚፈልገው እንግዳ ሀሳብ የመጀመሪያ ደረጃ ምንጮቹ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ Goldbart እና Hustler (2005፣89) እንደሚያስረዱት፣ መረጃ አቀባዮች በጥናቱ ሂደት እንደአስተማሪና መሪ በመሆን ጠቃሚ ሚና ይጫወታሉ፡፡

እንዲህ አይነት ቁልፍ መረጃ አቀባዮችን የማግኘቱ ሥራ ቀላል አልነበረም፡፡ Bernard (2006፣146)፣ Luisና ሌሎችም (2007፣180)፣ ትክክለኛ መረጃ አቀባዮችን መምረጥ በምርምር የጎሉ ችግሮች ተብለው ከሚጠቀሱት ውስጥ አንዱ እንደሆነ ያስገነዝባሉ፡፡ አንድን ባህል በትክክል የሚያንጸባርቁ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ስለዚያ ባህል ተክህኖ ያላቸውን (professional) መረጃ አቀባዮች ማግኘትን ይጠይቃል፡፡

Bernard (2006፣189-191) እንደሚያስገነዝቡት፣ ተክህኖ ያላቸውን የባህል መረጃ አቀባዮችን ለመምረጥ፣ እድል የማይሰጥ የንሞና ዘዴ (non probability sampling) አካል የሆነው ታላሚ ናሙና (purposive sampling) ዘዴ ተገቢነት አለው፡፡ ሌሎች ተመራማሪዎችም በዚህ ሀሳብ ስለሚስማሙበት፣ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች የተመረጡት በታላሚ ናሙና ዘዴ ነው፡፡ ምክንያቱም ባህላዊ መረጃ ለመሰብሰብ የሚፈለገው መረጃ አቀባይ፣ ስለባህሉ ጥልቅ እውቀት ያለው (expert) እንጂ፣ በዘፈቀደ ንሞና የተመረጠ መላሽ (respondent) አይደለም፡፡

መረጃ አቀባዮቹን ለመምረጥ ከላይ እንደተገለጸው ከየወረዳዎቹ ባህል ልማት ባለሙዎች ጋር በመወያየት ባሕላዊ እውቀቱ ያላቸውን በጣም ታዋቂ ግለሰቦች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና፣ የለቅሶ

ቃል-ግጥም ከዋኞች፣ የመለየት ሥራ ተከናውኗል። ለእነዚህ ሰዎች የጥናቱን ዓላማ በመንገር ፈቃደኝነታቸው ተገኝቶ ወደሥራው ሲገባ፣ በሙያ ጓድ ጥቆማ (snowball sampling) ሌሎች እውቀቱ ያላቸውን ባለሙያዎች እንዲጠቁሙ በማድረግ፣ ተጨማሪ መረጃ አቀባዮችን የማካተት ሥራም ተከናውኗል። ከዚህም በተጨማሪ በለቅሶ ሥርዓት ክወናዎች ላይ በመገኘት ጥሩ ችሎታ ያላቸውንና በተደጋጋሚ ሲከውኑ የተገኙትን የመምረጥና ከቁልፍ መረጃ አቀባዮቹ ውስጥ የማካተት ሥራ ተከናውኗል። በእነዚህ መንገዶች የተገኙት መረጃ አቀባዮች የሚፈለገውን ባሕላዊ መረጃ ለመስጠት ተገቢ ሰዎች መሆናቸውን ለማረጋገጥም፣ ስለችሎታቸው ሌሎች ሰዎችን በመጠየቅ የማጣራት ሥራ ተሰርቷል። በተለይ የለቅሶ ቃል-ግጥም ከዋኞች ርስበርስ ስለሚተዋወቁ፣ አንቱ የተባሉ መረጃ አቀባዮችን በመምረጡ ሥራ ጉልህ ሚና ተጫውተዋል። ቁልፍ መረጃ አቀባዮቹ በዚህ መንገድ ከተመረጡ በኋላ፣ ተገቢዎቹን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የመምረጡ ሥራ በሚከተለው መንገድ ተካሂዷል።

### 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለጥናቱ ተገቢ የሆኑ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ለመምረጥ፣ በጥናቱ ዘዴና በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ መካከል ያለው ትውራዊ ትስስርና፣ ዘዴው መረጃዎቹን ለማስገኘት የሚኖረው ፋይዳ፣ ሊተኮርባቸው እንደሚገባ የዘርፉ ባለሙያዎች ያስገነዝባሉ። ለምሳሌ Jaccard እና Jacoby (2010፣463) እንደሚገልጹት፣ የጋራ ባህል ያላቸውን ቡድኖች ባህሪ፣ እምነትና ቋንቋ በኢትኖግራፊያዊ የምርምር ዘዴ ለማጥናት፣ ምልከታና ቃለ መጠይቅ የተለመዱና ተቀባይነት ያላቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ናቸው። Denscombe (2007፣134) እንደሚያስረዱትም፣ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን መጠቀም፣ መረጃዎቹን ከተለያየ አቅጣጫ ለማየት ከማስቻሉም በተጨማሪ፣ እያንዳንዱ ዘዴ የየራሱ ድክመትና ጥንካሬ ስላለው ይህን ክፍተት ለመሸፈን ይረዳል።

ለዚህ ጥናት የሚያስፈልጉት በክወና ላይ ያሉ የለቅሶ ሥርዓቶች፣ በሥርዓቶቹ ዙሪያ የተቀረጹ የድምጽና የምስል እንዲሁም የጽሑፍ መረጃዎች ናቸው። እነዚህን መረጃዎች በተሻለ መንገድ ለመሰብሰብ፣ ተሳትፏዊ ምልከታ (participant observation)፣ ቃለ መጠይቅ (interview)፣ የቡድን ውይይት (focus group discussion) እና ሰነድ ምርመራ (document analysis) ተመርጠዋል። እነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተመረጡት፣ ከፍ ሲል እንደተጠቆመው፣

ከጥናቱ ዘዴ ጋር ያላቸው ትውራዊ ትስስርና መረጃዎቹን ለመሰብሰብ ያላቸው ጠቀሜታ ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ ነው። የእያንዳንዳቸው ጠቀሜታ ቀጥሎ ቀርቧል።

### 3.4.1. ተሳትፏዊ ምልከታ (participant observation)

Murchison (2010፣97) እንደሚያስረዱት፣ ተሳትፏዊ ምልከታ፣ በእይታ የሚገለጹ ባሕርያትንና ልማዶችን የሚመለከቱና የሚከተሉትን ጥያቄዎች የሚመልሱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ያስችላል። የደቡብ ጎንደር ዞን የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ማሕበረሰብ ሞት ሲከሰት፣ የሚያከናውናቸው የተለያዩ ሥርዓቶች ምን ምን ናቸው? ከዚሁ ጋር አያይዞ ያዳበራቸውን ልማዶችና የሚያቀርባቸውን የለቅሶ ቃል-ግጥሞች እንዴት ይከውናቸዋል? እነዚህን ክወናዊ መረጃዎች ከነአውዳቸው በመሰብሰብ ማሕበረሰቡ በጋራ ያዳበረውን ባሕላዊ እውቀት ለመረዳት፣ ሥርዓቶቹና ቃል-ግጥሞቹ በሚከወኑበት የዕለትተዕለት ሕይወት በመገኘት በተሳታፊነት መመልከትን በመጠየቁ፣ ተሳትፏዊ ምልከታ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ተመርጧል።

Hustler (2005፣84) እንደሚገልጹትም፣ ተሳትፏዊ ምልከታ ከኢትኖግራፊያዊ የምርምር ዘዴ ጋር የጠበቀ ትውራዊ ትስስር ያለው በመሆኑ፣ ለኢትኖግራፊያዊ ምርምር በዋና መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት ያገለግላል። ምክንያቱም Murchison (2010፣97) አክለው እንደሚገልጹት፣ ተሳትፏዊ ምልከታ በክወና ላይ የሚቀርቡትን የተለመዱ ወይም ተደጋጋሚና እንግዳ ወይም የተለዩ መረጃዎችን ለማግኘት ያስችላል። Bernard (2006፣390) እንደሚያስረዱትም፣ ተሳትፏዊ ምልከታ በተቻለ መጠን ተመራማሪው የመረጃ አቀባዮቹን ሕይወት የሚካፈልበት ስለሆነ፣ የሚያደርጓቸውንና የሚናገሯቸውን መረጃዎች ለመሰብሰብ ተመራጭ ዘዴ ነው። በተጨማሪም Murchison (2010፣91) እንደሚገልጹት፣ ተሳታፊ ተመልካች (participant - observer) ከመረጃ አቀባዮቹ ጋር በአካል በመገናኘት ልምዳቸውን ይካፈላል። ይህም ባህርያቸውን፣ አስተሳሰባቸውንና ስሜታቸውን፣ አብሮ እየኖረ በልምዱ ላይ ተመስርቶ እንዲያገኝ ስለሚረዳው፣ የሚጠናውን ክስተት በቀጥታ የመረዳት አጋጣሚና እድል ይፈጥርለታል።

Bernard (2006፣347) እንደሚገልጹት፣ አንድ የመስክ መረጃ ሰብሳቢ ሶስት* ሚናዎች ሊኖሩት ቢችሉም በርካታዎቹ ኢትኖግራፊያዊ ምርምሮች የሚካሄዱት፣ በተሳታፊ ተመልካችነት ላይ ተመስርተው ነው። እኒሁ ተመራማሪ አክለው እንደሚያስገነዝቡት፣ በባህል ላይ ሳይንሳዊ ጥናት ሲደረግ፣ ተሳትፏዊ ምልከታ የሚመረጥባቸው አምስት የተገቢነት ምክንያቶች አሉ። እነሱም የሚከተሉት ናቸው።

1. ተሳትፏዊ ምልከታ በአንጻራዊነት ሁሉንም አይነት መረጃዎች ለመሰብሰብና ነገሮችን ግልጽ ለማድረግ ያስችላል።

2. ተሳትፏዊ ምልከታ ሰዎች እየተጠኑ መሆናቸውን ሲያውቁ የሚያሳዩዋቸውን ያልተለመዱ ባህርያት ይቀንሳል።

3. ተሳትፍፏዊ ምልከታ ተመራማሪው በመረጃ ሰጭው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተገቢ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ይረዳዋል።

4. ተሳትፏዊ ምልከታ ለተመራማሪው በባህሉ ውስጥ ምን እየተካሄደ እንዳለ በተሳታፊነት እንዲገነዘብ ስለሚያደርገው፣ ስለመረጃው ትርጉም በልበሙሉነት ለመናገር ያስችለዋል።

5. በርካታ የምርምር ችግሮች ከተሳታፏዊ ምልከታ ውጭ በሌላ ነገር በተሟላ መንገድ ሊቀርቡ አይችሉም።

ከዚህ በላይ ከቀረቡት ሀሳቦች ለመረዳት እንደሚቻለው፣ ተሳትፏዊ ምልከታ ለጥናቱ የሚውሉ መረጃዎችን በተፈጥሯዊ መቸታቸው በሚቀርቡበት መንገድ ከተጠኚዎቹ በቀጥታ ለማግኘት ብቻ ሳይሆን፣ ምንነታቸውንም አብሮ እየኖሩ በልምድ ለመረዳት የሚያስችል የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው። እንዲሁም ይህ ዘዴ ተመራማሪውና ተጠኚዎቹ የጋራ ቋንቋ ስለሚጠቀሙ፣ በቋንቋ ችግር የሚከሰቱ ክፍተቶችን ከማስቀረቱ በተጨማሪ፣ በእምነት ወይም በባሕል ምክንያት ሊገኙ የማይችሉ መረጃዎችን ከሌሎቹ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በተሻለ የማስገኘት ጠቀሜታ አለው።

---

* ፍጹም ተሳታፊ (Complete Participant)፣ ተሳታፊ ተመልካች (Participant observer) እና ፍጹም ተመልካች (Complete Observer) ሊሆን ይችላል።

ከዚህም በተጨማሪ ተሳትፏዊ ምልከታ፣ ለሚጠናው ነገር ተገቢ የሆኑ ቁልፍ መረጃ አቀባዮችን ለመምረጥ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ቀላል እንዳልሆነ፣ ከመስክ ቆይታው ገጠመኝ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ ከሶስት ለቅሶዎች ላይ ‹‹ወየ›› ሲሉና ሙሾ ሲያወርዱ በተከታታይ የተቀረጹት አቶ ደሳለኝ፣ የተገኙት በዚህ መንገድ ነው፡፡ እኚህ ቁልፍ መረጃ አቀባይ፣ ስለአካባቢው የለቅሶ ሥርዓትና የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ካላቸው ጥልቅ እውቀት፣ በጥናቱ ለመሳተፍ ካሳዩት ፈቃደኝነትና መረጃውን በሚገባ ለመግለጽ ካላቸው ክህሎት በላይ፣ በዞኑ አሉ የተባሉ መረጃ አቀባዮችን በመጠቆም በኩል ያበረከቱት አስተዋጽኦ ቀላል አይደለም፡፡

በዚህ የመረጃ መሰብሰቢ ዘዴ አጥኚው እ.ኢ.አ ከሚያዝያ 22/2004 እስከሰኔ 10/2004፣ ከየካቲት 2/2005 እስከመጋቢት 03/2005 እና ከጥር 2/2006 እስከ22/2006 ባካሄዳቸው የመስክ ቆይታዎች፣ በ9 የዕለት፣ በ5 የቀጠሮና በ2 የመርዶ፣ በድምሩ በ16 የለቅሶ ሥርዓቶች ላይ ተገኝቶ በተሳታፊነት በመመልከት፣ መረጃዎቹ እየተከወኑ ባሉበት ሁኔታ ለመሰብሰብ ችሏል፡፡ 1 የእለትና 1 የቀጠሮ ለቅሶ ክወናዎች በረዳት መረጃ ሰብሳቢ በሚከወኑበት መቼት እንዲቀረጹ ሲደረጉ፣ ከግለሰቦች የተገኙ 2 የዕለትና 2 የቀጠሮ ለቅሶዎች ላይ የተቀረጹ የቪዲዮና የቴፕ መረጃዎችን ጨምሮ፣ በድምር 22 የለቅሶ ሥርዓቶች ላይ የተሰበሰቡ መረጃዎች ለጥናቱ ውለዋል፡፡ ከእነዚህ የለቅሶ ሥርዓቶች ውስጥ፣ አጥኚው በሚታወቅባቸው አካባቢዎች በተካሄዱት አራት የዕለት ለቅሶዎች፣ እንደአካባቢው ነዋሪ ቀኝ እጁን አውጥቶ ኩታውን በመልበስ፣ ከሀዘንተኞቹ ጋር በመዞር በአጃቢነት ተሳትፏል፡፡ በእነዚህም ሆነ በሌሎቹ የለቅሶ ሥርዓቶች ላይ እንደአካባቢው ነዋሪ በመልበስና በሀዘን ቦታው በመገኘት፣ የአስከሬን ቃሬዛ በመሸከምና ከቤት እስከቀብር በማጀብ፣ ወየባዮችንና ሙሾ አውራጆችን ከሕዝቡ ጋር አብሮ በመቀበልና በማርገድ ተሳትፏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ የእዝን እህል ውሃ አብሮ በመቅመስና በድንኳን ውስጥ ሀዘንተኞቹን በማጽናናት ሂደቶችም ተሳትፏል፡፡ ሕመምተኛ ለመጠየቅ በሄደበት በመኪና አደጋ ሆስፒታል የገቡ አንዲት እናት ሲያርፉ በተፈጠረ ግርግር፣ ጓደኞቹ ትተውት የሄዱትን ነርስ፣ ሬሳውን በስርዓት በማስተካከል አግዟል፡፡

በዚህ መንገድ በመሳተፍ፣ በሶስቱ የለቅሶ አይነቶች የሚከወኑትን የለቅሶ ሥርዓቶችና የቃል-ግጥም ክወናዎች፣ የሚኞች ረፍት ይፋ ከተደረገበት እስከቀብር ፍጻሜ ድረስ ያለውን ሂደት በቪዲዮና ፎቶ ካሜራዎች፣ በመቅረጸ ድምጽ፣ ተከታትሎ በመቅረጽና በማስታወሻ በመታገዝ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

አጥኚው በዚህ መንገድ እየተሳተፈ በክወና የቀረቡትን መረጃዎች ለመሰብሰብ ቢችልም፣ እያንዳንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የየራሱ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ያሉት በመሆኑ፣ ተሳትፏዊ ምልከታ ብቻውን ለጥናቱ የሚያስፈልጉትን ሁሉንም መረጃዎች በተሟላ መንገድ ለመሰብሰብ አላስቻለም። ስለሆነም በምልከታ ወቅት ምንነታቸውን በውል ለመረዳት ላልተቻሉ ክወናዎች፣ ጥያቄ ላጫሩና ማብራሪያ ለሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች፣ ተገቢ የሆነ ተጨማሪ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ መጠቀም አስፈልጓል። እንዲህ አይነት ክፍተቶችን በመሙላት በኩል ቃለ መጠይቅ የጎላ ድርሻ እንዳለው በተመራማሪዎች ስለሚታመንበት ተመርጧል። ለምንና የትኞቹን መረጃዎች ለመሰብሰብ እንደተመረጠ ቀጥሎ ቀርቧል።

### 3.4.2. ቃለ መጠይቅ (interview)

ቃለ መጠይቅ፣ ተመራማሪው ማወቅ ስለሚፈልገው ነገር ቀጥተኛ ጥያቄ አቅርቦ የተጠያቂውን ግለሰባዊ ሀሳቦችና ልምዶች የሚመለከቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚችልበት የመረጃ መሰብሰቢ ዘዴ እንደሆነ Murchison (2010፣100) ያስረዳሉ። ቃለ መጠይቅ ለዚህ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት የተመረጠው ከሚከተሉት ጥያቄዎች ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በማስቻሉ ነው። የለቅሶ ሥርዓቶቹ በጊዜ ሂደት ምን ምን ለውጦችን አሳይተዋል? የእያንዳንዱ ሥርዓት ክወና በዚያ መንገድ የሚከወነው ለምንድን ነው? የሟች የቅርብ ቤተሰቦች ሀዘናቸውን እንዴት ይገልጻሉ? በዚያ መንገድ ሀዘናቸውን መግለጻቸው ምን ትርጉም ይሰጠዋል? የለቅሶ ቃል-ግጥም ከዋኞች ሙያውን እንዴት ይለምዱታል? የለቅሶ ሥርዓቶቹም ሆነ ቃል-ግጥሞቹ መከወን ለማሕበረሰቡ ምን ፋይዳ አላቸው? እነዚህና ሌሎችም በክወና ወቅት የታዩ ማብራሪያ የሚፈልጉ ጉዳዮች፣ በቃለ መጠይቅ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ለቃለ መጠይቁ የነጻና (unstructured interview) የከፊል ነጻ (Semi structured interview) የቃለ መጠይቅ አይነቶች ተመርጠዋል። Davies (1999፣94-95)፤ Hammersley እና Atkinson (2007፣117)፤ እና Bernard (2006፣211-212) እንደሚገልጹት፣ እነዚህ የቃለ መጠይቅ አይነቶች የተመረጡት በኢትኖግራፊያዊ ምርምር ዘዴ በተሳትፏዊ ምልከታ መረጃ ለሚሰበስቡ አጥኚዎች ተገቢዎች ሆነው በመገኘታቸው ነው።

ነጻ ቃለ መጠይቆቹ የተካሄዱት፣ ተጠኚዎቹ ከላይ በተጠቀሱትና ተያይዘው በተነሱት ጥያቄዎች ዙሪያ ያላቸውን ሀሳብ እንዲገልጹ በማድረግና፣ ከሚያቀርቧቸው ሀሳቦች በመነሳት ሌሎች ጥያቄዎችን በማቅረብ ከመደበኛው ንግግር ባልራቀ መንገድ ነው፡፡ በእያንዳንዱ ጥያቄ ርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ፣ ተጠያቂዎቹ ሀሳባቸውን ሳይገደቡ እንዲገልጹ ተደርጎ፣ ከሚያነሷቸው ሀሳቦች ሌሎች ጥያቄዎች እየተነሱ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ይህ ዘዴ መረጃ አቀባዮቹ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ያካበቱትን እውቀት ሳይገደቡ እንዲገልጹና፣ ገጠመኞቻቸውን ጣል እያደረጉ ዘና ብለው ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ በማድረግ ተገቢ መረጃዎችን ለማግኘት አስችሏል፡፡

በከፊል ነጻ ቃለ መጠይቆቹ፣ በምልከታ ወቅት የታዩ ትዝብቶች፣ ግልጽ ያልሆኑ ነገሮችና፣ ማብራሪያ የሚፈልጉ ሌሎች ጉዳዮችም ሲያጋጥሙ፣ በእነዚህ ዙሪያ አስቀድመው የተዘጋጁትን ጥያቄዎች በቅደም ተከተል በማቅረብ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ተጠያቂዎቹ የቀረበላቸውን ጥያቄ ሳይገደቡ እንዲመልሱ እድሉ ተሰጥቷቸዋል፡፡ መልሰው ሲጨርሱ የሚቀጥለው ጥያቄ እንዲቀርብ ከመደረጉ ውጭ ከመልሶቻቸው በመነሳት ሌሎች ጥያቄዎችን ለማቅረብ አልተሞከረም፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች መረጃ አቀባዮቹ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን የጋራ ባሕላዊ እውቀት የሚመለከቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አስችለዋል፡፡

የቃለ መጠይቅ መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በምልከታው በተገለጹት የጊዜ ክልሎች ውስጥ ከ42 ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ሲሆን፣ ከአንዷ በስተቀር ሁሉም ወንዶች ናቸው፡፡ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ሴቶችን* ለማካተት ጥረት ቢደረግም፣ ለመረጃዎቹ ካላቸው ርቀት የተነሳ፣ ከአንዷ በስተቀር፣ ቁልፍ የሚባሉ መረጃ አቀባዮችን ለማግኘት አልተቻለም፡፡ የተሻለ ግንዛቤ ይኖራቸዋል ተብለው የተጠቆሙትም፣ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኞች ሆነው አልተገኙም፡፡ ስለሆነም፣ በቃል-ግጥሙ ክወናም ሆነ ሥርዓት በማስፈጸም የሚሳተፉት ወንዶች በመሆናቸው፣ ለመረጃው ቅርበት ስላላቸው እነሱ ላይ ተተኩሯል፡፡

ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው መረጃ አቀባዮች፣ ከሀይማኖት አባቶች፣ የአካባቢውን ታሪክና የለቅሶ ሥርዓት ከሚያውቁ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የለቅሶ ሥርዓት ከሚያስተባብሩ፣ የወየታ፣ የሙሾና የፉከራ ቃል-ግጥሞችን በመከወን ችሎታቸው በማህበረሰቡ እውቅና ከተሰጣቸው

* አቶ ጸጋየ የተባሉ መረጃ አቀባይ፣ ሴቶች ሬሳ ስለሚፈሩ እንደማይቀርቡና ሥርዓቱን በውል እንደማያውቁት ሲገልጹ፣ አቶ ገበያው ግን ሩህሩህና አዛኞች ስለሆኑ ስሜታቸው እንዳይጎዳ ሲባል እንዳይቀርቡ ስለሚከለከሉ እንጂ ስለሚፈሩ አለመሆኑን ይገልጻሉ፡፡ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን ጉዳይም ካለማወቅ ብቻ ሳይሆን ወደአደባባይ እንዲወጡ የማያበረታታው የባሕሉ ተጽዕኖ ጫና ስለሚያስድርባቸው መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡

መካከል የተመረጡ ናቸው፡፡ ከእያንዳንዱ መረጃ አቀባይ ጋር በመገናኘትና በመተዋወቅ የጥናቱን ዓላማ የማሳወቅና ፈቃደኝነታቸውን የማግኘት ሥራ ከተሰራ በኋላ፣ በሚመቻቸው ጊዜና ቦታ በመገኘት ቃለ መጠይቁን የማካሄድ ሥራ ተከናውኗል፡፡

ለሀይማኖት አባቶች፣ ስለሞት ምንነት፣ ከሞት ወዲያ ስለሚኖረው የነፍስ እጣ ፈንታ፣ በአካባቢው የሚከናወኑት የቀብር ሥርዓቶች ስላላቸው ሀይማኖታዊ አንድምታና ትዕምርታዊነት፣ የሀዘን አገላለጾቹ ልማዶች ስላላቸው ሀይማኖታዊ ዳራ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በሀዘን አገላለጽ ልማዶቹ ላይ ስላላት አቋምና፣ ስለመታሰቢያዎች ምንነት፣ እንዲሁም ስላላቸው ፋይዳ ተጠይቀዋል፡፡ የአካባቢውን ታሪክ የሚያውቁት ሽማግሌዎች ደግሞ፣ ስለከተማው አመሰራረት፣ በአካባቢው ስለተካሄዱ ጉልህ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ ሁነቶች፣ ማሕበረሰቡ በሀዘን ጊዜ ስለሚያከናውናቸው የእርስበርስ ግንኙነቶች፣ ቀደም ሲል ይከወን በነበረውና በአሁኑ ሰዓት እየተፈጸመ ባለው የለቅሶ ሥርዓት መካከል ስለሚታዩት ልዩነቶች ተጠይቀዋል፡፡

የለቅሶ ቃል-ግጥም ከዋኞችም፣ እንደየችሎታቸው ወደሙያው እንዴት እንደገቡ፣ የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹን እንዴት እንደሚደርሷቸው፣ የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ከጾታ፣ ከዕድሜና ከማሕበራዊ ደረጃ ጋር ስላላቸው ግንኙነት፣ ስለእያንዳንዱ የለቅሶ ቃል-ግጥም አካባቢያዊ ስያሜ፣ የመከወኛ መሳሪያዎችና የክወና ሥርዓት፣ በማሕበረሰቡ ዘንድ ስለሚሰጣቸው ቦታ፣ የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ስላላቸው ማሕበራዊ ጠቀሜታ፣ ቀደም ሲል በነበረውና ባሁኑ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ክወና መካከል ስለሚታዩት ለውጦች፣ ስለወደፊቱ የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ቀጣይነትና፣ በምልከታ ቢሰበሰቡም ተጨማሪ ማብራሪያ ስለሚፈልጉ መረጃዎች ተጠይቀዋል፡፡

የለቅሶ ሥርዓት አስተባባሪዎቹ ደግሞ፣ የሟች ነፍስ ከወጣበት ሬሳ እስከሚቀበርበት ድረስ በቅደም ተከተል ስለሚከናወኑት ድርጊቶች ምንነት፣ ድርጊቶቹ በዚያ መንገድ ስለሚከናወኑበት ምክንያት፣ በድርጊቶቹ ክወና ከማን ምን እንደሚጠበቅ፣ ስለሀዘን አገላለጽ ልማዶቹ ምንነት፣ በሥርዓቶቹ ዙሪያ ቀደም ሲልና በአሁኑ ጊዜ ስለሚታዩት ልዩነቶችና፣ ከእነዚህ ጋር ተያያዥ ስለሆኑ ጉዳዮች ተጠይቀዋል፡፡

አጥኚው ከላይ በተጠቀሱትና ከእነሱ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ዙሪያ፣ የባሕሉ እውቀት ኖሯቸው ከተመረጡት 42 ቁልፍ መረጃ አቀባዮች፣ በመደበኛ መንገድ በተካሄደ ቃለ መጠይቅ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ሰብስቧል፡፡ ከእነዚህ ባለሙያዎችና ከሌሎችም ነዋሪዎች

ጋር በኢመደበኛ መንገድም ሰፊ ውይይቶችን በማካሄድም ጠቃሚ መረጃዎችን አግኝቷል። የመረጃዎቹን አስተማማኝነት ለማረጋገጥና አንዱ የዘነጋውን ሌላው ሲያስታውስ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፣ ቀጥሎ የቀረበው የቡድን ውይይት ተካሂዷል።

### 3.4.3. ቡድን ተኮር ውይይት (focus group discussion)

ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተመረጠው፣ Lloyd-Evans (2006፣154) እንደሚያስገነዝቡት የተጠኚዎቹን የቡድን ባሕርያት፣ ተራክቦዎችና ልማዶች ለመመርመር የሚያስችሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ስለሚያስችል ነው። ከዚህም በተጨማሪ፣ የሚገኘውን መረጃ ከተለያየ አቅጣጫ በመሰብሰብ አስተማማኝነቱን ከፍ ለማድረግ ስለሚረዳ ነው። ተወያዮቹ በቡድን ስለሚቀርቡ፣ በአንድ በኩል ተገቢ ያልሆነ መረጃ መስጠት ትዝብት ላይ ስለሚጥላቸው በተቻለ መጠን በባሕሉ ውስጥ እየሆነ ያለውን ለመግለጽ ስለሚያበረታታቸው፣ በሌላ በኩል በአንዱ ተወያይ የተዛባ ሀሳብ ቢገለጽ ወይም በበቂ ሁኔታ ሳይብራራ የሚቀር ሀሳብ ቢኖር፣ ሌሎቹ ተወያዮች የማረምና አስፋፍቶ የማቅረብ እድል ስለሚያገኙ፣ የዘዴው አስፈላጊነት ታምኖበት ተመርጧል።

በዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በመወያያ ርዕሰ ጉዳይነት ቀርበው ከተመለሱት ጥያቄዎች ውስጥ፣ የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በአካባቢው የሚተገበሩ የለቅሶ ሥርዓት አይነቶች ምን ምን ናቸው? በመካከላቸው ያለው ልዩነትና አንድነትስ ምንድን ነው? ምን አይነት የሀዘን አገላለጽ ልማዶች አሉ? በጊዜ ሂደት በሀዘን አገላለጽ ልማዶቹ፣ በለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ክወናና ከዋኞቹ ዙሪያ ምን ምን ለውጦች ታይተዋል? የለቅሶ ሥርዓቶቹና ቃል-ግጥሞቹ ያላቸው ማሕበራዊ ፋይዳ ምንድን ነው?

በእነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ በአራት ወረዳዎች የቡድን ውይይት ለማካሄድ ታቅዶም ሁለቱ ሲሳኩ ሁለቱ በተሳታፊዎቹ ተሟልቶ አለመገኘት ምክንያት ሳይሳኩ ቀርተዋል። በደብረታቦር ዙሪያ ወረዳ ለተካሄደው የቡድን ውይይት የተመረጡት መረጃ አቀባዮች፣ እድር በመምራት፣ የለቅሶ ሥርዓት በማስተባበር፣ ሬሳ በመገነዝ፣ ሙሾ በማውረድና ወየ በማለት ለረዥም ጊዜ ያገለገሉ ሰባት ሰዎች ናቸው። ከዚህ የቡድን ውይይት ጠቃሚ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል።

በስማዳ ወረዳም ከተለያዩ የወረዳው አካባቢዎች የተውጣጡ መረጃ አቀባዮችን ያቀፈ ስድስት አባላት ካሉት ቡድን ጋር በአካባቢው ስለሚከናወነው የለቅሶ ሥርዓት፣ የሀዘን አገላለጽ ልማድና የለቅሶ ቃል-ግጥሞች አይነትና ክወና ጠቃሚ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ በሁለቱም የቡድን ውይይቶች፣ የመረጃ ሰብሳቢው ሚና የመወያያ ርዕስ ጉዳዮችን እያነሳ ሁሉም የቡድኑ አባላት ሀሳባቸውን ለመግለጽ እድል የሚያገኙበትን መንገድ ከመፍጠርና የውይይት ሂደቱን ከመምራት የዘለለ አልነበረም፡፡

በምልከታ፣ በቃለመጠይቅና በቡድን ውይይት ፊት ለፊት ከተሰበሰቡት መረጃዎች በተጨማሪ፣ ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ በተለያዩ ግለሰቦች፣ በጽሑፍ፣ በድምጽና በምስል የተቀረጹ ሰነዶች፣ ተጨማሪ መረጃዎችን ከማስገኘት ባለፈ፣ በጊዜ ሂደት የታዩትን ለውጦች ለማነጻጸር እንደሚረዱ በመታመኑ፣ በመረጃዎቹ ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ የሰነድ መረጃዎችን አስፈላጊነትና የተሰበሰቡትን ሰነዶች ምንነት የሚያብራራው ክፍል ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

### 3.4.4 ሰነድ ምርመራ (document analysis)

በኢትኖግራፊያዊ ምርምር፣ ተመራማሪው እየተከወኑና እየተነገሩ ያሉ መረጃዎችን በቀጥታ በመመልከት ወይም መረጃ አቀባዮችን በመጠየቅ ከሚሰበስበው በተጨማሪ፣ ከሰነዶች ለጥናቱ ጠቃሚ መረጃዎችን ሊያገኝ እንደሚችል ተመራማሪዎች ያስረዳሉ፡፡ ለምሳሌ Hammersley እና Atkinson (2007፣121)፣ ቀደም ባለው ጊዜ የሰነድ መረጃዎች በኢትኖግራፊያዊ ጥናት ቦታ ተነፍጓቸው እንደኖሩ ጠቁመው፣ ከሚያስገኙት ጠቀሜታ አንጻር፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ትኩረት እንደተሰጣቸው ያስረዳሉ፡፡ የተጠኚዎቹ ማሕበረሰቦች አባላት የሚጠኑትን ማህበራዊ መቼቶች በመቅረጽና በማሰራጨት መሳተፋቸው፣ ለእነዚህ ሰነዶች ትኩረት እንዲሰጥ እንዳደረገም ይገልጻሉ፡፡

ምክንያቱም ሰነዶች ስለሚጠናው ማሕበራዊ መቼት ወይም ስለሰፊው አውዳቸውና በተለይም ስለተቋማት ወይም ተዋናዮቹ መሰረታዊ መረጃ የሚሰጡ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ አንዳንዴ ከሰነድ የሚገኙት መረጃዎች፣ ከሌሎች ምንጮች የማይገኙ የሚሆኑበት ጊዜ መኖሩ ትልቅ ዋጋ እንደሚያሰጣቸውም ያስገነዝባሉ፡፡ በሌላ በኩል ከመረጃ አቀባዮች ወይም ከምልከታ የተገኙ ጠቃሚ መረጃዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ወይም የተዛቡ መሆናቸውን ለማሳያነት

እንደሚያገለግሉም ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ በማይተናነስ መልኩ ሰነዶች ተጠየቃዊ ሀሳቦች እንዲመነጩ የማነቃቃት ጠቀሜታ ሊኖራቸው እንደሚችልም ይገልጻሉ፡፡

Tavakoliም (2012፣180) ለአብዛኛዎቹ አይነታዊ ምርምሮች፣ ሰነዶች መሰረቶች መሆናቸውን ገልጸው፣ የሰነድ ምርመራው የተጻፈ (የማስተማሪያ መጻህፍት፣ ልቦለዶች፣ መጽሔቶች፣ የስብሰባ ቃለጉባኤዎች፣ ማስታዎሻዎች፣ ማስታወቂያዎች፣ የፖሊሲ አዋጆች፣ ጋዜጦች፣ የተለያዩ ማስረጃዎች፣ የልደት ካርዶች፣ የጋብቻ ውሎች፣ የበጀት መዝገቦች፣ ደብዳቤዎች፣ የኢሜል መልእክቶች ወዘተ.) ወይም የተቀረጹ (ፎቶግራፎች፣ ቴፖች፣ ቪዲዮዎች፣ የኮምፒር ላይ ምስሎች፣ ድረገጾች፣ የሙዚቃ ክወናዎች፣ በቴሌቪዥን የተላለፉ የፖለቲካ ንግግሮች ወዘተ.) ሊሆኑ እንደሚችሉም ይጠቁማሉ፡፡ Daviesም (1999፣161)፣ ሰነዶች ለተመራማሪው ጠቃሚ መረጃዎች የሚያስገኙ በመሆናቸው ቢስማሙም፣ በጥንቃቄ መታየት እንዳለባቸው ግን ያስገነዝባሉ፡፡ አንድ ተመራማሪ ሰነዶችን በሚጠቀምበት ጊዜ፣ ገና ከመነሻው ስለትክክለኛነታቸው (authenticity)፣ ስለተዓማኒነታቸው (credibility) እና ስለወካይነታቸው (representativeness) ጥያቄዎችን በማንሳት ልዩ ትኩረት መስጠት እንዳለበትም ያስገነዝባሉ፡፡

ከላይ የቀረቡትን መረጃዎች ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ለዚህ ጥናት ፋይዳ ኑሯቸው የተሰበሰቡትና የተመረመሩት ሰነዶች፣ ከደቡብ ጎንደር ዞን ባሕልና ቱሪዝም መምሪያና ለጥናቱ ከተመረጡት ወረዳዎች ባሕልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤቶች የተገኙ የለቅሶ ቃል-ግጥም ስብስቦች፣ የለቅሶ ሥርዓትን ጎጂ ባሕልነት በማስመልከት የተጻፉ ወረቀቶችና፣ ከግለሰቦች እጂ የተገኙ በቴፕ የተቀረጹ የወየታ፣ የቀረርቶና የፉከራ ቃል-ግጥሞችና፣ በቪዲዮ የተቀረጹ የለቅሶ ሥርዓቶች ናቸው፡፡

የለቅሶ ቃል-ግጥም ስብስቦቹ፣ በአካባቢው በርዕስ ጉዳዩ ዙሪያ የተሰራውንና ያልተሰራውን ለመለየት፣ የሚያተኩሩባቸውን ርዕሰ ጉዳዮች ለመገንዘብና፣ አይነታቸውን ለመለየት ረድተዋል፡፡ ከአውድ ውጪ የተሰበሰቡ በመሆናቸው ግን ለትንታኔ አልተመረጡም፡፡

በካሴትና በቪዲዮ ከግለሰቦች የተገኙት መረጃዎች፣ ከማን እንደተገኙ፣ መቼና የት እንደተቀረጹ፣ የሟችን እድሜ፣ ጾታና፣ ማሕበራዊ ደረጃ የሚመለከቱ መረጃዎችን፣ ከተገኙባቸው ግለሰቦች በመጠየቅ የማሟላት ሥራ ከተከናወነ በኋላ፣ ወደጽሑፍ ተቀይረው

አስፈላጊ በሆነበት ቦታ በምልከታና በቃለ መጠይቅ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ጋር እየተዋሃዱ ተተንትነዋል፡፡

በአጠቃላይ የተጠኚው ማህብረሰብ ከሞት ጋር የተያያዙ ሥርዓቶችና ቃል-ግጥሞች ክወና ምን እንደሚመስል፣ የእነዚህ ክወናዎችና የልማዶቹ ማህበራዊ ፋይዳ ምን እንደሆነ፣ ማህበረሰቡ ስለሞት ምንነት ያለው ዓለማዊና ሀይማኖታዊ አመለካከት ምን እንደሚመስል፣ ሞት ሲከሰት ማን፣ ለማን፣ በምን፣ መቼ፣ የትና እንዴት ምን፤ ምን ልማዶችን እንደሚያከናውንና፣ በለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ውስጥ የሚንጸባረቁት በሥጋ ዝምድናና በማህበራዊ ትስስር ላይ የሚከሰቱ የሞት ውጤቶች ምን እንደሆኑ ለመረዳትና ለመፈከር፣ በቦታው ተገኝቶ እየሆነ ያለውን በተሳታፊነት ማየትን፣ ስለእነዚህ መረጃዎች የካበተ እውቀት ያላቸውን ቁልፍ መረጃ አቀባዮች በተናጠል መጠየቅን፣ በቡድን ማወያየትንና፣ ተያያዥነት ያላቸውን ሰነዶች መመርመርን ይፈልግ ስለነበር፣ የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተገቢነት አላቸው፡፡ ቀጥሎ መረጃዎቹን ለመሰብሰብ አገልግሎት ላይ የዋሉት መሳሪያዎችና የተመረጡባቸው ምክንያቶች ቀርበዋል፡፡

### 3.5. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

እንደMurchison (2010፣72) ገለጻ፣ ለኢትኖግራፊያዊ ምርምር መረጃ መሰብሰቢያነት፣ መቅረጸ ድምጽ፣ ፎቶና ቪዲዮ ካሜራዎች እንዲሁም ማስታወሻ በጣም አስፈላጊ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ ለዚህ ጥናት በግብዓትነት የተሰበሰቡት መረጃዎች፣ ቃል-ግጥሞች፣ ፎቶግራፎችና የክወና ሥርዓቶች ስለሆኑ፣ እነዚህን መረጃዎች በተሟላ መንገድ ለመሰብሰብ፣ ዲጂታል የድምጽ መቅረጫ፣ ዲጂታል ፎቶ ካሜራ፣ ዲጅታል ቪዲዮ ካሜራና ማስታወሻ አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡

ዲጂታል የድምጽ መቅረጫው የተመረጠበት ምክንያት፣ የሙሾ ቃል-ግጥሞቹንና ቃለ መጠይቆቹን ለመቅረጽና በቀላሉ ወደኮምፒዩተር አስተላልፎ ወደጽሑፍ የመቀየር (transcribe) የማድረግ ስራውን ለማፋጠን ስለሚያግዝና፣ መረጃዎቹንም በቀላሉ አባዝቶ ለማስቀመጥ አመች ስለሆነ ነው፡፡ ዲጂታል ፎቶ ካሜራውም የፎቶግራፎቹን ጥራት ለመጠበቅ፣ በቀላሉ ለአገልግሎት ለማዘጋጀትና፣ ቅጂዎችን አባዝቶ ለማስቀመጥ ስለሚጠቅም ነው፡፡ ዲጂታል ቪዲዮ ካሜራውም ክወናዎቹን ከነድምጾቹ በጥራት ለመቅረጽ ከመርዳቱም በላይ፣ መረጃዎቹን በቀላሉ ለመጠቀምና ለማስቀመጥ ተመራጭነት አለው፡፡ ማስታዎሻው ደግሞ፣ Davies

(1999፤195) እንደሚያስገነዝቡት፣ በክወናና በቃለ መጠይቅ ወቅት ማብራሪያ የሚጠይቁ ጉዳዮችን፣ ቀረጻዎችንና የአጥኚውን ትዝብት አስፍሮ ለመያዝ፣ መቸቶችን ለመግለጽ፣ የቃለ መጠይቁን ወይም የምልከታውን ሂደት ለማስፈር በመርዳቱ ተመርጧል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ Murchison (2010፤73) በአጽንኦት እንደሚገልጹት፣ እያንዳንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የየራሱ ደካማ ጎኖች ስላሉት፣ እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት በጽሑፍ ማስታወሻ ማስደገፍ የላቀ ጠቀሜታ አለው፡፡ ለምሳሌ መቅረጸ ድምጽ፣ የአካል እንቅስቃሴዎችን፣ የፊት ገጽታ ለውጦችን፣ ድርጊታዊ ተራክቦዎችን፣ መቼቶችንና ሽታዎችን አይቀርጽም፡፡ ፎቶ ካሜራም፣ አንድ ቦታ ላይ የተወሰደን ቅጽበታዊ ምስል እንጂ፣ ከድምጽና ሽታ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን አያካትትም፡፡ ቪዲዮ ካሜራም ምስልንና ድምጽን ቢቀርጽም ከተወሰነ አቅጣጫ ብቻ ስለሚያነጣጥር፣ ሁሉንም ጠቃሚ መረጃዎች አካትቶ አያስቀርም፡፡ ስለዚህ ኢትኖግራፊያዊ መረጃውን የተሟላ ለማድረግ፣ የእነዚህን መሳሪያዎች ክፍተቶች በመሙላት በኩል ማስታወሻ የጎላ ድርሻ ይጫወታል፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት መሳሪያዎች በእያንዳንዳቸው የሚከተሉት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ቴክስቶች፣ በመቅረጸ ድምጽ በአጥኚውና በረዳቶች አማካይነት ከከዋኞቹ አንደበት በሚከወኑበት ቦታ በቀጥታ ተሰብስበዋል፡፡ ከሌሎች ሁለት ለቅሶዎች ክወና ላይ በሌሎች ሰዎች በካሴት ተቀርጸው የተገኙ መረጃዎችም ለጥናቱ በግብዓትነት አገልግለዋል፡፡ የመከወኛ ቁሶችና ክወናዎች ደግሞ፣ በፎቶና ቪዲዮ ካሜራዎች በተመሳሳይ ሁኔታ በሚከወኑባቸው ቦታዎች በአጥኚውና በረዳቶች ተቀርጸዋል፡፡ ቀደም ሲል ጥናቱ በተካሄደበት ዞን፣ ከቀጠሮ ለቅሶ ክወና ላይ በሌላ ሰው የተቀረጸ የምስል መረጃም፣ ከመረጃዎቹ ጋር እንዲካተት ተደርጓል፡፡

በአጭሩ የተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በጥምረት አገልግሎት ላይ በመዋላቸው፣ በአንዱ የሚታየውን ውስንነት ሌላው እያካካሰ የተፈለገውን መረጃ አሟልቶ ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

ከዚህ በላይ አጥኚው ከተጠኚዎቹ ጋር አብሮ እየኖረ በጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የሚያደርጓቸውንና የሚሏቸውን ማጥናቱንና መረጃዎቹን የሰበሰበባቸው ተገቢ መሳሪያዎች ተጠቅሰዋል፡፡ ከማሕበረሰቡ ጋር እንዴት እንደኖረ፣ የተሻለ እውቀት ያላቸውን መረጃ አቀባዮች በምን መንገድ እንደመረጠ፣ ከእነሱ ጋር የነበረው ግንኙነት እንዴት እንደነበር፣ የሰበሰባቸውን

መረጃዎች እስከምን እንደተጠቀመና ትንተናውን በምን ላይ ተመስርቶ እንዳካሄደ የሚገልጸው ሥነምግባራዊ ጉዳይ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 3.6. ሥነምግባራዊ ጉዳዮች (Ethical Issues)

የሥነምግባር ጉዳይ መረጃ ሰብሳቢው በመስክ ቆይታው ከሚጠናው ማህበረሰብ ጋር የሚኖረውን ግንኙነት፣ ያገኘውን መረጃ አጠቃቀምና፣ የጥናቱን ውጤት በመረጃዎቹ ላይ የተመሰረተ ማድረጉን የሚመለከት ሞራላዊ አንድምታ ያለው ጉዳይ ነው፡፡ Tolken (1996፣348 Sims እና Stephens (2005፣234) እና ፈቃደ አ.አ.አ. (1991፣128-129) እንደሚያስረዱት፣ ከመረጃ አቀባዮቹ ጋር በታማኝነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት መፍጠርና ባሕላቸውን ማክበር ለፎክሎረኞች የስነምግባር ዋልታዎች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ Jackson (1986፣259-69) የጥናቱን ዓላማ ለተጠኚዎች በትክክል መንገር (አለመዋሸት)፣ ለመረጃ አቀባዮች ተገቢውን ክፍያ መፈጸም፣ የተገኘውን መረጃ እስከምን ድረስ ለመጠቀም የሚያስችል የስምምነት ውል መፈጸም፣ ከመሰረታዊ የሥነምግባር ጉዳዮች ውስጥ እንደሚካተቱ ያስረዳሉ፡፡ Marczyk እና ሌሎችም (2005፣238) ደግሞ፣ መረጃ አቀባዮቹ በጥናቱ በመሳተፋቸው ሊከተል የሚችል ጉዳት አለመኖሩን ማረጋገጥ፣ መብታቸውን ማክበርና ሊያገኙ የሚገባቸውን ጥቅም እንዲያገኙ ማድረግ፣ ደህንነትን ከሚያስጠብቁት ሥነምግባራዊ መርሆዎች ውስጥ እንደሚጠቀሱ ይገልጻሉ፡፡

በዚህም መሰረት በጥናቱ በተለያየ ደረጃ ለተሳተፉ ግለሰቦች፣ የጥናቱ ዓላማ በግልጽ የተነገራቸው ሲሆን፣ መረጃዎችንም ያለምንም ጫና በፈቃዳቸው እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ መረጃ በማቀበልና በሌላም መንገድ ለጥናቱ ሲባል ላባከኑት ጊዜ ከግለሰቦቹ ጋር እንደነበረው ግንኙነት ወጪዎች ተሸፍነዋል፡፡ መረጃ አቀባዮቹን ተክተው ሥራቸውን ላከናወኑ ግለሰቦች ወጪ መሸፈኛ በሚል ሰበብ በአካባቢው ባለው የቀን ሰራተኛ ወይም የባለሙያ የክፍያ መነሻነት፣ ተቀራራቢ ክፍያ ለመክፈል ቢሞከርም ፈቃደኞች ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡ ጥሩ ግንኙነት ለመመስረት ተደጋጋሚ ግንኙነቶችን ማድረግ አስፈላጊ ስለነበር፣ የመስተንግዶ ወጪዎች ተሸፍነዋል፡፡ በአቅም ደከም ላሉና አንዳች ድጋፍ የመፈለግ አዝማሚያ ላሳዩም፣ አቅምን ያገናዘበ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡ ሁሉም ወጪዎች የተፈጸሙት በመረጃ ሽያጭና ግዥ ሳይሆን፣ ግንኙነትን በማጠናከርና በመተጋገዝ ስሜት ነው፡፡ ለጥናቱ የተሰበሰቡት መረጃዎች

ከጥናቱ ውጭ ለሌላ አገልግሎት እንደማይውሉ የተገለጸላቸው ሲሆን፣ በመረጃ አቀባዮች ዘንድ ጥሩ ስሜት ባለማሳደሩ፣ የጽሑፍ ስምምነት ለማድረግ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

እነዚህን በጥናት መስኩ ተመራማሪዎች መከበርና መተግበር እንዳለባቸው የታመነባቸው ሥነምግባራዊ ጉዳዮች በማክበር የተሰበሰቡት መረጃዎች፣ ለትንተና የተደራጁት በሚከተለው መንገድ ነው፡፡

### 3.7. የመረጃ አደረጃጀት ስልትና አተናተን ዘዴዎች

#### 3.7.1. የመረጃ አደረጃጀት ስልት

መረጃዎቹን ለማደራጀት በመጀመሪያ የተከናወነው በቃለ መጠይቅና በምልከታ የተሰበሰቡትን መረጃዎች እንዲሁም በቴፕና በቪዲዮ ካሴት ተቀርጸው ከግለሰቦች የተገኙትን ሰነዶች በጽሑፍ እንዲሰፍሩ ማድረግ ነው፡፡ እነዚህንና ሌሎች በጽሑፍ የተገኙ መረጃዎችን ደጋግሞ በማንበብ፣ ከቀብር ሥርዓት፣ ከሀዘን መግለጫ ልማድና ከመታሰቢያ ሥርዓት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን መረጃዎች በየዘርፋቸው የመለየት ሥራ ተከናወነ፡፡ ከለቅሶ ቃል-ግጥሞቹም ውስጥ ከጥናቱ ዓላማ ጋር ግንኙነት ያላቸው በየክፍላቸው ተለዩ፡፡ ከጥናቱ ጋር የበለጠና ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው መረጃዎች በዚህ መንገድ ከተለዩ በኋላ፣ እንደየተመሳስሏቸው በአብይና በንዑስ ምድቦች የመመደብና ቀጥሎ በቀረበው መንገድ ለትንተና የማዘጋጀቱ ስራ ተከናወነ፡፡

#### 3.7.2. የመረጃ አተናተንና ፍከራ ዘዴ

በመግቢያው ክፍል እንደተገለጸው፣ የጥናቱ መረጃዎች የተተነተኑት በመስረተ ባሕል ሞዴል ነው፡፡ በዚህ ሞዴል የገለጻና የትንተና ሥራው ሲከናወን፣ በሥርዓት ትንተና ተቀባይነት ያለውን አሰራር ለመከተል ትኩረት ተሰጥቷል፡፡ የሥርዓት ጥናት ታሪክ ሲቃኝ፣ በተለያዩ አጥኚዎች ለተለያዩ ክፍሎቹ ትኩረት ይሰጥ እንደነበር የጥናት ውጤቶች ያሳያሉ፡፡ Roth (1995) በሥርዓት ጥናት፣ አጽንኦት መስጠት በሚገባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ አትኩረው፣ የዘርፉን ጥናት ታሪካዊ እድገት በመመርመር፣ van Gennep (1960 [1909])፣ Durkheim (1965 [1912]) እና Turner (1967፣1969 [1966]) ለየትኞቹ ጉዳዮች ትኩረት ይሰጡ እንደነበር፣ እንደሚከተለው ቃኝተው የራሳቸውንም ሀሳቦችም ሰንዝረዋል፡፡

van Gennep የሥርዓት መዋቅር (ሥርዓቱን የገነቡት ቅንጣቶች)፣ ላይ በማተኮር አንድን ሥርዓት፣ ሥርዓት ያደረጉትን ነገሮች መለየት ላይ ሲያነጣጥሩ፣ ዘመነኛቸው Durkheim፣ የሥርዓቶቹን ፋይዳ (ውጤት) መግለጽ ላይ እንዳተኮሩ ያስረዳሉ፡፡ ወደኋላ ላይ የተነሱት Turner ደግሞ፣ እንደvan Gennep የሥርዓቶቹን መዋቅር መለየት ላይ ቢያነጣጥሩም፣ ከዚህ በተጨማሪ ትዕምርታዊነት ላላቸው ነገሮች ልዩ ትኩረት እንደሰጡ ያስገነዝባሉ፡፡

Roth (1986፣314)፣ በእነዚህ በዘርፉ ጥናት ትልቅ ቦታ በሚሰጣቸው ተመራማሪዎች የትኩረት ልዩነቶች የተነሳ፣ የሥርዓት ገለጻ በመዋቅራዊ አንጻር (compositional approach) እና በተግባራዊ አንጻር (functional approach) ጎራ ሲካሄድ መቆየቱን አውስተው፣ እያንዳንዱ አንጻር የየራሱ ጠንካራና ደካማ ጎን እንዳለውም ይጠቁማሉ፡፡ ማንኛውም የሥርዓት ገለጻ የተሟላ ይሆን ዘንድ፣ በሁለቱ አንጻሮች መተንተን እንዳለበትም ያስገነዝባሉ፡፡ ስለሆነም የመረጃዎቹ ገለጻ መዋቅራቸውንና ተግባራቸውን ያጣመረ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

የመረጃ ትንተናው ቀጥሎ በተዘረዘሩት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ መረጃ አቀባዮቹ ስለሞት፣ ስለቀብር ሥርዓትና ስለሀዘን አገላለጽ ልማድ የሰጡት ትርጉም ሳይጨመርበትና ሳይቀነስለት ተካትቷል፡፡ የሀይማኖት መጻሕፍትና ሌሎችም ሰነዶች ስለርዕሰ ጉዳዮቹ የሚያነሷቸው ነጥቦች አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ከመረጃ አቀባዮቹ ሀሳቦች ጋር እየተነጻጸሩ ወይም እንደመነሻ እየሆኑ ቀርበዋል፡፡ የተመራማሪውም ከምልከታ የተገኘ ግንዛቤና በሌሎች ባሕሎች፣ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ የተካሄዱ ጥናቶች የደረሱባቸው ግኝቶች፣ በተጠኚዎቹ የቀረቡ ሀሳቦችን ለማዳበር ወይም በማነጻጸር ልዩነታቸውን ለማሳየት ተካትተዋል፡፡ በለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ሞት የሚያስከትለው ውጤት እንዴት እንደተገለጸም፣ ከትንተና ግብዓቶቹ ውስጥ ተካትቷል፡፡ ትንተናና ፍከራውን የሚያጠናክሩ የፎቶግራፍ መረጃዎችም በተገቢዎቹ ቦታዎች እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

ለትንተናው የተመረጡትን መረጃዎች አስተማማኝነትና ትክክለኛነት ለማረጋገጥ፣ በተቻለ መጠን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ጥረት ተደርጓል፡፡ የመጀመሪያውና ዋናው በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መረጃዎቹን መሰብሰብ ነው፡፡ ይኸውም የተለያዩ መረጃ አቀባዮችን ቅደም ተከተሉን ባልጠበቀ መንገድ ተመሳሳይ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፣ ከቃለ መጠይቅ የተገኘውን መረጃ በክወና ላይ መኖር አለመኖሩን በመመልከትና፣ በምልከታ የታየውን በቃለ

መጠይቅ በማቅረብ፣ ተደጋጋሚነት ያላቸውን መረጃዎች በመውሰድ ነው። ልዩነቶች በሚታዩባቸው ዙሪያ ተጠያቂዎቹ ማብራሪያዎችን እንዲሰጡ በማድረግና፣ ሌሎች ሰዎችን በመጠየቅ፣ በማሕበረሰቡ በተጨባጭ እየተከወኑ ያሉትን ትክክለኛ መረጃዎች ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል።

በአጠቃላይ በጥናቱ በተለይ ደግሞ በመስክ የመረጃ ስብሰባው የተለያዩ ችግሮች አጋጥመው ነበር። መልካም አጋጣሚዎችም እንደዚሁ። በተለይ አጋጥመው የነበሩትን ችግሮችና የታለፉባቸውን ዘዴዎች መጥቀሱ በዚህ ጥናት ላይ ሊኖራቸው የሚችለውን አንድምታ ከመግለጹ በተጨማሪ፣ ለሌሎች ተመራማሪዎች የሚያስገነዝቡት ቁም ነገር እንደሚኖር በመታመኑ ቀጥሎ ቀርበዋል።

## 3.8. ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱ መፍትሔዎችና መልካም አጋጣሚዎች

### 3.8.1 ያጋጠሙ ችግሮች

በዚህ ጥናት፣ በሌሎች የመስክ ጥናቶች የሚጠበቁት እንደመጓጓዣ፣ ማረፊያ፣ አስቸጋሪ የአየር ንብረት አይነቶቹ የተለመዱ ችግሮች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር በተያያዘ ስለሞት በግልጽ ለመነጋገር ያለመድፈር፣ ከሬሳ ማስናዳትና ግንዘት ጋር የተያያዙ የቅድመ ቀብር ሥርዓቶችን በቅርበት ለመከታተልና የቪዲዮ ቀረጻ ለማከናወን ፈቃድ ያለማግኘት ችግሮች እንደሚያጋጥሙ ተጠብቀው ነበር።

በመስክ መረጃ ስብሰባው፣ አስከሬንን እርቃኑን መቅረጽ ኢሞራላዊ በመሆኑ ባይሞከርም፣ የግንዘት ሥርዓቱን ፎቶ ለማንሳት በስድስት የቀብር ሥርዓቶች ላይ ከተጠየቁት የቅርብ ቤተሰቦች ከአንዳቸውም ፈቃድ ለማግኘት አልተቻለም። ከዚህም በተጨማሪ፣ በክወና ላይ የለቅሶ ሥርዓቱን ለመቅረጽ ከሀዘንተኞቹ ፈቃድ ከተገኘ በኋላ፣ ከከዋኞቹም ሆነ ከለቀስተኞቹ አልፎ አልፎ ተቃውሞ አጋጥሟል። የተመረጡ ወየ ባዮችና ሙሾ አውራጆች ለቅሶ በሌለበት ስለሙያቸው ቃለ መጠይቅ በተደረገላቸው ጊዜ እንዲያንጎራጉሩ ሲጠየቁ፣ ሀዘንን እንደመመኘት በመቁጠር ፈቃደኛ ያለመሆን አዝማሚያ አሳይተዋል። Pritchardን (2011፣181) እንደገጠማቸው፣ ፈቃደኛ የሆኑት እንኳ ተጠይቀው የሚያቀርቡትን፣ በእውነተኛ ሥርዓቱ ላይ እንደሚያቀርቡት አድርገው ያለመከወን ችግር ታይቷል።

ከሙሾ አውራጆቹና ወየ ባዮቹ በተሻለ፣ ፎካሪዎቹ ከአውዱ ውጭ መረጃ ለመስጠትና በጉዳዩ ዙሪያ ለመነጋገር ፈቃደኞች ቢሆኑም፣ ክወናቸው በእውነተኛው ቦታ እንደሚከወነው ከስሜት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል ከዋኞቹ ከሀዘንተኞቹ ጋር ተቀላቅለው እየዞሩ ወየ ሲሉና በሰልፍ ሆነው ወዲያና ወዲህ እየተዛወሩ ሲፎክሩ፣ በሚፈጠሩት መጨናነቆች፣ የምስልም ሆነ የድምጽ መረጃዎቹን በጥራት ያለማስቀረትና አንዳንዴም ጭራሹን ያለማግኘት ችግሮች አጋጥመዋል፡፡

በለቅሶ ሥርዓት ላይ ሙሾ የሚያወርዱትና ወየ የሚሉት ግለሰቦች አስቀድሞ አለመታወቅ፣ ለቀረጻ ፈቃዳቸውን የመጠየቁ ስነምግባራዊ ጉዳይ ላይ፣ ትልቅ እንቅፋት የፈጠረ ችግር ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለባሕሉ መረጃ ያውቃሉ ተብለው ከተጠቆሙት መካከል፣ በጥናቱ ለመሳተፍ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን በግልጽ ባይናገሩም፣ የተዛባ መረጃ ለመስጠትና ከሌሎች መረጃ አቀባዮች ጋር ግንኙነት እንዳይደረግ በር ለመዝጋት የሞከሩ ግለሰቦች ማጋጠም፣ በአካባቢው ጎልቶ በሚታየው የዘረፋና የግድያ ወንጀል ምክንያት በተናጠል እንደልብ ለመንቀሳቀስ አለመቻል፣ ከሚጠቀሱት ችግሮች ውስጥ ጉልሆቹ ነበሩ፡፡

እንዲሁም በጥናቱ እቅድ፣ ከደብረታቦር ዩኒቨርሲቲና ከዞኑ ባሕልና ቱሪዝም መምሪያ የሚመረጡ ሰራተኞች፣ ቁልፍ መረጃ አቀባዮችና የሀገር ሽማግሌዎች በሚገኙበት መድረክ የትንተናውን የመጨረሻ ረቂቅ አቅርቦ በማስገምገም፣ በአንድ በኩል የጥናቱን አስተማማኝነት ከፍ የማድረግ፣ በሌላ በኩል ጥናቱ ያስገኘውን እውቀት ለተጠኚዎቹ የማካፈልና ለተግባራዊ እንቅስቃሴ ለማነሳሳት ታቅዶ ነበር፡፡ ለጥናቱ የተመደበው በጀት ለዚህ ቀርቶ መረጃዎቹን ለመሰብሰብ አለማስቻሉና እገዛ እንዲያደርጉ ከፌዴሬሽን ምክር ቤት እስከክልሉ ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ቢሮ፣ የርዕሰ መስተዳድሩ ቢሮና የዞኑ አስተዳደር ድረስ፣ የቀረቡት ማመልከቻዎች አወንታዊ ምላሽ ባለማግኘታቸው፣ እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ሳይቻል መቅረቱ ሌላው ያጋጠመ ችግር ነበር፡፡

### 3.8.2 የተወሰዱ መፍትሄዎች

በስነምግባር ጉዳይ በምልከታ ለመቅረጽ ያልተቻሉትን መረጃዎች በቃለ መጠይቅ ለማሟላት ጥረት ተደርጓል፡፡ በቪዲዮ ለመቀረጽ ፈቃደኛ ያልሆኑ ግለሰቦችን ፍላጎት በመጠበቅ ፈቃደኛ የሆኑትን ለመቅረጽ ጥረት ተደርጓል፡፡ ሙሾ አውራጆችና ወየ ባዮችን ለቀረጻ ፈቃድ መጠየቅ

ክወናውን እንዲያቋርጡ ማስገደድ ሆኖ በመገኘቱ፣ እየተቀረጹ መሆናቸውን በሚያውቁበት ደረጃ በግልጽ በመቅረጽ ችግሩን ለማቃለል ተሞክሯል፡፡ የቡድን ክወናን ለመቅረጽ እያንዳንዱን ከዋኝ ፈቃድ ያለመጠየቅ የተመራማሪነት መብት መኖሩም፣ ችግሩን በተጀመረው መንገድ ለማቃለል እንዲገፋበት እድሉን ፈጥሯል፡፡

መረጃ ላለመስጠት በግልጽ ሳይቃወሙ ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች የተቆራረጡና የተዛቡ መረጃዎችን ለመስጠት የሞከሩ ግለሰቦች፣ ለሰጧቸው መረጃዎች ተመስግነውና ከተመራማሪው የሚጠበቀው ተሟልቶላቸው ሲሰናበቱ፣ የተዛቡ መረጃዎቻቸውም ተወግደዋል፡፡ በተለይ ፎገራ ወረዳ ላይ ስለለቅሶ ሥርዓቱ እውቀት አላቸው ተብለው በመንግስት ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ሰራተኞች በኩል የተገኙት ግለሰብ፣ አጥኚው ጋዜጠኛ መስሏቸው መረጃውን ለመስጠት ፈቃደኛ ሆነው ቀርበው፣ የጥናቱ ዓላማ ሲገለጽላቸውና የሚሰጡት መረጃ በተሌቪዥን ወይም በሬዲዮ እንደማይተላለፍ በግልጽ ሲነገራቸው፣ ቀጠሮ ሰጥተው ከሄዱ በኋላ፣ የተለያዩ ምክንያቶችን እየፈጠሩ ለመገኘት ፈቃደኛ ካለመሆናቸውም በላይ፣ ከሌሎች መረጃ አቀባዮች ጋር ግንኙነት እንዳይደረግ በር እየዘጉ መሆናቸውን ከረዳቶች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ የመጀመሪያው ዙር የመስክ ቆይታ ጊዜ በመገባደዱ መፍትሔ ሳያገኝ ከመስክ ቢወጣም፣ በሁለተኛው ዙር የመስክ ጉዞ መረጃዎቹን ለማሟላት ተችሏል፡፡

ከዋኞቹ ከሀዘንተቹ ጋር እየዞሩ ሲከውኑ በሚርቁበት ጊዜ፣ ጥራት የጎደለውና አንዳንዴም ተሟልቶ ሳይያዝ የቀረው የቃል-ግጥም መረጃ፣ ለትንተናው አልተመረጠም፡፡ በሌላ በኩል አንዳንድ የሚታወቁ ከዋኞች ለቅሶ ላይ ሲገኙ፣ መቅረጸ ድምጹ ተሰጥቷቸው ከከዋኞቹ ጋር አብረው እየዞሩ እንዲቀርጹ በማድረግ፣ አጥኚው በሚታወቅበት አካባቢ ደግሞ፣ ከሀዘንተኞቹ ጋር እየዞረ በመቅረጽ፣ ችግሩን ለመቀነስ ተሞክሯል፡፡

ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የተከሰተውን ጥናቱን በታቀደው መድረክ ለማቅረብ ያለመቻል ችግርና በዚሁ ምክንያት ሊከሰት ይችል የነበረውን ክፍተት ለመሙላት፣ ሦስተኛ ዙር የመስክ ጉዞ በማድረግ፣ የመረጃዎቹን አስተማማኝነት ለመጠበቅ ጥረት ተደርጓል፡፡

በዚህ የመስክ ጉዞ በአንድ በኩል በቃለ መጠይቅ የተገኙትንና ለትንተና የተመረጡትን መረጃዎች፣ ሌሎች መረጃ አቀባዮችን በመጠየቅ የምላሾቹን ተመሳሳይነት በማየት፣ በሌላ በኩል መረጃውን ከሰጡት ቁልፍ መረጃ አቀባዮች መካከል ለተወሰኑት የተሰጠውን ትንታኔ በማንበብ የሰጡት መረጃና በአካባቢው እየተተገበረ ያለው የለቅሶ ክወና ሳይቀነስና ሳይጨመርበት

መቅረቡን እንዲገመግሙ ተደርጓል፡፡ ሀይማኖታዊ ትዕምርትነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ የተካሄዱት ፍከራዎች ከሀይማኖታዊው ቀኖና ማፈንገጥ አለማፈንገጣቸውን እንዲያጣሩ በጥናቱ በቁልፍ መረጃ አቀባይነት ለተሳተፉት ለመሪጌታ ክፍለማርም አለነ (አባ.2.ቁ.2) በማስነበብና ማስተካካያዎችን በመቀበል፣ ችግሩን የማቃለል ጥረት ተደርጓል፡፡ አልፎ አልፎም ቀጥሎ እንደቀረቡት ያሉትን መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀም ሥራውን ለማሳካት ተችሏል፡፡

### 3.8.3. መልካም አጋጣሚዎች

ያልተጠበቁት መልካም አጋጣሚዎች ከቤተሰብ ትውውቅ ወይም በአካባቢው ከመወለድ ጋር በተያያዘ የተገኙ ናቸው፡፡ የተጠኚውን ማሕበረሰብ ከእምነት ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ያውቃሉ ለተባሉ የቤተክህነት ሰው የተጻፈ ደብዳቤ ለመስጠት አጥኚው ቢሯቸው ሲሄድ፣ መታመማቸው ስለተነገረው ቤታቸውን የሚያውቅ ዘመዱን ይዞ በመሄድ ያገኛቸዋል፡፡ የጥናቱን ዓላማ አስረድቶ ፈቃደኝነታቸውን ጠይቆ፣ መቼ እንደሚመቻቸው የቀጠሮ ቀን ሲያመቻች፣ መደብ ላይ ጋደም እንዳሉ፣ ሊነግሩት እንደሚችሉ በመግለጻቸው መቅረጫ መሳሪያዎቹን ሲያዘጋጅ፣ አብሮት ከሄደው ሰው ጋር አንዳንድ ነገሮችን ሲጨዋወቱ ወረዳ ቤተክህነት ውስጥ ይሰራ ስለነበረና ከስድስት ዓመት በፊት ስለሞተ ቄስ ልጆች ደህንነት ይጠይቁታል፡፡ ተጠያቂው ደህና መሆናቸውን ገልጾ፣ አጥኚው የዚያ ሰው የእህት ልጅ መሆኑን ሲነግራቸው፣ በጣም ተገርመው ማወቅ የሚፈልጋቸውን ጥያቄዎች ጽፎ እንዲሰጣቸውና ቀን ቆርጠው በዚያ ቀን ቢሯቸው ሄዶ እንዲያነጋግራቸው ይቀጥሩታል፡፡  አጥኚው በቀጠሮው ቀን ሲሄድ፣ ጥያቄዎቹን የሚመልሱ መጻሕፍትን በአይነት አዘጋጅተው፣ ማብራሪያቸውን በእነዚህ መጻሕፍት እያስደገፉ እጅግ መሰረታዊ የሆኑ መረጃዎችን ሰጡት፡፡ በመሀሉም፣ ‹‹የወዳጄ ዘር ሁነህብኝ ነው እንጂ ለመልሱማ ነካ ነካ አድርጌ በቀደም እሸኝህ አልነበር›› ያሉት በድንገት የተፈጠረለትን መልካም አጋጣሚ ያሳያል፡፡

ሁለተኛው መልካም አጋጣሚ በመስክ ሥራው መጀመሪያ፣ አጥኚው ተወልዶ ካደገበት አጎራባች ቀበሌ ገበሬ ማሕበር ዘመዱ የምትሆን ባልቴት ማረፏን በስልክ ሰምቶ በለቅሶው በመገኘቱ የተፈጠረ ነበር፡፡ ከሀዘንተኞቹ ጋር በመቀላቀል መረጃውን ለመቅረጽ፣ የታዋቂ ፎካሪ አማት በመሆኗ፣ ከሩቅ አገር ሳይቀር ወየባዮችና ሙሾ አውራጆች በመገኘታቸው፣ ጥሩ ጥሩ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ከመቻሉም በላይ፣ ከአንዳንድ ከዋኞች ጋር የአይን ትውውቅ ለመፍጠር እድሉን አግኝቷል፡፡ የሟች አማችም የጥናቱ ዓላማ ተነግሯቸው እንዲሳተፉ ሲጠየቁ፣

መረጃዎችን ለመሰብሰብ ከመቻሉም በላይ፣ ከአንዳንድ ከዋኞች ጋር የአይን ትውውቅ ለመፍጠር እድሉን አግኝቷል። የሟች አማችም የጥናቱ ዓላማ ተነግሯቸው እንዲሳተፉ ሲጠየቁ፣ የአጥኚውን በአማታቸው ለቅሶ መገኘት እንደትልቅ ቁምነገር በመቁጠር፣ በንቃት ተሳትፈዋል። በሌሎች ለቅሶዎች ከዋኞችን ለቀረጻ ፈቃድ ለመጠየቅ፣ በዚህ ለቅሶ ላይ ከነበሩ ከዋኞች ጋር የተፈጠረው የአይን ትውውቅ መንገዱ ቀና እንዲሆን አድርጓል።

አጥኚው በማይታወቅበት አካባቢ ከተጠራ ለቅሶ ሂዶ ፈቃድ ለማግኘት ኃላፊነት የሚወስድ ሰው አጥቶ በተቸገረበት ወቅት፣ ቀደም ሲል በቡድን ውይይቱ ከተሳተፉት ግለሰቦች መካከል አንዱን ማግኘቱ፣ ፈቃድ በማግኘት ብቻ ሳይሆን፣ በመረጃ ቀረጻውም አግዘውታል። ከሶስት የዕለት ለቅሶዎች የቀብር ሥርዓቶች ላይ ሙሾ ሲያወርዱ፣ ወየ ሲሉና ሲያስተባብሩ በዐይን የተዋወቃቸው መረጃ አቀባይ፣ በወረዳው ውስጥ የሚገኙትን ታዋቂ ፎካሪዎች፣ ወየባዮችና ሙሾ አውራጆች በመጠቆም፣ በጥቆማ የተገኙትም በተራቸው ሌሎቹን በመጠቆም፣ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጋቸው፣ ከመልካም አጋጣሚዎቹ ውስጥ በጉልህነት ሊጠቀሱ የሚችሉት ናቸው።

በዚህ ምዕራፍ ከጥናቱ ዘዴ እስከተገቢነቱ፣ አጥኚው ለተጠኚው ማሕበረሰብም ሆነ ለመረጃዎቹ ካደረጋቸው ስነምግባራዊ ጥንቃቄዎች፣ መረጃዎቹ እስከተሰበሰቡባቸው ዘዴዎች ተገቢነት፣ የመረጃዎቹን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ከታለፉባቸው መንገዶች፣ በሂደቶቹ እስካጋጠሙት መሰናክሎች፣ መሰናክሎቹ ከታለፉባቸው ዘዴዎች እስከተገኙት መልካም አጋጣሚዎች በመግለጽ የጥናቱን ዘዴ አጠቃላይ መልክ ለማሳየት ተሞክሯል። የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ ደግሞ፣ በሚቀጥለው ምዕራፍ ቀርቧል።

# ምዕራፍ አራት

## 5. የለቅሶ ሥርዓትና ቃል-ግጥሞች ክወና ትንተና

ቀደም ባሉት ሦስት ምዕራፎች የጥናቱ መግቢያ፣ ክለሳ ድርሳናትና የጥናቱ ዘዴ ቀርበዋል። በዚህኛው ምዕራፍ ደግሞ፣ የለቅሶ ሥርዓትና የቃል-ግጥሞች ክወና ተተንትኗል። የለቅሶ ሥርዓት፣ በማንኛውም ማህበረሰብ ሰው ሲሞት ቤተሰብ፣ ጓደኛ፣ ዘመድና ጎረቤት፣ ሟች የሚኖርበት ማህበረሰብ ባህል እንደሚፈቅደው፣ በተደራጀ መንገድ ሟችን የሚሸኙበት ሥርዓት ነው። ይህ ሥርዓት በማሕበራዊ የስምምነት ልማድ ላይ የተመሰረተ መጀመሪያና መጨረሻ ይኖረዋል። ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ድረስም በዚሁ ማሕበራዊ ስምምነት የሚመሩ የተለያዩ ድርጊቶች ይፈጸማሉ።

እነዚህን የተለያዩ ድርጊቶችና ልማዶች መስመር አስይዘው ካጠኑት ውስጥ፣ van Gennep (1908 [1960]) በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ። እኒህ ተመራማሪ የሞትን ሥርዓት፣ የመለየት (separation) የሽግግርና (transition) የመታቀፍ (incorporation) በሚሉት ሶስት ደረጃዎች ከፍለው ተመልክተውታል። የመለየት ሥርዓቱ እንደየሁኔታው የሟችን አስከሬን አፈር በማልበስ፣ ሳጥን ውስጥ በማስገባት፣ መገልገያ ቁሶቹንና ንብረቶቹን በማቃጠል፣ ሚስቱን፣ አገልጋዩን ወይም የሚወደውን እንስሳ በመግደል ይገለጻል። የሀዘን መግለጫው ደግሞ ሽግግር ነው። ሀዘንተኞቹ ከሟችም ሆነ ከጓደኛ ጎረቤቶቻቸው ይለያሉ። ለተወሰነ ጊዜ ከመደበኛ ማሕበራዊ ሕይወታቸው ይታቀባሉ። እያንዳንዱ ድርጊታቸው በነውሮች የተከበበ ነው። ሰውነታቸውን ማጎሳቆል፣ ከመደበኛው በወረደ መንገድ መልበስ፣ ደስታ ወዳለበት አለመሄድ፣ የዚህ ሥርዓት ጉልህ መገለጫዎች ናቸው። የመታቀፉ ሥርዓት፣ ሀዘንተኞቹ የሚጠበቁባቸውን ሥርዓቶች አሟልተው የመንጻት ሥርዓት ሲያከናውኑ ይጀመራል። ከማሕበረሰቡ ጋር የማንጫውን ምግብ ከበሉ በኋላ ወደመደበኛ ሕይወታቸው ይመለሳሉ።

ከዚህ በላይ የቀረቡት ሶስት ደረጃዎች በተለያዩ ባህሎች ውስጥ እንዳሉ ጥናቶች ቢያሳዩም፣ መገለጫዎቻቸው ላይ ግን ከባህል ባህል ልዩነቶች ይኖራሉ። ለምሳሌ ይህ ጥናት በተካሄደበት በደቡብ ጎንደር ዞን ማሕበረሰብ፣ ከላይ ድንበር ተለይቶላቸው የተቀመጡት የሽግግርና የመታቀፍ ስርዓቶች የሚከወኑባቸው ጉልህ ድንበሮች ያሏቸው አይመስሉም።

ስለሆነም ተጠኚው ማሕበረሰብ ሞት ሲከሰት የሚያከውናቸውን ድርጊቶችና የሚፈጽማቸውን ልማዶች፣ ከባህሉ ጋር አጣጥሞ በሚገባ ለመመርመር፣ በእነጀኔፕ የሥርዓት መዋቅር ላይ መጠነኛ ማስተካከያዎች ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ የለቅሶ ሥርዓቱ፦ የቀብር፣ የሀዘንና የመታሰቢያ በሚሉት ሶስት ሥርዓቶች ተከፍሏል።

ሥርዓቶቹን ለመክፈል ከቅደም ተከላዊ ክንውንነታቸው ይልቅ፣ ለምንነታቸው ወይም ለትኩረቶቻቸው ቦታ ተሰጥቷል። ሥርዓቶቹን እንደነጄኔፕና ተርነር በቅደም ተከትል ለማየት ያልተፈለገው፣ በአንድ በኩል፣ ከላይ እንደተገለጸው በአንዱ ውስጥ ሌላው ጣልቃ ገብቶ ስለሚከወን ድንበር ለማበጀት ባለመቻሉ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ሙሉውን የለቅሶ ሥርዓት

ለመረዳት እንደገመድ ተሻርቧቸውንና እንደሰንሰለት ቁርኝታቸውን መነሻ በማድረግ እንጂ፣ እንደጡብ ድርድር በአንዱ ላይ የሌላውን መገንባት በማየት ስላልሆነ ነው። ምክንያቱም የሥርዓቶቹ ሕልውና የተመሰረተው በውስጣዊ ትስስር እንጂ፣ በየየቅል ንጣፍ ተደራርቦ አይደለም።

ይህ ትስስራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አጠቃላይ የለቅሶ ሥርዓቱንና በውስጡ ያሉትን ክወናዎች ምንነትና እንዴትነት በጥልቀት ለመረዳት፣ በክፍል በክፍል ማየቱ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣ በዚህ ምዕራፍ የቀብር ሥርዓትና የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ክወና ገለጻና ማብራሪያ ብቻ ቀርቧል።

## 4.1. የቀብር ሥርዓት ክወና ትንተና

የቀብር ሥርዓት ቆይታ እንደተጠኚው ማህበረሰብ ባህል፣ እንደ ሟች ማሕበራዊ ደረጃና፣ ሞት እንደሚከሰትበት ጊዜ የሚለያይ ቢሆንም፣ ነፍስ ከወጣበት አስከሬን አፈር እስከሚለብስበት ድረስ ያለውን ልዩ ልዩ ክወና ያካትታል። በቀብር ሥርዓት ስር፣ በቅደም ተከተል የሚከናወኑ የተለያዩ ሥርዓቶች አሉ። አስከሬን የመገነዝ፣ የሟችን ዜና ረፍት ይፋ የማድረግ፣ የገዞ ፍትሃትና የቀብር አፈጻጸም ሥርዓቶች፣ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በእነዚህ ሥርዓቶች የሚከናወኑት ተግባራት፣ አንድም ሀይማኖታዊ አለዚያም ዓለማዊ ይዘት አላቸው።

ሥርዓቶቹ በእነዚህ ሁለት ጎራዎች ተከፍለው ገለጻው ቀርቧል። እያንዳንዳቸውን በውል ለማሳየት በሁለት ቢከፈሉም፣ ሀይማኖታዊው ሥርዓት ከዓለማዊው ሥርዓት ጎን ለጎን የሚከናወንና የአንዱ ሥርዓት ወደሚቀጥለው ደረጃ ሽግግር፣ በሌላው ሥርዓት መፈጸም ላይ የተመሰረተ በመሆኑ፣ ጥብቅ ትስስር አላቸው። ስለሆነም ተነጣጥለው ሲታዩ የሥርዓቶቹ ቅደም ተከተላዊ የክወና ፍሰት የተቆራረጠ እንዳይሆን፣ በሀይማኖታዊ ሥርዓቱ ገለጻ ወቅት፣ ጎን ለጎን የሚከወኑ ዓለማዊ ሥርዓቶች፣ የት ላይ ተሻርበው እንደሚከወኑ ከመጠቆም ውጭ፣ ስለክወና ባህሪያቸው ሰፊ ማብራሪያ አልተሰጠም። በዓለማዊው ሥርዓት ገለጻ ወቅት፣ ጎን ለጎን ለሚካሄዱት ሀይማኖታዊ ሥርዓቶችም እንደዚሁ። በቅድሚያ እስከቀብር ድረስ የሚከናወኑ ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች ቀጥሎ ቀርበዋል።

### 4.1.1. እስከቀብር ድረስ የሚፈጸሙ ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች ክወና

እስከቀብር ድረስ የሚከወኑትን ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች ከመግለጽ በፊት፣ በተጠኚዎቹ ውስጥ የሚገኙትን የለቅሶ አይነቶች መለየት አስፈላጊ ነበር። ምክንያቱም በየለቅሶ አይነቶቹ የሚኖረው ክወና ተመሳሳይ ላይሆን ስለሚችል ነው። በዚህም መሰረት የደቡብ ጎንደር ዞን የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ሦስት የተለያዩ የለቅሶ አይነቶች እንዳሏቸው በምልከታና በቃለ መጠይቅ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል። እነሱም፡- የዕለት፣ የቀጠሮና የመርዶ ለቅሶዎች ናቸው። የዕለት ለቅሶ ሬሳ ባለበት የሚካሄድ ሲሆን፣ የቀጠሮ ለቅሶ ሟች ባረፈበት ወቅት፣ በችግር፣ በውሃ ሙላት ወይም በሌላ ምክንያት፣ ሩቅ ያሉት ዘመዶቹ ሳይጠሩ ሟች ከተቀበረ በኋላ፣ አመች ጊዜ ተመርጦና ቀን ተቆርጦ፣ ሩቅ ላሉት ዘመዶቹ መልዕክት እንዲደርስ ተደርጎ፣ የሚካሄድ የለቅሶ አይነት ነው። የመርዶ ለቅሶ ደግሞ፣ ሟች ከትውልድ አካባቢው እርቆ በሚኖርበት ቦታ ሞቶ ከተቀበረ በኋላ፣ የቅርብ ቤተሰቦቹ ወይም ዘመዶቹ በጠዋት ተቀስቅሰው የሟችን ማረፍ የሚረዱበት የለቅሶ አይነት ነው። በየለቅሶ አይነቶቹ የሚከናወኑት መንፈሳዊ ሥርዓቶች ቀጥሎ ቀርበዋል።

#### 4.1.1.1. በዕለት ለቅሶ እስከቀብር ድረስ የሚከናወኑ ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች ክወና

በደቡብ ጎንደር ዞን የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ማሕበረሰብ፣ ትልቅ ትኩረት ከሚሰጣቸው የለቅሶ አይነቶች ዋናው የዕለት ለቅሶ ነው። በዚህ ለቅሶ የሚከተሉት ሥርዓቶች በቅደም ተከተል ይከናወናሉ።

##### 4.1.1.1.1. ግንዘትና ከፈን

በተጠኚው ማሕበረሰብ ከግንዘት በፊት ተመሳሳይ የሬሳ ማሰናዳት ልማድ እንዳለ ከላይ ጋይንት አቶ ገበያው አለሜ (አባ.2.፣ ቁ.11፣ ክፍ.1.1.1.1.1.፣ አን.1)፣ ከፎገራ አቶ ትእዛዙ አያሌው (አባ.2.፣ ቁ.20.፣ ክፍ.1.1.1.1.1.፣ አን.1)፣ ከፋርጣ አቶ አራጋው ታረቀኝ (አባ.2.፣ ቁ.32.፣ ክፍ.1.1.1.1.1.፣ አን.1)፣ ከደብረታቦር ዙሪያ፣ አቶ ጸጋዬ ጀንበሬ (አባ.2.፣ ቁ.19.፣ ክፍ.1.1.1.1.1.፣ አን.1) እና ከስማዳ አባ አቸነፍ እንግዳ (አባ.2.፣ ቁ.12.፣ ክፍ.1.1.1.1.1.፣

አን.1) ያስረዳሉ፡፡ እነዚህ መረጃ አቀባዮች በተመሳሳይ ሁኔታ እንደሚገልጹት፣ የሟች ነፍስ እንደወጣች በቅርብ የተገኘ ሰው፣ የፈጠጡ ዓይኖቹ እንዲከደኑና የተከፈተ አፉ እንዲገጠም ያደርጋል፡፡ በአፍና አፍንጫው የወጣ ፈሳሽ ካለም ይጠርጋል፡፡ ሟች ነፍሱ ስትወጣ በጣር ተይዞ በሚንፈራገጥበት ጊዜ እግሮቹና እጆቹ ሊዛቡ ስለሚችሉ፣ ወደትክክለኛ ቦታቸው መልሶ፣ ከታጠፉም ወደታች ቀጥ አድርጎ ዘርግቶ ካስተካከለ በኋላ፣ አንጋሎ በማስተኛት ፊቱን ጭምር ሸፍኖ ኩታ ያለብሰዋል፡፡ ሬሳው ፊት ለፊት ከሚመጣ ሰው እይታ በመጋረጃ እንዲከለል ይደረግና በመጀመሪያ በውሃ ይታጠባል፡፡ ሬሳው በውሃ ከታጠበ በኋላ እንደገና በእንተ ድህነተ ነፍስ የሚለው መስተብቁዕ፣ መቶ ሃምሳ መዝሙረ ዳዊት፣ አስራ አምስቱ መሐልየ ነቢያት፣ አምስቱ መሐልየ ሰሎሞን፣ ወንጌለ ዮሐንስ፣ ውዳሴ ማርያምና አንቀጸ ብርሃን በተጸለየበት ጠበል ይታጠባል (መላከ ሰላም ዳኛቸው እና ሌሎችም፣ 1986፣13)፡፡

ሬሳ በውሃ የሚታጠበው ሟች ራሱን ስለማይቆጣጠርና የተለያዩ ፈሳሾች ስለሚወጡት ንጽህናውን ለመጠበቅ ሲባል እንጂ ሌላ ትርጉም የሌለው መሆኑን መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ፡፡ ካህናቱም ሟች ንጽህናውን ሳይጠብቅ ወደቤተክርስቲያን መግባት እንደሌለበት በቀኖና ቤተክርስቲያን ስለተደነገገ እሱን ለመፈጸም ተብሎ እንደሚደረግ ያስረዳሉ፡፡ የተጠኚው ማህበረሰብ የሀዘን አገላለጽ ልማድ በብሉይና በሀዲስ ኪዳኖች ከሚፈጸሙት ልማዶች ጋር የጠበቀ ቁርኝት ያለው ከመሆኑ አኳያ ሲታይ፣ ሬሳን በውሃ ማጠቡም ከዚህ ሀይማኖታዊ ትውፊት ጋር ተያያዥነት ይኖረዋል ቢባል ያስኬዳል፡፡ ምክንያቱም በሐዋርያት ሥራ (9፣38) ላይ፣ ጣቢታ የተባለች ሴት እንደሞተች፣ ሥርዓተ እጥበት የተፈጸመላት መሆኑ ተጠቅሶ ስለሚገኝ ነው፡፡ ከውሃ እጥበቱ በኋላ በተጸለየበት ውሃ (ጠበል) መታጠቡ ደግሞ፣ ጠበሉ በሽተኞችን እንደሚፈውስ ሁሉ፣ ሬሳውም ላይ ሲረጭ መድሃኒት ነው ተብሎ ስለሚታመን መሆኑ በቀኝ ጌታ ዜናዊ ስቡህ (አባ፣2፣ ቁ.1) ተገልጿል፡፡

የሬሳ በውሃ መታጠብ በተጠኚው ማሕበረሰብ ከዚህ የተለየ ትርጉም እንደሌለው ቢገለጽም፣ በአንዳንድ የአፍሪካ ማሕበረሰቦች ግን እጥበቱ ከንጽህና መጠበቂያነት ያለፈ ትርጉም እንዳለው የሚያሳዩ መረጃዎች ተገኝተዋል፡፡ ለምሳሌ Alembi (2002) በአባንዮሌ ማህበረሰብ ላይ ያደረጉት ጥናት ውጤት እንደሚያሳየው፣ በዚህ ማሕበረሰብ የሬሳ በውሃ መታጠብ የአሮጌውን ሕይወት መጠናቀቅና የአዲሱን ሕይወት መጀመር (ሽግግሩን) አመልካች ነው፡፡ ሽግግሩ ለሬሳው

ከሕያውነት ወደሙትነት፣ ለሕያዋኑ ከመደበኛ ሕይወት ወደሀዘንተኝነት ጎራ በመግባት ይገለጻል።

በእስራኤልም አንዳንድ አክራሪ አይሁዶች፣ በመካከለኛው ዘመን ከሌሎች በወረሱት ልማድ ሬሳ በውሃ ያጥባሉ። ይህን ልማድ የሚያከናውኑት ደግሞ፣ ጣረሞትና መናፍስት ውሃ አይሻገሩም ብለው በማሰብ *(ሬሳውን መናፍስት እንዳይከተሉት)*[*] እንደሆነ Levine (2004፣104) ይገልጻሉ። ይህ ልማድ በትግራይ፣ በሸዋ ክርስቲያን አማራ፣ በሀረሪና በሀረር ሙስሊም ገበሬዎች እንደሚፈጸም የግንዘት ሥርዓት በተገለጸበት ክፍል መጠቀሱ ይታወሳል። ልማዱ በተለያዩ ማሕበረሰቦች ብቻ ሳይሆን፣ በተለያዩ ሀይማኖቶች በተመሳሳይ ሁኔታ የሚፈጸምበትን የጋራ ምክንያት ለመመርመር ተሞክሯል። የጋራ ጉዳዮቹንም በሁለት መሰረታዊ ነጥቦች ከፍሎ ማየት ይቻላል።

የመጀመሪያው ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ከንጽህና መጠበቂያነት ጋር ይያያዛል። ይህ በአንድ በኩል በጣር ጊዜ ከሟች የሚወጡትን ፈሳሾች ለማጽዳት፣ በሌላ በኩል የአስከሬኑ ጠረን በቶሎ እንዳይቀይር ለመከላከል ሲባል፣ እጥበቱ ሊከናወን ይችላል። በሞት ጊዜ የሚወጡት ፈሳሾችም ሆኑ የአስከሬን መበስበስ ዘርና ሀይማኖት ሳይለዩ በሁሉም የሰው ልጅ ላይ የሚከሰቱ መሆናቸው ደግሞ፣ ለልማዱ በሁሉምና በስፋት መገኘት ምክንያት ሆነዋል ቢባል ያስኬዳል።

ሁለተኛው ምክንያት ከማሕበረሰብ ማሕበረሰብና ከሀይማኖት ሀይማኖት የተለያየ ትርጉም ስለሚሰጠው እንደላይኛው የጋራ ምክንያት ሊወጣለት አይችልም። በውሃ መታጠብ እንደየማሕበረሰቦቹ ባህልና ሀይማኖት፣ ከላይ በተናጠል እንዳየናቸው የየራሳቸው ትዕምርታዊ ፍች ሊኖራቸው ይችላል። ውሃ ለሰው ልጅ ከሚሰጠው አገልግሎትና ከህይወት መሰረትነቱ አንጻር፣ የወል ትዕምርትነት ሊያዳብር እንደሚችል መገመት ግን ይቻላል። ሰባ አምስት እጁ የዓለማችን ክፍል በውሃ የተሸፈነ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ የዚህን ያህሉ የሰውነታችን ክፍልም ውሃ መሆኑ፣ ውሃ ለህይዎት አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን በተፈጥሮም ሰፊውን ድርሻ የያዘ መሆኑን ያሳያል። እነዚህ ሁለት ነገሮች ከአገልግሎቱ የሚመነጩ የጋራ ትእምርቶችን ሊያፈልቁ እንደሚችሉ ለመገመት አያስቸግርም። ስለሆነም፣ ውሃ ለክርስቲያኖች የህይወት ‹‹ከውሃና

---

[*] በቅንፉ ውስጥ ያለው ሀሳብ የአጥኚው ነው።

ከመንፈስ ቅዱስ ያልተወለደ ሰው ወደእግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም›› ብሎ ኢየሱስ ክርስቶስ ለኒቆዲሞስ እንዳስረዳው (ዮሐ.3፣5)፣ ለሙስሊሞች የመንጫ (ወደፈጣሪ የመቅረቢያ) ትእምርትነት አለው። ከእነዚህ የመታደስ፣ የመንጻትና የሽግግር ትዕምርቶች ሊወጡ መቻላቸው ልማዱ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት በአንዱ ወይም በሌላው በስፋት ለመገኘቱ ምክንያት ሊሆን ችሏል ቢባል ያስኬዳል።

ሲጠጡት ጥም ማርካቱ፣ ነፍስ በሀጢያት ስትያዝ ጠውልጋ ስትነጻ ከመርካቷ፣ እድፍ ማስለቀቁ፣ ከሀጢያት ከማንጻቱ፣ አትክልቶችን ማለምለሙ፣ ነፍስን ከማሳበብና ለፍሬ ከማብቃቱ፣ አካባቢውንና መልክን ማሳየቱ መልክአ ነፍስን ከእግዚአብሔር ከማገናኘቱ ጋር ይያያዛሉ።

ሬሳው ከታጠበ በኋላ ችሎታው ያላቸውና ሀይማኖታዊ ሥርዓቱ የሚፈቅድላቸው ሰዎች ወደመጋረጃው ይገቡና፣ የግንዘትና ከፈን ሥርዓቱን ያከናውናሉ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በምትከተለው ሥርዓት መሰረት የግንዘትና የከፈን ሥርዓት እንደሚች ማዕረግ በሚከተሉት መንገዶች እንደሚከወን፣ መላከ ሰላም ዳኛቸውና ሌሎችም (1986፣14-16) ይገልጻሉ።

> የሰው ልጅ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ አካሉ ታጥቦ ሽቱ ተቀብቶ (ተርከፍክፎ) የሰውነቱ ክፍሎች እንደሚገባ ተገጣጥመውና ተስተካክለው የእግሩና የእጁ ጣቶች በፈትል ታስረው በአዲስ ልብስ (ከፈን) ተጠቅልሎ ይገነዛል። በልብሰ መግነዙም ላይ … ወላዲተ አምላክ፣ ወላዲተ እግዚአብሔር፣ ወላዲተ መድኅን፣ ወላዲተ ሕይወት፣ ወላዲተ ክርስቶስ፣ ወላዲተ ኢየሱስ፣ ወላዲተ አማኑኤል ወዘተ. የሚባሉት የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ጸሎቶች ይጸለያሉ።
>
> የአገናነዙም ሥርዓት በክርስትና ሃይማኖት የተለያየ ማዕረግና ትርጉም አለው። ሟች ካህን ከሆነ የክህነት ቀሚሱን እንደለበሰ እጆቹ በትዕምርተ መስቀል ተመሳቅለው በአዲስ ልብስ ይገነዛል። ‹መስቀሌን ተሸክሞ ያልተከተለኝ ሊያገለግለኝ አይችልም› ባለው መሰረት በስልጣነ ክህነቱ ምዕመናንን ይባርክና ነገረ መስቀሉን ያስተምር እንደ ነበር ለማዘከር ነው።

በድኑ በአዲስ ልብስ ከተጠቀለለ በኋላ በሦስት ክር (ማዕተብ) ይታሰራል። በተጨማሪም ሰባት ትእምርተ መስቀል ያለበት ማዕተብ ተሰርቶ ከሰባት ቦታ ላይ ይቋጠራል። ይኸውም አንዱ በራስ፣ አንዱ በእግር፣ አንዱ በቀኙ፣ አንዱ በግራው፣ ሦስቱ በመካከል ሆኖ ይቋጠራል። ይህም ሥርዓት በሚፈጸምበት ጊዜ አስራ ሁለት መብራት* ይበራል። መብራቱም የሚበራበት ምክንያት ከዚህ የጨለማ ዓለም ወደ ብርሃን ዓለም መሄዱን ያመለክታል።

ሚች መነኮስ ቢሆን፣ እጆቹን በዐይኖቹ ላይ ጭኖ ይገነዛል። ይህም ሟቹ መነኮስ በዚህ ዓለም በሕይወተ ሥጋ በነበረበት ጊዜ በዐይኖቹ የዚህን ዓለም ክፉ ነገር ከማየት ተአቅቦ አድርጎ መኖሩን የሚያመለክት ነው። የፈትሉ፣ የከፈኑና የመግነዙ የመብራቱም ሥርዓት ለቄሱ እንደ ተፈጸመ ለሁሉም በየመዓረጋቱ ይፈጸማል።

ሟች ዲያቆን ሲሆን ግን እጆቹን ግራና ቀኝ አስተላልፎ በሠቅ (ቀበቶ) መልክ በትጥቅ መዋያው ላይ በማሳረፍ ይገነዛል። ይህም የሚያመልክተው ዲያቆናት፣ በሕይወት ዘመናቸው እንደ ቀዳሜ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት ለተልእኮ ሲፋጠኑ መኖራቸውን ነው።

በድኑ እንደተለመደው በአዲስ የከፈን ጨርቅ ከተጠቀለለ በኋላ፣ በሁለት ፈትል ክር (ማዕተብ) ይታሰራል። በፈትሉ አስተሳሰር የሚደረገው የመስቀል ምልክት ለቄሱ እንደ ተደረገ ለዲያቆኑም ይፈጸማል። ይህም በሚፈጸምበት ጊዜ ሰባት መብራት ይበራል።

ሕዝባዊ ከሆነ ግን አውራ ጣቶቹ በፈትል ታስረው እጆቹን በብልቱ ላይ ጭኖ ይገነዛል። ይህም በህጋዊ ጋብቻ ተወስኖ መኖሩን የሚገልጥ ነው። ሥርዓቱ ሁሉንም ጾታ … ያጠቃልላል። … በድኑም የሚታሰረው በአንድ ክር ነው። ለህዝባዊ የሚበራው መብራት አራት ነው።

---

* መብራቱ በግንዘት ወይም ከሰባቱ ሥርዓተ ጸሎቶች በኋላ አስከሬኑ ቤተክርስቲያኑን እየዞረ ሲታወድ ወይም በሁለቱም ጊዜያት ሊበራ እንደሚችልና ከአካባቢ አካባቢ ልዩነት እንደሚታይ መሪጌታ ክፍለማርያም ያስረዳሉ። በደቡብ ጎንደር በግንዘት ጊዜ፣ በሰሜን ጎንደር ደግሞ በኡደት ጊዜ እንደሚበራም ከልምዳቸው በመነሳት ይገልጻሉ።

አባ ዮሐንስ (1987፣41) በተግሳጽ መጽሐፋቸው፣ ይህንኑ የግንዘት ልማድ በተመሳሳይ መንገድ ገልጸውታል።



ሥዕል ሁለት[*]፣ የካህናትን አገናነዝ የሚያሳይ



ሥዕል ሦስት፣ የመነኮሳትን አገናነዝ የሚሳይ



ሥዕል አራት፣የዲያቆናትን አገናነዝ የሚያሳይ



ሥዕል አምስት፣ የሕዝባውያንን አገናነዝ

በዚህ ሀይማኖታዊ ትውፊት መሰረትነት የግንዘትና የከፈን ሥርዓቱ በተጠኚው ማሕበረሰብ በሚከተለው መንገድ እንደሚፈጸም መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ።

የመገነዝ ሥርዓቱ፣ በደብረ ታቦር በዚሁ ችሎታው በሚታወቅ ወንድ የዕድር አባል፣ በላይ ጋይንት በቅርብ ወንድ ቤተሰብ ወይም ዘመድ (ለመነኮሳት ቄስ)፣ በስማዳና በፎገራ፣ ችሎታው ባለው አዋቂ ወንድ ይፈጸማል። ሴት የማትገነዘው ከቤተመቅደስ ካለመግባቷ ምስጢር ጋር እንደሚያያዝ መሪጌታ ክፍለማርም አለነ (አባ.2.፣ ቁ.2፣ ክፍ.1.1.1.1.1.፣ አን.1-9) ያስረዳሉ። የግንዘት ሥርዓቱም የእጅና እግር አውራ ጣቶቹ ታጥፈው እንዳይገሩ ወይም እንዳይዛነፉ፣ ጎን ለጎን ተገጥመው በክር ይታሰሩና አስከሬኑ ከስር ውሃ ባልነካው አቡጀዴ ወይም ነጠላ፣ ከላይ በነት ወይም በሰሌን ይጠቀለላል። ከዚያ እንደሟች ማዕረግ በተዘጋጀለት ባለሶስት፣ ባለሁለት ግማድ ወይም ነጠላ ክር ከእግሮቹ ጀምሮ እስከአንገቱ ድረስ ሰባት ቦታ ላይ በትእምርተ መስቀል አምሳያ ይታሰርና ተንጋሎ እንዲቆይ ይደረጋል።

[*] ሁሉም የግንዘት ሥዕሎች የተወሰዱት ከመጽሐፈ ግንዘት ነው።

ሬሳው የሚያድር ከሆነ ተስተካክሎ እንዲቀመጥ ከተደረገ በኂላ፣ የክፈና ሥርዓቱ በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ይደረጋል። በጋይንት ሬሳ ሳይከፈን በሚያድርበት ጊዜ እንዳይበላሽ (ከውስጥ ያለው ፈሳሽ እንዲንጠፈጠፍ) ባፉ ተደፍቶ እንዲተኛ ይደረጋል። አስከሬኑ በዕለቱ የማይቀበር ከሆነ፣ መከፈኛ ጨርቅ በማይኖርበት ጊዜ ተገዝቶ እስኪመጣና፣ ባለሙያም በወቅቱ በማይገኝበት ጊዜ እስኪፈለግ፣ የግንዘት ሥርዓቱ በሚቀጥለው ቀን ሊካሄድ ይችላል።

ሬሳ ውሃ ባልነካው አዲስ ፈትል ወይም አቡጀዲ የሚከፈነው፣ ለምን እንደሆነ የተጠየቁት መረጃ አቀባዮች፣ ባሕል በመሆኑ ከመደረጉ ውጭ፣ ሌላ ትርጉም ስለመኖሩ የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ገልጸዋል። በሀይማኖቱ ግን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ከተልባ እግር በተሰራ ልዩ በፍታ (ጥሩ ለስላሳ ልብስ)፣ ከመገነዙ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ቀኝ ጌታ ዜናዊ ስቡህ (አባ.2.፣ቁ.1) እና መሪጌታ ክፍለማርያም አለነ (አባ2.፣ቁ.2) ያስረዳሉ። ቀደም ሲል በሌሎቹ ሥርዓቶች እንደተገለጸው ሁሉ፣ የከፈን ሥርዓቱም ከአይሁድ ልማድ ጋር የተሳሰረ ሆኖ ተገኝቷል። ስለሆነም ተጠኚው ማህበረሰብ ለከፈን የሚጠቀምበት ልብስ ውሃ ያልነካው መሆኑ፣ በአንድ በኩል ኢየሱስ ክርስቶስ ማንም ባልተጠቀመበት አዲስ በፍታ ከመገነዙ፣ በሌላ በኩል ከሬሳ ክቡርነት ጋር በተያያዘ ‹‹ንጹህ ነገር ቢደረግለት ጥሩ ነው›› ከሚል የመነጨ መሆኑን ከቀኝ ጌታ ዜናዊ ስቡህ (አባ፣2፣ ቁ.1፣ ክፍ.1.1.1.1.1.፣ አን.7) ማብራሪያ ለመረዳት ተችሏል። ማሕተም ሥላሴ (1960፣34) ደግሞ፣ ሟች በሕይወት ሳለ ይለብሰው በነበረው ሸማ ከተጠቀለለ የሰራውን ሁሉ ይመሰክርበታል ተብሎ ስለሚታመን በአዲስ ጨርቅ እንደሚከፈን ይገልጻሉ።

ይህ ሀይማኖታዊ ማብራሪያ፣ ውሃ ያልነካው ጨርቅ ለማህበረሰቡ የሚሰጣቸው ሌሎች ከእምነት ጋር የተያያዙ አገልግሎቶች እንዲቃኙ አነሳስቷል። በቅኝቱም ሰው ያልተጠቀመበት ንጹሕ ልብስ ለሬሳ መከፈኛ ብቻ ሳይሆን፣ ሕጻናት ክርስትና ሲነሱ በጠበሉ ከተጠመቁ በኂላ የሚታቀፉበት፣ በሥርዓተ ምንኩስናም ጸጉር ከተላጨ በኂላ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚጫነው ቆብ፣ ከተመሳሳይ ጨርቅ የሚዘጋጅ መሆኑን ከልምድ ለመገንዘብ ተችሏል። ከዚህም በተጨማሪ፣ ከሚታሰሩ ወይም እንዲሸተቱ ከሚደረጉ ባሕላዊ መድሃኒቶች ውስጥ አብዛኛዎቹ፣ በዚሁ ጨርቅ እንደሚቋጠሩ ለመገንዘብ ተችሏል። ለጊዜው የመድሃኒቱ ተትቶ ሶስቱ ሥርዓቶች (ግንዘት፣ ክርስትና መነሳትና ምንኩስና) ሲታዩ፣ ከአንድ የሕይወት ምዕራፍ ወደሌላው የሚደረጉ ሽግግሮች ሆነው ይገኛሉ። ስለሆነም ሰው ያልተጠቀመበት ንጹሕ ልብስ ይህንን ሽግግር የማስፈጸሚያ ወይም የማብሰሪያ ትዕምርትነት አለው ለማለት ይቻላል።

በክለሳ ድርሳናቱ ስለሞት አይነቶች በተብራራበት ክፍል በአባ መልከ ጸዴቅ (1984፣80) እንደተገለጸው፣ ሞት ከዚህ የመከራ ዓለም የመገላገያና ዘላለማዊ ሠላም ወደሚገኝበት ዓለም መሸጋገሪያ ደልድይ ተደርጎ ይታያል። መሪጌታ ክፍለማርያም አለነ (አባ.2፣ቁ.2) እንደሚያስረዱት ደግሞ፣ ክርስትና መነሳት አንድ የኦርቶዶክስ ሀይማኖት ተከታይ ከአብራክ መንፈስ ቅዱስ አዲስ ልደትን የሚያገኝበት ተድርጎ ይወሰዳል። ምንኩስናም በንስሃ ከሀጢያት ራስን አጽድቶ ከዓለማዊ ኑሮ ወጥቶ ወደመንፈሳዊው ዓለም የሚገባበት ሆኖ ተገኝቷል።

ስለሆነም አዲስ ጨርቅ፣ ከጨለማ ሕይወት ወጥቶ የአዲስ ሕይወት መጀመርን የምስራች የማብሰር ትዕምርትነት አለው ለማለት ይቻላል። ምክንያቱም በሶስቱም ሥርዓቶች የሚታየው ዞሮ ዞሮ ከጨለማ ዓለም ወደብርሃን ዓለም መምጣትን ነውና፣ ልብሱ በአንድ በኩል የጨለማ ዘመን አብቅቶ የብርሃን ዘመን መጀመርን አብሳሪ፣ በሌላ በኩል በሰው ልጅ እድሜ በቁጥር የሚለካው የጥሮ ግሮ ዘመን አልቆ፣ በቁጥር የማይለካው ዘላለማዊ የደስታ ዘመን መጀመርን አብሳሪነት አለው።

በዓለማዊውና በተለመደው እይታ፣ የሰው ልጅ ተወልዶ እድሜው የፈቀደለትን ያህል ኑሮ ይሞታል። በመንፈሳዊው ይህ ከውልደት እስከሞት ያለው እድሜ በጨለማ የተዋጠ፣ መከራ የበዛበትና ከንቱ ተደርጎ ይታያል። ስለሆነም የሥጋዊ ሞት የመጨረሻ ጣር፣ የለዘላለማዊ ህይወት ልደት ምጥ ነው ለማለት ይቻላል። ይህ የጣርና ምጥ ፍጻሜ በነፍስ ከስጋ መለየት ሲቋጭ፣ አፈር ወደአፈር የመመለሱ ትንቢት እውን ሁኖ፣ ሽግግሩ ይጠናቀቃል። የልደትና ሞት ዓለማዊና ጊዜያዊ ዑደት፣ በሞትና ልደት መንፈሳዊና ዘላለማዊ አዙሪት ሲገለበጥ፣ አዲስ ጨርቅ በአጠቃላይ በሞት የመወለድ ትዕምርትነትም አለው ለማለት የሚቻል ይመስላል።

ከዚህም በተጨማሪ፣ አዲስ ጨርቅ የነጻ መውጣት ትዕምርትነት ዓለው። የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ለሰው ልጅ ነጻ መውጣት እንደሆነ በቅዱሳት መጻሕፍት ተደጋግሞ ተገልጾ ይገኛል። ለምሳሌ መላከ ሰላም ዳኛቸውና ሌሎችም (1986፣9) እንደሚገልጹት፣ አዳምና ሔዋን እንዳይበሉ የተከለከሏትን ዕፀ በለስ በመብላታቸው በደረሰባቸው እርግማን ዘራቸውና ትውልዳቸው በሞተ ሥጋ ወደመቃብር፣ በሞተ ነፍስ ወደሲኦል መውረድ ግድ ሁኖባቸው ሲኖሩ፣ አምላክ ተሰቅሎ ሞቶ ተነስቶ ዓለሙን በደሙ እስኪያድነው ድረስ፣ ሞት የበደሉትንም ያልበደሉትንም በአንድ ላይ ገዝቷል። በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ቅጽበት የተፈጸሙት ታምራት (የመቃብራት መከፈት፣ የሙታን መነሳት) የመርገመ ሞትን ድል መሆን አብሳሪዎች ተደርገው

ሊወሰዱ ይችላሉ። ይህም ሞት በሰው ልጅ ላይ የነበረውን ስልጣን የተነጠቀውና ድል የተነሳው፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ነፍስ ከስጋው በተለየችበት ቅጽበት እንደሆነ ያሳያል። ምክንያቱም መቃብራት የተከፈቱት፣ ሲኦል የተበረበረችውና አዳም ከነልጆቹ ነጻ የወጣው በዚህ ቅጽበት ነውና። ነፍስ ከሚያጎድፋት ሥጋ መለየቷ፣ ሕጻናቱ ከአብረከ መንፈስ ቅዱስ መወለዳቸው፣ (ከመንፈስ ቅዱስ ያልተወለደ ሕይወት የለውም እንዲል ዮሐ.3፣5)፣ መነኮሳት ለሥጋዊ ፍላጎት ከማጎብደድ ወጥተው፣ (አንድም ዓለምን በእነሱ ዘንድ በመግደል፣ አንድም ‹‹መነኮስ ሞተ››ን ተግባራዊ በማድረግ)፣ ለዘላለማዊ ሕይወት ወደሚያዘጋጀው መንፈሳዊ ሕይወት መሻጋገራቸው፣ ዞሮ ዞሮ የነፍስን ከእግዚአብሔር የሚለይ የስጋ ተገዥነት ነጻ መውጣት አመለካች ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ይህ የነፍስ ነጻ መውጣት የመጀመሪያው ማብሰሪያ ደግሞ ከኋላ ወደፊት ሲታይ፣ መታቀፊያ ቁራጭ (እራፊ)፣ ቆብና ከፈን እየሆነ በተመሳሳይ ይዘት፣ ግን በተለያየ ቅርጽና ስም የሚመጣው አዲስ ጨርቅ ሆኖ ተገኝቷል።

አስከሬን በጨርቅ ከተከፈነ በኋላ ከከፈኑ በላይ በሰሌን ወይም በነት እንደሚጠቀለል በገለጻው ክፍል ተጠቅሷል። ነቱና ሰሌኑ ስለሚኖራቸው ትርጉም የተጠየቁት መረጃ አቀባዮች፣ ነቱ የሚችን ክብር ለማሳየት ካልሆነ በስተቀር ሌላ ትርጉም እንደሌለው ገልጸዋል። ሰሌኑም ከአባት ሲወርድ የመጣ ባሕል በመሆኑ ከመደረጉ ውጭ ሌላ ነገር ስለመኖሩ የሚያውቁት ነገር እንደሌለ አስረድተዋል። ቀኝ ጌታ ዜናዊ ስቡህም (አባ..2.፣ቁ.1) ስለዚሁ ጉዳይ ምንነት ለቀረበላቸው ጥያቄ እሳቸውም እንደማያውቁትና ራሳቸውን ሲጠይቁ እንደኖሩ ገልጸዋል። የነቱና የሰሌኑ ለሀዘን መዋሉ ግልጽ ባይሆንላቸውም፣ በሀይማኖት ሰሌን ለደስታ መግለጫነት እንደሚያገለግል የሚከተሉትን መረጃዎች በማንሳት አብራርተዋል። አብርሃም ይስሃቅን፣ ይስሃቅ ያዕቆብን፣ በወለዱ ጊዜ፣ ዮዲት ሆሎፎርኒስን ገድላ እስራኤልን ነጻ ባወጣቻቸው ጊዜና በሆሳዕና፣ እሥራኤላውያን ደስታቸውን ለመግለጽ ሰሌን እየያዙ አመስግነዋል። መረጃ አቀባዩ ስለሞት ምንነት ባብራሩበት ክፍል፣ በኦርቶዶክስ ሀይማኖት ሟች ከዚህ የመከራና የሥቃይ ዓለም ተገላግሎ ዘላለማዊ ረፍት ወዳለበት ዓለም ይሄዳል ተብሎ እንደሚታመን ካነሱት ሀሳብ ጋር ይኽ ሲያያዝ፣ ሰሌኑ እንደአዲስ ጨርቅ፣ ከመከራ የመገላገል፣ ነጻ የመውጣት ትዕምርትነቱን አሁንም እንደያዘ ነው ቢባል የሚያስኬድ ይመስላል።

መሪጌታ ክፍለማርያምም የሰሌንን የድል አድራጊነት ትዕምርትነት ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ፣ የአባ እንጦንስን ታሪክ በማንሳት ያስረዳሉ። አባ እንጦንስን አጋንንት እየተፈታተነ

ሲያስቸግራቸው፣ ቅዱስ ሚካኤል ሰሌን እየሰራ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ሰባት ጊዜ ስለታያቸው ምንነቱን ሲጠይቁ፣ መልአኩ ጸሎታቸውን አድርሰው ሰሌን ከሰሩ መስቀል ስላለው አጋንንትን ድል እንደሚነሱበት ይነግራቸዋል፡፡ ልብሳቸውንና ቆባቸውን ሰሌን በማድረግ አጋንንትን ድል ስለነሱበት፣ ሬሳ በሰሌን መቀበሩ ይህን ዓለም ድል የመንሳቱ ምልክት ተደርጎ እንደሚወሰድ ለመረዳት ተችሏል፡፡

አስከሬኑ፣ ከስር ጨርቅ ከላይ ነት ወይም ሰሌን ተደርጎ ከተጠቀለለ በኋላ፣ እንደሚቹ ማዕረግ ሶስት ወይም ሁለት ሽርብ (ግማድ) ባለው ወይም በነጠላ ክር ሰባት ቦታ ላይ በትእምርተ መስቀል አምሳያ መታሰሩን ዓለማዊ መረጃ አቀባዮቹ ካባት የመጣ ልማድ በመሆኑ ከመደረጉ ውጭ ሌላ የሚያውቁት ትርጉም እንደሌለ ሲገልጹ፣ ሀይማኖታዊ መረጃ አቀባዮቹ ከልማዳዊ ትውፊትነቱ በተጨማሪ፣ ሌሎች ትረጉሞች እንዳሉት ያስረዳሉ፡፡ ሰባት ቁጥር ከሀይማኖት ጋር ያለውን ትዕምርትነት፣ ሰባት መላዕክት ከመኖራቸው፣ ሰባት በዕብራውያን የቁጥር ማብቂያ ከመሆኑ (አቆጣጠራቸው ሰባት ከደረሰ በኋላ እነዚያኑ ቁጥሮች ይደጋግማል)፣ እግዚአብሔር ዓለምን ስድስት ቀን ፈጥሮ ጨርሶ በሰባተኛውን ቀን ከማረፉ፣ አንድ ሱባዔ ሰባት ቀን ከመሆኑና ሰውም ከሰባት ባህርያት የተፈጠረ ከመሆኑ ጋር የተያያዙ ትዕምርቶች ያሉት መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ የክሮቹ ሶስት፣ ሁለትና አንድ መሆንም፣ የየራሳቸው ትርጉም አላቸው፡፡ ለምሳሌ ካህናት ሶስት ክሮች በአንድ ላይ ተገምደው መገነዛቸው፣ ምሥጢረ ሥላሴንና ስልጣናቸውን አመልክች ትዕምርትነት አለው፡፡ የፈተቱት የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም፣ አብ፣ ወልድና መንፈስቅዱስ የተዋሀዱበት ሶስትነት ያለው ሲሆን፣ በማዕረጋቸው ደግሞ፣ ሕዝባዊነት፣ ዲቁናና ክህነት ያላቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ዲያቆናት ሁለት ግማድ ባለው ክር መገነዛቸው፣ የሕዝባዊነትና ዲቁና ማዕረግ ያላቸው መሆኑን ያመላክታል፡፡ ሕዝባዊ በአንድ ክር የሚገነዘው፣ ተጨማሪ ማዕረግ የሌለው መሆኑን ማሳያ ነው፡፡

ካሕናቱ፣ ዲያቆናቱና ሕዝባውያኑ፣ በግንዘት ወቅት ያለምንም ልዩነት ሰባት ቦታ ላይ መታሰራቸው፣ ከላይ ከሰባት ቁጥር ጋር ተያይዘው ከተጠቀሱት ሀይማኖታዊ ክንውኖች ጋር የተሳሰረ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በሃይማኖቱ የሰባት ቁጥር በተለያዩ መንገዶች እየተደጋገመ መከሰት፣ ከቁጥሩ በእግዚአብሔር መባረክና መቀደስ ጋር በተያያዘ መሆኑ በብሉይና በሀዲስ ኪዳናት መጻህፍት ተገልጾ ተገኝቷል፡፡ ‹‹...እግዚአብሔርም ሰባተኛውን ቀን ባረከው፣ ቀደሰውም እግዚአብሔር ሊያደርገው ከፈጠረው ሥራ ሁሉ በእርሱ አርፎአልና›› (ዘፍ.2፣2)፡፡ ስድስት ቀን

በደመና ከተሸፈነው የሲና ተራራ በሰባተኛው ቀን የሙሴ መጠራትና የእግዚአብሔር ክብር መገለጥ (ዘጸ. 24፣16፡17)፣ የኢያሪኮ ግንብ ከስድስት ቀን ዙረት በኋላ በሰባተኛው ቀን ሰባተኛ ዙረት መፍረስ ጋር ሲታይ፣ በዚህ ቁጥር ልክ የሚፈጸሙትን ድርጊቶች መባረክና መቀደስ አጠይቆ ለድል መብቃትን ለመግለጽ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በተጠኚው ማሕበረሰብ ለካህንና ለመነኮሳት፣ ቀሳውስት ከመመረጣቸው በስተቀር፣ የሥጋ ዝምድና ወይም ልምዱ ያላቸው የመገነዝ ሥርዓቱን እንደሚያከናውኑ መረጃ አቀባዮቹ ይገልጻሉ፡፡ ፋሲካ እ.ኢ.አ (2002፣205-6) የሸዋ ክርስቲያን አማሮችን የግንዘት ሥርዓት በመረመሩበት ጥናት ግን፣ የግንዘት ሥርዓት የሚያከናውኑት ከሟች ጋር ተመሳሳይ ጾታና ማሕበራዊ ደራጃ ያላቸው ሰዎች ናቸው (ሕዝባዊን ሕዝባዊ፣ መነኩሴን መነኩሴ፣ መነኩሲትን መነኩሲት፣ ቄስን ቄስ)፡፡ በፋሲካ የተገለጸው የግንዘት ሥርዓት ከላይ በሀይማኖቱ ከተገለጸው በተለየ ሴቶች የሚገንዙ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ መሪጌታ ክፍለማርያም እንደሚያስረዱት ግን፣ ከሴቶች አለመገነዝ በተጨማሪ፣ ሕዝባዊ ሕዝባዊን እንጂ፣ ቀሳውስትንና መነኮሳትን እንዲገንዝ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን አይፈቅድም፡፡

ሬሳው ከላይ በተገለጸው መንገድ ከታጠበና ከተገነዘ በኋላ፣ የፍትሃት ጸሎት በሚከተለው መንገድ ይከናወናል፡፡

4.1.1.1.2. የፍትሀት ጸሎት

ከግንዘትና ከፈን ቀጥሎ የሚካሄደው ሀይማኖታዊ ሥርዓት ፍትሃት መሆኑ ከፍ ሲል ተገልጿል፡፡ የሟች ነፍስ በምትወጣበት ጊዜ ወይም ትንሽ ዘግየት ብሎ፣ ጸዓተ ነፍስ (የነፍስ መውጣት) ጸሎት ከመገነዙ በፊት ይደገማል፡፡ የፍትሃት ሥርዓት ሟች እንዳረፈበት ጊዜ እንደሚለያይ መሪጌታ ክፍለማርያም (አባ.2. ቁ.2.፣ ክፍ.1.1.1.1.2.፣ አን.1-6) ያስረዳሉ፡፡ ለምሳሌ ሟች ከቀኑ አስራ አንድ ሰዓት በኋላ ቢሞት ነፍሱ ስትወጣ ጸአተ ነፍስ ይደገምና፣ እንዲገነዝ ከተደረገ በኋላ፣ ሰዓታት (በሌሊት እግዚአብሔር የሚመሰገንበት ጸሎት) ተቁሞ ያድራል፡፡ ማንኛውም ሰው ምግብ አይበላም፡፡ ከዚያ ጠዋት ላይ ሬሳው ከቤት ሳይወጣ የመጀመሪያው የፍትሃት ጸሎት ይጸለይና፣ መቃብር እስከሚወርድ በአጠቃላይ ሰባት ጊዜ በገዞና በማርገጃ ሙሉ ፍትሃት ይፈታል፡፡

ጠዋትና ቀን ላይ የሚሞቱ በዕለቱ መቀበር ስላለባቸው፣ ሰአታት አይቆምላቸውም። ከጳጳሳት እስከዲያቆናት ላሉት ‹‹ስቡሀ›› (ምስጋና) ተብሎ የተለየ ጸሎት ከመደረጉ በስተቀር፣ ለማንኛውም ክርስቲያን በተመሳሳይ መንገድ የፍትሃት ጸሎት መካሄድ እንዳለበት ስርዓተ ቤተክርስቲያን እንደሚደነግግም ይገልጻሉ።

በተጠኚው ማህበረሰብ እየተተገበረ ያለው የፍትሃት ሥርዓት ግን፣ እንደሟች እድሜ፣ ማሕበራዊ ደረጃና ሀይማኖታዊ ማዕረግ ይለያያል። ሟች በጊዜ ሙቶ ሳይቀበር የሚያድር ከሆነ፣ የማታ ፍትሃት ይደረግለታል። እንዲህ የሚደረግለት ግን፣ ሟች ስልጣነ ክህነት ያለው፣ የመነኮሰ ወይም ለቤተክርስቲያን ያገለገለ፣ ግብረ ሰላም ያበላ (ለካህናት በዓመት በዓል በተለይ በትንሳኤ አካባቢ የሚቀርብ ግብዣ)፣ የእድሜ ባለጸጋና ወገን ያለው ከሆነ ነው። ከእነዚህ አንዱን ላሟላ፣ ካህናት ማታ ላይ ወደቤቱ መጥተው ፍትሃት እንደሚቆሙና እያሸበሸቡ እንደሚፈቱ አቶ ደጀን አመኑ (አባ2.፣ ቁ.17፣ ክፍ.1.1.1.1.2.፣ አን.1) ይገልጻሉ። ምልከታ በተካሄደባቸው የዕለት ለቅሶዎች ይህ ልዩነት መኖሩንና ለተራ ሰው የማታ ፍትሀት ማካሄድ የቀረ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

መሪጌታ ክፍለ ማርያም አለነ (አባ.2.፣ ቁ.2፣ ክፍ.1.1.1.1.2፣ አን.9) በቤተክርስቲያን ሥርዓት በማዕረግ ልዩነት ከሚኖረው ውጭ ሌላ ልዩነት እንደሌለ እንደሚከተለው ገልጸዋል።

> ... ‹ለእከሌ ይህን ያህል ፍታ፤ ለእከሌ ይህን ያህል ፍታ› የሚል ነገር የለም። እንደ ማዕረግ ግን አራት አይነት ፍትሃት አለ። አንዱ የመነኮሳት ወይም የባሕታውያን፣ ሁለተኛው የካህናት፣ ሶስተኛው የዲያቆናት፣ አራተኛው የሕዝብ ነው። ከዚህ ውጭ ‹እገሌ ግብረ ሰላም ስላበላ በተለየ ይፈታለት› የሚል የለውም። ለሀብታምና ለድሃ የሚል ልዩነት ካለ፣ ይኸ ሥርዓት የቤተክርስቲያን አይደለም። ምናልባት ግብረ ሰላም ያበሉ ሰዎች ለቤተክርስቲያን ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገውም ሊሆን ስለሚችል፣ እነዚህ ሰዎች ሲሞቱ በደንብ ካልተፈቱ ሌላውም ለመልካም ነገር አይነሳሳም በሚል ሀሳብ ልማዱን የሚያደርጉት ማህበረሰቦች አስበውት ሊሆን ይችላል። ግብረ ሰላም ስላበላ ከፍ ይበል አይባልም። መልካም ስላደረገ ግን ሌላውም ነገ እንደዚህ እንዲነሳሳ ከፍ ሊደረግለት ይችላል።

በማዕረጎቹ ምክንያት ከሚከሰቱት ልዩነቶች በተጨማሪ ሟች ከአስር ሰዓት በፊት ከሞተ ሀዘንተኞቹ ሬሳ አስቀምጠው እህል ስለማይበሉና ሟችም መቅመስ ያለበትን አፈር መቅመስ ስለሚኖርበት፣ በዕለቱ እንዲቀበር ሲደረግ በሰዓት እጥረት ምክንያት ሰባቱ ፍትሃቶች ሳይፈጸሙ የሚችሉበት አጋጣሚ መኖሩንም ይገልጻሉ (አባ2.፣ ቁ.2፣ ክፍ.1.1.1.1.2፣ አን.8)፡፡

ሟች ሌሊት ላይ አርፎ በዕለቱ የሚቀበር ከሆነ፣ ካህናት ቀደም ብለው መጥተው ከሟች ቤት እስከቤተ ክርስቲያን ሰባት ጊዜ የጉዞ ፍትሃት ያደርጋሉ፡፡ ሟች የሚኖርበት አካባቢ ከቤተ ክርስቲያን በጣም ሩቅ ሁኖ ካህናቱ ለጉዞ የሚቸገሩ ወይም ሟች በተላላፊ በሽታ ሞቶ ካልሆነ በስተቀር፣ ከሰባት ዓመት በላይ የሆነው ክርስቲያን ባረፈበት ቤት በጠዋት የፍትሃት ሥርዓት ይከናወንለታል፡፡ በተጠኚው ማሕበረሰብ በተለይ በከተሞች አካባቢ፣ ለፍትሃት ብዙም ትኩረት እየተሰጠው እንዳልሆነ የሚያመለክቱ መረጃዎች አሉ፡፡ የትኩረቱ መላላት ከማርፈድ፣ የጉዞ ፍትሃቶቹን በቤተክርስቲያን ላይ ብቻ እስከማካሄድ ባለው ይገለጻል፡፡ ለምሳሌ ከወ/ሮ ቀኑብሽ እ.ኢ.አ. በ22/09/2004፣ ከእሙሐይ አስማረች እ.ኢ.አ. በ1/10/2004 እና ከወ/ሮ ፀሐይ እ.ኢ.አ. በ09/10/2004 ከዋሉ የዕለት ለቅሶዎች ላይ በተደረገ ምልከታ፣ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ከሩብ እስከተኩል ባለው ጊዜ፣ ልብሰ ተክህኖ የለበሱና ጥላ የዘረጉ ሁለት ሁለት ቀሳውስትና ከሶስት የማያንሱ ዲያቆናት ለፍትሃት ሲመጡ ታይተዋል፡፡ በማርፈዳቸው በመናደድ ይመስላል ‹‹እኒህ ቄሶች እኮ ዝም ብለው አውጥተው ሊጥሉን ነው›› የሚል የለቀስተኛ ምሬትም ተደምጧል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ በደብረታቦር ዙሪያ ወረዳ፣ አስከሬን እስከአራት ሰዓት እንዲቀበር በመወሰኑ፣ የጉዞ ፍትሃት በጊዜ እጥረት ምክንያት እየቀረ መሆኑን መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ፡፡

ከሥርዓተ ቤተክርስቲያን ውጭ ከሚታዩት ልዩነቶች ውጭ ቤተክርስቲያን በተለያየ መንገድ ራሳቸውን ላጠፉ ሥርዓተ ፍትሃት እንዳይፈጽምላቸው የደነገገች መሆኗን መሪጌታ ክፍለማርያም (አባ2.፣ ቁ.2፣ ክፍ.1.1.1.1.2፣ አን.7)) እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> የሃይማኖቱ ተከታይ ሁኖ የሚፈታና የማይፈታ አለ፡፡ ለምሳሌ የሀይማኖቱ ተከታይ ሁኖ ታንቆ የሞተ በሥርዓተ ቤተክርስቲያን አይፈታም፡፡ ለምን ያው ራሱን ስላጠፋ ነው፡፡ ... ታንቆ የሞተው ክርስቲያንነቱ እንዳለ ቢሆንም እሱ የእግዚአብሔር ሕንጻ ሁኖ ሳለ ራሱን ስላጠፋ ከፍትሃ ነገስቱ ላይ ስለተከለከለ አይፈታም፡፡

መሪጌታ ዜናዊ ስቡህም (አባ.2፣ ቁ.1፣ ክፍ.1.1.1.1.2፣ አን.4) ሰው የእግዚአብሔር ሕንጻ (ቤተመቅደስ) ሁኖ ሳለ፣ ያልሰራውን ማፍረሱ ሀጢያት በመሆኑ የፍትሃት ሥርዓት እንደማይፈጸምለት ቅዱሳት መጻሕፍትን አጣቅሰው እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

> … ራሳቸውን ለሚያጠፉ ሰዎች የፍትሃት ጸሎት እንዳይደረግላቸው ቤተክርስቲያን ደንግጋለች። ዱሮ የሰው ልጅ ሞትን አመጣ። ዛሬም የሰው ልጆች ሞትን በተለያየ መንገድ ጎትተው ያመጣሉ። ይኸውም ጽንስን በማስወረድ፣ የራሳቸውንም የልጆችንም ሕይወት ያጠፋሉ። በመታነቅ፣ መርዝ በመጠጣትና በተለያዩ ድርጊቶች ሕይወታቸውን ያሳልፋሉ፤ ከዚህም ሁሉ ጋር ሰዎች በተፈጥሮ ሕማምና ጦርነትን ከመሰለ በሰውነታቸው ላይ በሚደርስ አደጋ ሲሰቃዩ በራሳቸው ወይም በሌላው ሕይወታቸው እንዲያልፍ የሚያደረጉም አሉ። ይህም ሁሉ በቅዱሳት መጻሕፍት የተከለከለና በቤተክርስቲያን የተወገዘ ነው፤ በዚህ አይነት አሟሟት ሕይወታቸውን የሚያጠፉ ሁሉ በሀይማኖት ትምህርት ተቀባይነት የላቸውም። በሞቱም ጊዜ በህግና በሥርዓት ኖረው በክብር ለሞቱ ሰዎች የሚፈጸመው የቤተክርስቲያን ጸሎተ ፍትሃት ሌላውም ስርዓት ሁሉ አይፈጸምላቸውም (2 ሳሙ.1፣1-10፤ማቴ. 27-30)።

የሟች ሬሳ ከቤት የሚወጣው ካህናቱ የጠዋት ፍትሃት ማጠናቀቃቸውን ለለቅሶ አስተባባሪው ካሳወቁና ቤተሰብ ወደቤት ገብቶ በመሪር ለቅሶ ከተሰናበተ በኋላ ነው። ሬሳ ሲወጣ ሲል መሪር ለቅሶ ለምን እንደሚለቀስ የተጠየቁት ቀኝ ጌታ ዜናዊ ስቡህ (አባ.2፣ ቁ.1) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፣ ለሞተ ሰው ነፍሱ ከስጋው በምትለይበት ጊዜ፣ በድኑ ከኖረበት ቤት ወጥቶ ወደ መቃብር ሲሄድና ግብዓተ መሬት ሲፈጸም፣ በእነዚህ በሶስቱ ጊዜያት ብቻ በስርዓት ማልቀስ ግዴታ እንደሆነ በመደንገጉ እንደሆነ ያስረዳሉ። እንደመረጃ አቀባዮቹ ማብራሪያ ደግሞ፣ ሟች የኖረበትን ቤት ለመጨረሻ ጊዜ ተሰናብቶ ሲሄድ የዓለምን ከንቱነት ስለሚያሳስብ በጽኑ ያስለቅሳል።

ሬሳው ከቤት ከወጣ በኋላ በካህናት የሚፈጸመው ሥርዓት፣ ከጉዞ ፍትሃት እስከስንብት ጸሎት ያለውን ያጠቃልላል። እንደመላከ ሰላም ዳኛቸውና ሌሎችም (1986፣22) ገለጻ፣ የሟች ሬሳ

ከቤት ወጥቶ ቤተክርስቲያን እስከሚደርስ ድረስ እንደአስፈላጊነቱ በሰባት ምዕራፎች የተከፈለ የጉዞ ፍትሐት ይደረግለታል።

መላከ ሰላም ዳኛቸውና ሌሎችም (1986፣21)፣ የፍትሀተ ጸሎት ሥርዓት የሚካሄደው፣ የሟች ነፍስ ይቅርታ እንድታገኝ ለመለመን መሆኑን እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

> ካህናት ጸሎተ ፍትሀት በሚያደርጉላቸው፣ መስዋዕትና ቁርባን ለእነርሱ በሚያቀርቡላቸው ጊዜ መላእክት፣ ነፍሳቸውን ለመቀበል ይወርዳሉና ኃጢአተኞች ከሆኑ ስለ ስርየተ ኃጢአት ይለምኑላቸዋል፤ ይማልዱላቸዋል። ንጹሃንም ከሆኑ ደስ ይላቸዋል። ‹ሰውን ለወደደው ለእግዚአብሔር በሰማያት ክብር ምስጋና ይገባል፣ በምድርም ሰላም› እያሉ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል። ይህም የመላእክት ምሥጋናና ደስታ ስለ ሰው ልጅ ድኅነት ነው ተብሎ ተጽፏል።

የፍትሀቱ ሥርዓት የቤተ መቅደሱን የቅዳሴ ሥርዓት የተከተለ እንደሆነና የሚካሄደውም፣ ቤተ መቅደስ የእግዚአብሄር ማደሪያ እንደሆነች ሁሉ፣ የሰው ልጅ አካልም የእግዚአብሔር ማደሪያ መሆኑን ለማጠየቅና በተለይም የሬሳን ክቡርነት ለማሳየት እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል። ፍትሀት፣ ከዚህ ዓለም በሞት የሚለዩት ሰዎች በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ከሰሩት ኃጢአትና ከፈጸሙት በደል እንዲነጹ ወይም ከሀጢአት ማሰሪያ እንዲፈቱ ወደእግዘአብሔር የሚቀርብ ጸሎት መሆኑንም ለመገንዘብ ተችሏል። በሌላ በኩል ሰባቱ የጉዞ ፍትሃት ከኢያሪኮ ግንብ መፍረስ* ጋር የተያያዘ ተምሳሌትነት ያለው ሁኖ ተገኝቷል። ኢያሱ ከእግዚአብሔር በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት፣ ሰባት ጊዜ የኢያሪኮን ግንብ ከወገኖቹ ጋር ሲዞር፣ ግንቡ እንደፈራረሰውና ጠላቶቻቸውን ድል እንዳደረጉት ሁሉ፣ ለሟች የሚፈጸምለት ሰባት የፍትሃት ጸሎትም፣ የሃጢያት ግንቡን ንዶ ወደጽድቅ የሚያስገባው መሆኑን ያጠይቃል።

በቡድን ውይይቱ ከተሳተፉት ውስጥ አቶ ጸጋየ ጀንበሬ (አባ.2፣ ቁ.19.፣ ክፍ.፣ 1.1.1.1.2.፣ አን.1) እና ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው መካከል አቶ ወንዳያ ጓንጉል (አባ.2.፣ ቁ.15.፣ ክፍ.1.1.1.1.2.፣ አን.1.)፣ የጉዞ ፍትሀት ልማድ መኖሩን ይገልጻሉ። ቀኛ ጌታ ዜናዊ ስቡህ (አባ.2.፣ ቁ.1.፣ ክፍ.1.1.1.1.2.፣ አን.2) በእምነቱ መሰረት የፍትሐት ጸሎት የሚፈጸምላቸው

* መጽሀፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ፣6 ላይ ሙሉ ታሪኩ ይገኛል።

እድሜያቸው ከሰባት ዓመት* በላይ ለሆኑ ምዕመናን መሆኑን ገልጸው፣ በእድሜ እርከንም የሕጻናት፣ የወጣቶች፣ የጎልማሶችና የሽማግሌዎች ፍትሀት ተብሎ እንደሚከፈል ያስረዳሉ፡፡

በደብረ ታቦርና በፋርጣ ወረዳዎች ምልከታ በተካሄደባቸው የዕለት ለቅሶዎች፣ ከሁለት ጊዜ በላይ የጉዞ ፍትሀቶች ሲደረጉ አልታዩም፡፡ ሬሳው ከቤት እንደወጣ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ወደሚገኝ ማርገጃ ከተጓዘ በኋላ፣ ለለቀስተኛው የሚሆን ሰፋ ያለ ቦታ በመተው፣ በስተምስራቅ በኩል እግሩ ወደምስራቅ፣ ራሱ ወደምዕራብ ዞሮ እንዲያርፍ ተደርጎ ፍትሃት ይካሄዳል፡፡

በፍትሃቱ የሚሳተፉት ቀሳውስትና ካህናት የየራሳቸው ቋሚ ቦታና ሚና እንዳላቸው እንደቀኝ ጌታ ዜናዊ ስቡህ (አባ.2.፣ ቁ.1፣ ክፍ.1.1.1.1.2.፣ አን.7) እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> … በፍትሃት ጊዜም ካህኑ በምዕራብ (ራስጌ) ቁሞ ፊቱን ወደ ምስራቅ ይዞራል፡፡ ዲያቆኑ በምስራቅ (በእግር) ቁሞ ፊቱን ወደ ምዕራብ ይመልሳል፡፡ ንፍቁ (ረዳቱ) ቄስ በደቡብ ቁሞ ፊቱን ወደ ሰሜን ሲመልስ፣ ንፍቅ ዲያቆኑ ደግሞ በሰሜን ቁሞ ፊቱን ወደ ደቡብ መልሶ ነው የሚጸልይ፡፡ ሬሳው ራሱ ወደ ምዕራብ እግሩ ወደ ምስራቅ ዞሮ በአልጋው ላይ ተንጋሎ ይቀመጣል፡፡ ያው ስርዓቱ እንደቤተ መቅደሱ እንደቅዳሴው ስርዓት ነው፡፡

መሪጌታ ክፍለማርያም አለነ (አባ.2፣ ቁ፣2 አን.4) እንደሚያስረዱት ከቤት ጀምሮ ሙሉ ፍትሃት ሲደረግ የሚፈጸመው ክውንን የሚከተለውን ይመስላል፡፡

> …ካህናቱ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው መስቀል ይይዛሉ፣ መሪጌታውና ዲያቆናቱ ጸናጽል፣ ከበሮ ይይዛሉ፡፡ ካህናቱ ከቤት ገብተው ከውስጥ የሚያስፈልገውን ሥርዓት ሲፈጽሙ መዘምራኑ ወይም እንግዶቹ ከሁለተኛው መድረክ ላይ ወይም ከበሩ ላይ ሁነው መዋሲት ይመራሉ፤ እዝል ከድጓ (ድጓ ዘመን ዘመን አለው) … አንድ አንስተው ለእለቱና ለዘመኑ ያመቻል የሚሉትን ድጓ አውጥተው እዝል መርተው መዋሲት ይመራሉ፣ ያን ይጠረጥራሉ፡፡ … ሥርዓቱን ከቤት ጀምሮ ወደመቃብር እስከሚወርድበት ጊዜ ድረስ ሰባት ፍትሃት ፈትተው ጉድጓድ ያስገቡታል፡፡

---

* ከሰባት ዓመት በታች ያሉ ሕጻናት አዕምሯቸው ስላልበሰለ ለሀጢያት ያልተጋለጡ ንጹሆች ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡

በምልከታው ወቅት ሙሉ ፍትሃት የተካሄደበት የለቅሶ ሥርዓት ለማግኘት ባይቻልም በጎደሎው የሥርዓት አፈጻጸም ላይ ለማየት እንደተቻለው የካህናት፣ የዲቆናትና የመሪጌቶች አሰላለፍና አለባበስ ከላይ በቀኝ ጌታ ዜናዊና በመሪጌታ ክፍለማርያም ከተገለጸው ተመሳሳይ ነው፡፡ ሟች ታዋቂ ከሆነ፣ (ከታች በፎቶግራፎቹ እንደሚታየው) ድባብ ከሬሳው አጠገብ ይቆማል፡፡ ቄሶቹ የቤተክርስቲያን ጥላ ዘርግተው የሚይዙ ሲሆን፣ መሪው ቄስ በጥናው ሬሳውን እየዞረ ያጥናል፡፡ የጸሎት መጽሀፍም በቃለ ፍትሃቱ መካከል ያነባል፡፡ የሟች የክርስትና ስም እየተጠራ ፈጣሪ ነፍሱን እንዲቀበላትና በሠላም እንዲያሳርፋት ይጸለያል፡፡

መሪጌታ ክፍለማርያም አለነ (አባ.2፣ ቁ.2፣ ክፍ.1.1.1.1.2፣ አን.1-8) እንደሚገልጹት በሙሉ ፍትሃት ጊዜ ከመጀመሪያው እስከሰባተኛው የፍትሃት ጸሎት ዘጠኙ ኪዳናት ይነበባሉ፤ ከአራትና ከሃዲስ ኪዳን መጻህፍት፣ በምስጢር የሚገናኙት ከመዝሙረ ዳዊትና ከመልዕክታት እየተጠቀሱ ይጸለያሉ፡፡ ‹‹ከዚያ በኋላ ደግሞ ወደ ኋላ ተመልሶ ‹ወካይበ ናስተበቁ› ብሎ ነው ቄሱ የሚነሳ፡፡ ‹ዲያቆኑ ተንስዑ ለጸሎት› ይላል፡፡ መልእክታት ሁሉ ይነበባሉ፡፡››

በእያንዳንዱ ፍትሃት የሚነበበው ወንጌልና የዳዊት መዝሙር፣ የሟችን በአስፈሪው የሞት መዳፍ ውስጥ መውደቅንና መቅበዝበዝን በመግለጽ የእግዚአብሔርን እርዳታ ከመማጸን፣ መረታትን አምኖ እስከመቀበል፣ በዝች ዓለም ስደተኛና እንግዳ መሆንን ከመገንዘብ፣ ከጨለማ ውስጥ ብዙ ጨለማ ወዳለበት ጉድጓድ እስከመግባት ያለውን ጣር የሚገልጹና በመጨረሻም የተስፋ ቃል እስከማግኘት የሚዘልቁ መሆናቸውን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ለምሳሌ በመጀመሪያው ፍትሃት ከሚጸለየው የዳዊት መዝሙር (መዝ. 54፣4-6)፣ ውስጥ ‹‹ልቤ በላዬ ተናወጠብኝ፣ የሞት ድንጋጤም ወደቀብኝ፡፡ ፍርሃትና እንቅጥቅጥ መጡብኝ፣ ጨለማም ሸፈነኝ፡፡ በርሬ አርፍ ዘንድ እንደርግብ ክንፍን ማን በሰጠኝ!››፣ ከሚለው መቅበዝበዝ፣ በሁለተኛው ‹‹አቤቱ ጌታ ሆይ ጸሎቴን ስማ፣ የቃሌን ልመናም ስማኝ›› እስከሚለው ተማጽኖ፤ በሶስተኛው ‹‹የሞት ጻዕር ጭንቀት ያዘኝ››፣ ከሚለው ድንጋጤ፤ በአራተኛው ‹‹የኔ አካል ታየኝ አሁን እንደ ገል ሆነ፤ ደከመ አንደበቴ የምናገረው ሁሉ ምንም የለውም በጉሮሮየ ውስጥ ነው አይሰማም፡፡›› እስከሚለው መረታትን ማወቅ፤ በአምስተኛው ‹‹እኔ በዚህ ዓለም ስደተኛ ነኝ፡፡ እንደወገኖቼም እንግዳ ነኝ፡፡›› ከሚለው ተስፋ መቁረጥ፤ በስድስተኛው ‹‹ነፍሴ በምትወጣበት ጊዜ በኔ ላይ አንተ ደግሞ ጌታ ሆይ መንገዴን ተውቃለህ፡፡›› ከሚለው ተማጽኖ፤ በሰባተኛው

‹‹ዝቅ ወዳለ ጉድጓድ ቆፍረው አስገቡኝ። በጉድጓዱም ውስጥ የሞት ጨለማ አለበት። በጨለማውም ውስጥ ብዙ ጨለማ አለበት።›› እስከሚለው ሰቆቃ፣ ሟች እስከሚቀበር ድረስ የሚያልፍባቸውን ስቃዮች የሚገልጹት የዳዊት መዝሙሮች ከወንጌሉ ጋር እየተመሳጠሩ ይነበባሉ። የፍትሃት ጸሎቱ፣ በሰባተኛው ፍትሃት ጊዜ በሚነበበው (የዮሐወ.17፥20)፣ ‹‹እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ ነገር ግን ሀዘናችሁ ወደደስታ ይለወጣል›› እስከሚለው የተስፋ ቃል የተቀናበረ መሆኑ፣ ሙታን ከሀጢያት ማሰሪያ መፈታታቸውን የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል። ይህም ተጠኚዎቹ ሥርዓቱን ከሚፈጸምበት ዓላማ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

ከካህናቱ ጸሎት ጎን ለጎን፣ መሪጌቶች (*የቤተክርስቲያን አገልጋዮችና መምህራን*) እና መዘምራን ከበሮና ጸናጽል በመያዝ ቅዱስ ያሬድ ለነፍሳት ከደረሰው ድጓና መዋሲት በማውጣጣት እያቀናበሩ ከበሮና ጸናጽሉን በዝማሜ እየመቱ ሥርዓተ ጸሎቱን እንደሚፈጽሙ መሪጌታ ክፍለማርያም አለነ (አባ.2፣ ቁ.2.፣ ክፍ.1.1.1.1.2.፣ አን.4) ይገልጻሉ። የእነሱም ሥርዓት በቀሳውስት ከሚፈጸመው ሰባት ሥርዓት ጋር አብሮ የሚሄድ እንደሆነና ፍትሃቱ ሊጠናቀቅ ሲል ከበሮና ጸናጽል እንደሚመታም ያስረዳሉ።



*ምሥል ስድስት፣ በአቶ ዓለምነው መንግሥቱ ለቅሶ በማርገጃ ፍትሃት ሲካሄድ (ፎቶ በለማ ንጋቱ)*



ምስል ሰባት፤ በእሙሀይ አጸዴ ስመኝ ለቅሶ የገዞ ፍትሃት ሲካሄድ (ፎቶ በለማ ንጋቱ)

መሪጌታ ክፍለማርም አክለው እንደሚያስረዱት የጉድጓዱን መድረስና የፍትሀቱን መጠናቀቅ የሚከታተሉ አስተባባሪዎች ለቀሳውስቱ ጉድጓዱ እንደደረሰ ሲነግሯቸው፣ ሬሳውን አስከትለው እነሱ በክበሮና በጸናጽል በታጀበ ዜማ እየጸለዩ፣ ወደቤተ ክርስቲያን ቅጥር ይገቡና ሬሳውን አንድ ጊዜ ቤተክርስቲያኑን ወደቀኝ አዙረው በደቡብ በኩል እንዲያርፍ ያደርጉታል፡፡ ምልከታ ከተካሄደባቸው የዕለት የለቅሶ ሥርዓቶች መካከል በ22/09/04 ከዋለው ከወ/ሮ ቀነብሽ ለቅሶ አስከሬኑ ወደቤተክርስቲያን ሲወሰድ ካህናት ከበሮ እየመቱና፣ በጸናጽል በታጀበ ዜማ እየጸለዩ ሲያጅቡ ለመመለከት ተችሏል፡፡

ከዚህ በኋላ፣ የሟች የሕይወት ታሪክ ተዘጋጅቶ ከሆነ አንባቢ እንዲወጣ ይጠየቃል፡፡ ካዘጋጁ ይነበባል:: ካላዘጋጁ ሬሳው እንደጸታው (ወንድ ከሆነ ወደሰሜን፣ ሴት ከሆነች ወደደቡብ) የቤተክርስቲያኑ መግቢያ በር ይወሰድና፣ ራሱ ወደቤተ ክርስቲያኑ ዞሮ ከፊት ለፊት የያዙት ሰዎች ሶስት ጊዜ ከፍ ዝቅ እያደረጉ ሲያሰግዱት፣ መሪው ቄስ በዚያው ልክ በትልቅ መስቀል ይባርከዋል፡፡ ከዚያ እግሩ ቀድሞ በመሪው ቄስና በአንድ ዲያቆን እየተመራና ግብዓተ መቃብር እየተጸለየ ወደመቃብር ቦታ ይወሰዳል፡፡

ሬሳው ሦስት ጊዜ እንዲሰግድ መደረጉ የነፍስን በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም፣ ለፈጣሪዋ መስገድ አመልካች ትዕምርትነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመጽሀፍ ቅዱስ፣ (ዕዝ.ሱቱ.6፣9) ‹‹...ከልዑል እግዚአብሔር ዘንድ የትእዛዝ ቃል ከመጣ በኋላ እገሌ ይሙት ባለ

ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADDIS ABABA, ETHIOPIA

ጊዜ ነፍሱ ከሥጋው ትለያለች፤ ወደሰጭዋ ወደእግዚአብሔር ትመለሳለች፤ ለጌትነቱም አስቀድማ ትሰግዳለች›› ተብሎ የተጻፈው በማስረጃነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ሟች ከቤተክርስቲያን ከዚያ በኋላ ቁሞ ሊያስቀድስ ስለማይችል፣ የመጨረሻ የመሰናበቻ ሥርዓት ማስፈጸሚያ ትዕምርትነት እንዳለውም ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ሬሳው ከቀብር ቦታ ሲደርስ፣ መሪው ቄስ ጉድጓዱን ይባርክና ጸበል ይረጨዋል፡፡ ሲታወድበት ከዋለው ከጽናው እምነትም፣ ይበትንበታል፡፡ የሀይማኖቱ ሥርዓት በሚያዘው መሰረት፣ ከቤተክርስቲያን ሲታወድ ካልተፈጸመ በዚህ ቦታ፣ ለካህን ሃያ አራት ወይም አስራ ሁለት፣ ለዲያቆን ሰባትና ለምዕመናን አራት የጧፍ መብራቶች እንዲበሩ ይደረጋል፡፡ ከዚያ አስከሬኑ ከነአልጋው እንዲጠጋ ይደረግና አራት ሰዎች ከላይ ኩታ ሲወጥሩ፣ ሁለት ሰዎች ከስር አጎበሩን በመግለጥ አስከሬኑን ከአልጋው በአንዱ ጫፍ ስበው አውጥተው ጉድጓዱ ውስጥ ራሱን ወደምዕራብ፣ እግሩን ወደምስራቅ፣ በማዞር አንጋለው ያጋድሙታል፡፡ እንዲህ ተደርጎ መቀበሩ የገነትን በምስራቅ መገኘት፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ወደምስራቅ ዞሮ ማረግና በዳግም ምጽአት ጊዜ በዚሁ አቅጣጫ ይመጣል ተብሎ መጠበቅንና ሟች ፈጣሪውን ለመቀበል ዝግጁ ሆኖ መጠበቅን አመልካች ትዕምርትነት እንዳለው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በፍትሃት ወይም በኡደት ጊዜ ወይም በሁለቱም ለካህን ሃያ አራት ወይም አስራ ሁለት፣ ለዲያቆን ሰባትና ለምዕመን አራት መብራቶች እንዲበሩ መደረጉ፣ እንደመገነገቸ ክሩ ሁሉ ከማዕረጋቸው ጋር የተያያዘ ትዕምርትነት አለው፡፡ ለካህን የሚበራው አስራ ሁለት መብራት የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ምሳሌ ሲሆን፣ ሐዋርያት የዓለም ብርሃን ሁነው ወንጌልን እንዳስተማሩ ሁሉ፣ የእነሱን ስልጣን ይዘው ምዕመናንን ሲያስተምሩ መኖራቸውን ለማዘከር ይበራላቸዋል፡፡ በአንዳንድ ቦታ ሀያ አራት የሚበራውም የካህናተ ሰማይ (ኪሩቤል) ተምሳሌት ነው፡፡ ካህናት ለእግዚአብሄር የሚያቀርቡት ምስጋና ኪሩቤል ከሚያቀርቡት ጋር አንድ በመሆኑ፣ ያንን ለማጠየቅ የሚበራ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ መብራቱ ሃያ አራትም ይሁን አስራ ሁለት (አንዱ ከተበራ ሌላው አይበራም)፣ ቤተክርስቲያን አገልጋዩዋ ከዚህ የጨለማ ዓለም ወደብርሃን ዓለም መሄዱን የማጠየቂያ ተምሳሌትነት አለው፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ (1983፣41)፣ መብራት የሚበራው አንድም ወደንጹሕ ዓለም፣ ወደብሩሕ ዓለም መሄዳቸውን፣

አንድም በብሩህ ትንሳዔ፣ በንጹሕ ትንሳዔ መነሳታቸውን ለመግለጽ እንደሆነ ማስረዳታቸው፣ የተነሳውን ሀሳብ ያጠናክራል፡፡

ለዲያቆናቱ ሰባት የሚበራውም የሰባቱ ዲያቆናት ምሳሌ እንደሆነና በእነሱ የነበረውን ሥልጣን ተረክቦ ሕዝበ ክርስቲያኑን እያስተማረ ብርሃን ስላደረገ፣ ብርሃን እንዲከተለው በማለት መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለሕዝባዊ አራት የሚበራው ደግሞ፣ ስልጣን ባይኖራቸውም፣ የተፈጠሩባቸውን አራት ባህርያት (እሳት፣ ውሃ፣ ነፋስና መሬት) በማስታወስ ነው፡፡ ሀዘን የመጥፎ ነገር ተምሳሌት በሆነው በጨለማ ሲመሰል (ሀዘንተኞቹ ጥቁር ልብስ መልበሳቸውን ልብ ይሏል)፣ ደስታና ብሩህ ተስፋ በብርሃን ይመሰላሉ፡፡ የሟች መለየት በፈጠረው ሀዘን (ጨለማ) መብራት መበራቱ፣ ብሩህ ተስፋ ወዳለበት መንዝን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም ለሁሉም ‹‹ጨለማና ብርሃን ሲፈራረቅባቸው ኑረው፣ ከዚህ በኋላ ምንጊዜም ብርሃን ወደሆነችው ዓለም ሄዱ›› የሚል ትእምርትነት እንዳለው ለመረዳት ተችሏል፡፡

እንደሟች ማሕበራዊ ደረጃና እንደቤተሰቦቹ ምርጫ ድመም* ሲሰራ፣ ወይም ዝምብሎ ሲቀበር ይችላል፡፡ ድመም ቢሰራም ባይሰራም፣ ሬሳውን ጉድጓድ ውስጥ ያጋደሙትና በመቃብሩ ዙሪያ ያሉት ወንዶች ወዲያው እየተቀባበሉ በአካፋ አፈር ሲመልሱ፣ የሟች የቅርብ ቤተሰቦች ያለጾታና እድሜ ልዩነት ከጉድጓዱ ከወጣው አፈር በእጃቸው እየጨበጡ መቃብሩ ላይ እንዲበትኑ ይደረጋል**፡፡ አፈር መላሾቹ ከጉድጓዱ የወጣውን መልሰው በድንጋይ እያስታቀፉ እንደመደብ ከፍ አድርገው ደምድመው ሲጨርሱ፣ በራስጌና በግርጌ በኩል ሞለል ሞለል ያሉ ሁለት ድንጋዮች አቁመው፣ የቀረው ቦታ ላይ ድንጋይ ረብርበው ቀብሩ ይጠናቀቃል፡፡

---

* *እ.ኢ.አ. በ10/05/06 ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው አቶ ታደለና አቶ ሀይሌ እንደሚገልጹት፣ በስማዳ ድመም፣ በፋርጣ እርመን፣ የሚባለው የአቀባበር አይነት፣ ሬሳ ከተጋደመበት ትንሽ ከፍ ብሎ፣ የጉድጓዱ የጎን ግድግዳዎች ወደውስጥ ተቦርቡረው ሞላላና ጠፍጣፋ ድንጋዮች እየተደረደሩ ወደሬሳው አፈር እንዳይገባ ጉድጓዱ ከተገጠመ በኋላ፣ አፈር የሚመለስበት የአቀባበር አይነት ነው፡፡ የዚህ ተቃራኒ ‹‹ወረዳ ቀብር›› በመባል የሚታወቅ ሲሆን፣ ጥናቱ በተካሄደባቸው በአብዛኞዎቹ ገጠራማ አካባቢዎች በስፋት ተግባራዊ እየተደረገ ያለ፣ አፈር ሬሳው ላይ በቀጥታ የሚመለስበት የአቀበባበር አይነት ነው፡፡*

** *በአይሁዶችም በሟች መቃብር ላይ ቤተሰቦችና የቅርብ ጓደኞች አፈር በአካፋ የመመለስ፣ በጣም አስፈላጊ ልማድ እንዳላቸው* Levine *(2004፣110) ያስረዳሉ፡፡ ይህም ሀዘንተኞቹ የሞት ፍጻሜና የሟች የመለየት እውነታ ላይ ትኩረት እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል፡፡ መቃብሩን በአፈር በመሸፈኑ ሥራ መርዳትም እንደክብር ይቆጠራል፡፡*

አስከሬን በሳጥን ወይም በድመም የሚቀበረው፣ ከሟች ከፍ ያለ ማሕበራዊ ደረጃ፣ ወይም በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅ ከመሆንና፣ ቋሚ ዘመዶች በቀጥታ አፈር ሲጫነው ለማየት ካለመፈለግ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከሬሳው ላይ  አፈር በቀጥታ የሚመለስበት የወረዳ አቀባበር ሥርዓት ደግሞ፣ በማሕበራዊ ደረጃ ዝቅ ከማለት፣ በአካባቢ ምክንያት የድንጋይ እጥረት ከመኖር ብቻ ሳይሆን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በቀጥታ ያረፈበትን አፈር ለመቅመስ ተናዞ ከመሞት፣ ‹‹አፈር ነህና ወደአፈር ትመለሳለህ›› የሚለውን ቃል ታሳቢ ከማድረግ ጋር ተያያዥ ሀይማኖታዊ አንድምታ ያለው መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

አስከሬኑ ከሁለቱ የአፈር አመላለስ አይነቶች በአንዱ ሲመለስበት፣ የሟች የቅርብ ቤተሰቦች ከጉድጓዱ ከወጣው አፈር ቆንጥረው መቃብሩ ላይ እንዲበትኑ የሚደረገው ደግሞ፣ በአንድ በኩል ዳግመኛ መከራ እንዳይደርስባቸው ለመመኘት ሲሆን፣ በሌላ በኩል የሟችን አፈር መልበስና ዳግም የማይገኝ መሆን አውቀው፣ ሆዳቸው እንዲቆርጥላቸውና እንዲረጋጉ ለማድረግ መሆኑን መረጃ አቀባዮቹ ይገልጻሉ፡፡ ወንድ ለቀስተኞች አፈር በመመለሱ ሂደት እየተቀባበሉ የሚረባረቡት ደግሞ፣ ‹‹ቆመን አፈር አልብሰናል››፣ በማለት ለሟች ያላቸውን ታማኝነት ለመግለጽ እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ሴቶች አፈር በመመለሱ የማይሳተፉት በአንድ በኩል በፍጥነት መከናወን ያለበት የጉልበት ሥራ በመሆኑ ወንዶቹ ስለሚቀለጥፉ ሲሆን፣ በሌላ በኩል በከፈን ሥርዓቱ ስር እንደተጠቀመው ወደአስከሬን እንዲጠጉ ባህሉም ሆነ ሀይማኖቱ ስለማያበረታታ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

ቀብሩ እንደተጠናቀቀ የመሰናበቻ ጸሎት መጽሀፈ ሳሙኤል በመሪ ቄሱ ይነበባል፡፡ ነፍሱን እግዚአብሔር ተቀብሎ በሰላም እንዲያሳርፋት ከተጸለየ በኂላ፣ በአበ ነፍሱ ወይም በመሪጌታው መሪነት፣ ለሀዘንተኞች የሚያጽናና ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ ወይም ከቤተክርስቲያን መጻሕፍት አንዱን ጠቅሶ፣ ለአምስት ደቂቃ ያህል ካስተማረ በኂላ፣ ማሰናበቻ ጸሎት በአበነፍሱ ወይም ከአባቶች መካከል በእድሜ ወይም በማዕረግ ትልቅ ናቸው በሚባሉት አባት፣ አቡነዘበሰማያትና ኑዛዜ ተሰጥቶ ለቀስተኛው ይሰናበታል፡፡

የፍትሃት ሥርዓተ ጸሎት እድሜያቸው ከሰባት ዓመት በታች ለሆኑ ሕጻናት እንደማያስፈልግ ከመገለጹ በስተቀር፣ ለሁሉም የእምነቱ ተከታዮች መፈጸም እንዳለበት የቤተክርስቲያን ህግ ያዛል፡፡ በተግባር እንደሚታየው ግን፣ ማሕበራዊ ደረጃቸው አነስተኛ ለሆነና ግብረሰላም ላላበሉ ምዕመናን የማይፈጸምበት ሁኔታ አለ፡፡ በደብረ ታቦር ከተማ ደግሞ፣ የለቅሶ ሰዓቱ ማጠር፣

ግብረሰላም ላበሉና ታዋቂ ለሆኑትም የሰባት ጊዜ ፍትሃት እንዳይተገበር እንቅፋት በመሆን ላይ እንደሚገኝ መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ፡፡ በእሙሃይ አጸዴ እ.ኢ.አ. (በ27/09/04 የተፈጸመ) ለቅሶ ላይም፣ የበኩር ልጃቸው በሰዓቱ ማጠር ምክንያት ለእናታቸው ሥርዓቱ በሚገባ ሳይከናወንላቸው መቀበራቸውን በማማረር ለለቀስተኛው ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡

የሟች የቅርብ ቤተሰቦች አፈር ዘግነው ወደ መቃብሩ እንዲበትኑ የሚደረገው ደግሞ፣ በአንድ በኩል ዳግመኛ መከራ አይድረስብን ለማለት ሲሆን፣ በሌላ በኩል የሟችን አፈር መልበስና ዳግም የማይገኝ መሆኑን አውቀው ሆዳቸው እንዲቆርጥላቸው፣ እንዲረጋጉ ለማድረግ ታስቦ እንደሆነ ከመረጃ አቀባዮቹ መካከል አቶ ጸጋዬ ያስረዳሉ፡፡ ለቀስተኛው አፈር በመመለሱ ሂደት እየተቀባበለ የሚረባረበው ደግሞ ‹‹ቆሜ አፈር አልብሻለሁ›› በማለት ለሟች ያለውን ታማኝነት ለመግለጽ እንደሆነም ያስገነዝባሉ፡፡

በዕለት ለቅሶ እስከቀብር ድረስ የሚከናወነው ሀይማኖታዊ ሥርዓት ከዚህ በላይ የተገለጸውን ሲመስል፣ አስከሬን በማይኖርባቸው የቀጠሮና የመርዶ ለቅሶዎች የሚከናወኑት ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች ደግሞ ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

#### 4.1.1.2. በቀጠሮና በመርዶ ለቅሶ የሚከናወኑ ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች ክወና

በቀጠሮና በመርዶ ለቅሶዎች ላይ አስከሬን ስለማይኖር ሬሳ ከማሰናዳት፣ ከመገነዝና ከመከፈን ጋር ተያይዘው የሚከናወኑት ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች እንደማይፈጸሙ በምልከታ የተሰበሰቡት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እነዚህ ለቅሶዎች ከሟች ቤት ወደቤተ ክርስቲያን በሚደረግ ጉዞ ሳይሆን፣ በገበያ ዳር፣ በማርገጃ ወይም በተመረጠ አማካይ ቦታ ላይ ስለሚካሄዱ፣ የጉዞ ፍትሃትም አይከናወንም፡፡

በፎገራና በላይ ጋይንት በገበያ ዳር በሚካሄዱ የቀጠሮ ለቅሶዎች ምንም አይነት ሀይማኖታዊ ሥርዓት የማይካሄድ ሲሆን፣ በስማዳና በፋርጣ ወረዳዎች በማርገጃ በሚካሄዱ የለቅሶ ሥርዓቶች፣ ካህናት ልብሰ ተክህኗቸውን ለብሰውና ጥላ ዘርግተው የቡድን ጸሎት እንደሚያካሂዱ ከምልከታና ቀደም ሲል ተቀርጸው ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለምሳሌ ስማዳ ወረዳ እ.ኢ.አ. በ23/02/2003 በተካሄደው በአቶ አማረ የቀጠሮ ለቅሶ ላይ ልብሰ ተክህኖ የለበሱና ጥላ የዘረጉ የደብሩ ካህናትና፣ ከሌሎች ደብሮች የመጡ ነጭ የለበሱና

የጠመጠሙ ካህናት ክብ ከሰራው ለቀስተኛ በአንዱ ጫፍ አንድ አካባቢ ሰብሰብ ብለው ጸሎት ሲያደርጉ ተስተውሏል፡፡ የደብሩ ካህናት ጸናጽላቸውን እያንሻDሹና እየጸለዩ በመምራት ወደክቡ መሃል ሲገቡ፣ ከሌላ ደብሮች የመጡ ካህናት ወደጎን ረዘም ያለ መስመር ሰርተው፣ ከሁለት ሜትር በማይበልጥ ርቀት ፊት ለፊት እየተያዩ እየወረቡ ይከተሏቸዋል፡፡ ለወረቡ ማድመቂያ ከበሮም ይመታል፡፡ ከምስሉ አካባቢ ሲደርሱ፣ አንድ ላይ ሰብሰብ ብለው ሁለት ከበሮ እየተመታ፣ ጸናጽሎች ስልት ጠብቀው እየተንሻEሹ፣ መቋሚያ እየተሰበቀ፣ አካባቢው በጽና እየታጠነ፣ ሲወረብ ከቆየ በኋላ፣ ትልቅ መስቀል የያዙ ካህናት እየመሩ አሁንም ወደክቡ ውስጥ በመግባት ይጸልያሉ፡፡

ካሕናቱ ከክቡ መሃል መስመር እየሰሩ በመጸለይ ሲዛወሩ፣ አምስት አዝማሪዎች በዘለስኛ ቅኝት ማሲንቆ እየመቱ ያጅቧቸዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ አንዴ ወደድንኳኑ፣ አንዴ ወደሚች ምስል እየተንቀሳቀሱ ሲጸልዩ ቆይተው፣ የሕይወት ታሪክ ከተነበበ በኋላ፣ በደመቀ ሁኔታ ሲወርቡ ተስተውለዋል፡፡

በቀጠሮ ለቅሶ ካህናት የሚገኙት፣ ሚች በጣም ታዋቂ ሰው ወይም ካህን ሲሆን እንደሆነ መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ፡፡ ካህናቱ በሚገኙበት ጊዜም ከፍትሃቱ ይልቅ ወደወረብና ሚችን በቅኔ ወደማሞገስ እንደሚያደሉና፣ ይህንም ለብቻቸው ቋሚ ቦታ ሳይዙ በለቀስተኛው መሃል ወዲያና ወዲህ እያሉ እንደሚከውኑ ያስረዳሉ፡፡ በምልከታ እንደታየውም፣ ከለቅሶው ዳር ወደመሃል፣ ከመሃል ወደዳር እየተዛወሩ ይከውናሉ፡፡ በለቅሶው ሥርዓት መጨረሻ ወረቡን ደመቅ በማድረግ መቋሚያቸውን ወደላይ አንስተው አየር እየቀዘፉ፣ በጭብጨባና በሽብሸባ ወረቡን ደመቅ ያደርጉታል፡፡

በደብረታቦር ዙሪያ ወረዳም ካህናት በአቶ ዋለ የቀጠሮ ለቅሶ ላይ (በ29/09/04 የዋለ)፣ ልብሰ ተክህኗቸውን ለብሰውና ጥላ ዘርግተው የተገኙ ሲሆን፣ የፍትሃት ጸሎት ሲያደርጉ አልተስተዋሉም፡፡ ቤተክርስቲያን ውስጥ በመቆየት ለቅሶው ሲፈታ ሲል መጥተው መስመር ይዘው በመቆም፣ ለቅሶውን ካስቆሙ በኋላ፣ መታረም ስለሚገባቸው በዕለቱ የታዩ ድርጊቶች (በባዕለ ማርያምና በባዕለ እግዚአብሔር የቀጠሮ ለቅሶ መካሄዱ፣ ጥይት መተኮሱ) ሲናገሩና፣ የሚችን ነፍስ እግዚአብሔር በሠላም እንዲያሳርፍ ተማጽነው የመሰናበቻ ጸሎት ሲሰጡ እንጂ፣ የፍትሃትም ሆነ ሌላ ጸሎት ሲያካሂዱ አልታዩም፡፡



ምስል ስምንት፣ በ29/09/04 ደብራታቦር ዙሪያ ወረዳ በዋለው በአቶ ዋለ ቸኮል የቀጠሮ ለቅሶ ካህናት ለቅሶውን አስቁመው ሲገስጹና የመሰናበቻ ጸሎት ሲሰጡ (ፎቶ በለማ ንጋቱ)

በአጭሩ በቀጠሮና በመርዶ ለቅሶ የሚካሄደው ሀይማኖታዊ ሥርዓት፣ ከእለት ለቅሶ ጋር ሲነጻጸር ቀዝቀዝ ያለ መሆኑን ከመረጃ አቀባዮቹም ሆነ ከምልከታ መረጃዎቹ ለመገንዘብ ተችሏል። በእነዚህ የለቅሶ አይነቶች የሚፈጸመው ፍትሃት፣ ሬሳ ባለበት ከሚፈጸሙት ከሰባቱ አንዱ ብቻ ነው። በተለይ የመርዶው ለቅሶ በቤት አካባቢ በሚፈጸምበት ጊዜ፣ ምንም አይነት ሀይማኖታዊ ሥርዓት እንደማይካሄድ ከመረጃ አቀባዮቹና ከምልከታ መረጃዎቹ ለመረዳት ተችሏል።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ተጠኚው ማሕበረሰብ በሚያከናውናቸው ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች፣ ሞትን ከዚህ የመከራ ዓለም ማረፊያ አድርጎ እንደሚመለከተው መረጃዎች ያሳያሉ። ለምሳሌ መሪጌታ ክፍለማርያም አለነ (አባ.2.፣ ቁ.2፣ ክፍ.ለ፣ አን.1) ይህንኑ ሁኔታ እንደሚከተለው ይገልጹታል።

> ሞት ሲባል ረፍት ማለት ነው። የጻድቅ ሰው ሞቱ በእግዚአብሔር ፊት ረፍትና በጎነት ነው። በዚህ ዓለም ውጣ ውረድ አለ። በዚህ ዓለም ጨለማ አለ። መብላት መጠጣት የድካም ውጤት ነው። ከዚህ በኋላ መራብ ወደሌለበት፣ ድካም ወደሌለበት፣ መጠማት ወደሌለበት መራቆት ወደሌለበት፣ ደስተኛ ወደሚኮንበት ወደብርሃን ዓለም

ነው የሚሄደው፡፡ ስለዚህ ከዚህ ዓለም ያለውን ድካም መላቀቂያ ስለሆነ እረፍት ነው፡፡ በቤተክርስቲያን ሥርዓት የነፍስ ከስጋ መለየት እረፍት እንጂ ሞት አይባልም፡፡

ሞት በጥቅሉ መለየት ይሁን እንጂ፤ የመለየቱ አይነትና ክብደት የተለያየ መሆኑንም ይገልጻሉ፡፡ አንደኛው ሞት የነፍስ ከስጋ መለየት ሲሆን፣ ሁለተኛው ሞት፣ በአካል እየተራመዱ እግዚአብሔርን ረስቶ ለሰይጣን መገዛት ነው፡፡ ሶስተኛው ሞት ደግሞ በፍርድ ቀን ከእግዚአብሔር ተለይቶ ወደሲኦል መውረድ ሲሆን መጠሪያውም የሞት ሞት ነው፡፡ እነዚህን ሞቶች ቀኝ ጌታ ዜናዊ ስቡህ (አባ. 2፣ ቁ.1) ሞተ ሥጋ፣ ሞተ ህሊናና ሞተ ነፍስ ብለው ከመጥራታቸው ውጭ የእያንዳንዳቸው ማብራሪያ ከላይ ከተገለጸው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

በአጠቃላይ ተጠኚው ማሕበረሰብ በነፍስ ከሥጋ መነጠል የሚከሰተውን ዓለማዊው ሞት፣ በሀይማኖት ከመከራ እንደመገላገያ እንደሚያየውና የሚፈጸሙት ሥርዓቶች አጠቃላይ ግብም ሟች በሀጢያት ምክንያት ከእግዘአብሔር በመለየት (በኩነኔ) ከባዱን ሞት እንዳይሞት ፈጣሪን ምህረት መለመኛዎች መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከዚህ በላይ ከተገለጹት ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች ጎን ለጎን የሚካሄዱትና ከሟች ቤተሰብ አንስቶ እስከለቀስተኛው በቀጥታ የሚሳተፍባቸው እስከቀብር ድረስ የሚከናወኑት ዓለማዊ ሥርዓቶች ምን እንደሚመስሉ ደግሞ፣ ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

### 4.1.2 እስከቀብር ድረስ የሚከናወኑ ዓለማዊ የለቅሶ ሥርዓቶች ክወና

በዚህ ክፍል በዕለት፣ በቀጠሮና በመርዶ ለቅሶዎች እስከቀብር ድረስ የሚከናወኑ ዓለማዊ ሥርዓቶች ቀርበዋል፡፡

#### 4.1.2.1. በዕለት ለቅሶ እስከቀብር ድረስ የሚከናወኑ ዓለማዊ ሥርዓቶች ክወና

የሟች ነፍስ ከወጣበት ሬሳ እስከሚቀበር ድረስ የሚከናወኑ የተለያዩ ዓለማዊ የለቅሶ ሥርዓቶች አሉ፡፡ እነሱም የሟችን ረፍት ይፋ የማድረግና የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ክወና ሥርዓቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ሥርዓቶች፣ የሟች ነፍስ እንደወጣ ወዲውኑ አይጀምሩም፡፡ የሟች ነፍስ እንደወጣ ሬሳ የመገነዝና የመከፈን ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች ከመጋረጃ ጀርባ በሚመለከታቸው ባለሙያዎች

ሲካሄዱ፣ ሀዘንተኞቹ ውጭ እንዲወጡ ይደረጋል፡፡ በቅርብ ያለ ሰው እየመጣ ከቤተሰብ ጋር ይቀላቀላል፡፡ በዚህ ወቅት የሟች ቤተሰቦችና የቅርብ ዘመዶች ራሳቸውን ሳይቆጣጠሩ እየተነሱ እየወደቁ፣ ፊታቸውን እየነጩ፣ ጸጉራቸውን እየቧጠጡ፣ ደረታቸውን በድንጋይ እየመቱ፣ በአካላቸው ላይ ጉዳት እያደረሱ፣ ቅጥ ባጣ መንገድ ያለቅሳሉ፡፡ የቅርብ ሰዎች የሟችን ቤተሰቦች ከአደጋ የመከላከልና ለቅሶው ሥርዓት እንዲይዝ የማድረግ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን የሟች ዜና ረፍት በሚከተለው መንገድ ለዘመድ አዝማድ እንዲደርስ የማድረጉ ተግባር ይጀመራል፡፡

የሟች ረፍት ይፋ የሚደረገው፣ በገጠርና በከተማ በተለያዩ መንገዶች መሆኑን ከመረጃ አቀባዮቹ ገለጻና ከምልከታዎቹ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለምሳሌ ከስማዳ ወረዳ አባ አቸነፍ እንግዳ (አባ.2፣ ቁ.12፣ ክፍ.1.1.1.2.1.፣ አን.1)፣ ከደብረታቦር ዙሪያ ወረዳ አቶ ዋለ ጎበና (አባ.2፣ ቁ.14፣ ክፍ.1.1.1.2.1.፣ አን.1-2)፣ ከፎገራ ወረዳ አቶ መላሽ ወርቁ (አባ.2.፣ ቁ.21፣ ክፍ.1.1.1.2.1.፣ አን.1) እንደሚገልጹት በከተማ ሟች እንዳረፈበት ሠዓት ሊለያይ ቢችልም፣ አብዛኛውን ጊዜ ከንጋቱ አስራ አንድ ሰዓት ጀምሮ፣ ገንዘብ የሚከፈለው የእድር ለፋፊ፣ ጥሩንባ እየነፋ የሟችን ስም በመጥራት፣ ‹‹እገሌ›› ወይም ‹‹እገሊት ተጎድቷል/ታለችና አላቅሱን ተብላችኋል›› በማለት የቀብር ሥርዓቱ የሚፈጸምበትን ቦታና የየትኛው እድር አባል እንደሆነ ይለፋል፡፡

ሟች ከተማ ውስጥ ቢኖርም ብዙም የማይታወቅ ልጅ ሲሆን፣ በዕድሜያቸው ትልቅ ቢሆኑም በማሕበራዊ ግንኙነታቸው ብዙም እውቅና የሌላቸው ሴቶች ሲሞቱ፣ ራቅ ካሉ ገጠራማ አካባቢዎች ለሞተ ሰው፣ ከከተማ ያሉ ወገኖቹ ሲያስለፍፉ ወይም ከሌላ አካባቢ ለሞተ ሰው መርዶ፣ ከተማ ውስጥ ዜና ረፍቱ ሲነገር፣ ለቅሶው የሚጠራው በሟቾቹ ሳይሆን፣ ለልጆች በአባታቸው፣ ለሴቶች በባሎቻቸው፣ ለሌሎች በቅርብ ታዋቂ ቤተሰባቸው ስም ነው፡፡ ለፋፊው ‹‹አቶ እገሌ ልጁ፣ እህቱ ፣ወንድሜ፣ እናቱ፣ አባቱ ወዘተ.›› (የዝምድናው አይነት ተገልጾ) ‹‹ተጎድቷልና አላቅሱኝ ተብላችኋል›› ካለ በኋላ፣ የለቅሶውን የቀብር ቦታና የአስለፋፊውን እድር ይናገራል፡፡

በገጠር የሟች ረፍት ይፋ የሚደረገው ከዚህ በተለየ መንገድ እንደሆነ ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎችም መረጃ አቀባዮች ይገልጻሉ፡፡ አንድ ሰው ሲሞት ለቤተዘመድና ለአጎራባች አካባቢዎች

ዜና ረፍቱ የሚደርሰው፣ እንደከተማው ገንዘብ በሚከፈላቸው ለፋፊዎች ሳይሆን፣ በመላላክ ነው። የሟች ነፍስ እንደወጣ ዘመድ ተጠርቶ የማይደርስበት አጉል ሰዓት ከሆነ፣ በምስጢር ይያዛል። ከሰዓት በኋላ ከሆነ ቀብሩ የሚፈጸመው በሚቀጥለው ቀን እንደሚሆን ስለሚታወቅ፣ ቤተሰብና ጎረቤት በመላቀስ በዙሪያው የሚገኙ ሰዎች እንዲሰሙ ያደርጋሉ። ሰው ሲሰባሰብ የሟችን ማረፍ በየአቅጣጫው ለሚገኙ ወገኖቹ ለማድረስና በለቅሶው እንዲገኙ ለማድረግ፣ ሁለት ሁለት ሰዎች እየተመረጡ እስከየት ድረስ ማስጠራት እንዳለባቸው እየተነገራቸው፣ ራቅ ወዳሉ አካባቢዎች ይላካሉ። እነዚህ ሰዎች ጥና ጠሪ* ይባላሉ።

መልእክተኞቹ ወደተላኩበት አካባቢ በመሄድ፣ ከሚያውቁት ሰው ቤት አርፈው ምሽቱን ያሳልፋሉ። ሌሊት ላይ ዶሮ ሲጮህ (ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ)፣ ከፍተኛ ቦታ ላይ ሁነው የሚያውቁትን ባሻጋሪ የሚገኝ ሰው ስም ይጣራሉ። ‹‹አቤት›› የሚል ምላሽ ሲያገኙ፣ ሠላምታ** ሳይሰጡ የሟችን መኖሪያ ቀበሌና ስም ጠቅሰው፣ ‹‹እገሌ ተጎድቷልና አላቅሱን ተብላችኋል።›› በማለት ይናገራሉ። መረጃ ተቀባዩ መልዕክቱን በትክክል መስማቱን ለማረጋገጥ፣ ‹‹ሰማኸኝ ወይ;›› በማለት ይጠይቁታል። መልዕክት ተቀባዩ ከተጠራጠረ ‹‹ማን ነው ያልከኝ አልሰማሁህም›› በማለት እንዲደግሙለት ሲጠይቅ፣ በትክክል ከሰማቸው ግን ‹‹ሰምቸሃለሁ›› በማለት ያረጋግጥላቸዋል።

መልዕክት ተቀባዩ ለሌሎች ሰዎች መርዶውን እንዲያደርስ በሚፈለግበት ጊዜ፣ ጥና ጠሪዎቹ ‹‹ለእነ እገሌ እንዲደርስና ጥናውን አስይዘው እንዲመጡ አድርገህ አስጠራ ተብለሃል››፣ በማለት ይነግሩታል። መልዕክቱን የተቀበለው ሰው በተራው፣ ከከፍተኛ ቦታ ላይ ሆኖ በማዶ ወደሚገኝ ሰው በመጣራት በተመሳሳይ ሁኔታ መልዕክቱን ያስተላልፋል። በዚህ መንገድ አንዱ ለሌላው እየነገረ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ መልዕክቱ ሩቅ ቦታ ላሉት ሁሉ ይዳረሳል። በየአቅጣጫው የተላኩት በሙሉ በተመሳሳይ መንገድ የሟችን ረፍት ለቤተዘመድና ለሚመለከታቸው ሁሉ ያደርሳሉ።

---

* ጥና የሚለውን ቃል የአማርኛ መዝገበ ቃላት እ.ኢ.አ (1993፣583)፣ ‹‹ክብረት ወይም ከነሃስ የሚሰራ የቤተክርስቲያን እጣን ማጨሻ፣ ሻኩራ›› በማለት ይፈታዋል። መልእክት አድራሾቹ፣ ‹‹ጥና ይዛችሁ እንድትመጡ›› ብለው ስለሚናገሩ ‹‹ጥና ጠሪ›› የሚል ስም እንደተሰጣቸው መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ።

** በለቅሶ ጥሪ በባሕሉ መሰረት ሠላምታ አይሰጥም። ለቅሶ ደራሾችም እስከሰልስት ድረስ ቤተዘመድ ሀዘኑን በጋራ ወደሚገልጽበት ድንኳን ወይም ቤት ሲገቡ እያለቀሱ ወይም ዝም ብለው ይቀላቀላሉ እንጂ፣ ሰላምታ አይሰጡም። ይህ ልማድ በእሥራኤላውያንም እንዳለ Levine (2004) ያስረዳሉ።

ጥሪው በመደበኛ መልኩ ከላይ በተገለጸው ሁኔታ ቢተላለፍም፣ እስከአጎትና አክስት ድረስ ላሉት የሚች የቅርብ ቤተሰቦች፣ ሰዓቱ ሊያደርሳቸው የሚችል ከሆነ ወይም በመንገድ አደጋ የሚያስከትሉ ነገሮች ከሌሉ (ውሃ ሙላትና የዱር አውሬ)፣ ጥና ጠሪዎቹ ሰዓት ሳይጠብቁ ይነግሯቸዋል፡፡ በዚህ መንገድ የሚሰሙትና በአቅራቢያው የሚኖሩት ወደሚች ቤት በመሄድ፣ ለቅሶውን በሚከተለው መንገድ ያከናውናሉ፡፡

ሽማግሌዎች ወይም በዕድሜ ጠና ያሉ የሚች የቅርብ ሰዎች ለለቅሶ ጥሪው ከላይ በተገለጸው መንገድ ጥና ጠሪዎችን ካሰማሩ በኋላ፣ በሚች ቤት የለቅሶ ሥርዓቱ መስመር ይዞ እንዲካሄድ ያደርጋሉ፡፡ ምልከታ ከተካሄደባቸው ከወ.ሮ ቀኑብሽ (በ22/09/04) እና ከወ.ሮ ጸሀይ (በ8/10/04) የምሽት ለቅሶ ሥርዓቶች ለመረዳት እንደተቻለው፣ ቤተሰብ ቀደም ሲል በደረሱት ሰዎች ተከቦ ከግራ ወደቀኝ እየዞረ ሲያለቅስ፣ አዳዲስ ለቅሶ ደራሾች በግምት ከስድስት ሜትር ባልቀረበ ርቀት ፊታቸውን ወደለቀስተኛው በመዞር ትከሻ ለትከሻ ገጥመው ወደጎን መስመር ሰርተው ሲጠብቁ፣ አስተባባሪው ጥሩንባ በማስነፋት ሀዘንተኞቹ ከክቡ ወጥተው በረድፍ የሚጠብቃቸውን ለቅሶ ደራሽ እንዲገናኙ ያደርጋል፡፡ በእድሜ ጠና ያለው ሀዘንተኛ ከፊት ቀድሞ፣ ሌሎቹ እሱን ተከትለው ከክቡ ይወጡና፣ ከግራ ጀምረው ወደቀኝ፣ በቀኝ እጃቸው የደራሹን ቀኝ ትከሻ አንድ ባንድ እየነኩ የቅርብ ቤተሰባቸውን ሲያገኙም አንገት ለአንገት ተያይዘው እየተላቀሱ፣ ዳር ሲደርሱ ወደክቡ ይመለሳሉ፡፡

ከለቅሶ ደራሹ መካከል የቅርብ ዘመዶችና ወዳጆች ከሀዘንተኞቹ ጋር አብረው ሲገቡ፣ ሌላው ወደክቡ በመሄድ ይቀላቀላል፡፡ አዳዲስ ደራሽ በመጣ ቁጥር በርከት እስኪል እንዲጠብቅ እየተደረገ፣ በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጥሎ በቀረበው ፎቶግራፍ በሚታየው መንገድ ግንኙነቱ ይከናወናል፡፡



ምሥል ዘጠኝ፣ በ14/09.04 ዓ.ም በዋለው በአቶ ዓለምነው መንግሥቱ ለቅሶ ሀዘንተኞቹ አዲስ ለቅሶ ደራሾችን ሲገናኙ (ፎቶ በለማ ንጋቱ)

ሰዓቱ በጣም ካልመሸ፣ ወየታ ይጀመራል፡፡ ከሀዘንተኞቹ ጋር አብረው የሚዞሩ ችሎታው ያላቸው ሰዎች፣ በእራፊ ወይም በመሀረብ የተሸፈነ ዋንጫ እየተቀባበሉ ወየ ይላሉ፡፡ ወየታ ሲጀመር ሀዘንተኞቹ ድምጻቸውን አጥፍተው እየዞሩ ያለቅሳሉ፡፡ ወየ ባዩ የመድፊያውን ስንኝ አቅርቦ በሚጨርስበትና ሌላው ወየ ባይ እስኪወስድ ባለችው ክፍተት ካልሆነ በስተቀር፣ ሀዘንተኞቹ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው አያለቅሱም፡፡ ሟች ታዋቂ ከሆነና የሚሰበሰበው ሰው ብዙ ከሆነ ደግሞ ሙሾም ሊወረድ ይችላል፡፡

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አካባቢ ሲሆን፣ ሀዘንተኞቹ፣ ጎረቤቶችና በቅርብ ያሉ የዕድር አባላት ሲቀሩ፣ ሌላው ወደየቤቱ ስለሚመለስ፣ ሀዘንተኞቹ ወደድንኳን ገብተው ለቅሶው ይቀጥላል፡፡ አራት ሰዓት አካባቢ ሀዘንተኞቹ ለቀብር እንዳይደክሙ ለቅሶው እንዲቆም ይደረግና ይተኛል፡፡

ሟች በሌሊት ወይም በዕለቱ ለመቀበር በሚቻልበት ሰዓት ከሞተ ግን የምሽት ለቅሶ አይኖርም፡፡ ሞቶ ላደረ የንጋት ለቅሶ ከሌሊቱ አስር ሰዓት አካባቢ በቤተሰብ መላቀስ ይጀመራል፡፡ ሟች በሌሊት ወይም በዕለቱ ለመቀበር በሚችልበት ሰዓት ሲያርፍ፣ ለቅሶው በዚያው ሰዓት

የሚጀመር ሲሆን፣ ሬሳ የመገነዙና የሚችን ዜና እረፍት ለቤተዘመድ የመንገሩ ሂደት ከላይ በተገለጸው መንገድ ይካሄዳል፡፡ በቅርብ ያሉ ጎረቤቶችም ወደለቅሶው በመሄድ ሀዘንተኞቹን የማረጋጋት፣ ለቅሶውን ሥርዓት የማስያዝና፣ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት የማሟላት ሥራ ይሰራሉ፡፡ እየነጋ ሲሄድ፣ የእድር አባላትና ያካባቢው ሰው ሁሉ ወደሚች ቤት ስለሚሄድ፣ ሀዘንተኞቹ ከግቢ ውጭ ወዳለ ሰፊ ሜዳ ወይም መንገድ ይወጡና በተደራጀ መልኩ ለቅሶው ይጀመራል፡፡ ሀዘንተኞቹ ክብ በሰራው ሰው መሀል ወደቀኝ እየዞሩ ሲያለቅሱ፣ ወየታ ይጀመራል፡፡ ወየ ባዮቹ አብረው እየዞሩ ወይም ክብ ከሰራው ሰው በውስጥ በኩል ተደርበው ጎን ለጎን ቁመው ዋንጫ እየተቀባበሉ ተራቸውን እየጠበቁ ወየ ይላሉ፡፡ ለቅሶ ደራሹ እየመጣ ክብ ሰርቶ ሲቆምና በርከት ሲል፣ አስተባባሪው ጥሩንባ አስነፍቶ ሀዘንተኞቹ ወጥተው በምሽት ለቅሶው በተገለጸው የግንኙት መንገድ እንዲቀበሉ ያደርጋል፡፡

ካህናቱ ከቤት ውስጥ ፍትሃተ ጸሎት ሲያከናውኑ፣ ከውጭ በዚህ መልኩ ይለቀሳል፡፡ ካህናቱ ፍትሃት መጨረሳቸውን ለሀዘንተኞቹ እንዲያሳውቅ ለለቅሶ አስተባባሪው ሲነግሩት፣ ጥሩንባ ያስነፋና ሀዘንተኞቹ ወደቤት ገብተው ሬሳውን እንዲሰናበቱ ይነግራቸዋል፡፡ ሀዘንተኞቹ እጆቻቸውን ወደላይ ዘርግተው እያወናጨፉ ግር ብለው ወደቤት ይገባሉ፡፡ ሬሳውን እየዞሩ፣ በእጃቸው እየነኩ፣ አንዳንዴም ተንበርክከው ሬሳው ከተጋደመበት አልጋ ላይ በግንባራቸው እየተደፉ፣ ለሚች እንዳላቸው ዝምድና ‹‹ደህና ሁን፣ አባባ፣ እማማ፣ ወንድማለም፣ እህታለም ወዘተ.››፣ እያሉ ቅጥ ባጣ መንገድ ሲጯጯሁ፣ አስተባባሪዎች እየገፉ ወደወጭ ያስወጧቸዋል፡፡ እጆቻቸውን በተከሻዎቻቸው ትይዩ ወደላይ ዘርግተው እያርገበገቡ፣ ጎንበስ ቀና እያሉና ወገባቸውን በእጆቻቸው ጥርቅም አድርገው ይዘው ጎንበስ ብለው እየሄዱ፣ በመሪር ለቅሶ ወደውጭ ይወጣሉ፡፡ በዚህ ጊዜ፣ ሀዘንተኛው ሁሉ አብሯቸው የመረረ ለቅሶ ያለቅሳል፡፡

ደብረ ታቦር ከተማና ፋርጣ ወረዳ ከተካሄዱ ተደጋጋሚ ምልከታዎች ለመረዳት እንደተቻለው፣ ሀዘንተኞቹ ቤቱን ለቀው እንደወጡ፣ ካህናቱ እየመሩ ሬሳውን የተሸከሙ ሰዎች በዋናው በር ይወጣሉ፡፡ አስከሬኑ ከበሩ ሙሉ በሙሉ ሲወጣ፣ ውሃ የያዘ ቶፋ፣ ድስት ወይም ቅል፣ ከበረንዳው ላይ ድምጽ እንዲያሰማ በሀይል ተወርውሮ ይሰበራል፡፡ አስከሬኑ ከግቢው እንደወጣ ለቤተሰቡ ታማኝ የሆነች ሴት፣ ቤቱን ትጠርጋለች፡፡



*ምሥል አስር፣ በ22/02/04 ዓ.ም ደብረታቦር ዙሪያ ወረዳ ሬሳ ከቤት ሲወጣ በር ላይ የተሰበረ ሸክላ (ፎቶ በለማ ንጋቱ)*

ስለሬሳ ከቤት አወጣጥ ስርዓት ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው አቶ ገበያው ዓለሜ (አባ.2፣ ቁ.11፣ ክፍ.1.1.1.2.2.፣ አን.1) እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> … ሬሳ ሲወጣ ትልቅ ሰው ሲሆን በግ ይታረዳል፡፡ በጉ ይታረድና «ሬሳው ደም እረግጦ ይውጣ» ይባላል፡፡ ደግሞ እሬሳው እየወጣ መቃውን ጨርሶ ሳይወጣ እንደ ድስት ያለ ወይም እንደ ቶፋ ያለ ሸክላ ይሰበራል፡፡ ዳግም እንዳይተካ እግሩን ደረቅ እንዲያደርገው ነው ባህሉ፡፡ እሚታረደው ላለው ሲሆን እሚሰበረው ግን ለሁሉም ነው፡፡ የሚታረደው በግ ለቁሶቹ ነው የሚሄድ፡፡ ያለው ከሆነማ ለመኳንንቱም በሬውን ያርዳል፡፡ ቶፋው ወይም ድስቱ ግን ኳ ኳ ብሎ እንዲጮህ ሰውየው እንደተሰበረው ዳግም እንዳይተካ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ እንግዲህ ሟች ጥቅም የሌለው ነገር ነው አበቃ ማለት ነው፡፡ ሰባሪው የሚቆመው ከቤት ውጭ ነው፡፡ አስከሬኑ ወደ ውጭ ብቅ ሲል ያንን ይሰብራል፡፡ ሬሳው ርጥብ ረግጦ ይውጣ ተብሎ በግ የሚታረደውም ከመውጫ በሩ ላይ ነው፡፡ ዱሮ የተለያየ የሬሳ አወጣጥ አለ ይባል ነበር፡፡ የባለቤት ሬሳ በደንብ ለብሶ በዋናው በር ሲወጣ የአገልጋዮች በበር ሳይሆን በጓዳና በመስኮት ይወጣ ነበር፡፡ እንዲህ የሚደረገው አገልጋይ እንደቤተሰቡ አባል ሳይሆን እንደ ትርፍ ሰው ስለሚቆጠር ነው፡፡

ሲ.ቀ ማዕምራን አማረ ጌጡ (አባ.2፣ቁ.1፣ ክፍ.1.1.1.2.2.፣ አን.1ና2) እንደሚገልጹት የሸክላው መሰበር፣ ሰውም ሆነ ሸክላ ከተመሳሳይ አፈር መሰራታቸውንና ሁለቱም ፈራሾች መሆናቸውን በማጠየቅ ቋሚን ማስተማሪያ ነው። ሬሳው ሲወጣ የሚታረደው በግ ለፈጻሚው ከአራት ዘመን አምልኮ ጋር የተያያዘ ልማድ እንዳለውና ለካህናቱ ግን ግብዣ መሆኑን ይገልጻሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ አደባባይ ከተሰቀለ በኋላ እንዲህ መደረጉ በሀዲስ ነውር መሆኑን እያስተማሩ እንደሆነና ድርጊቱ ግብዣን ከአምልኮት ያቀላቀለ ተገቢ ያልሆነ ነገር እንዳለው ያስረዳሉ።

የአገልጋዮችና የሌሎች ሰዎች ሬሳ ከዋናው በር በተለየ በጓዳ በር፣ በመስኮት ወይም ግድግዳ ተቀዶ እንዲወጣ የሚደረገው፣ በሁለት የተለያዩ ምክንያቶች መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል። ይኸውም ለአገልጋዮች እንደቤተሰብ አባል ሳይሆን እንደባዕድ መቆጠራቸውንና በማህበራዊ ደረጃቸው ከቤተሰቡ እኩል አለማሆናቸውን ለማመልከት ሲሆን፣ ከአገልጋዮች ውጭ ለሆኑ ሰዎች፣ ሀብታቸው ተከትሏቸው እንዳይሄድ (እንዳይወድም) ለመከላከል በማሰብ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል።

Abbink (1992፣70) በመኤን ማሕበረሰብ፣ ሬሳውን ለብቻው ከተቀመጠበት ጎጆ በጓዳ በኩል ቀዶ የማውጣት ልማድ እንዳለ ቢገልጹም፣ ለምን እንደዚያ እንደሚደረግ አላብራሩም። በቴክሳስ በሞት ዙሪያ በሚነገሩ ሎሮች ላይ ምርምር ያካሄዱት Untiedt (2008፣6-7) ግን፣ ሬሳው በበር ሳይሆን በመስኮት ወይም በሌላ ቀዳዳ ተወጥቶ የሚወሰደው፣ ከእሱ የወጣውን መንፈስ ግራ አጋብቶ፣ ሬሳውን እንዳይከተል ለማድረግ እንደሆነ ከነምክንያቱ ያስረዳሉ።

የመኤኖችን ልማድ ስለምንነት ለማግኘት ባይቻልም፣ በተጠኚውና በቴክሳስ ማሕበረሰቦች ሬሳን በዋና በር ያለማውጣት ልማድ የሚያመላክተው የጋራ ጉዳይ ያለ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል። ይኸውም ከሟች የህይወት ዘመን እጣ ፈንታ መወሰኛና መንፈስ መስፈሪያነት ጋራ ተያያዥነት የነበራቸው እንደእድልና መናፍስት ያሉት ጉዳዮች፣ ነፍስ ስትወጣ ከሬሳው ተለይተው፣ ነፍስንም ሳይከተሉ ራሳቸውን ችለው እንደሚኖሩ መታመኑ ነው። ማደሪያቸው የነበረውንና ሞት ያፋታቸውን አካል በር ላይ ጠብቀው እንዳይከተሉትና መቃብሩ ድረስ ተጉዘው በዚያው እንዳይቀሩ ሬሳ በጓዳ እንዲወጣ መደረጉ፣ በአካባቢው ሆነው ለሟች

ይፈጽሙት የነበረውን ነገር ለቋሚዎች እንዲቀጥሉ ከመፈለግ የመነጨ ሳይሆን እንዳልቀረ ለመገመት ይቻላል፡፡

በመሪር ለቅሶ ታጅቦ ሬሳው ከቤት ሲወጣ የሚሰበረው ሸክላ ደግሞ፣ በአንድ በኩል የሚችን ከንቱ የመቅረት ፍጻሜ አመላካችነት፣ በሌላ በኩል፣ ሚች እግረ ደረቅ እንዲሆን (ሞት እዚያ ቤት ዳግም እንዳይከሰት) የመመኛነት ትዕምርቶች ያሉት መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ሬሳ ሲወጣ ቤቱ የሚጠረግበት ምክንያትም፣ በአንድ ጎኑ ከዚሁ ሚችን እግሩን ደረቅ ያድርገው ምኞት ጋር ተያያዥነት ያለው መሆኑንና በሌላ በኩል ሬሳው ሲሰነዳዳ ውሃ ስለሚደፋፋ፣ ቆሻሻውን ከማጽዳት ጋር እንደሚገናኝ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ጩኸትና ዋይታ በተቀላቀለበት መሪር ለቅሶ ሬሳው ከቤት ከወጣ በኋላ፣ ብዙ ጊዜ አጎበር በተሰራበት አልጋ ከላይ ግምጃ ለብሶ፣ ወደቤተክርስቲያን ጉዞ ይጀመራል፡፡ በጉዞ ወቅት ካሕናት ሲቀድሙ ሬሳው ይከተላል፡፡ ከሬሳው በኋላ ሀዘንተኞቹና ለቀስተኛው እንደቅደም ተከተላቸው ይከተላሉ፡፡ በዕምነቱ መሰረት ሬሳው የሚጓዘው እግሩ ቀድሞ ነው፡፡

የሬሳ እግሩ ቀድሞ መሄድ በተለያዩ ባሕሎች በተመሳሳይ ሁኔታ የሚፈጸም ልማድ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በተጠኚው ማሕበረሰብ ባህል ተደርጎ በመወሰዱ ሲፈጸም፣ በቴክሳስ ግን ከሬሳው ወጥቶ ከኋላ የሚከተለው መንፈስ፣ ሬሳውን ፊት ለፊት ሲመለከት ተመልሶ እንዳይገባበት ለመከላከል ታስቦ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ሬሳውን ከመናፍስቱ ሰውሮ ለመውሰድ በዋናው በር እንዳይወጣ ከሚደረግበት ዓላማ ጋር ተደጋጋፊነት ያለው ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በሌሎች ባህሎች ደግሞ፣ የሬሳ እግር ቀድሞ እንዲሄድ የሚደረገው፣ በሕያዋን ላይ የሚቀናው የሚች መንፈስ፣ ከኋላው ከሚከተሉት ቤተሰቦቹ አንዱን ጠቅሶ እንዳያስከትል ለመከላከል ታስቦ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከነዚህ ከባሕል ልዩነት ጋር ተያይዘው ከዳበሩት እምነቶች ባሻገር፣ የሬሳ እግር እንዲቀድም መደረግ ተመሳሳይነት፣ ከሥርዓተ ተፈጥሮ የተወረሰ ሳይሆን እንዳልቀረ ለመገመት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ሰው በማንኛውም መደበኛ እንቅስቃሴ የሚሄደው ወደፊት ሲሆን፣ ጉዞው

የሚመራው ደግሞ በእግሩ ነው፡፡ ይህ ነባራዊ ሁኔታ የፈጠረው ግንዛቤ ለልማዱ በስፋት መገኘት መነሻ ሳይሆን አይቀርም ቢባል ምክንያታዊ ይመስላል፡፡

አስከሬን ከቤት ወጥቶ ሲሄድ፣ ሀዘንተኞቹ በየግላቸው ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እየጮሁ በማልቀስ ይከተላሉ፡፡ ሌላው ለቀስተኛ እነሱን ተከትሎ ወደማርገጃ ወይም ሟች የገዞ ፍትሀት የሚደረግለት ከሆነ፣ ወደመጀመሪያው የማረፊያ ቦታ ይኬዳል፡፡ አስከሬኑ ካረፈበት በስተደቡብ ለቀስተኛው ክብ ይሰራና ሀዘንተኞቹ ውስጥ ገብተው ወደቀኝ እየዞሩ ለቅሶ ይጀመራል፡፡

ቀኝ እጃቸውን አውጥተው ትከሻ ለትከሻ በመግጠም ረድፍ የሰሩ ወየባዮች፣ ሀዘንተኞቹን እየተከተሉ ወየ ማለት ይጀምራሉ፡፡ አንዱ ሲጨርስ ዋንጫውን ለሌላ ተረኛ እያስተላለፈ እየዞሩ ወየ ሲሉ፣ ለቅሶ ደራሾቹም፣ በምሽት ለቅሶ በተገለጸው መንገድ ይገናኛሉ፡፡ ሀዘንተኞቹ ከግራ ጫፍ ጀምረው ወደቀኝ ከእያንዳንዱ ለቀስተኛ ጋር በቀኝ እጃቸው ትከሻ ለትከሻ እየተነካኩ ሲዞሩ፣ ገና ያልደረሰው ጠደፍ ጠደፍ እያለ በቀኝ ጫፍ መስመር ይገባል፡፡ ሀዘንተኞቹም ለሟች እንዳላቸው ቅርበትና እድሜ ለቀስተኛውን የሚገናኙት በተራ መስመር ይዘው ነው፡፡ ከሰው ጋር ብዙም እውቂያ የሌላቸው ሀዘንተኞችና ልጆች፣ ከሚገናኙት ሀዘንተኞች በውስጥ በኩል እየዞሩ ያለቅሳሉ እንጂ፣ እንደትልቆቹ ትከሻ ለትከሻ አይገናኙም፡፡ ለቅሶ ደራሾቹ የሀዘንተኞቹን ትከሻ በእጃቸው እየነኩ የሚያለቅሱት በአንድ በኩል የሀዘንተኞቹን መጎዳት ለመግለጽና ከጎናቸው መሆናቸውን ለማመልከት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ከለቅሶው መገኘታቸውን ለማሳወቅ ነው፡፡ ግንኙቱ ሲያልቅ፣ ሀዘንተኞቹ ወደነበሩበት ቦታ ሲመለሱ ለቀስተኛው ወደክቡ ይቀላቀላል፡፡

ቀደም ሲል ወየ ሲሉ የነበሩት፣ በዚህ ጊዜ ክብ ከሰራው ለቀስተኛ በውስጥ በአንድ በኩል ጎን ለጎን ገጥመው በመቆም ከግራ ወደቀኝ ዋንጫ እየተቀባበሉ ተራ በመጠበቅ ወየ ይላሉ፡፡ ዋንጫ መቀባበሉ ከሟች ቤት መብላት መጠጣትን ወይም የሟችን እንግዳ ተቀባይነት እንደሚያመልከትና ቅብብሉ ወደአንድ አቅጣጫ መጓዙም ተራውን ጠብቆ ሁሉም ከዋኝ እንዲደርሰው ለማድረግ እንደሆነ መረጃ አቀባዮቹ ይገልጻሉ፡፡ አዳዲስ ወየ ባዮች ሲመጡ በቀኝ ጫፍ በመግባት ወረፋቸውን ይጠብቃሉ፡፡ ከወየ ባዮቹ መካከል በጣም ያማረ ድምጽ ያለው፣ ስለሟቹ የአሟሟት ሁኔታ ወይም ታዋቂ ስለሆነበት ተግባሩ እያነሳ ወየ ማለት ሲጀምር፣ ከቁርጥ ሀዘንተኞቹ መካከል፣ እናት፣ አባት፣ ባል፣ሚስት፣ ልጅ፣ እህት ወይም ወንድም ወደዚያ ከዋኝ ፊታቸውን በመዞር፣ ጎንበስ ብለው ወደፊትና ወደኋላ በመመላለስ፣ ወይም ቀና ብለው የሟችን ልብስ ወይም መገልገያ ቁስ በእጆቻቸው ይዘው ግራና ቀኝ በማወዛወዝ፣

እያሶመሶሙ ይከታተላሉ፡፡ ‹‹እንዲያ በለውማ፣ እኔ ልጠራ›› የሚሉትን ሀረጋት ከመናገር ውጭ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዳያለቅሱ ይከለከላሉ፡፡ ወየ ባዩ ሲደፋው እሪ እያሉ ከሌሎቹ ሀዘንተኞች ጋር ይቀላቀላሉ፡፡



ምስል አስራ አንድ፣በ8/09/04 ዓ.ም በዋለው በእሙሀይ አዛለች ለቅሶ ሀዘንተኞቹ ወደወየ ባዩ ዙረው ድምጻቸውን አጥፍተው እያሶመሶሙ ሲያለቅሱ (ፎቶ በለማ ንጋቱ)

ከውስጥ እንዲህ ሲለቀስ፣ ከክቡ ውጭ አስተባባሪዎች አዳዲስ ለቅሶ ደራሾችን መስመር እያስያዙ፣ በርከት ሲሉ ጥሩንባ እያስነፉ ሀዘንተኞቹ እየወጡ ቀደም ሲል በተገለጸው መንገድ እንዲገናኙ ያደርጋሉ፡፡ ሬፌድ ማለት ሲጀምር የሟች ዕድሜ ከሃያ ዓመት በላይ ከሆነ፣ ሙሾ አውጭዎች ይመራረጡና ሶስት ወይም አራት ሆነው ትክሻ ለትከሻ ይገጥሙና በምስራቅ በኩል ‹‹ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ ዋዋ››፣ ይላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ሀዘንተኞቹ ቦታቸውን ለቀው በደቡብ በኩል አስር ሜትር ያህል ራቅ ብለው በለቀስተኛው ተከበው በተመሳሳይ ሁኔታ እየዞሩ ያለቅሳሉ፡፡ ወየ ባዮችም አብረው እየዞሩ ወየ ይላሉ፡፡



ምስል አስራ ሁለት፣ በ8/10/04 ዓ.ም ከዋለው ከወ.ሮ ጸሐይ እንግዳየሁ ለቅሶ ከፊት ለፊት የሙሾ ከጀርባ የወየታ ቃል ግጥሞች ጎን ለጎን ሲከወኑ (ፎቶ በለማ ንጋቱ)

ለቀስተኛው፣ ሀዘንተኞቹንና ሙሾ አውራጆቹን ለማጀብ እንድየችሎታው፣ ጾታውና ፍላጎቱ ለሁለት ይከፈላል፡፡ ሙሾ አውራጆቹን የሚያጅባቸው ለቀስተኛ ከጀርባቸው መስመር፣ ከጎናቸው ክብ ሰርቶ፣ እነሱ እያረገዱ ወደፊት ሲሄዱና ሲመለሱ አብሮ እያረገደ በመሄድ ይመለሳል፡፡ ሙሾው ሲያበቃ ለቀስተኞቹ ተመልሰው ከዋናው ክብ ውስጥ ይገባሉ፡፡ ወየታው ቀደም ሲል በነበረው ሁኔታ ይቀጥላል፡፡ እንደሚቹ ሁኔታ ፋከራ ሊኖር ይችላል፡፡

ሚች አርበኛ፣ ተሚጋች፣ ሀብታምና ለጋስ ገበሬ ወይም ነጋዴ ከሆነ፤ እንዲሁም ሴቷ ጥሩ የባልትና እውቀት ያላት፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ልጆቿን በሥርዓት አሳድጋ የዳረች የኳለች ከሆነች፣ ይፎከርላቸዋል፡፡ ፎካሪዎቹ የአካባቢው ነዋሪዎች ወይም ከሌላ ቦታ በክፍያ የመጡ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ፋከራ የሚኖር ከሆነ የሙሾ ሥርዓቱ ከአንዴ ወይም ከሁለቴ በላይ ላይኖር ይችላል፡፡

ፋከራ ከሌለ የመጀመሪያው ዙር ሙሾ ከተወጣ በኋላ ትንሽ ቆየት ብሎ፣ ሁለተኛው ዙር ሙሾ ይጀመራል፡፡ ሀዘንተኞቹ ወጥተው የራሳቸውን ክብ በመስራት ወየ እየተባለ ይለቀሳል፡፡ ከወዲህም ከላይ በተገለጸው ሁኔታ፣ ሙሾ ይወረዳል፡፡ ሚች በጣም ታዋቂና ትልቅ ሰው ከሆነና ሰዓቱ አመች ከሆነ እስከአምስት ጊዜ፣ ያለዚያ ግን እስከሶስት ጊዜ ሙሾ ይወጣለታል፡፡ አምስትም ይሁን ሶስት፣ በመጨረሻ የሚወረደው ሙሾ ‹‹ዋ ተለያየነ››፣ የሚባለው ነው፡፡ ቀሳውስቱ ፍትሃት ጨርሰው፣ ጉድጓድ ማሾችም አድርሰው ከሆነ፣ አጠር አጠር ተደርጎ ይጠናቀቃል፡፡ ጊዜ ካለ ግን፣ ረዘም ሊል ይችላል፡፡ ያም ሆነ ይህ፣ ‹‹ዋ ተለያየነ›› የሚለው

ሙሾ ሲወረድ፣ የቀብር ሰዓት እየደረሰ መሆኑን ለቀስተኛው ይረዳል። ቀሳውስቱ የፍትሃት ጸሎቱን ጨርሰው አስከሬኑን ለስንብት ወደቤተ ክርስቲያን ካልወሰዱ ሙሾው ያበቃና ሀዘንተኞቹ ወደዋናው ክብ ተመልሰው ወየታው ይቀጥላል። መቃብሩ ተምሶና ፍትሃቱ ተጠናቆ አስከሬኑ ወደቤተክርስቲያን ከተወሰደ ግን፣ ለቀስተኛው መከተል ይጀምራል። የቤተክርስቲያን ደወል ሲደወል፣ ሀዘንተኞቹ ግር ብለው ወደመቃብሩ ቦታ እየተጯጯሁ ይሄዳሉ። ለቀስተኛውም ይከተላል። የቀብሩ የመጨረሻ አፈር የመመለስ ሥርዓት ከፍተኛ ጩኸት በተቀላቀለበት ለቅሶ ይካሄዳል። የቀብር ሥርዓቱን የሚያስፈጽመው ካህን ማሳረጊያ ጸሎት ሰጥቶ ሲጠናቀቅ፣ የቀብር ሥርዓቱ ፍጻሜ ይሆናል።

ከዚህ በላይ እስከቀብር ድረስ በሀይማኖታዊም ሆነ በዓለማዊ ሥር የተገለጹት የለቅሶ ሥርዓቶች፣ ክርስትና ከተነሱ ሕጻናት በላይ ያሉትን የማሕበረሰብ ክፍሎች የሚመለከቱ ሲሆኑ፣ ክርስትና ያልተነሱ ሕጻናት የቀብር ቦታና ሥርዓት የሚፈጸመው ለየት ባለ መንገድ መሆኑን መረጃ አቀባዮቹ ይገልጻሉ። በህጻናት የለቅሶ ሥርዓት ጥሪ እንደማይካሄድ፣ ምንም አይነት የለቅሶ ቃል-ግጥም እንደማይከወንና፣ ካህናትም ሆኑ ከቤተሰብ ውጭ የሆኑ ሌሎች ሀዘንተኞች እንደማይገኙ፣ አቶ አያሌው ተሾመ (አባ.2፣ ቁ.22፣ ክፍ.1.1.ሐ.፣ አን.1) እና አቶ ሀይሌ ረታ (አባ.2.፣ ቁ.37፣ ክፍ.1.1.ሐ፣ አን.1) ያስረዳሉ።

የሕጻናቱ የቀብር ቦታ ከቤተክርስቲያን ቅጥር ውጭና በመኖሪያ አካባቢ እንደሚከናወንም፣ እነዚሁ መረጃ አቀባዮች ያስረዳሉ። አስር ቀን ያልሞላቸውና ጠበል ያልተረጩ ሕጻናት በተወለዱበት ቤት ጥግ እንደሚቀበሩና፣ አስር ቀን ሞልቷቸው ጠበል ከተረጩ፣ ወደቤተክርስቲያን ተወስደው ከቅጥሩ በውጭ በኩል ከጥግ እንደሚቀበሩ ያስረዳሉ። እንዲህ የሚደረገውም ክርስትና ስላልተነሱ ክርስቲያን አይደሉም ተብሎ በመታመኑ እንደሆነ ይገልጻሉ። የለቅሶ ሥርዓት የማይኖረውም የማሕበረሰቡ ሙሉ ዓባላት ባለመሆናቸውና ሞታቸው የሚፈጥረው ሀዘን እንደ ሙሉ አባላቱ ከባድ ተደርጎ ስለማይታይ ነው። በሌሎቹ የቀብር ሥርዓቶች እንደታየው ሁሉ በሕጻናት የቀብር ሥርዓት ዙሪያ የሚታየው ልማድም ከእሥራኤል አይሁዶች የሕጻናት ቀብር ሥርዓት ጋር ተቀራራቢነት ያለው መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። ለምሳሌ ለሕጻናት የቀብር ሥርዓት ቀለል ያለ ትኩረት የሚሰጠው መሆኑን፣ Levine (2004፣122) ያስረዳሉ። ሕጻናት ሰላሳ ቀን ሳይሞላቸው ቢሞቱ፣ በሕይወት እንደኖሩ

ስለማይቆጠሩ፣ ምንም አይነት የጸሎት ሥርዓት እንደማይደረግላቸውና ሶስት ያህል ሰዎች ወስደው እንደሚቀብሯቸውም ይገልጻሉ፡፡

ሀይማኖትን መነሻ በማድረግ ሕጻናቱን ክርስትና ከተነሱት በተለየና እንግዳ በሆነ መንገድ መቅበር በተጠኚው ማህበረሰብ የተለመደ ቢሆንም፣ ድርጊቱ ከላይ የተገለጸው ሀይማኖታዊ መሰረት እንደሌለው መሪጌታ ክፍለማርያም አለነ (አባ.2፣ ቁ.2.፣ ክፍ.1.1.ሐ፣ አን.1) ያስረዳሉ፡፡ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን እንኳንና ዘጠኝ ወር ሞልቶት ተወልዶ ለሞተ፣ ጊዜውን ሳያሟላ በተለያዩ ምክንያቶች ለተጨነገፈም፣ አካል ካለው በቤተክርስቲያን መቀበር እንዳለበትና የክርስቲያን ልጅ በመሆኑም፣ አንድ ፍትሃት ሊደረግለት እንደሚገባ እንደሚደነግግ ይገልጻሉ፡፡

ከዚህ በላይ የተገለጸው ሥርዓት፣ ሬሳ በሚኖርበት የዕለት ለቅሶ እስከቀብር ድረስ የሚከወን ሲሆን፣ ሬሳ በሌለበት በቀጠሮ ለቅሶ የሚከናወነው ዓለማዊ የለቅሶ ሥርዓት ምን እንደሚመስል ደግሞ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

#### 4.1.2.2. በቀጠሮ ለቅሶ የሚከናወኑ ዓለማዊ የለቅሶ ሥርዓቶች ክወና

የቀጠሮ ለቅሶ ሟች ከተቀበረ ከሳምንታትና ወራት በኋላ የሚካሄድ ስለሆነ፣ የሀዘን ድባቡ የዕለት ለቅሶን ያህል ከባድ አይደለም፡፡ ሬሳ ባለመኖሩ እንደምሽት ለቅሶ፣ የጉዞ ፍትሃት አይነቶቹ ሥርዓቶችና ከሬሳ ማሰናዳት ጋር የተያያዙት ልማዶች አይኖሩም፡፡ የሟች ዜና ረፍት ይፋ የሚደረግበት መንገድም የተለየ ነው፡፡ በዚህ የለቅሶ አይነት የሟች ዜና ረፍት በሁለት መንገድ እንደሚተላለፍ መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ፡፡ የመጀመሪያው የቅርብ ቤተሰቦቹ ወስነው በቀብሩ ላይ፣ ‹‹በዚህ ቀን ከዚህ ቦታ ዘመዱ እንዲያላቅሰን ንገሩ›› ተብሎ የሚለፈፍበት ነው፡፡ ሁለተኛው ወቅቱ አላመች ሲል ወይም ቤተዘመድ በመደናገጥ ሳይወስን ሲቀር፣ በቀብሩ ላይ ወደፊት የቀጠሮ ለቅሶ እንደሚኖርና ቀኑም ተቆርጦ እንደሚነገር የሚገለጽበትና ቀኑ ከተቆረጠ በኋላ በተገኘው አጋጣሚ በመላላክ ሰው እንዲሰማ የሚደረግበት ነው፡፡

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ቀደም ባለው ጊዜ አንድ ሰው በክረምት ሲሞት ሩቅ ላሉት ዘመዶቹ ለመንገር ውሃ ሙላት ስለሚከለክልና እህል ውሃ ለማዘጋጀት ችግር ስለሚኖር፣ ‹‹ቀን ሲወጣ ይለቀስ›› ተብሎ በጋ ላይ ተቀጥሮ ይለቀስ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ በዕለቱ የቀጠሮ ለቅሶ

እንደሚኖር ይገለጻል፡፡ ቤተዘመድ ከመከረ በኋላ ቀኑ ተቆርጦ በቤተክርስቲያንና በሌሎች ሰዎች ለቅሶ ላይ የቀጠሮ ቀኑ ይነገራል፡፡ በጣም ሩቅ ላሉት ዘመዶች መልዕክት ቀደም ብሎ እንዲደርሳቸው ይደረግ ነበር፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በፋርጣና በደብረታቦር ዙሪያ ወረዳዎች የቀጠሮ ለቅሶ የለም ለማለት በሚቻልበት ደረጃ እየቀነሰ ቢሆንም፣ በተቃራኒው በፎገራ፣ በላይ ጋይንትና በስማዳ ወረዳዎች እየተስፋፉ መሆኑን መረጃ አቀባዮቹ ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ አቶ አበረ ከበበው (አበ.2.፣ ቁ.10፣ ክፍ.1.1.2.2.፣ አን.2) በፎገራ ወረዳ በዕለት ለቅሶ ላይ የቀጠሮ ለቅሶ እንደሚለፈፍ ይገልጻሉ፡፡ አቶ ወንዳያ ጓንጉል (አባ.2፣ ቁ.15.፣ ክፍ.1.1.2.2.፣ አን.1-4) እና አቶ ብርሃን አበበ (አባ.2፣ ቁ.16፣ ክፍ.1.1.2.2.፣ አን.1-5) በዕለት ለቅሶ የቀጠሮ ለቅሶ እንደሚኖር እንደሚለፈፍ ወይም ወደፊት ቀን ተቆርጦ በየቤተክርስቲያኑና በሌሎች ሰዎችም ለቅሶ እንደሚገለጽና፣ ራቅ ላሉት ሰዎች በመልዕክት እንዲደርሳቸው እንደሚደረግ ይገልጻሉ፡፡

እነዚሁ መረጃ አቀባዮች አክለው እንደሚያስረዱት፣ በአሁኑ ጊዜ የሚካሄደው የቀጠሮ ለቅሶ ቀደም ሲል ከነበረው በብዙ መልኩ ይለያል፡፡ ለምሳሌ በላይ ጋይንት ወረዳ፣ የቀጠሮ ለቅሶ ከደርግ መንግሥት ጀምሮ ‹‹የግንኙት ለቅሶ››፣ በሚል ተቀይሮ ገበያ ላይ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ባሕሉ ከአጎራባች ወረዳ ከመቄት እንደተወረሰ አቶ ምህረት አለነ (አባ.2.፣ ቁ.18.፣ ክፍ.1.1.2.2.፣ አን.1-2) እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> የላይ ጋይንት የገበያ ላይ ለቅሶ መቄት ወረዳ ወሎ ውስጥ ነው የተጀመረው፡፡ ኸዚያ እሚያደርጉት ምንድነው፣ ዘመድ ኸዚያ ኸቀብሩ ላይ ይመካከሩና «ለዚህን ቀን ብለናል ዘመድ እንዳይለፋ ተላላኩልን» ይላሉ፡፡ አሁን ሂደው ገበያ ላይ ኸዚህም ኸዚም የተጎዳው ቁጭ ይላል፡፡ ኸዚያ በኋላ ያ ገበያ የሄደ አንዱን አንዱ ይነግረዋል «እንዲህ ነው» ይለዋል፡፡ ሰው ሲሄድ መቄት ላይ ሁለት ብር ከኪሱ፣ ባገልግል እንጀራ ያለው በወጥ፣ የሌለው በጨው ሁለት እንጀራ ቀብቶ ይዞ ነው የሚወጣው ለቅሶ ደራሹ፡፡ ኸዚያ በኋላ ያንን ብር የሚሸክፍ አለ ይሸክፍ ይሸክፍና ሰዎቹ ኸዚያው እንደተቀመጡ ጠላ ሀለበት ይፈልጋሉ፡፡ ከተገኘበት ቤት ሀዘንተኞቹን ወስደው ያገልግል እንጀራቸውን ጨርቅ ላይ ዘርግተው ይበላሉ፡፡ ጠላቸውን ጠጥተው የተረፈውን ብር ለተጎዳው አካል «ለቡና ይሁንህ» ተብሎ ይሰጣል፡፡

ጉርብትና መቼም ችግር ነው ያንን ተሞክሮ ጋይንት ከዚያ ለመደ፡፡ አሁን ጋይንት ላይ ስናየው የብሪቱና የእንጀራይቱ ነገር ... የለችም፡፡ በአብዛኛው ግን ሰው ወደዚህ እየዞረ ነው፡፡ ... ሰው ለቅሶ ለመድረስ ከሩቅ ቦታ መጥቶ መቼም ሻይ ቡና ሳይል አይመለስም፡፡ ያስተዛዘነውን ሰው «ግባ» ለማለትና ለማስተናገድ ሰው አቅም አጣ፡፡ ይህንን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ነገር ነው፡፡ ... «ኧህ ይኸነገር ሰው ቢመጣ አሁን እህል ውሃውስ መች» ይባላል፡፡ ስለዚህ «ኸገበያው ጠብቁ እንበላቸውና ሰውም እንዳይደክም እኛም በዚው እንሸኛቸው» እየተባለ የሚደረግ ሁኔታ ነው ያለው፡፡

በዞኑ ከሚገኙት ወረዳዎች፣ የግንኙት ለቅሶ በፎገራ ወረዳ በስፋት እንደሚተገበር እ.ኢ.አ. በ25/9/04፣ በ9/10/04፣ በ30/6/05 እና በ17/05/2006 በቦታው በመገኘት ከተካሄዱት ምልከታዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ በዚህ ወረዳ ከላይ ጋይንት በበለጠ፣ የገበያ ላይ ለቅሶ በከተማው መግቢያና መውጫ በሮች በደመቀ ሁኔታ እንደሚካሄድ ለመመልከት ተችሏል፡፡ በእነዚህ የከተማዋ መግቢያና መውጫ በሮች በየሳምንቱ ቅዳሜ የቀጠሮ ለቅሶ እንደሚካሄድና ልማዱ ከደርግ መንግሥት ወዲህ እየተስፋፋ እንደመጣም አቶ አበረ ክበበው (አባ.2. ቁ.10፣ ክፍ.1.1.2.2.፣ አን.1) ይገልጻሉ፡፡ ሟችን በቅርብ የሚገኙ ዘመድ ወዳጆቹ በዕለቱ ከቀበሩ በኋላ፣ ወቅቱ አመች ከሆነ እስከሁለት ሳምንት ከሚውለው ቅዳሜ ባንዱ ቀጠሮ ተይዞ፣ ለዘመዱ በቀብሩ ላይ መልዕክት ይተላለፋል፡፡ በቀጠሮው መሰረት የሟች ዘመድ ወዳጆች ከየአቅጣጫው ተሰባስበው፣ ለዚሁ በተከለለው ቦታ ተላቅሰው እንደሚለያዩ ለመመልከት ተችሏል፡፡

 

ምሥል አስራ ሶስት፣ በ25/09/04 ዓ.ም ፎገራ ወረዳ የገበያ ዳር የቀጠሮ ለቅሶን የሚያሳዩ ፎቶዎች (ፎቶ በለማ ንጋቱ)

ስለሆነም በፎገራ ወረዳ አንድ ሰው ሲሞት ባረፈበት ቦታና ቀን የዕለት ለቅሶ፣ በገበያ ደግሞ የግንኙት ለቅሶ ይደረግለታል፡፡ መረጃ አቀባዩ አቶ አበረ እንደገለጹት፣ የግንኙት ለቅሶው

የሚደረግበት ዋናው ምክንያት፣ በተለያዩ ምክንያቶች በዕለቱ ተገኝተው መቅበር ያልቻሉ ለቅሶ ደራሾች እየተንጠባጠቡ ወደሟች ቤት በመሄድ ሀዘንተኞቹን ሥራ እንዳያስፈቱና ለመስተንግዶም ወጭ እንዳያስወጡ ታስቦ ነው፡፡

በስማዳ ወረዳም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለአንድ ሰው የዕለት ለቅሶ ከተከናወነ በኂላ የቀጠሮ ለቅሶ ማካሄድ እየተዘወተረ መምጣቱን ብርሃን አበበ (አባ.2፣ ቁ.16፣ ክፍ.1.1.2.2.፣ አን.2) ያስረዳሉ፡፡ አንድ ሰው አመች ባልሆነ ጊዜና አልቃሽ ተቀጥሮ መድረስ በማይችልበት ጊዜ ሲሞት፣ በዕለቱ ይቀበርና ቀን ተቆርጦ የቀጠሮ ለቅሶ መደረጉ የማይቀር መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

የቀጠሮ ለቅሶ በዞኑ በተመሳሳይ ሁኔታ ይኑር እንጂ፣ ለቅሶው ከሚደረግበት ዓላማ፣ ቦታና ዝግጅት አኳያ ከወረዳ ወረዳ ልዩነቶች መኖራቸውን በቃለ መጠይቅና በምልከታ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በላይ ጋይንትና በፎገራ ወረዳዎች፣ የቀጠሮ ለቅሶ የሚዘጋጀው፣ በተለያዩ ምክንያቶች በዕለት ቀብር መድረስ ያልቻሉ የሟች ዘመድ ወዳጆች ተገኝተው ሀዘናቸውን እንዲገልጹ ለማድረግ ሲሆን፣ በስማዳ አልቃሽ ቀጥሮና ድግስ ደግሶ የለቅሶ ሥርዓቱን በደመቀ ሁኔታ ለማካሄድ ታስቦ እንደሆነ መረጃዎቹ ያሳያሉ፡፡ ለቅሶው ከሚካሄድበት ስፍራ አኳያ ደግሞ፣ በላይ ጋይንትና በፎገራ ወረዳዎች በገበያዎች ዳርቻ ሲካሄድ፣ በስማዳ ወረዳ ሟች በሚኖርበት አካባቢ በሚገኝ ቤተክርስቲያን ማርገጃ ይካሄዳል፡፡ በዚህ ወረዳ አንድ ሰው በሟች ለቅሶ ሳይገኝ ቀርቶ ከቀጠሮ ለቅሶ በፊት የሟችን የቅርብ ቤተሰብ ገበያ ላይ በድንገት ቢያገኝ እንኳ፣ በሟች መታጣት መጎዳቱን ገልጾ ያልፋል እንጂ ለቅሶ አይደርስም፡፡ (በዚህ መልኩ ጉዳቱን መግለጹ ለቅሶ እንደመድረስ አይቆጠርም)፡፡ ምክንያቱም በዚህ ወረዳ ሟች ከተቀበረበት ቤተክርስቲያን ወይም ከተጎጂው ቤት ውጭ ገበያ ላይ ለቅሶ መድረስ ተጎጂውን እንደመናቅ ስለሚቆጠር በጣም ነውር መሆኑን አቶ ደጀን አመኑ (አባ.2፣ ቁ17. ክፍ.1.1.መ.፣ አን.1-4) ይገልጻሉ፡፡

አቶ አያሌው ተሾመ (አባ.2.፣ ቁ.22፣ ክፍ.1.1.መ፣ አን.1-2) እንደሚገልጹትም፣ በስማዳ ወረዳ አንድ ለሀዘንተኞቹ ቅርበት ያለው ሰው በዕለት ለቅሶ ባይገኝ፣ አብዛኛውን ጊዜ ከቀጠሮው ቀን በፊት፣ አልፎ አልፎ በቀጠሮው ቀን፣ በዚህም ሳይሳካለት ቢቀር፣ በጣም አልፎ አልፎ ከቀጠሮ ለቅሶ በኂላ፣ በጠዋት ወደተጎጂው ቤት በመሄድ ለቅሶ የመድረስ ልማድ አለ፡፡ እ.ኤ.አ. በ10/05/06 በተካሄደው የመስክ ምልከታ፣ እናቷ ከአንድ ወር በፊት ሌላ ቦታ ሙታባት ቀብራ ከተመለሰች ልጅ ቤት፣ በጠዋት ለቅሶ ደራሽ መጥቶ ሲላቀሱ ለማየትና የልማዱን መኖር

ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ለቅሶ በቤት መድረስ በፋርጣ ወረዳም የተለመደ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

የለቅሶ ሥርዓቱ በገበያ ዳርቻ በሚካሄድባቸው በላይ ጋይንትና በፎገራ ወረዳዎች መካከል የለቅሶ ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ አቶ ደጀን አመኑ (አባ.2.፣ ቁ.17፣ ክፍ.1.1.መ.፣ አን.5) እንደሚገልጹት፣ ረፋድ ላይ ሀዘንተኞቹ ከገበያው ዳርቻ መስመር ሰርተው እንደሚቀመጡና፣ ደራሹ አንድም ሁለትም እየሆነ ወደተቀመጡበት በመሄድ ከፊታቸው ጎንበስ ብሎ በጋቢው ጫፍ ግራና ቀኝ ፊቱን ነካ ነካ አድርጎ አብሮ በመቀመጥ መጎዳታቸውን ገልጾ ከትንሽ ቆይታ በኋላ፣ ‹‹እግዚአብሔር ያጥናችሁ›› እያላቸው እንደሚሄድ ያስረዳሉ፡፡ በዚህ ወረዳ በቀጠሮ ለቅሶ ምንም አይነት የለቅሶ ቃል-ግጥም እንደማይቀርብም ይገልጻሉ፡፡ እ.ኢ.አ. በ16/06/05 በሁለት የገበያ ዳር የቀጠሮ ለቅሶዎች ላይ በተካሄደው ምልከታም፣ ይህንኑ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በፎገራ ወረዳ ግን እ.ኢ.አ በ25/09/04 በዋለው በአቶ ደባልቄ ገበየሁ የቀጠሮ ለቅሶ በተካሄደው ምልከታ፣ ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት አካባቢ ሲሆን ሀዘንተኞቹ የሀዘን ልብሳቸውን ለብሰው በገበያው ዳርቻ ማልቀስ ጀመሩ፡፡ ሰው እየመጣ መገናኘት ሲጀምር ሀዘንተኞቹ እንደዕለት ለቅሶ ወዲያ ወዲህ እየሮጡ፣ እጆቻቸውን እያርገበገቡና አልፎ አልፎ የሟችን ስም፣ ብዙ ጊዜ ግን ዝምድናዊ ግንኙነታቸውን እያነሱ፣ ‹‹አባታለም፣ አባታለም እያሉ በመጮህ ያለቅሱ ጀመር፡፡ የለቀስተኛው ቁጥር እየጨመረ ሲመጣ ክብ ሰርተው ለቀስተኞቹ ከውስጥ ገብተው እየዞሩ ለቅሶው በወየታ፣ በሙሾና በፉከራ ቃል-ግጥሞች ክወና ታጅቦ በደመቀ ሁኔታ ተካሄደ፡፡



ምሥል አስራ አራት፣ በ25/09/04 ዓ.ም በዋለው በአቶ ደባልቄ ገበየሁ የቀጠሮ ለቅሶ ቤተሰቦቻቸው ለቅሶውን ሲጀምሩ (ፎቶ በለማ ንጋቱ)

በዚህ ወረዳ የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ክወና ከዕለት ለቅሶ ባልተለየ መንገድ እንደሚከወን በተካሄዱት ምልከታዎች ለማረጋገጥ ተችሏል። ዋንጫ የያዙ ወየ ባዮች ሀዘንተኞቹን ከከበበው ለቀስተኛ በስተውስጥ በኩል በረድፍ ቆመው፣ እየተቀባበሉ ወየ ይላሉ። በፋርጣና በደብረታቦር ወረዳዎች ከዕለት ለቅሶ ተመሳሳይ በሆነ አሰላለፍ፣ የወየታ ቃል-ግጥም በቆሙበት ቦታ ሳይንቀሳቀሱ ሲያዜሙ፣ በፎገራ በእያንዳንዱ ሐረግ ወየ ባዮቹ ምት ጠብቀው አንድ እርምጃ ወደቀኝ በመሄድ ከክቡ ውስጥ ስልት ጠብቀው እየተንቀሳቀሱ ወየ ይላሉ።

በዚህ ሁኔታ የወየታ ቃል-ግጥሙ በቅብብሎሽ እየተከወነ ሲለቀስ ካረፈደ በኋላ፣ የሟች ዕድሜ ከ20 ዓመት በላይ ከሆነ፣ ሙሾም ይወረዳል። በአቶ ደባልቄ እ.ኢ.አ. (በ25/09/04) በተካሄደ የቀጠሮ ለቅሶ 4:30 አካባቢ አምስት ሰዎች በአንድ በኩል ትከሻ ለትሻ ገጥመው ሲቆሙ፣ በተመሳሳይ ሁኔታ ሌሎች አምስት ሰዎች መስመር ሰርተው ፊት ለፊት ቆመው ሙሾ ማውረድ ጀመሩ። የሙሾ አውራጆቹ አለባበስና አሰላለፍ በደብረታቦርና ፋርጣ ወረዳዎች ካለው አለባበስና አሰላለፍ ተመሳሳይ ሲሆን፣ እንቅስቃሴ ላይ ግን መጠነኛ ልዩነቶች ይታያሉ። በፎገራ ሙሾ መሪውም ሆነ አውራጅ አጃቢዎቹ፣ ‹‹ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ ዋየ›› የሚለውን የሙሾ አይነት ሲያወርዱ፣ እንደደብረ ታቦርና ፋርጣ ወረዳዎቹ የሙሾ ክወና የሚያረግዱት ግራ ቀኝ እየዘመሙ ሳይሆን፣ ፊት ኋላ እየተናጡ ነው። ክብ ከሰራው ለቀስተኛ መሀል ሙሾ ሲወረድ፣ ሀዘንተኞቹ ከፈካሪዎችና ከአቅራሪዎች ጋር ተቀላቅለው ሙሾውን ክብ ሰርቶ ይቀበል የነበረውን ለቀስተኛ ሲዞሩ ተስተውለዋል።

በዚህ መንገድ የተወሰነ ሙሾ እንደተወጣ፣ ከሀዘንተኞቹ ጋር ተቀላቅለው በውጭ ከሚዞሩት ግለሰቦች መካከል አንዱ አቅራራ። ሌሎቹ እየተቀበሉት ሶስቴ ክቡን እንደዞሩ በአንድ በኩል ጥሰው ወደውስጥ ገቡ። ሙሾ አውራጆቹ አቋርጠው ሲወጡ አቅራሪዎቹ በሁለት ተከፍለው ፊት ለፊት እየተያዩ ከአንደኛው ምድብ አንድ ሰው እያቅራራ ሌሎቹ እየተቀበሉ ትንሽ እንደቆዩ፣ ፉከራ ተጀመረ። ፎካሪው በርከክ ሲል ተቀባዮቹም እየተንበረከኩ፣ ተነስቶ ቦታ ሲቀይር አብረውት ቦታ እየቀየሩ፣ የፉከራ ሥርዓቱ ቀጠለ። አንዱ ሲደክም አቅራሪ እየገባ በማሳረፍ ለሌላው ፎካሪ እየሰጠ፣ አንዱን ፎካሪ ሲደናገረው ሌላው ፎካሪ እየቀማ፣ በለቀስተኛው መሃል ባለች ጠባብ ቦታ ወደምስራቅ ሂደው ወደምዕራብ እየተመለሱ ሲፎክሩ ከቆዩ በኋላ፣ ሽማግሌዎች፣ ‹‹በቃ›› ብለው ክወናውን አስቆሙ። በዝምድና ምክንያት ከለቅሶው

የተገኙ ቄስ፣ ለቀስተኛውን መርቀውና አቡነ ዘበሰማያት ሰጥተው 5:30 አካባቢ ለቅሶው ተጠናቀቀ፡፡

በዚህ የቀጠሮ ለቀሶ በሀዘንተኞቹና በለቀስተኛው ግንኙት ዙሪያ በዕለት ለቅሶ ከሚደረገው መጠነኛ ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ በዕለት ለቅሶ ከቀብር መልስ የሚመጡ ለቀስተኞች ካልሆኑ፣ ሀዘንተኞቹን የሚገናኙት ሰልፍ ይዘው ነው፡፡ በቀጠሮ ለቅሶው አልፎ አልፎ ሰልፍ ይዘው ሲገናኙ ቢታይም፣ ባብዛኛው ግን ደራሹ ክቡን ጥሶ በመግባት ከሀዘንተኞቹ የሚያውቃቸውን ሰዎች ከሚዞሩበት ልብሳቸውን ይዞ በማስቆም፣ ‹‹አየ እእ›› ብሎ በማንጎራጎር ትከሻቸውን በመንካት ይገናኛል፡፡

በቀጠሮ ለቅሶ ዙሪያ በወረዳዎቹ ከሚታዩት ልዩነቶች ውስጥ፣ በምስል (ሟችን አስመስሎ በመስራት) እና ያለምስል ማስለቀስ እንደሚገኝበት በምልከታ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ በስማዳ ወረዳ ሟችን ከቅልና ከእንጨት አስመስሎ በመስራትና ከማህበራዊ ደረጃው ወይም ከሙያው አኳያ ይጠቀምባቸው የነበሩ አልባሳቱን በማልበስ፣ ከድንኳኑ ፊት ለፊት አልጋ ላይ በማስቀመጥ ወይም በማቆም ሀዘንተኞቹ እሱን እያዩ እንዲያለቅሱ ይደረጋል፡፡ በላይ ጋይንትና በፎገራ ወረዳዎች በሚካሄድ የቀጠሮ ለቅሶ ምስል ማዘጋጀት የተለመደ አይደለም፡፡





ምስል አስራ አምስት፣ ስማዳ ወረዳ በቀጠሮ ለቅሶ ሟቾቹን በማስመሰል ተሰርተው የቀረቡ ማስለቀሻ ምስሎች (ፎቶ ከስማዳ ባህልና ቱሪዝምና ከላይ ጋይንት የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤቶች የተገኘ)

በምስል ማስለቀስ ያስፈለገው የቀጠሮ ለቀሶው ለዝግጅት ሲባል ሟች ከተቀበረ ከሃያ ቀናትና አንዳንዴም ከወራት በኋላ ስለሚከናወን፣ የሀዘንተኞቹ ትዝታ እንዳይደበዝዝና ከልብ እንዲያለቅሱ ስሜታቸውን ለመንካት ታስቦ እንደሆነ ከመረጃ አቀባዮቹ መካከል አቶ ሀይሌ ዘውዴ (አባ.2.፣ ቁ.37.፣ ክፍ.1.1.2.3.፣ አን.2) ያስረዳሉ። አቶ ደጀን አመኑም (አባ.2፣ ቁ.17፣ ክፍ.1.1.2.3.፣ አን.1-3)፣ ምስሉ... ሰውየው በአደባባይ አዘውትሮ የሚለብሰውን ልብስ፣ ባርኔጣ፣ ይለብሳል። ምንም ቀጠሮው ቢሰነብት ሰው ያንን በርቀት ሲያየው ሰውየውን አስታውሶ ያነባል።› በማለት ይገልጻሉ።

በላይ ጋይንትና በፎገራ ወረዳዎች ካህናት በቀጠሮ ለቅሶ ሥርዓት ፍትሀት የማያከናውኑ ሲሆን፣ በስማዳ ወረዳ በቀጠሮ ለቅሶ ቀሳውስት የቤተክርስቲያን ጥላ ዘርግተው በመያዝ፣ ከበሮ እየመቱ፣ ቅኔ እየዘረፉ፣ በሽብሸባና በጸሎት ይሳተፋሉ።

በደብረ ታቦርና በፋርጣ ወረዳዎች፣ የቀጠሮ ለቅሶ ቀደም ሲል በተለይ በክረምት ወራትና በችግር ዘመን፣ ትልቅ ሰው ሲሞት፣ አመች ጊዜ ተፈልጎ ተቀጥሮ ይለቀስ እንደነበርና በአሁኑ ሰዓት በኑሮ ውድነት ምክንያት እየቀረ እንደሆነ የቡድን ውይይቱ ተሳታፊዎች ይገልጻሉ። በእነዚህ ወረዳዎች በአሁኑ ሰዓት የቀጠሮ ለቅሶ የሚደረገው፣ ወገን ተጠርቶ በማይደርስበት አስቸጋሪ ሰዓት ሞተው በዕለቱ ለተቀበሩና በውሃ ተወስደው ሬሳቸው በፍለጋ ሳይገኝ ለቀረ ግለሰቦች መሆኑንም፣ በማከል ይገልጻሉ። እ.ኢ.አ. በ29/09/04 በደብረታቦር ዙሪያ ወረዳ ከታካሄደው አንድ የቀጠሮ ለቅሶ ክወና ለመረዳት እንደተቻለው ግን፣ ከትውልድ ቦታቸው ውጭ ለሞቱና ወገን ላላቸው ሰዎችም የቀጠሮ ለቅሶ የሚካሄድበት አጋጣሚ ይኖራል። ለምሳሌ የቀጠሮ ለቅሶው የተካሄደላቸው ሟች፣ ከአካባቢያቸው ርቀው (ወለጋ) ኖረው አርጅተው ሲሞቱ በሰጡት ኑዛዜ መሰረት፣ ልጆቻቸው የአባታቸውን የትውልድ አካባቢና ዘመዶቻቸውን ፈልገው ካገኙ በኋላ፣ የተካሄደ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል። ለቅሶው ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ማርገጃ ላይ ከመከናወኑና ሬሳ ካለመኖሩ በስተቀር፣ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች እንደዕለት ለቅሶ በሥርዓት መከናወናቸውንም ለመመልከት ተችሏል። የመጨረሻው ‹‹ዋ ተለያየን›› ሙሾ እንደተከወነ፣ ቀሳውስት ልብሰ ተክህኗቸውን ለብሰውና የቤተክርስቲያን ጥላ ዘርግተው ከወጡ በኋላ፣ በመስመር ቁመው ጸሎት ሲያደርጉ ሳይሆን፣ የለቅሶውን በዚያ ቀን (በባለ እግዚአብሔር)፣ መቀጠር ሲያወግዙ ተስተውለዋል። በመጨረሻም፣ አቡነዘበሰማያት ሰጥተው የሟችን ነፍስ ይማር ብለው ሲያሰናብቱ እንጅ፣ የፍትሃት ጸሎት ሲያደርጉ አልታዩም።

በቀጠሮ ለቅሶ ከምስል ዝግጅትና የቀሳውስት ፍትሃት በተጨማሪ፣ በእዝን አቀራረብም በወረዳዎች መካከል ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ በላይ ጋይንት የሟች ቤተሰቦች እስከመጨረሻው ከነሱ ጋር የቆዩትን ጥቂት ሰዎች ወደጠላ ቤት ወስደው ይጋብዟቸዋል፡፡ የሟች ቤተሰቦች ሀብት ያላቸው ከሆኑ፣ ከከተማው ጠላ አስጠምቀው፣ ለቅሶ ደራሹን አጠጥተው የሚሸኙበት አጋጣሚም ይኖራል፡፡ ከለቀስተኛው መዋጮ አይጠበቅም፡፡ በፎገራም ወረዳ ግን፣ የሟች ቤተሰቦች ወረታ ከተማ ከሚገኙ ጠላ ጠማቂዎች ከአንዷ ጋር ውል በመውሰድ፣ ጠላ እንድትጠምቅና፣ ንፍሮ እንድታዘጋጅ ያደርጋሉ፡፡ ለቀስተኞቹም ከሶስት ብር ጀምሮ በማዋጣት፣ ስማቸውን እያስመዘገቡ የተዘጋጀውን ንፍሮና ጠላ ቀምሰው እየተሰናበቱ ወደየጉዳያቸው ይሄዳሉ፡፡ በስማዳ ወረዳ ደግሞ፣ የሟች ቤተሰቦች ለአካባቢው ነዋሪና ለዘመድ አዝማዱ ሶስት ሶስት ብርጭቆ ጤፍ አፍስሰው*፣ ከቤታቸውም ጋግረው፣ አርደውና ጠምቀው፣ ለለቀስተኛው ዳስ ሰርተው ወይም ድንኳን ተክለው፣ እዚያ ውስጥ በማሳረፍ አቆልቋይ (ከፍተኛ ድግስ በሚደገስ ጊዜ አቡጀዲ ወይም የኮባ ቅጠል በረጅሙ በመስመር ተዘርግቶ፣ በሁለት አቅጣጫ መስመሩን ተከትለው ለሚቀመጡ ሰዎች ምግብ የሚቀርብበት) ጥለው ይጋብዛሉ፡፡ ከለቀስተኛው መዋጮ የማይጠበቅ ሲሆን፣ ሌሊቱን ሁሉ እየተባለና እየተጠጣ ይታደራል፡፡ የአዳር ወይም የቀን ጠላ ያላጠጣ እንደሚናቅም መረጃ አቀባዮቹ ይገልጻሉ፡፡ በደብታቦርና ፋርጣ ወረዳዎች ግን፣ የእድር አባላት መደበኛ መዋጮ መፈጸም ይጠበቅባቸዋል፡፡ የዕዝን መስተንግዶውም ከዕለት ለቅሶ የተለየ አይደለም፡፡

የቀጠሮ ለቅሶ በሌሎች የአፍሪካም ሆነ የኢትዮጵያ ማሕበረሰቦች የሚከናወን የተለመደ የለቅሶ ሥርዓት መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ የዮሩባ ማሕበረሰብ አባላት፣ አዳኞች ሲሞቱ አብዛኛውን ጊዜ በሰባተኛው ቀን፣ የእድር አባላቱ ተሰባስበው ሟች ጓደኛቸውን በቀረርቶና በፉከራ የመሰናበት ልማድ እንዳላቸው Babalola (1966፣15-16) ያስረዳሉ፡፡ ነጋ (2002) እንደሚገልጹት፣ በትግራይ ማሕበረሰብ የቀጠሮ ለቅሶ ከፍተኛ ማሕበራዊ ደረጃ ያላቸው ሰዎች ሌላ አካባቢ ሞተው በችኮላ ሲቀበሩ፣ የአኀበር ለቅሶ ይኖራል፡፡ ይህን የለቅሶ አይነት የመሳፍንቱ ቤተሰቦች ማሕበራዊ ደረጃቸውን ለማሳየት ይጠቀሙበት እንደነበርም ይገልጻሉ፡፡ የቀብር

---

* በርካታ ተጋባዥ የሚገኝባቸው እንደሰርግና የቀጠሮ ለቅሶ አይነት ድግሶች ሲኖሩ፣ ደጋሾቹ በአንድ ቋሚ መለኪያ በመስፈር በድግሱ ለሚሳተፉ ዘመዶቻቸው፣ ወዳጆቻቸውና የአካባቢው ነዋሪዎች ጋግረው እንዲመጡ ጤፍ የሚሰጡበት ልማድ ነው፡፡ ልማዱ እንዳሁኑ ዘመናዊ ወፍጮ ባልነበረበት ጊዜ ለመተጋገዝ ተብሎ ሳይጀመር እንዳልቀረ ቢታመንም፣ አሁንም በማብሰሉ በኩል ለመረዳዳት ስለሚያስችል ተግባራዊ እየተደረገ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ሥርዓቱ በመደበኛው መንገድ ከተካሄደ በኋላ እንኳ፣ የአጎበር ለቅሶ በርካታ ሕዝብ የሚሰበሰብበትንና ሩቅ አገር የሚገኙ ዘመዶቻቸው በለቅሶው ላይ የሚገኙበትን እድል ስለሚፈጥር፣ እንደሚያካሂዱት ይገልጻሉ።

አቶ ነጋ የአጎበር (የቀጠሮ) ለቅሶ በቤተክርስቲያን ሳይሆን፣ አማካይ በሆነ ቦታ እንደሚካሄድና በስማዳ ወረዳ በሚች ምስል እንደሚለቀሰው፣ በትግራይም በሬሳ ሳጥን እንደሚለቀስ ያስረዳሉ። ቀሳውስት የሬሳ ሳጥኑን ከበው የፍትሃት ጸሎት እንደሚያካሂዱና፣ አገልጋዮችም የሚችን የጦር መሳሪዎች በመያዝ በሬሳ ሳጥኑ ዙሪያ እንደሚቆሙ ይገልጻሉ። በለቀስተኛው ፊት አገልጋዮች በሰልፍ በግምጃ የተሸፈነ የጠጅ ገንቦ፣ ጠጅ በብርሌ፣ ሥጋና ቢለዋ፣ ሞሶብና በቀይ ግምጃ የተሸፈኑ ድስቶችን ተሸክመው፣ እንዲሁም የተሸለሙ ፈረሶችንና በቅሎዎችን እየሳቡ እንደሚያልፉና፣ ይህም የሚችን የግብር ማብላት ሥርዓት ለማሳየት ተብሎ እንደሚከናወን ያስረዳሉ። ከዚህም በተጨማሪ፣ የሙሾ ቃል-ግጥም ክወና እንዳለም ይገልጻሉ። ይህም በVernon (1970) ሞት፣ እንደማሕበራዊ ክብር ማግኛ እንደሚታይ ከገለጹት ጋር ይመሳሰላል። የቀጠሮ ለቅሶ ሥርዓት ይህን ሲመስል፣ የመርዶ ለቅሶ ዓለማዊ ሥርዓት ምን እንደሚመስል ደግሞ ቀጥሎ ቀርቧል።

#### 4.1.2.3. በመርዶ ለቅሶ የሚከናወኑ ዓለማዊ የለቅሶ ሥርዓቶች ክወና

የመርዶ ለቅሶ በዞኑ ከሚካሄዱት የለቅሶ አይነቶች አንዱ እንደሆነ ቀደም ሲል ተገልጿል። የመርዶ ለቅሶ፣ አንድ ሰው በሥራ ምክንያት ከትውልድ ቦታው ርቆ በሚኖርበት አካባቢ ሞቶ በዚያው ከተቀበረ በኋላ፣ ቤተሰብ እርሙን እንዲያወጣ ተቆርቋሪ የሆነ የሚች ጓደኛ ወይም ዘመድ የሚችን ማረፍ ለቅርብ ቤተሰቦቹ ይፋ የሚያደርግበት የለቅሶ አይነት ነው። አቶ አራጋው ታረቀኝ (አባ.2፣ ቁ.32፣ ክፍ.1.1.3.2፣ አን.1-7) እንደሚያስረዱት፣ የመርዶው ሥርዓት ለቤተሰብ በሁለት መንገድ እንዲደርስ ሊደረግ ይችላል። አንደኛው መንገድ ሚችን ከቀበረ ተቆርቋሪ መካከል ወደቤተሰቡ በመሄድ፣ ከዚህ በፊት እውቂያ ካለው ለመጠየቅ የሄደ በመምሰል በቤት ያድርና፣ ከንጋቱ አስራ አንድ ሰዓት አካባቢ ቤተሰቡን ቀስቅሶ የሚችን ስም እየጠራ በማልቀስ የሚያረዳበት ነው። ከዚህ በፊት ከሚች ቤተሰቦች ጋር እውቂያ የሌለው ከሆነ፣ ቅርበት ያለው ሰው አፈላልጎ ሁኔታዎችን በማመቻቸት፣ በጠዋት ተነስተው ወደሚች ቤተሰብ ከዚያ ሰው ጋር በመሄድ ያረዳሉ። ሁለተኛው የማርጃ መንገድ፣ ደብዳቤ በመጻፍ

የሚከናወን ነው። የሟች ጓደኛ ወይም ዘመድ፣ ለቤተሰቦቹ ደብዳቤ በመጻፍ ሟች መቼ እንዳረፈና የት እንደተቀበረ ያረዳል። ደብዳቤው ለቤተሰብ በቀጥታ ደርሶ በማንኛውም ሰዓት ሲነበብ ሊረዱ ይችላሉ። አብዛኛውን ጊዜ ግን አንባቢው በምስጢር ይዞ፣ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ተደርጎ፣ የማርዳቱ ሥራ በጠዋት ይከናወናል። በጦር ሜዳ የሞቱ ወታደሮች መርዶ በዚህ መንገድ ለቤተሰብ ይደርሳል።

በመርዶ ለቅሶ የሚከናወነው ሥርዓት፣ እንደሟችና ተረጂዎች ማሕበራዊ ደረጃና የገንዘብ አቅም ይወሰናል። ሟች አገሩን ከመልቀቁ በፊት በአካባቢው እውቅና የነበረውና ማሕበራዊ ደረጃው ከፍ ያለ ከሆነ፣ ወይም ሟች ለረዥም ጊዜ ከአካባቢው በመራቁ እውቅና ባይኖረውም፣ የተረጂዎቹ ማሕበራዊ ደረጃ ከፍ ያለ ከሆነ፣ የለቅሶ ሥርዓቱ በሁለት መንገድ ሊካሄድ ይችላል። የመጀመሪያው በመርዶው ቀን እንደዕለት ለቅሶ ተለፎ የሚለቀስበት ሲሆን፣ ሬሳ ካለመኖሩ በስተቀር፣ የሀዘን ድባቡ ከዕለት ለቅሶ ብዙም አይለይም። ምክንያቱም የሟች ቤተሰቦችና ዘመዶች የሟችን ማረፍ እንደሰሙ የሚፈጠርባቸው ድንጋጤና ሀዘን ትኩስ ስለሆነ፣ የሀዘን አገላለጻቸውም ሆነ አለቃቀሳቸው እንደዕለት ለቅሶ በመሆኑ ነው። በዚህ ለቅሶ ማርገጃ ላይ ወይም የተመረጠ አማካይ ቦታ ላይ ለቀስተኛው ተሰባስቦ፣ የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ እንደዕለት ለቅሶ በደመቀ ሁኔታ እየተከወኑ ይለቀሳል።

የሟችም ሆነ የተረጂዎቹ ማሕበራዊ ደረጃ ዝቅተኛ ከሆነ ወይም የገንዘብ አቅም ከሌላቸው፣ ለቅሶው በተረጂዎቹ ቤት በጠዋት ይጠናቀቃል። ተረጂዎቹ ዕድር ካላቸውና ለሟች ያላቸው ቀረቤታ በእድሩ ደንብ እርዳታ የሚያስገኝላቸው ከሆነ፣ ለቅሶው ይለፈፋል። የዕድር ድንኳንም ይተከላል። ለቀስተኛው ወደተረጂዎቹ ቤት በመሄድ እየደረሰ ይመለሳል። በቡድን ውይይት ከተሳተፉት ውስጥ አቶ አለምነው አሉላ (አባ.2፣ ቁ.23፣ 1.1.3.2.፣ አን.1) እንደሚያስረዱት፣ በደብረ ታቦር ወረዳ የመርዶ ለቅሶ ቅዳሜ ጠዋት ብቻ እንዲደረግ በመወሰኑ፣ ተረጂዎቹ በዚሁ ቀን ከጠዋቱ አስራ ሁለት እስከአንድ ሰዓት ተኩል አካባቢ በማርገጃ ተገኝተው ለቀስተኛውን ይቀበላሉ። ከዚያ ወደቤት ይመለሱና ሀዘናቸውን በድንኳን ውስጥ ይገልጻሉ።

መረጃ አቀባዮቹ ቀደም ባለው ጊዜ የመርዶ ለቅሶም በደመቀ ሁኔታ የሙሾ ቃል-ግጥሞች እየተከወኑ ይካሄድ እንደነበርና፣ በአሁኑ ሰዓት እየቀረ እንደሆነ ይገልጻሉ። በወ/ሪት ዘውዴ ከበደ እና በእሙሃይ አስናቀች የማታ (በ11/09/04) በዋሉ የመርዶ ለቅሶዎች ላይ በተካሄዱት ምልከታዎች፣ ሀዘንተኞቹ ለቀስተኛ ሲመጣ ተነስተው አንዳንዴ በቀኝ እጆቻቸው ትከሻ ለትከሻ

በመነካካት፣ አንዳንዴ፣ ፊት ለፊት አንገታቸውን ደፍተው በመቆም፣ እየተቀበሉ ይቀመጣሉ፡፡ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ክወናም ሆነ እየዞሩ ማልቀስ አይታይም፡፡ የሀዘን መግለጫ አለባበሳቸው ግን፣ በዕለት ለቅሶ ከሚለበሰው የተለየ አይደለም፡፡ እስከሁለት ሰዓት በማርገጃው ለቀስተኛውን በዚህ መንገድ ሲያስተናግዱ ቆይተው ወደየቤታው ሲመለሱ፣ ከቤተዘመድ ውጭ ለቀስተኛ አልተከተላቸውም፡፡ ከእሙሃይ አስናቀች ወንድም ግቢ በተተከለው ድንኳን፣ ተረኛ የእድር አባላት ለሀዘንተኞቹ እህል ውሃ ሲያቀርቡ ተስተውሏል፡፡

ተረጂዎቹ ለቅሶው እንዲለፈፍና ድንኳን ተጥሎ እንዲለቀስ የማይፈልጉ ከሆነ፣ የለቅሶ ሥርዓቱ በተነገረበት ጠዋት በተረጂዎቹ ቤት ይጠናቀቃል፡፡ በለቅሶው ላይ የሚሳተፉትም የቅርብ ጎረቤቶች ብቻ ይሆናሉ፡፡ እድሩ ለተረጂዎቹ ገንዘብ በጥሬ ይከፍላቸዋል፡፡ እንዲህ የሚደረገው፣ ሀዘንተኞቹ ማህበራዊ ደረጃቸው ዝቅተኛ ሲሆን ወይም የገንዘብ አቅም ሳይኖራቸው ሲቀር ወይም በቀጠሮ የማስለቀስ እቅድ ሲኖራቸው መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በዞኑ የሚካሄደው የመርዶ ለቅሶ ድምቀት፣ እንደዕለትና የቀጠሮ ለቅሶዎች በሟች ማሕበራዊ ደረጃ፣ ሀብትና ወገን የሚወሰን ቢሆንም፣ እንደሁለቱ ለቅሶዎች በለቀስተኞች ትኩረት እንደማይሰጠው ከመረጃ አቀባዮቹና ከምልከታ መረጃዎቹ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ሟች በጦር ሜዳ ከሞተ፣ አካባቢውን ከመልቀቁ በፊት ወይም በኖረበት አካባቢ ለፉከራ የሚያበቃ ሥራ ካከናወነና ተረጂ ወገኖቹ ጠንካሮች ከሆኑ፣ የለቅሶ ሥርዓቱ በቀረርቶና በፉከራ በደመቀ ሁኔታ ይካሄዳል፡፡ የወየታና የሙሾ ቃል-ግጥሞችም ይከወናሉ፡፡ ከዚህ ውጭ ግን፣ በመርዶ ለቅሶ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ክወና አይካሄድም፡፡ የሀዘን ድባቡ ግን ለቤተሰቦቹ አዲስ ስለሆነ፣ ከቀጠሮ ለቅሶ ከበድ ይላል፡፡ የሀዘን አገላለጹም ከላይ እንደተገለጸው፣ ከዕለት ለቅሶ የተለየ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ ይህ ጥናት በተካሄደበት በደቡብ ጎንደር ዞን፣ በሦስቱ የለቅሶ አይነቶች የሚፈጸመው የቀብር ሥርዓት ክንውን፣ ከሟች መሸኛነቱና ከሀዘን መጋሪያነቱ ባሻገር፣ በሰፊው ሲታይ የማሕበረሰቡን፣ ወረድ ሲል ደግሞ የሥጋ ዝምድና፣ የጋብቻ ትስስርና በተለያዩ የመቀራረቢያ መተሳሰሪያዎች፣ (ጓደኝነት፣ አበልጅነት፣ ማሕበርተኛነት ወዘተ.) የሚገናኙ የማሕበረሰብ ክፍሎችን ትስስር ማጠናከሪያና እንዳይላላ ማጥበቂያ ገመድ ተደርጎ ሊታይ ይችላል፡፡

ስዚህ ደግሞ በአገር እያሉና አልጋ ላይ ሳይውሉ በአንድ ሰው ለቅሶ ላይ እንዳለመገኘት፣ ለቀሪው የሚያሳፍር፣ ለተጎጂው የሚያስቀይምና ለብድር ምለሳ የሚያነሳሳ ነገር አለመኖሩ፣ የለቅሶ ሥርዓት የሚጫወተውን የማሕበራዊ አስተሳሳሪነት ሚና ማሳያ ይሆናል፡፡ ሞት ሲከሰት የተጣላ ያለ ይቅር አባባይ፣ በሌላው ማሕበራዊ ግንኙነቱ ቸልተኛ የሚባለው ያለ ዋዛ ፈዛዛ፣ በንቃት የሚሳተፈውና ሁሉም የየስራ ድርሻውን ለመወጣት ብቻ ሳይሆን ሌሎቹም እንዲወጡ የሚረባረበው፣ ሟችን በክብር ለመሸኘት ብቻ ሳይሆን፣ ነግለኔን በማሰብ ነው ቢባል ያስኬዳል፡፡ ሞት መቼ እንደሚመጣ ያለመታወቁና ለማንኛውም ፍጡር የማይቀር መሆኑ፣ ቋሚዎች ለሟች ብቻ ሳይሆን ከእርሱ ጋር በአንድ የእጣ ፈንታ ገመድ መቆራኘታቸውን እያሰቡና ራሳቸውን በእሱ ቦታ እያዩ፣ ለመተጋገዝ እንዲተጉና ለሰው ልጅ ከንቱነት (ለራሳቸው ጭምር) እንዲያለቅሱ ሰው ሁኖ የመገኘት የወል መተሳሰሪያ ገመድ ግድ የሚል ይመስላል፡፡

ሞት የሰው ልጅ የጋራ እጣፈንታ መሆኑ፣ ሲከሰት ሟችን በባህሉ መሰረት በመሸኘትና ሀዘንተኞችንም በዚያው መልኩ በማስተዛዘን ከሚፈጥረው መተባበር ባሻገር፣ የቋሚን አጠቃላይ ስነምግባር በማረቅና ሕይወትን መስመር በማስያዝ በኩልም የጎላ ሚና ይጫወታል ለማለት ይቻላል፡፡ ሀይለኞች በደካሞች፣ ባለጸጎች በድሆች፣ ጊዜ ያነሳቸው ጊዜ በጣላቸው ላይ ጫና የማሳደር አቅማቸውን ያለገደብ እንዳይጠቀሙ፣ ከወቅትና ሁኔታ ጋር እንዲመቻቹ እየተደረጉ ከሚረቀቁ ህጎች ይልቅ፣ የሞት መኖር የጎላውን ድርሻ የሚጫወት ይመስላል፡፡ ምክንቱያም እንደየሁኔታዎቹ ለአድሎ ከሚጋለጠው የሰው ልጅ ሕግ ይልቅ፣ ሞት ፈጥኖም ይሁን ዘግይቶ ያለምንም አድሎ፣ ሀይለኛውን ከደካማው፣ ባለጸጋውን ከድሃው፣ ጊዜ ያነሳውን ጊዜ ከጣለው፣ ሳይለይ በእያንዳንዱ ላይ የመከሰቱ አይቀሬነት፣ የሁሉንም ነገር ከንቱነትና የተሸናፊነትን ስሜት በመፍጠር፣ በሟች የቀብር ሥርዓት ላይ በሚገኙት ተሳታፊዎች ልብ ውስጥ የሚፈጥረው ስብራት፣ ተዛዝኖና ተረዳድቶ ለመኖር የሚያስችሉ መልካም ባህርያት እንዲዳብሩ ያደርጋል፡፡

ሟችን እየሸኙ ስለሱና ስለራስ ብቻ ሳይሆን፣ ስለሰው ከንቱነት እያሰቡ ማልቀሱም ይሁን መተባበሩ፣ የለቅሶ ሥርዓቱ ከርስበርስ ግንኙነት ማጠናከሪያነት ባለፈ፣ የማሕበራዊ ልምድ መቅሰሚያነት ሚና እንዲኖረው አድርጎታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ የዘር ሀረግ ግንኙነትን የማጠናከር ሚና እንደሚጫወት ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተለያየ ምክንያት ተራርቀው የሚኖሩ

የሥጋ ዝምድና ያላቸው የአካባቢው ነዋሪዎች፣ በሀዘን ጊዜ ሳይሰሙ ቀርተው እርማቸውን እንዳይበሉ በሚል እምነት፣ ሽማግሌዎች ዘር እየቆጠሩ በሩቅ ለሚገኙት ሁሉ ጥና ጠሪ ወይም መልዕክተኛ በመላክ መርዶው እንዲደርሳቸው ስለሚያደርጉ፣ ቤተዘመድ ይሰባሰባል። ከለቅሶ በኂላ ከየአቅጫው የመጡት ቤተዘመዶች ተሰብስበው በታላላቆቹ አስተባባሪነት ዘር እየቆጠሩ ይተዋወቃሉ። እውቂያው ኖሯቸው ለረዥም ጊዜ ሳይገናኙ የኖሩትም፣ እየተሳሳሙ ሲጠያየቁና ሲወያዩ ለመመልከት ተችሏል። ይህም የቀብር ሥርዓት አጋጣሚ ለተጠኚው ማህበረሰብ፣ ሀዘንን መጋሪያ ብቻ ሳይሆን፣ መተዋወቂያ፣ መጠያየቂያ፣ ቀደም ሲል በአባቶች የነበረውን የመረዳዳት ባህል እየተረከ ማስተማሪያ፣ ግንኙነትን ማጠናከሪያና ባህልን ማስተላለፊያ ጭምር ሆኖ ሲያገለግል ለማስተዋል ተችሏል።

እንዲህ አይነቱን የሰዎችን የርስበርስ ግንኙነትና በተለያዩ ባሕሎች ሞት የሚያስከትለውን ውጤት በመረመሩበት ጥናታቸው Parkes (2004፣236) እንደሚገልጹት፣ በቀብር ሥርዓት ላይ መገኘት፣ የሀዘን ስሜትን ከመግለጽ በላይ፣ በሟች ሕልፈት ልባቸው የተነካ ሰዎች በአንድ ላይ የሚገናኙበትና ሀዘኑን በጋራ የሚሸከሙበት ጠቃሚ ማህበራዊ አጋጣሚ መሆኑ፣ ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር ይደጋገፋል። ሀዘንተኞቹ የሞትን አይቀሬነት እንዲቀበሉና የሚናቸውን እንዲወጡ፣ አስተዛዛኞቹ ከራሳቸው ቀደም ያለ ልምድ ተነስተው እያበበረታቱ እንደሚያጽናኑ መግለጻቸውም፣ በቀብር ሥርዓት ከሚታዩት ጠቃሚ መደጋገፎች አንዱ ተደርጎ ይወሰዳል። ምክንያቱም ሞት በዘመድና ቤተሰቡ ያልደረሰበት ሰው ስለማይኖር፣ አጽናኞቹ ከልምዳቸው ተነስተው የሚሰጡት ምክር በተግባር የተሞከረ ከመሆን ባለፈ፣ ተጎጂዎቹ በሁኔታው ውስጥ ካለፈ ሰው የሚሰጣቸውን ምክር አምነው ስለሚቀበሉ ሀዘናቸውን የመቆጣጠር ጥንካሬ ይጨምርላቸዋል። በእነሱ ላይ የደረሰው የተለየ እንዳልሆነ ስለሚያስገነዝባቸውም መጽናናትን ይፈጥርላቸዋል።

እንዲህ አይነቶቹ የልምድ ልውውጦችና የስሜት መጋራቶች ጎልተው የሚታዩባቸው የመጀመሪያዎቹ የሶስት ቀናት የድንኳን ቆይታዎች ሲሆኑ፣ በዚህ ወቅት በቡድን ኃላፊነት የሚቀርበው የእዝን እህል ውሃም ለሀዘንተኞቹ፣ ለለቀስተኛውና ሟች ለሚገኝበት ማሕበረሰብ የጎላ ሥነልቡናዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ለመረዳት ተችሏል። ሀዘንተኞቹ በደረሰባቸው ጉዳት ለማስተዛዘን የመጣው ሰው በሥርዓት ተስተናግዶ ሲሸኝ ከሚሰማቸው እርካታ በላይ፣ መተጋገዙ ብቻቸውን ያለመሆናቸውን የሚያሳይ ተግባር ስለሆነ፣ መጽናናትን

ይፈጥርላቸዋል። ለቀስተኛው ሬሳ ሳይቀበር እህል ውሃ ስለማይቀምስ፣ ከድካሙ አገግሞ ወደየመጣበት እንዲመለስ እድሉን ይፈጥርለታል። በእድር አባላት በድንኳን ውስጥ ለሀዘንተኛው የሚቀርበው መስተንግዶ ደግሞ፣ ለማሕበረሰቡ የመተጋገዝና የመደጋገፍ ባሕሉን በማጠናከር፣ አብሮ የመኖር ዋልታ የሆነውን ቡድናዊ ስሜት ያዳብርለታል።

በተለያዩ ምክንያቶች በቀብር ሥርዓት ዙሪያ የሚታዩ የቡድናዊ ስሜት መላላቶች እያስከተሏቸው ያሉት ማሕበራዊ ቀውሶች፣ የሥርዓቶቹን ሥነልቡናዊ ፋይዳ የሚያጎሉ ሆነው ተገኝተዋል። ለምሳሌ የእንግሊዝን የሞት ሥርዓትና ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተከሰተውን የሀዘንና የለቅሶ ለውጥ የመረመሩትን Gorerን (1965) ዋቢ በማድረግ Yoder (1986፣151-2) እንደሚገልጹት፣ የከተሞች ማደግና የዘመናዊነት መስፋፋት ለሀዘን ግለሰባዊ ግንዛቤ እንዲሰጠው ማድረጋቸው፣ የማህበረሰብ የቡድናዊነት ስሜት መቀዝቀዝ፣ የግለሰብ ሞት በሰፊው ማህበረሰብ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ አናሳ መሆን፣ ከቦታ ወደቦታ የሚደረገው እንቅስቃሴ መጨመር፣ የቤተሰብ ቁጥር መቀነስ፣ የግለኝነት ማደግ፣ በአንዳንዶች ዘንድ ሚስጥራዊ የመሆን ፍላጎት መኖር፣ ማህበራዊ ተሰሚነት ያለው ሽማግሌ መታጣት፣ የቀብር ሥርዓት በሰለጠኑ ባለሙያዎች በንግድ መያዝ፣ የበለጸገ ባሕላዊና ሐይማኖታዊ መሰረትና ትርጉም የነበራቸው ማሕበራዊ እሴቶች እንዲጠፉ አስተዋጽኦ በማድረጋቸው፣ ባጠኑት ማሕበረሰብ ውስጥ ችግሮች እየተከሰቱ መሆናቸውን ይጠቁማሉ።

በዘመናዊው የቀብር ሥርዓት፣ እዝን ይሰጠው በነበረው ማሕበራዊና ሥነልቡናዊ ፋይዳ ቀስ በቀስ ከባሕሉ እየጠፋ መምጣት ጋር ተያይዞ፣ በሟች ቤተሰቦች ላይ ማህበራዊና ስነልቡናዊ ችግር እየፈጠረ መገኘቱን በማሳያነትም ይገልጻሉ። ዘመናዊው የቀብር ሥርዓት፣ የቅርብ የሚባል ሰው ሲሞት ሳይቀር ማድረግ የሚጠበቅበትን እየሳተ እንደሆነና አስፈላጊውን ድጋፍ እየሰጠ እንዳልሆነም ያስገነዝባሉ። በርካታ ማሕበረሰቦች፣ ማህበረሰቡን በሙሉ የሚያሳትፍና የሀዘንተኞቹን ሕይወት የሚያሻሽል ቢያንስ እስከአንድ ዓመት የሚቆይ የድጋፍ ማድረጊያና የፍቅር መግለጫ ሥርዓቶች ያሏቸው መሆናቸውን ገልጸው፣ እነዚህ ዛሬ በእንግሊዝ ማሕበረሰብ መጥፋታቸውንና የቀብር ሥርዓቶቻቸው ስሜታዊና ማሕበራዊ መደጋገፍ የነጠፈባቸው መሆናቸውን ያስረዳሉ። የቀብር ሥርዓት ማሕበራዊነት እየቀረቀዘ መምጣት፣ ስነልቡናዊና ማህበራዊ ጫና እያሳደረ መሆኑንም ይገልጻሉ። የGorerን (1965) ጥናት ዋቢ አድርገው በስነልቡና በኩል ተቀባይነት ያለው ሥርዓትና አመራር መታጣት፣ ለበርካታ

መልካም ያልሆኑ ባህርያት (maladaptive behavior) መከሰት ምክንያት እንደሆነ ሲገልጹ፣ የSheffን (1980) ጥናት ዋቢ በማድረግ፣ ለረጅም ጊዜ ሀዘን ከሚያጋልጡ ምክንያቶች አንዱ፣ ሰዎች የሚያዝኑበት አውድ ማጣትና ፈቃድ መከልከል መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

በተጠኚው ማሕበረሰብ ከዚህ በተለየ መንገድ የሚታየው ቡድናዊ መደጋገፍ፣ ከላይ በተገለጸው መልኩ እያስገኘ ያለው ጠቀሜታ፣ በአሁኑ ወቅት በአጉል ባሕል ሰበብ እገዳ እየተጣለበት መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በስማዳና በፋርጣ ወረዳዎች በዕለቱ ያልተገኙ ሰዎች ያለጊዜ ገደብ (ከወራት በኋላም የሚደርሱ እንዳሉ ለመረዳት ተችሏል)፣ ከሟች ቤት እየሄዱ የሚላቀሱበት ልማድ፣ ሀዘን እንዲያገረሽ በማድረግ ለስነልቡናዊ ጉዳት፣ ለአላስፈላጊ ወጭና የጊዜ ብክነት በመዳረግ ሀዘንተኞቹን መጉዳቱ ባያጠያይቅም፣ ክልከላው መቀጠልና መወገድ ያለበትን ያልለየ መሆኑ ከሚያስገኘው ጥቅም ይልቅ የሚያስከትለው ጉዳት የላቀ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በቡድናዊ መደጋገፉ ላይ በጥቅል እየታየ ላለው ክልከላ የነገ ውጤት፣ በYoder ጥናት የተረጋገጠው፣ በእንግሊዝ ማሕበረሰብ ላይ የተከሰተው ማሕበራዊ ንቅዘትና ስነልቡናዊ ሁከት፣ ጥሩ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

ከዚህ በላይ ጥናቱ በተካሄደበት ማሕበረሰብ በሚታወቁት በሶስቱ የለቅሶ ሥርዓቶች እስከቀብር ድረስ የሚከናወኑት ዓለማዊ ሥርዓቶች ምን እንደሚመስሉ ተገልጸዋል፡፡ ቀጥሎ ደግሞ የዚሁ ክወና አካል የሆኑት የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ድረሳ፣ ምደባና ክወና ቀርቧል፡፡

## 4.2. የተጠኚው ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ድረሳ፣ ምደባና ክወና

በዚህ ክፍል ተጠኚው ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹን መቼና እንዴት እንደሚደርሳቸው፣ ምን ምን ብሎ እንደሚጠራቸው፣ ለማን፣ የትና እንዴት እንደሚከውናቸው የሚያብራሩ በመረጃዎች የተደገፉ ገለጻዎች ቀርበዋል፡፡ ከለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ክወና ገለጻ በፊት፣ ተጠኚዎቹ እንዴት እንደሚደርሷቸውና በአይነት ምን ብለው እንደሚጠሯቸው ማስተዋወቁ ተገቢ በመሆኑ፣ ለእነዚህ ቅድሚያ ተሰጥቶ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 4.2.1. የተጠኚው ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ድረሳ

ስለቃል-ግጥም ድረሳ በየዘመኑ የተነሱ ተመራማሪዎች የየራሳቸውን የተለያዩ ትውሮች ማዳበራቸውን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እንደFinnegan (1977፣84) ገለጻ ግን፣ በባሕል ወይም በአገጣጠም ባሕል፣ በግለሰብ ገጣሚዎች መካከል በሚኖሩ ልዩነቶችና በአንድ ባሕል በሚገኙ የተለያዩ የቃል-ግጥም ዘውጎች መካከል በሚኖሩ የአደራረስ ልዩነቶች፣ ስለቃላዊ ድረሳ አንድን ትውር ይዞ ማጠቃለያ ላይ ለመድረስ መሞከር ነገሩን አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ስለሆነም ለተጠኚዎቹ የድረሳ ስልት ትኩረት በመስጠት ቃል ግጥሞቹን እነማንና እንዴት እንደሚደርሷቸው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በተጠኚው ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞችን የሚደርሱትና የሚከውኑት ባለሙያዎች ያማረ ድምጽ ያላቸውና ለመከወን ደፋር የሆኑ ግለሰቦች ናቸው፡፡ ለመከወን ጥሩ ድምጽ ባይኖራቸውም የመድረስ ችሎታ ያላቸው ግለሰቦች ግጥሞቹን ጥሩ ድምጽ ላላቸው ከዋኞች በመስጠት በድረሳው ይሳተፋሉ፡፡

እነዚህ ግለሰቦች የሚከውኗቸው ቃል-ግጥሞች ከትውልድ ትውልድ በቃል የሚተላለፉ፣ ቀደም ሲል ቢገጠሙም ከሁኔታዎች ጋር እንዲጣጣሙ የተደረጉና በክወና ላይ በራሳቸው የተደረሱ እንደሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እንዲህ አይነቶቹ ድረሳዎች በሌሎች ማሕበረሰቦችም ይስተዋላሉ፡፡ ለምሳሌ Hampton (1982፣76)፣ ጋና ውስጥ የሚገኙት የጋ (ga) ማህበረሰብ የቀብር ሙዚቃና ጭፈራ አቅራቢ ሴት የኤድዋ (adowa) ተጨዋቾች፣ ክህሎቱን አብረዋቸው ከሚኖሩት የእናታቸው ወገን ሴት ዘመዶቻቸው እንደሚማሩት መግለጻቸው፣ ከትውልድ ትውልድ ለሚተላለፉት፤ Aborampah (1999፣264)፣ የአካን ማሕበረሰብ ሴቶች በለቅሶ ሥርዓት የሚጫወቱትን ሚና በተነተኑበት ጥናታቸው፣ ሴቶች ጥበባዊ በሆነ መንገድ የለቅሶ ቃል-ግጥሞችን እንደሚደርሱ መግለጻቸው፤ ለክወና ላይ ድረሳ ጥሩ ማሳያዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው መረጃ አቀባዮች ውስጥ አቶ ሞላ አየሁ (አባ.2፣ ቁ.9፣ ክፍ.1.2.1.፣ አን.2-7) የለቅሶ ቃል-ግጥሞችን ሌሊት ላይ በማምሰልሰል እንደሚገጥሟቸው ገልጸዋል፡፡ የሚከተለው የአንድ ለቅሶ ላይ ገጠመኛቸው ለድረሳ ዘዴያቸው ጥሩ ማሳያ

ይሆናል። ቡሮ ገብርኤል ቀበሌ ገበሬ ማሕበር (በ197ዎቹ የመጀመሪ ዓመታት) በአንድ አዳኝ ለቅሶ ላይ፣

ገድብ (የጎጥ ስም) ነው እንጂ አገር የሚያውቀው፣ አርበኛ እሚያውቀው፣
እንደሸለቶ ጠጅ እሚፈልቀው
ዛሬም ይሸታል ሀደባልቄ ቤት የገድብ ጠጅ፣ (በአባታቸው እግር የተተኩ ሀብታም ናቸው)
አሳላፊ አጥተው አይሰጡም እንጅ።

ብለው በገጠሙት የፉከራ ግጥም ምክንያት እኒያ ሀብታም የተሰደብኩ ስሜት ያድርባቸውና፣ ፎካሪውን የሚያዋርድ ሰው ሲፈልጉ አንዱ ‹‹እኔ አለሁ›› ይላል። ገና ጀማሪ ፎካሪ ሆነው ግጥም ስለሚያንሳቸው፣ ከአንድ ቦታ ላንድ አርበኛ የገጠሙትን፣ ሌላ ቦታ ለሌላ አርበኛ፣ ላንድ ገበሬ የገጠሙትን፣ እንዲሁ ለሌላ ገበሬ እየገጠሙ መከወናቸው እንደነውር ይወሰድባቸዋል። ከዚያው ገበሬ ማሕበር እ.ኢ.አ. በ1976 ዓ.ም አንድ ሽማግሌ ለቅሶ ላይ እንደተለመደው ለፉከራ ተሰልፈው ሲጠብቁ፣ ያ ‹‹ብድር እመልሳለሁ›› ባይ ቀድሞ ተራ ይደርሰውና፣

‹‹ያንዱነን ልቅሶ ሀንዱ ኸማልቀስ፣
መሞት ይሻላል ኧረ አፈር መልበስ።
ያንዱነን ልቅሶ ሀንዱ ኸመደብለቅ፣
መሞት ይሻላል ኧረ መታነቅ››። ብሎ ይፎክርባቸዋል። ተራቸው ሲደርስ፣

‹‹ፋርጣ* በፈረስ ሲጠቀጥቀኝ፣
የርቡን** ሞላ ስሜን ሳያውቀኝ።
ጥንትም የሞተ ወገናችን ነው፣
ዛሬም የሞተ ወገናችን ነው፣
የሚያላቅሰን ወገናችን ነው፣
ያን እያነሳን ብናለቅስበት ነውሩ ምንድን ነው;
በል!?

* *ተሳዳቢው ፋርጤ መሆኑን ለመግለጽ ነው*

***ፎካሪው በሚኖሩበት አካባቢ የሚገኝ ታዋቂ ወንዝ ስም*

ለስሙ ሱሪ የማይችለው፣
ለደረቱ ኮት የማይችለው፣
ሊሰድበኝ መጣ ባለጌው ሰው፡፡
ምን ግንፍል ግንፍል እንደ ጫሀና*፣
አሽርሻለሁ ዳግም በይና!

በማለት እዚያው ላይ መልስ መስጠታቸውን ይተርካሉ፡፡ ይህን ግጥም መቼ እንደደረሱት ለቀረባላቸው ጥያቄ፣ ‹‹በፊት ቀንም ለሴቶች መፎከር እንደሚገባው የእኩልነት ዘመን መሆኑን አንስቼ ስፎክር፣ ‹ደሞ ለሴት› ብሎ ጎሰም አድርጎኝ ስለነበር፣ ለእንግዳ መጠባበቂያ (ለባለጌ መከላከያ) ብየ አምስልስየ ነበር››፣ በማለት ቀደም ብለው የደረሱትን እንደከወኑ ገልጸዋል፡፡ በየቦታው ሲሄዱ የሚፈክሯቸውን የፉከራ ቃል-ግጥሞች እንዴት እንደሚገጥሟቸው ለቀረበላቸው ጥያቄም፣ ‹‹ገበሬ ተሆነ ያንዱ ላንዱ ይሆናል፡፡ ብቻ ስሙ ነው እንጅ የሚለወጥ ያንዱ ላንዱ ይሆናል፡፡ ወታደር ተሆነ ያንዱ ላንዱ ይሆናል፡፡ ያንዱ መደብ ለብዙ ይሆናል፡፡››፣ በማለት አስረድተዋል፡፡

የወየታና የሙሾ ቃል-ግጥሞች ባለሙያው አቶ ደሳለኝ ታየም (አባ.2፣ ቁ.7፣ ክፍ.1.2.1.፣ አን.2) ሚችን የማያውቁት ከሆነ፣ በምኑ እንደሚገጠምለት ሙያውን አስቀድመው እንደሚጠይቁና፣ በዚያ መሰረት ተዘጋጅተው ወየ እንደሚሉ ወይም ሙሾ እንደሚያወርዱ ገልጸዋል፡፡

የፉከራ ባለሙያው አቶ አበረ ክበበው (አባ.2፣ ቁ.10፣ ክፍ.1.2.1.፣ አን.1-2) የፉከራ ቃልግጥሞቹን እንዴት እንደሚገጥሟቸው ለቀረበላቸው ጥያቄ የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል፡፡

> መጠጥ እጠጣለሁ፡፡ እንዲህ ብየ ውየ ህጀ ከቤቴ ስተኛ፣ ጠቅላላ ብርሃን ሆኖ ነው የሚታየኝ፡፡ ሌሊት እንዲህ አድርጎ ሲያሳድረኝ አንዱን ከአንዱ፣ አንዱን ከአንዱ፣ ሳጣልፈው አድራለሁ፡፡ አንዱን ካንዱ እያደረኩ አሁን ስሞክር፣ ስሞክር ትንሽ የሁለት ሶስት ጊዜ ሞክርኩ፡፡ የሶስት አራት ጊዜ ጨመርኩበት፡፡ አሁን ትንሽ እንደመጠጥ ያለ ከጠጣሁኝ፣ ከበላየ ላይ ያለው በቃ አይታወቀኝም፡፡ ከደረሰም የማደርገውን አላውቅም፡፡

* *ተሳዳቢው በሚኖርበት አካባቢ የምትገኝ በቀላል ጎርፍ የምትሞላ ወንዝ ስም*

ዝም ብሎ መጥቶ ራሱ ግጥም፣ ራሱ ግጥም ነው እንጂ፣ ወይም ጽፌ ወይም አንብቤ አይደለም፡፡ ስሜን እንኳን አልጽፍም፡፡ መጥቶ ጥልፍ ጥልፍ ይልልኛል፡፡ ዝም ብሎ ወጥ ሁኖ ይቀርብልኛል፡፡ ከበላየ ላይ ያለው ያሳካዋል፡፡ አሁን በግብርና ሙያ እፎክራለሁ፣ በዚህ በጀግኖችም፣ በመምሮችም፣ በዘማቾችም፣ በተለያየ ነገርም እያነሳሁ እፎክራለሁ፡፡ አንዳንዶች ግን፣ ‹ላንተ እስቲ ጻፍ ትንሽ እናስጽፍህ እንድትጨምር› ይሉኛል፡፡ ታዲያ አልገባኝ ብሎ ቀረ፡፡ ጽፌው የሰጡኝ ስለማላነበው አልገባኝ ብሎ ቀረ፡፡ ግን ራሱ እግዚአብሔር የፈጠረኝ ንጉሥ ግን፣ በቃ እንዳየሁው ነው፡፡

በዕለቱ ሲፈክሩላቸው ከነበሩት ሟች ጋር ምን ትውውቅ እንደነበራቸው ሲጠየቁ፣ በዘመዳቸው በኩል የተሰጧቸውን መረጃዎች መሰረት በማድረግ እንደከወኑና ሟችን በአካል እንደማያውቋቸው ገልጸዋል፡፡ ‹‹ ‹አጎቴ ሙቷልና እንሂድ› ብሎኝ ነው እንጅ ሰውየው ጥቁር ይሁን ቀይ ይሁን አላውቀውም፡፡ ታሪኩን ነግሮኛል፡፡ የቀደም አድራጎቱን የወንድሙን ‹እንዲህ እንዲህ ያርስ ነበር፣ እንዲህ ያል ሀብት ነበረው፣ እንዲህ እንዲህ አድርጓል፣ ልዥ ድሯል፣ አምርቷል፣ እንዲህ እንዲህ አድርጓል፣› ብሎ ነገረኝ፡፡ በቃ እኔ ይህን እያነሳሁ ማንጠባረቅ ነው፡፡›› በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከምልከታ መረጃዎቹና ከእነዚህ መረጃ አቀባዮች ከተገኙት መረጃዎች ለመገንዘብ እንደተቻለው፣ የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ድረሳ፣ ከክወና በፊትና፣ በክወና ላይ ይካሄዳል፡፡

ከዋኞቹ በአካባቢያቸው ከሚገኘው ማሕበረሰብ ሙያ ጋር የተያያዙ ግጥሞችን በተለይ በሌሊት እያሰላሰሉ እንደሚገጥሙና፣ አንድ ባለሙያ ሲሞት ቀደም ሲል ለሞተው ተመሳሳይ ባለሙያ ከገጠሙት ውስጥ ቋሚ የጋራ ነጥቦችን በመውሰድ የሟችን ስምና ቦታ እያቀያየሩ ይከውናሉ፡፡ አዳዲስ ነገሮች ሲያጋጥሟቸው በክወናው ላይ ከሁኔታው ጋር በማያያዝ እንደሚደርሱም የሚከተለው የመረጃ አቀባዩ የአቶ ደሳለኝ ታየም (አባ.2፣ ቁ.7፣ ክፍ.1.2.1.፣ አን.3-4) ገጠመኝ ጥሩ ማሳያ ይሆናል፡፡

> በአንድ ወቅት ወየ ባዮች ከአንድ ሰው ቤት ለግብገ ተሰባስበን ሳቅ ጨዋታ ሆነ ማታ፡፡ መቼም ብዙ ነገር አለ ይኸ ሙሾ አውጭ ሲገናኝ ረፍት ሲገኝ እንደዚህ ባለው አጋጣሚ ቧልት ጨዋታ ሞልቷል፡፡
>
> ‹‹‹አቶ እገሌ› ብሎታል››
> ‹አቤት›

‹አንተ እኮ ፈጥረህ ነው የምትል ግጠምልኝ› አለው፡፡

‹በምን?›

‹ለእኔ ብልት ወየ በልለት፡፡ ሙቶብኛል ወየ በልልኝ› ብሎታል፡፡

‹እሺ›

አሁን ያ ‹ግጠምልኝ› ያለው ሰው መልከኛ ነበር ያየኸው እንደሁ የተቀሸረ መኳንንት ነው፡፡ አብልቶ የሚያጠጣ ሀብታምም ነው፡፡

‹እሽ ልበልልህ;›

‹አወ›

‹ኧረ አይዋ እገሌ (ስሙን ጠርቶ) መልኩ የሰለሞን ቁመቱ ያንበሳ፣ ቁመቱ ያንበሳ፣ ሲለፋ ይኖራል ተሸክሞ ሬሳ፡፡› አለው፡፡

ከዚያ ‹አንቺ ሰውየ ዛሬ› አለና ወደመጠጥ ቤት ህደን፣ ካሳ ቢራ አስመጣና ‹ጠጡ!› አለ፡፡ እንደዚህ እየተጠጣ ገብስ ጥሬ ኸወለል ላይ ተደፍታለይ፡፡ ‹አሁን በዝች ገብስ የሚገጥም ማነው;› ብሎ ያው ጋባዥ ይጠይቃል፡፡ ‹እኔ አቶ እገሌ በዚህ እገጥማለሁ፤ ብቻ ወደነውርነቱ አትውሰዱብኝ እንጂ፣ እኔ እገጥምበታለሁ› ይለዋል፡፡ ሀይለኛ ነው ይኸኛው ገጠመበት፡፡

‹ጌሾው ይደፋ እንጂ ምን ባለ ነው ገብሱ፣

እንግዲህ እስዎ ዝም ብለው ይፈሱ› አለው፡፡ ሴትዮዋ ያስገጣሚው ውሽማ ነበረች፡፡

እነዚህ ገጣሚዎች ስለልፍስፍስ ብልትም ሆነ፣ ስለተደፋ ገብስ ከዚህ በፊት የወየታ ግጥም ገጥመው ለዚህኛው ሁኔታ እንዲመቻች አድርገው አቅርበዋል ለማለት ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም በባህሉ ለሁለቱም ነገሮች የወየታ ግጥም አይገጠምም፡፡ የመጀመሪያው በነውርነቱ፣ ሁለተኛው ሰው ባለመሆኑ አይገጠምላቸውም፡፡ ስለሆነም ከላይ የቀረቡት ቃል-ግጥሞች፣ ጨዋታ በፈጠረው አውድ በክወና ላይ የተገጠሙ መሆናቸውን ለመረዳት አያዳግትም፡፡

አቶ ታካለ ንጋቱ ደግሞ (አባ.2፣ ቁ.13፣ ክፍ.1.2.1.፣ አን.2)፣ የሚችን ታሪክ ካጠኑ በኋላ፣ እንደሙያና ሥራው ከዚያው ላይ እንደሚገጥሙለት ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የቀረቡት መረጃዎች እንደሚያሳዩት፣ ተጠኚዎቹ የለቅሶ ቃል-ግጥሞችን ከክወና በፊት በመድረስ፣ በክወና ወቅት ከሁኔታዎች ጋር በማጣጣም እንደሚጠቀሙባቸው

ለመረዳት ተችሏል። ከዚህም በተጨማሪ በክወና ላይ በወጥነት ይደርሳሉ። በዚህ መንገድ የሚደርሷቸው ግጥሞች የተለያየ ዘውግ እንዳላቸው የሚያሳየው ክፍል ደግሞ ቀጥሎ ቀርቧል።

## 4.2.2. የተጠኚው ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች አካባቢያዊ ምደባ

ቃል-ግጥሞቹ በየትኛውም ዘዴ ይደረሱ፣ በክወና፣ በቅርጻዊ ባህሪ ወይም በሌላ ምክንያት የተነሳ እንደተመሳሰሏቸው ሊያስመድብ የሚችል የየራሳቸው ባህሪ ሊኖራቸው እንደሚችል ይታመናል። ይሁንና ጌቱ (2000፣67)፤ Okpewho (1992፣156)፤ Finnegan (1977፣145) እንደሚያስረዱት፣ በአፍሪካም ሆነ በኢትዮጵያ የተካሄዱ ጥናቶች፣ የለቅሶ ቃል-ግጥሞችን፣ ሞት ሲከሰት በአንድ ሰው የቀብር ሥርዓት ላይ በመዜም የሚከወኑ ግጥሞች አድርገው በጥቅል የመመልከት የጋራ ባህርያት ይታዩባቸዋል። የሲሳላን የለቅሶ ቃል-ግጥሞች የመረመሩት Sanka Confidence (2010፣30) ግን፣ የተለያዩ ተመራማሪዎችን ለምሳሌ Cuddon (1998) እና Abramsን (2005)፣ ዋቢ አድርገው፣ በለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ መካከል የሰበበ ድርሰትና የቅርጽ ልዩነቶችን መሰረት በማድረግ ሙሾ (dirge) እና ሟች አወዳሽ ግጥም (elegy)፣ ብለው በሁለት ጎራ የመክፈል ልማድ እንዳለ ያስረዳሉ።

ስለሆነም፣ ‹‹በቀብር ላይ የሚቀርቡ ቃል-ግጥሞች›› የሚለው ጥቅል ምደባ፣ በክወናና በቅርጽ ልዩነት የሚታይባቸውንና በየግል ባሕሪያቸው መጠናት የሚገባቸውን በአንድ የሚጨፈልቅ ስለሆነ ቀርነት ይታይበታል። በሙሾና በሟች አወዳሽ ግጥሞች ስር የመመደቡ አሰራርም፣ የራሳቸውን የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ከታሪካዊ አመጣጣቸውና ከክወናቸው በመነሳት ለመረመሩት ለምዕራባውያን ይሰራ እንደሆነ እንጂ፤ በባህልና ቋንቋ ለማይገናኙ ለሌሎች ማሕበረሰቦች የለቅሶ ቃል-ግጥሞች መመደቢያነት ማዋሉ፣ በዘመኑ የስነቃል ጥናት ሳይንስ የሚመከር አይደለም።

በአማራ ማሕበረሰብ የለቅሶ ሥርዓቶች ላይ የሚከወኑትን ቃል-ግጥሞች ምንነት ለመግለጽ ከሞከሩት ውስጥ፣ ጎሩይ፣ (1910፣18)፣ ማኅተም ሥላሴ (1942፣587) እና ብርሃኑ (2002፣1910) ይጠቀሳሉ። ጎሩይ በለቅሶ ዜማ ግጥም፣ ማህተመ ሥላሴ በእንጉርጉሮ፣ ብርሃኑ በሙሾ፣ ያጠቃለሏቸውን የለቅሶ ቃል-ግጥሞች፣ ስለአይነታቸው ፍንጭ ሊሰጥ በሚችል መንገድ ለመክፈል በመሞከር በሪሁን (2004) ይጠቀሳሉ። በሪሁን በደብረ ታቦር ከተማ የሚከወኑትን የለቅሶ ቃል-ግጥሞች፣ በሙሾ ስር ጠቅለሎ መጥራት እንደማይገባና በየባህሪያቸው መጠናት እንዳለባቸው ለማሳየት ተነስተው፣ የደብረ ታቦር ከተማ የለቅሶ ቃል-

ግጥሞች፣ የወየታ፣ የሙሾና የፉከራ ቃል-ግጥሞችን እንደሚያካትት ይጠቅሳሉ። በእያንዳንዳቸው መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በተጨባጭ መረጃዎች አስደግፈው ለማሳየት ባለመቻላቸው ግን የተነሱበትን ግብ እንዳያሳኩ አድርጓቸዋል። በትንተናቸው ክፍል የሙሾ ቃል-ግጥሞችን አለማካተታቸውም ከወየታ ግጥሞች ለመለየት የተሳናቸው ለመሆኑ እንደማስረጃ ሊጠቀስ ይችላል። ይህም የተጠኚው ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች፣ በየራሳቸው ባሕሪ ተለይተው አለመመደባቸውን ያሳያል።

በዚህ ጥናት፣ ለአካባቢያዊ ምደባ ትኩረት በመስጠት፣ የተጠኚውን ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች በራሱ መጠሪያዎች የመመደብ ሥራ ተከናውኗል። በአምስቱም ወረዳዎች ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለመገንዘብ እንደተቻለውና ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው ቁልፍ መረጃ አቀባዮች መካከል፣ መሪጌታ ስቡህ ዘላለም (አባ.2፣ ቁ.4፣ 1.2.2.፣ አን.1) እና አቶ ብርሃን አበበ (አባ.2፣ ቁ.16፣ ክፍ.1.2.2.፣ አን.1-2) እንደሚገልጹት፣ የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ወየታ፣ ሙሾ፣ ፉከራና ቀረርቶ በሚባሉት አራት ዘሮች የሚመደቡ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል። በእነዚህ ዘውጎች፣ በክወና ወቅት በከዋኝና ታዳሚ መካከል በሚካሄደው መስተጋብርና በአካል እንቅስቃሴ፣ በሟች ማሕበራዊ ደረጃና በእድሜ ሳቢያ፣ በመካከላቸው ልዩነቶች መኖራቸውንና እነዚሁ መስፈርቶች ለመመደቢያነት ማገልገላቸውንም ለመገንዘብ ተችሏል።

በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ለማየት እንዲረዳ፣ የእያንዳንዳቸው ምንነት ማስተዋወቅ አስፈላጊ ስለሆነ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 4.2.2.1 ወየታ

በደቡብ ጎንደር ዞን የኦርቶዶክስ እምነት ተካታይ ማሕበረሰብ፣ በሞት አጋጣሚ ከሚቀርቡት የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ውስጥ፣ በማንኛውም መንገድ ልዩነት ሳይደረግበት ለሟች የሚቀርበውን የለቅሶ ቃል-ግጥም፣ ባለቤቶቹ ‹‹ወየታ›› በማለት ይጠሩታል። የወየታን ቃል-ግጥም ከጸሀፊዎች መካከል ኀሩይ እ.ኢ.አ (1910) በለቅሶ ዜማ ግጥም፣ ማሕተም ሥላሴ እ.ኢ.አ (1942) በእንጉርጉሮ ስር ሲያጠቃልሉት፣ ከተመራማሪዎቹ ውስጥ ደግሞ ምግባሩ (2009) በሙሾ፣ ብርሃኑ (2002) የሙሾ ንዑስ ክፍል አድርገው በወሰዱት እንጉርጉሮ ስር ያስገቡታል።

ከመረጃ አቀባዮቹ መካከል አቶ ደሳለኝ ታየ (አባ.2.፣ ቁ.7፣ ክፍ.1.2.2.1.፣ አን.1.) እና አቶ ዋለ ጎበና (አባ.2፣ ቁ.14፣ ክፍ.1.2.2.1.፣ አን.1-6) እንደሚገልጹትና በክወና ላይ እንደታየው ግን፣ ወየታ ራሱን የቻለ በዜማ የሚቀርብ የለቅሶ ቃል-ግጥም ነው። መሪጌታ ስቡህ ዘላለም (አባ.2፣ ቁ.4፣ 1.2.2.፣ አን.1) እንደሚገልጹት ‹‹ወየታና ሙሾ ባቀራረብና በዜማ ይለያዩ እንጂ በግጥም ለሙሾ የተባለው ወየታም ይሆናል።›› በተካሄዱት ምልከታዎችም ይህንኑ ለማረጋገጥ ተችሏል።

በከዋኞቹ የድምጽ ግሪት ከሚፈጠረው የድምጽ መርዘምና ማጠር፣ መለስለስና መሻከር፣ ከሚስተዋሉ መጠነኛ የላሕይ ልዩነቶች ውጭ፣ በቃል-ግጥሞቹ ባህሪ ወይም በክወናቸው ምክንያት የሚፈጠር ልዩነት ስለማይታይባቸው፣ የወየታ ቃል-ግጥሞች ቀጥሎ እንደቀረበው የሙሾ ቃል-ግጥም በንዑስ ምድብነት ሊታይ የሚችል ዘር የላቸውም።

### 4.2.2.2. ሙሾ

ከፍ ሲል እንደተጠቆመው፣ በተለያዩ አጥኚዎች ሙሾ ለወየታ ግጥሞችና ክወና መጠሪያነትም ሲያገለግል ይስተዋላል። ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (1948፣816) ሙሾን፣ ‹‹የለቅሶ ቅንቀና፣ ኻሃራ፣ ግጥም፣ ዜማ፣ ቁዘማ፣ እንጉርጉሮ፣ ረገዳ፣ ጭብጨባ ያለበት››፣ በማለት ይበይኑታል። ይህ መዝገበ ቃላዊ ፍች ለወየታም የሚሰራ መሆኑ፣ አጥኚዎቹ ሁለቱን ዘውጎች እንደአንድ እንዲወስዷቸው ወይም ወየታን ሙሾ እያሉ እንዲጠሩት በር የከፈተ ይመስላል። ጌጡ እ.ኢ.አ (1989፣28)፣ የሙሾን ክወና ለማሳየት ያቀረቡት የወየታ ቃል-ግጥም ክወና፣ ለዚህ ጥሩ ማስረጃ ይሆናል።

ከመረጃ አቀባዮቹ መካከል አቶ ደሳለኝ ታየ (አባ.2፣ ቁ.7፣ ክፍ.1.2.2.2.፣ አን.2-3) እንደሚገልጹት፣ በተጠኚው ማሕበረሰብ ሙሾ፣ ከሶስት እስከዘጠኝ በሚደርሱ ሁለት ቡድኖች አማካይነት በመሪ፣ አውራጅና ተቀባይ ቅብብሎሽ፣ በእርግዶ (ሽብሸባ) ለሚከወን የለቅሶ ቃል-ግጥም የሚሰጥ መጠሪያ ነው። በክወናው ወቅት የተካሄዱት ምልከታዎችም ይህንኑ ያረጋግጣሉ። የሙሾ ቃል-ግጥም ከሚከወንበት ቦታ፣ ከከዋኝና ታዳሚው መስተጋብርና፣ ከእርግዶ አኳያ ሲታይ ተመሳሳይ ቢሆንም፣ በአዝማቾቹ ልዩነት በሚፈጠር የዜማ ልዩነት፣ አምስት ንዑስ ዘሮች ያሉት መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል።

የሙሾ ዜማዎቹን መጠሪያዎች መሰረት በማድረግ፣ ከመረጃ አቀባዮቹ መካከል አቶ ደሳለኝ ታየ (አባ.2፣ ቁ.7፣ ክፍ.1.2.2.2.፣ አን.1-5)፣ በደቡብ ጎንደር ዞን አምስት የሙሾ አይነቶች እንደሚከወኑ ያስረዳሉ፡፡ በተሳትፏዊ ምልከታ የተቀረጹት መረጃዎች የሚያሳዩት ግን፣ አራት የሙሾ አይነቶች መኖራቸውን ነው፡፡ በየሙሾ ሀረጋቱ መካከል ተቀባዮቹ እየደጋገሙ የሚያወርዱት አዝማች ርዝመትና ከዚሁ የሚመነጨው ዜማ፣ እንዲሁም የአቀራረብ ቅደም ተከተል፣ ሙሾን በአይነት ለመክፈል እንዳገለገሉ፣ በምልከታ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በዚህም መሰረት፣ የሙሾ አይነቶቹ፣ ‹‹ወዳጅ ወዳጄ ፈረስክ እያሉኝ ልዘን ዋ›› ፣ ‹‹ዋየ እያሉ ኸዱ ዋየ ዋየ››፣ ‹‹ዋየ ዋይ ወየሁ››፣ ‹‹አወየው ዋይ ዋይ/ ወየሁ›› እና ‹‹ዋ/አየ ተለየኝ/ያለው ማነው›› በሚሉት አካባቢያዊ መጠሪያዎች እንደሚመደቡ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረቡት የወየታና የሙሾ ቃል-ግጥሞች ጋር በለቅሶ ሥርዓት ላይ ቢቀርቡም፣ በሚያዙት የመከወኛ መሳሪያዎችና በክወና ላይ በሚታዩት እንቅስቃሴዎች ልዩነት የተነሳ፣ ራሳቸውን ችለው የሚቀርቡት የለቅሶ ቃል-ግጥሞች፣ በአካባቢው ማሕበረሰብ ቀረርቶና ፉከራ በመባል ይታወቃሉ፡፡ መለያ ባሕርያታቸው ምን እንደሚመስሉ ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

#### 4.2.2.3. ቀረርቶና ፉከራ

በቀረርቶና በፉከራ ቃል-ግጥሞች መካከል በዜማና በአከዋወን በሚታዩት ልዩነቶች ራሳቸውን የቻሉ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ተደርገው ቢወሰዱም፣ በአቀራረብ ተደጋጋፊነታቸው የጎላ ስለሆነ በአንድ ላይ ቢታዩ መልካም ሊሆን እንደሚችል ታምኗል፡፡ ከአቀራረብ ተደጋጋፊነታቸው በተጨማሪ፣ በለቅሶ ሥርዓት ላይ በማሕበረሰቡ ዘንድ በየትኛውም ዘርፍ ‹‹ጀግና››፣ የሚያስብል ሥራ ላከናወኑ የማሕበረሰብ ክፍሎች ሥራዎቻቸውን ለመዘከር ወይም ለማወደስ የሚከወኑ መሆናቸው፣ በጋራ የመታየታቸውን ተገቢነት የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የሚከተሉት መዝገበ ቃላዊ ፍችዎች የሚያሳዩትም ይህንኑ ተደጋጋፊነታቸውን ነው፡፡ ደስታ (1962፣1117) እንደሚያስረዱት፣

> ‹‹ቀረርቶ በጦርነት ጊዜ አልያም በልዩ ልዩ ጨዋታዎች (በሰርግ፣ በክብረ በዓላት)፣ በመሸታ ቤቶች ወታደር በጌታው ፊት፣ የከፋው ሰው በየጋራውና ተራራው

የሚዘፍነው ዜማ ለበስ ግጥም ነው፡፡ በባህሪው ጀግናን የሚያወድስ፣ ወኔ የሚቀሰቅስና ፊሪ የሚገስጽ›› እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ፉከራንም ‹‹ዘራፍ ማለት፣ ድንፋታ፣ ገቦዱ ቆጠራ፣ መፎከር፣ መደንፋት፣ ዝሆን፣ አንበሳ፣ ጠላት ገዳይ ማለት››፣ በማለት ይበይኑታል፡፡

Fenneganም (1970፣111)፣ ፉከራ (panegyric) በጦርነትና በአደን ውጤታማ ለሆኑ ጀግኖችና ለመሪዎች ማወደሻነት እንደሚያገለግል ያስረዳሉ፡፡ አንተነህ እ.አ.አ. (2001፣112) ደግሞ፣ ቀረርቶና ፉከራ የጀግንነት መግለጫ፣ የወንድነት ማመጫ፣ የጠላትና የፈሪ መተንኮሻ፣ ስልቶች መሆናቸውንና፣ የሚዘወተሩትም በዋዜማ ጦርነትና በጦርነት፣ በባሕላዊ ዓመት በዓላትና በሽፍትነት ወቅቶች መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

የቀረርቶና የፉከራ የለቅሶ ቃል-ግጥም ዘውጎች፣ ከጀግንነት ጋር የተያያዘ ስሜት የሚገለጽባቸው መሆናቸውን የመዝገበ ቃላት ፍቺዎቹ ይጠቁማሉ፡፡ ጥናቱ በተካሄደበት በደቡብ ጎንደር ዞን፣ እነዚህ ዘውጎች በስፋት አገልግሎት ላይ እንደሚውሉ፣ ከአቶ አበረ ክበበው (አባ.2፣ ቁ.10)፣ ከአቶ ሞላ አየሁ (አባ2.፣ ቁ.9)፣ ከአቶ ታከለ ንጋቱ (አባ.2.፣ ቁ.13)፣ እና ከአቶ መላሽ ወርቁ (አባ2.፣ ቁ.21) ምላሾች ለመረዳት ተችሏል፡፡ እነዚህ መረጃ አቀባዮች፣ ፉከራ በማህበረሰቡ ዘንድ በጀግንነታቸው፣ በጠንካራ ሰራተኝነታቸው፣ በጥሩ ቤት አያያዛቸው፣ በሀብታቸውና በተሚጋችነታቸው ወዘተ. ለተመሰከረላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ብቻ፣ ጾታ ሳይለይ እንደሚከወንና፣ ቀረርቶው ለማሟሟቂያነት አብሮ እንደሚቀርብ ያስረዳሉ፡፡ ምልከታ በተካሄደባቸው የለቅሶ ሥርዓቶች ላይ፣ ቀረርቶና ፉከራ እየተደጋገፉ የተጠቀሱትን እሴቶች ስሜት በተሞላበት ሁኔታ ሲገልጹ ተስተውለዋል፡፡

ቀረርቶና ፉከራ በሚያነሷቸው ጉዳዮችና በአቀራረባቸው ተደጋጋፊነት ይኑራቸው እንጂ፣ በክወናቸው ልዩነት ይታይባቸዋል፡፡ ራሳቸውን ችለው እንዲመደቡ የሚያደርጓቸውም፣ በግጥሞቹ ዜማዎችና በክወናዎቻቸው ላይ የሚታዩት ልዩነቶች ናቸው፡፡ ጉልህ ልዩነቶቻቸው ክወናቸው በተተነተነበት ክፍል ቀርቧል፡፡

ቀረርቶ ንዑስ ዘሮች የሌሉት ሲሆን፣ ፉከራ ግን በክወና ሳይሆን፣ በክወና ወቅት በሚያዙት መሳሪያዎችና ግጥሞቹ በሚያንጸባርቋቸው የጀግንነት አይነቶች፣ (በሟች ሙያ)፣ የጦር ሜዳ፣ የግብርና፣ የሙግት፣ የአደንና የአስተዳደር፣ ተብለው በአምስት እንደሚከፈሉ ታዋቂዎቹ ፎካሪዎች፣ አቶ ሞላ አየሁ (አባ.2.፣ ቁ.9.፣ ክፍ.1.2.2.3.፣ አን.1-4) አቶ ታከለ ንጋቱ (አባ.2.፣

ቁ.13፣ ክፍ.1.2.2.3.፣ አን፣1-2)፣ አቶ መላሽ ወርቁ (አባ.2.፣ ቁ.21፣ ክፍ. 1.2.2.3.፣ አን.1) እና አቶ አበረ ክበበው (አባ.2፣ቁ.10፣ ክፍ.1.2.2.3.፣ አን፣1-2) ያስረዳሉ፡፡ እንደሚች ማንነት ከሚተኮርበት ይዘትና ከሚያዘው መሳሪያ ውጭ፣ በከዋኝና ታዳሚ መስተጋብርም ሆነ በክወና እንቅስቃሴ ልዩነት እንደማይታይ መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ፡፡ በምልከታ የተሰበሰቡትና ተቀርጸው የተገኙት መረጃዎችም፣ ይህንኑ ሀሳብ ያጠናክራሉ፡፡

ከዚህ በላይ፣ የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ዘሮች ምን ምን እንደሆኑ በአካባቢው ማሕበረሰብ ምደባ ተለይተው ተዘርዝረዋል፡፡ እነዚህ ቃል-ግጥሞች፣ በእነማን፣ ለእነማን፣ መቼና እንዴት; እንደሚከውኑ የተገለጸበት ክፍል ደግሞ፣ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

### 4.2.3. የተጠኚው ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ክወና

ሁሉም የለቅሶ ቃል-ግጥሞች የሚከወኑት፣ በዓለማዊ የቀብር ሥርዓት ስር ነው፡፡ የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ክወና የየራሳቸው ባህሪ ቢኖራቸውም፣ በአቀራረብ በአንዱ መሀል ሌላው ጣልቃ የመግባት ሁኔታ እንዳለ ከተካሄዱት ምልከታዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ የወየታ ቃል-ግጥም የሚች ነፍስ ከወጣ ከጥቂት ጊዜ በኂላ ጀምሮ እስከቀብር መዳረሻ የሚከወን ሲሆን፣ ለቀስተኛው ከተሰባሰበና ለቅሶው ከደመቀ በኂላ በአብዛኛው በማርገጃ የሚከወኑት የሙሾና የፉከራ ቃል-ግጥሞች፣ በወየታ ላይ ጣልቃ ሲገቡ ተስተውሏል፡፡

ምልከታ ከተካሄደባቸው የለቅሶ ሥርዓቶች ለመረዳት እንደተቻለው፣ የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ክወና ከአቀራረብ ቅደም ተከተል አኳያ በአብዛኛው ሲታይ፣ የወየታ ቀድሞ፣ የሙሾ ተከትሎ፣ የቀረርቶ ለጥቆና የፉከራ በመጨረሻ ይመጣል፡፡ ይህ ሲባል ግን በዚሁ ደረጃቸው በለቅሶ ሥርዓቶቹ ክንውኖች ወይም በሌላ መንገድ ድንበር ተለይቶላቸው፣ አንዱ ተከውኖ ሲጠናቀቅ፣ ሌላው ይቀርባል ማለት አይደለም፡፡

አንዳንዴ የአንዱ የመጀመሪያ ወይም የሁለተኛ ዙር ክወና ሲጨረስ፣ የሌላኛው ቃል-ግጥም እንዲሁ የተወሰነ ዙሩ እየቀረበ የሚፈራረቁበት፣ አንዳንዴ ደግሞ ለቀስተኛው ጎራ ለይቶ ጎን ለጎን የሚቀርቡበት ሁኔታ መኖሩ ታይቷል፡፡ ለምሳሌ የወየታ ቃል-ግጥም እየተከወነ ሙሾ ሲጀመር፣ ለቀስተኛው ከሁለት ተከፍሎ ጾታ የማይለየውና ሀዘንተኞቹ የሚገኙበት ቡድን፣ የወየታ ቃል-ግጥም ሲከውን፣ ወንዶች ብቻ የሚገኙበት ሌላው ቡድን ሙሾ የሚያወርድበት

ሁኔታ መኖሩን፣ ከአቶ ዓለምነው እ.ኢ.አ. (በ14/09/04) እና ከወይዘሮ ፀሀይ እ.ኢ.አ. (በ8/10/04) ከተካሄዱት ለቅሶዎች ክወና ላይ ለመመልከት ተችሏል፡፡ የመጀመሪያው ሙሾ እንዳበቃ የወየታው ክወና ወደነበረበት ቦታ ተመልሶና ለቀስተኛውም በአንድ ተቀላቅሎ ሲቀጥልም ተስተውሏል፡፡ አንድ ዙር ሙሾ ተወርዶ ሲጨረስ ወይም እየተወረደ እያለ፣ የፋከራ ቃል-ግጥም ጣልቃ ገብቶ ሊከወን እንደሚችልም እ.ኢ.አ. በ26/09/04 በተፈጸመው የአቶ ደባልቄ የቀጠሮ ለቀሶ ላይ ለመመልከት ተችሏል፡፡ ፋከራው ሲጠናቀቅም፣ ከወየታ ወይም ከሙሾ ቃል-ግጥሞች አንዳቸው ሊከውኑ፣ ወይም ሁለቱም ጎን ለጎን ሊካሄዱ እንደሚችሉ፣ ከምልከታዎቹ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ስለሆነም ከላይ ስለለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ክወና ቅደም ተከተል የተነሳው ሀሳብ፣ አጀማመራቸውን መሰረት ያደረገ እንጂ፣ ሙሉ ክወናቸውን ወይም ፍጻሜያቸውን መሰረት ያደረገ እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በዚህ ገለጻ የየዘውጎቹን የየግል ክወና ለማሳየት ሲባል፣ የአንደኛው ክወና ሲቀርብ፣ ሌላኛው የለቅሶ ቃል-ግጥም ጣልቃ የሚገባበትን አጋጣሚ ከመጠቆም ውጭ በየራሳቸው እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡

የክወና ገለጻው፣ ቃል-ግጥሞቹ በተፈጥሯዊ መቸታቸው የሚቀርቡበትን አንጻራዊ ቅደም ተከተል ጠብቆ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን፣ በማንኛውም ለቅሶ ላይ የወየታ ክወና በመጀመሪያ የሚቀርብ በመሆኑ፣ በገለጻውም ቅድሚያ ተሰጥቶታል፡፡ የሙሾና የፋከራ ክወናዎች ተከታትለው የሚቀርቡ ስለሆነ፣ በዚሁ ቅደም ተከተላቸው ከዚህ በታች ተገልጸዋል፡፡

#### 4.2.3.1. የወየታ ክወና

በተጠኚው ማሕበረሰብ ወየታ፣ ጾታ፣ እድሜ፣ ማህበራዊ ደረጃና ቦታ ሳይለይ በስፋት የሚከወን የለቅሶ ቃል-ግጥም መሆኑን ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ ወየታ ለሚከወንላቸው ብቻ ሳይሆን፣ ለከዋኞቹም ጾታ አይለይም፡፡ የወየታ ቃል-ግጥም ለመከወን፣ የግጥም ችሎታ ብቻ ሳይሆን፣ የድምጽ ተሰጥኦም እንደሚያስፈልግ፣ ከመረጃ አቀባዮቹ መካከል አቶ ትእዛዙና አቶ ደሳለኝ ይገልጻሉ፡፡ ምክንያቱም በክወና ወቅት የሚኖረው ድባብ ሀዘን ጎልቶ የሚወጣበት ስለሆነ፣ ከሚችና ከሰው ልጅ ከንቱነት ጋር የተያያዙ ቃል-ግጥሞች በሚያምር ድምጽ ሲከወኑ፣ ሆድ አስብሰውና ስሜት ኮርኩረው እንባ ማስወጣት ስለሚጠበቅባቸው ነው፡፡

ክወናው በአንድ/ዷት ከዋኝ መሪነት፣ በሌሎች ወየ ባዮች፣ በሀዘንተኞችና በለቀስተኞች፣ ተቀባይነት እንደሚካሄድም ለመመልከት ተችሏል፡፡

የወየታ ክወና የሟች ነፍስ ስትወጣ ከሚፈጠረው ቅጥ ያጣና ያልተደራጀ ለቅሶ፣ ወደ ተደራጀ ለቅሶ በሚደረገው ሽግግር እንደሚጀመር፣ ከተካሄዱት ምልከታዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ ሟች ሳይቀበር የሚያድር ከሆነ፣ ምሽት ላይ ከሟች ግቢ ወይም ወጣ ተብሎ መንገድ ላይ በሚካሄድ ለቅሶ ይከወናል፡፡ በጠዋትም የአካባቢው ሰው ከተሰባሰበበት ጊዜ ጀምሮ ሬሳ እስከሚወጣ ድረስ ይቀጥላል፡፡ የጉዞ ፍትሃት በሚካሄድባቸው ቦታዎችና በማርገጃ ላይም እንደዚሁ፡፡

በወየታ ክወና ከዋኝና ሀዘንተኞች አይለያዩም፡፡ ከዋኞቹ ከሀዘንተኞቹ ጋር አብረው እየዞሩ፣ ወይም ክብ ሰርቶ ሀዘንተኞቹን ከከበበው ለቀስተኛ በውስጥ በኩል በረድፍ ቁመው፣ አልፎ አልፎ በእራፊ ጨርቅ የተሸፈነ፣ በአብዛኛው ያልተሸፈነ ዋንጫ ይዘው፣ እየተቀባበሉ በየተራ ‹‹ወየ›› እያሉ ያስለቅሳሉ፡፡ ተረኛው ዋንጫውን ይዞ ግራና ቀኝ እጁን እያወዛወዘ ከግጥሙ ስንኞች ውጭ የሆኑ መሸጋገሪያዎችንና መንደርደሪያዎችን ድምጹን ዘለግ አድርጎ፣ (ለምሳሌ በእሙሀይ አዛለች ለቅሶ ላይ እ.ኢ.አ. በ06/09/10 እንደታየው)፣ ‹‹አወይ … አወይ … እመቤቲቱ›› ብሎ በአሳዛኝ ቅላጼ ይጀምራል፡፡ ሀዘንተኞቹና ለቀስተኛው በአንድ ላይ ‹‹እህ››፣ በማለት በተመሳሳይ ስሜት ይቀበሉታል፡፡ ከዚህ በኋላ፣ ከሟች መልክና ቁመና፣ የአሟሟት ሁኔታ፣ ከሰው ልጅ ከንቱነት፣ ከሟች ሀብት፣ ቀደም ሲል ከሞቱ ዘመዶችና፣ ከዘመኑ ሁኔታ ጋር የተያያዙ ማንጎራጎሪያ ሀረጋትን፣ ሲገጥም ባሰበው የወየታ ግጥም ስንኞች መሃል ጣልቃ እያስገባ ወይም ስንኞቹን እየደጋገመ፣ ከተቀባዮቹ ጋር እየተቀባበለ እንደሚከተለው ያዜማል፡፡

ወየ ባይ፣ · · · ኧኧኧ · · · ኧኧኧ · · · ኧኧኧ · · · ኧኧኧ · · · እመቤቲቱ እመቤቲቱ
ተቀባይ፣ እህ
ወየ ባይ፣ እህ · · · እመቤቲቱ · · · እረግ አስማረ አስረስ (ቀደም ሲል የሞቱ
የሟች ባል)
ተቀባይ፣ እህ
ወየ ባይ፣ እህ ጌትየ ጌትየ እሙሀይ አዛለች
ተቀባይ፣ እህ
ወየ ባይ፣ እህ · · · እሙሀይ አዛለች ቸኮለ · · · ዘላኔ .. ዘላኔ .. ዘላኔ .. ዘላኔ …
ተቀባይ፣ እህ
ወየ ባይ፣ ኸረ ወየ ወየ፣ ኸረ አገሬ ወየ፣ ኸረ እናባ ብሃር፣
ተቀባይ፣ እህ፣
ወየ ባይ፣ እህ ኸረ ወየ ወየ · ·፣ ኸረ ወየ ወየ፣ ·ረ ወየ ወየ፣ አያልነሽ አስማረ (ቀደም
ሲል የሞተች ልጃቸው)

ተቀባይ፣ እህ፣
ወየ ባይ፣ ኸረ ወየ፣ አገሬ ወየ ···፣ እንኳን የበላሽ በላትማ!
ተቀባይ፣ እህ፣
ወየ ባይ፣ እህህ ··· እሙሁይ አዛለች፣ አዛለች ቸኮለ፣
ተቀባይ፣ እህህ፣
ወየ ባይ፣ እህ እናባ ብሃር ···፣ እነ ልጅ አስማረ፣ እረግ አስማረ አስረስ፣
ተቀባ፣ እህ፣
ወየ ባይ፣ እህ ···፣ ያ ደመላሽ አስረስ፣ (ቀደም ሲል የሞቱ የሟች ባል ወንድም)
ተቀባይ፣ እንዷያ!
ወየ ባይ፣ ኸህህ እነ ዝልል ···፣ እሙሁይ አዛለች፣
ተቀባይ፣ እህህ፣
ወየ ባይ፣ እንኳንስ የጠላሽ፣ እንኳንስ የእንጀራሽ በላትማ አንተ! (የወየታ ግጥሙ የመጀመሪያ ስንኝ መነሻ ሀረጋት)
ተቀባይ፣ እህ
ወየ ባይ፣ ኸሽ አይ አገሬዋ፣ እናባ በሃር፣ እናባ ዝልል፣
ተቀባይ፣ እህ፣
ወየ ባይ፣ የጥሬሽ ማዛ አለው፣ ···፣የጥሬሽ ማዛ አለው፣ (የመጀመሪያው ስንኝ መድረሻ ሀረግ)
ተቀባይ፣ እህ፣
ወየ ባይ፣ አዛለች ቸኮለ፣ ወደረኛሽ ማነው; ···፣ (መድፊያ ስንኝ)

ወየ ባዩ የመድፊያ ስንኙን የመጨረሻ ሀረግ ሲያዜም፣ ተቀባዮቹ አብረውት ያዜማሉ፡፡ ከላይ በቀረበው ምሳሌ መሰረት፣ ‹‹ወደረኛሽ ማነው;›› የሚለውን የመድፊያ ስንኙን መድረሻ ሀረግ፣ ከወየ ባዩ ጋር እኩል ሲያዜሙ ተስተውሏል፡፡ በዚህ የመሸጋገሪያ ወቅት ሀዘንተኞቹ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እየተንጫጩ ያለቅሳሉ፡፡



ምሥል አስራ ስድስት፣ በ14/09/04 በዋለው በአቶ አለምነው መንግሥቱ ለቅሶ የወየታ ክወና (ፎቶ በለማ ንጋቱ)

በዚህ የጫጫታ ወቅት፣ ተቀባዩ ወየ ባይ፣ ድምጹን ረዘም አድርጎ፣ ብዙውን ጊዜ፣ ከሱ በፊት የከወነውን ወየ ባይ መድፊያ ሀረግ (በዚህ ክወና መሰረት) ‹‹ወደረኛሽ ማነው;›› የሚለውን ያንጎራጉራል፡፡ አልፎ አልፎ፣ ‹‹ዋ ክንብል ያድርገኝ፣ አየ የሰው ነገር፣ ኧረ እኔን ይብላኝ፣ ኧረ አገሬ ይብላኝ›› ወዘተ. አይነቶቹን የመሸጋገሪያ ሀረጋት እየደጋገመ ወይም የራሱን ግጥም የመጀመሪያ ስንኝ፣ በረዥሙ በሚያሳዝን ቅላጼ እያዜመ፣ ክወናውን ይረከባል፡፡

በዚህ ወቅት ብዙ ጊዜ ወረፋ ያልደረሳቸው ወየ ባዮች ተደራርበው ክወናውን ለመቀበል እኩል የሚጀምሩበት አጋጣሚ መኖሩ ታይቷል፡፡ እንዲህ ሲሆን፣ አንዳንዴ ራሳቸው ተናበው በመከባበር ለአንዱ ከዋኝ ሲለቁ፣ አልፎ አልፎ ለቀስተኛው አንዱን ዝም እንዲል ያደርገዋል፡፡ በጣም አልፎ አልፎ ደግሞ፣ ሁለቱም ቀጥለው ጥሩ ድምጽ ያለው አሸንፎ ሲከውን ተስተውሏል፡፡

በላይኛው መንገድ ተቀባዮቹ «እህ፣ እንዲያ በልማ!፣ እኔ ልጠራ» ወዘተ. በሚሉት ቃላትና ሀረጋት ወየ ባዩን እየተቀበሉት፣ በሚገጥማቸው የወየታ ስንኞች መሀል ከሟች ጋር ዝምድና ያላቸውን ቀደም ሲል የሞቱ ግለሰቦች ስም እየጠራ፣ ስለሟች ደግነት፣ ሀብት፣ ልገሮችና ወይም ሌሎች ተያያዥ ነገሮች እያነሳ ያዜማል፡፡ ራሱ ወደሚያቀርበው ግጥም የመጀመሪያ ስንኝ እየተመለሰና የተጠቀሱትን ማንጎራጎሪያዎች ጣልቃ እያስገባ ሲያዜም ቆይቶ፣ የሁለተኛውን ስንኝ መድረሻ ሀረግ ሲደፋ፣ እንደላይኛው ተቀባዮቹ በሙሉ ድምጻቸውን ከፍ በማድረግ አብረውት ያዜማሉ፡፡

በዚህ ጊዜ በለቀስተኛው ተከበው ከመሃል እየዞሩ ድምጻቸውን አጥፍተው የሚያለቅሱት የሟች የቅርብ ዘመዶች፣ ፍጥነታቸውን ጨምረውና ድምጻቸውን ከፍ አድርገው፣ እጆቻቸውን ግራና ቀኝ በትከሻዎቻቸው ትይዩ ወደፊት ዘርግተው ጎንበስ ቀና እያሉ የሚችን አልባሳት (በተለይ ልጆች ሲሆኑ)፣ ጌጣጌጦችና የማዕረግ መለያ ቁሶች (ለጀግና መሳሪያውን፣ ለመነኮሳት፣ መቁጠሪያቸውንና ቆባቸውን፣ ለካህናት የመጻህፍት ማሕደሮቻቸውንና መስቀሎቻቸውን)፣ እያወዛወዙ ይንጫጫሉ፡፡ ሌላው ወየ ባይ ከላይ እንደተገለጸው፣ ከሱ ቀድሞ ወየ ያለውን ሰው የመድፊያ ሀረግ በመድገም፣ ወይም የመሸጋገሪያ ሀረጋትን ወይም የራሱን ግጥም የመጀመሪያ

ADABA UNIVERSITY LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADABA, ETHIOPIA

ስንኝ በማዜም፣ ወየ ማለት ሲጀምር፣ ሀዘንተኞቹ ድምጻቸውን አጥፍተው እያሰመሰሙ ይዞራሉ። ክወናው በተመሳሳይ መንገድ ይቀጥላል።

በወየታ ክወና ሁለቱም ጾታዎች ወየ በማለትም ሆነ በማጀብ ይሳተፋሉ። ጥሩ ድምጽ ያለው ማንኛውም ሰው በክወናው የሚሳተፍ ሲሆን፣ የመግጠም ችሎታ ኖሮት ድምጽ የሌለው ደግሞ፣ ጥሩ ድምጽ ላለው ግጥም በማቀበል በክወናው እንደሚሳተፍ ከምልከታ መረጃዎቹ ለመረዳት ተችሏል። አንድ ሰው የተለየ ሁኔታ ካልተፈጠረ (የሚከውኑ ሰዎች ቁጥር በጣም አነስተኛ ሁኖ የሚቀበል ካልጠፋ፣ ወይም የከዋኙ ድምጽ በጣም ያማረና ጥሩ የማስለቀስ ችሎታ ያለው ሆኖ፣ በለቀስተኛው እንዲደግም ካልተገፋፋ) በስተቀር፣ አንድ ከዋኝ በአንድ ዙር ወየ የሚለው አንድ ጊዜ ብቻ መሆኑን ለመታዘብ ተችሏል። ከዋኟ ሴት ስትሆን ግን፣ እሷን መንጠቅ እንደነውር ስለሚቆጠር እንድትደግም እንደሚፈቀድላት ወ/ሮ ፈለቁ ከበደ (አባ.2፣ ቁ.31፣ ክፍ.1.2.2.3.1፣ አን.1--6) እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

> አፌን ከከፈትኩ አይቀሙኝም። በወዲያም ያሉት ‹‹ስጣት እንዳትቀማት›› ይላሉ። ያከብሩኛል። ሴት አፏን ስትከፍት በእፍረት ላይ ይመለሳሉ እያሉ ያከብሩናል፤ አይቀሙንም። ወንዱ ነው እስበሱ የሚጋፋ እንጂ፣ ሴት አፏን ስትከፍት አይቀሙም። ወንዶቹ ግን ሁሉም በድፍረት ስለሚነሱ የገፉ ይነጥቃል። ጥሩ ድምጽ ያለውና አሰማሙ ላይ ነቃ ያለው ይቀማል። ቢቀማም ጠብ የለውም። ‹‹ቆይ ፈንታህ ዙሮ ይመጣልሃል›› ይባላል፤ ዋንጫ ይሰጠዋል ተራው ሲደርስ ያወርዳል።

ወየታን ያም ያም እየተቀባበለ ስለሚከውነውም፣ ለወየ ባዮች ክፍያ መፈጸም የተለመደ እንዳልሆነ፣ መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ።

የለቅሶ ቃል-ግጥም በለቅሷቸው ላይ እንዳይከወን ተናዘው ከሚሞቱ አንዳንድ የሀይማኖት ሰዎች ወይም የለቅሶ ቃል-ግጥም እንዳይከወን የሚገዝቱ የሀይማኖት አባቶች ባሉበት ከሚፈጸም የለቅሶ ሥርዓት ውጭ፣ ወየታ ለማንኛውም ሟች እንደሚከወን መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ። በምልከታዎቹ የታየውም ይኸው ነው። ቀጥሎ ደግሞ ቀደም ሲል በዞኑ በስፋት ይከወን የነበረውና በአሁኑ ወቅት በስማዳና በላይ ጋይንት ወረዳዎች በመቅረት ላይ ያለው የሙሾ ክወና ቀርቧል።

4.2.3.2.የሙሾ ክወና

በደቡብ ጎንደር ዞን ስለሙሾ ክወና ታሪካዊ ዳራ ማብራሪያ እንዲሰጡ ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸውና በቡድን ውይይት ከተሳተፉ አዛውንቶች ምላሽ፣ ቀደም ሲል በዞኑ ተመሳሳይ የሙሾ ክወና ሥርዓት እንደነበር ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከደብረታቦር ዙሪያ፣ ብላታ ቀዲሙ ዓለሙ (አባ.2፣ ቁ.24፣ ክፍ.1.2.2.3.2.፣ አን.1-2) ፣ ከስማዳ፣ አቶ ታደለ ሲሳይ (አባ.2፣ ቁ.38፣ ክፍ.1.2.3.2.፣አን.1-2) እንደሚያስረዱት፣ እነሱ በደረሱበት በኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥትና ከዚያም በፊት ሙሾ የሚከወነው በዚሁ ችሎታቸው በሚታወቁ ሴቶች ነበር፡፡ አቶ ጸጋየ ጀንበሬ (አባ.2፣ ቁ.19፣ ክፍ.1.2.3.2.፣ አን.1) ደብረታቦር አካባቢ በየቦታው ሁለት ሁለት ሙሾ አውራጅ ሴቶች እንደነበሩና፣ ትንንሽ ከበሮዎች እየመቱ ያወርዱ እንደነበር የደረሱባቸውን የሁለት ከዋኞች ስም በመጥቀስ ያስረዳሉ፡፡ ከእነዚህና ከሌሎቹም መረጃ አቀባዮች ለመረዳት እንደተቻለውም፣ የሴቶች የሙሾ ክወና የሚከተለውን ይመስል ነበር፡፡

ለቀስተኛው በምስራቅ የቆመው በምእራብ፣ በሰሜን የቆመው በደቡብ ከቆመው ጋር በትይዩ በአራት ማዕዘን ቅርጽ ይሰለፋል፡፡ ሴቶቹ ከመሀል ይገቡና፣ ከአንዱ መስመር ጥግ ጎን ለጎን ቁመው ከበሯቸውን እየመቱ፣ ግጥሙን ሲደረድሩ፣ ከፊት ለፊታቸውና ከኋላቸው ያለው መስመር እየተቀበለ ያረግዳል፡፡ እንዲህ እያወረዱና እያረገዱ ወደፊት ሲሄዱ፣ ከኋላቸው ያለው መስመር ሲከተላቸው፣ ከፊት ለፊት ያለው መስመር በቆመበት እያረገደ ይቀበላቸዋል፡፡ ከፊት ለፊት ካለው መስመር ሲደርሱ፣ በተመሳሳይ ሁኔታ እያረገዱና እያስረገዱ ወደተነሱበት መስመር ይመለሳሉ፡፡ አሁንም ከኋላቸው ያለው መስመር እያረገደ ይከተላቸዋል፡፡ በዚህ መልኩ በአንድ አቅጣጫ ደርሶ መልስ ካስረገዱ በኋላ፣ አቅጣጫቸውን ቀይረው በተመሳሳይ ሁኔታ በደርሶ መልስ እያስረገዱ ያስለቅሱ እንደነበር፣ ለመረዳት ተችሏል፡፡ የከዋኝ ታዳሚ መስተጋብሩም፣ በአውራጅና ተቀባይ ላይ የተመሰረተ እንደነበር፣ መረጃዎቹ ያሳያሉ፡፡

እነዚሁ መረጃ አቀባዮች የክወና ልማዱ ከጥንት አባቶች ሲወርድ የመጣ መሆኑን ገልጸው፣ ከኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት አጋማሽ ጀምሮ ግን፣ ሴቶች ሙሾ ማውረዱን እየተው ወንዶች እየገቡበት እንደመጡ ይጠቁማሉ፡፡ ሁሉም መረጃ አቀባዮች እንደገለጹት፣ በአሁኑ ሰዓት ሴቶች ሙሾ በማውረድም ሆነ በመቀበል አይሳተፉም፡፡ በሙሾ ክወና ቦታም አይገኙም፡፡

ምልከታ በተካሄደባቸው የለቅሶ ሥርዓቶች፣ ሴቶች በክዋኝነትም ሆነ በተቀባይነት ሲሳተፉ አልታዩም።

በሙሾ ክወና ሴቶች በወንዶች ስለተተኩበት ምክንያት ከተጠየቁት ውስጥ፣ አቶ ታደለ ሲሳይ (አባ.2፣ ቁ.38፣ ክፍ.1.2.3.2.፣ አን.4)፣ ሙሾ አውራጇ የሞተውን ሰው ትታ ያልሞተውን ሰው በማንሳቷ በደረሰባት ተግሳጽ በማፈሯ እንደሆነ ሲገልጹ፣ አቶ ጠና ገበያው (አባ.2፣ ቁ.36፣ ክፍ.1.2.3.2፣ አን.3) በፉከራና ቀረርቶ ክወና ሳቢያ ሴቶች ተገፍተው መውጣታቸውን ይገልጻሉ።

እነብላታ ቀዲሙ በፋርጣና በደብረታቦር አካባቢ ሾተል ላቀይ የምትባልና፣ አንዷት ስሟን የማያስታውሷት ሴት፣ እነአባ አቤ በጥናፋ፣ በቆማ፣ በአንዳቤትና በስማዳ፣ እየተዘዋወረች የምታስለቅስ በላይነሽ ወልዱ የምትባልና ስሟን የማያስታውሷት ጓደኛዋ፣ ከበሮ እየመቱ ሙሾ ያወርዱ እንደነበር መግለጻቸው፣ በሙያው ይሳተፉ የነበሩት ሴቶች በቁጥር አነስተኛ እንደነበሩ ስለሚያመለክት፣ በአቶ ታደለ እንደተገለጸው፣ አንዷ የሞተውን ትታ ያልሞተውን በማንሳቷ የሚደርስባት ተግሳጽ፣ በጓደኛዋም ላይ ሀፍረት ስለሚያስከትልና ብቻዋን መከወን ስለማትችል፣ ለሴቶች ከሙሾ መውጣት ምክንያት ሳይሆን አልቀረም ቢባል፣ ምክንያታዊነት ያለው ይመስላል። በሌላ በኩል አባ አቤ ከጣሊያን ጋር ሲዋጉ ለሞቱ አርበኞች ሴቶቹ፦

‹‹አገር እንደመግዛት ወንዝ እንደማስከበር፣

በትከሻው ድንጋ በጎፈሬው አፈር።››፣ እያሉ ሙሾ ያወርዱ እንደነበር መግለጻቸው፣ በጣሊያን ወረራ ወቅት ሴቶች ሙሾ ያወርዱ እንደነበር መጠቆሙና፣ አቶ ጤናው በቀረርቶና በፉከራ ክወና ሴቶች ከሙሾ እንደተገፉ መግለጻቸው፣ በጠላት ወረራ ወቅት በአርበኝነት ለሞቱት ከሙሾ ይልቅ፣ በአንድ በኩል ለቅሷቸው የጀግና ገድል በሚተረክበት በቀረርቶና በፉከራ ክወና እንዲፈጸም የሚገፋፋ መሆኑ፣ በሌላ በኩል አርበኛ ባልሆኑት ሞትም የጠላት ግፍ የፈጠረው ብሶት፣ ሙሾ ከማንጎራጎር ይልቅ ቀረርቶና ፉከራ ለብሶት መተንፈሻነትና ወኔ መቀስቀሻነት በበለጠ መንገድ የሚከወኑበት እድል መስፋትና፣ በቀረርቶና ፉከራ ክወና ሴቶች የማይሳተፉ መሆን፣ ሴቶቹን ከሙሾ ክወናው ጋር የሚገለሉበትን አጋጣሚ ሰፊ ሳያደርገው እንዳልቀረ ለመገመት ይቻላል።

በሁሉም የሙሾ ክወናዎች በቀጥታ የሚሳተፉት፣ መሪ፣ አውራጅና ተቀባይ ሲሆኑ፣ አስተባባሪዎችና ለቀስተኞች በድጋፍ ሰጭነትና በተቀባይነት ይሳተፋሉ። የመሪ ሚና

ለአውራጆቹ የሙሾ ግጥሙን በየሀረጋቱ እየከፈለ መንገርና ከእነሱ ጋር እየተደረበ ማውረድ ነው፡፡ የአውራጆቹ ድርሻ ደግሞ፣ በመሪው የተነገራቸውን የግጥም ሀረግ፣ በአንድ ላይ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በማዜም፣ ለተቀባዮቹ ማስተላለፍ ነው፡፡ ተቀባዮቹ የሙሾውን የዜማ አይነት አዝማች፣ በየሙሾ ግጥሞቹ ሀረጋት መሃል በመደጋገም የሙሾ ክወናውን ያደምቃሉ፡፡ አስተባባሪዎቹ ደግሞ፣ ክብ ከሰራው ለቀስተኛ መሃል ገብተው፣ ከከዋኞቹ ጋር አብረው በማርገድ እያበረታቱ፣ ለቀስተኛውንም እየዞሩ በማነቃቃት ያስለቅሳሉ፡፡ ለቀስተኛው ደግሞ ሙሾውን እየተቀበለ ከማዜምና እያረገደ ክወናውን ከማድመቅ በተጨማሪ፣ የሙሾ መከወኛ ሜዳውን ጎን ለጎን በመቆም በአራት ማዕዘን ቅርጽ ይከልላል፡፡

በሁሉም ሙሾዎች ክወና፣ መሪው፣ ከአውራጁ ቡድን የሚመረጥ ሲሆን፣ አውራጆቹ፣ መሪው የሚገኝባቸው የመጀመሪያዎቹ የሙሾ ቃል-ግጥም ከዋኞች ናቸው፡፡ ተቀባዮቹ ደግሞ፣ ለሙሾ ተመርጠው የገቡት ቡድኖችና ዙሪያውን ከበው ሥርዓቱን የሚያጅቡት ለቀስተኞች ናቸው፡፡ እነዚህ ቡድኖች በሁሉም አይነት ንዑስ የሙሾ ክወናዎች የሚኖራቸው አሰላለፍና ሚና ተመሳሳይ ነው፡፡

ከዋኞቹ እንደሚኖራቸው ቁጥር ከሶስት እስከዘጠኝ በአንድ ቡድን ትክሻ ለትክሻ በመግጠም ወደጎን መስመር ሰርተው ሲሰለፉ፣ አቻ ቁጥር ያለው ቡድን፣ በትይዩ በአራት ማዕዘኑ ሌላኛው ጫፍ በተመሳሳይ አሰላለፍ፣ ፊት ለፊት ይቆማል፡፡ ለማውረድ ከመረጡት የሙሾ ዜማ አይነት (ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ ዋየ፣ ዋየ ዋይ ወየሁ፣ አወየወ ዋይ ዋይ/ ወየሁ እና ዋ/አየ ተለየነ/ያለው ማነው)፣ አንዱን በማዜም ወደክወናው ይገባሉ፡፡ ለምሳሌ ‹‹ዋየ እያሉ ኸዱ ዋየ ዋየ››ን ለማውረድ ቢመርጡ፣ ሁለቱም ይህን እያዜሙ ሲያረግዱ ለቀስተኛው ይቀበላል፡፡ በዚህ መንገድ የክወና ሜዳው ለክወና እስኪመቻችና አጃቢያቸው ከኂላና ከጎን ተሰልፎ በሚገባ መከታተል እስኪችል ድረስ፣ ለማውረድ የተዘጋጁትን የሙሾ አዝማች በአንድ ላይ ደጋግመው ያዜማሉ፡፡

ሁኔታዎች ሥርዓት ይዘው ለክወና ሲመቻቹ፣ የአውራጅነቱን ሚና ለመያዝ የፈለገው ቡድን መሪ፣ አዝማቹን ለአውራጆቹና ለተቀባዮቹ፣ ‹‹ዋየ እያሉ ኸዱ ዋየ ዋየ›› በማለት፣ ድምጹን ከፍ አድርጎ ያወርዳል፡፡ ይህ የሙሾውን መጀመር ጠቋሚ ስለሆነ፣ ሁሉም የሚጠበቅባቸውን በንቃት ለመከወን ይዘጋጃሉ፡፡ ከዚያ ተቀባዩ ቡድን አዝማቹን በሚያዜምበት ቅጽበት፣ መሪው ሊያቀርበው የፈለገውን ግጥም የመጀመሪያ ስንኝ መነሻ ሀረግ፣ ለአውራጆቹ ሹክ ይላቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ አብረው የአዝማች ዜማውን ሲያዜሙ ከቆዩት፣ በመሪው በኩል ያለው ቡድን፣

በመሪው የተነገረውን ሀረግ በማዜም፣ ወደአውራጅነት፣ በተቃራኒ የሚገኘው ቡድን ደግሞ ‹‹ዋየ እያሉ ኸዱ ዋየ ዋየ›› በማለት፣ ወደተቀባይነት ይሸጋገራሉ፡፡ ክወናው ተረጋግቶ መጀመሩን ለማረጋገጥ መሪው አሁንም የመጀመሪያውን ስንኝ መነሻ ሀረግ ለአውራጆቹ፣ ደግሞ ይነግራቸዋል፡፡ እነሱም ያንኑ ሀረግ ተቀብለው ሲያወርዱ፣ ተቀባዮቹ የአዝማች ዜማውን፣ ከለቀስተኛው ጋር አብረው ያዜማሉ፡፡ ከዚህ በኋላ መሪው፣ ተቀባዮቹ የአዝማች ዜማውን በሚያቀርቡበት ቅጽበት፣ ለአውራጆቹ ድምጹን ዝቅ አድርጎ የመጀመሪያውን ስንኝ መድረሻ ሀረግ ይነግራቸውና ከእነሱ ጋር ተደርቦ ያወርዳል፡፡ ተቀባዮቹ አዝማቹን ሲያወርዱ፣ መሪው ሌላውን ሀረግ ለከዋኞቹ እየነገረ አብሮ በማውረድ፣ የሙሾ ክወናው በሚከተለው መንገድ ይካሄዳል፡፡ (ከላይ በምሳሌነት የተመረጠው የሙሾ አይነት በስፋት አገልግሎት ላይ የሚውለው ሲሆን፣ ከዜማ ልዩነት በስተቀር በሌሎቹ የሙሾ ንዑስ አይነቶች ክወና ያለው የመሪ፣ የአውራጅና የተቀባይ ግንኙነት ተመሳሳይ ነው፡፡)

አውራጅ ተቀባይ፣ ዋየ እያሉ ኸዱ ዋየ ዋየ፣ (ቢያንስ ለ5 ጊዜ ያህል ያዜሙታል)
ለቀስተኛ፣ ዋየ እያሉ ኸዱ ዋየ ዋየ፣ (በአውራጅ ተቀባዮቹ የዜማ መጠን ያዜማሉ)
መሪ፣ ዋየ እያሉ ኸዱ ዋየ፣ ዋየ፣
አውራጅ ተቀባይና ለቀስተኛ፣ ዋየ እያሉ ኸዱ ዋየ ዋየ፣
መሪ፣ ኸለይ ይጋገራል፣
ተቀባይ፣ ዋየ እያሉ ኸዱ ዋየ ዋየ፣ (ለቀስተኛና የክወና ተቀባዮች ተመሳሳይ ሚና ይይዛሉ)
መሪ፣ ኸለይ ይጋገራል፣ (ከዋኝና ታዳሚ ሚናቸውን እንዲለዩ ይደግመዋል)
ተቀባይ፣ ዋየ እያሉ ኸዱ ዋየ ዋየ፣
መሪና አውራጅ፣ ኸለይ ይጋገራል፣
ተቀባይ፣ ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ ዋየ፣
መሪ፣ ኸተይ ወጥ ይሰራል፣
ተቀባይ፣ ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ ዋየ፣
መሪና አውራጅ፣ ኸተይ ወጥ ይሰራል፣
ተቀባይ፣ ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ ዋየ፣
መሪ፣ አንድ የሚቀር የለም፣
ተቀባይ፣ ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ ዋየ፣
መሪና አውራጅ፣ አንድ የሚቀር የለም፣

ተቀባይ፣ ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ ዋየ፣

መሪ፣ ይህ ሁሉ ይጠራል፣

ተቀባይ፣ ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ ዋየ፣

መሪና አውራጅ፣ ይህ ሁሉ ይጠራል፡፡

ተቀባይ፣ ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ ዋየ

በዚህ መንገድ አውራጁ ቡድንና ከእርሱ ጀርባ መስመር ሰርቶ የሚያጅበው ለቀስተኛ፣ ከአንዱ የክቡ ጫፍ በመነሳት፣ ከጉልበቱ ሸብረክ ቀና እያለ፣ ከትክሻው ግራና ቀኝ እየዘመመ፣ ወደተቀባዩ ቡድን ስልት ጠብቆ እያረገደ ሲንቀሳቀስ፣ ተቀባዩ ቡድንና ከእሱ ጀርባ መስመር የሰራው ለቀስተኛ፣ በዚያው ስልት እያሸበሸበ በተመሳሳይ ፍጥነት ወደአውራጁ ቡድን ይንቀሳቀሳል*፡፡ መሃል ላይ ሲገናኙ ፊት ለፊት ተጠጋግተው የሙሾውን አዝማች ዜማ በአንድ ላይ፣ ‹‹ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ ዋየ›› በማለት ደጋግመው በጋራ ሲያዜሙ አጅበዋቸው የተንቀሳቀሱት ቡድኖች ከኋላቸው ተሰልፈው ፊት ለፊት እየተያዩ፣ አዝማቹን እየተቀበሉ ያረግዳሉ፡፡ ከከዋኞቹና ተቀባዮቹ ግራና ቀኝ ያሉት ቡድኖች ባሉበት ሁነው እያረገዱ ይቀባላሉ፡፡



ምሥል አስራ ሰባት፣ በ27/09/04 ዓ.ም በዋለው በእሙሃይ አጸዶ ለቅሶ የሙሾ ክወና አውራጁ ቡድን ከተቀባዩ ቡድን ጋር አማካይ ቦታ ላይ ፊት ለፊት ተገናኝቶ የሙሾውን አዝማች በጋራ ሲያወርዱ (ፎቶ በለማ ንጋቱ)

---

* አንዳንዴ ተቀባዩ ቡድን ወደመሃል ሳይንቀሳቀስ በቆመበት እያረገደ አውራጁን ቡድን የሚቀበልበት ሁኔታ አለ፡፡ ተቀባዮቹም ደጋግመው ሲገቡና ሲደክማቸው በድምጽ ሳይቀበሉ ሲያረግዱ ይችላሉ፡፡

አውራጅና ተቀባዮቹ የሙሾውን አዝማች ደጋግመው እያዜሙ ትንሽ እንደ ቆዩ፣ ተቀባዮቹ በሚቀበሉበት ቅጽበት የከዋኙ ቡድን መሪ፣ የአውራጅነት ሚናውን በጋራ እየተወጣ ላለው ቡድን፣ የሚያወርዱትን ሙሾ ግጥም የመጀመሪያ ስንኝ መነሻ ሀረግ ሹክ ይላቸውና አብሮ ያወርዳል፡፡ የመቀበል ሚናውን ለቀስተኛው ይቀጥላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ከአራት እስከድስት የሚደርሱ የሙሾ ቃል-ግጥሞችን ካወረዱ በኋላ፣ ሚና ሊለዋወጡ ሲሉ፣ መሪው ከተቀባዮቹ ተደርቦ የሙሾ አዝማቹን አብሮ ያዜማል፡፡ አምስት ስድስት ጊዜ በጋራ ደጋግመው እንዳዜሙ፣ ተጠጋግተው ከቆሙበት ስፍራ ትንሽ ወደኋላ እያረገዱ ማፌግፌግ ሲጀምሩ፣ ተቀባይ የነበረው ቡድን የአውራጅነት፣ አውራጅ የነበረው ቡድን የተቀባይነት ሚና ይለዋወጣሉ፡፡ ተቀባይ ከነበሩት ቡድኖች ከላይ በተገለጸው መንገድ አንዱ የሙሾ ሀረጋቱን በመንገር እየመራና አብሮ እያወረደ ወደኋላ ሲያፈገፍግ፣ አውራጅ የነበረው ቡድን ከለቀስተኛው ጋር አብሮ እየተቀበለ (ከደከማቸውና ለቀስተኛው ንቁ ከሆነ ሳይቀበሉ ሊያረግዱ ይችላሉ) እንደከዋኙ ቡድን በተመሳሳይ ስልት እያረገደ ወደተነሳበት ስፍራ ይመለሳል፡፡



ምሥል አስራ ስምንት፣ በ27/09/04 ዓ.ም በዋለው በእሙሃይ አጸዪ ስመኝ ለቅሶ በሙሾ ክወና ከዋኙ ቡድን በስተግራ ወደ ተቀባዩ ቡድን እያረገደ ሲሄድ (ፎቶ በለማ ንጋቱ)

ሁለቱንም ቡድኖች ከኋላ አጅበው የሚንቀሳቀሱት ቡድኖች ግራና ቀኝ በረድፍ ከቆሙት ቡድኖች ደርሰው አራት ማዕዘን ሲሰሩ ከዋኙ ቡድን አዲስ ሙሾ ማውጣቱን አቁሞ፣ እንደተቀባዮቹ የሙሾውን አዝማች ያዜማል፡፡ ሁለቱ ቡድኖች አዝማቹን እየተቀባበሉ ትንሽ ከደጋገሙ በኋላ በአንድ ላይ ማውረድ ይጀምራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ የተቀባይነት ሚናውን ሙሉ በሙሉ ያጀባቸው ለቀስተኛ ይወስዳል፡፡ ከደርሶ መልስ የሙሾ ክወና በኋላ፣ አቅጣጫ

ስለሚቀይሩ (የመጀመሪያውን ሙሾ ምስራቅ ምዕራብ ከውነው ከሆነ፣ ሁለተኛውን ሰሜን ደቡብ ስለሚከውኑ)፣ የሙሾ አዝማቹን እያዜሙ ረድፋቸውን እንደጠበቁ እንደመጀመሪያው ክወና፣ ከክቡ ጫፍና ጫፍ በትይዩ ቆመው ተቀባይ የነበረው ቡድን የአውራጅነት ሚናውን ይወስዳል፡፡ አውራጅ የነበረው ቡድን ከለቀስተኛው ጋር ተቀባይ ይሆናል፡፡ ዳር ሁነው ሲቀበሉ የቆዩት ቡድኖች ከዋኝና ተቀባዮቹን ከኋላ አጅቦ ሲንቀሳቀስ፣ አጅበው ሲያረግዱ የነበሩት ቡድኖች በቆሙበት እየተቀበሉ ያረግዳሉ፡፡

ከላይ በተገለጸው መንገድ አውራጅና ተቀባዮቹ ከኋላቸው የተሰለፉትን ቡድኖች አስከትለው እያረገዱ ደርሶ መልስ እንዳወረዱ፣ የሙሾውን አዝማች በጋራ አምስት ስድስት ጊዜ አዚመው የመጀመሪያውን ዙር ክወና ያጠናቅቃሉ፡፡ የመጀመሪያው ዙር የሙሾ ክወና ሲጠናቀቅ የፉከራ ክወና ካለ ይጀመራል፡፡ ከሌለ ለሙሾ ክወናው ሲባል የወጡት ሀዘንተኞች ወደዋናው ክብ ይመለሱና የወየታ ክወና ይቀጥላል፡፡

ሁለተኛው ዙር የሙሾ ክወና ሲጀመር ሀዘንተኞቹና እነሱን ያጀበው ቡድን ዋናውን ክብ ለሙሾ ከዋኞቹ ለቅቆ፣ እልፍ ብሎ ክብ በመስራት በወየታ ቃለ-ግጥም ክወና ለቅሶውን ይቀጥላል፡፡ በዋናው ክብ ደግሞ በአንደኛው ክወና በተገለጸው መንገድና ሥልት፣ የሙሾ ክወናው ይካሄዳል፡፡ እንደሚች ማሕበራዊ ደረጃና እንደሚኖረው የለቅሶ ሥርዓት ማከናወኛ ጊዜ እጥረትና ርዝመት፣ ከአንዴ እስከአምስቴ በተመሳሳይ ሁኔታ እየተወጣና እየተገባ ሲከወን ይቆይና ‹‹ዋ/አየ ተለየነ›› የሚባለው ሙሾ በማሳረጊያነት ይቀርባል፡፡ ከዜማው መለየትና በመጨረሻ ከመቅረቡ በስተቀር፣ በዚህኛው ሙሾ የሚኖረው የመሪ፣ አውራጅና ተቀባይ ግንኙነት ከሌሎቹ ሙሾዎች ክወና የተለየ አይደለም፡፡

በዚህ ሙሾ ክወና መሪው የመምራትና አውራጆቹ በመሪው የሚነገራቸውን የሙሾ ግጥም የማውረድ ሚናቸውን ትተው በአንድ ላይ የሙሾ አዝማቹን ዜማ ማውረድ ሲጀምሩ፣ የሙሾ ክወናው ድምዳሜ ላይ መድረሱን ይጠቁማል፡፡ ከዚህ በኋላ ለተወሰነ ጊዜ መሪና አውራጆቹ ከተቀባዮቹ ጋር እየተቀባበሉ የሙሾ አዝማች ዜማውን ትንሽ እንዳወረዱ፣ ሁለቱ እንደገና በአንድ ላይ ሆነው የሙሾውን አዝማች ሲያዜሙ፣ ዙሪያቸውን የከበበው ለቀስተኛ ይቀበላቸዋል፡፡ ሶስት አራቴ እንደተመላለሱ የሙሾ ክወናው ፍጻሜ ይሆናል፡፡

ከዚህ በላይ የተገለጸው የሙሾ ክወና፣ በፋርጣ፣ በደብረ ታቦር ዙሪያና በፎገራ ወረዳዎች፣ የሚከወን ሲሆን፣ በላይ ጋይንትና በስማዳ ወረዳዎች በአሁኑ ሰዓት በመደበኛነት ሙሾ

አይከወንም፡፡ በተለይ በቀጠሮ ለቅሶ የሚከፈለው አልቃሽ በተገኘበት የሚከወንበት ሁኔታ ቢኖርም፣ አውራጁ ከዳር ቁሞ ግጥሙን ሲደረድር ሀዘንተኞቹና ለቀስተኞቹ የሚቀበሉት ክብ ሰርተው በቆሙበት በድምጽ ብቻ እንጂ፣ ከላይ እንደተገለጸው በእርግዶ ጭምር አይደለም፡፡

በደቡብ ጎንደር ዞን ሙሾ ለሟች የጾታ ልዩነት ሳይደረግበት ቢከወንም፣ እድሜና ማሕበራዊ ደረጃ የክወና ልዩነት ሲፈጥሩ ተስተውሏል፡፡ መረጃ አቀባዮቹ እንደሚያስረዱትና ከምልከታ መረጃው ለመገንዘብ እንደተቻለው፣ እድሜው ለአካለ መጠን ላልደረሰ (ከ18 ዓመት በታች ለሆነ) ሟች፣ ሙሾ አይወረድም፡፡ ለአካለ መጠን ለደረሰ፣ ወገን ላለው፣ ወይም ለታዋቂ አዛውንት፣ እስከአምስት ጊዜ ሙሾ የሚወረድ ሲሆን፣ ወገን ለሌለውና ለተራ ሰው፣ ከሁለት እስከሶስት ጊዜ ይወረድለታል፡፡ ሟች በሥራ ቀን ከሞተ፣ የሙሾ ክወናው በቁጥር ሊቀንስ በቆይታም ሊያጥር የሚችል ሲሆን፣ በአሁኑ ሰዓት በደብረ ታቦር ከተማ በጊዜ እጥረት ምክንያት ክወናው በጣም አጥሮ እንዲቀርብ እየተደረገና እየተተወ መሆኑን ከመረጃ አቀባዮቹና ከተካሄዱት ምልከታዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

ቀጥሎ ደግሞ እንደወየታ ለማንኛውም ሰው፣ እንደሙሾ፣ እድሜውና ማሕበራዊ ደረጃው ለፈቀደለት ሳይሆን፣ በማሕበረሰቡ ጀግና በሚያስብል ስራ ለተሳተፉ የማሕበረሰብ ክፍሎች ብቻ የሚፈጸመው የፉከራ ክወና ቀርቧል፡፡

### 4.2.3.3. የፉከራ ክወና

የፉከራ ክወና በአጀማመር ከወዮታ ወይም ከሙሾ ቀጥሎ በማርገጃ ወይም ለቀጠሮ ለቅሶ በተመረጠ ቦታ እንደሚካሄድ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከመረጃ አቀባዮቹ መካከል ፎካሪ መላሽ ወርቁ (አባ.2፣ ቁ.21፣ ክፍ.1.2.3.3.፣ አን.1) እና አቶ ታከለ ንጋቱ (አባ.2፣ ቁ.13፣ ክፍ.1.2.2.2.3.፣ አን.1-2) እንደሚያስረዱት፣ በጦር ሜዳ ለዋሉ፣ በግብርና ሥራቸው ለተመሰከረላቸው፣ በአዳኝነታቸው ለታወቁ፣ ተሚግተው ለረቱና ሕዝብን በጥሩ ሁኔታ ዳኝተው ላስተዳደሩ፣ ለጀግንነት ያበቋቸው መሳሪያዎች በአካል ተይዘው ወይም በስም እየተጠሩ በለቅሷቸው ላይ ይፎከርላቸዋል፡፡

የሚቀርበው ፉከራ፣ ሟቹ እንደሰራው ጀግንነት አይነት የሚወሰን ሲሆን፣ የሚያዙት መሳሪያዎችም፣ ሟችን ለጀግንነት ካበቃው ጉዳይ ጋር ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ

ሚች አርበኛ ወይም ጦር ሜዳ የዋለ ወታደር ከሆነ፣ አብረው የዘመቱ ጓደኞቹ፣ አብሯደጎቹና ሌሎቹም የሚያውቁት ፎካሪዎች፣ ጠበንጃ፣ ሽጉጥ፣ ጦርና ጋሻ ይዘው፣ ዝናር ታጥቀው፣ የተሸለመ ፈረስ ወይም በቅሎ እያስሳቡና፣ ብዛት ያለው ባንዲራ ከፍ አድርገው እያውለበለቡ፣ ጋቢም ሆነ ኩታ ሳይደርቡ ኮተኛ ሁነው ይሰለፋሉ። ከዚያ አቅራሪው ጉረሮውን ጠረግ፣ ጠረግ አድርጎ፣ መሳሪያ ባልያዘበት እጁ አመልካች ጣት ጆሮውን ወትፎ፣ ‹‹ኧረ ጎራው›› በማለት ድምጹን ሳብ አድርጎ ያቅራራል። አጃቢዎቹ፣ ‹‹እንዲያበል!›› በማለት ጠንከር ባለ ድምጽ ይቀበሉታል። አቅራሪው፣ ፎካሪው ከበቅሎ ላይ ወጥቶ ከሆነ፣ ጎን ለጎን እያጀበ፣ ያለዚያ ግን ከቡድኑ ትንሽ ቀደም ብሎ እየመራ፣ ተቀባዮቹ እየተከተሉ፣ ሰልፍ ይዘው ቆፍጠን ብለው በፍጥነት መዞር ይጀምራሉ። በዚህ ጊዜ የፉከራ ክወና መጀመር ስለሚታወቅ፣ የወየታ ክወናም ሆነ እየተንጫጩ ማልቀስ ይቆምና፣ ለቀስተኛው ክብ ሰርቶ ክወናውን ይታደማል።

መረጃ አቀባዮቹ እንደሚገልጹትና በምልከታም ለማረጋገጥ እንደተቻለው፣ በፉከራ ክወና የሚሳተፉት ወንዶች ብቻ ናቸው። ሴቶች ከመቀበል ውጭ በከዋኝነት ሲሳተፉ አልታዩም። የባህል ተጽእኖም በምክንያትነት ይጠቀሳል። በለቅሷቸው ላይ ግን፣ ለፉከራ የሚያበቃ ሥራ ካላቸው ይፎከርላቸዋል። ለምሳሌ በአርበኝነት ለተሳተፉ፣ ሹም ባሎቻቸውን በሀሳብ ይደግፉ ለነበሩ፣ ከባሎቻቸው ጋር በግብርና ሥራ ተሰልፈው ጠንክረው ከመስራታቸው በተጨማሪ፣ እንግዳ በማስተናገድና በጥሩ የባልትና ችሎታቸው ለሚታወቁ ሴቶችም፣ በተመሳሳይ ሁኔታ እንደሚፎከርላቸው መረጃ አቀባዮቹ ይገልጻሉ። እ.ኢ.አ. በ4/05/06 ስማዳ ወረዳ፣ ምንድቅ ቀበሌ ገበሬ ማሕበር በዋለው የቀጠሮ ለቅሶ፣ ባላቸው ሞተውባቸው ልጆቻቸውን ብቻቸውን አሳድገው በወግ በማዕረግ ለዳሩትና፣ ለቁም ነገር ሳበቁት ለወ/ሮ ያለም ሉላዩ፣ ሲፎከርላቸው ለማየት መቻሉ፣ ለሴቶች እንደሚፎከርላቸው ማስረጃ ይሆናል።

የፉከራ ክወና የሚጀመረው በቀረርቶ መሆኑን ከምልከታ መረጃዎቹ ለመረዳት ተችሏል። በፋርጣ፣ በደብረ ታቦር ዙሪያ፣ በፎገራና በላይ ጋይንት ወረዳዎች፣ አቅራሪው የሽለላውን የመጀመሪያ ስንኝ ሲያቅራራ፣ አጃቢዎቹና ዙሪያውን ከተሰበሰበው ለቀስተኛ መካከል የነሸጠው ‹‹እንዲያ በል!››፣ ወይም ድምጹን ከፍ አድርጎ ‹‹ተው!፣ ተው!፣ ተው!፣ ተው!››፣ በማለት ይቀበላል። አቅራሪው የመጀመሪያውን ስንኝ ከደገመ በኋላ፣ የተቀባዮቹን ምላሽ ተከትሎ የመድፊያ ስንኙን ሲገጥም ተቀባዮቹ፣ እንደወየታው ሁሉ፣ የመድፊያ ስንኙን መድረሻ ሀረግ፣ ድምጻቸውን ዘለግ አድርገው ከአቅራሪው ጋር አብረው ያዜሙታል። የፉከራ ክወናው በአንድ

ቀረርቶ ስለማይደምቅ፣ ሌላ አቅራሪ ወይም የመጀመሪያው አቅራሪ በተመሳሳይ ሁኔታ ሌላ ግጥም አቅራርቶ፣ የመድፊያ ሀረጉን ከተቀባዮቹ ጋር ሲያዜም፣ ፎካሪው ‹‹ዘራፍ! አካኪ ዘራፍ!››፣ በማለት ለሚቹ የሚገባውን የፉከራ አይነት መፎክር ይጀምራል፡፡ አጃቢዎቹ፣ ሀዘንተኞቹና ለቀስተኛው በየስንኞቹ ጣልቃ፣ ‹‹እውነት!›› ወይም ‹‹ይል ነበር!›› እያሉ ይቀበላሉ፡፡

ፎካሪው ከወዲያ ወዲህ እየተሸከረከረ፣ እየተንበረከከ፣ እየተፊነጠረ፣ ደረቱን ገልብጦ ከተከሻው እየተናጠ፣ የሚችን ሥራ በማንሳት፣ ሀይልና ወኔ በተሞላበት ቅላጼ ሲፎክር፣ አጃቢዎቹ ጠበንጃዎቻቸውን እየወደሩ፣ በጋሻቸው እየመከቱ፣ አብረው ወዲና ወዲህ በቁጣ ተሞልተው እያሶመሶሙ፣ ‹‹እውነት!፣ እውነት!›› ይላሉ፡፡ በዙሪያቸው ያለው ሰውም እነሱን እየተከተለ ‹‹እውነት!›› ይላል፡፡ ፎካሪው በበቅሎ ወይም በፈረስ ላይ ወጥቶ የሚፎክር ከሆነ፣ ሌሎች ፈረሰኞች እየጋለቡ ያጅቡታል፡፡ መሳሪያ የያዘው ሰልፈኛ ከፈረስ ላይ የተቀመጠውን ፎካሪ ከስር ከስሩ እየተከተለ ያጅባል፡፡ ሀዘንተኞቹ ከጎንም፣ ከኋላም ተከትለው እየሮጡ በስሜት ተሞልተው ‹‹እውነት!›› እያሉ አብረው ይዞራሉ፡፡ ጥሩ ፎካሪ የሚችን ስራ ስሜት በሚነካ መንገድ ሲያቀርብ ሀዘንተኞቹ፣ ‹‹እልል!›› እስከማለት ይደርሳሉ፡፡

ከሃምሳ አለቃ ጌትነት የቀጠሮ ለቅሶ (በ09/10/04 የዋለ)፣ ለመመመልከት እንደተቻለው፣ የፉከራ ከዋኞቹ በሁለት ተከፍለው ወደጎን መስመር በመስራት፣ ስድስት ሜትር ያህል ራቅ ብለው ፊት ለፊት እየተያዩ፣ አቅራሪውን እየተቀበሉና ቦታ እየተቀያየሩ መሳሪያቸውን ዘቅዝቀው ከተከሻቸው እየተናጡና፣ እየተቁነጠነጡ ትንሽ እንደቆዩ፣ አቅራሪው የመድፊያ ስንኙን መድረሻ ሀረግ ከተቀባዮቹ ጋር ሲያዜም፣ ፎካሪው ‹‹ሀይ ዘራፍ ብሎ ዘራፍ ሲነሳ!››፣ በማለት ፉከራውን ጀመረ፡፡ ተቀባዮቹ፣‹‹ይል ነበር!›› በማለት ተቀበሉት፡፡ ፎካሪው፣ ‹‹ሻምበል ጌትነት የዱር አንበሳ!›› ብሎ የፉከራ ግጥሙን ሲደፋ፣ ተቀባዮቹ ‹‹ይል ነበር!›› እያሉ መቀበላቸውን ቀጥሉ፡፡



ምሥል አስራ ዘጠኝ፣በ9/10/04 ዓ.ም ከዋለው ከ፺ አለቃ ጌቴ የቀጠሮ ለቅሶ ከቀረቡት የፋከራ ክወናዎች ከዋኙ የሚገኝበት ቡድን አሰላለፍ (ፎቶ በለማ ንጋቱ)

ፎካሪው በቀኝ እግሩ ተንበርክኮ፣ ግራ እግሩን ወደፊት አጥፎ፣ መሳሪያውን በቀኝ እጁ ከሰደፉ ላይ በመያዝ በጠርዙ መሬት አስመርኩዞ፣ በግራ እጁ ክንዱን ከግራ ጉልበቱ ላይ አስደግፎ፣ የጠበንጃውን አፈሙዝ ቀና አድርጎ በመያዝ፣ ከትከሻው ግራና ቀኝ እየተናጠ፣ ወደፊትና ወደኋላ አፈፍ መለስ እያለ፣ ኮስተር ብሎ ሀይል በተሞላበት ድምጽ የፋከራ ስንኞቹን ሲደረድር፣ እንደእርሱ ተንበርክከው ወኔ ተላብሰው የሚናጡት ከጎኑና ከፊት ለፊቱ ያሉት አጃቢዎች፣ ወዲያ ወዲህ እየሮጡ ድምጻቸውን አጥፍተው የሚያስቅሱት ሀዘንተኞችና ለቀስተኛው፣ ድምጻቸውን ጠንከር አድርገው እንደከዋኝ አጃቢዎቹ ወኔ ተላብሰው ‹‹ይል ነበር!›› እያሉ ተቀበሉት፡፡ ፎካሪው በዚያው ስሜትና እንቅስቃሴ አንድ ስንኝ በጨረሰ ቁጥር፣ ተቀባዮቹም በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ሁነው ‹‹ይል ነበር!›› እያሉ እየተቀበሉ ፋከራው በሚከተለው መንገድ ቀጠለ፡፡

ፎካሪ፣ ሀይ ዘራፍ ብሎ ዘራፍ ሲነሳ!፣
ተቀባይ፣ ይል ነበር!
ፎካሪ፣ ሻምበል ጌትነት የዱር አንብሳ!
ተቀባይ፣ ይል ነበር!
ፎካሪ፣ አስተጣጠቁ ያለው ከፍ ከፍ!፣
ተቀባይ፣ ይል ነበር!

ፎካሪ፣ ከጠባብ ቦታ የሚለው ከተፍ!

ተቀባይ፣ ይል ነበር!

ፎካሪ፣ ተወለዱ አይቀር ታልቀረ ምጡ!፣

ተቀባይ፣ ይል ነበር!

ፎካሪ፣ እንደ ጌትነት እንደረመጡ!

ተቀባይ፣ ይል ነበር!

ፎካሪው ከተንበረከክበት ተስፈንጥሮ በመነሳት ጠበንጃውን በቀኝ እጁ ዘቅዝቆ ወኔ ተላብሶ እየወገሸ ወደፊት ሲሄድ፣ አብረውት የተሰለፉትና ከፊት ለፊት የሚገኙት ተቀባዮች በተመሳሳይ ሁኔታ ተነስተው ቦታ ተቀያየሩ። ፎካሪው እንደመጀመሪያው ተንበርክኮ ከትከሻው እየተናጠ ሲፎክር፣ ተቀባዮቹም በተመሳሳይ ሁኔታ ተንበርክከው በጋለ ስሜት መቀበሉን ቀጠሉ።

ፎካሪ፣ ከዚህም አይደል ውጋዴ ምላሽ!፣

ተቀባይ፣ ይል ነበር!

ፎካሪ፣ ጠላቱን ገዳይ በጊዜ ድራሽ!

ተቀባይ፣ ይል ነበር!

ፎካሪ፣ አይወረወር የሳት አለሎ!፣

ተቀባይ፣ ይል ነበር!

ፎካሪ፣ አይቆረጠም የድንጋ ቆሎ!

ተቀባይ፣ ይል ነበር!

ፈካሪ፣ አስተጣጠቁ እንደ ወይዘሮ!፣

ተቀባይ፣ ይል ነበር!

ፎካሪ፣ ጠላት ሲመጣ ያፍቃል ዙሮ!

ተቀባይ፣ ይል ነበር!

ፎካሪ፣ ሻምበል ጌትነት ሻምበል ምስጋናው!፣

ተቀባይ፣ ይል ነበር!

ፎካሪ.፣ ዘር አለባቸው እንደ ንስናሽ!

ተቀባይ፣ ይል ነበር!

ፎካሪ፣ ሀብታቸው ትልቅ እድሜያቸው ትንሽ!

ተቀባይ፣ ይል ነበር!

...

የፉከራ ሥርዓቱ በዚህ መንገድ ይቀጥላል፡፡

መረጃ አቀባዮቹ እንደሚገልጹትና በምልከታም እንደተረጋገጠው፣ ፎካሪው ግጥም ሲያልቅበት ወይም ሲደናገረው፣ ከተቀባዮቹ መካከል አንዱ ፈጠን ብሎ ክወናውን ተረክቦ ወይም ነጥቆ ይወስዳል፡፡ እሱንም በተመሳሳይ ሁኔታ ሌሎች ይተኩታል፡፡ ፎካሪው እውቅና ያለው ከሆነ ግን፣ ቢደናገረው ያበረታቱታል እንጂ አይነጥቁትም፡፡ ግጥም ሲጨርስ ሲልም፣ በቀረርቶ ሲያሳርፉት እንጂ፣ ከእሱ ላይ ተደርበው ለመፎከር ሲደፍሩ አልታዩም፡፡

ሁለቱ የሥነቃል ዘሮች በዚህ መንገድ እየተደጋገፉ ሲቀርቡ፣ ሚች ወገንና ሀብት ያለው ከሆነ፣ ከሌላ ቦታ ታዋቂ ፎካሪዎች በክፍያ እንዲመጡ ስለሚደረግ፣ የፉከራ ክወናው ይበልጥ ሥርዓቱን የጠበቀና የደመቀ ይሆናል፡፡ ፎካሪዎቹ የተሸለመ ፈረስ ወይም በቅሎ ላይ ወጥተው፣ በክቡ መሀል እየዞሩ፣ ከኮርቻው ላይ ቁጭ ብድግ እያሉና ከተከሻቸው ግራና ቀኝ እየተናጡ፣ በጋለ ስሜት ይፎክራሉ፡፡ አቅራሪውና ተቀባዩ ከበቅሎው ጎን ጎን፣ ሀዘንተኞቹ ኋላ ኋላ እየተከተሉ ከላይ በተገለጸው መንገድ እነሱም በተመሳሳይ ስሜት ይቀበላሉ፡፡ በእንዲህ አይነቱ የፉከራ ክወና እንደሚቹ የጦር ሜዳ ውሎ ከቅርብም ከሩቅም ያለው ታሪክ ይነሳል፡፡ አንድ ስሙ ያልታወቀ ከዋኝ (ክፍ.1.2.3.3.፣ አን፣1-3) ሃምሳ አለቃ ጌትነት የዘመናዊ ጦር አባል በመሆናቸው፣ ሲፎክርላቸው፣ በአርበኞች ለቅሶ ላይም ከጣሊያን ጋር የተካሄደውን የአርበኝነት የጦር ሜዳ ውሎ ትዕይንት የሚያሳዩ ፉከራዎች እንደሚቀርቡ ፎካሪ ሞላ አየሁ (አባ.2.፣ቁ.21፣ ክፍ.1.2.3.3.፣አን.1-2) ያስረዳሉ፡፡

በእነዚህ ፉከራዎች ከዋኙ የጦርሜዳውን ድባብና የጀግናውን ገድል በምናቡ ስሎ በሚጠቀማቸው ገላጭ ቃላት እዚያ ውስጥ ሁኖ እየተደረገ ያለውን ትንቅንቅ በእልህና በወኔ በፈጣን እንቅስቃሴ የሚያቀርበው ስዕላዊ ትረካ፣ ታዳሚውን የምዕናባዊ ድርጊቱ ተሳታፊ ስለሚያደርገው የሚኖረው አጠቃላይ የክወና ድባብ ቁጣ፣ እልህና ወኔ የተሞላበት ነው፡፡ በክወና ድባቡ ሞቱ ከሚፈጥረው ሀዘን ይልቅ፣ ገድሉ የሚቀሰቅሰው መነቃቃትና ደስታ ጎልቶ ይነበባል፡፡

በፉከራ ክወናም እንደሙሾና ወየታ ቃል-ግጥሞች፣ የሟች ቀደም ሲል የሞቱ ጀግና ዘመዶች ይነሳሉ። ከሁለቱ የቃል-ግጥም ዘሮች በተለየ፣ በተለያዩ ወረዳዎች የነበሩ ታዋቂ አርበኞች ስም እየተጠቀሰ ይፎከራል። አቶ ዳምጤ ፈረደ (አባ.2፣ ቁ.8.፣ ክፍ.1.2.3.3.፣አን.1)፣ በደቡብ ጎንደር ዞንና በአጎራባች ቦታዎች፣ በጣሊያን ወረራ ዘመን በተካሄዱት ጦርነቶች፣ ትልቅ ስም የነበራቸውን አርበኞች በስም እየጠሩ ቁጭት በተሞላበት ቅላጼ ያቀረቡት የፉከራ ግጥም፣ ለዚህ ጥሩ ማስረጃ ይሆናል።

በደቡብ ጎንደር ዞን በአርበኝነትና በውትድርና ውሏቸው ከተመሰከረላቸው ጀግኖች በተጨማሪ፣ በግብርና ሥራቸው ጀግና ለተባሉ አርሶ አደሮችም እንደሚፎከር በመግቢያው ተገልጿል። አቶ ወንዳያ እንደሚያስረዱት፣ ለጀግና ገበሬዎች የሚቀርበው ፉከራ ለአርበኞቹ ከሚቀርበው የሚለየው፣ ቀደም ባለው ጊዜ በፉከራ ክወናው ላይ የሟች የራሱ ካልሆነ በስተቀር መሳሪያ የማይያዝና፣ በቅሎም የማይጫንለት መሆኑ ነው። ፎካሪው፣ ስለሟች ዝናብ ሳይፈራ፣ ቁር ሳይበግረው በጠዋት ወጥቶ በምሽት ገብቶ ስለመስራቱ፣ ብዙ ምርት ስለማምረቱ፣ ስለብዙ ከብትና ቀፎ ባለቤትነቱ፣ ስለእንግዳ ተቀባይነቱ፣ ለተራብ ስለማብላቱ፣ ለተቸገረ ስለማበደሩ፣ ወገኑን ይዞ የሚበላ ለጋስ ስለመሆኑ፣ እያነሳ ከመፎከር ውጭ፣ ‹‹እዚህ ቦታ ገዳይ›› ብሎ መፎከር አይፈቀድለትም። ስለሆነም አጠቃላይ ድባቡ እልህና ቁጭት ያልተቀላቀለበት ሙገሳ የሰፈነበት ነው። ከዚህ ውጭ ያለው የከዋኝ ተቀባይ ግንኙነት፣ ለአርበኞች ከሚፈጸመው ክወና ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው ለመረዳት ተችሏል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ለገበሬም የተሸለመ በቅሎ ወይም ፈረስ እየቀረበ መሆኑንና ፎካሪዎችም በቅሎ ላይ ወጥተው መፎከር መጀመራቸውን፣ ከመረጃ አቀባዮቹና ከምልከታ መረጃዎቹ ለመገንዘብ ተችሏል።



ምሥል ሀያ፣ በ8/10./04 ዓ.ም በዋለው በወ.ሮ ጸሀይ እንግዳየሁ ለቅሶ ቀሚስ ለብሰው የዋሉ ፈረሶች (ፎቶ በለማ ንጋቱ)

እንደአርበኞቹ ሁሉ፣ ለገበሬም በጥቅልና በተናጠል እንደሚፎክርለት፣ የተሰበሰቡት መረጃዎች ያሳያሉ። ፎካሪ ሞላ አየሁ (አባ.2. ፣ቁ.21፣ ክፍ.1.2.3.3.፣አን.3)፣ በማንኛውም ጀግና ገበሬ ለቅሶ ላይ፡-

ፎካሪ፣ ደህናው ገበሬ እውቀት ያለው፣
ተቀባይ፣ እውነት!
ፎካሪ፣ ያለ ጥረጨው* ሁሉን ዘራው።
ተቀባይ፣ እውነት!
ፎካሪ፣ ገበሬ ዓለሙ፣
ተቀባይ፣ እውነት!
ፎካሪ፣ ካማጋው** ብኸድ በሬና ላሙ፣
ተቀባይ፣ እውነት!
ፎካሪ፣ ከቤት ብገባ ቅቤና ማሩ፣
ተቀባይ፣ እውነት!
ፎካሪ፣ ኸገበሬ ቤት ብገባበት፣
ተቀባይ፣ እውነት!
ፎካሪ፣ አቅርቦ ሰጠኝ እኔ እንዳልኩት።
ተቀባይ፣ እውነት!
ፎካሪ፣ እኔ ገበሬን እወደዋለሁ፣
ተቀባይ፣ እውነት!
ፎካሪ፣ ገንቦ አዘንብሎ አግኝቸዋለሁ።
ተቀባይ፣ እውነት!
ፎካሪ፣ የገበሬ ሚስት የታደለችው፣
ተቀባይ፣ እውነት!
ፎካሪ፣ እያቀረበች ሁሉን ሰጠችው።
ተቀባይ፣ እውነት!

በማለት ሀብቱንና ልግሥናውን እያነሱ እንደሚፎክሩ ያስረዳሉ።

---

* የምግብ ጨው
** የከብቶች ማገጃ ቦታ

እንደአርበኞቹ ሁሉ ለገበሬም በጥቅል ብቻ ሳይሆን በስም ተጠርቶ እንደሚፎከር አቶ ደጀን አመኑ (አባ.2፣ ቁ.17፣ ክፍ.1.2.3.3.፣አን.1) እ.ኢ.አ. ግንቦት 18/1997 ተቀብረው፣ ታኅሳስ 18/1998 የቀጠሮ ለቅሷቸው ተደግሶ ከተፈጸመላቸው ከአቶ አመን ሽፈራው ለቅሶ ላይ ከቀረቡት የፉከራ ግጥሞች መካከል ጠቅሰው ያስረዳሉ።

በስማዳ ወረዳ የቀጠሮ ለቅሶ ስፊ ዝግጅት ተደርጎ የሚካሄድ በመሆኑ፣ ገንዘብ የሚከፈላቸው ፎካሪዎች ይሳተፋሉ። በዚህ ወረዳ ጥናቱ ከተካሄደባቸው በዞኑ ከሚገኙ ሌሎቹ ወረዳዎች ለየት ያለ የቀረርቶ አይነት ያለ መሆኑና በክወናውም መጠነኛ ልዩነት የሚታይ መሆኑን በቦታው ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል። በዚህ ወረዳ ከፉከራ በፊት አዝማሪዎች ማሲንቆ እየመቱ በርከት ያሉ የቀረርቶ ቃል-ግጥሞችን በአሳዛኝ ቅላጼ እንደሚደረድሩ፣ የተሰበሰቡት መረጃዎች ያሳያሉ። ከአቶ አመኑ የቀጠሮ ለቅሶ ላይ ከቀረበው የሁለት አዝማሪዎች ቀረርቶ ለመረዳት እንደተቻለው፣ በዚህ ወረዳ ቀረርቶ፣ እንደፎገራ፣ ደብረታቦር ዙሪያ፣ ፋርጣና ላይ ጋይንት ወረዳዎች፣ ለፉከራ ማጀቢያነት ብቻ ሳይሆን፣ ራሱን ችሎ ለሀዘን መግለጫነት የሚከወን ይመስላል። የሚከተለው በ18/04/1998 ስማዳ ወረዳ በማሲንቆ ታጅቦ የቀረበ የቀረርቶ ክወና ይህንኑ ሃሳብ ያጠናክራል።

አቅራሪ፣ አለቁ ቦታው ክፍት አደረ ጀግኖቹም አለቁ፣
አለቁ እን እእእ ኧረ እሪ በል ወንዱ እእእ አየ ጉድ እእእ አመኑ አባ አበጋዝ፣
ተቀባይ፣ ኸኸ! (አመኑ አባ ደራ በለው!)
አቅራሪ፣ እህ እእእ አየ ጉድ እእእ የኔው ነገር ወዲያ ወዲያ እኔን ይብላኝ፣
ተቀባይ፣ እኸ!
አቅራሪ፣ እህ አመኑ አባ በሃር እእእ የኛው ነገር ወዲያ፣
　　አየ ጉድ አመኑ አባ በሃር እነ አምሳ አለቃ ታደሰ በላቸው፣
　　አየ ጉድ እእ ወንድማማች በሬ አርሶ የታከተው፣
　　እህትማማች ላም አልቦ የታከተው፣
　　አየ ጉድ እን እእእ፣
　ጥንድ ጥንድ ሙክት የሚገጠግጠው፣
ተቀባይ፣ አሀ!
አቅራሪ፣ ኑሮን እንዳመኑ አድርጎ ነው መተው፤ አድርጎ ነው መተው!

እ ድ ድድ ድድ፣እእ

የአባ በሀር ልጆች እእእ አመኑ አባ በሃር ወዲያ ወዲያ፣

በነነጋ መሞት፣ በታደሰ መሞት፣ በመኮነን መሞት፣

በዘውዳለም መሞት፣ በማሪቱ መሞት፣ ተቆርቁረው ሳለ ተቆርቁረው ሳለ፣

ተቀባይ፣ እህ!

አቅራሪ፣ አየ ጉድ እእእ አመኑ ሲሞት አንዳርጌ ምን አለ?

አገሩ ምን አለ?

ተቀባይ፣ እኸ!

አቅራሪ፣ አየ ጉድ እእእ እኔስ የገረመኝ የልገሮች ዝምታ ያገሩ ዝምታ፣

እእእ የነ አመኑ ቤት ገበያው ሲፈታ፤

እእእ እእእ አመኑ አባ ሙላት እእእ፣ አየ ጉድ አየ ጉድ፣ አየ ጉድ አገሬ፣

ከተቀባዮቹ (አንዱ ግጥም ለአዝማሪው መንገር ጀመረ)

አቅራሪ፣ አይ እእእ አገሩ እስተ ጋይንት እእእ አመኑ አባ ብሃር፣

እእእ አገሩ እስተጋይንት ከጅባ ደንበር ከጅባ ደንበር፣

እን እእእ አየ ጉድ አየጉድ አመኑ አባ ብሃር፣

ቤቱ ከጎድጓዳው ኸገደሉ ስር፣

ጠበንጃው ምንሽር ሰውየው ነብር፣

ማነው ያለ ሠዓት በዛች የሚዞር።

ይል ነበር! ወዲያ… ወዲያ… ወዲያ… (ፎካሪ ገባ)

አቅራሪው ይህን ረዘም ያለ ቀረርቶ ሲከውን፣ በሌሎቹ በጥናቱ በተካተቱ ወረዳዎች የቀረርቶ ክወና እንደታየው፣ በፈጣን አካላዊ እንቅስቃሴና በስሜት እየደነፋ ሳይሆን ማሲንቆውን እየገዘገዘ በቆመበት፣ ከወኔ ቀስቃሽነቱ ይልቅ አሳዛኝነቱ ጎልቶ በሚሰማ ቅላጼ ነው። በየስንኞቹ መጨረሻም አጃቢዎቹ አይቀበሉትም። በእነሱ ፋንታ ማሲንቆውን እንደመሸጋገሪያ ሲጠቀምበት ተስተውሏል። እንዲሁም የዚህን ቀረርቶ ክወና ከሌሎቹ ወረዳዎች ለየት የሚያደርገው፣ በማሲንቆ ታጅቦ መቅረቡና፣ ረዥምም መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ አቅራሪው የመድፊያ ስንኞቹን መድረሻ ሀረግ ሲያዜም፣ አጃቢዎቹና ታዳሚው አብረውት የማያዜሙ መሆናቸው ጭምር

ነው። ፎካሪውም በመድፊያ ሀረጉ ዜማ ላይ ተደርቦ ሳይሆን፣ አቅራሪው ዜማውን ከጨረሰ በኋላ ሲጀምር ተስተውሏል።

በተጨማሪም በዚህ ወረዳ፣ በሌሎቹ በጥናቱ በተካተቱት ወረዳዎች ያልታየና ከላይ ከተጠቀሰውም ቀረርቶ፣ በዜማውም ሆነ በከዋኝ ታዳሚ መስተጋብሩ ለየት ያለ የቀረርቶ አይነት ያለ መሆኑን ከላይ በተጠቀሰው ቀን ከዋለው የቀጠሮ ለቅሶ ከቀረበው ክወና ለማየት ተችሏል። ይህ ቀረርቶ፣ ከዋኙ ድምጹን ለስለስ አድርጎ በማሲንቆው ቅኝት እያዋዛ የሚያቀርበው እንጉርጉሮ መሰል ቀረርቶ ሲሆን፣ ተቀባዮቹ በማሲንቆ ተተክተው፣ እንደሚከተለው አቅራሪው ብቻ የሚከውንበት መሆኑን ለማስተዋል ተችሏል።

ያ ደሳለኝ ብሩ የበለሳው በሬ ግራዝማይ ተብሎ፣
ቀኛዝማች ተብሎ ግራ ዝማች ተብሎ የልቡ ባይደርስ፣
ያመርት አልነበረ በአንድ አውድማ ሙቶ አቅማዳ ገብስ።
ተኝቶ ይመስላል እንደበሬው አመን፣
ያምትኩ በላይ የነካሴ ወንድም፣
ተኝቷል መሰለኝ ያርማጭሆው በሬ የበለሳው በሬ፣
ካራውን* አምጡ ይመተርበት፣
ገበታውን አምጡ ይፈትፈትበት፣
ማርና ሥጋውን የበላንበት።
በለሳ አርመጭሆ በሽንብራ ቆሎ የዘመተው፣
አመን እንዴት አደረከው።
አለቅልቁ ዋንጫ ብርሌውን አንሱ፣
ለካ ሙቶ ነው ወይ ልገሮቹ ሲደርሱ።
እነ ነጋ ቀሩ፣ እነ አጅሬ ቀሩ፣ ቀሩ... ቀሩ... ቀሩ፣
እነ አበራ ቀሩ፣ አምሳ አለቃ ታዬ፣ እነ ቢተው ቀሩ፣
ያ ጅሬማ ልጆች፣ የቢተውስ ልጆች፣ ያመኑማ ልጆች፣
የነነጋ ልጆች፣ የነአጅሬ ልጆች፣ የመኮንን ልጅች፣ የነዘውዴ ልጆች፣የነብሩ ልጆች፣
እንግዲያው እም ... እም ነው፣

---

* ቢለዋውን

እንግዲህ ታይ ጋይንት፣ መመኪያችን ታዴ ቀርቷል በጠዋት፣
አገራችን ወዲያ ይማም አባ በሀር፣ ገስጥ አባ በሀር፣
እንደአፈረ ዋናት እንደውዶው ደንበር፣
አመን ያንተ ቤትስ መገናኛ ነበር፡፡
እንኳን የወገንህ እንኳን የዘመዱ፣
እንቦንጭ እንቦጭ አለ የበሬውም ሆዱ፣
‹ምን ይበጀኝ› ብሎ ገለባና ጭዱ፡፡

አቅራሪው ይህን በማሲንቆ የታጀበ ወደእንጉርጉሮነት የተጠጋ ቀረርቶ አዚሞ ሲጨርስ፣ ሌላ ፎካሪ ገብቶ ተቀባዮቹ ከላይ በተገለጸው መንገድ እየተቀበሉት ፉከራው ይቀጥላል፡፡

በስማዳ ወረዳ የቀጠሮ ለቅሶ፣ ከቀረርቶና ፉከራ ጋር በተያያዘ ሌላው የሚታይ ልዩነት፣ ከክወና ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በዚህ ወረዳ ለቀስተኛው በሰፊ ሜዳ ላይ ሰፊ ክብ ሰርቶ ይቆምና፣ ከክቡ መሃል በርካታ ሰው ይሰበሰባል፡፡ ዙሪያውን በዛ ያለ ባንዲራ ተይዞ ይውለበለባል፡፡ የተከፈላቸው ፎካሪዎች በተሸለሙ ፈረሶች ላይ ተቀምጠው፣ ተረኛው ከኮርቻው ላይ አፈፍ ቁጭ እያለ እየፎከረ ሜዳውን በከበበውና መሀል ላይ ባለው ሰው መሃል ከግራ ወደቀኝ ሲዞር፣ ሀዘንተኞቹና ተቀባዮቹ ከኋላው እየሮጡ፣ ‹‹እውነት ነው!›› እያሉ ይቀበላሉ፡፡ ፎካሪው የሟቹን ሥራ በጥሩ ሁኔታ የሚያወሳ ስንኝ ሲደረድር፣ ሀዘንተኞቹ ‹‹እልል!›› ይላሉ፡፡ ሌሎች የለቅሶ አድማቂ ፈረሰኞች፣ ከፎካሪው ቡድን በውጭና፣ ክብ ከሰራው ለቀስተኛ መሃል፣ የተሸለሙ ፈረሶቻቸውን ሽምጥ እየጋለቡ፣ ዙሪያውን ይዞራሉ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተከለከለ ቢሆንም ጥይትም ይተኮሳል፡፡

በዚህ ወረዳ በቀጠሮ ለቅሶ፣ አብዛኛውን የለቅሶ ሥርዓት የሚሸፍነው የፉከራ ክወና መሆኑን ከምልከታ መረጃዎቹ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከዋኞቹ ሲዳከሙና ሰዓቱ ሲገፋ ፉከራው እንዲቆም ይደረግና የሟች የሕይወት ታሪክ ይነበባል፡፡ አንባቢው የሟችን ታሪክ እየዘረዘረ ‹‹እንዲህ አድርገዋል›› ወይም ‹‹ከዚህ ተዋግተዋል›› ሲል፣ በዙሪያው ያለው ለቀስተኛና ሀዘንተኞቹ እንደፉከራው ክወና ‹‹እውነት ነው!›› እያሉ ይቀበላሉ፡፡ ከዚያ ለቀስተኛው ሰብሰብ ብሎ የተከፈለው አልቃሽ ሙሾ ማውረድ ሲጀምር፣ የፉከራ ሥርዓቱ ሙሉ በሙሉ ይጠናቀቃል፡፡

በዞኑ ከጦር ሰውና ከጀግና ገበሬ በተጨማሪ፣ አዳኝ ሲሞትም ከአርበኛ ተቀራራቢ በሆነ መንገድ እንደሚፎከርለት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እንደአርበኞቹ ‹‹ከዚህ ቦታ ገዳይ፣ ከዚህ ማራኪ›› ባይባልለትም፣ የገደላቸው የዱር እንስሳት እየተዘረዘሩ፣ የሀይለኞቹ ቆዳ ተይዞ ስማቸው እየተጠራ፣ ‹‹ይህን ገዳይ፣ ይህን ገዳይ!››፣ እየተባለ እንደሚፎከርለት ከስማዳ ወረዳ አቶ ብርሃንና ከፋርጣ ወረዳ አቶ ሞላ ያስረዳሉ፡፡ አቶ ሞላ አየሁ (አባ.2.፣ቁ.9)፣ ያዛቸው ጠጋዬ ለሚባል የፋርጣ ወረዳ ነዋሪና በአዳኝነቱ ለተመሰከረለት ጀግናም፡-

ኸተኮሱ አይቀር እንደያዜ ነው፣
ወይም አንገቷን ወይም ወርቿን ነው፣
አሰቴም እንደሁ ይታይ ቆዳው፣
የበጉ ሳይሆን የድኩላው፡፡
በብሎት ትቶ በጦም ታልመጣ፣
ኸነ ያዜ ቤት አያጣም ቋንጣ፡፡
ኧረ ተው ያዜ አብላኝ ዱለት፣
እንዲህ በድንገት ለሚቀር ቤት፡፡

ብለው መፎከራቸውን ይገልጻሉ፡፡

መረጃ በተሰበሰበባቸው ወረዳዎች ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው መረጃ አቀባዮች በጋራ እንደሚገልጹት፣ በሁሉም ወረዳዎች፣ በጦር ሜዳ፣ በአደንና በግብርና ከታወቁ ጀግኖች በተጨማሪ፣ ሕዝብን በጥሩ ሁኔታ በማስተዳደር ለሚታወቁ ሹማምንትና፣ በተሚጋችነታቸው ለተመሰከረላቸው ጀግኖችም ይፎከራል፡፡ በሹም ፉከራ ክወና ላይ ቀጥሎ እንደተገለጸው ማዕረጉን የሚጠቁሙ ድርጊቶች ይስተዋላሉ፡፡

አቶ ገቢያው እንደሚገልጹት፣ ባለ ማዕረግ ሹም ሲሞት እንደማዕረጉ በቅሎ ቀሚስ ተሸልሞ፣ በርኖስና ለምድ ተለብሶ፣ በርካታ ባንዲራዎች ተይዘው ይዞራል፡፡ አገልጋዮችም ግምጃ የለበሰ ገንቦና ሞሶብ ተሸክመው፣ ከሀዘንተኞቹ ኋላ ኋላ እየተከተሉ አብረው ይዞራሉ፡፡ ፎካሪዎችና አቅራሪዎች በአለባበስና በመሳሪያ አያያዝ ለአርበኛ እንደሚያደርጉት ለብሰውና ይዘው እየዞሩ ይፎክራሉ፡፡ ሟች በአስተዳደር ዘመኑ ለአካባቢው ያበረከታቸው አስተዋጾዎች፣ ፍርድ አሰጣጡ፣ የአደባባይ ውሎው፣ እየተጠቀሰ ይፎከርለታል፡፡ ተቀባዮቹም ‹‹እውነት!››፣ እያሉ ያጅባሉ፡፡

ከግጥሞቹ ይዘት ውጭ፣ በከዋኝ ታዳሚ መካከል የሚታየው መስተጋብርና እንቅስቃሴ፣ ለጦር ሜዳ ወይም ለግብርና ጀግኖቹ ሲፎከር ከሚኖረው የተለየ አለመሆኑንም ይገልጻሉ፡፡

ጥናቱ በተካሄደበት ማሕበረሰብ፣ ከጦር ሜዳና ከግብርና ጀግኖች ባልተናነሰ ክብር ተሰጧቸው ከሚፎከርላቸው የማሕበረሰብ ክፍሎች ውስጥ፣ ተሚጋቾች እንደሚገኙበት የተሰበሰቡት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከስሶ መርታት፣ ፍርድ በይግባኝ ማስሻርና፣ ለግልም ሆነ ለአገር የጋራ ጥቅም መሟገት፣ ክብር የሚያሰጡ ድርጊቶች መሆናቸውን፣ አቶ ዋለ፣ አቶ ምህረትና አቶ ሞላ ይገልጻሉ፡፡ ከግጥሞቹ ይዘትና ከሚያዙት መሳሪያዎች ውጭ፣ በከዋኝና ታዳሚው መካከል ያለው ግንኙነት፣ ለአርበኛ፣ ለጀግና ለገበሬና ለአዳኝ፣ ከሚቀርበው ክወና የተለየ አለመሆኑንም መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ፡፡ የሚከተለው የፉከራ ግጥም ፋርጣ ወረዳ ውስጥ እ.ኢ.አ. በ2001 ገላየ ክብረቴ በተባሉ ተሚጋች ለቅሶ ላይ ከቀረቡት ፉከራዎች የተወሰደ ነው፡፡

ፎካሪ፣ ከመስሪያ ቤት ላይ ገዳይ በግራው፣  
(ተቀባይ በየስንኞቹ መጨረሻ ‹‹እውነት!›› ይላል፡፡)  
የሚያስቸግረው ለባላንጋራው፡፡  
ገዳይ በኮቢ[*] በትንሽቱ፣  
በሞጥሚጣይቱ ባፈ ሹሊቱ፣  
ሌባው ቀጣፊው በማይወዳቱ፣  
ገሎ ይመጣል ያዜ አንድ የናቱ፡፡  
እሪ በል አገር እሪ በል ወንዙ፣  
ገላየ ክብረቴ ወድቋል ጎበዙ፡፡  
መስሪያ ቤት ገብቶ አይ አጣጣፉ፣  
ጠላት በይግባኝ ይደፋል ባፉ!  
ይቦት ነው እንጂ ይህ መናጢ ሞት፣  
ይቀርኝ ነበር የሙግቱ ለት;  
በደብረታቦር የረታበቱ፣  
በአዲስ አበባ የረታበቱ፣  
በጎንደር ህዶ የረታበቱ፣

---

[*] መጻፊያ እስክርፒቶ

በክልል ገብቶ የረታበቱ፣
ውሳኔ አገኘ ዛሬ ከቤቱ፤
ከውሳኔው ላይ ከወረቀቱ፣
ገላየ ክብረት ይላል ባናቱ።
ደረሴ ክብረት የከሰሰው ሰው፣
‹አስታርቁኝ› አለ መጥሪያው ሳይደርሰው።
ጌቴ ደረሴ የከሰሰው ሰው፣
ይዝረጠረጣል ጉልበት ሳያንሰው።

ፉከራው በዚህ መንገድ ይቀጥላል። (አባ.1.፣ክፍ.1.2.3.3.፣ለተሟጋች፣ ይምለከቱ)

ጥናቱ በተካሄደባቸው አካባቢዎች የተለመዱት የፉከራ ክወናዎች ከላይ የተገለጹትን ይመስሉ እንደነበርና፣ ከቅርብ አመታት ወዲህ ለውጥ እየታየ መሆኑን በሁሉም ወረዳዎች ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው መረጃ አቀባዮች በተመሳሳይ ሁኔታ ይገልጻሉ። ቀደም ሲል ይፎከርላቸው የነበሩት ከላይ ከተገለጹት የጀግንነት መለኪያዎች በአንዱ ለተመሰከረላቸው እንደነበርና፣ ፎካሪዎች ያልዘመተውን አርበኛ አድርገው፣ ያልተሾመውን ቀሚስ አልብሰው፣ ሀብት የሌለውን ባለጸጋ አድርገው፣ መፎከርን እንደነውር ይቆጥሩት እንደነበር፣ መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ። ይህንን ማሕበራዊ ስምምነት ጥሰው ለመፎከር የሚሞክሩ ቢኖር እንኳ፣ ታዳሚው ‹‹ውሸት!›› እያለ ከዚያው ላይ በመቃወም ያሳፍራቸው እንደነበር፣ አቶ ገበያው ዓለሜ (አባ.2.ቁ.11) በአንድ ለቅሶ ላይ የተከሰተውን ሁኔታ አንስተው እንደሚከተለው ይገልጹታል።

> ፋርጣ ወረዳ ለሞተ አርበኛ ፎካሪው ‹ዘራፍ እገሌ!› እያለ ሲፎክር፣ አጃቢውም ለቀስተኛውም ‹እውነት!፣ እውነት!› እያለ ይቀበለዋል። እንዲህ እየተባለ ሲዞር፣ የሟችን ቀደም ሲል የሞተ አርበኛ ያልሆነ ወንድሙን ስም ፎካሪው አንስቶ፣ ‹ዘራፍ እገሌ!፣ ዘራፍ እገሌ!›› ሲል፣ ቀኝ እጃቸውን አውጥተው የለቅሶ ሥርዓቱን ሲያስተባብሩ የነበሩት ታዋቂ አዛውንት፣ ‹ይህን ለቅሶ ሊያበላሸው ነው፣ ተው በለው!፤ ተው በለው!› ሲሉ፣ ‹ዘራፍ እገሌ ብር ዘሪ!› ብሎ በሀብታምነቱ ሲፎክርለት፣ ‹ይኽ ላይ እውነት!› ብለው መቀበላቸውን ያስረዳሉ።

በአሁኑ ጊዜ የሚካሄደው ፉከራ ግን፣ ከሟች ትክክለኛ ሥራ ጋር የማይሄድ መሆኑን፣ ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው መካከል አቶ ገበያው፣ አባ አቸነፍ፣ አቶ ሞላና አቶ ታከለ፣ በቅሬታ

ያስረዳሉ። ለፉከራ ሥርዓቱ መለወጥም፣ በኃይለሥላሴ ዘመነ መንግስት ማዕረግ የተሰጣቸው ሹሞችና በጣሊያን ወረራ ወቅት የተዋጉ አርበኞች በቁጥር እየተመናመኑ መሄድ፣ በምክንያትነት ይጠቀሳል። በተለይ ወጣቱ ትውልድ፣ ከአብዮቱ ማግስት፣ ‹‹ሁሉም ሰው እኩል ነው›› በሚለው አስተሳሰብ በመጠመቁ፣ መሳሪያ ይዞ የማያውቀውን መሳሪያ እንደያዘ፣ ፈረስ የሌለውን ፈረስ እንደጫነ፣ ለራሱ ቀለብ አሟልቶ የማያመርተውን፣ የተትረፈረፈ ምርት እንዳመረተ፣ እያደረገ ለማንኛውም ሚች እየፎከረ መሆኑን ማየታቸውን፣ አቶ ገበያው ይገልጻሉ።

በማሕበራዊ ደንቡ መጣስ እየተቆረቆሩ፣ ሰውን ያለሙያው ማዋል ተገቢ አለመሆኑን የሚናገሩ ሰዎችም፣ ‹‹ፊውዳል›› የሚል ቅጽል ስም እየተሰጣቸው ሰሚ ማጣታቸውንና፣ በዚህ የተነሳ አንዳንድ ማዕረግ የነበራቸው ሰዎችና አርበኞች፣ ‹‹ሰው ያለስራውና ያለክብሩ እንዲህ የሚለቀስለት ከሆነ፣ ለቅሶዬ በፈረስና በፉከራ እንዳይለቀስ››፣ ብለው እየገዘቱ መሞታቸውን ያስረዳሉ።

ሁኔታዎች በዚህ መልኩ እየተለወጡ ቢሆኑም፣ ፎካሪዎቹ ‹‹በሉልን›› እየተባሉ የሚችን ዘመዶች ለማስደሰትና ለቅሶውን ለማድመቅ ሲሉ፣ ሚች ባልዋለበትና ባልሰራው መፎከራቸው ተገቢ አለመሆኑን እንደሚያምኑ የሚያሳዩ መረጃዎች አሉ። ለምሳሌ ፋርጣ ወረዳ ውስጥ የታወቁት አዛውንት ፎካሪ አቶ ሞላ አየሁ (አባ.2.ቁ.9)፣ እንዲህ አይነት ነገር ሲያጋጥማቸው፣ እዚያው ለቅሶው ላይ፣

አገሬ አሙስ ወንዝ፣ አዳምጥ አገሬ፣ ማድመጥ ድንቅ ነው፣
ያላበላውን አብልቷል ብዬ፣
ያላረሰውን አርሷልኝ ብዬ፣
ያልዘመተውን ዘምቷልኝ ብዬ፣
ሽልቅሶው ላይ ሀሰት መስክሬ፣
የነብሴን ነገር ምን አለ አገሬ;
እንግዲህ ይብቃኝ ነገር ባፍላ ነው፣
ሲውል ሲያድርማ እሜት ሲሆን ነው።

በማለት ራሳቸውንና ድርጊቱን በክወና ቦታው ላይ እንደሚተቹ ይገልጻሉ። በእንዲህ አይነቱ ራስን የመተቻ ፉከራ፣ ተቀባዩ ‹‹እውነት!›› አይልም። ፎካሪውም ይህን ምላሽ ስለማይጠብቅ፣

ሀይል በተሞላበት ሳይሆን ሀፍረት በተቀላቀለበትና ለስለስ ባለ የተማጽኖ ቃና እንደሚፎክር ያስረዳሉ።

የፉከራ ክወና ቀደም ካለው ጊዜ በበለጠ ሁኔታ እየተጠናከረ መምጣቱንና፣ አዳዲስ ወጣቶች ወደሙያው እየገቡ መሆኑን ከፍ ሲል የተጠቀሱት መረጃ አቀባዮች ገልጸዋል። ለሁሉም ያለ ገደብ መፎከር እንደነውር አለመቆጠርና፣ ፉከራ ጥሩ ድምጽ ባለውም ሆነ በሌለው ሲከውን መቻሉ፣ ለስነቃል ዘርፉ መስፋፋት በምክንያትነት ይጠቀሳሉ። በእድሜ የገፉ አባቶችና ነባር ፎካሪዎች ያለማህበራዊ ደረጃ ልዩነትና ያለሥራው ለማንም የሚደረገውን ፉከራ አጥብቀው እንደሚተቹም፣ ለመረዳት ተችሏል።

በአጠቃላይ ይህ ጥናት በተካሄደበት በደቡብ ጎንደር ዞን፣ እንደሟቹ ማሕበራዊ ደረጃና እንደለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ አይነት፣ የተለያዩ ማጀቢያ መሳሪያዎች እንደሚያዙ ከመረጃ አቀባዮቹና ከምልከታዎቹ ለመረዳት ተችሏል። የሟች ማሕበራዊ ደረጃ ከፍ ያለ ሲሆን፣ ቀሚስ የለበሱ በቅሎዎች ወይም ፈረሶች ይኖራሉ። ሟች አርበኛ ወይም ወታደር ከሆነም በአቅራሪዎቹ፣ ፎካሪዎቹና እነሱን በሚያጅቧቸው ሰዎች ጠበንጃ፣ ጎራዴ፣ ጦር፣ ሻ፣ ሽጉጥ፣ ዝናርና ጀበርና ይያዛል። በወየታ ክወና በግምጃ የተጠቀለሉ ዋንጫዎች በወየባዮቹ የሚያዙ ሲሆን፣ በማሕበርተኞች ደግሞ፣ ዋንጫዎችና ብርሌዎችም ይያዛሉ። የሟች ልብሶችም ወንድ ከሆነ ኮትና ሱሪው፣ ሴት ከሆነች ቀሚሷና መቀነቷ፣ እንዲሁም ጌጣጌጦቿ ቅርበት ባላቸው ሀዘንተኞች ይያዛሉ። ሟቾቹ ልጆች በሚሆኑበት ጊዜ፣ ልብሶቻቸውና ጌጣጌጦቻቸው በምርኩዝ ወይም ባላ ባለው እንጨት ተንጠልጥለው፣ ከፍ ተደርገው ተይዘው ሲለቀስባቸው ይውላል። የመነኩሴ ቆብና መቁጠሪያ፣ የቄስ ዳዊትና መስቀልም እንደዚሁ።

በአጠቃላይ የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ፣ በሟች እድሜ፣ በማሕበራዊ ደረጃ፣ በከዋኝ ጾታና ብዛት፣ በከዋኝ ታዳሚ መስተጋብር፣ በመከወኛ ቁሶችና በአከዋወን ልዩነት የተነሳ፣ በተለያዩ ስያሜዎች ይጠሩ እንጂ፤ Sanka Confidence (2010፣196)፣ ጋና ውስጥ በሚገኙት የሲሳላ ማሕበረሰቦች የለቅሶ ቃል ግጥሞች፣ Bamia (2001፣11) በአልጀርያ ማሕበረሰብ ቃል-ግጥሞች ላይ ባካሄዷቸው ጥናቶች፣ የሁሉም ተቀዳሚ ተግባር፣ ቋሚዎች ለሟቾች የተሰማቸውን ጥልቅ ሀዘን ለመግለጫነትና ለብሶት መተንፈሻነት መሆኑን እንዳረጋገጡት ሁሉ፣ የተጠኚው ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞችም ይህኑ ሚና የሚጫወቱና የለቅሶ ሥርዓቱን የሚያደምቁ መሆናቸውን ጥናቱ አሳይቷል።

በእነዚህ ቃል-ግጥሞች ተደጋግሞ እንደታየው፣ ከሟች አልፎ ቀደም ሲል የሞቱ ሰዎችና የተፈጸሙ ሁነቶች እየተነሱ ታሪክ ይዘከርባቸዋል፡፡ ስለሆነም የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ፣ የጀግኖች፣ የታታሪ ሰራተኞችና የተለያዩ ባለሙያዎች ጠንካራ ጎኖች እየተነሱ ታሪካቸው ለተተኪው ትውልድ የሚተላለፍባቸው ብቻ ሳይሆኑ፣ ተተኪው ትውልድ በመልካም አርያነት እንደተነሱት ቀዳሚዎቹ እንዲሆን የማነሳሳት ሚና ይጫወታሉ ተብሎ እንደሚታመን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በፈቃደ (1996) እና በብርሃኑ (2002) እንደተገለጸው፣ ተጠኚው ማሕበረሰብ በሰዎችም ይሁን በተፈጥሮ የደረሱበትን ጫናዎችና ወቅት ፈጠር ብሶቶች አደባባይ በማውጣት መከፋቱን ይገልጽባቸዋል፡፡ በሟች መለየት ምክንያትም ሆነ በእነዚህ ጫናዎች የተፈጠረው ሀዘንና ብሶት በቃል-ግጥሞቹ መተንፈሱ ደግሞ፣ በToher (2001፣336) ጥናት እንደተረጋገጠው፣ ታምቆ ቢቀር በጤና ላይ ሊከተል ከሚችለው ችግርና ሠላም ማጣት በመታደግ፣ ሥነልቡናዊ ጠቀሜታ ያላቸው መሆናቸውን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ እንዲህ በቡድን በተወሰነ ጊዜና ቦታ፣ በቃልና በአካላዊ እንቅስቃሴ ከሚገለጸው ስሜት፣ በአንጻራዊነት ለረዥም ጊዜና በተናጠል የሟች መለየት የሚፈጥረውን ሀዘን የሚገልጽበት ልማድ ደግሞ፣ በሚቀጥለው ምዕራፍ ተገልጿል፡፡

## ምዕራፍ አምስት

### 5. የሀዘን አገላለጽ ልማድ

የሀዘን አገላለጽ ልማድ፣ በአንድ ማሕበረሰብ ውስጥ የሟች ነፍስ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ እስከሙት ዓመት/ዓመታት መታሰቢያዎች ድረስ የሟች ቤተሰቦች፣ የቅርብ ዘመዶችና አንዳንዴም ጎሳዎች፣ የሟችን መለየት በማሰብ ጉዳታቸውን ለመግለጽ በተለያየ መንገድ የሚያከናውኗቸውን ልማዳዊ ድርጊቶች ይመለከታል። እነዚህ የሀዘን መግለጫ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ ከባሕል ባሕልና ከማሕበረሰብ ማሕበረሰብ እንደሚለያዩ የጥናት ውጤቶች ያሳያሉ። ለመለያየታቸውም ስለሞት ምንነትና ሟች በሚሄድበት ዓለም ያጋጥመዋል ተብሎ ስለሚታሰበው መልካም ነገር፣ ወይም ይጠብቀዋል ተብሎ ስለሚፈራው ፍዳ፣ የተለያዩ ሀይማኖቶች የሚከተሉት እምነትና፣ ከዚሁ የሚመነጩት ስብከቶች በዋናነት የሚጠቀሱ ይመስላሉ።

የልዩነቱ መንስኤ ምንም ይሁን ምን፣ የሀዘን አገላለጹ በአካል ላይ ጉዳት በማድረስ በሚፈጸሙ ልዩ ልዩ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ የማይለበሱ ነገሮችን በመልበስ ወይም አልባሳትን ከመደበኛ አለባበሳቸው በተለየ መንገድ በመልበስና፣ ሰውነትን በማጎሳቆል ወይም ደስታና ምቾት ከሚሰጡ ነገሮች ለተወሰነ ጊዜ በመታቀብ፣ እንደሚገለጽ ከመስክ የተሰበሰቡት መረጃዎች ያሳያሉ። ሀዘንተኞቹ ከእነዚህ በአንዱ ወይም በሁሉም፣ ሀዘናቸውን ሲገልጹ ይችላሉ። ሆኖም ግን፣ የሀዘን አገላለጹ በግለሰቦች ፍላጎት ብቻ የሚወሰን አይደለም። ከፍ ሲል እንደተገለጸው፣ አንድ ማሕበረሰብ ለሞት እንዳለው አመለካከትና እንደሚከተለው ሀይማኖት አስተምህሮት፣ ከሟች ቤተሰቦች ጀምሮ በዙሪያው እስከሚገኙ የማሕበረሰቡ አባላት ድረስ፣ ለሟች እንዳላቸው ቅርበት፣ ሀዘናቸውን እንዴት መግለጽ እንደሚገባቸው የሚጠበቁ ማሕበራዊ ልማዶች ስላሉ፣ ለእነዚህ መገዛትም የግድ ይሆናል።

በዚህ ምዕራፍ፣ በደቡብ ጎንደር ዞን የኦርቶዶክስ ሀይማኖት ተከታይ ማህበረሰብ፣ ሞት ሲከሰት እነማን በምን መንገድ ሀዘናቸውን እንደሚገልጹ ቀርቧል።

## 5.1. በአካል ላይ የሚፈጸሙ የሀዘን መግለጫ ልማዶች

አንድ ሰው ሲሞት የሚፈጠረው ሀዘን፣ መርዶው ከተሰማበት ጊዜ ጀምሮ ለወራትና እንዲያም ሲል ለአመታት የሚዘልቅ ቢሆንም፣ የሚኖረው ክብደትና የሀዘን መግለጫ መንገዱ ከጊዜው ቅርበትና ርቀት ጋር በተያያዘ እንደሚለያይ የተሰበሰቡት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ የነፍስ መውጣት በትንፋሽ መቋረጥና በልብ ትርታ መቆም ሲረጋገጥ፣ የሟች ሕይወት ማለፍ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚታወቅበት በመሆኑ፣ ደረጃው ሊለያይ ቢችልም ለቤተሰብም ሆነ መርዶውን ለሚሰሙ ሌሎች ሰዎች እጅግ አስደንጋጭ የሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የሟች የቅርብ ሰዎች በሚደርስባቸው ከባድ ድንጋጤ፣ ራሳቸውን በከፊል እስከመሳትና የሚያደርጉትን እስከመዘንጋት ሊደርሱ ይችላሉ፡፡ ውስጣቸው በሀዘን ክፉኛ ስለሚሰበር፣ ከፍተኛ የተስፋ መቁረጥ ስሜትም ያድርባቸዋል፡፡ ራሳቸውን በመሳትም ይሁን ተስፋ በመቁረጥ በአካሎቻቸው ላይ የከፋ ጉዳቶች የሚያደርሱት በዚህ የመጀመሪያው የሀዘን ወቅት መሆኑን ከመረጃ አቀባዮቹና ከምልከታ መረጃዎቹ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

የሟች ነፍስ መውጣት ሲሰማ ከባድ ድንጋጤ መፈጠርና፣ በአካል ላይ ጉዳት ማድረስ በሌሎች አካባቢዎች በሚኖሩ ማሕበረሰቦችም እንደሚስተዋል ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ በትግራይ፤ ጸጉርን በመቧጠጥና ፊትን በመንጨት፣ በቋሪት፤ ሴቶች ጉንጫቸውንና ግንባራቸውን በመንጨት፣ ወንዶች በመነሳትና በመውደቅ፣ በሸዋ፤ ጸጉርን በመንጨት፣ ፊትን በመቧጨር፣ ደረትን በመምታት፣ በላይ አርማጭሆ፤ ሴቶች በመውደቅ በመነሳት እንደሚለቀስ፣ እንደቅደም ተከተላቸው፣ የነጋ (1953)፤ የሽመልስ (1997)፤ የፋሲካ (2002) እና የሞገስ (2003)፣ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ በአይሁዶችም የሟች ነፍስ እንደወጣ በቅርብ ቤተሰቦች አካባቢ ከባድ መደናገጥ እንደሚፈጠርና፣ ልብሳቸውን ቀደው ደረታቸውን በመግለጥ እንደሚያገዙ Levine (2004፣113) ያስረዳሉ፡፡

በተጠኚው ማሕበረሰብ የሟች ማረፍ እንደተሰማ በአካል ላይ ከሚፈጸሙት የሀዘን መግለጫ ልማዶች መካከል መሬት ላይ ወድቆ መንከባለል፣ ደረት መድቃትና ፊት መንጨት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ ከቀብር መልስ ወይም እንደሁኔታው በሁለተኛውና በሶስተኛው ቀን ደግሞ ጸጉርን መላጨት ይከተላል፡፡

ለመረጃ አቀባዮቹ ልማዶቹ እንዴትና መቼ እንደተጀመሩ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች፣ ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ እየተላለፉ መምጣታቸውን ከመግለጽ ውጭ፣ የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ያስረዳሉ፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከሌሎች የሀይማኖት መጻሕፍት የተገኙት መረጃዎች ግን፣ እነዚህ ልማዶች በሞትም ይሁን በሌላ ምክንያት ሀዘን ሲያጋጥማቸው በጥንት እስራኤላውያን ዘንድ የሚፈጸሙ እንደነበሩ ያሳያሉ፡፡ አባይነህ (1994፣130) እሥራኤላውያን ደረት በመድቃትና ራስን በመላጨት ሀዘናቸውን ይገልጹ እንደነበር ከመግለጻቸው በተጨማሪ፣ በመጽሐፍ ቅዱስም ልማዱ እንደነበር በተለያዩ ቦታዎች ላይ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ ኢዮብ (ኢዮ.1፣1-20)፣ በሬዎቹና አህዮቹ በሳባ ሰዎች መወሰዳቸውን፣ ከሰማይ የወረደች የእግዚአብሔር እሳት በጎቹንና ጠባቂዎቻቸውን ማቃጠሏን፣ ከለዳውያን ግመሎቹን መውሰዳቸውንና ብላቴኖቹን በሰይፍ መግደላቸውን እንዲሁም ከምደረበዳ የመጣ ነፋስ ልጆቹን በሙሉ መግደሉን ከየአደጋው የተረፉ መልዕክተኞች አንዱን መርዶ ሰምቶ ሳይጨርስ ሌላውን እያደራረቡ ሲነግሩት፣ ባጋጠመው ከባድ ሀዘን መጎናጸፊያውን መቅደዱና ራሱን መላጨቱ ተጠቅሷል፡፡

እንዲሁም የካሕናት አለቆችና ጻፎች (ሉቃ.23፣44-49)፣ ኢየሱስ ክርስቶስን በሰቀሉት ጊዜ፣ በፀሀይ መጨለምና በቤተክርስቲያን መጋረጃ መቀደድ ከታዩት ታምራት በተጨማሪ ኢየሱስ፣ ‹‹አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ›› ብሎ የነፍሱን መስጠት ባዩ ጊዜ፣ በእውነትም ጻድቅ መሆኑን በመረዳት ሁኔታውን ለማየት ተከማችተው የነበሩት ሰዎች ደረታቸውን እየደቁ ተመልሰዋል፡፡ ይህ በሀዘን ጊዜ የደረት መድቃት፣ የፊት መንጨትና የራስ መላጨት ልማድ በእሥራኤላውን ዘንድ ባህል ለመሆኑ በኦሪት ዘዳግምም ‹‹ስለሞተው ሰው አካላችሁን አትንጩ፣ በአይኖቻችሁም (በባሎቻችሁ) መካከል ራሳችሁን አትላጩ›› (ዘዳግም 14፣1-2)፣ ተብሎ ተጽፎ ይገኛል፡፡

እነዚህ መረጃዎች፣ በሀዘን ጊዜ የራስ መላጨትም ሆነ የደረት መድቃት ልማዶቹ በእስራኤላውያን ይከወኑ እንደነበር በዋቢነት ያስረዳሉ፡፡ ልማዶቹ በተጠኚው ማሕበረሰብ የሚፈጸሙት ኢትዮጵያውያን በዘመነ ብሉይ በእምነት ምክንያት ከእስራኤላውያን ጋር እጅግ የቀረበ የማሕበራዊ ኑሮ ግንኙነት ስለነበራቸው እንደሆነም፣ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ አባይነህ (1994፣130)፣ በሀዘን ጊዜ ራስን መላጨትና ፊትን መንጨት በሀገራችን የተለመደ ባሕል መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህም በዘመነ ብሉይ ኢትዮጵያውያን ከእምነታቸው የተነሳ ከሕዝበ

እስራኤል ጋር እጅግ የቀረበ የማሕበራዊ ኑሮ ግንኙነት እንደነበራቸው አመልካች መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

ከእስራኤላውያን ወደኢትዮጵያ መግባትና በሁለቱ ሕዝቦች መካከል በእምነት ከመተሳሰር ጋር በተያያዘ፣ በርካታ ልማዶችን መጋራታቸውን ከመረጃ አቀባዮቹ መካከል መሪጌታ ክፍለማርም አለነ (አባ.2፣ቁ.2) ከመጽሐፍ ቅዱስ እያጣቀሱ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

ኢትዮጵያዊቱ ንግሥት ሳባ አምልኮተ እግዚአብሔርን ለማወቅና የሰሎሞንን ጥበብ ለማየት ወደእየሩሳሌም በሄደች ጊዜ፣ ‹‹ኢትዮጵያ እጆቿን ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች›› (መዝ.67፣31) የሚለው ትንቢት እንደተፈጸመና፣ በርካታ ነገሮችን እንዳገኘች፣ ‹‹ንጉሥ ሠሎሞንም በገዛ እጁ ከሰጣት ሌላ የወደደችውን ሁሉ፣ ከእርሱም የለመነችውን ሁሉ፣ ለሳባ ንግሥት ሰጣት፤ እርስዋም ተመልሳ ከባሪያዎችዋ ጋር ወደምድርዋ ሄደች›› (1ኛ ነገሥት፣10፣13)፡፡ ተብሎ መጠቀሱን በዋቢነት ያስረዳሉ፡፡

በዚህ ጉብኝት በተፈጠረ ግንኙነት፣ ንግሥት ሳባ ከንጉሥ ሰሎሞን ቀዳማዊ ምኒልክን መውለዷንና፣ ሃያ ሁለት ዓመት ሲሞላው ወደአባቱ ተመልሶ ነግሶ ሲመለስ፣ ንጉሥ ሰሎሞን ‹‹እኔ የበኩር ልጄን ከላኩ እናንተም የበኩር ልጆቻችሁን ላኩ››፣ ብሎ በማዘዙ ከአስራ ሁለቱ ነገድ፣ አስራ ሁለት ሺህ እሥራኤላውያን አጅበውት ወደኢትዮጵያ መግባታቸው፣ ለባሕልና ሀይማኖት መቀራረቡ በር ከፋቾች እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡ ከሄኖክ ጀምሮ ንጉሥ ሠሎሞን እስከጻፋቸው ያሉትን የሀይማኖት መጻሕፍት እንዲተረጉሙም ሶስት መቶ አስራ ስምንት ሌዋውያንን መላኩና የታቦተ ጽዮንም ወደኢትዮጵያ መምጣት በተለይም የኦሪት ሀይማኖቱን ግንኙነት እንዳጠናከሩትና የባሕል ቅርርቡንም እንዳሳደጉት ያስረዳሉ፡፡ በፍትሃ ነገሥት (ከአንቀጽ፣43-55) እንደተገለጸው፣ የሰሎሞን ልጅ ወደኢትዮጵያ ነግሶ ሲመለስ፣ ለንጉሡ የበኩር ልጆቻቸውን እንዲሰጡ ንጉሥ ሰሎሞን እስራኤላውያንን ማዘዙንና፣ ታቦተ ጽዮንን ሰርቀው ወደ ኢትዮጵያ ይዘው መግባታቸውን የሚያስረዳ ታሪክ ይገኛል፡፡

በመረጃ አቀባዮቹ ከተጠቀሰውና ከእነዚህ መረጃዎች ለመረዳት እንደሚቻለው፣ በኢትዮጵያውያንና በእሥራኤላውያን መካከል በለቅሶ ሥርዓቱ ልማድ ላይ የሚታየው መመሳሰል፣ በኦሪት ዘመን ከነበረው የሀይማኖት ቅርርብና በሁለቱ ሕዝቦች ግንኙነት ከተፈጠረ የባሕል መወራረስ የመጣ መሆኑን ለመገመት አያዳግትም፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P.O. BOX 1176
ADDIS ABABA, ETHIOPIA

ከላይ ከተገለጸው የእሥራኤላውያን ወደኢትዮጵያ መግባት በተጨማሪ፣ ለሁለተኛና ለሶስተኛ ጊዜ በስደት ወደኢትዮጵያ መጥተው እንደተቀላቀሉም መሪጌታ ክፍለማርም ያስረዳሉ፡፡

ከመጀመሪያው የአጅብ ጉዞ በኋላ አብስያኖስና ጥጦስ የተባሉት የሮም ነገሥታት በ70 ዓ.ም እየሩሳሌምን ወርረው ሰሎሞን የሰራውን ቤተ መቅደስ ባቃጠሉት ጊዜ፣ እሥራኤላውያን በየሀገሩ ሲበተኑ ወደኢትዮጵያ እንደገቡም ይገልጻሉ፡፡ ኦቶማን ቱርኮች ከ1517-1917 ዓ.ም ለአራት መቶ ዓመታት እየሩሳሌምን ሲጨፈጭፏት ከተሰደዱት እሥራኤላውያን መካከልም፣ ቀድመው ከፈለሱት ጋር መጥተው የተቀላቀሉ እንደሚገኙበት ያስረዳሉ፡፡ ቤተ እስራኤላውያን እ.ኢ.አ እስከ1990ዎቹ የመጀመሪያ አጋማሽ ዓመታት ድረስ ጥናቱ በተካሄደበት ዞንና በአካባቢው ሰፍረው ይኖሩ እንደነበርም ከአካባቢው የተሰበሰቡት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ አመጣጣቸውን መነሻ በማድረግ ሳይሆን አይቀርም፣ የአካባቢው ማሕበረሰብ ‹ፈላሻ› በሚለው ስም ይጠራቸው እንደነበር መረጃ አቀባዩ አክለው ያስረዳሉ፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለጸው፣ ከእሥራኤላውያን የሀዘን አገላለጽ ልማድ ጋር ተመሳሳይነት እንዳላቸው የተጠቆሙት ተጠኚው ማሕበረሰብ በአካል ላይ የሚፈጽማቸው የሀዘን መግለጫ ልማዶች፣ ቀደምትነት ያላቸው መሆናቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ መረጃዎቹ ያሳያሉ፡፡ ማህተመ ሥላሴ እ.ኢ.አ. (1948፣587)፣ ከ1925 በፊት የሀዘን አገላለጽ ልማዱ ምን ይመስል እንደነበር የገለጹበት ቀጥሎ የቀረበው ሀሳብም ይህንኑ ቀደምትነታቸውን ያሳያል፡፡

> አባት፣ እናት፣ ባል፣ ሚስት፣ ልጅ፣ ዘመድ፣ ወዳጅ፣ በሞቱ ጊዜ በተወላጆቹና በወገኖቹ ዘንድ ብርቱ ሀዘን ይደረጋል፡፡ መርዶውም እንደተሰማ ወዲያው በዝተት ደም እስኪወጣ ፊት ይነጫል፤ ጠጉር ይቆረጣል ወይም ይላጫል፡፡ ሴቶች ክንብንባቸውን ተገልጠው ቀሚሳቸውን ይሰነጥቁ*ና፣ ከደረታቸው በታች አሽርጠው ምንም ትልቅ ወይዘሮ ቢሆኑ በርኖስ እንኳን ከተከሻቸው ሳያደርጉ አዕምሯቸው እስኪጠፋ እየተንጠራሩ ‹ዋይ ዋይ› እያሉ ደረታቸውን እስኪቆስልና ደም እስኪመስል በመሪር ሀዘን እየመቱ ያለቅሳሉ፡፡

* በአይሁድ የሟች ቤተሰቦች ሀዘናቸውን ለመግለጽ ልብሳቸውን እንደሚቀዱና ልማዱ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚወደውን ሰው ሞት የሰማ ሀዘንተኛ ልብሱን ከመቅደዱ ምሳሌ የመጣ መሆኑን፣ ዳዊት የንጉስ ሳኦልን ሞት በሰማ ጊዜ ልብሶቹን ቀድዶ ማልቀሱን በምሳሌነት በመጥቀስ Levine (2004፣113) ያስረዳሉ፡፡ በአይሁዶች ዘንድ ልብስን መቅደድ የቁጣና የሚወዱት ሰው ሞት መግለጫ ተደርጎ እንደሚወሰድም ይገልጻሉ፡፡

እንዲህ አይነቱ መሪር ሀዘን ቋሚ ዘመድ ወዳጅን ከመጉዳት በቀር ለሟች ጥቅም የማይሰጥ መሆኑን በመረዳት እ.ኢ.አ በ1925 የልጃቸውን የልዕልት ዘነበወርቅን ሞት ምክንያት በማድረግ አጼ ኃይለሥላሴ፣ የመርዶ ሀዘን፤ ከተሰማበት፣ የዕለት ሞት፤ ከተቀበረበት፣ ጊዜ ጀምሮ በቤት ለሶስት ቀን ብቻ እንዲቆይ አዋጅ ሲያወጡ፣ በአካል ላይ በሚፈጸሙት የሀዘን መግለጫ ልማዶች ልክና ሥርዓት ላይም የሚከተለውን ደንግገው ነበር፡፡

> ወንድም ቢሆን ሴትም ብትሆን ፊት ነጭቶ፣ ልብስን ጥሎ፣ አካልን ገልጦ እየዘለሉ ማልቀስ እንዲቀር ይሁን፡፡ ለክርስቲያን የሚገባው ሀዘን ድምጡን አሰምቶም ቢሆን በመንሰቅሰቅም ቢሆን እንባውን ማፍሰስ ነው እንጂ ፊትን ነጭቶ፣ ልብስን ጥሎ አካልን ገልጦ እየዘለሉ ማልቀስ ተስፋ ትንሳኤ የሌላቸው አህዛብን መመስል ነው፤ ይልቁንም ለሴቶች በሌላ ስፍራ ይቅርና በቤተክርስቲያን እንኳ ይከናነቡ የተባለውን አፍርሰው አካል ገልጠው ልብስ ጥለው እየዘለሉ ማልቀስ የማይገባ ነገር ነው፤ በዚህም ላይ ደግሞ ፊቱን ነጭቶ ልብሱን ጥሎ አካሉን ገልጦ በፀሀይ በብርድ እየዘለለ ሲያለቅስ በሽታ ላይ እስከመውደቅና እስከመታመም ቢደርስ ሁለተኛ ጉዳት ነው፡፡ (ገጽ፣593)

አዋጁ እምነትን ከሳይንስ አጣምሮ በአካል ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ድርጊቶችን እየፈጸሙ ማልቀስ ተገቢ እንዳልሆነ የሚያስከትሉትን ጉዳት በመጥቀስ ይመክራል፡፡ በሀይማኖቱም በኩል ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እ.ኢ.አ. (1983፣43)፣ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ የሞተላቸው መሆኑን ለሚያምኑ ክርስቲያኖች፣ ፊትን በመንጨት፣ ፀጉርን በመላጨት፣ እየጮሁ ከማልቀስ የበለጠ ውርደት እንደሌለ በመግለጽ ከገሰጹ በኋላ፣ እነዚህ ሰዎች መላ ዘመናቸውን ወደቤተክርስቲያን እንዳይገቡና ከምዕመናን እንዳይገናኙ መከልከል እንዳለባቸው ይደነግጋሉ፡፡

በዚህ መልኩ በአዋጁም ሆነ በሀይማኖቱ፣ በአካል ላይ ጉዳት እያደረሱ ማልቀስ ተገቢ አለመሆኑ ቢወገዝም፣ በተጠኚው ማሕበረሰብ የተሰበሰቡት መረጃዎች የአዋጁ ድንጋጌዎችም ሆኑ የሀይማኖቱ ውግዘቶች ተፈጻሚነት አለማግኘታቸውን ያመለክታሉ፡፡ ከክልከላዎቹ ጀርባ ማሕበረሰቡ በምን ዓይነት የእድሜና የኑሮ ደረጃ የሚገኝ ሰው፣ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ሲሞት፣ እነማን ሀዘናቸውን እንዴት መግለጽ እንደሚገባቸው፣ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የሚጠበቅ ልማድ ማዳበሩን ከምልከታ መረጃዎቹ ለመታዘብ ተችሏል፡፡ የሟች መለየት

ከሚፈጥረው ድንጋጤ በተጨማሪ፣ እነዚህን ማሕበራዊ ልማዶች ለማክበር ሲባልም፣ የተለያዩ ጉዳቶችን አካል ላይ በማድረስ ሀዘን እንደሚገለጽ፣ መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ።

ለሀዘን ክብደቱና በተለያየ መንገድ ለመገለጹ፣ የመለያየት (የሞት) ከባድነት የሚፈጥረው ድንጋጤና ለሁሉም የማይቀር መሆኑ፣ በምክንያትነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። በተጠኚው ማሕበረሰብ፣ ሞት ዳግም ላይገናኙ እስከወዲኛው መለያየት ተደርጎ ስለሚታይ፣ በሟች ቤተሰቦች ላይ ከባድ ሀዘን ያስከትላል።

ከሞት በኋላ በአካል ለመገናኘት አለመቻል የጋራ ጉዳይ ቢሆንም፣ ከአሟሟትና ከሌሎች ነገሮች ጋር በተያያዘ የሚሰጠው የሀዘን ክብደት ከሟች ሟች ይለያያል። ለምሳሌ በተጠኚው ማሕበረሰብ፣ ቤተሰባቸውን በማገዝ (በተለይ ደካሞች ወላጆቻቸውን በመጦር) ላይ ያሉና እወጣ-እወጣ የሚሉ ወጣቶች ሞት፣ ገና ልጅ በማሳደግ ላይ ካሉ ባለትዳሮች የአንዳቸው ሞት፣ ሀብት ያላቸውና የተቸገሩትን በማገዝ ላይ የሚገኙ ሰዎች ሞት፣ ለዘመዱም ሆነ ለሚኖርበት ማሕበረሰብ ደጀን ተደርጎ የሚታይ ሰው ሞት፣ የቅርብ ቤተሰቡንም ሆነ የሚኖርበትን ማሕበረሰብ በእጅጉ እንደሚያሳዝን ሁሉም መረጃ አቀባዮች በተመሳሳይ ይገልጻሉ። ሀዘኑን ከባድ የሚያደርገው፣ በአጭር ከመቀጨት በተጨማሪ፣ እነዚህ ሰዎች ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች መከታና አጋዥ በመሆናቸው፣ የእነሱ መታጣት በቀሪዎቹ ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ስለሚታሰብ መሆኑንም ያስረዳሉ።

ከዚህም በተጨማሪ፣ በማንኛውም የዕድሜ ክልል የሚገኝ ሰው በአደጋ ምክንያት በድንገት መሞት፣ በተለይም በሰው እጅ መሞት፣ እጅግ ከባድ ድንጋጤ ከሚፈጥሩትና በቤተሰብ ላይ የመረረ ሀዘን ከሚያስከትሉት የሞት አይነቶች ውስጥ እንደሚፈረጁ፣ ከስማዳ፣ አባ አቸነፍ፤ ከላይ ጋይንት፣ አቶ ደጀን፤ ከፋርጣ፣ አቶ ሞላ፤ ከደብረታቦር፣ አቶ ዋሰና ከፎገራ፣ አቶ ካሳው፤ ያስረዳሉ። የሀዘን ክብደቱ የሚመነጨውም ምንም ባልታሰበበት ሁኔታ በድንገት ከመከሰቱ፣ ሟች እመለሳለሁ ብሎ ወጥቶ በዚያው ከመቅረቱ፣ በጭካኔና በአሰቃቂ ሁኔታ ከመገደሉ ጋር ተያይዞ ስለሚታሰብ እንደሆነ፣ መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ።

ድንገተኛ ሞት በሌሎች ማሕበረሰቦችም ከባድ ሀዘን እንደሚያስከትል መረጃዎች ያሳያሉ። ለምሳሌ Mallon (2008፤47-8) የተለያዩ የጥናት ውጤቶችን ጠቅሰው፣ ምንም እንኳ የአንድ ሰው ሞት በቅርብ ቤተሰቡና በዘመድ ጓደኞቹ ላይ ከፍተኛ ድንጋጤ መፍጠሩ የተለመደ ቢሆንም፣ የሟች በድንገተኛ አደጋ መሞት፣ ራሱን ማጥፋት ወይም በነፍስ ገዳዮች መገደል፣

ሀዘኑን ከሌሎቹ የሞት አይነቶች በተለየ እጅግ መራራና ውስብስብ እንደሚያደርገው ይገልጻሉ፡፡ ያልተጠበቀ ሞት፣ እውነት መሆኑን አምኖ ለመቀበል መክበዱና ሀዘንተኛው አደጋውን ወይም ግድያውን ካየ ወይም ራሳቸውን ያጠፉ ሰዎችን ሬሳ ካገኘ፣ በአሰቃቂ ምስሎቹ ጭንቀት እንደሚሰቃይም ያስረዳሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ ድንገተኛ ሀዘን ውስብስብና የተለያዩ ገጽታዎች ያሉት ሂደት መሆኑንና አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ ስነልቡናዊና ማሕበራዊ ገጽታዎች ያሉት መሆኑንም ያስረዳሉ፡፡

Parkesም (1997፣236)፣ ሀዘንተኞቹን ከሚያጋጥማቸው ስነልቡናዊ ችግር አንዱ፣ የሞቱ ድንገተኛነት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ በአንዲት ደቂቃ ውስጥ፣ የሚወዱት ሰው በሕይወት ከመኖር ወደአለመኖር መቀየርና በዚህ ቅጽበታዊ ሂደት፣ ባለትዳር የነበረች ሚስት ወደጋለሞታነት፣ ልጆችም ወደወላጅ አልባነት መቀየር፣ እንዲሁም ሀዘንተኞቹ ለዚህ ሽግግር ራሳቸውን የሚያዘጋጁበት ጊዜ አለመኖር፣ ለችግሩ መባባስ አስተዋጽኦ ከሚያደርጉት ውስጥ እንደሚጠቀሱ ያስረዳሉ፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች በሚከሰቱ ድንገተኛ ሞቶች ጊዜ ከሚፈጠረው ከባድ ድንጋጤና መሪር ሀዘን በተጨማሪ፣ ሀዘንተኞቹ ለዚህ ምላሽ እንዲሰጡ ከማሕበረሰቡ የሚጠበቅባቸው ልማድ፣ በአካላቸው ላይ የሚያደርሱትን የሀዘን መግለጫ እንዲከብድ እንደሚያደርገው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ አቶ ብርሃን አበበ (አባ.2.፣ቁ.16) ሀዘንተኞቹ ራሳቸውን ከማጥፋት ጀምሮ በተለያዩ የአካል ክፍሎቻቸው ላይ ጉዳት እስከማድረስ በሚዘልቁ መንገዶች ሀዘናቸውን እንደሚገልጹ ያስረዳሉ፡፡ ደረትን በድንጋይ መውገር፣ ፊትን በጆንያ መንጨትና ጸጉርን መበጠጥ፣ ትኩስ ሀዘናቸውን የሚገልጹባቸው መንገዶች እንደሆኑም ይገልጻሉ፡፡ ከመረጃ አቀባዮቹና ክምልከታ መረጃዎቹ ለመገንዘብ እንደተቻለው፣ በላይ ጋይንት፣ በደብረ ታቦር፣ በፋርጣ፣ በወረታና በፎገራ ወረዳዎች፣ በተለይ ለሴቶች ፊትን መንጨት ዋናው በአካል ላይ የሚፈጸም የሀዘን መግለጫ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አባ አቸነፍ እንግዳ (አባ.2.፣ቁ.12) እና አቶ ገበያው ዓለሜ (አባ.2፣ቁ.11) እንደሚገልጹት፣ ቀደም ባለው ጊዜ በላይ ጋይንትና በስማዳ ወረዳዎች የሚች የቅርብ ዘመድ የሆኑ ሴቶች ፊታቸውን በደንብ አድርገው መንጨት ይጠበቅባቸው ነበር፡፡ ካልነጩ የአካባቢው ማህበረሰብ ‹‹መሞቱን/ቷን አልሰሙም እንዴ?›› በማለት ይተቿቸው እንደነበርና፣ ፊት መንጨቱ ይከናወን የነበረው፣ በአቅራቢያው ላሉ የሚች ነፍስ መውጣት እንደታወቀ፣ በሩቅ ለሚገኙ ደግሞ፣

የሚችን ረፍት በሚሰሙበት ጊዜ እንደነበር እነዚሁ መረጃ አቀባዮች ያስረዳሉ። ከቀብር መልስ ለቀስተኛውን ካሰናበቱ በኋላ ደግሞ፣ በዕለቱ ወይም በሁለተኛው ቀን፣ ሴቶች ጸጉራቸውን በመላጨት ሀዘናቸውን ይገልጹ እንደነበር ያስረዳሉ።

እነዚህ ድርጊቶች ዓለማዊና ሀይማኖታዊ ትርጉም እንዳላቸውም ለመገንዘብ ተችሏል። ከዓለማዊ አንጻር ለሟች ከምር ወይም ከአንጀት ማዘንን ማሳያነታቸው ጉልህ ቦታ እንደሚሰጠውም ለመረዳት ተችሏል። በማሕበረሰቡ ዘንድ ፊትን በጣም መንጨት፣ ከልብ የማዘን ምልክት ተደርጎ የመወሰድና የመመስገን፣ አለመንጨት ለሟች እንዳላዘኑ ተደርጎ የመታየትና የመተቸት ባሕል መኖር፣ ድርጊቱን ለመፈጸም አበረታች ምክንያት ሆኖ ተገኝቷል።

ትችቱን በመፍራትም ይሁን ሙገሳውን በመፈለግ ፊትን መንጨት፣ ቁስሉ ከሚያስከትለው ህመም በተጨማሪ፣ ጥሎት የሚያልፈው ጠባሳ በቶሎ ስለማይጠፋ የሀዘንተኞቹን ውበት ያበላሻል። ከዚህም ሌላ ከረዥም ጊዜ በኋላም እንኳ የሀዘኑን ትዝታ እየቀሰቀሰ ስነልቡናዊ ሁከት መፍጠሩ እንደማይቀር ለመገንዘብ ይቻላል።

በመንፈሳዊው ደግሞ፣ ደረት እየደቁ፣ ፊት እየነጩ፣ ጸጉር እየቧጠጡ፣ መሪር ሀዘን ማዘን፣ ትንሳኤ ሙታን የለም ብለው ከሚያምኑ የአህዛብ ሥራ የተወረሰ መሆኑን ከመሪጌታ ክፍለማርያም አለነ (አባ.2፣ቁ.2) ገለጻ ለመገንዘብ ተችሏል። የሀይማኖት ትምህርት ማነስ፣ ከሀዲስ ኪዳን በፊት የነበሩት እነዚህ የአህዛብ ተግባራት እንዲፈጸሙ ምክንያት እንደሆነም ይጠቀሳል። ቅዱሳት መጻሕፍት ሀዘንን አክብዶ በአካል ላይ ጉዳት እያደረሱ የማልቀስን ልማድ ኢተገቢነት እየገለጹ፣ ማሕበረሰቡ ልማዶቹን ሲፈጽም መታየቱ ግን፣ ለሀይማኖታዊ ትምህርቱ ማነስ ብቻ ሳይሆን ማሕበረሰቡ ለሞት ያለውን ፍራቻ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

በሀይማኖት ሀዘን ቀልሎ እንዲታይ ያደረገው የዳግም ትንሳኤ ተስፋ መሆኑን ከመረጃዎቹ ለመገንዘብ ተችሏል። ቅዱሳት መጻሕፍት ሥጋዊ ሞትን እንደእንቅልፍ አቅልለው የመመልከታቸው መሰረታዊ ምክንያትም፣ ከዚሁ ጋር የተያያዘ ሆኖ ተገኝቷል። ክርስቲያኖች ዳግም ምጽአትን ተስፋ በማድረግ ሀዘናቸውን ማቅለል እንዳለባቸው ከመከሩት ውስጥ፣ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደተሰሎንቄ ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ የሚከተለውን አስፍሮ ይገኛል። ‹‹ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ተስፋ እንደሌላቸው እንደሌሎች ሰዎች ደግሞ እንዳታዝኑ አንቀላፍተው ስላሉት ታውቁ ዘንድ እንወዳለን። ኢየሱስ እንደሞተና እንደተነሳ ካመንን

እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና (1ኛ ተሰ.4፣13፡14)፡፡››

ክርስቲያን ሀዘኑን በልክ ማድረግ እንዳለበት በሀዲስ ኪዳን ብቻ ሳይሆን በፍትሐ ነገስትም (አንቀጽ፣22) የሚከተለው የምክር ቃል ተጽፎ ይገኛል፡፡

> ሰው በሞተ ጊዜ እንደአረማውያን አትሁኑ፡፡ ልብሳችሁን አትቅደዱ፡፡ ፊታችሁን አትንጩ፡፡ አካላችሁን አታቁስሉ፡፡ ደረታችሁን አትምቱ፡፡ ራቁት አትሁኑ፣ ለቅሶ አታዘውትሩ፣ የራስ ጠጉራችሁን አትላጩ፣ እግዚአብሔርን በትዕግስት አመስግኑት፡፡ እንደእዮብ ትዕግስተኞች ሁኑ፣ ሰው ሞቶ አይቀርም በኋላ ትንሳኤ መነሳቱን እመኑ፡፡ በጌታችን በኢየሱስ ዙፋን ፊት በቀኝና በግራ ቁሞ ሁሉም እንደየስራው ፍርድ መቀበሉን አትዘንጉ፡፡

ከቅዱሳት መጻሕፍቱ እንዲህ አይነት ምክር በተጨማሪ በልማዱ ላይ፣ ሀዲስ ኪዳን በተጠኚው ማሕበረሰብ ከተሰበከበት ጊዜ ጀምሮ ሀይማኖታዊ፣ እ.ኢ.አ ከ1925 ዓ.ም ወዲህ ደግሞ፣ ዓለማዊ ክልከላ ቢጣልም፣ እስካሁን ድረስ ተግባራዊ እየተደረገ አለመሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ለዚህም ቀደም ብሎ እንደተገለጹት፣ የሞት ከባድነት በሀዘንተኞቹ ላይ የሚፈጥረው ድንጋጤና በማሕበረሰቡ የሚጠበቀው የሀዘን አገላለጽ ልማድ፣ በሀዘንተኞቹ ላይ የሚያሳድሩት ሥነልቡናዊ ጫና በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

በአካል ከሚገልጹት በተጨማሪ በአለባበስና በሌሎችም መንገዶች የሚገለጹትን ቀጥሎ የቀረቡ ልማዶች ተጠኚው ማህበረሰብ ያከናውናል፡፡

## 5.2. በአለባበስ የሚገለጹ የሀዘን ልማዶች

ሞት በተከሰተ ጊዜ በአካል ላይ የሚፈጸሙ የሀዘን መግለጫዎች እንዳሉ ሁሉ፣ በአለባበስም ሀዘን የሚገልጽባቸው የተለያዩ ልማዶች አሉ፡፡ እነዚህ ልማዶች በአካል ላይ እንደሚፈጸሙት ቀደምትነት ያላቸውና ከእሥራኤላውያን ልማዶች ጋር እንደሚመሳሰሉም መረጃዎቹ ያሳያሉ፡፡

ከተመሳስሎዎቹ ውስጥ የሀዘንተኞቹ ልብስ መቅደድ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ Levine (2004፣113-114)፣ የአይሁድ ሀዘንተኞች ከቀብሩ ሰዓት ትንሽ ቀደም ብሎ፣ በመካነ መቃብሩ ላይ ወይም

ወደቤት ከተመለሱ በኋላ፣ የሟች ቤተሰቦች ሀዘናቸውን ለመግለጽ ልብሳቸውን እንደሚቀዱ ያስረዳሉ፡፡ ልማዱ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚወደውን ሰው ሞት የሰማ ሀዘንተኛ ልብሱን ከመቅደዱ ምሳሌ የመጣ እንደሆነና ልብስን መቅደድ የቁጣና የሚወዱት ሰው ሞት መግለጫ ተደርጎ እንደሚወሰድ ያስረዳሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ የሸዋ ክርስቲያን አማራ ሴቶች የሚወዷቸው ቤተሰቦቻቸው ሲሞቱባቸው፣ ከቀብር በፊት ቀሚሳቸውን በደረታቸው ትይዩ ወደታች ቀደው እንደሚያለቅሱ፣ ፋሲካ (1953) ያስረዳሉ፡፡ እ.ኢ.አ በ1925 በአፄ ኃይለ ሥላሴ በወጣ የሀዘን አገላለጽ ሥርዓት አዋጅ፣ ለሴቶች በሴላ ስፍራ ይቅርና በቤተክርስቲን እንኳ ‹‹ይከናነቡ›› የተባለውን አፍርሰው አካል ገልጠው፣ ልብስ ጥለው፣ እየዘለሉ ማልቀስ የማይገባ እንደሆነ መገለጹ፣ ልማዱ በኢትዮጵያ ለመኖሩ በማስረጃነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

በአይሁዶች ዘንድ ልብስን መቅደድ ብሉያዊ መነሻ ያለው ከመሆኑ በተጨማሪ፣ ማሕበራዊ ሕግና ትርጉም እንዳለው ተጠቅሷል፡፡ ወላጅ ሲሞት ልብስ በደረት ትይዩ ወደታች ተቀዶ ልብን የማራቆት ልማድ ያለ ሲሆን፣ ይህም የአይሁድን የልብ ማራቆት ሕግ ለማሟላትና የሀዘንተኛው ልብ በሀዘን መሰበሩን ለማሳየት እንደሆነ Levine ያስረዳሉ፡፡ በኢትዮጵያ የልማዱ መኖር ከመገለጹ ውጭ ያለው ትዕምርታዊ ትርጉም አልተጠቀሰም፡፡

በተጠኚው ማሕበረሰብ በአለባበስ የሚፈጸሙት የሀዘን መግለጫዎች፣ የሟች ነፍስ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ እስከዓመታት ድረስ የሚዘልቁ እንደሆኑ መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ፡፡ እነዚህ ልማዶች ሀዘንተኞቹ ለሟች ያላቸውን ቅርበትና የሀዘናቸውን ክብደት ደረጃ እንደሚያሳዩም ተገልጿል፡፡ ስለሆነም፣ በአለባበስ የሚገለጹትን የሀዘን መግለጫ ልማዶች፣ ሀዘንተኞቹ ለሟች እንደሚኖራቸው ቅርበት፣ በለቀስተኞች፣ በቤተ ዘመድና በቅርብ ቤተሰብ የሚተገበሩ በሚሉት ምድቦች ከፋፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

ለቀስተኞች ወደለቅሶ ቦታ ሲሄዱ ሀዘናቸውን ከሚገልጹበት አለባበስና ይህንኑ ከሚያስተካክሉበት ቦታ አኳያ፣ በወንዶችና በሴቶች ልዩነት ይታያል፡፡ ለምሳሌ ከመረጃ አቀባዮቹ መካከል አቶ ጸጋየ ጀንበሬ (አባ.2፣ ቁ.19፣ ክፍ.1.3.2.፣ አን.1) እንደሚገልጹት፣ ወንዶች በአብዛኛው ከለቅሶው ቦታ ሲደርሱ ቀኝ እጃቸውን ያወጣሉ፡፡ በዚህ መንገድ ለብሰው የሚቆዩትም ከሀዘንተኞቹ ጋር እስኪገናኙ ድረስ ብቻ ነው፡፡ ሴቶች ግን ከቤታቸው ጀምረው ነጠላቸውን ዘቅዝቀው ይለብሳሉ፡፡ ቀብር ተጠናቆ ከቤታቸው እስኪገቡ ድረስም አለባበሳቸውን አይቀይሩም፡፡

የሥጋ ዘመዶች ከሆኑ ግን፣ የሚችን ረፍት እንደሰሙ ከቤታቸው ጀምሮ ወንዶች ኩታቸውን ወይም ጋቢያቸውን ቀኝ እጃቸውን አውጥተው በማጣፋት፣ ሴቶች የነጠላቸውን አንድ ጫፍ ከወገባቸው ላይ አስረው ሌላኛውን ጫፍ በጀርባቸው ወደላይ በመመለስ ከአንገታቸው ላይ አጣፍተው እንደሚወጡ ይገልጻሉ፡፡ አንዳንድ ሴቶች በነጠላቸው ወገባቸውን አስረው ከላይ ሌላ ነገር ሳይደርቡ ወደለቅሶው ቦታ እንደሚጓዙና፣ በዚሁ ሁኔታ ሲያለቅሱ እንደሚውሉም ያስረዳሉ፡፡ በተጠኚዎቹ፣ የነጠላ፣ የጋቢና የኩታ ጥለት ወይም ዘርፍ የሚደረገው ለጌጥ ሲሆን፣ ሴቶች የነጠላቸውን ጫፍ ወደላይ የሚዘቀዝቁት፣ ጌጥነቱን በማጥፋት ሀዘንተኛ መሆናቸውን ለማመልከት መሆኑን ከመረጃ አቀባዮቹ ገለጻ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከለቅሶ መልስ ደግሞ፣ ወንዶች ተጎጂዎቹን ከተሰናበቱና ከእይታቸው ዘወር ካሉ በኋላ በመደበኛው መንገድ እንደሚለብሱ፣ ሴቶች ግን ከለቅሶው ላይ በዋሉበት አለባበስ ወደቤታቸው እንደሚመለሱ መረጃ አቀባዩ ያስረዳሉ፡፡ ከግለሰብ ግለሰብ ቢለያይም፣ የሚች ተዝካር እስከሚወጣ (እስከአርባና ሰማንያ ቀን ድረስ) ወደቤተክርስቲያን፣ ወደማሕበር፣ ወደገበያና ወደመሳሰሉት ቦታዎች ሲሄዱም ነጠላቸውን አጥፈው ዘርፉን ወይም ጥለቱን ወደአንገታቸው በማድረግ ዘቅዝቀው እንደሆነ አቶ አለምነው አሉላ (አባ.2፣ ቁ.23፣ ክፍ.1.3.2.፣ አን.1) ይገልጻሉ፡፡

የቅርብ ዝምድና ያላቸው እስከአጎትና አክስት ልዥ ድረስ ያሉ የቅርብ ቤተሰቦችና ጓደኞች ደግሞ፣ በአለባበስ አይነቱ ብቻ ሳይሆን በቆይታ ጊዜውም የሀዘን መግለጫቸው ከላይ ካየናቸው ከሁለቱ ሀዘንተኞች እንደሚለይ በመስክ ከተካሄደው ምልከታ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በእድሜ ጠና ያሉ ወንድ ሀዘንተኞች ካፖርት ደርበው፣ ከአንገታቸው ላይ ፎጣ ወይም ሻሽ ጣል ያደርጋሉ፡፡ በገጠሩ አካባቢ ወጣቶችና ለቅሶ ለመዋል የደረሱ ልጆች ጋቢያቸውን በቁመቱ አጥፈው ከአንገታቸው ላይ አንዴ በመጠምጠም ዘርፍና ዘርፉን በትከሻዎቻቸው አውርደው ወደፊት በማድረግ በእጆቻቸው ይዘው ግራ ቀኝ፣ ፊት ኋላ፣ እያወዛወዙ ያለቅሳሉ፡፡ በከተማ ደግሞ ያለ ዕድሜ ልዩነት ጋቢያቸውን በወርዱ አጣጥፈው ከትከሻቸው ላይ ጣል ያደርጉታል፡፡

በገጠር ለሚች በጣም ቅርበት ካላቸው ወንድ የቤተሰብ አባላት መካከል በእድሜ ጠና ያሉት፣ ወይም ልብሱን ለማግኘት የሚችሉት፣ በርኖስ ወይም ማቅ ይደርባሉ፡፡ ቀደም ባለው ጊዜ ከላይ ምንም ነገር ሳይደርቡ፣ ቁረንጮ፣ ጆንያ፣ ቡትቶ ወይም ገመድ ታጥቀው የሚያዝኑ ቤተሰቦች እንደነበሩ አባ አችነፍ እንግዳ (አባ.2፣ ቁ.12፣ ክፍ.1.3..2.፣ አን.1) ያስረዳሉ፡፡ ከእነዚህ የቅርብ

ዘመዶች መካከል በገጠር የሟች አባት፣ ወንድሞች ወይም ወንድ ልጆች፣ ጥቁር ኮፊያ ሲደፉ፣ እናት፣ እህቶች ወይም ሴት ልጆች፣ ጥቁር ሻሽ ያስራሉ፡፡ በከተማ ከጥቁር ኮፊያና ሻሽ በተጨማሪ፣ ከሁለቱም ጾታዎች አንዳንዶቹ ሙሉ ጥቁር በመልበስ ያዝናሉ፡፡ ከአቶ ደባልቄ የቀጠሮ ለቅሶ ላይ በተደረገው ምልከታ ከልጆቻቸው መካከል፣ ወንዶቹ ጥቁር ኮፊያ ደፍተው፣ ሴቶቹ ጥቁር ሻሽ አስረውና ሁለቱም ጾታዎች ወገባቸው ላይ ገመድ ታጥቀው ሲያስቅሱ ተስተውለዋል፡፡



ምሥል ሃያ አንድ፣ የቅርብ ሀዘንተኞች አለባበስ ምልከታ በተካሄደባቸው ሁለት የለቅሶ ሥርዓቶች (ፎቶ በለማ ንጋቱ)

እነዚህ አለባበሶች ሀዘንተኛው ለሟች በጣም የቅርብ ሰው መሆኑን ከመጠቆማቸው በተጨማሪ፣ ለባሾቹ መሪር ሀዘን ማዘናቸውን መግለጫወች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ በገመድ መታጠቅ የሟችን በአጭር መቀጨት ወይም ባልታሰበ አደጋ መሞት አመልካችነት ሲኖረው፣ ያልተለፋ ቁረንጮ፣ ጆንያ ወይም ቡትቶ ማሸረጥ ደግሞ፣ በደረሰው መሪር ሀዘን ራስን መጣልንና ከክብር መውረድን ያመለክታል፡፡ ለዚህ ደግሞ፣ አዳም ‹‹አትብላ›› ተብሎ የተከለከውን ዕፀበለስ በልቶ በተገኘ ጊዜ ተረግሞ ከገነት ወደተገኘባት ምድር ሲሰናበት የቁርበት ልብስ እንዲለብስ መደረጉ፣ ከክብሩ ለመውረዱ ጥሩ ማሳያ ሁኖ ተገኝቷል (ኩፋ.4፣23-24)፡፡ ማቅና በርኖስ መደረብ ደግሞ፣ ልብሶቹ ሰውነትን እየኮሰኮሱ ምቾት እንደሚነሱት ሁሉ፣ የሟች መታጣትም ሕሊናን እየኮሰኮሰ ረፍት መንሳቱን የማሳየት ትዕምርትነት አላቸው፡፡

የቅርብ ሴት ቤተሰቦች የሟችን ረፍት እንደሰሙ፣ እንደእርባን፣ ድሪ፣ መስቀል፣ ጉትቻና አንባር የመሳሰሉትን ጌጣጌጦች፣ አውልቀው እንደሚያስቀምጡ መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ፡፡ ማተባቸውን በነጭ ክር እንደሚቀይሩ፣ ቀሚሳቸውን ገልብጠው እንደሚለብሱም ይገልጻሉ፡፡ ሟች ሴት ከሆነች በቀሚሷ እጅጌዎች መቀነት አስገብተው የቀሚሷን የፊቱን ወደኋላ በማድረግ አንገታቸው ላይ መቀነቱን አስረው በጀርባቸው እንደሚለብሱትና በነጠላቸው አንድ ጫፍ ወገባቸውን አስረው ሌላኛውን ጫፍ ወደኋላ በመመለስ ከአንገታቸው ዘቅዝቀው እንደሚቋጥሩት ለመመልከት ተችሏል፡፡ እንዲህ አይነቶቹ አለባበሶች እስከአክስት ድረስ ያለን የቅርብ ዝምድናና የልብ ጓደኝነትን አመልካቾች እንደሆኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡





ምሥል ሀያ ሁለት፣ የሟች የቅርብ ቤተሰብና ጓደኛ የሆኑ ሴቶች ሀዘናቸውን የሚገልጹባቸው አለባበሶች (ፎቶ በለማ ንጋቱ)

ሟች ትዳር የመሰረተ ወንድ ከሆነ ሚስቱ ኮቱን ከላይ ደርባ፣ ሱሪውን ከጉልበቱ አካባቢ በመርፌ ቁልፍ አያይዛ የእግሮቹን ወደፊት፣ የወገቡን ወደኋላ፣ በማድረግ ከአንገቷ አጥልቃ እንደምትለብስ ከምልከታ መረጃዎቹ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህም በአንድ በኩል የሚስትነት የሀዘን መግለጫ ምልክቷ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ቃልኪዳኗንና ሀይማኖቷን በጽናት ጠብቃ የያዘች መሆኗን አመልካች ትዕምርትነት አለው፡፡ ይህን አለባበስ አርባ እስኪወጣ ወደቤተክርስቲያንም ሆነ ገበያ ስትሄድ ተግባራዊ እንደምታደርግና እስከስድስት ወርና ዓመት ድረስ የሚቀጥሉበትም እንዳሉ መረጃ አቀባዮቹ ይገልጻሉ፡፡ ተዝካር ከወጣ በኋላ የሀዘን መግለጫ አለባበሱን ተግባራዊ

የሚያደርጉት ከላይ በአቶ ዓለምነው አሉላ እንደተጠቆመው በአካባቢው ሰው ሞቶ ለቅሶ በሚውሉበት ጊዜ ብቻ እንደሆነም ይገልጻሉ፡፡

ኮት ደርቦ በላዩ ላይ ሱሪ በአንገት አጥልቆ ለባል ሀዘንን የመግለጽ ልማድ ጥናቱ በተካሄደባቸው በሁሉም ወረዳዎች በተመሳሳይ ሁኔታ የሚተገበር ሲሆን፣ ልማዱ ከአባት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ መሆኑንም መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን፣ ባልተለመደ ሁኔታ በላይ ጋይንትና በፋርጣ ወረዳዎች ወንድ ሲሞት፣ ልጅ፣ ወንድምና እኅት ሳይቀር ሱሪ እየለበሱ መሆናቸውን አቶ ገበያው ዓለሜ (አባ.2፣ ቁ.11፣ ክፍ.1.3.2.፣ አን.1-2)፣ እና አቶ ጸጋየ ጀንበሬ (አባ.2፣ ቁ.19፣ ክፍ.1.1.2.2.፣ አን.2) እንደቅደም ተከተላቸው ያስረዳሉ፡፡

በላይ ጋይንት፣ ሴት ልጅ ያልወለደች እናት ስትሞት ወንድ ልጇ ቀሚሷን የመልበስ፣ በፋርጣ ሚስት ያላገባ ወንድ ሲሞት፣ እናቱ ሱሪውን የመልበስና በሁሉም ወረዳዎች ሴቶች የወንድማቸውን ኮት የመልበስ ልማዶች ቢኖሩም፣ በአሁኑ ሰዓት በወንዶች እየታየ ያለውን ለሴት ቀሚስና ለወንድ ሱሪ የመልበስ ሁኔታ እየገሰጹና የማስወለቅ እርምጃ እየወሰዱ መሆናቸውን እነዚሁ መረጃ አቀባዮች በአጽንኦት ይገልጻሉ፡፡

ከእነዚህ በተጨማሪ፣ ከላይ በአባ አቸነፍ እንደተገለጸው ማቅ፣ በርኖስና ድሪቶ ለብሶ፣ ቁረኝጮና ጀንያ ታጥቆ መሪር ሀዘን በሚገለጽበት ልማድ ዙሪያም፣ በስማዳና በላይ ጋይንት ወረዳዎች ለውጦች እየታዩ መሆናቸውን መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ፡፡ ሀዘንተኞቹ ከላይ የተዘረዘሩትን ልብሶች በመልበስ ፋንታ፣ ግብገር እንደተጠራ ሰው አዳዲስ ልብሳቸውን እየለበሱ ለቅሶ ላይ መዋል እንደጀመሩና የማሕበረሰቡ አባላት ለውጡን በበጎ አለማየታቸውን አባ አቤ ገበያው (አባ.2.፣ቁ.25) ይገልጻሉ፡፡ በዚህም የተነሳ ለቅሶ ላይ፣

ፊትማ ሰው ሲሞት ማቅም ይለበሳል፣
ፊትም ይመለጣል፣
ዛሬማ ሰው ሲሞት አዲስ ይለበሳል፣
ጸጉርም ይነቀሳል፣
ይህን ያየ እግዚአብሔር በየት ይመለሳል፡፡ እየተባለ ሲገጠም መስማታቸውንም ይገልጻሉ፡፡

አሁን እንደሚታየው ዘመን የራሱን ለውጥ ይዞ ሳይመጣ፣ በአካል ላይ በሚፈጸሙ የሀዘን መግለጫ ልማዶች ላይ እንደተደረገው ሁሉ፣ በአለባበስ በሚገለጽ የሀዘን ልማድ ላይም አጼ

ኃይለሥላሴ አዋጅ አውጥተው እንደነበር ማህተም ስላሴ (1942፣593) እንደሚከተለው ይገልጻሉ። ‹‹ዘመድና ወዳጅ በሞተ ጊዜ ስለሀዘኑ ምልክት በጫፉ ጥቁር ጥለት የተሰራበት ወይም የተለጠፈበት ነጠላ ልብስ እየለበሰ ቢገኝም በርኖስ እየደረበ ይዘን እንጂ ወይባ ወይም ጥቁር ወይም ማናቸውንም አይነት ቀለም የገባ ከል መልበስ እንዲቀር ይሁን።››

በአጠቃላይ በአለባበስ ሀዘን የሚገልጽበት ልማድ የሟችን ጾታና እድሜ፣ ማሕበራዊ ደረጃ ከማሳየቱ በተጨማሪ ሀዘንተኞቹ ከሟች ጋር ያላቸውን ዝምድናም ይጠቁማል። ቀጥሎ ደግሞ በተለያየ መንገድ የሚተገበሩት የሀዘን መግለጫ ልማዶች ቀርበዋል።

## 5.3. ሌሎች የሀዘን መግለጫ መንገዶች

በአካል ላይ ከሚፈጸሙትና በአለባበስ ከሚገለጹት የሀዘን መግለጫዎች በተጨማሪ፣ የሟች የቅርብ ቤተሰቦች በተለያዩ መንገዶች ከምቾት በመራቅና ራሳቸውን በማጎሳቆል ሀዘናቸውን የሚገልጹባቸው ልማዶች፣ በዚህ ስር ይካተታሉ። መረጃዎች እንደሚያሳዩት፣ መዋቢያዎችን አለመጠቀም፣ ምቾት በሚሰጡ ቁሳቁሶች አለመገልገል፣ ደስታ ካለባቸው ቦታዎች ራስን ማግለል፣ ከዋና ዋናዎቹ የሀዘን መግለጫዎች ውስጥ ይጠቀሳሉ። ለምሳሌ አቶ አቸነፍ፣ አቶ ዋለና አቶ ገበያው እንደሚያስረዱት፣ በስማዳ፣ በፋርጣና በላይ ጋይንት ወረዳዎች፣ ሀዘንተኛ ሴቶች ሁሉንም አይነት መዋቢያዎቻቸውን ከጆሮዎቻቸው፣ ከአንገታቸውና ከእጆቻቸው አውልቀው ያስቀምጣሉ። ቅቤም ሆነ ማንኛውንም አይነት ቅባትም አይጠቀሙም።

በሌላ በኩል ሀዘንተኞቹ በድንኳን ወይም በቤት ውስጥ ሆነው ለቅሶ ደራሹን የሚቀበሉት ወለል ላይ በመቀመጥ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል። የሚተኙትም አልጋ ላይ ሳይሆን መሬት ላይ መሆኑን አቶ ወንዳያ ጓንጉል (አባ.2፣ ቁ.15፣ ክፍ.1.3.3.፣ አን.1) ይገልጻሉ። ሙቀት የሚሰጥ የሌሊት ልብስ እንደማይደርቡና ዘፈንም ሆነ ጭፈራ ካለበት የደስታ ቦታ ራሳቸውን እንደሚያገሉ፣ ቴሌቪዥናቸውንም ሆነ ሬዲዮናቸውን እንደማይከፍቱም ያስረዳሉ።

ይኸኛው የሀዘን መግለጫ ልማድም ቀደም ሲል እንዳየናቸው ሁሉ ከእሥራኤላውያን የሀዘን አገላለጽ ልማድ ጋር ተቀራራቢነት ያለው መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። ለምሳሌ Levine (2004፣117)፣ የሟች የቅርብ ቤተሰቦች ጺማቸውን እንደማይላጩ፣ ጸጉራቸውን

እንደማይስተካከሉ፣ አዲስ ልብስ እንደማይለብሱ፣ ግብዣም ሆነ ደስታ ወዳለባቸው ቦታዎች እንደማይሄዱ፣ ቴሌቪዥን ከማየትና ሬዲዮ ከመስማትም እንደሚታቀቡ ይገልጻሉ።

በተጠኚው ማሕበረሰብ የሟች የቅርብ ቤተሰቦች በዚህ መንገድ የሚቆዩበት የጊዜ ገደብ እንደግለሰቦቹ ሁኔታ ቢለያይም፣ ለወንድ በአርባው፣ ለሴት በሰማንያዋ፣ ተዝካር እስኪወጣላቸው ድረስ መቆየት እንደሚጠበቅባቸው ማሕበራዊ ደንቡ እንደሚያስገድድ፣ ከመረጃ አቀባዮቹ መካከል አቶ ጸጋዬ ጀንበሬ (አባ2.፣ ቁ.19፣ ክፍ.1.3.3.፣ አን.1) ያስረዳሉ። የሟች የቅርብ ቤተሰቦች ከላይ እስከተገለጸው የጊዜ ክልል እንዲያዝኑ በአካባቢው ማሕበረሰብ ቢጠበቅባቸውም፣ ለሟች እንዳላቸው ፍቅር ከዚህ ጊዜ ቀድመው ሊተው ወይም እስከዓመትና ከዚያም ላለፈ ጊዜ ቀጥለው ሊያዝኑ እንደሚችሉ ያስረዳሉ። አቶ ዓለምነው አሉላ (አባ.2፣ ቁ.23፣ ክፍ.1.3.3.፣ አን.1) እንደሚገልጹት፣ ባሏ የሞተባት ሴት በአካባቢው ለቅሶ ሲኖር እስከስድስት ወርና እስከዓመትም ቢሆን ራሷን እንዳጎሳቀለች ትወጣለች። ከዚህ አለፍ የሚሉት ቃል ኪዳን አክባሪ ሴቶች ደግሞ፣ ባል ላለማግባት ያለ እድሜያቸው እንደሚቆርቡና እንደሚመነኩሱ ይገልጻሉ።

ሀዘንተኞቹ ተዝካር ሳይወጣ በጣም ራሳቸውን በሚያጎሰቁሉበትና ተዝካር ከወጣም በኋላ ሀዘናቸውን በሚቀጥሉበት ጊዜ፣ ተቆርቋሪ ዘመድ ወይም ጓደኛ ቀርቦ፣ ሀዘናቸውን በልክ እንዲያደርጉ ወይም እንዲተው እንደሚመክራቸው ለመረዳት ተችሏል። ከተቆርቋሪ ዘመድና ጓደኛ በተጨማሪ፣ የሀይማኖት አባቶችም ይገስጿቸዋል። ይሁንና በአንድ በኩል ከአርባ ቀን በፊት የሟች ዓይን አይፈስም ተብሎ ስለሚታሰብ ይታዘበናል በሚል እምነት፣ በሌላ በኩል ከአካባቢው ማሕበረሰብ በተለይም ከባል ወይም ከሚስት ወገን የሚሰነዘርን ሽሙጥ ከመፍራት፣ ራሳቸውን በማጎሳቆሉ እንደሚቀጥሉበት አባ አቸነፍ አንግዳ (አባ2.፣ ቁ.12፣ ክፍ.1.3.3.፣ አን.1) ያስረዳሉ።

የሟች መለየት የሚፈጥረው ጥልቅ ሀዘን በሚያስከትለው ተስፋ መቁረጥ፣ ቃል ኪዳንን ላለማፍረስ በሚኖር ጽናትና ሀይማኖቱም ሆነ ማሕበረሰቡ ለእንዲህ አይነቶቹ ጠንካሮች የሚሰጠው ክብር፣ አንዳንዶች እድሜ ልካቸውን ከደስታ ርቀው እንዲኖሩ እንደሚያደርጓቸውም መረጃ አቀባዮቹ ይገልጻሉ።

እንደተጠኚው ማሕበረሰብ ራስን በማጎሳቆል ሀዘንን የመግለጽ ልማድ፣ በኢትዮጵያ በሚገኙ ሌሎች ማሕበረሰቦችም የተለመደ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። ለምሳሌ በትግራይ ማሕበረሰብ

ሀዘን ውስጧን የሰበራት ሴት፣ አርባ እስኪወጣ ድረስ ጸጉሯን በሻሽ አስራ፣ ሳትታጠብ፣ ሳታበጥርና ሳትሰራ፣ በቆሻሻና ቅማል እየተሰቃየች እንደምትቀመጥ ነጋ (2002) ይገልጻሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ ቅቤም ሆነ ቅባት አስከስድስት ወር ድረስ እንደማትጠቀምና ሟች ባሏ ከሆነ ደግሞ አስከአንድ ዓመት ድረስ እንደምትቆይ ያስረዳሉ፡፡ በተለይ እስከሰባተኛው ቀን ድረስ ሌሊት ወለል ላይ በመተኛትና የሟች የወንድ ዘመዶች ቀን የለበሱትን ሳያወልቁ በተቀመጡበት በመተኛት ሀዘናቸውን እንደሚገልጹም ያስረዳሉ፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የሸዋ ክርስቲያን አማሮችም ራሳቸውን በማጎሳቆል ሀዘናቸውን እንደሚገልጹ ፋሲካ (1953) ያስረዳሉ፡፡ የሟች ነፍስ ከወጣበት ጊዜ አንስቶ የቸኮሉት እስከአስራ ሁለተኛው ቀን፣ ሌሎቹ ከአርባ ቀን እስከአንድ ዓመት ድረስ፣ ወለል ላይ በመተኛት ሀዘናቸውን ይገልጻሉ፡፡ ሀዘንተኞቹ ጫማ ካላቸው እስከአስራ ሁለተኛው ቀን ድረስ የማይጫሙ ሲሆን፣ ሴቶች ጸጉራቸውን አርባ እስኪወጣ ድረስ እንደማይታጠቡ፣ ቅቤም እስከአንድ ዓመት ድረስ እንደማይቀቡና እንደመዋብ ስለሚቆጠር ጥፍራቸውንም እንደማይቆርጡ ይገልጻሉ፡፡ እንደሰዎቹ ጽናት ሊለያይ ቢችልም፣ ከአስራአምስት እስከአርባ ቀን ለሚሆን ጊዜ ወለል ላይ እንደሚተኙና ብርድ ልብስ እንደማይለብሱም ያስረዳሉ፡፡

በአጠቃላይ ጌጣጌጦችን በማውለቅ፣ መዋቢያ ቅባቶችን ባለመጠቀም፣ ወንዶች ጺማቸውን በማሳደግ፣ ሴቶች ጸጉራቸውን በመላጨት ወይም ባለማበጠርና ባለመታጠብ፣ ደስታ ካለበት አካባቢ ራስን በማግለል፣ ምቾት የሚሰጡ ነገሮችን ባለመጠቀም ሀዘን የሚገለጽባቸው መንገዶች፣ የሟችን አፈር መሆን በማሰብ ራስን በአካልም ሆነ በሥነልቡና የማጎሳቆያ የሀዘን መግለጫ መንገዶች ናቸው ለማለት ይቻላል፡፡

ቋሚዎች ከደስታ ርቀው በሚቆዩባቸው ጊዜያት፣ ሟችን የሚያስቡት ራሳቸውን በማጎሳቆል ብቻ ሳይሆን፣ የተለያዩ የመታሰቢያ ሥርዓቶችን በማከናወን ጭምር ነው፡፡ የእነዚህ የመታሰቢያ ሥርዓቶች ክንውናዊ ገለጻ በሚቀጥለው ምዕራፍ ቀርቧል፡፡

## ምእራፍ ስድስት

### 6. የመታሰቢያ ሥርዓት

የመታሰቢያ ሥርዓት የሟች ቤተሰቦች ወይም የቅርብ ዘመዶች የሟች ነፍስ እንድትጸድቅ በመመኘት ወይም እነሱን መጥፎ ነገር እንዳይገጥማቸው በመፍራት፣ ቀብር ከተፈጸመ በኋላ የሚያከናውኗቸውን ልዩ ልዩ ሥርዓቶች ያካትታል። እነዚህ ሥርዓቶች በአመዛኙ ሀይማኖታዊ ተግባራት የሚፈጸሙባቸውና በጸሎት የሚታጀቡ ሲሆኑ፣ ከሟች ዕድሜና ከአሟሟት ሁኔታ ጋር በተያያዘ፣ ሥርዓቶቹ ተሟልተው የማይፈጸሙበት ሁኔታ እንዳለ መላከ ሰላም ዳኛቸውና ሌሎችም (1986) እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

> እንደሚገልጹት፣ በመታነቅ፣ መርዝ በመጠጣትና በተለያዩ ድርጊቶች ህይወታቸውን ያሳለፉ... በራሳቸው ወይም በሌላው ህይወታቸው እንዲያልፍ የሚያደርጉ ... ሁሉ በቅዱሳት መጻህፍት የተከለከለና በቤተክርስቲያን የተወገዘ ነው። ... በሞቱም ጊዜ በሕግና በሥርዓት ኖረው በክብር ለሞቱ ሰዎች የሚፈጸመው የቤተክርስቲያን ጸሎተ ፍትሃትና ሌላውም ስርዓት ሁሉ አይፈጸምላቸውም (ገጽ፣12)።

ቀደም ሲል እንደታዩት እንደሌሎቹ ከቀብር ጋር የተያያዙ ሥርዓቶች ሁሉ፣ የመታሰቢያ ሥርዓትም ቀደምትነት ያለው መሆኑ በማህተመ ሥላሴ (1942) እንደሚከተለው ተገልጿል።

> በኢትዮጵያ ሲያያዝ በወረደው ልማድ መሰረት ዕድሜው 12 ዓመት ከሆነው ልጅ ዠምሮ ወደላይ ላለው ክርስቲያን ሁሉ በሞተ ጊዜ ቋሚ ዘመድና ወዳጅ ሕግ አድርገው መጽሀፈ ግንዘት እንደሚያዘው ፍታት ያስፈታሉ፤ ደግሞ በሳልስቱ፣ በሰባቱ፣ ባርባው፣ በሰማንያው፣ በመንፈቁ፣ ባመቱ፣ በሰባት ዓመቱ፣ በ14 ዓመቱ፣... ይደግሱና ካህናትን፣ ቤተዘመድንና፣ ወዳጅን ይጋብዛሉ፤ ለነዳያንም ምጽዋት ይሰጣሉ። ከነዚህ ከተመለከቱት ቀኖች ሌላ ቋሚ ዘመዶች ... በየመቱ ያስቀርባሉ።

ይህ ሥርዓት ከእሥራኤላውያን ሬሳን ሽቱ የመቀባት ልማድ የመጣ መሆኑን መሪጌታ ክፍለማርያም አለነ (አባ.2፣ቁ.2) ያስረዳሉ። ለሟች የሚጠቅመው ሬሳውን ሽቱ መቀባት

ሳይሆን ለሽቱ መግገ የሚሆነውን ገንዘብ ለድሆች መመጽወት እንደሆነ ሊቃውንት መክረው፣ ሥርዓቱን እንደቀየሩት በፍትሃ ነገሥት ተገልጾ እንደሚገኝ ይገልጻሉ፡፡ ሐዋርያትም ሬሳን ሽቱ መቀባቱ መዓዛ ሥጋ ነው እንጂ መዓዛ ነፍስ ስለማይሆን ለሟች ዳዊት ድገሙለት፣ መስዋእት ሰውለት፣ ማለታቸውንና ለሽቱ መግገ የሚውለውን ገንዘብ ለምጽዋት እንዲውልና መታሰቢያ እንዲደረግለት መደንገጋቸውን በመጥቀስ የመታሰቢያን ሥርዓት አጀማመር ያስረዳሉ፡፡

እነዚህን የመታሰቢያ ሥርዓቶች፣ ሟች ከተቀበረበት ዕለት ያላቸውን ርቀትና ተደጋጋሚነታቸውን መሰረት በማድረግ፣ በሁለት መክፈል ይቻላል፡፡ የመጀመሪያዎቹ የሟች ቀብር ከተፈጸመበት ዕለት አንስቶ ቀናት እየተቆጠሩ በቅደም ተከተል የሚከበሩ ሲሆኑ፣ እነሱም፡- ሰልስት፣ ሰባት፣ አስራ ሁለት፣ ሠላሳ፣ አርባ፣ ሰማንያ፣ መንፈቅ፣ ዓመት፣ ሰባት ዓመት፣ አስራ አራት ዓመት የሚባሉት ሲሆኑ ሁለተኛው ተዝካር ነው፡፡

ከቀብር በኂላ በዕለትም ሆነ በቀጠሮ ለቅሶ የሚከናወነው የመጀመሪያው ተግባር፣ ለቀስተኛውን የማሰናበት ሥርዓት ነው፡፡ ይህ በvan Gennep የሽግግር ሥርዓት ደረጃ ሲታይ፣ ሀዘንተኞቹ ሰከን ብለው ማን እንደመጣና እንዳልመጣ ለመቆጣጠር ልቦና የሚገዙበት፣ ሟች በአካል ከሙታን ጋር፣ በነፍስ ቀደም ሲል ከሞቱ ወገኖቹ ጋር የሚቀላቀልበት ስለሆነ፣ በመታቀፍ ሥርዓት ስር እንዲታይ ያደርገዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የመታሰቢያ ሥርዓት ከዕለት እንደሚጀምር መላከ ሠላም ዳኛቸውና ሌሎችም (1986፣49) ቢያስረዱም፣ የነፍስን ወደአስገኝዋ እግዚአብሔር መሄድና የሥጋን ወደአፈር መመለስ ከመግለጽ ውጭ፣ የትኛው ሥርዓት ለመታሰቢያ ተብሎ እንደሚፈጸም አይገልጹም፡፡ መሪጌታ ክፍለማርያምም የመታሰቢያ ሥርዓት በዕለት የሚጀምር በመሆኑ ይስማማሉ፡፡

በዚህ ጥናት፣ በዕለት ከሚከናወኑት የመታሰቢያ ሥርዓቶች የመጀመሪያዎቹ፣ ከቀብር በኂላ የሚከናወኑት ሀዘንተኛን የማሰናበትና የዕዝን ሥርዓቶች ተደርገው ተወስደዋል፡፡ ምክንያቱም ከቀብር መልስ ለቀስተኛው ሀዘንተኞቹን ‹‹እግዚአብሔር ያጽናችሁ›› ሲላቸው፣ ‹‹እሱን›› ወይም ‹‹እሷን ያስችለው/ላት›› በማለት ከደቂቃዎች በፊት አፈር የተመለሰበትን ቤተሰባቸውን እንደተለያቸው ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያስቡት በዚህ ሥርዓት ስለሆነ ነው፡፡ የዕዝን ሥርዓትም ቤተሰብና የቅርብ ዘመድ ከሟች ረፍት በኂላ ለመጀመሪያ ጊዜ እህል የሚቀምሱበትና ‹‹ነፍስ

ይማር››፣ የሚባልበት ስለሆነ ሟች ይታሰብበታል። van Gennepን (1960፣ [1908]) ዋቢ በማድረግ Yoder (1986፣149) እዝን የመታቀፍ ሥርዓት /rite of incorporation/ አካል መሆኑን ይገልጻሉ።

የቀብር ሥርዓት መጠናቀቅና የመታሰቢያ ሥርዓት መጀመር፣ ሀዘንተኞቹ ወደደጀ-ሰላም ወይም ማርገጃ ተመልሰው፣ በመሪው ቄስ ጸሎት በመስጠት ይጀመራል። አቡነ ዘበሰማያት ተደግሞ ‹‹እግዚኦ መሀረነ ክርስቶስ›› ከተባለ በኋላ፣ ከለቅሶው ጋር ንኙነት ያላቸውና ሌሎችም መልእክቶች ይተላለፋሉ። የሟች ቤተሰቦች ተወካይ ወይም ከለቅሶ አስተናባሪዎቹ አንዱ፣ ለቀስተኛውን አመስግኖ፣ ‹‹ያላየነው ዘመድ የለም ከኛ መከራ ያድናችሁ። እህል ውሃ ስለተዘጋጀ በቤት ሳትደርሱ እንዳትሄዱ››፣ በማለት ለቀስተኛውን ይጋብዛል።

በላይ ጋይንትና፣ በፎገራ ወረዳዎች በገበያ ዳር የሚካሄድ የቀጠሮ ለቅሶ ስለሚኖር፣ ቀኑ መቼ እንደሚሆን ይቆረጥና ‹‹በሩቅ ላለው ዘመድ ሁሉ ንገሩ››፣ ይባላል። በስማዳ፣ በፋርጣና በደብረታቦር ዙሪያ ወረዳዎች የሌላ ሰው የቀጠሮ ለቅሶ ካለ፣ ‹‹በዚህ ቀን ከዚህ ቦታ የእገሌ የቀጠሮ ለቅሶ ስላለ ‹እንድታላቅሱን› ብለዋል›› ተብሎ ይለፈፋል።

ከለቅሶ ጋር ግንኙነት ከሌላቸው መረጃዎች፣ በአካባቢው የአስተዳደር አካላት የሚተላለፉ አስተዳደራዊ መልእክቶችና ሌሎች ማሕበራዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ይገኙባቸዋል። ለምሳሌ ልዩ ልዩ ማሕበራዊ ጉዳዮችን ከሚመለከቱት ውስጥ፣ ለቅሶው ከተካሄደበት ወይም ከአጎራባች ቀበሌዎች የጠፋ የቤት እንስሳ ካለ፣ መልኩና ምልክቶቹ ተገልጸው፣ ‹‹ያያችሁ›› ወይም ‹‹የደረሰባችሁ›› ተብሎ ይጠየቃል። በሌባ የተሰረቁ እንስሳት ካሉም፣ የጠፉበት ቦታና ቀን ከነመልካቸው ተጠቅሶ፣ የአፋልጉን ትብብር ይጠየቃል። ከአስተዳደር አካላትም ሆነ ከሽማግሌዎች ሌሎች አስቸኳይ መልዕክቶች ካሉ፣ በዚህ ሰዓት ይነገራሉ። የቀብር ሥርዓቱ ፍጻሜ ይሆንና የሥንብት ሥርዓቱ በሚከተለው መንገድ ለቀስተኛውን በመሸኘት ይጀመራል።

## 6.1. የሥንብት ሥርዓት

የሟች የቅርብ ዘመዶች ቤተሰቡን ከቤት ሳያስገቡ ባይመለሱም፣ የሟች ቤት ከቤተክርስቲያኑ ራቅ ያለ ከሆነ፣ ወደተለያየ አቅጣጫ የሚሄዱት ለቀስተኞች ሀዘንተኞቹን የሚሰናበቱት ከማርገጃ ነው። ሀዘንተኞቹ ይህን ስለሚያውቁ፣ ሰብሰብ ብለው በዕድሜ ከፍ ያለውን ወደፊት

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADDIS ABABA, ETHIOPIA

አስቀድመው ይቀመጣሉ። ከተሰናባቾቹ መካከል በአገር ርቀት ወይም በሥራ ምክንያት የቸኮሉት፣ ሰልፍ ይዘው ተራ በተራ እየቀረቡ ጉልበታቸውን በእጃቸው በመንካት ‹‹እግዜር ያጥናችሁ እንግዲህ የሞተ አይመለስም ያለውን ይባርክላችሁ፤ እግሩን ደረቅ ያድርገው›› እያሉ ይሰናበታሉ*። ሀዘንተኞቹም ከተቀመጡበት እንደመስገድ እያሉ፣ ሟች ታሞ ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ የሞተ ከሆነ፣ ‹‹ቸር ይምጣላችሁ›› በማለት መልስ ይሰጣሉ። ሟች ሳይታሰብ በድንገት ወይም በአደጋ (በሰው፣ በውሃ፣ በእሳት ወዘተ.) የሞተ ከሆነ፣ ‹‹እንደኛ ከመሆን ያድናችሁ›› ወይም ‹‹አይድረስባችሁ›› በማለት መልስ ይሰጣሉ።

በከተማ አካባቢ ግን፣ ሀዘንተኞቹ ለቀስተኛውን ማርገጃ ላይ አያሰናብቱም። ወደሟች ቤት መልስ ከተደረገ በኋላ፣ ወደድንኳን ገብተው እህል ውሃ ይቀምሳሉ። አጅቦ የመጣው ለቀስተኛ ተነስቶ ከፊት ለፊታቸው በመቆም፣ ጎንበስ በማለት ሲሰግድ፣ እነሱም ከተቀመጡበት ከአንገታቸው ሰበር በማለት አጸፋውን ሰጥተው ያሰናብታሉ።

በገጠር በእጅ እየነኩ የሚሰናበቱበት ምክንያት፣ ከለቅሶው መዋላቸው እንዲታወቅላቸው ለማድረግ እንደሆነ አቶ ጸጋየ ያስረዳሉ። ቀኝ ጌታ ዜናዊ እንደሚያስረዱት ለቅሶ አለመድረስ ለቀሪው ሰው ትልቅ ሀፍረት ሲሆን፣ ለሀዘንተኞቹ ደግሞ ከባድ በደል ነው። ስለዚህ ከለቅሶው የዋለ ሰው በምንም መንገድ መዋሉን ሳያሳውቅ አይሄድም። በላይ ጋይንት በቀጠሮ ለቅሶ ስንብት ጊዜ፣ አሰናባቾቹ በደንብ የማያውቋቸው የሚመስላቸው ወጣቶች፣ የሚሰናበቱትን ሰው ጉልበቱን እንደነኩ ሳይቃኑ፣ ‹‹የእገሌ ልዥ ነኝ፤ አውቀኸኛል?›› ብለው እንደሚጠይቁ አቶ ወንዳያ ጓንጉል (አባ.2፣ ቁ.15፣ ክፍ.1.4.1.፣ አን.1-2) ያስረዳሉ። በፎገራና በስማዳ ወረዳዎችም ተመሳሳይ ባህል እንዳለ ለመረዳት ተችሏል።

በከተማ ጉልበት ነክቶ መሰናበት የቀረው፣ የአንድ ሰው ለቅሶ መዋልና አለመዋል የሚረጋገጠው በሀዘንተኞቹ ብቻ ሳይሆን በእድር ዳኞች ጭምር በመሆኑ እንደሆነ አቶ አበበ በዛ (አባ.2፣ቁ.29) ገልጸዋል። ምልከታ ከተካሄደባቸው የዕለት ለቅሶዎች፣ በእሙሀይ አስማረች (በ1/10/04

---

*በእሥራኤልም ለቅሶ ደራሽ ጓደኞች ከቤት ሲወጡ ለቤተሰቡ ‹‹ጌታ እንደ ጺዮንና እየሩሳሌም ሀዘንተኞች መጽናናትን ይላክላችሁ›› ወይም ‹‹መንግሥተ ሰማያት መጽናናትን ትላክላችሁ››፣ በማለት ባሕላዊውን መሰናበቻ እንደሚያቀርቡ Levine (2004) ይገልጻሉ።

የተፈጸመ) እና በወ/ሮ ቀኑብሽ (በ22/09/04 የተፈጸመ) ለቅሶዎች ከቀብር በኋላ የእድር አባላት ስም ጥሪ ሲደረግ ለመታዘብ ተችሏል፡፡

ከላይ በተገለጸው መንገድ ከቀብር መልስ ጉልበትን እየነኩ መሰናበት፣ በእሥራኤል፣ በትግራይና በሰሜን ሸዋ አማሮችም የተለመደ መሆኑን Levine (2004)፣ ፋሲካ (1953፣209) እና ነጋ (2002፣112) እንደቅደም ተከተላቸው ይገልጻሉ፡፡ በእሥራኤል ለቅሶ ደራሽ የተጎዱ ጓደኞች ከቤት ሲወጡ ለቤተሰቡ ‹‹ጌታ እንደ ጺዮንና እየሩሳሌም ሀዘንተኞ መጽናናትን ይላክላችሁ›› ወይም ‹‹መንግሥተ ሰማያት መጽናናትን ትላክላችሁ››፣ በማለት ባሕላዊውን መሰናበቻ ያቀርባሉ፡፡ በትግራይና በሰሜን ሸዋ አማሮች የስንብቱ ዓላማ፣ ከለቅሶ መዋልን ለማሳወቅ እንደሆነም ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከለቅሶ አለመገኘት የሚችን ወገን የሚያስቀይመውና ቀሪውንም የሚያሸማቅቀው በተጠኚው ማሕበረሰብ ብቻ ሳይሆን፣ በእነዚህም ጭምር መሆኑን መረጃዎቹ ያሳያሉ፡፡ ማርየ (2008፣34) በፎገራ ወረዳ አንድ ሰው ለቅሶ ባይደርስ፣ ተጎጂው ክፍል ቂም ይዞ የቀሪው ዘመድ ሲሞት በመቅረት ብድር እንደሚመልስ ይገልጻሉ፡፡ ለቅሶ መቅረት ማህበራዊ ግንኙነትን እንደሚጎዳና የእግዜር ሰላምታ እንደሚያስቀርም ያስረዳሉ፡፡

ይህም በተጠኚው ማሕበረሰብ በሀዘን ጊዜ ያለው መደጋገፍ ጠንካራ መሆኑን፣ የሚች መለየት በቀሪው ማሕበረሰብ ላይ ጉዳት ማስከተሉን፣ ከግለሰባዊነት ይልቅ የቡድናዊነት አስተሳሰብ መኖሩን ያሳያል፡፡ ሀዘንተኞቹን ቤተዘመድ ብቻ ሳይሆን የሚኖሩበት ማሕበረሰብ ጭምር መደገፉ፣ የማሕበረሰቡን ትስስር ከማጠናከሩ በተጨማሪ፣ ሀዘንተኞቹ ሀዘናቸውን የሚገልጹበትን ሁኔታ በማመቻቸት ለከፋ ስነልቡናዊና ማሕበራዊ ጉዳት እንዳይጋለጡ ያደርጋቸዋል፡፡

ሀዘንተኞቹ የቸኮለውን ለቀስተኛ ማርገጃ ላይ ካሰናበቱ በኋላ ወደቤት ይመለሱና፣ እዝኑ ከተዘጋጀበት ድንኳን ወይም የዛፍ ጥላ ስር አርፈው፣ እህል ውሃ እንዲቀምሱ ይደረጋል፡፡ አጅቧቸው ለተመለሰው ለቀስተኛም የእዝን መስተንግዶው በሚከተለው መንገድ ይቀርባል፡፡

### 6.2. የእዝን አቀራረብ ሥርዓት

ከቀብር ሥርዓት ጋር በተያያዘ ለለቀስተኛውና ለሀዘንቶቹ ምግብ (እዝን) ማቅረብ በበርካታ ባህሎችና ሀይማኖቶች የተለመደ መሆኑን ታሪክ እንደሚያስረዳ፣ Yoder (1986፣149) ይገልጻሉ። ከእነዚህም ውስጥ፣ ሲሎን (Ceylon)፣ ኢራን፣ ኢትዮጵያ፣ ናይጀርያ፣ ስዊድን፣ ፖላንድ፣ ሀንጋሪ፣ ሩማንያ፣ እንግሊዝና አሜሪካ ይጠቀሳሉ።

ከእነዚህ በተጨማሪ የእዝን እህል ውሃ ማቅረብ በክርስቲያኖች ዘንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት እንዳለው፣ እነመላከ ሰላም ዳኛቸውና ሌሎችም (1986፣26) ያስረዳሉ። በኢትዮጵያ ከቅርብ ጎረቤት፣ ከዘመድና ከወዳጅ የሚመጣው የእዝን እህል ውሃ ከብሉይ ኪዳን ዘመን ጀምሮ የነበረና ያለ መሆኑንም የሚከተሉትን ማስረጃዎች በመጥቀስ ያስረዳሉ። ‹‹በጥንቱ ጊዜ ሀዘንተኞቹን ሀዘናቸውን ለማስተው ሕይወታቸውን ለማረጋጋት፣ ለማጽናናት ጥቂት ጽዋ ወይንና የበሰለ እህል የማቅረብ ልማድ ነበር›› (ኤር.16፣7። ሆሴ.9፣4)።

የእዝን ምግብ ከላይ በተገለጹት አገሮች የተለመደ ቢሆንም፣ በሚቀርበው ምግብ አይነትና ብዛት እንዲሁም በአቀራረቡ ዙሪያ፣ በርካታ ልዩነቶች እንዳሉ Yoder (1986፣149) ይገልጻሉ። ምግቡ በጎረቤቶችና ጓደኞች ወይም በሟች ቤተሰቦች የሚቀርብበት ሁኔታ መኖሩ፣ የእዝን አቀራረቡ ሥርዓት ድባብ አንዳንዴ ከበራዊ መሆኑና ሌላ ጊዜ በጸጥታ የተዋጠ መሆኑ፣ ከሚታዩት ልዩነቶች ውስጥ እንደሚጠቀሱ ይገልጻሉ። ብዙውን ጊዜ ምግቡ የሚበላው በሟች ቤት ውስጥ መሆኑና ምግቡ የሚቀርበውም ከቀብር ወይም ከሬሳ ማቃጠል ሥርዓት ተከትሎ መሆኑ ደግሞ፣ ከሚያመሳስሏቸው ውስጥ እንደሚጠቀሱ ያስረዳሉ።

እዝን ብዙውን ጊዜ የቡድኑን አባላት ርስበርስ፣ አንዳንዴም ከሟች ጋር የማስተሳሰርና አንዱ አያያዥ ቀለበቱ የተቆረጠበትን የቡድኑን ሰንሰለት እንደገና የማገናኘት ጠቀሜታ እንዳለውም Yoder (1986) ያስገነዝባሉ። መላከሠላም ዳኛቸውና ሌሎችም (1986፣26) እንደሚያስገነዝቡት፣ በኢትዮጵያውያን ባህል ሰው ሲሞት ነፍስ ከወጣችበት እስከቀብር ድረስ የሟች ቤተሰብ ምግብ ስለማይበላ፣ የእዝን እህል ውሃ፣ ሀዘንተኖችን ለማረጋጋት፣ ከሀዘናቸው ለማጽናናትና ከድካማቸው ለማበረታታት ይረዳል።

ምልከታ በተካሄደባቸው የዕለት ለቅሶዎች በከተማ ጠዋት ላይ የእድር አባላት እንጀራ እያዋጡ ወደለቅሶ ቤቱ በመውሰድ ስማቸውን እያስመዘገቡ ሲያስረክቡ፣ በገጠርም በተመሳሳይ ሁኔታ በተዘጋጀ ቋሚ መስፈሪያ (ልክ)፣ ድፍድፍና ጥሬ እያስለኩ ሲሰጡ ለማየት ተችሏል፡፡

በዚህ መንገድ የተሰበሰበውን ጥራጥሬ የማንፈር፣ ጠላውን የመጥመቁና ወጡን የመስራቱ ኃላፊነት በእድር አባላቱ ይከናወናል፡፡ ለዚሁ ተብለው የተገዙ የእድር እቃዎች አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ለቀስተኛው ከቀብር ሲመለስ የማስተናገዱ ሥራም በተመደቡ የእድር አባላት ይከናወናል፡፡ በከተማ እንጀራ በወጥ በሰሃን እየተደረገ፣ ሀዘንተኞቹን አጅቦ ወደሚች ቤት ለተመለሰው ለቀስተኛ በየግል ይሰጣል፡፡ ውሃ አሳላፊም ይኖራል፡፡ በገጠሩ ንፍሮው በወራንታ ይያዝና አንድ ሰው በእፍኙ እየዛቀ በተመጋቢው ጋቢ ላይ ያደርጋል፡፡ ጠላ ቀጁም እግር በእግር እየተከተለ በጣሳ ወይም በጽዋ ያድላል፡፡ የቀመሰው እየወጣ ከላይ በተገለጸው መንገድ እየተሰናበተ ሲሄድ ያልቀመሰው ይተካል፡፡

ለቀስተኛው ቀስበቀስ እየተሰናበተ ሲሄድ፣ የቅርብ ዘመዶችና ጎረቤቶች ከሀዘንተኞቹ ጋር ይቀራሉ፡፡ እስከሰልስት ድረስ የእድር አባላትም በሀዘንተኞቹ ቤት እየተገኙ ለቅሶ ደራሾችን የማስተናገድና ሀዘንተኞቹን የማጽናናት ሥራ ያከናውናሉ፡፡

የእዝን ሥርዓት በስማዳና በፋርጣ ወረዳዎች በተመሳሳይ ሁኔታ እንደሚሰበሰብና እንደሚስተናገድ፣ አቶ ሲሳይ ታደገ (አባ.2.ቀ.28) ያስረዳሉ፡፡ በዕለት ለቅሶ የሚቀርበው ከላይ ከተገለጸው የተለየ ባይሆንም፣ በቀጠሮ ለቅሶ ቤተሰብ በሰፊው ደግሶና ጠምቆ ለቀስተኛውን የሚጋብዝበት ሥርዓት ለየት ያለ ገጽታ እንዳለው ይገልጻሉ፡፡ ልማዱ ቀደም ሲልም የነበረ ቢሆንም፣ በተለይ ከስድስትና ከአምስት ዓመት ወዲህ ‹‹ከማን አንሳለሁ›› በሚል ውድድር ከአቅም በላይ ደግሶ ማብላትና ማጠጣት እየተስፋፋ መምጣቱን ያስረዳሉ፡፡ ሞገስም (2003፣82)፣ በላይ አርማጭሆ ወረዳ የእዝን አቅርቦት የሟችንና የቤተሰቦቹን ሀብታምነትና ለጋስነት በማሳየት ማሕበራዊ ደረጃቸውን ከፍ ለማድረግና ዝና ለማግኘት ተብሎ የሚቀርብበት ሁኔታ እንዳለ ይገልጻሉ፡፡

በዕለት የሚከናወነው የዕዝን ሥርዓት ይህን ሲመስል፣ ከዚህ በኋላ የሚመጡት ከሰልስት ጀምሮ የሚከናወኑ የቀናቀን ሥርዓቶች ደግሞ የሚከተለውን ይመስላሉ።

## 6.3. የቀናቀን አከባበር ሥርዓት

የቀናቀን የመታሰቢያ ሥርዓት የሚጀምረው ቀብር በተፈጸመ በሶስተኛው ቀን ነው። ይህ ሥርዓት የሚፈጸምላቸው ያለጸታ ልነት ለአቅመ አዳምና ሔዋን ለደረሱ የማሕበረሰቡ አባላት ሲሆን፣ ማሕበራዊ ደረጃና ሀብት ለሥርዓቶቹ ድምቀት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። ሟቾቹ የተሻለ ማሕበራዊ ደረጃ ያላቸው ወይም ሀብታሞች ሲሆኑ፣ ለሥርዓቶቹ የሚዘጋጅላቸው ድግስ ለነዳያን እንዲተርፍ ስለሚደረግና ምጽዋትም ስለሚሰጥ ደመቅ ይላል። ማህበራዊ ደረጃቸው ዝቅተኛ ለሆኑና ለድሆች ግን የሚቀርበው ድግስ ለካህናትም የማያረካ ሊሆን ስለሚችል ፈዘዝ ሊል ይችላል። ሟቾቹ ቤተሰብ የሌላቸው ወይም በጣም ደካሞች ካልሆኑ በስተቀር ግን የመታሰቢያ ሥርዓቶቹ አይታጎሉም።

በመታሰቢያ ሥርዓቶቹ ዓለማዊና ሀይማኖታዊ ድርጊቶች የሚከናወኑ መሆናቸውን ከምልከታ መረጃዎቹ ለመገንዘብ ተችሏል። ለምሳሌ ከዓለማዊው የሟች ቤተሰቦች፣ የቅርብ ዘመዶችና ጎረቤቶች ከጠዋቱ አስራ አንድ ሰዓት አካባቢ ተነስተው ወደቤተክርስቲያን በመሄድ፣ በመቃብሩ ዙሪያ ተሰብስበው የሚላቀሱበት ይጠቀሳል። በተለያየ ምክንያት በዕለቱ ለቅሶ ያልደረሰ ሰው ከየቦታው ስለሚሰባሰብ፣ እስከአንድ ሰዓት አካባቢ ለቅሶው ደመቅ ብሎ ይቆያል። ሽማግሌዎች ሀዘንተኞቹ ዝም እንዲሉ ሲያደርጉ፣ በዕለት ለቅሶ ስንብት በተገለጸው መንገድ እየተሰናበቱ ይሄዳሉ። ከሀዘንተኞቹ ጋር ቅርበት ያላቸው ሰዎች አብረው በመቀመጥ ከሟች አሟሟትና ከመጎዳታቸው ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን እያነሱ ያዋሯቸዋል። ሀዘንተኞቹ ቂም እንዳይዙባቸውም በዕለቱ ያልተገኙበትን ምክንያት በሚያሳምን መንገድ ይነግሯቸውና ተሰናብተው ይሄዳሉ።

በሀይማኖታዊው ደግሞ፣ ለሟች ከቀብር በኋላ እሱን በማሰብ የቅዳሴና የጸሎት ሥርዓት ለመጀመሪያ ጊዜ የሚከናወንለት በዚሁ ዕለት መሆኑን፣ ከመረጃ አቀባዮቹና ከምልከታ መረጃዎቹ ለመረዳት ተችሏል። የሰልስት የመታሰቢያ ሥርዓት፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሳት ተምሳሌትነት ጋር ተያያዥ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል። ኢየሱስ ክርስቶስ ሶስት

ሌሊትና ሶስት ቀን በመቃብር ቆይቶ እንደተነሳ፣ ‹‹ሠላም ለእናንተ ይሁን›› ብሏቸው ከእነሱ ጋር በቤት መገኘቱ፣ የሙታን ነፍሳት በተቀበሩበት አካባቢ የመገኘታቸው ተምሳሌት ተደርጎ እንደሚወሰድ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በመካከላቸው እንደተገኘ የሚበላ ነገር ጠይቆ መመገቡም፣ በመቃብራቸው አካባቢ የሚገኙት የሙታን ነፍሳት፣ የእነሱ ምግብ የሆነውን ጸሎት የሚፈልጉ ለመሆኑ ማጠየቂያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ፍላጎታቸው እንዲሟላ ከተቆረበላቸውና ከተቀደሰላቸው መርቀው ይመለሳሉ ተብሎ እንደሚታመን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በሕይወት ያሉት ሥርዓቱን በማሟላት ለሙታን እንደሚለምኑ ሁሉ፣ ሙታንም በሕይወተ ሥጋ ላሉት ሠላምና ደህንነት በረቂቅ መንገድ ይለምናሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ የሶስተኛው ቀን ሥርዓት የዚህ የጋራ መተሳሰብ መዘከሪያ ተደርጎ እንደሚወሰድም ከመሪጌታ ክፍለማርም አለነ (አባ.2.፣ቁ.2) ገለጻ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

እንደሰልስቱ ሁሉ፣ በሰባተኛው ቀንም በተመሳሳይ ሁኔታ የቅዳሴና የጸሎት ሥርዓት ቢፈጸምም የሚከናወንበት ምክንያት ግን ከሰለስቱ ይለያል፡፡ እንደመሪጌታ ክፍለማርያም አለነ (አባ.2. ቁ.2.፣ ክፍ.1.4.3.1.፣ አን.4) ገለጻ፣ የሰባተኛው ቀን ሥርዓት ከሰባቱ የሰው የአፈጣጠር ባሕርያት (ባሕርያተ ሥጋ፤ ነፋስ፣ እሳት፣ መሬትና፣ ውሃ፤ ባሕርያተ ነፍስ፤ ነባቢት፣ ልባዊት እና ሕያዊት) ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የሰራው ሀጢያት ይቅር እንዲባልለት በዚህ ዕለት እንደሚቀደስለትና ከገንዘቡ ተነስቶ ለድሆች እንደሚመጸወትለትም ያስረዳሉ፡፡

ከሰባተኛው ቀን በኋላ የአስራ ሁለተኛው ቀን መታሰቢያ በተመሳሳይ ሥርዓት ይከበራል፡፡ ሥርዓቱ የሚከበርበት ምክንያት ከአስራ ሁለቱ ሀዋርያትና ከተሰጣቸው ሥልጣን ጋር ተያያዥነት ስላለው፣ ከሶስተኛውና ከሰባተኛው የቀናቀን ሥርዓቶች የተለየ መሆኑን መሪጌታ ክፍለማርም ይገልጻሉ፡፡

የአስራ ሁለተኛው ቀን መታሰቢያ፣ ይህ ዓለም በትምህርታቸው ጸንቶ የሚኖርበት የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ምሳሌ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በአንድ በኩል፣ ሟች የአስራ ሁለቱን ሐዋርት ትምህርት ሳያውቅ ቀርቶና ተሳስቶ የሰራው ሀጢያት እዳ በደል እንዳይሆንበት፣ በሌላ በኩል ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያቱ፣ (ማቴ.19፣28) ‹‹እውነት እለችኋለሁ፣እናንተ የተከተላችሁኝ፣ በዳግመኛ ልደት የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን በሚመጣበት ጊዜ እናንተ ደግሞ በአስራ ሁለቱ የእሥራኤል ነገድ ስትፈርዱ በአስራ ሁለቱ ዙፋን ትቀመጣላችሁ›› ብሎ ከገባላቸው ቃል ኪዳን

ጋር ይያያዛል፡፡ ሐዋርያት ያስተማሩት ትምህርት ለዚህ ክብር ስላበቃቸውና መንግስተ ሰማያትም አስራ ሁለት መግቢያ በር ስላላት ሟች በዚያ እንዲገባ በማሰብ ሥርዓቱ እንደሚካሄድለት ለመረዳት ተችሏል፡፡

የሰላሳኛው ቀን ሥርዓትም እንደላይኞቹ ሁሉ የሚፈጸምበት የራሱ ምክንያት አለው፡፡ የዚህ ቀን የመታሰቢያ ሥርዓት፣ በአንድ በኩል እሥራኤላውያንን ከግብጽ ባርነት ያወጣቸውና ባህረ ኤርትራን ያሻገራቸው ሙሴ በሞተ ጊዜ፣ ለሰላሳ ቀናት ያለቀሱበት ምሳሌ ሲሆን (ኦሪት ዘዳግም 34፣8)፣ በሌላ በኩል የሰላሳ ዓመት ጎልማሳ ሆኖ ተፈጥሮ በሀጢያት የወደቀውን አዳምን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰላሳ ዓመቱ ተጠምቆ ከማዳኑ ጋር ተያያዥነት አለው፡፡ በሰላሳ ዓመትህ ተጠምቀህ አዳምን ከሀጢያት ያዳንክ አምላክ፣ ሟችንም በቸርነትህ ከሀጢያት አድንልን ብሎ ለመለመን ቀኑ ተጠብቆ ሥርዓቱ እንደሚፈጸም ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከሰላሳ ቀን የመታሰቢያ ሥርዓት በኋላ በሚከናወነው የአርባ ቀን የመታሰቢያ ሥርዓት፣ እስካሁን ከቀረቡት የክወና ሥርዓቶች፣ በሚከወንበት ምክንያት ብቻ ሳይሆን በአከዋወንም ልዩነት ይታይበታል፡፡ እስከሰላሳ ባሉት ሥርዓቶች፣ ምግብና መጠጥ ከሟች ቤት ተዘጋጅቶ ወደቤተክርስቲያን የሚወሰድ ሲሆን፣ በዚህ ሥርዓት ግን ምግቡ የሚዘጋጀው በቤተክርስቲያን እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ አባ አቸነፍ እንግዳ (አባ.2፣ ቁ.12፣ ክፍ.፣ 1.4.3.1.፣አን.1) እንደሚገልጹት፣ በስማዳ ለወንድ በአርባ፣ ለሴት በሰማንያ ቀናቸው ደም መቃብራቸው ላይ እንዲፈስላቸው በማሰብ፣ እንደቤተሰባቸው አቅም፣ በግ ወይም በሬ መቃብራቸው ላይ ይታረድና እዚያው ተዘጋጅቶ ይበላል፡፡ በዚህ ቀን የቅርብ ዘመድ የሚመጣ ሲሆን፣ ማታና በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ላይ የለቅሶ ሥርዓትም ይኖራል፡፡

እርድ የሚካሄደውና ደም እንዲፈስ የሚደረገው በዓለማዊ መንገድ ሲታይ፣ ከአባት ሲወርድ የመጣ ልማድ በመሆኑ እንጂ ሌላ ትርጉም ኖሮት አለመሆኑን ከመረጃ አቀባዮቹ ገለጻ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በሀይማኖቱ በኩል ግን፣ ልማዱ ከኦሪት ዘመኑ ሥርዓት ጋር ተያያዥነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚያ ዘመን በግ፣ ፍየልና፣ በሬ ወዘተ. ሰውተው ደሙን በመንበሩ አድርገው ሲጸልዩ፣ የሥጋ ፈውስ ያገኙ ስለነበር፣ ደሙን መቃብር ላይ የሚያፈሱት ከዚህ ልማድ ጋር በተያያዘ የሟች ነፍስ ትድናለች በሚል እምነት መሆኑን ከመሪጌታ ክፍለማርያም አለነ (አባ.2፣ቁ.2) ገለጻ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176

በሌላ በኩል የአርባ ቀን የመታሰቢያ ሥርዓት፣ ከእሥራኤላውያን ሙታቸውን ሽቱ የመቀባት ሥርዓት ጋር የሚያያዝ ሲሆን፣ በተጠኚው ማሕበረሰብ በዚህ ቀን መስዋዕት የሚቀርበው ግን፣ ሟች በሕይወት ዘመኑ የሰራውን ሀጢያት እግዚአብሔር ይቅር እንዲለው በማሰብ መሆኑን ከመሪጌታ ክፍለማርያም አለነ (አባ.2፣ቁ.2) ገለጻ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ከእናታቸው ማሕጸን ከተወለዱ በኂላ ከአብራክ መንፈስ ቅዱስ፣ ከማሕጸነ ዮርዳኖስ፣ በጥምቀት የሚወለዱት፣ ወንዶች በአርባ፣ ሴቶች በሰማንያ ቀናቸው ስለሆነ፣ በዚህ መንገድ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆኑ በኂላ በዓለም ሲኖሩ በሰሩት ሀጢያት ከልጅነት እንዳይፋቁ ይቅር እንዲላቸው፣ በተጠቀሱት ቀናት ተዝካር ይወጣላቸዋል፡፡

በአርባና በሰማንያ ቀን የመታሰቢያ ሥርዓቶች፣ ወቅቱ አመች ከሆነና ቤተሰቡ አቅም ካለው፣ የተዝካር የመታሰቢያ ሥርዓት አብሮ እንደሚከበር መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ፡፡ በደብረታቦር ዙሪያ፣ በፋርጣና በፎገራ ወረዳዎች በአብዛኛው ለወንድ በአርባና፣ ለሴት በሰማንያ ቀናቸው የተዝካር የመታሰቢያ ሥርዓት የሚከናወን ሲሆን፣ በላይ ጋይንትና በስማዳ ወረዳዎች የሟች ቤተሰብ በተመቸው ጊዜ ሊያወጣ እንደሚችል መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ፡፡ ተዝካር ለሙታን ብቻ ሳይሆን አልፎ አልፎ በሕይወት ላሉትም ‹‹የቁም ተዝካር›› በሚል መጠሪያ እንደሚወጣ አቶ ሀይሌ ዘውዴ (አባ.2፣ ቁ.37፣ ክፍ.1.4.3.2.1.፣ አን.1-4) ያስረዳሉ፡፡

የቁም ተዝካር ማውጣት፣ የእናት አባትን ተዝካር አለማውጣት ከሚያስከትለው ማሕበራዊ ጫና ልጆች እንዲድኑ ለማድረግ ወይም ይህን ጫና በመፍራት ልጆች፣ ‹‹በእናውጣ፣ አናውጣ›› እንዳይጣሉ ከማሰብና ሳይችሉ ቢቀሩ አጽም እንዳይወቅሱ በመፍራት እንደሚፈጸም ለመረዳት ተችሏል፡፡ የቁም ተዝካር አውጪዎች ከራሳቸው ተዝካርም ሆነ የእነሱ ከተወጣ በኂላ ከሌላ ሰው ተዝካር ተገኝተው እህል ውሃ ያለመቀመሳቸውም፣ እንደሞቱ የመቆጠር ተምሳሌትነት ያለው መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

በሁሉም ወረዳዎች ተዝካር ማውጣት ሀይማኖታዊ ጠቀሜታ ያለው ብቻ ሳይሆን፣ ማሕበራዊ ግዴታ ተደርጎ የሚታይ መሆኑንም በተመሳሳይ ሁኔታ ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ አባ አቸነፍ እንግዳ (አባ.2፣ ቁ.12፣ አን.3.4) በስማዳ ወረዳ አንድ ቤተሰብ የወላጆቹን ተዝካር ካላወጣ፣ በዘፈንም ሆነ በፉከራ ጊዜ ስድብ ይደርስበታል፡፡ በሚሞትበትና ቤተሰብ ተዝካሩን ሊያወጣ በሚጠይቅበት ጊዜ፣ ካህናት የእናት አባቱን ተዝካር ካላወጣ የእሱ እንዲወጣለት የማይፈቅዱ መሆኑ፣ ለሥርዓቱ ተጠናክሮ መቀጠል በምክንያትነት እንደሚጠቀስ ያስረዳሉ፡፡ የአንድ ሰው ተዝካር

ሳይወጣ ቢቀር፣ ‹‹እገሌ ልኸ አልወለደም ሳይፈታ ቀረ›› ስለሚባል፣ አነሰም በዛ ተዝካር ማውጣት ማሕበራዊ ግዴታ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

አቶ ገበያው ዓለሜም (አባ.2 ቁ.11) በላይ ጋይንት ወረዳ ተዝካር ያላወጣ ሰው ስለሚተች፣ ከዚህ ለመዳንና ‹‹እገሌ አውጥቶ እኔ ሳላወጣ አልቀርም›› በሚል ፉክክር ተዝካር እንደሚወጣ ይገልጻሉ፡፡ የቤተሰቡን ተዝካር ያላወጣና ለማውጣት ያልተዘጋጀ ሰው ከሌላ ሰው ተዝካር ቢጠራ አይሄድም፡፡ ለዚህ ደግሞ በመረጃ አቀባዮቹ እንደተገለጸው ቀደም ባለው ጊዜ የወላጆቹን ተዝካር ሳያወጣ በሌላ ሰው ተዝካር የተገኘ ግለሰብ በተሰለፈበት መሶብ ወጥ በማለቁ አስተናጋጁን እንዲያወጣላቸው ሲጠይቅ፣ ‹‹አውጥተህ ብላ›› ብሎ ከሰጠው ቅኔያዊ ምላሽ ጋር የተያያዘው ስድብ በምክንያትነት ይጠቀሳል፡፡ ይህም የማሕበረሰቡን ልማድ በመጣሱ የሚጣልበት የማግለያ ቅጣት ሁኖ ተገኝቷል፡፡

የወላጆቹን ተዝካር ላላወጣ ሰው የእርሱ ተዝካር እንዲወጣ የማይፈቀድ መሆኑ፣ ማሕበራዊ ቅጣቱ ለልጅ እየተላለፈ የሚቀጥል መሆኑን ያሳያል፡፡ አቅም ሳይኖራቸው ከዚህ ቅጣት ለመዳን ሲሉ ሰዎች ተዝካር ለማውጣት መገደዳቸው፣ በኑሯቸው ላይ ችግር የሚያስከትል መሆኑና ተዝካር ሳያወጣ የሞተ አባት፣ ተከታታይ ትውልዶቹ ባላጠፉት ጥፋት ሲቀጡ አንገት ያስደፋቸውን አባት፣ አያት፣ አለፍ ሲልም ቅድመአያት አጽም እንዲረግሙና እንዲወቅሱ ማድረጉ፣ የዘር ሀረግ ግንኙነትን የሚያሻክር ሁኖ ተገኝቷል፡፡

በተጠኚው ማሕበረሰብ ለአባት፣ ለልጅ የሚተላለፍ እዳ መተው፤ ለልጅ፣ ሙት መውቀስ የሚወገዙ ተግባራት መሆናቸው፣ ለተዝካር ሥርዓት ተጠናክሮ መቀጠል አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ዓለማዊ ምክንያቶች መሆናቸውን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በእነዚህና በሌሎችም ማህበራዊ ቅጣቶች ምክንያት እየተተገበረ ያለው የተዝካር የመታሰቢያ ሥርዓት፣ ከሀይማኖታዊ አገልግሎቱ በተጨማሪ፣ ማሕበራዊ ደረጃ ማስጠበቂያና ክብር ማግኛ ተደርጎ እንደሚወሰድም ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በመንፈሳዊው በኩል ደግሞ፣ ተዝካር የሚወጣው፣ ቄሶቹ በልተውና ጠጥተው ‹‹ነፍስ ይማር›› ብለው ሲመርቁ፣ የሟች ነፍስ ትጸድቃለች ተብሎ ስለሚታመን እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ አቶ ፈለቀ (2004፣156)፣ በእንግድነት የታደሙበትን አንድ የተዝካር ድግስ መነሻ አድርገው እንደሚገልጹት ደግሞ፣ ጎጃም ውስጥ ተዝካር የሚወጣው የሟች አምላክ ይታዘበናል በሚል ፍራቻ ነው፡፡

አባ ጎርጎርዮስ እ.ኢ.አ. (1991፣147-8) እንደሚገልጹትም፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሙታንን የምታስብበት ሥርዓት አላት፡፡ ‹‹እህልህንም በጻድቃን መቃብር ላይ አሳድር›› (ጦቢ.ት፣4፣17)፣ ‹‹የሞተ ሰውስ አረፈ ነገር ግን ነፍሱ ታርፍ ዘንድ ተዝካር አውጣለት፡፡ ከዚህ በኋላ ለቅሶህን አቁም›› (ሲራክ 38፣23)፡፡ እና ‹‹መፍትው ንገብር ተዝካሮሙ ለምውታን በዕጣን ወበመሥዋዕት›› (ግንዘት፣147) የሚሉትን ከተለያዩ ምንጮች የተገኙ መረጃዎች በማቅረብም፣ ሀሳባቸውን ያጠናክራሉ፡፡ ቤተክርስቲያን ይህን ዓለም ድል ነስተው የሄዱና በዚህ ዓለም በተጋድሎ ላይ ያሉ ምዕመናን ማሕበር መሆኗን ጠቅሰው፣ አንዳቸው ለሌላቸው እንደሚጸልዩ ይገልጻሉ፡፡ ሙታን በሕይወት ላሉት የሚያቀርቡት ምህላና ጸሎት በእነሱና በእግዚአብሔር ብቻ የሚታወቅ ምሥጢራዊ እንደሆነና በሕይወት ያሉት ለሙታን የሚያቀርቡት ግን፣ ግብር ሰፍረውና እጣን ቋጥረው ወደቤተክርስቲያን በመውሰድ ቅዳሴ በማስቀደስና ደግሰው ለካህናትና ለነዳያን በማብላት ስለሆነ፣ በግልጽ የሚታይ እንደሆነ ያስገነዝባሉ፡፡

ከዚህ በላይ የቀረቡት መረጃዎች እንደሚያሳዩት፣ ተዝካር በሕያዋንና በሙታን መካከል ያለውን ትስስር የሚያጠናክር መገናኛ መንገድ ተደርጎ ይታያል፡፡ አቶ ግዛቸው ደምሴ* (አባ.2፣ ቁ.35፣ ክፍ.1.4.3.2.2፣ አን.1-3) እንደሚገልጹት፣ ተዝካር በስማዳ ወረዳ የአባት ቅርስ ተደርጎ የሚታይ፣ ልጆች ለወላጆቻቸው ውለታቸውን የሚመልሱበት፣ የዓዕምሮ ሠላም የሚገኝበትና ማሕበራዊ ግንኙነት የሚጠናከርበት ነው፡፡ አቶ ፈለቀ (2004)፣ ሙታን ተዘንግተው እንዳይቀሩ መታወሳቸው፣ ለነዋሪው መተሳሰቢያ መድረክ ከመክፈቱ በተጨማሪ፣ የሙታን አርአያነት እንዲቀጥል የማድረግ የማሕበራዊ እሴት ግንባታ አስተዋጽኦው ከፍተኛ እንደሆነም ይገልጻሉ፡፡

---

* *ከአዲስ አበባ ስማዳ በመሄድ እ.ኢ.አ. ሰኔ 15/1997 ዓ.ም የሞቱ አባታቸውንና በሕይወት ያሉ እናታቸውን ተዝካር አራት በሬ አርደው ባወጡበት ዳስ ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው ናቸው፡፡ በሁኔታዎች አለመመቻቸት ምክንያት እስካሁን ባለማውጣታቸው ይጨነቁ እንደነበርና አሁን በጣም ደስተኛ እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡ ወጪ ቀላል ባይባልም ደክመው ላሳደጓቸው ወላጆቻቸው ሊከፈል ከሚገባው ውለታ ይኸ በጣም ትንሹ መሆኑን ጠቁመው፣ ተራርቀው የሚኖሩ ዘመዶች ተገናኝተው ያለፈውን እያስታወሱ እንዲጫወቱ፣ የማይተዋወቁ ልጆቻቸው እንዲተዋወቁ፣ የተጣሉ እንዲታረቁ በማድረግ ተዝካር ማሕበራዊ ፋይዳ እንዳለውም ያስረዳሉ፡፡ ከአራት ዓመት በፊት ከባሏ ጋር የተፋታች እህታቸው፣ ባሏ ባይጠራም ይመለከተኛል ብሎ በመምጣቱና በመገናኘታቸው፣ እንዲያስታርቁት ጠይቆ እሷም ፈቃደኛ በመሆኗ መታረቃቸውን በመግለጽ የተዝካርን ማሕበራዊ ፋይዳ ያስረዳሉ፡፡ አብረዋቸው ከነበሩት ዘመዶቻቸው መካከል አቶ ብርሃንና አቶ ኮራ፣ በተዝካሩ አለመውጣት ሲያዝኑ እንደነበርና በዚህ መልኩ በመውጣቱ ደስተኛ መሆናቸውን በመግለጽ ልጆቹን የመረቁበት መንገድ ተዝካር አለማውጣት በአካባቢው ያለውን ማሕበራዊ ጫና አመልካች ሆኖ ተገኝቷል፡፡*



ምሥል ሀያ ሶስት፣ በ9/05/06 ዓ.ም አቶ ግዛቸው ደምሴ የሚች አባታቸውንና በቀኝ በኩል የሚገኙ እናታቸውን ተዝካር ባወጡበት ዳስ ቃለ መጠይቅ ሲደረገላቸው (ፎቶ በብርሃን አበበ)

በጾታ ልዩነት የቀን መርዘምና ማጠር ካልሆነ በስተቀር፣ የአርባና የሰማንያ ቀን የመታሰቢያ ሥርዓቶች በክወናም ሆነ በሚከወኑበት ምክንያት ተመሳሳይ መሆናቸውን መሪጌታ ክፍለማርያም አለነ (አባ.2፣ ቁ.2) ያስረዳሉ፡፡ እነዚህ መታሰቢያዎች፣ በተዝካር ሲታጀቡ ወይም ራሳቸውን ችለው ሊከበሩ የሚችሉ መሆናቸውም ያመሳስላቸዋል፡፡

ከሰማንያ ቀን በኋላ ለሙታን የሚከበረው የመታሰቢያ ሥርዓት መንፈቅ ነው፡፡ በመንፈቅ ቅዳሴና ጸሎት የሚከናወን ሲሆን፣ ዓላማውም ሟች በዚህ ጊዜ ውስጥ የሰራውን ሀጢያት እግዚአብሔር ይቅር እንዲልለት መሆኑን መሪጌታ ክፍለማርያም ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የሚፈጸመው የሙት ዓመት መታሰቢያም ከጸሀይ ዑደት መጨረሻ ጋር የተያያዘ እንደሆነና በእነዚህ እለታት የሰራውን ሀጢያት እግዚአብሔር ይቅር እንዲለው ታስቦ የቅዳሴና የጸሎት ሥርዓት እንደሚፈጸም ያስረዳሉ፡፡ አራቱ ዘመናት ቢቀያየሩም፣ ከአንድ ዓመት 365/6 ቀናት ውጭ ሌላ አዲስ ቀን ስለሌለ፣ ይህ ሥርዓት የቀናቀን መታሰቢያ ሥርዓቶች መደምደሚያ እንደሆነም ይገልጻሉ፡፡

ከዚህ በኋላ መፈጸሚያ የሚባሉ በየሰባት ዓመት ልዩነት እስከአርባ ዘጠኝ ዓመት ድረስ ሟች የሚታሰብባቸው ሥርዓቶች አሉ፡፡ ሰባት ጊዜ ሰባት አርባ ዘጠኝ ስለሆነ፣ እንደአንድ ሙሉ ሱባኤ ይቆጠራል፡፡ አቅም የሌላቸው በሰባተኛው ዓመት መታሰቢያውን አድርገው ሊያቆሙ ይችላሉ፡፡ ከእነዚህ የተሻሉት በአስራ አራተኛውና በሀያ አንደኛው ሊያስቀርቡ ይችላሉ፡፡ ጽናቱና

አቅሙ ያላቸው እስከአርባ ዘጠኝ የሚቀጥሉ ሲሆን፣ የሟችን አጽምና ነፍስ ምርቃት የፈለጉ ልጆች፣ በሕይወት እስካሉ ድረስ መታሰቢያውን ሳያቋርጡ ያቀርባሉ።

መሪጌታ ክፍለ ማርያም አለነ (አባ.2፣ ቁ.2.፣ ክፍ.1.4.3.1.፣ አን.8-12) እንደሚያስረዱት፣ እስከሃያ አንደኛው ዓመት ድረስ የሟች ነፍሳት በተቀበሩበት ዕለት፣ በየዓመቱ ወደመቃብራቸው ተመልሰው በመምጣት ይጎበኛሉ። መታሰቢያ ከተደረገላቸው ደስ ብሏቸውና መርቀው ይሄዳሉ። ባሮክ* እንዳየው ዛፍ በቅሎ ክንፍና ክንፉ እስከአድማስ አውጥቶ ለምልሞ ይታያል። ካልተደረገላቸው አዝነውና ረግመው ይመለሳሉ። እስከሃያ አንድ ዓመት በየዓመቱ መታሰቢያ ማድረግና ከሟች ንብረት ለድሆች መመጽወት እንደሚገባ፣ የኦርቶዶክስ ሀይማኖት እንደሚያዝ ያስረዳሉ። ከሙሉ ሱባኤ በኋላ ነፍስ ወደመቃብር ቦታ ተመልሳ አትመጣም ተብሎ እንደሚታመንም ይገልጻሉ።

እንደተጠኚው ማሕበረሰብ፣ በሌሎች አገሮችም ሙታንን በያመቱ ማሰብ የተለመደ መሆኑን አንዳንድ መረጃዎች ያሳያሉ። ለምሳሌ አቶ ፈለቀ (2004፣156) እንደሚገልጹት፣ በጆርጅያ የሟች ቤተሰቦችና ዘመድ አዝማድ፣ በዳግም ትንሳኤ የሟችን መቃብር በማጽዳት፣ አበባ በማስቀመጥና ሟች በሕይወት ዘመኑ ይወደው የነበረውን መጠጥ በመጠጣት፣ ያስቡታል። ይህን የሚያደርጉት በመንፈስ ከሟች ነፍስ ጋር በመገናኘት ሟችንና ጠባቂ አምላኩን ለማስደሰት እንደሆነም ይገልጻሉ።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የተገለጹት በተጠኚው ማሕበረሰብ ተግባራዊ እየተደረጉ የሚገኙ የመታሰቢያ ሥርዓቶች፣ በሀይማኖቱም ይባል በዓለማዊው ለሟች ብቻ ሳይሆን ለቋሚም ጠቀሜታ ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል። የመታሰቢያ ሥርዓቶቹ ከሞት በኋላ የሁለቱ መተሳሰቦች (አንዳቸው ለሌላቸው እንደሚጸልዩ መገለጹ ሳይዘነጋ) የሚጠናከሩባቸው ብቻ ሳይሆኑ፣ ሟቾች ቋሚዎችን እንዳይረግሙና ጉዳት እንዳያደርሱ መማጸኛዎች ጭምር

---

*እንደአስቆራቢው ትጋት መጠን፣ እንደሟቹ ተድላ ደስታ መጠን፣ ታረከ ባሮክ እንዳየው ረጅም ዛፍ በቅሎ ክንፍና ክንፉ እስከአድማስ ደርሶ ላዩ አፍርቶ አዕዋፍ ሲመገቡት ከታች እንደማር፣ እንደወተት ያለ የሚጣፍጥ ፈልቆላቸው ሕጻናት ሲጠጡ አየ፤ ነቅቶ ተመልሶ ተኛ። ዛፉ ደርቆ ፍሬው ረግፎ አዕዋፍ ሲጮሁ ምንጩ ደርቆ ሕጻናቱ ሲያለቅሱ አየ። መልአኩን ‹ተርጉምልኝ› አለው። ዛፉ የመስዋእት የቁርባን፣ የፍትሀቱ። አዕዋፍ የነፍሳቱ፣ ፍሬው በመስዋእቱ ምጽዋቱ በፍትሀቱ የሚያገኙት ክብር ነው። ሕጻናት የሕያዋን፣ ምንጩ የሕያዋን፣ መስዋእቱ በምጽዋቱ፣ በፍትሀቱ የሚያገኙት ክብር ነው። መስዋእት የሰውላቸው ቁርባን ያስቆረቡላቸው እንደሆነ፣ ሙታን ባረፉበት ቀን ነፍሳት ይመጣሉ። በምድር ‹‹ክፉይ ልጅ አይንሳችሁ፣ ከርስታችሁ ከጉልታችሁ አይንቀላችሁ›› ብለው መርቀው ክብር አግኝተው ይሄዳሉ። ሕያዋኑም ክብር አግኝተው ይቀራሉ። ደርቆ ማየትህ መስዋእት ያልሰውላቸው፣ ቁርባን ያላስቆረቡላቸው እንደሆነ ‹‹ብድር ከፉይ ልጅ ይንሳችሁ፣ ከርስታችሁ ከጉልታችሁ ይንቀላችሁ›› ብለው ረግመው ክብር አጥተው ይሄዳሉ። እኒህም ይቀሰፋሉ ብሎ ተርጉሞለታል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADDIS ABABA, ETHIOPIA

መሆናቸውን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህም Stuart እና Jun (1992፤68)፣ የሚንሂ ቱ (Minhe Tu) ማህበረሰቦች፣ የሟች መንፈስ ቁጣ ከሚያመጣው ጥፋት ለመዳን ከሞት ጋር ለተያያዙ ሥርዓቶች ከፍተኛ ወጭ እንደሚያወጡ ከገለጹትና Abbink (1990) የመኤን ጎሳዎች ከአያት ቅድመ አያት ነፍሶች ጋር እንገናኝበታለን ብለው በጥንቃቄ ለሚያከናውኗቸው ከሞት ጋር የተያያዙ ሥርዓቶች ልዩ ትኩረት ከመስጠታቸው ጋር ተያያዥነት ያለው ሁኖ ተገኝቷል፡፡ ምክንያቱም በተጠኚው ማሕበረሰብ ተዝካር ያልወጣለት የአባት አጥንትም ሆነ የመታሰቢያ ሥርዓት ጸሎት ያልተከናወነላት ነፍስ እርግማኖች፣ በቋሚዎች ላይ የሚያስከትሉት ጉዳት እንዳለ ጠቋሚዎች ናቸው፡፡

ስለሆነም የመታሰቢ ሥርዓቶቹ በሕያዋንና በሙታን መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖር፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚከወነው ባሕላዊ ልማድ ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፍና በቋሚዎቹ መካከል መተሳሰብ እንዲፈጠር በማድረግ ሥነልቡናዊ፣ ባሕላዊና ማሕበራዊ ጠቀሜታ ያላቸው መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የመታሰቢያ ሥርዓት የሚከናወንበት ምክንያት፣ የእያንዳንዱ የመታሰቢያ ሥርዓት አፈጻጸም፣ እንዲሁም ዓለማዊና ሐይማኖታዊ ትርጉሙ ተገልጿል፡፡ በሚቀጥለው ምዕራፍ ደግሞ ሞት በቤተሰብ አባላትና ሟች በሚኖርበት ማሕበረሰብ ላይ የሚያስከትለው ውጤት ቀርቧል፡፡

## ምዕራፍ ሰባት

### 7. ሞት በሥጋ ዝምድናና በማህበራዊ ትስስር ላይ የሚያስከትለው ውጤት፡፡

Carr እና Moorman (2011፣145)፣ ማሕበራዊ ግንኙነት የተለያየ መልክ፣ መዋቅርና ተግባር ያለው ጽንሰ ሀሳብ መሆኑን ገልጸው፣ ግንኙነቶቹ በሕጋዊ ቁርኝት፣ በሥጋ ዝምድና፣ በጉርብትና፣ ወይም በመዋደድ ላይ ሊመሰረቱ እንደሚችሉ ያስረዳሉ፡፡ ግንኙነቶች፣ ወደትስስሩ ለመግባት ወይም ላለመግባት ባለ ምርጫ፣ ለማቋረጥ በመቻልና ባለመቻል እንዲሁም በጊዜ ቆይታ መጠን ሊለያዩ እንደሚችሉም ያስረዳሉ፡፡ በወላጆች፣ በወንድማማቾችና እህትማማቾች እንዲሁም በልጆች መካከል ያለው ቤተሰባዊ የሥጋ ዝምድና ትስስር በፈቃደኝነት ላይ ሳይሆን፣ በጠንካራ የግዴታ ስሜት የተመሰረተና በቀላሉ ሊቋረጥ የማይችል መሆኑን Litwakንን (1985) ዋቢ በማድረግ ያስረዳሉ፡፡ በሌላ በኩል በዘመናዊው የምእራቡ ማሕበረሰብ፣ በጓደኝነትና በፍቅር ወይም በጋብቻ የሚመሰረት ግንኙነት፣ በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተና ከግዴታ ይልቅ መሰረታዊ የሆኑ ሥነምግባሮችን ባልጣሰ መንገድ ሊቋረጥ የሚችል እንደሆነ ያስገነዝባሉ፡፡

ለአረጋውያን የወንድማማችነትና እህትማማችነት ግንኙነት፣ ከልደት እስከሞት ድረስ የሚዘልቅ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ግንኙነት ሲሆን፣ የባልና ሚስት ወይም የፍቅር ጓደኛ እንዲሁም የወላጅና ልጅ ግንኙነት፣ ከጋብቻና ከመውለድ በኂላ ዘግይቶ የሚመሰረት ስለሆነ በአንጻራዊነት አጭር እንደሆነም ያስረዳሉ፡፡

ከእነዚህ በሥጋ ዝምድና፣ በግዴታና በውዴታ ከሚፈጠሩ ግንኙነቶችና ከቆይታ ጊዜያቸው በተጨማሪ በተጠኚው ማሕበረሰብ፣ ቀደም ሲል የሞት ሥርዓት፣ የሀዘን አገላለጽ ልማድና የመታሰቢያ ሥርዓቶች፣ በቀረቡባቸው ክፍሎች፣ ከሟች ማንነትና የአሟሟት ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ የሀዘን አገላጽ ደረጃው እንደሚለያይ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ተገልጿል፡፡ በዚህ ምእራፍ ደግሞ፣ ከቤተሰብ አባላት (ወላጆች፣ ወንድማማቾችና እህትማማቾች እንዲሁም ልጆች) የአንዱ መሞት በቀሪዎቹ የቤተሰብ አባላት ላይ፣ (ሟች ሽማግሌ ወይም የማሕበረሰቡ አለኝታ ጀግና ሲሆን)፣ በሚኖርበት ማሕበረሰብ ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ምን እንደሆነ ተተንትኗል፡፡

የአንድ ሰው በሞት መለየት አብረውት ይኖሩ በነበሩት ሰዎች ላይ ሀዘን ማስከተሉ የተለመደ ነው፡፡ የሟችን አፈር መሆን በማሰብ የሚከሰተው ሀዘንንና እሱ በመታጣቱ ኑሯቸው

የሚናጋባቸውና ሕይወታቸው አደጋ ላይ የሚወድቅባቸው ክፍሎች ሀዘን፣ በጥልቀትም ሆነ በስፋት የሚለያዩ መሆናቸው አያጠራጥርም። የመጀመሪያዎቹ አይነት ሀዘንተኞች እየዋለ ሲያድር ከሀዘኑ ጋር የመላመድና የመርሳት አዝማሚያ የሚያዩ ሲሆኑ፣ ሁለተኛዎቹ አይነት ሀዘንተኞች ግን፣ የለመዱትን ሲያጡ፣ ክብራቸው ሲነካ፣ ሲጠቁ፣ ሲራቡ፣ ሲታረዙ፣ ሲገለሉና አድሎ ሲፈጸምባቸው፣ ሀዘናቸው ያገረሻል። በብሶታቸው ውስጥ የሚፈልጉትን የሚያሟላላቸውን፣ ደጀን በመሆን ጥቃታቸውን የሚከላከልላቸውንና የሚያስከብራቸውን፣ አጉራሽ አልባሻቸውን እያሰቡ፣ በሆድ ብሶት ለረጅም ጊዜ እንዲያዝኑ ሁኔታዎች ያስገድዷቸዋል።

በCarr እና Moorman (2011) ክፍ ሲል እንደተገለጸው፣ ተጠኚው ማሕበረሰብ በሥጋ ዝምድና ብቻ ሳይሆን በመፈቃቀድ ትስስር በሚመሰርትባቸው በጓደኝነት፣ በጋብቻና አብሮ በመኖር የሚመሰረቱት ግንኙነቶች፣ በአኗኗር ሥርዓቱ ቡድናዊነት የተነሳ፣ እንደምዕራባውያኑ በውዴታ ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በግዴታም ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል። እንዲህ አይነቶቹ ግንኙነቶች፣ በሀዘን አገላለጽ ብቻ ሳይሆን የአንድ ሰው ሞት በሌላው ላይ በሚያስከትለው ጉዳትም በተለያየ መልኩ ይንጸባረቃሉ።

ለምሳሌ Meeks (2002) እንደሚገልጹት፣ የእያንዳንዱ ሰው ሞት የየራሱ ትርጉምና የተለየ ሀዘን አለው። ብዙ ማድረግ የሚችለው ነገር እያለ በመካከለኛ እድሜ ለሞተ ጓደኛችን የሚሰማንን ሀዘን ጥልቀት ለመግለጽ እንቸገራለን። ራስን የማጥፋት መርዶን የምንቀበለው በድንጋጤና በፍራቻ አንዳንዴም በተሸናፊነት ስሜት ነው። የልጅ ሞት ሀዘን በጣም መራራ ነው። ምክንያቱም ተፈጥሯዊውን የሕይወት ጉዞ የተገላቢጦሽ የመሆን ስሜት ይፈጥራል። ምክንያቱም ተጠኚው ማህበረሰብ፣
በኋላ ሂድ እንጂ ለምንድን በፊቴ፣
እንደልጅነትህ እንዳባትነቱ። በማለት ተፈጥሯዊውን የሕይወት ጉዞ በለቅሶ ቃል-ግጥሙ ይገልጸዋል።

ቀጥሎ ከቤተሰባዊ ትስስር አኳያ፣ የአንዳቸው መሞት በሌሎቹ የቤተሰብ አባላት ላይ የሚያስከትለው ውጤት በቃል-ግጥሞቹ እንዴት እንደተገለጸ ተተንትኗል።

### 7.1. የእናት ሞት በልጆች ላይ

በእናትና በልጅ መካከል የተለየ ፍቅር መኖሩ በእለተለት ሕይወት የሚታይ እውነታ ነው። እናት ዘጠኝ ወር በማሕጸንዋ ተሸክማ፣ አምጣ ወልዳ የአካሏን ክፋይ ከማየቷ፤ ልጅ ከሚደረግለት እንክብካቤ፣ ከምታጠባው ጡትና ከምታሳየው ፍቅር በተጨማሪ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያውቃት እሷን መሆኑ፣ ለፍቅራቸው ጥንካሬ መሰረት ከሚሆኑት ውስጥ ይጠቀሳሉ።

ይህ በአብዛኛው ማሕበረሰብ ሊኖር እንደሚችል የሚገመት ሲሆን፣ በተጠኚው ማሕበረሰብ ደግሞ እናት ለልጅ ሁሉንም ነገር በመሆኗ፣ ከሌሎቹ የቤተሰብ አባላት በላቀ ሁኔታ በሁለቱ መካከል የጠበቀ ፍቅርና መቀራረብ ይታያል። እናት በምትሞትበት ጊዜ ልጆች የሚያጡት አካላዊ እሷነቷን ብቻ ሳይሆን፣ ለሕወታቸው አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ ነገሮችንም ጭምር ነው። እናም ከዚህ የሚመነጨው የመሪር ሀዘናቸው መግለጫ የሆነው እንጉርጉሯቸው፣ ለአድማጭ ውስጥ ድረስ ዘልቆ የሚሰማ መሆኑ፣

አንጀቴን አንጀቴ ሲበላው አደረ፣
እናት የሌለው ልጅ እያንጎራጎረ። በሚለው መንቶ የወየታ ቃል-ግጥም ተገልጿል።

በዚህና ቀጥሎ በሚቀርቡት የወየታ ቃል-ግጥሞች፣ በለቅሶዋ ላይ ስለእርሷ መጎዳት ሳይሆን፣ ለልጆቿ ስለምታደርጋቸው የተለያዩ መልካም ነገሮችና ባለመኖሯ ምክንያት ስለሚደርሱባቸው መጥፎ አጋጣሚዎች፣ ተደጋግሞ መገለጹ፣ ይህንኑ ያሳያል። ይህም በሕይወት እያለች ከራሷ ይልቅ ለልጆቿ ከማድላቷ ተፈጥሯዊ ባሕሪ ጋር ተያይዞ የመጣ መሆኑን ለመገመት ይቻላል። በተጠኚው ማሕበረሰብ እናት የደግነት፣ የርህራሄ፣ የአዛኝነትና የቤዛነት ትዕምርት ተደርጋ እንደምትወሰድ መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ። ልግስናዋም፡-
እናት አውድማ* ናት የተለቀለቀ፣
ብትሰጠው ብትሰጠው አትልም አለቀ። ተብሎ ተገልጿል።

በለቅሶዋ ላይ ከእርሷ ይልቅ ለቀሪ ልጆቿ መጻኢ እድል ትኩረት ሲሰጥ የሚታየው፣ እርሷ የማታሳዝን ወይም ሞቷ የማይጎዳ ሆኖ ሳይሆን፣ ለሌሎች ነዋሪነቷ የፈጠረው ልማድ ወይም ባሕሪዋ ያመነጨው ስብእና የወለደው አመለካከት ነው ለማለት ይቻላል።

* አውድማ፣ በቁሙ የሰብል ማበራያ ቦታ ቢሆንም፣ በባህሉ የልግስናና የማያልቅ ሀብት ተምሳሌትነት ይሰጠዋል።

እናት ልጆቿን ራስ አስችያለሁ ብላ እንደማትለያቸው የሚገልጸው የሚከተለው የወየታ ቃል-ግጥም፣ለራሷ ሳይሆን ለአብራክ ክፋዮቿ ነዋሪነቷን ያጠናክራል ለማለት ይቻላል፡፡
እናት አንድ ባላ፣ እናት ሁለት ባላ፣ እናት ሶስት ባላ፣
የልጆቿን ቤት ጎደሎውን ሁሉ ሁልጊዜ እምትሞላ፡፡

ባላ፣ እንደማማና፣ አጥር ላሉት መስሪያዎች የሚሆን መንታ ያለው እንጨት ሲሆን፣ በተጠኚው ማህበረሰብ የደጋፊነት ትእምርት እንዳለው መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ፡፡ እናት የልጆቿን ጎደሎ ለመሙላት የምታደርገው ጥረት፣ ከአንድ አልፎ እስከሶስት ባላ በሚደርስ ድጋፍ ተገልጿል፡፡ ይህም ለልጆቿ በሁሉም አቅጣጫ ያላትን ደጋፊነትና ጠቃሚነት ይጠቁማል ለማለት ይቻላል፡፡

እናት ለልጆቿ ሁሉንም ነገር ብትሆንም፣ በእናቶች ሞት ላይ ከተሰበሰቡት የወየታ ቃል-ግጥሞች፣ እናት ረሃብን በማስወገድ በኩል በሚኖራት ሚና ላይ የሚያጠነጥኑት ቀዳሚውን ቦታ ይዘው ተገኝተዋል፡፡
እናትስ አትሙት ትኑር ተጎልታ፣
ራብ ትገላለች ከደጅ ጎትታ፡፡

የሚለው የወየታ ቃል-ግጥም፣ ራሳቸውን ላልቻሉትና በቤት ውስጥ ለሚገኙት ልጆቿ ብቻ ሳይሆን፣ ራሳቸውን ለቻሉትም የረሃብ መድሃኒት መሆኗን ይጠቁማል፡፡ በተጠኚው ማሕበረሰብ በተለያዩ ምክንያቶች ከቤቱ ወጥቶ የሚውል ሰው ምግብ የሚያገኘው በሄደበት አቅጣጫ ከሚገኙ የቅርብ ዘመዶቹ ወይም ጓደኞቹ ነው፡፡ በባሕሉ እንግዳ ክቡር ስለሆነ ጋባገሮቹን ላለማስቸገር ሲባል ተጋባዥ ወደቤት እንዲገባ ሲጠየቅ ፈቃደኛ አይሆንም፡፡ በዚህ ጊዜ ጋባዥ ቅርበትና ተቆርቋሪነት ሲኖረው፣ የማስገደድ ያህል ጎትቶ በማስገባት፣ እህል ውሃ እንዲቀምስና እንዲያርፍ ያደርጋል፡፡ በቃል-ግጥሙ የተጠቀሰው ይኸው የእናት መለያ ባሕሪ ነው፡፡

በተጠኘው ማሕበረሰብ ፍትፍት፣ ክብር ከሚሰጣቸው የምግብ አይነቶች ውስጥ እንደሚገኝበት፣ ‹‹ከፍትፍቱ ፊቱ›› የሚለው ምሳሌዊ አነጋገር ማስረጃ ተደርጎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ እናት ይህን ምግብ እያበላች ያሳደገችው ልጅ፣ ከሌሎች የሚከፋፊሉ የቤት እቃዎች በማስበለጥ፡-

ከቤት እቃሽ ሁሉ ገበታሽ ይድረሰኝ፣
እየፈተፈተ እንዳንቺ እንዲያጎርሰኝ፡፡

በማለት ተራ ቢሆንም የእሷን ግብር የሚተካለትን እቃ ይመርጣል፡፡

እናት በሕይወት እያለች ብቻ ሳይሆን፣ ከሞተች በኂላም የረሃብ መድሃኒት ተደርጋ ትታያለች፡፡
እናትን ቀበሯት በነጠላ ሸማ፣
እንዲሸሽ ራቡ ድምጽዋን እየሰማ፡፡

የሚለው የወየታ ቃል-ግጥም ለዚህ ጥሩ ማስረጃ ይሆናል፡፡ የከፈን ሥርዓት በታየበት ክፍል፣ ሬሳ በአዲስ ጨርቅ ተጠቅልሎ እንደሚከፈን ተገልጿል፡፡ ወየ ባዩ፣ የሸማው መደራረብ የእናትን ድምጽ ከመቃብር ውስጥ አፍኖ እንዳያስቀረው፣ በነጠላ መከፈን እንዳለባት ያሳስባል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ድምጿን ሰምቶ ረሃብ እንዲሸሽ ነው፡፡ ይህ ቃል-ጥም ቀጥታተኛ ፍቹ ተግባራዊ የሚሆን አይደለም፡፡ ወየባዩም ይህንን ስቶት አይመስልም፡፡ ከተዜመው ወየታ ጀርባ እናት የረሃብ መድሃኒት መሆኗን ለማጠየቅ የቀረበ ለመሆኑ አያጠራጥርም፡፡

ከዚሁ የእናት የረሃብ መድሃኒትነት ሳንወጣ
እራቤ በሆዴ በቅሎ ዘረዘረ፣
እናቴ ብትኖር ታጭደው ነበረ፡፡

የሚለውን የወየታ ቃል-ግጥም እንመልከት፡፡ ረቂቅ የሆነው ረሃብ፣ ተጨባጭ በሆነው አዝመራ ክሱት እንዲሆን የተደረገበት ዘይቤ፣ የረሃቡን ስር መስደድና መጎልበት ተጨባጭ በሆነ መንገድ ያሳያል፡፡ ረሃቡ የአንድ ቀን፣ የሳምንት ወይም የወር ሳይሆን የወራት ይመስላል፡፡ ምክንያቱም በቅሎ ለመዘርዘር፣ የተመሰለበትን ሰብል ያህል ጊዜ እንደሚያስፈልገው ስለማያጠያይቅ ነው፡፡ ከመብቀል እስከመዘርዘር የደረሰው ደግሞ፣ በእናት አለመኖር ምክንያት ነው፡፡ ገጣሚው በቀጥታ አይገለጸው እንጂ፣ ረሃቡ ከዝርዝር ወደፍሬ እንደሚሸጋገር በሰቀቀን

ይጠብቃል፡፡ ያኔ እንደሌለች እናቱ እሱም እንደማይኖር ስጋቱን ጭምር መግለጹን ከቃል-ግጥሙ መንፈስ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ለአብነት በታዩት የእናት ረሃብ መድሃኒትነት ቃል-ግጥሞች፣ ለዕለት ረሃብ ማስታገሻ ጎትታ ከምታበላው፣ እየፈተፈተች እስካሳደገችበትና በመጨረሻም በእሷ መታጣት ምክንያት መቃብር አፋን ከፍቶ ተጎጂው መውደቁን እስከሚጠብቅበት ያለው ሂደት ተገልጿል፡፡ የረሃብ ሂደቱ ሲታይ፣ የእናት አለመኖር ለወዲያው አይሁን እንጂ፣ ልጆችን ለሞት እስከሚዳርግ አደጋ እንደሚያጋለጥ ቃል-ግጥሞቹ ይገልጻሉ፡፡

እናት ረሃብ ከማስወገዷ ሌላ የልጆቿን ምሥጢር ጠባቂና ገመና ከታች መሆኗን የሚያሳዩ የወየታ ቃል-ግጥሞች ተሰብስበዋል፡፡ በተጠኚው ማሕበረሰብ ባሕል፣ ተበድሮ መብላት የተሸናፊነትና የደካማነት፣ አለፍ ሲልም የስንፍና ምልክቶች ተደርጎ እንደሚታይ ከመረጃ አቀባዮቹ መካከል፣ አቶ ትእዛዙ አያሌው (አባ.2፣ቁ.20) ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ የሚከፋውና በማሕበረሰቡ ዘንድ እንደከባድ ነውር የሚታየው ግን፣ የተበደሩትን ‹‹አልከፍልም›› ማለት እንደሆነም ይገልጻሉ፡፡ እናት ስትሆን ይህ አሳሳቢ እንዳልሆነ፣
ምንኛ ጥሩ ነው የናት ጎረቤት፣
ተበድሮ በልቶ የለኝም ማለት፡፡

ከሚለው የወየታ ቃል-ግጥም ለመረዳት ተችሏል፡፡ አሳሳቢ የማይሆነው፣ እናት የልጇን ገመና አውጥታ ለማንም ስለማትናገር እንደሆነም መረጃ አቀባዩ ያስረዳሉ፡፡
እናት ደገላ* ናት ገዞሆን የማይጥሰው፣
የልጇን ገመና አትገልጠም ለሰው፡፡

የሚለው የወየታ ቃል-ግጥም፣ የእናትን የልጇን ምሥጢር ጠባቂነት በማሳየት፣ ከላይ የተገለጸውን ሃሳብ ያጠናክራል፡፡ ሁለቱም ቃል-ግጥሞች በተቃራኒያቸው ሲታዩ፣ የእናት ሞት ገመና አጋላጭ መሆኑን ያሳያሉ፡፡

* በሀረግና ረጃጅም አረም የተሳሰረ ጥቅጥቅ ያለ ደን፡፡

ከዚህ በላይ የእናት ሞት በልጆች ላይ በሚያስከትለው ውጤት ዙሪያ የቀረቡት ቃል-ግጥሞች፣ በየትኛውም እድሜ ያሉት ልጆች ላይ የሚከሰቱትን ሁኔታዎች የሚያሳዩ ነበሩ። የሚከተሉት ግን፣ ነፍስ ያላወቁ ልጆች በእናታቸው ሞት ምክንያት የሚጠብቃቸውን እጣ ፈንታ የሚገልጹ ናቸው።

እናት የሌለው ልጅ ተደማጭነት የሚያጣ ብቻ ሳይሆን፣ እንደውሸታም እንደሚቆጠር፡-
እናት የሌለው ልጅ ቀላል እንደጌሾ፣
ባይበላም በላ ነው ቢናገርም ዋሾ።

በሚለው የወየታ ቃል-ግጥም ተገልጿል። በማሕበረሰቡ ዘንድ መዋሸት እንደነውር የሚቆጠር ብቻ ሳይሆን፣ ከክብር ዝቅ የሚያደርግ የተወገዘ አመል ነው። እናት የሌለው ልጅ ከጌሾ ተነጻጽሮ መቅለሉ የተገለጸው በአካል ሳይሆን በሰብዕና ነው። ይህ የሰብእና ዝቅጠት በምግባር ሳይሆን በእናት መታጣት የሚመጣ መሆኑ፣ ባለሰሩት መቀጣትን ብቻ ሳይሆን፣ በምክር ሊስተካከልም ሆነ በጸጸት ሊታረም አለመቻሉንም ያሳያል። እናም ሁሌ ከክብር ዝቅ ብሎና ተገፍቶ መኖር፣ እናት የሌላቸው ልጆች እጣ ፋንታ ይሆናል።

እናት የሌለው ልጅ በማሕበረሰቡ ዘንድ እንክብካቤ የማይደረግለትና የተረሳ መሆኑ፡-
እናት የሌለው ልጅ ከደጃፍ ያመሻል፣
ጅብ ይበላውና ያስፈርድብሻል።

በሚለው መንቶ ተገልጿል። በተጠኚው ማሕበረሰብ ሕጻናት ከአራትና አምስት ዓመታቸው ጀምሮ፣ ጥጃ፣ ፍየልና በግ በመጠበቅ ሥራ ይሳተፋሉ። በጠዋት የተሰጣቸውን በልተው በዚሁ አድካሚ ሥራ ተጠምደው ውለው ወደቤት ሲመለሱ፣ ምግብና እሳት በጣም አስፈላጊዎቻቸው ከሆኑት መሰረታዊ ነገሮች መካከል ይጠቀሳሉ። እናት ከሌለች ‹‹ወደቤት ግቡ›› ባይ የላቸውም። በቃል-ግጥሙ፣ ለእነዚህ የልጆቹ ስቃዮች ሳይሆን፣ በጅብ ለመበላታቸው ትኩረት መስጠቱ፣ እናት የሌላቸው ልጆች መራብና መበረድ በማንም ላይ የማያስፈርድ ስጦታቸው ተደርጎ እንደተወሰደ ለመረዳት ይቻላል።
እናት የሌለው ልጅ ጌታ ያጣ ውሻ፣

ውጣ ውጣ ሲሉት የለውም መድረሻ፡፡

የሚለው መንቶም፣ ከላይ እንደተገለጸው፣ እናት የሌለው ልጅ የሚገጥመውን መገለልና መገፋት ይገልጻል፡፡ ውሻ በተጠጊው ማሕበረሰብ አገልግሎቱ ብዙ፣ ታማኝነቱ ጽኑ ቢሆንም፣ እዚህ ግባ የሚባል ትንሽ ክብር እንኳ የሚሰጠው እንስሳ አይደለም፡፡ ይልቁንም ባሕሪ ላነሰውና ክብር ለጎደለው መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ መከበሪያው ጌታው ነውና፣ እሱ ከሌለ ያም-ያም ‹‹ውጣ ውጣ›› ሲለው ርቆ ከመሄድ በአይኖቹ እየተማጸነ፣ በጭራው እያባበለ፣ በአካባቢው ለመቆየት ከመሞከር ያለፈ አማራጭ የለውም፡፡ ከዚህ እንስሳ ተነጻጽሮ የቀረበው እናት የሌለው ልጅ፣ ክብር የማይሰጠው መሆኑን ብቻ ሳይሆን፣ ሲገለልና ሲገፋ የሚገጥመውን ከለላ የማጣትና የመደናበር ስሜት ይገልጻል፡፡

ከላይ በተገለጸው መንገድ፣ መረሳቱም ሆነ መገፋቱ የሚያስከትለው ስነልቡናዊ ሁከት፣ የልጅነት አበባውን እንደሚያረግፈውና የተረሳ እንደሚያደርገው፣ አግድም ከተጣለ ንብ የሌለው ቀፎ ተነጻጽሮ የቀረበበት የሚከተለው ቃል-ግጥም፣ የውጤቱን መራራነት ያሳያል፡፡
እናት የሌለው ልጅ ንብ የሌለው ቀፎ፣
ሁልጊዜ ይኖራል አበባው ረግፎ፡፡

በማሕበረሰቡ ዘንድ ንብ የሌለው ቀፎ ጥቅም የማይሰጥ ነገር መገለጫ ነው፡፡ ቀፎ ንብ ከሌለው በስርዓት አይቀመጥም፡፡ ዙሮ የሚያየው ስለሌለም ፣የሸረሪት ማድሪያ፣ የአይጥ መዋለጃ ይሆናል፡፡ ጸሀይና ዝናቡ ሲፈራረቅበት፣ የተለቀለቀበት እበት እየተቅረፈረፈ ይነሳል፤ ሀረጉ እየተሰባበረ ይጨረማመታል፡፡ ወደትቢያነት ለመሸጋገር በሚያልፍበት በዚህ ሂደት ሲያዩት ያስጠላል፡፡ እናት የሌለው ልጅ ጉስቁልና ምን ያህልነት፣ በዚህ ቀፎ ተለውጦ፣ በጉስቁልናው ግዝፈት የልጅነት አበባው መርገፍ ክሱት ሆኖ እንዲታይ ተደርጓል፡፡

ከዚህ በላይ በቀረቡት ናሙና ግጥሞች፣ እናት የሌለው ልጅ አስተዋሽ የማያገኝ ብቻ ሳይሆን፣ ተገፊና መድረሻ የለሽ ቀበዝባዛ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ይህ የሚያስከትልበት አካላዊና ሥነልቡናዊ ጉዳት፣ ለጉስቁልና እንደሚዳርገው በልጅነት አበባው መርገፍ ተጠቅሷል፡፡ ቀጥሎ የቀረበው መንቶ፣ እናት የሌለው ልጅ በደል ከእነዚህ የከፋ መሆኑን ይጠቁማል፡፡

እንደፍየል ግልገል እንደላም እንቦሳ፣
የመናይቱን ልጆች የእኩል የሚያነሳ።

ይህ ቃል-ግጥም በቀረበበት ባሕል፣ አንድ ሰው በጠባቂ እጦት ወይም በቦታ ጥበት ምክንያት የቤት እንስሳቱን የእኩል ለሚጠብቅ ሰው አሳልፎ የመስጠት ልማድ አለ። ባለቤት እንዲህ የሚያደርገው፣ እንስሶቹን ከራሱ ጋር ለማቆየት የማይችልበት ካቅሙ በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥመው እንጂ፣ በቀላሉ አሳልፎ አይሰጣቸውም። ምክንያቱም፣ የእኩል ተቀባዩ በአግባቡ እንደማይንከባከባቸውና እንስሳቱ ለአደጋ እንደሚጋለጡ በሚገባ ያውቃል። ‹‹ከሰው ቤት ካለ ከብት ከቤት ያለ ቆዳ ይሻላል›› የሚለው ከዚያው አካባቢ የሚነገር ምሳሌያዊ አነጋገር ይህንኑ ያሳያል።

በቃል-ግጥሙ የሟችን ልጆች እንደእንስሳቱ ለእኩል ስጦታ ማቅረቡ፣ ከእለቱ ችግር ፋታ ከማግኘት እንጂ፣ የሚደርስባቸውን ችግር ከግምት ውስጥ ከማስገባት አለመሆኑ፣ በልጆቹ ላይ የሚደርሰውን ችግር አግዝፎ ያሳያል ለማለት ይቻላል። ሰብሳቢያቸው የለችምና፣ መበተን ተፈርዶባቸዋል፤ ክብራቸው የለችምና እንደእንስሳቱ መጎዳታቸው እየታወቀ በአማራጭ እጦት ለቅርምት ቀርበዋል። ይህ ጉዳይ ሰዋዊ ክብራቸውን እንደሚጥስና የከፋ አደጋ እፊታቸው እንደተደቀነ እየታወቀ፣ የይግቡበት ውሳኔ መሰጠቱ፣ የማሕበረሰቡን ችላ ባይነት ሳይሆን፣ በእናት ሞት ምክንያት በልጆች ላይ የሚደርሰው ጉዳት የሚያስከትለውን የማሕበረሰብ ቀውስ ያመለክታል።

የእናት ሞት በታዳጊ ልጆችም ሆነ ራሳቸውን በቻሉት ላይ የሚያስከትለው ውጤት ከፍ ብሎ ተገልጿል። የትዳሩ መፍረስ፣ የልጆቹ መበተንና ለአካላዊና ሥነልቡናዊ አደጋ መጋለጥ፣ አባትን በቀጥታ የሚመለከተው ቢሆንም፣ በቃል-ግጥሞቹ እምብዛም ተጎጂ ተደርጎ ሲቀርብ አልታየም። ይህም በባሕሉ ወንድ ልጅ ምግብ አብስሎ ልጆቹን ለማብላትም ሆነ ኑሮውን ለመግፋት ባለመቻሉ፣ ሚስቱ በሞተች ሲፈጥን በሳምንታት፣ ሲዘገይ ደግሞ በወራት ውስጥ ሌላ ሚስት ማግባቱ ከሚፈጥረው ቅሬታ ወይም፣ አብሮ ከመላቀስ ውጭ የሚሰጠው መፍትሄ ካለመኖር ጋር ተያያዥነት ያለው እንደሆነ፣ አቶ አያሌው ተሾመ (አባ.2፣ቁ.22) ይገልጻሉ።

ሕጻን ልጅ ትታ የሞተች እናት ስለመጎዳቷ ሳይሆን ባሏን ያለአባት አደሩ ልጅ ማሳዘኗ ተጠቅሶ መወቀሷም ከዚሁ ባሕል የመነጨ ነው፡፡

ኧረ አየዋ እገሌ ታጠቃት ነበረ ዛሬስ አጠቃችህ፣
ደሞ ብላ ብላ ልኸ እዘል አለችህ፡፡

የሚለው መንቶ፣ ባሕል ለባል አሸናፊነትንና አዛዥነትን፣ ለሚስት የተገላቢጦሹን ያጎናጸፈ መሆኑን ያሳያል፡፡ ግጥሙ ከባል ተሸናፊነት በላይ፣ ባል ልጅ እንዲያዝል ሚስት ትእዛዝ የሰጠችበት መንገድ እንደሚያስገርም ይጠቁማል፡፡ ዞሮ ዞሮ ባል በሚስቱ ሞት ምክንያት ባሕል ከደነገገለት ኃላፊነት ውጭ የሚገጥመውን ፈተና ያሳያል፡፡ ቢርበው አጥብቶ፣ ቢበርደው አቅፎ አሙቆ፣ ዝም የማያሰኘውን ልጅ ማዘሉ፣ ሚናውን ከፍ ሲል እንደተገለጸው አብሮ ከመላቀስ ያለፈ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡ የእናት ሞት ክብደት የተገለጸውም በዚሁ መፍትሄ የማያስገኝ የተያይዞ መላቀስ ድርጊት ነው፡፡

በአጠቃላይ የማሕበረሰቡ ዳራ በተቃኘበት ክፍል እንደተገለጸው፣ የተጠኚው ማሕበረሰብ ማሕበራዊ መዋቅር አባዊ ቢሆንም፣ የእናት ሞት በልጆች ላይ በሚያስከትለው ውጤት ዙሪያ በተገጠሙት የለቅሶ-ቃል ግጥሞች፣ ለረሃብ መጋለጥ፣ ሰብሳቢ ማጣትና መገለል ተደጋግመው ሲነሱ ተስተውለዋል፡፡ እናት ልጆቿን አቅፋ በመያዝ፣ በመንከባከብና ራሷን አሳልፋ እስከመስጠት በማፍቀር፣ የቤተሰብ ምሰሶ መሆኗ በስፋት ተገልጿል፡፡ ለዚህ ደግሞ ተፈጥሮ ከሰጣት ኃላፊነት በተጨማሪ፣ የማሕበረሰቡ የአኗኗር ልማድ የመመገቡና የመንከባከቡ ድርሻ በእርሷ ትከሻ ላይ እንዲያርፍ ማድረጉ፣ በልጆች ሕይወት ውስጥ ከማንም በላይ የጎላ ቦታ እንዲኖራት ያደረጋት መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ስለሆነም የንጹሕ ፍቅር፣ የርህራሄና የቤዛነት ትዕምርት የሆነችው እናት ሞት፣ በልጆች ላይ፣ ከአካላዊና ስነልቡናዊ ድቀት ለሚመነጭ የሰብዕና ንጥፈት፤ በማሕበረሰቡ ላይ፣ አንዱ ሌላውን እየወለደ ለሚበራከት ተራዛሚ ችግር ወይም ማሕበራዊ ድቀት እስከመዳረግ ለሚደርስ የከፋ ጉዳት የሚዳርግ መሆኑን ከለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ የአባት ሞት በልጆች ላይ የሚያስከትለው ውጤት ደግሞ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 7.2. የአባት ሞት በልጆች ላይ

በእናት እንደታየው ሁሉ፣ የአባት ሞትም በልጆች ላይ የከፋ ችግር እንደሚያስከትል ከተሰበሰቡት የወየታ ቃል-ግጥሞች ለመረዳት ተችሏል፡፡ ችግሩ ግን ከመበተን፣ የህልውና አደጋ በረሃብ መዳፍ ስር ከመውደቅ፣ ሰብሳቢ አጥቶ ለቅርምት ከመዳረግ፣ በተወሰነ መልኩም ቢሆን የተሻለ ይመስላል፡፡

አባት የሌለው ልጅ ከምንም በላይ የሚጎዳው ዋስና ጠበቃ በማጣት እንደሆነ በወየታ ቃል-ግጥሞቹ ተደጋግሞ ተጠቅሷል፡፡ በማሕበረሰቡ ባህልና እምነት፣ አባት የኩራት ምንጭና ጠበቃ ተደርጎ ይታያል፡፡ የእሱ መታጣት በልጆች ላይ ከሚያስከትለው ስነልቡናዊ ጉዳትና ማሕበራዊ ጫና መካከል፣ በዚህ ዙሪያ የሚደርሱባቸው ጉልሁን ቦታ ይይዛሉ፡፡

አባት በሌላቸው ሴት ልጆች ላይ ከሚፈጸሙት በደሎች፣ በባሎቻቸው የሚደርስባቸው ድብደባ አንዱ መሆኑን፣

ከባልሽ ተጣልተሽ ዱላ ቢውልብሽ፣
በሉ አባቴን ጥሩ ማለቱ ቀረብሽ፡፡

የሚለው መንቶ ይገልጻል፡፡ በተጠኘው ማሕበረሰብ ባሎች በተለያዩ ምክንያቶች በሚነሱ ግጭቶች ሚስቶቻቸውን መደብደባቸው የተለመደ ነገር እንደነበር መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ፡፡ አባት በሕይወት ካለ፣ እንዲህ አይነት በደል ሲደርስባት ልጅ ለአባቷ በመናገር ባሏ እንዲጠየቅ የማድረግና ካልተስማማትም ሀብቷን ተካፍላ የመፋታት መብቷ የተጠበቀ ይሆናል፡፡ የሚከተለውን ውጤት ስለሚያውቅ ባልም በረባ ባልረባው ዱላ ከማንሳት ይቆጠባል፡፡ አባት ከሌለ ግን፣ ባል ተቆጭ ስለሌለበት ሚስቱን እንደፈለገ ሲደበድባት፣ አለፍ ሲልም ሀብቷን ቀምቶ ሊያባርራት ይችላል፡፡ በግጥሙ የተንጸባረቀው ይኸው ማህበራዊ ልማድ ነው፡፡ የዱላው ከባድነት በውሎው፣ ችላ መቀበሏ፣ ‹‹በሉ አባቴን ጥሩ›› ማለቷ በመቅረቱ መጠቆሙ፣ የአባት ሞት፣ በሴት ልጆቻቸው ላይ የሚያስከትለውን የከፋ የበደል ውጤት ያሳያል፡፡

አደባባይ ውየ የሚዋሰኝ ባጣ፣
ምድር ምድር አየሁ ቆፍሬ ሳወጣ፡፡

የሚለው መንቶም፣ የአባትን ዋስ ጠበቃነት ይገልጻል፡፡ በባሕሉ በችሎት ላይ ዋስ ማጣት፣ የበታችነትና የብቸኝነት መገለጫ ብቻ ሳይሆን፣ የተስፋ ቢስነትና የተሸናፊነት ትዕምርትነትም አለው፡፡ የተበዳይ ምድር ምድር ማየት፣ ከሚች አባት ውጭ ጠበቃ የሌለ መሆኑን አመልካችነት አለው፡፡ በአደባባይ ዋስ የሌለው ብቸኛ፣ ተሟግቶ የማሸነፍ እድሉ የመነመነ ነው፡፡ በተጠኚው ማሕበረሰብ ዘንድ ተሟግቶ መሸነፍ ደግሞ እንደትልቅ ውርደት ይቆጠራል፡፡ ተሸናፊው በፍርድ ከሚያጣው ነገር ወይም ከሚደርስበት ቅጣት ይልቅ፣ በማሕበረሰቡ የሚደርስበት ንቀት የሚፈጠረው ስነልቡናዊ ጫና፣ እንዲሸማቀቅ ያደርገዋል፡፡ የማይቻለውን ለመሞከር (ቆፍሮ ለማውጣት) የሚነሳሳውም ከዚህ መሸማቀቅ ለማምለጥ ይመስላል፡፡ የሚከተለው መንቶም ከሽንፈት ለመዳን የሚወሰደውን አመራጭ ይጠቁማል፡፡

አባቴስ ሞተብኝ ልፍተል መቀነት፣
ዋስና ጠበቃ የምገዛበት፡፡

በተጠኚው ማሕበረሰብ፣ ታዋቂነትና ተሰሚነት ያላቸው ሰዎች፣ ለተጎጂው ብቻ ሳይሆን ለራሳቸው ክብርና ዝና ሲሉ፣ በአቅመ ቢሶች ላይ የሚደርስን ጉዳት በአደባባይ ቁመው የሚቃወሙበትና ጥብቅና የሚቆሙበት ልማድ አለ፡፡ ለዚህ አገልግሎታቸው ገንዘብ በጥሬ ሳይሆን፣ የቻለ ክብት ይሰጣል፤ አቅም የሌላቸው ሴቶች ደግሞ ሞሶብ ሰፍተው ወይም ጥጥ ፈትለው በማበርከት ውለታቸውን ይመልሳሉ፡፡ በግጥሙ ውስጥ የተጠቆመው ይኸው ነባር ባሕል ሲሆን፣ በጠበቃና አስከባሪ አባቷ ሞት በደል የተደራረበባት ሴት ልጅ፡-

አባቴ ብቅ በል ከፈሰሱ* ድረስ፣
የከፋኝን ሁሉ ነግሬህ ልመለስ፡፡

በማለት ትጠይቃለች፡፡ መንቶው አባት ብሶት አድማጭ ብቻ ሳይሆን ተከላካይነቱንና እሱ ሲታጣ በልጆች ላይ በዚህ በኩል የሚደርሰውን በደል ይገልጻል፡፡

አባት ለልጆቹ ዋስና ጠበቃ ከመሆኑ በተጨማሪ፣ ልጆቹ ማሕበረሰቡ የሚያከብራቸውን እሴቶች እንዲያከብሩና ከመጥፎ ነገር እንዲርቁ፣ ሰብእናቸውን በማረቅ በኩልም የጎላ ሚና ይጫወታል፡፡ ይህን ሚናውን ማሕበራዊ ደረጃው ወይም የሀብት እርሾው ሊተካው እንደማይችል፡-

---

* ሰብል እንዳያበላሽ ወይም በመንደር እንዳይገባ ለመከላከል ለውሃ መውረጃ የተዘጋጀ ቋሚ ቦይ፡፡

ከጎረቤት ሀብታም ያባት ድሃ ይሻል፣
የሚሰጠው ቢያጣ ሲመክር ያመሻል።

የሚለው መንቶ ይገልጻል። የሚከተለው ሶስቶም አባት ማብላትና ማጠጣት ቢሳነው እንኳ፣ መኖሩ ብቻ ከዚህ በላይ የሆነ ዋጋ ስላለው ለልጆቹ ጠቃሚ መሆኑን ያሳያል።
መብላቱም ይቅርብኝ አፈሩን ልብላው፣
መጠጡም ይቅርብኝ ደሙን* ልጠጣው፣
ከደጃፍ ቁጭ በል ድምጽህን ልስማው።

አባት ላልበሰሉ ልጆቹ በስሙ ከማስከበር፣ ልምዱን በማካፈል በሰብዕና ከማነጹ በተጨማሪ፣ ልጆቹ አሸናፊና ተጠቃሚ ሲሆኑ የሚችሉበትን የሕይወት መንገድ አመልካቻቸው እንደሆነም፦
አባት ያለውማ ነገሩን ከተተው
በስተኋለው ሁኖ እያመለከተው። የሚለው የወየታ መንቶ ያሳያል።

አባት የሌለው ልጅ ጠበቃና መካሪ ስለሚያጣ ቀጥለው እንደቀረቡት ያሉ የተለያዩ ችግሮች ያጋጥሙታል።
አባት የሌለው ልጅ ትል የወጋው ቀጋ፣
ሁል ጊዜ ይኖራል ጐኑ እንደተወጋ።
የሚለው የወየታ ቃል-ግጥም የሚያሳየው ይህንኑ ነው። የጎን መወጋት በተጠኚው ማሕበረሰብ ዘንድ፣ በአንድ በኩል የጋሻ ማጣት፣ በሌላ በኩል የከባድ ድንጋጤ ሰለባ መሆን ትእምርትነት አለው። ጋሻ መከታ ማጣቱ ከላይ እንደተገለጸው ሲሆን፣ የጎን መወጋቱ ደግሞ የሚገጥሙት ችግሮች የሚፈጥሩበትን ድንጋጤ ያመለክታሉ። መክሮ መንገድ የሚመራ፣ ጠበቃ ሁኖ የሚያስፈታ፣ አባት በሌለበት፣ ስጋትና ፍርሃት የየዕለት ሕይወት ክስተቶች ይሆናሉ። ምክንያቱም አባት የሌለው ልጅ ምንም አይነት በደል ቢደርስበትና ቢከፋው፣ ለችግሩ ጆሮ የሚሰጠው እንደሌለ፦
ቢያለቅስ ቢተክን ምንም ቢከፋው፣
ልጅ አድማጭ የለውም አባት ከሌለው። የሚለው የወየታ ቃል-ግጥም ያስረዳል።

---

* መጠጡን አምርሮ መጥላቱን ለመግለጽ (እርሜን ልጠጣ እንደማለት) ነው።

በማሕበረሰቡ ዘንድ አባት የሌለውን ልጅ ማግለል የተለመደ መሆኑን፦

አባት እየሞተ ልጅ እየተተካ ይላልኝ ሰው ሆየ፣
አገር ሽረኛ ነው ተቀማጭ ካላየ።።

የሚለው መንቶም ያሳያል።። ይህ ልማድ ስር የሰደደና አባታቸው በሞተ ልጆች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር መሆኑ፦

ድንጋይ ቢወረውር ወረወርኩኝ ኩበት፣
አባት የሌለው ልጅ የለውም አንደበት።።

ተብሎ ተገልጿል።። ይህ መንቶ አባት የሌለው ልጅ ለሚደርስበት ጥቃት ተገቢውን አጸፋ ለመመለስ አለመቻሉን ያሳያል።። ለተወረወረበት ከባድ ድንጋይ በቀላሉ ኩበት መመለሱ፣ የአቅም ማነስ ሳይሆን፣ ተደማጭነትን ከማጣት የተፈጠረ የተማጽኖ ተምሳሌት ነው።።

ከአደባባይ ቆሜ ይለኛል ድንግርግር፣
ለካስ አባት ኖሯል የልብ የሚያናግር።።

የሚለው መንቶም፣ ተጎጂው ‹‹በነገ ምንይመጣ›› ፍርሃት፣ የሚናገረውን ለመወሰን አስኪያቅተው ስነልቡናዊ ምስቅልቅል ያጋጠመው መሆኑን ይጠቁማል።።

ከዚህ በላይ የቀረቡት ቃል-ግጥሞች፣ አባት የሌለው ልጅ፣ ጠበቃ የሌለው፣ ተደማጭነት የማያገኝና ከንደኛ በታች ሁኖ በሰቀቀን የሚኖር መሆኑን ይገልጻሉ።። የአባት አለመኖር እስካሁን ከታዩት በልጆች ላይ የሚደርሱ ጉዳቶች የከፋ መሆኑ የተገለጸው ደግሞ፦

የዛሬው በጋ አልፎ ለሚመጣው በጋ፣
ልጆችህ በሰው ቤት ሚስትህ በሰው አልጋ።።

በሚለው መንቶ ነው።። ቀደም ሲል በቀረቡት የወየታ ቃል-ግጥሞች፣ የቤተሰብ መፍረስ አልተገለጸም ነበር።። በዚህኛው ግን ወየ ባዩ የቤተሰቡን መበታተን አይቀሬነት ገልጾበታል።። በአካባቢው ልማድ፣ የሰው ቤት በአንዳች ችግር ምክንያት በወር ወይም በዓመት ክፍያ ሰዎች ስምምነት ፈጥረው ለሥራ የሚቀዩበትን ሁኔታ ያሳያል።። በዚህ መንቶ በአባት አለመኖር ምክንያት በቤተሰቡ ላይ የተጋረጠውን አደጋ የከፋ የሚያደርገው፣ ልጆች እናታቸውን ጭምር የሚያጡ መሆናቸውን ስለሚጠቁም ነው።።

ቀደም ሲል የእናት ሞት በልጆች በሕይወት የመቆየት ጥያቄ ላይ አደጋ እንደሚደቅንና የአባት ሞት በአብዛኛው ለሥነልቡና ጉዳት የሚዳርግ እንጂ፣ ለሞት የሚያጋልጥ እንዳልሆነ ተጠቁሟል። በሥነ ሕይወታዊው፣ እናት ለልጆቿ ከአባት የበለጠ ቀረቤታና ልዩ ፍቅር ያላት በመሆኗ፣ በባሕላዊው፣ በአቅርቦት እጥረት ከሚመጣ ችግር ካልሆነ በስተቀር፣ እናት ምግብ እያበሰለች ለልጆቿ ስለምታቀርብ፣ የቤተሰቡ መበተን እድል ከአባት ሞት ጋር ሲነጻጸር አናሳ ነው ለማለት ይቻላል። ይሁን እንጂ፤ እናት ምንም ጥሪት የሌላት ስትሆን ወይም አንዳንዴ ከልጆቿ ይልቅ የራሷን ምኞት ስታስቀድም፣ የሚያገባት ሰው ልጆቿን ለመቀበል ፈቃደኛ በማይሆንበት ጊዜ፣ በየሰው ቤት በትናቸው ባል ታገባለች። ወየ ባዩ ከሁለቱ በአንዱ፣ ቤተሰቡ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ተበትኖ ለአካላዊና ስነልቡናዊ ችግር የሚጋለጥ መሆኑን ጠቁሟል።

የአባት ሞት እናት ለልጆቿ እንዳላት ፍቅርና እንደምትገኝበት እድሜ አልፎ አልፎ በልጆቹ ላይ እንዲህ አይነት ከባድ ችግር የሚያስከትልበት ሁኔታ ቢኖርም፣ ጠበቃ፣ መንገድ አመልካችና አድማጭ ማጣቱ፣ አንገቱን አስደፍቶ ከንደኛ በታች ቢያደርገውም፣ የእናት እንክብካቤና ምክር ስለማይለየው፣ የአደባባዩ መገለል የሰብዕና ንጥፈት እስከማምጣት የማያደግበት ሁኔታ መኖሩ፣ የሚከሰተውን ውጤት በእናት ሞት ከሚከሰተው ቀለል የሚያደርገው ይመስላል። አቶ ታደለ ሲሳይ (አባ.2.፣ ቁ.38)፣ ‹‹ከእናቱ የዋለ እንቁላል አይሰበርም›› እና የወ.ሮ ፈለቁ ከበደ (አባ.2፣ ቁ.31)፣ ‹‹የእናት ድሃ የላትም››፣ የሚሉት ምሳሌያዊ ንግግሮች ይህንኑ እውነታ ያጠናክራሉ።

የእናት ሞት በልጆች ላይ በሚያስከትለው ውጤት ስር እንደተጠቆመው በማሕበረሰቡ የአኗኗር ልማድ ምክንያት ወንድ ምግብ አብስሎ ልጆችን ማብላትና መንከባከብ ይቅርና ለራሱ ሀዘኑን በወጉ እስኪገልጽ ድረስ እንኳ ምግብ የሚያዘጋጅለት ስለሚያጣ ሚስት ለማግባት የሚገደድ መሆኑ፣ ለሚች ሚስቱና ለልጆቹ ያለው ፍቅር እምብዛም ተደርጎ እንዲታይ ምክንያት ይሁን እንጂ፣ የእሱም ሞት ልጆችን ለከፋ ጉዳት እንደሚያጋልጥ ተገልጿል። የጋሻነትና የጥላነት ትዕምርትነት ያለው አባት ሲሞት፣ ልጆቹ ጠበቃ የሌላቸው፣ ተደማጭነት የማያገኙና ከንደኛ በታች ሁነው በሰቀቀን እንዲኖሩ እንደሚያደርጋቸው በቃል-ግጥሞቹ ተደጋግሞ ተነስቷል።

በአጠቃላይ የወላጆች ሞት በልጆች ላይ ከዕለት ህልውና እስከወደፊት ተስፋ መጨለም ድረስ የሚዘልቅ ጠባሳ እንደሚያሳርፍ በቃል-ግጥሞቹ በስፋት መገለጹን ለመገንዘብ ተችሏል።

የሚደርሱባቸው አካላዊና ሥነልቡናዊ ጉስቁልናዎች፣ በሕይወት ዘመናቸው በሙሉ የሚንጸባረቁ ችግሮችን ትተው ስለሚያልፉ፣ የወላጆች ሞት በልጆች ላይ የሚያስከትለው ውጤት ዘላቂና መራራ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ከዚህ በላይ የእናትና አባት ሞት በልጆች ላይ የሚያስከትሏቸው አካላዊና ሥነልቡናዊ ጉዳቶች በለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ እንዴት እንደተገለጹ ለማየት ተሞክሯል፡፡ ቀጥሎ ደግሞ፣ በተገላቢጦሹ የልጆች ሞት በወላጆች ላይ የሚያስከትሏቸው ጉዳቶች በለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ እንዴት እንደተገለጹ ቀርቧል፡፡

## 7.3. የልጅ ሞት በወላጆች ላይ

በየትኛውም የዕድሜ ክልል የሚገኝ ሰው ሞት፣ በቀሪ ቤተሰቡና በሚኖርበት ማሕበረሰብ ላይ የሚፈጥረው ሀዘንና የሚያሳድረው አንዳች ጉዳት መኖሩ የማይቀር መሆኑን የጥናት ውጤቶች ያሳያሉ፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሁኖ በተለያዩ ማሕበረሰቦች፣ የልጆች ሞት የሚፈጥረው ሀዘንና የሚያስከትለው ጉዳት ከሌላው የማህበረሰብ ክፍል ሞት የበለጠ ከባድ እንደሆነ የምዕራቡን ዓለም ማሕበረሰብ ልምድ በመጥቀስ፣ Papadatou እና Papadatosን (1991) ዋቢ በማድረግ፣ Young እና Papadatou (2004፣91) ያስረዳሉ፡፡ በተለይ ለወላጆች የሀዘኑ ክብደት የሚመነጨው፣ በወላጅና ልጅ መካከል ያለው ግንኙነት በማንኛውም በሰው ልጅ መካከል ከሚፈጠር ግንኙነት የበለጠ ጥብቅና ዘላቂ በመሆኑ እንደሆነም ይጠቁማሉ፡፡ ከተጠኚው ማሕበረሰብ የተገኘው፡-

ከቶ ለምንድነው ልጅ አንጀት መብላቱ፣
ባድማው ሁኖ አይደል የበቀለበቱ፡፡

የሚለው የሙሾ ቃል-ግጥም የሚያሳየውም ይህንኑ ነው፡፡ ባድማ የሚለው ቃል፣ በቋሙ ለተወሰነ ጊዜ በመኖሪያነት አገልግሎ የተለቀቀን ቦታ ሲያመለክት፣ በተጠኚው ማሕበረሰብ ባሕል፣ እትብት የተቀበረበት፣ ድሆ የታደገበት፣ በመልካምና ክፉ የተለያየ ሕይወት የተመራበት ቦታ ከመሆኑ አንጻር፣ ልዩ ክብር የሚሰጠውና ትዝታው የማይደበዝዝ ተደርጎ

ይወሰዳል፡፡ በቃል-ግጥሙ፣ በዚህ አምሳያነት የልጅ ሀዘን አይረሴነት በሆድ ውስጥ በመብቀል ተለውጦ ቀርቧል፡፡

‹‹እንኳንስ ለአንድኛው ከቀየው ሲጠፉ፣
ልጅ አንጀት ይበላል አንገቱን ሲደፉ፡፡›› እና

‹‹አርቀው ቢቀብሩት መች ይቀራል ልጅ፣
ተመልሶ መጥቶ ሆድ ይበላል እንጂ፡፡››

በሚሉትና በሌሎችም የወየታ ቃል-ግጥሞች፣ የልጅ ሞት አሳዛኝነት ክብደት፣ ከአንጀትና ሆድ መብላት ጋር ተያይዞ ሲጠቀስ ተስተውሏል፡፡ በጊዜ ሂደት ልርሳህ ቢሉት የማይረሳ፣ እንደአዲስ እያገረሸ የሚታወስና ስሜትን የሚያውክ ሀዘን ጥልቀት የሚለካው ወይም የሚገለጸው፣ በአንጀትና ሆድ መብላት መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ከፍ ሲል የታዩት የእናትና አባት ሞቶች በቀሪዎቹ ላይ የሚፈጠሯቸው ችግሮች አይነትና ጥልቀት ተጠቁሟል፡፡ የልጅ ሞት ከዚህ ክፍል ቀጥለው የቀረቡት የእህትና የወንድም ሞቶች ከሚያስከትሏቸው ውጤቶች ሁሉ ለወላጆች የከፋ መሆኑ፣
አባት የሞተለት ድንበሩ ይገፋል፣
እናት የሞተችለት ምድር ሰማይ ያልፋል፣
እህት የሞተችለት ኮሶ ይደነፋል፣
ወንድም የሞተለት ባላንጣ ይፋፋል፣
ከዚህ ከዚህ ሁሉ የልዥ ሞት ይበልጣል፣
አለካራ አርዶ አለሳት ይጠብሳል፡፡ በሚለው ስድስቶ ተገልጿል፡፡

የልጅን ሞት በንጽጽር ከቀረቡት የማሕበረሰብ ክፍሎች ሞት ገዝፎ እንዲታይና ያለእሳት እንዲጠብስ ያደረገው፣ ከጥቅማጥቅም መቅረት ጋር መያያዙ ሳይሆን፣ ከዚህ ከበለጠ ሌላ ነገር የመነጨ መሆኑን ለመገመት ይቻላል፡፡ በተጠኚው ማህበረሰብ ‹‹በስለት ግደለኝ›› የሚል አባባል አለ፡፡ አባባሉ በተገላቢጦሹ ሲፈታ፣ ዱልዱሙ ጣር እንደሚያበዛ ያጠይቃል፡፡ አለካራ መታረድ ነፍስና ሥጋ የማይለያዩበት እጅግ የከፋ ጣር የሚያስከትል ወይም ጣረሞትን የሚያራዝም

መሆኑን ከአባባሉ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ የስሜት ጣር የሚወለደው መብሰክሰክ ውስጥን እያርመጠመጠ ያለእሳት መጥበሱ፣ የልጅን ሞት ሀዘን ከሌሎቹ የማሕበረሰብ ክፍሎች ሞት፣ የበለጠ መሪር እንደሚያደርገው በቃል-ግጥሙ ተገልጿል፡፡

የጉዳቱ ምንነት በግልጽ ባይነገርም፣ በግልጽ ከተጠቀሱት ከሌሎቹ የማሕበረሰብ ክፍሎች የሞት ውጤቶች በልጅ ሞት የሚመጣው ሀዘን የከፋ መሆኑ ይፋ መደረጉ፣ መንስኤውን የማወቅ ጉጉት ፈጥሯል፡፡ የምዕራቡን ዓለም በቤተሰብ ሞት የሚከሰት ሀዘን ያጠኑት Parkes (1997፣91) የልጅ ሞት፣ የወላጆች የወደፊት ደህንነትና እድገት ላይ የተለየ እንቅፋት መፍጠሩ፣ ሀዘናቸውን ከባድ እንደሚደርገው መግለጻቸው፣ የጉዳቱን አቅጣጫ ጠቋሚ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በተጠኚው ማሕበረሰብ ልጅ በእግር ተተኪና ወራሽ፣ አለኝታና አጋዥ ተደርጎ ስለሚታይ፣ ሲሞት በአካል ከመለየቱ በተጨማሪ እነዚህንም ጥቅሞች ማሳጣቱና የዘር ሀረግ ጉዞን ገትቶ ተስፋን ማጨለሙ፣ ሀዘኑን መሪር እንደሚያደርገው የተሰበሰቡት ቃል-ግጥሞች ያሳያሉ፡፡ ከዘር ሀረግ መዝገብ መፋቅ እጅግ ከባድ እንደሆነና ሕይወትን ትርጉም አልባ እንደሚያደርግ፣ ለእናት ሴት፣ ለአባት ወንድ ልጅ አለመውለድን አስመልክቶ የተገጠሙት የሚከተሉት የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ጭብጦች፣ ጥሩ ማሳያዎች ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡

እሴት ልጅ መች አለሽ እሴትስ በኖረ፣
ማተብሽም ድሪሽም ከማገር ባልቀረ፡፡

የሚለው መንቶ ከሟች ጉዳት ይልቅ፣ የሴት እቃዋን ተረካቢ ማጣቷ ክብደት የተሰጠው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህ የመነጨው ደግሞ በተጠኚው ማሕበረሰብ ለተተኪ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው በመሆኑ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

የዚያን ሟች ላሞች በመድን ሽጧቸው፣
ልጅ አላደረሰ ማልዶ የሚያልባቸው፡፡

የሚለው መንቶም፣ ወንድ ልጅ ሳይተካ የሞተን ሰው የዘር ሀረግ ፍሰት መገደብ፣ በልጅ ተተኪነትና ወራሽነት ማንጸሪያ ያሳያል፡፡ የሟች ላሞች በተያዥ እንዲሸጡ የሚወሰንባቸው፣

በአባቱ እግር ተተክቶ የሚንከባከባቸው ልጅ ያላፈራ በመሆኑ መገለጹ፣ ለተተኪዎች የሚሰጠው ቦታ ከፍተኛ መሆኑን ያመለክታል።

የመሃን* ምን አላት ያለመቀነቷ
ቀብረው ሲመለሱ ይወረሳል ቤቷ።

የሚለው መንቶ ደግሞ፣ የእናትን ወይም የአባትን ሚና የሚወርስ ከመታጣት ባለፈ፣ ጭራሹን ዘር አለመተካትን ስለሚገልጽ፣ የጉዳቱን ደረጃ የከፋ ያደርገዋል። ከፍ ሲል እንዳየናቸው ሁሉ፣ ከሚች ከንቱ መቅረት፣ ለቤቷ መወረስ ትኩረት መስጠቱ፣ የልጅን የትውልድ ሀረግ መቀጠያነት ለማጉላት ከማለም የመነጨ ነው ለማለት ይቻላል። በመንቶው የመካን ድህነት በአንድ በኩል በተተኪ እጦት ሲጠቆም፣ በሌላ በኩል ንብረቷን የሚረከብ በመታጣትና በቀብሯ ቅጽበት በመወረስ ተገልጿል። በእግር የሚተካ ከማጣት ጭራሽ አለመውለድ የሚያስከትለው ጉዳት የከፋ መሆኑ፣ መካን የምትወረሰው ንብረቷን ብቻ ሳይሆን ስሟን ጭምር በመሆኑ በግጥሙ ተጠቁሟል ለማለት ይቻላል። ምክንያቱም በማሕበረሰቡ ዘንድ ሚች ልጅ ከሌለው፣ የሚታወስበት ስለሌለ በቶሎ ይረሳል ተብሎ ይታመናል።

ደረቅ እንጨትና መካን አንድ ናቸው፣
አንዴ ከነገሉ መተኪያም የላቸው።

የሚለው መንቶም የልጅን የትውልድ መቀጠያነት ወይም የወላጅን ስም ማስጠሪያነት በግልጽ ያሳያል። የደረቅ እንጨት እጣ ፈንታ ከስሩ ተፈንግሎ መውደቅ መሆኑን በማሳያነት በማቅረብ፣ የመካንን ከሞት ወዲያ የትውልድ ሀረግ አለመቀጠል ወይም ተረስቶ መቅረት፣ ሁለቱን ባሕሪ በማወራረስ ያጠይቃል። የሚከተለው በእሳት መጥፋትና በውሃ መድረቅ ንጽጽር የቀረበው መንቶም የሚያሳየው ይህንኑ ነው።

ደረቀች እንደ እኂ ጠፋች እንደ እሳት፣
ባይሆን ለመሳሪያው ልዥ ሳትተካበት።

* በተጠኚው ማሕበረሰብ መካን ተደርጋ የምትታይ ሴቷ እንጂ ወንዱ አይደለም። ችግሩ ሲከሰት ወደሀኪም ቤት ሄደው ከማረጋገጥ ይልቅ ችግሩ በፍች ይደመደማል። የሚወዳት ከሆነ ከውጭ እየወለደ ትዳራቸው ይቀጥላል። ችግሩ የእርሱ ሁኖ ከውጭ መውለድ ባይችል ገመናውን ሸፍኖ እንዳልሞከረ ይቆጠራል እንጂ ወንድ ይመክናል ተብሎ አይታሰብም።

በመካን እጣ ፈንታ ማሳያነት ከዚህ በላይ የቀረቡት የወየታ ቃል-ግጥሞች፣ የልጅን አስፈላጊነት አጉልተው ያሳያሉ፡፡ ይህ የልጅ ሞት ከባድ ሀዘን ማስከተሉ የትውልድ ሀረግን ካለማስቀጠል ብቻ ሳይሆን፣ በዚህ ምክንያት ከሚመጣው የተስፋ መጨለም ጋርም ተያያዥነት ያለው በመሆኑ ጭምር ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም፣ Young እና Papadatou (2004፣192) እንደሚገልጹት፣ በልጆች ሞት የወላጆች ግማሽ አካል አብሮ ይሞታል፡፡ ጤናቸውን ለሚያቃውስ ሀዘን የሚጋለጡትም ለልጁ የነበራቸው ርዕይ፣ መልካም ነገርና ተስፋ አብሮ ስለሚቀበር መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ የማንነታቸውን ማስቀጠያ፣ አጋዣቸውንና ጠበቃቸውን መነጠቃቸው፣ አጠቃላይ የተሸናፊነትን ስሜት መፍጠሩ፣ ሀዘናቸውን በቀላሉ የማይሽርና ውስብስብ እንደሚያደርገውም ያስረዳሉ፡፡

በተጠኚው ማሕበረሰብ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው፣ ልጆች የትውልድ ሀረግ ማስቀጠያና ሥም ማስጠሪያ ከመሆናቸው በተጨማሪ፣ ለቤተሰቡ ዋና የሥራ አጋሮችም ናቸው፡፡ አብዛኛው በገጠር የሚኖረው አርሶ አደር በግብርና የሚተዳደር ስለሆነ፣ ሥራውን በወቅቱ ለማከናወን ልጆች ያላቸው ሚና፡-

እንዴት ጥሩ ነበር ይህ ልጅ የሚሉቱ፣
አንዱን ወዳተላው አንዱን ወደከብቱ፡፡

በሚለው መንቶ ተገልጿል፡፡ ልጆች በተለያዩ ሥራዎች ተሰማርተው ቤተሰባቸውን ከማገዛቸው በተጨማሪ፣ የማገዶ እንጨት የማቅረቡም ኃላፊነት የሚጣለው በእነርሱ ላይ ነው፡፡ ከብት ሲጠብቁም ሆነ ከሌላ ሥራ ውለው ሲመለሱ፣ የማገዶ እንጨት ለቅመው ማቅረባቸው የተለመደና በእነሱ ትከሻ ላይ የወደቀ ሥራ ነው፡፡ ይህን ለምዳ በልጇ ሞት ምክንያት የቀረባት እናት፡-

እምቢ አለኝ ምጣዱ እያነኳኰረ፣
የልጅ እንጨት ለምዶ የተሰባበረ፡፡

በማለት የቀረባትን ሲሳይና ያጋጠማትን ችግር ገልጻለች፡፡

ሁልጊዜ በገረድ እንደ ዘመናይ፣
ወልዶ ማዝዘማ ቀርቶ የለም ወይ?

የሚለው መንቶም፣ ልጅ ለወላጆች የሥራ አጋዥ መሆኑን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ በተጠኚው ማሕበረሰብ የወላጆች ሞት በልጆች ላይ ከሚያስከትለው ውጤት በባሰ፣ የልጆች ሞት በወላጆች ላይ የሚያስከትለው ውጤት የከፋ መሆኑ በቃል-ግጥሞቹ ተደጋግሞ ሲገለጽ ተስተውሏል፡፡ ጉዳቱን የከፋ የሚያደርገው በአንድ በኩል በጉልምስናቸው ዘመን አጋሮቻቸውን፣ በእርጅናቸው ዘመን ጧሪና ቀባሪዎቻቸውን ማጣታቸው ሲሆን፣ በሌላ በኩል የወላጆችን ርዕይ መና የሚያስቀር፣ ተስፋቸውን የሚያጨልምና ከዘርሀረግ መዝገብ መፋቅን የሚያስከትል መሆኑ ነው፡፡ Young እና Papadatou (2004፣191) በምዕራቡ ዓለም የቤተሰብ ሞት የሚያስከትለውን ውጤት በመረመሩበት ጥናታቸው፣ የልጆች ሞት የወላጆችን ህልምና ተስፋ አብሮ ስለሚገድልና ለአጠቃላይ ተሸናፊነት ስለሚያጋልጣቸው፣ ጤናቸውን እስከማቃወስ የሚደርስ መሪር ሀዘን የሚያስከትል መሆኑን ከገለጹበት ግኝት ጋር የዚህ ጥናት ውጤት ይስማማል፡፡

በልጆች ሞት ምክንያት በወላጆች ላይ የሚከሰቱት ውጤቶች ከዚህ በላይ የተነሱትን ይመስላሉ፡፡ ቀጥሎ የእህት ሞት በእህትና ወንድሞቿ፣ የወንድም ሞት በወንድምና እህቶቹ ላይ የሚያስከትሉት ውጤት በቅደም ተከተላቸው መሰረት ቀርበዋል፡፡

ሴት ልጅ ቤተሰብ እንዳይራብ በማድረግም ሆነ በሰብሳቢነት ከእናት ቀረቤታ ያለው ተግባር ትፈጽማለች፡፡ እሷ ስትሞት በእህት ወንድሞቿ ላይ የሚከሰተው ውጤት በቃል-ግጥሞቹ እንዴት እንደተገለጸ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 7.4. የእህት ሞት በወንድምና እህት ላይ

በተጠኚው ማሕበረሰብ ዘንድ ሴት ልጅ የእናቷን እግር ተከትላ እንድትወጣ ስለምትኮተኮት፣ ጎን ዳሳሽና የረሃብ መድሃኒት ተደርጋ ትታያለች፡፡ የተሰበሰቡት የወየታ ቃል-ግጥሞች ይህንኑ ሀሳብ የሚያጠናክሩ መሆናቸውን ቀጥሎ የቀረቡት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

እባክሽ እህቴ ራቤን ተቆጪው፣
አንችን ይሰማሻል ስትገላምጪው፡፡

በመንቶው ረቂቁ ረሃብ አካል ገዝቶ ቁጣና ግልምጫ እንዲቀበል ተደርጎ ተስሏል። ወየ ባይ እህት ወይም ወንድም ሊሆኑ ይችላሉ። እህታቸው ምን ያህል የረሃባቸው አስታጋሽ እንደነበረች የሰፈር ልጅ ሲተነኩስ፣ ጉልበት ያለው ወንድም ተቆጥቶ እንዳይደርስ በሚያደርግበት ባሕል አምሳያ፣ ጎንን የመዳሰስ ጉልበት ያላት እህት፣ ረሃብን እንድታስፈራራላቸው ይጠይቃሉ። ተማጽኗቸው እሷ ስትገላምጠው ረሃብ ዝምም ጭጭ ከማለቱ ጋር ተያይዞ ሲታይ፣ የእሷን ልግስናና በመሞቷ የሚደርስባቸውን ጉዳት መጠን ያሳያል።

አየ ጉድ እህቴ ሞሰቧ ጎድጓዳ፣
የራበው ታውቃለች ጎኑ የተጎዳ።

የሚለው መንቶም፣ የእህትን የረሃብ መድሃኒትነት ይገልጻል። በማሕበረሰቡ ለሚወዱት የቅርብ ሰው ምግብ የሚቀርበው፣ ብዙው ትንሽ እንዲመስል፣ ጎድጎድ ባለ እቃ ነው። እንዲህ የሚደረገውም ብዙ የሚበላ ወይም ሆዳም በጥሩ አይን ስለማይታይ ነው። ወየ ባዩ/ዋ ይህን ልማድ መሰረት አድርጎ/ጋ፣ በረሃብ የተጎዳ ጎኑን ወይም ጎኗን እንዴት እንዳታናችለት/ላት ገልጸዋል።

ረሃብ ጎን የሚወጋው፣ ሄደት መጣ ሲል ስለሆነ፣ በዚህ ደረጃ ሆድ እስኪሞላ አይበላ እንጂ የሚቀመስ ነገር ይኖራል። የሚከተለው መንቶ ረሃቡ ጓዙን ጠቅልሎ በመግባቱ የከፋ መሆኑንና በዚህ ጊዜ እህት የሚኖራትን ሚናም ይጠቁማል።
እራቡ በሆዱ ጎጆ ሰራ እንደሰው፣
ይህን ያለ እህቴ ማነው የሚያፈርሰው?

አንድ ነገር ለምሳሌ በሽታ፣ ጥቃት ወዘተ. ከአንድ ቤት ገብቶ ለረዥም ጊዜ ሲቆይና አልወጣ ሲል፣ በገባበት ቤት ‹‹ጎጆ ሰርቷል››፣ የሚል ልማዳዊ አባባል አለ። በመንቶው የረሃቡ ጎጆ መስራት መጠቀስ፣ ችግር ከዚያ ቤት ከገባ አለመውጣቱንና ቤተሰቡ በከፋ የድህነት አደጋ ላይ መሆኑን ይጠቁማል። እንዲህ ስር የሰደደን ረሃብ በማብላት የምታስወግደው እህት መሆኗ፣ በችግር ጊዜ እናት ብቻ ሳትሆን እሷም አብረዋት ለተወለዱት እህት ወንድሞቿ፣ የጎን ዳሳሽነቷ መጠን እስከምን እንደሆነ ይገልጻል።

እንደምግብ መሰረታዊ ባይሆንም፣ በተጠኚው ማሕበረሰብ አካባቢ፣ ጠላ ለጥም መቁረጫ ብቻ ሳይሆን፣ ለጨዋታና ለተዝናኖት የሚቀርብ ባሕላዊ የክብር መጠጥ ነው፡፡ በባልትናው ከለላ፣

እቱ የእናቴ ልጅ የሰጠሽኝ ጠላ፣
ምን ቅጠል አለበት አንጀት የሚበላ፡፡

ተብሎ የተገጠመው መንቶ፣ ሟች ለእህት ወንድሞቿ አስተናጋጅ እንደነበረች ብቻ ሳይሆን፣ ሞቷ ያስከተለባቸውን ጉዳት ይገልጻል፡፡ ተስተናጋጆቹ መስተንግዶዋን እያስታወሱ ከምር ማዘናቸውም በአንጀታቸው መቆረጥ ተጠቅሷል፡፡

በአጠቃላይ የእህት ሞት በእህት ወንድሞቿ ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት ለማሳየት ለአብነት በተመረጡት የለቅሶ ቃል-ግጥሞች፣ እህት፣ ለእህትና ወንድሞቿ በርሃባቸውና በጥማቸው ጊዜ ዳሳሻቸውና አስተናጋጃቸው መሆኗ ተገልጿል፡፡ የእሷ ሞት ከሥጋ ክፋያቸው መታጣት በተጨማሪ፣ የእናት ምትክ ተምሳሌትነቷንና ጎን ዳሳሽነቷን ስለሚያሳጣቸው፣ እንደሚጎዱና ከአንጀት እንደሚያዝኑ ተገልጿል፡፡

በትይዩ የወንድም ሞት በእህትና ወንድቹ ላይ የሚያስከትለው ውጤት ምን እንደሚመስል በቃል-ግጥሞቹ የተገለጸበት ክፍል ደግሞ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 7.5. የወንድም ሞት በእህትና ወንድም ላይ

ጥናቱ በተካሄደበት ማሕበረሰብ ከፍተኛውን ቁጥር የሚሸፍነው የገጠር ነዋሪ መተዳደሪያ፣ በግብርና ሥራ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ፣ ነዋሪዎቹ፣ በእርሻ መሬት፣ በግጦሽና በከብቶች አዝመራ መብላት ሳቢያ፣ ለሚከሰቱ ግጭቶች የተጋለጡ ናቸው፡፡ በማሕበረሰቡ ዘንድ ከምንም በላይ መራራ ተደርጎ የሚታየውን ከእንዲህ አይነቶቹ ግጭቶች የሚመነጭ ጥቃት ላለማስገባት፣ የወንድም መኖር በጣም ይፈለጋል፡፡ ለዚህም ነው፣
እህልም ይበላል ባቄላ መሳይ፣
ልብስም ይለበሳል ነጠላ መሳይ፣
እኔስ የምቀና ወንድም ያለው ሳይ፡፡

በሚለው ሦስቶ፣ በምግብና ልብስ ከሚገኝ የኑሮ ደስታ ይልቅ፣ በእንደምንም ኑሮ ወንድም የሚመረጥ መሆኑ የተገለጸው፡፡

ያለወንድም በምቾት ከመኖር ይልቅ፣ ወንድም ኖሮ ያለምቾት መኖር እንዲያስቀና ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ፣ ወንድም ጥቃት ተከላካይና መከበሪያ መሆኑ ነው፡፡

ኧረ ወንድማለም ድረስ ከኒላዬ፣
አካሌ ሳይቀስል ሳይደማ ገላዬ፡፡

የሚለው መንቶ፣ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ይሆናል፡፡ መንቶው ወንድም አንድም ከኒላው ደርሶ በትር እንዳያርፍበት ከመከላከል፣ አንድም አጋዥ ያለው መሆኑን አይቶ ባላንጋራው ጉዳት ሳያደርስ እንዲሸሽ ከመመኘት፣ የተገጠመ ነውና የወንድምን ደጀንነት ያሳያል፡፡

ጎባጣ ነህ አሉኝ ጎባጣ ነኝ ወይ?
ከሰው አልጣላም ጀርባየን ሳላይ፡፡

የሚለው በማሕበረሰቡ ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ በዘፈን፣ አልፎ አልፎ ደግሞ ከወገን መጨመርና መቀነስ ጋር የተያያዙ ጨዋታዎች ሲነሱ እንደምሳሌያዊ አነጋገር ጣል የሚደረገው መንቶ፣ የደጀንን አስፈላጊነት ይገልጻል፡፡

ወንድም አልኩሽ እንጂ ሲወድቁ የሚወድቅ ሲደሙ እሚደማ፣
ባድማ መች አጣሁ እየበላ እሚያማ፡፡

የሚለው መንቶም፣ ወንድም በጥቃት ጊዜ አብሮ መከራ የሚጋፈጥ መሆኑን ብቻ ሳይሆን፣ ተፈላጊነቱም በዚሁ የቁርጥ ቀን ጊዜ መሆኑን ጭምር ይገልጻል፡፡ ይህ ውለታው የማይዘነጋና እሱም የወንድም እህቶቹን ጥቃት መቼም የማይፈልግ መሆኑ፡-

መቼ ለዚህ በቅቶ መቼውን ሊረሳ፣
ጠላት መጣ ቢሉት አሁን በተነሳ፡፡

በሚለው መንቶ ተጠቁሟል፡፡ በዚህኛው መንቶም ከላይ እንተገለጸው፣ ወንድም የእህትና ወንድሞቹን ጥቃት መካች መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ከምንም ነገር በላይ ለዚህ ልዩ ትኩረት የሚሰጥ መሆኑ፣ በማይችልበት ሰዓት እንኳ እንደሚችል ተደርጎ በመቅረብ ተገልጿል፡፡ እንዲህ

ያለው ወንድም በሚሞትበት ጊዜ፣ ለሟች ሳይሆን ለቀሪው መታዘኑም፣ ወደፊት የሚጠብቀውን አደጋ ክብደት ግምት ውስጥ ያስገባ ይመስላል፡፡

ሁለት ወንድማማች ባንድ ይወለድና፣
አንዱ ይሞትና ሲቀር አንዱ ብቻ፣
ይሆናል ገበጣ* ያገር መጫወቻ፡፡

የሚለው ሶስቶ፣ ከላይ እንደተጠቆመው በሟች ወንድም ላይ የሚከሰተውን ውጤት ይገልጻል፡፡ ያገር መጫዎቻ ገበጣ መሆን፣ የትንሽ ትልቁ ተሽናፊነትንና አቅመቢስነትን ጠቋሚነቱ፣ የጥቃትን ወደዚያ ቤት መግባት ይጠቁማል፡፡

ወንድም ከሌለ ምንም ማድረግ ስለማይቻል፣ የሚመጣውን ሁሉ ፍዳ በጸጋ ለመቀበል ራስን ማበርታት እንደሚገባ፡-

ኧረ እነእገሌ አየ ወንድሞቼ መታሰር ነው እንጂ ክንድን አበርትቶ፣
ተውሶ እሚያስፈታ ወንድም ወት ተገኝቶ፡፡

በሚለው መንቶ ተገልጿል፡፡ እህት የእናትን ድርሻ እንደምትወጣው ሁሉ፣ ወንድምም በቤተሰብ ውስጥ የአባትን ሚና የሚተካ መሆኑ፣ በግጭት ጊዜ ደርሶ በማበር ድርጊታዊ ምላሽ በመስጠት ብቻ ሳይሆን፣ ግጭቶቹ በሕግ ሲያዙ ዋስ ሆኖ በማስፈታት መመኪያ መሆኑም ተጠቅሷል፡፡

ወንድም ተገንዞ ሲወጣ ተራራ፣
በዚህ ጊዜ አይደለ ጠላት የሚኮራ፡፡

በሚለው መንቶ፣ በሞቱ ቅጽበት የጠላት ማንሰራራት መታየት ተጠቁሟል፡፡ በወንድም ሞት ጠላት የሚኮራው፣ በእሱ መለየት ምክንያት ትከሻ የቀለላቸው ቀሪ እህቶችና ወንድም ላይ ጥቃት ቢፈጽም፣ የሚያሰጋው ነገር ካለመኖሩ ጋር የተያያዘ መሆኑ ሲታይ፣ የውጤቱን አስከፊ ገጽታ ያጎላዋል፡፡

* ገበጣ ከብይ መጫዎቻ ገደል በመጠኑ ሰፋና ጎድጎድ ያሉ ስድስት ጥንድ ጉድጓዶች ብዙ ጊዜ ንጥፍ ገሃ ድንጋይ ተቦርቡሮ፣ አልፎ አልፎ መሬት ተጭሮ በእያንዳንዱ ጉድጓድ ሶስት ሶስት ጠጠሮች ተቀምጠው በሂሳባዊ ስሌት የሚካሄድ ባህላዊ ጨዋታ ነው፡፡ ጨዋታው መዝናኛ ስለሆነ ያለልዩነት ሰዎች እየተፈራረቁ በመጫዎታቸው ማጠየቂያነት፣ ወንድም የሌለውን ሰውም ሁሉም እንደሚያጠቃው ለመግለጽ ነው፡፡

በአጠቃላይ ወንድም ለእህትና ወንድሞቹ ጥቃት መካች፣ መከበሪያና ዋሳቸው ስለሆነ፣ የእሱ መሞት፣ መደፈርን፣ መዋረድንና መናቅን እንደሚያስከትልባቸው ቃል-ግጥሞቹ ይገልጻሉ፡፡

በወንድም ሞት፣ ከአካላዊ መለየቱ በላይ፣ በመታጣቱ በእህት ወንድሞቹ ላይ የሚደርሱባቸው ከላይ የተዘረዘሩት በደሎች፣ ለከፉ አካላዊና ስነልቡናዊ ጉዳቶች የሚያጋልጧቸው መሆናቸውን ቀጥለው የቀረቡት ቃል-ግጥሞቹ ያስረዳሉ፡፡

ደጀኖቹ ሳሉ የልቡን ተናግሮ ያስቀየማቸው ሰዎች ብቻውን ሲቀርና ትከሻው ሲቀል ጉዳት እንዳያደርሱበት፡-

ኧረ ማሩኝ ሰዎች ሰዎች እባካችሁ፣
ወንድሞቼ ሳሉ የተናገርኳችሁ፡፡

በማለት ተማጽኖ ማቅረቡ፣ ለንስሃ ከመዘጋጀት ሳይሆን፣ ብቻን መቅረት ከወለደው ተስፋ መሚጠጥና ከባድነት ስሜት መመንጨቱ ሲጤን፣ ጥቃትን አምኖ መቀበልን ያሳያል፡፡ ይህ ደግሞ፣ ከከባድ የመንፈስ ስብራት የተወለደ እንገት መድፋትን ያስከትላል፡፡ ምክንያቱም፡-

ታርሶም ተሸምቶም ይበላል እንጀራ፣
እንደምን ነሽ ጥቃት የሞት ባልንጀራ፡፡

በሚል ማሕበረሰብ ውስጥ፣ ጥቃትን አምኖ ለመቀበል ራስን ማዘጋጀት፣ የቁም ሞትን በጸጋ መቀበልን ይጠቁማል፡፡ ይህ ደግሞ የስነልቡና ሥብራቱ በሕይወት መሳምዘዝ መደምደሙን ስለሚገልጽ፣ ቀደም ሲል ከተጠቀሱት የወንድም ሞት ከሚያስከትላቸው ውጤቶች፣ የከፋውን ገጽታ ጠቋሚ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

በአጠቃላይ ወንድም ለእህትና ወንድሞቹ ጥቃት መካች፣ መከበሪያና ዋሳቸው ስለሆነ፣ የእሱ መሞት፣ መደፈርን፣ መዋረድንና መናቅን ስለሚያስከትልባቸው፣ ከአካላዊ መለየቱ በላይ በመታጣቱ የሚደርሱባቸው በደሎች ለከፉ አካላዊና ስነልቡናዊ ጉዳቶች የሚያጋልጧቸው መሆናቸውን ቃል-ግጥሞቹ ያሳያሉ፡፡

እንደተጠኚው ባለ ከግለሰባዊነት ይልቅ ቡድናዊነት ጎልቶ በሚታይበት ማሕበረሰብ፣ የአንድ ሰው ሞት የሚያስከትለው ውጤት የሚጎዳው፣ ከላይ እንደተገለጹት የሥጋ ዝምድና ያላቸውን

የቤተሰብ አባላት ብቻ አይደለም። በምክራቸው መልካሙን መንገድ በሚያመላክቱት፣ በሕይወት ልምዳቸው እያስተማሩ በሚያንጹት፣ የተጣላን በማስታረቅ ሠላም በሚያወርዱትና ለማሕበረሰቡ ደህንነት በሚጨነቁት ሽማግሌዎች፣ የቡድኑን ጥቃት በሚመክቱትና ጥቅሙን በሚያስከብሩለት ጀግኖች ላይም ሲደርስ ነው።

ቀጥሎ የሽማግሌዎችና የጀግኖች ሞት በማሕበረሰቡ ላይ የሚያስከትለው ውጤት በቃል-ግጥሞቹ እንዴት እንደተገለጸ ተተንትኗል።

## 7.6. የሽማግሌ ሞት በማሕበረሰቡ ላይ

በተጠኚው ማሕበረሰብ ለሽማግሌዎች የሚሰጠው ክብር ከፍተኛ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። መንገድ ቀድመው እንዲሄዱ፣ በላይ በኩል እንዲቀመጡ፣ ምግብ ወይም መጠጥ በቡድን በሚቀርብበት ጊዜ በቅድሚያ እንዲያገኙ፣ ቀድመው እንዲናገሩ፣ ምርቃት እንዲያሳርጉ መደረጉ፣ ከክብር መገለጫዎቻቸው መካከል ጥቂቶቹ ናቸው። የማሕበረሰቡ ማሕበራዊ መዋቅር አባዊ መሆንና ሽማግሌዎች በማሕበራዊ ሕይወት ውስጥ ያላቸው ሚና ሰፊ ቦታ መያዝ፣ ለዚህ ክብር እንዳበቋቸው ለመረዳት ይቻላል።

ሽማግሌዎች ለማሕበረሰቡ ከሚሰጧቸው አገልግሎቶች ውስጥ፣ የተጣላን ማስታረቅ አንዱ ነው። ቀደም ሲል እንደተገለጸው፣ የማሕበረሰቡ ኑሮ በግብርና ላይ የተመሰረተ በመሆኑ፣ በድንበር፣ በግጦሽ፣ በመሬት ይገባኛል፣ በአዝመራ መበላትና በመሳሰሉት የመጋጨት እድሉ ሰፊ ነው። ጠቡ እየተካረረ ሄዶ ወደከፋ ደረጃ እንዳይሸጋገር፣ ሽማግሌዎች በዳይና ተበዳይን አገናኝተው አጥፊውን ገስጸው፣ ተበዳዩን መክረው፣ ይቅር በማባባል ሠላም ያወርዳሉ። እንዲህ የሚያደርጉት ሽማግሌዎች ሲሞቱ፡-

ሰው ሲጣላ አስታራቂ ማነው፣
እንግዲህስ ወዲያ ብላ ተባላ ነው።

በማለት ማሕበረሰቡን የሚጠብቀው የሠላም መታጣት አደጋ ይተነበያል።

ሽማግሌዎች የተጣላን በማስታረቅ ብቻ ሳይሆን፣ ጠብ እንዳይፈጠር ወይም ወጣቶች ከተለመደው የሕይወት መንገድ እንዳይወጡና የማሕበረሰቡ ሕልውና እንዳይናጋ ምክር በመለገስም፣ የማስተማርና የማረም ሚና ይጫወታሉ። እነሱ ሲሞቱ ይህን ማሕበራዊ አገልግሎት የሚሰጥ ስለሚጠፋ፡-

*ያንን ማዶ ዋርካ ማን ነው የቆረጠው፣*
*እንግዲህ እሾህ ነው የሚያቆጠቁጠው።*

በማለት አሁንም በማህበሩ ውስጥ ሊከሰት የሚችለው አደጋ ተገልጿል።

በበርካታ የወየታ ቃል-ግጥሞች፣ ሽማግሌዎች በዋርካና ባንባ እየተመሰሉ ተገልጸዋል። ዋርካ የትልቅነት፣ የመስፋፋት፣ የጥላነት፣ የከለላነት፣ የመታፈር፣ ተምሳሌት ተደርጎ ሲታይ፣ ባንባም በተመሳሳይ ሁኔታ ይገለጻል። ዛፎቹ በተፈጥሯቸው ቅርንጫፈ ብዙዎች ስለሆኑና ወደጎን በመስፋፋት ስለሚያድጉ፣ በእነሱ ተጽእኖ ምክንያት ከሥራቸው እነሱን በልጠው ሊወጡ የሚችሉ ሌሎች እጸዋት የማደግ እድል አያገኙም።

ይህን ከምልከታ የተገኘ ተፈጥሯዊ እውነት ወስደው፣ ከሰዋዊ ተቋማቱ ጋር በማያያዝ፣ ሽማግሌን በዋርካና ባንባ፣ ተንኮለኛንና የማሕበረሰብን ደህንነት የሚያውክን፣ በእሾህ ወክለው አቅርበውታል። ዋርካው ከስሩ በሚገኙ ቁጥቋጦዎች ላይ ተጽእኖ በመፍጠር በቁጥጥሩ ስር እንዲኖሩ እንደሚያደርገው ሁሉ፣ ሽማግሌዎችም ባላቸው ተሰሚነት፣ ከተከታዮቻቸው ከእነሱ በላይ ልሁን የሚል ተንኮለኛና ለማሕበሩ የማይበጅ እንዳይኖር እንደሚያደርጉ፣ በተመሳስሎ ተገልጿል። ዋርካው ሲወድቅ ከስሩ የእሾህ ማቆጥቆጥ በማጠየቂያነት ተወስዶ፣ በሽማግሌ ሞት ለማሕበሩ የማይበጁ ወገኖች መፈጠር አይቀሬነት ተገልጿል።

ትላልቁ አለቀ ዋርካና ባንባው*፣
ቀረ ኩሽሽላ**ው ሲያልፉ እሚወጋው።

የሚለው ቃል-ግጥምም ይህንኑ ሀሳብ የሚያጠናክር ነው።

* በመጠኑ አነስ ከማለቱ በስተቀር ቅጠሉም ሆነ አስተዳደጉ እንደዋርካ ያለ ዛፍ ነው።
** ቅጠሉ በጫፉና በጎኖቹ እሾህ የሚያወጣና የሚዋጋ የእጸዋት አይነት ነው።

ሽማግሌዎች በማስታረቅም ይሁን በማስተማርና እየተቆጣጠሩ መልካም ተከታዮችን በማፍራት፣ የማሕበረሰቡን ደህንነት ከማስጠበቅ በተጨማሪ፣ የሚኖሩበትን ቦታ ጥሩ ስም እንደሚያስጠብቁም መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ያንን ትልቅ ዋርካ ማን ነው የቆረጠው ስሩን ምሶ ምሶ?
‹የሰው የለሽ አገር› ለማለት ነው እንጂ ህዝብን አስለቅሶ፡፡

የሚለው ቃል-ግጥም፣ በላይኞቹ መንቶዎች እንደተገለጸው፣ እነሱ ሲሞቱ ምግባር የሚጎድላቸውና ማሕበረሰቡን የሚያውኩ ክፍሎች ስለሚያቆጠቁጡ፣ የማሕበረሰቡን ሕይወት ከማወካቸው በተጨማሪ፣ የሀገሩንም ሥም ያጠፋሉ፡፡ በባሕሉ፣ ‹‹የሰው የለሽ አገር›› የሚለው ሀረግ፣ የሰው ዘር አለመኖርን ሳይሆን፣ የደግን ሰው ካካባቢው መጥፋት ያመለክታል፡፡ ሽማግሌዎች ለሚኖሩበት ማሕበረሰብ ብቻ ሳይሆን፣ ለቦታቸውም አስከባሪዎች ተደርገው ስለሚታዩ፣ ሞታቸው የሚያስከትለው ጉዳት በሁለቱም ላይ ይንጸባረቃል፡፡

ታላላቁ ሞተ ያገር ከለላው፣
ሲቸግር የሚሰጥ ሲርብ የሚያበላው፡፡

የሚለው መንቶም፣ ከላይ የተገለጸውን ሀሳብ ያጠናክራል፡፡ እናት ልጆቿን ሰብስባ በመያዝ ጥላ ከላላ እንደምትሆናቸው ሁሉ፣ ሽማግሌዎችም የሚኖሩበትን ማሕበረሰብ በማቀፍ፣ ተመሳሳይ ኃላፊነት ይወጣሉ፡፡ በባሕሉ በእድሜ የገፉ ሰዎች ማሕበረሰቡን እንደራሳቸው ቤተሰብ አድርገው ስለሚያዩና ደህንነቱም የዚያኑ ያህል ስለሚያሳስባቸው፣ ግለሰቦች የሚገጥማቸውን ችግር የመጋራት ሚናቸው ሰፊ ነው፡፡ በመንቶው የተራበን በማብላትና የተቸገረን በመርዳት፣ ለማሕበረሰቡ ጥላ መሆናቸው ተገልጿል፡፡

የእነሱ መሞት ማሕበረሰቡን በመልካሙ እንዲሄድና ከመጥፎው እንዲርቅ የሚመክሩትንና የሚያስተምሩትን እንዲሁም አሳቢና ተንከባካቢዎቹን ስለሚያሳጣ ለጉዳት እንደሚጋለጥ በቃል-ግጥሞቹ ተደጋግሞ ተነስቷል፡፡ የማረፊያና የመጠለያ የትልቅ ዛፍ ተምሳሌትነት ያላቸው ሽማግሌዎች ሞት፣ የሚኖሩበትን ማሕበረሰብ፣ መካሪውን፣ አስታራቂውን፣ ተቆጣጣሪውንና አስተማሪውን በማሳጣት አንድነቱንና ሠላሙን ስለሚያናጋው፣ ጉዳቱን ከባድ እንደሚያደርገው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ABABA UNIVERSITY LIBRARIES BOX 1176 ADDIS ABABA, ETHIOPIA

ከዚህ በላይ በሽማግሌዎች ሞት፣ የሚኖሩበት ማሕበረሰብ የሚደርስበት ጉዳት በወየታ ቃል-ግጥሞቹ ተደጋግሞ ተገልጿል፡፡ የጀግኖች ሞት በሚኖሩበት ማሕበረሰብ ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ደግሞ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 7.7. የጀግና ሞት በማሕበረሰቡ ላይ

በማሕበረሰቡ ዘንድ አንድ ሰው ጀግና የሚባለው ሀሩርና ቁር ሳይፈራ ሰርቶ ጥሩ ምርት ያስገባና ለሌሎች የተረፈ፣ በተለያዩ ቦታዎች ለሀገሩ ተሰልፎ የተዋጋ፣ በቤተሰቡም ላይ ሆነ በሚኖርበት ማሕበረሰብ ላይ የተፈጸመን በደል ወደሕግ ወስዶ ተሟግቶ የረታ፣ በኃላፊነት ባስተዳደረበት ዘመን በቅንነት ያገለገለና ሚዛናዊ ፍርድ የሰጠ፣ እንዲሁም በአዳኝነቱ የታወቀ ተኳሽ ሲሆን ነው፡፡ ከእነዚህ በአንዱ የጀግንነት ክብር የተሰጠው ሰው ሲሞት፣ እንደሽማግሌዎቹ በጥቅል ሳይሆን በመጠሪያ ሥሙ ለጀግንነት ያበቃው ተግባር እየተጠቀሰ በቃል-ግጥሞቹ ይወሳል፡፡

በጀግና ለቅሶ የሚነሳው የሟች ሥምና ገድል ብቻ ሳይሆን፣ ከዚያ በፊት ለማሕበረሰቡ ጠቃሚ ሥራ ሰርተው ያለፉና በተግባራቸው የሚዘከሩ ሌሎች ጀግኖች ሥምና ሥራ ጭምር መሆኑን የተሰበሰቡት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ለቅሶ ላይ በአንዱ ሞት፣ የሥጋ ዝምድና ወይም የጋብቻ ትስስር የሌለውን ሰው በወየታና በሙሾ ቃል-ግጥሞች ማንሳት፣ አቅራቢውን የሚያስነቅፍ እንደሆነ አቶ ደሳለኝ ታየ (አባ.2፣ ቁ.7) ቢያስረዱም፣ በፉከራና ሽለላ ቃል-ግጥሞች ግን፣ የሙያ ግንኙነት ካለ የሥጋ ዝምድና የሌለውን ሁሉ እያነሱ መፎከርና መሸለል የተለመደ መሆኑን ከምልከታ መረጃዎቹ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በተጠኚው ማሕበረሰብ የቀረርቶና የፉከራ ግጥሞች በስፋት የሚከወኑ ሲሆን፣ በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ እንደሚያተኩሩም ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የሞታቸውን ጎጅነት በቀጥታ የሚገልጹ ይገኙባቸዋል፡፡

ፀሐይዋስ ጠለቀች ጨረቃን ተክታ፣
አሁን ምን ይሆናል ያለ ጀግና ቦታ፡፡

የሚለው መንቶ፣ ከሚች ረፍት ይልቅ ተተኪ ላለመኖሩ ትኩረት መስጠቱ፣ ጀግና ከሌለ ቦታው ሊደፈር የሚችል መሆኑን ከመገንዘብ ይመስላል። ከቦታ መደፈር በተጨማሪ፣ የጀግና ሞት በራሱ ማለፍ ብቻ የማይገደብ መሆኑንና በማሕበረሰቡ ላይ ጫና የሚያሳድር መሆኑን፡-

ደህና ጎበዝ ሲሞት ይስቃል ጅሉ ሰው፣
የታገተ ጥጃ የማያስመልሰው። እና
ደህና ጎበዝ ሲሞት ይስቃል ሞኝ ሰው፣
አገሩ ሲወረር ድንበሩን ሲያፈርሰው። የሚሉት ቃል-ግጥሞች ያመለክታሉ።

በባሕሉ ከብቶች የሰው ሰብል ሲበሉ፣ የሰብሉ ባለቤት ከህግ አግባብ ውጭ ከብቶቹን አግቶ ባለቤታቸውን ካሳ ይጠይቃል። የማገት ሂደቱ የአጋችን ጉልበተኛነትና የከብቶቹን ባለቤት ደካማነት ስለሚያሳይ፣ ጀግና የበላይነቱን አሳይቶ ንብረቱን ያስመልሳል እንጂ፣ ለእንዲህ አይነቱ ድርድር ፈቃደኛ አይሆንም። በሁለተኛው መንቶም በሞኙ ሳቅና ማድረግ በማይችለው ድርጊት፣ የጀግናው ማሕበረሰባዊ ጥቅም ተገልጾበታል። ጠላት አንድን ሀገር ወርሮ ድንበር የሚያፈርሰው፣ ሙሉ በሙሉ አሸናፊነቱን ሲያረጋጥና በስሩ ጠቅልሎ መያዝ ሲፈልግ ነው። በቃል-ግጥሙ፣ የሞኙ በጅግና ሞት ሳቅ፣ ይህን ካለመረዳት መሆኑ ከላይ ሲገለጽ፣ ከስር ጀግና የሀገሩን ድንበር በማስከበር የማሕበረሰቡ ደጀን መሆኑ ተጠቁሞበታል።

ከፍ ሲል እንደተገለጸው፣ በተጠኚው ማሕበረሰብ ተሚግቶ ማሸነፍ በተለይም ለማሕበረሰቡ ጥቅም ሲሆን፣ የተለየ የጀግንነት ክብር ያጎናጽፋል። በደቡብ ጎንደርና በሰሜን ጎንደር (በያኔው አጠራር በበጌምድርና ሰሜን ጠቅላይ ግዛት) መካከል፣ በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት የተነሳን የወሰን ይገባኛል ክርክር፣ ፋርጣ ወረዳ ውስጥ የሚኖር አግማሴ መኮንን የሚባል ተሚጋች፣ ለሕዝቡ ቁሞ በማሸነፍ የማሕበረሰቡን ጥቅም በማስከበሩ፣ በለቅሶው ላይ፡-

‹‹ደራና ፎገራ፣ ግራሪያና ውዶ፣ መና መቀጣዋ፣
እብናት፣ አሙስ ወንዝ፣ ኃይንትና ፋርጣ አገሬ ምናለ፣
የእነ አግማሴ ሱሪ ከመከታው* ዋለ።››

---

*ማጆቱን ከዕይታ ለመከለልና ከሳሎኑ ለመለየት የሚያገለግል ብዙ ጊዜ ከሸንበቆና አልፎ አልፎ ከቀጫጭን ጠገጎች ተሰርቶ በቀጭኑ የተመረገ ግድግዳ መሰል አካፋይ ሲሆን ከምርግ በላይ ከሚውሉት ቋሚ እንጨቶች ላይ ቅሎች ይንጠለጠሉበታል፤ አጎዛ ይሰቀልበታል።

ተብሎ ተገጥሞለታል፡፡ የለቅሶ ቃል-ግጥሙ ከዋኝ ከዚህ ታሪክ ተነስቶ፣ በቃል-ግጥሙ በተዘረዘሩት በደቡብ ጎንደር ውስጥ በሚገኙት ቦታዎች የሚኖረው ሕዝብ፣ በጀግናው ሞት ምን ስሜት እንደተሰማው፣ ምናልባትም ዱብእዳው የፈጠረበትን ድንጋጤ መጠን ይጠይቃል፡፡

በተጠኚው ማሕበረሰብ ሱሪ የጀግንነት ትዕምርትነት አለው፡፡ መከታ ላይ ሲውል ግን ተረካቢ ማጣትንና መውለቅን (መሸነፍን) ይገልጻል፡፡

የሰሜን ገበሬ በሰፊው ትለም፣
ይኽ ነው ደንበሩ የሚልህ የለም፡፡
አግማሴ ነበረ፣ ነበር በድንገት፣
ድንጋይ ተተንተርሷል፣
ያፈር ልጓም ጎርሷል፡፡

የሚለው ቃል-ግጥምም ከላይ የተገለጸውን ሀሳብ ያጠናክራል፡፡

በቀዳሚው ቃል-ግጥም የጀግናው ሱሪ መከታ ላይ መዋል፣ ተተኪ ያለማግኘትና የተሸናፊነት ትእምርትነት እንዳለው በተዘዋዋሪ የተገለጸው ሀሳብ፣ በዚህኛው ቃል-ግጥም በይፋ ይነገራል፡፡ የጀግናው ባላንጋራ ድንበር ተሻግሮ ዘና ብሎ እንዲያርስ እድሉ እንደከፈተለት ሲገለጽ፣ ያለአግማሴ ድንበር አሳይ (ወሰን አትሻገር ባይ) አለመኖሩ መጠቀሱ፣ በጀግናው እግር ሰው አለመተካቱን ብቻ ሳይሆን፣ ሟች ወደር የለሽ ጀግና መሆኑንም ይገልጻል ለማለት ይቻላል፡፡ ዞሮ ዞሮ የዚህ ጀግና ድንጋይ መንተራስና የአፈር ልጓም መጉረስ፣ የቦታ መደፈርን ስለሚያሳይ፣ በእሱ መታጣት ሞት ያመጣው ጣጣ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

እባክህ ወታደር ከገባህም አይቀር ቁርስህነን ብላ፣ ቡናህነን ጠጣ አታንገላታኝ፣
አግማሴ ሙቶብኝ ጠበቃም የለኝ፡፡

የሚለው ቃል-ግጥምም፣ ከላይ የተገለጸው ጀግና ለማሕበረሰቡ ይሰጠው የበረውን አገልግሎት ይገልጻል፡፡ ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት፣ በተለያዩ ቦታዎች ሽፍቶች እየተነሱ በአስተዳደሩ ላይ ያምጹ እንደነበር ታሪክ ያስረዳል፡፡ በደርግ ዘመንም፣ በበለሳና

በጉና ከተነሱት ሽፍቶች በተጨማሪ፣ የኢሕአፓ፣ የኢህዲንና የሕውሓት ታጋዮች ብቅ ጥልቅ እያሉ ስርዓቱን ያውኩ ነበር። በዚህ ጊዜ፣ እነሱን ለመደምሰስ የሚዘምተው መደበኛ ጦር ሳይሆን፣ ጠመንጃ ያለው የአካባቢው የገበሬ ሚሊሽያ ጦር (የጢስ ብረት) ነበር። ጦሩ ስንቅ ስለማይዝ፣ በየደረሰበት በገበሬዎች ቤት እየተመራ ምግብ ይበላል። የተዘመተበት አካባቢ የሽፍታ አገር ወይም የወንበዴ ደጋፊ ተደርጎ ስለሚታይ፣ በየቤቱ የሚመሩት ወታደሮች የገበሬውን ፍየልና በጎች አስገድደው በማረድ፣ ጠላ፣ እርጎና ማር እንዲቀርብላቸው በማፋጠጥ፣ ገበሬውን የማስጨነቅና አለፍ ሲልም የመደብደብ ተግባር ይፈጽሙ ነበር።

የሚዘመትበት አካባቢ ተቆርቋሪና ተሚጋች ጀግና ካለው ግን፣ ከአዝማቹ ጋር ተነጋግሮ ወታደሩን አልፎ እንዲሄድ፣ ቢገባ እንኳ በሥርዓት ተስተናግዶ እንዲወጣ የማድረግ አቅም ይኖረዋል። በቃል-ግጥሙ ውስጥ አግማሴ በአካባቢው ወታደር እንዳይመራ በማድረግ ለማሕበረሰቡ የጥብቅና ሥራ ይሰራ እንደነበርና እሱ ከሞተ በኋላ አካባቢው ተጎዳ እንደሆነ በቀጥታ ተገልጿል።

ጀግና የወጣበትን ማሕበረሰብ የጋራ ጥቅም በማስከበር ብቻ ሳይሆን፣ ወራሪ ጠላትን በመመከት ላበረከተው አስተዋጽዖ ወይም ላሳየው ተጋድሎ ክብር ተሰጥቶት እንደሚዘከር፣ ቀጥሎ የቀረቡት ቃል-ግጥሞች ይገልጻሉ። ከላይ ከተገለጸው ታሪካዊ ክስተት በፊት፣ በጣሊያን ወረራ ወቅት አርበኞች ደፈጣ እየጣሉ ቢያውኩ፣ የወራሪው ጦር ደካሞችንና ሕጻናትን ሳይለይ የአከባቢውን ሰው ሰበስቦ፣ አንድ ጎጆ ቤት ውስጥ ዘግቶ አቃጥሎ ይፈጃቸዋል። በዚህ ምሬት ወደትግል ለገባውና የአካባቢውን ማሕበረሰብ ለታደገው ጀግና፡-

ሰባ ሰባት ሰው እያዳ* ነደደ፣
ይህንን አየና ተነሳ ከበደ፣
ተስቦ ተስቦ እንደውንጮ** አገዳ፣
የሰው ዘር ያወጣው ያ ከበደ እንግዳ።

---

*ከጉና በስተሰሜን ፋርጣ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ የጣሊያን ወታደሮች ሰባሰባት ሰው ከአንድ ቤት ውስጥ ዘግተው በእሳት በጅምላ ያቃጠሉበት ቦታ።
** የማሽላ አይነት ሲሆን ራሱን የሚሸከመው አገዳ (አንገቱ) ረጅም በመሆኑ ግራና ቀኝ ዘነብል እያለ ተላልፎ ይጠላለፋል።

ተብሎ ተገጥሞለታል፡፡ ቃል-ግጥሙ ጀግናውን በወገን ላይ የተፈጸመ ግፍ ለትግል እንዳነሳሳውና ወገኑን ከመሰል ጥቃት ለማስጣል የቻለ ባለድል መሆኑን በመግለጽ ባለውለታነቱን ይዘክራል፡፡

በአያዳ የተፈጸመው የጅምላ አሰቃቂ ፍጅት በሌሎች አካባቢዎች እንዳይደገም ወደውጊያ ለገቡት አርበኞች፡-

እንደ ወገኔ ሳልንገበገብ፣
ታጥቆ ተነሳ ደስታ አባ ታገል፣
‹እሰየፋለሁ› አለ ላገሬ፣
ፈረደ በላይ ግራዝማይ በሬ፣
መልዛን በሙሉ ሱሪ አስታጠቀው፣
አንጠበጠበው ተሾመ ላቀው፡፡

ተብሎ መፎከሩ፣ እነዚህ ጀግኖች ለማሕበረሰባቸው በክፉ ቀን የዋሉትን ውለታ ከመዘከሩ ባሻገር፣ ሞታቸው የሚያስከትለውን ጉዳት ይጠቁማል፡፡

በአካባቢው ‹‹ጎረቤቴ በሰላም ይዋል እኔም በሰላም እንድውል›› የሚል አባባል አለ፡፡ ይህ ቀደም ሲል እንደተገለጸው፣ የቡድን መተሳሰብን አመልካች ነው፡፡ ጀግኖች፣ የሚኖሩበት ማሕበረሰብ በጉልበተኞች እንዳይጠቃ፤ በጦር ሜዳ ታግለው፣ በቀማኞች ድርሻውን እንዳያጣ፤ በፍርድ ቤት ተሟግተው፣ ጥቅሙን ሲያስከብሩና አካባቢውንም በመልካም ሥም ሲያስጠሩ፣ በዚያውም ቡድናዊ መተሳሰቡን የማጠናከርና ተተኪዎችን የማነሳሳት ሚና ይጫወታሉ፡፡ በእነሱ ላይ የሞት መምጣት የሚያስከትለው ውጤት፣ እነዚህን ሁሉ መልካም እሴቶች የሚያሳጣ መሆኑ፣ የማሕበረሰቡን ሀዘን ከባድ ያደርገዋል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ የቤተሰብ አባል ሞት፣ በቀሪ ቤተሰቦች ላይ፣ የጀግኖችና የሽማግሌዎች ሞት፣ በሚኖሩበት ማሕበረሰብ ላይ፣ የሚያስከትሉት ጉዳት ብቻ ሳይሆን፣ የርስበርስ ትስስራቸው ጥብቀትና ከዚሁ የሚመነጨው ስነልቡናዊ ስብራት ጭምር በለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ እንዴት እንደተንጸባረቀ ተተንትኗል፡፡

እስካሁን በዓለማዊ ሥርዓቶቹ ክወና በቀረቡት መረጃዎች ከተንጸባረቁትና ቀጥሎ ከቀረቡት ቃል-ግጥሞች ለመረዳት እንደተቻለው፣ ተጠኚው ማሕበረሰብ ሞትን ሰዋዊ ባህሪ አላብሶ በተለያየ ግብሩ ይገልጸዋል፡፡ በየቤቱ እየዞረ ሁሉንም የሚጠይቅ መሆኑ፡-

ከደጅ አሳድሩት ሞት እንግዳውን፣

በየ ሁሉ ደጃፍ የሚደርሰውን፡፡

በሚለው መንቶ ተገልጿል፡፡ ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ እንግዳ ክቡር ሆኖ እያለ ሞት ከውጭ እንዲያድር የሚፈረድበት፣ እንከን ያለበት ተደርጎ ስለሚታይ ነው፡፡ ከእንከኖቹ አንዱ አስፈሪነቱ መሆኑ፡-

ኸረ ሞት አጅሬ ሲመጣ በበሩ፣

ድንግጥ ድንግጥ ይላል መኳንንቱ ሁሉ፡፡

በሚለው መንቶ ተገልጿል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ መኳንንት ከፍተኛ ማህበራዊ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የማሕበረሰብ ክፍሎች የሚሰጥ የማዕረግ ስም ስለሆነ፣ እነዚህ የማሕበረሰብ ክፍሎች የሚከበሩና የሚፈሩ እንጂ፤ እንደተራ ሰው የሚደነግጡና የሚፈሩ ተደርገው አይወሰዱም፡፡ ሞት ሲመጣ መደንገጣቸው ቀጪና ተቆጪው መሆኑን ይጠቁማል፡፡

ሞት ሰዋዊ አካል ለብሶ ሰዎችን ለመጠየቅ ሲጓዝ ያገኘው መንገደኛ እንደተጠኚው ማሕበረሰብ ወግ ሰላምታ ሲሰጠው፣ የሚጠበቀውን ምላሽ ሳይሆን ቀጥሎ በቀረበው አራቶ እንደታየው ከሰላምታ ሰጪው ጋር አለመተዋወቁን ይገልጻል፡፡

አያ ሞት አጅሬን አግኝቼው ከምንገድ፣
‹‹እንደምን ዋልክ›› ብለው ‹‹አላውቅህም›› አለኝ፣
‹‹ምነው አታውቀኝም ታውቀኛለህ እንጂ፣
አንተ በየቀኑ ሰው አጥፊ ነህ እንጂ፡፡››

ቃለ ምልልስ አድራጊው ለሠላምታው በጎ ምላሽ ላለማግኘቱ በሞት የቀረበውን ምክንያት ሳይሆን ዘወትራዊ ዝንጉነቱን መግለጹ፣ ተጠኚዎቹ ስለሞት ያላቸውን ዓለማዊ አመለካከት ጠቋሚ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በባህሉ ለአንድ ሰው አጅሬ የሚለው ቅጽል በገንቢም ይሁን በአፍራሽ የሚሰጠው፣ ከሌሎች ልቆ የሚታወቅበት አንዳች ባህሪ ሲኖረው ነው፡፡ ሞት ከላይ በቀረቡት

ሁለት ቃል-ግጥሞች በዚህ ቅጽል የተገለጸው፣ በአስደንጋጭነቱና በዝንጉነቱ መሆኑ፣ እውቅና የተሰጠው በአፍራሽ ጎኑ መሆኑን ይገልጻል፡፡ ይህ ዓመሉ በቃል-ግጥሞቹ እንደተገለጸው በሰዎችና በሞት መካከል ላለው አለመግባባት መንስኤ ተደርጎ ቀርቧል፡፡ በሠላምታ ልውውጣቸው የተስተዋለው አለመግባባትና መወቃቀስ እርቅ ለማይገኝለት የሁለቱ ግንኙነት ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ሠላምታ አቅራቢው ትውውቃቸው (አብረው መኖራቸው?) በሞት ሁሌ ሰው አጥፊነት መሻከሩን የገለጸበት ቅኔ፣ ያለመግባባታቸው ቁልፍ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ተጠኚው ማሕበረሰብ ለሞት ያለው ዓለማዊ አመለካከት ዋና ማሳያ ሊሆን ይችላል ቢባል ያስኬዳል፡፡ ምክንያቱም ሰውን ያለ አድሎ እየጠየቀ ቸር እንግዳ ተደርጎ የማይታየውና በበር ሲያልፍ የተከበሩትን ሳይቀር የሚያስደነግጠው፣ በየቀኑ ሰው አጥፊ (ገዳይ) በመሆኑ ነው፡፡

ተጠኚዎቹ ለድርጊት ፈጻሚው ያላቸው አመለካከት ለድርጊቱ ውጤት ያላቸውን ግንዛቤ ይጠቁማል፡፡ ሞትን የሚጠሉት ውጤቱ እስከውዲኛው ድረስ መለያየት በመሆኑ እንደሆነ፡-

ማዘን ለሞተ ሰው ማልቀስ ለሞተ ሰው፣

እስከወዲያው ድረስ ለማይመለሰው፡፡

በሚለው መንቶ ተገልጿል፡፡ ይህ ደግሞ በሞት ብያኔ ስር እንደተጠቀሰው፣ ተጠኚው ማሕበረሰብ ሞትን መለየት አድርጎ እንደሚመለከተው ይገልጻል፡፡ መለየቱ የሚገለጸው ግን በሟች ከምድራዊ ሕይወት መወገድና ከቋሚዎች ጋር ዳግም በአካል ባለመገናኘት እንጂ፣ በሀይማኖታዊ አመለካከት እንደተገለጸው፣ ተስፋ ከሚደረገው የወዲያኛ ዓለም ሕይወት (ጽድቅ) ጋር የተያያዘ አይደለም፡፡

## ምዕራፍ ስምንት

### 8. ማጠቃለያ

ከተጠኚው ማህበራሰብ የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደሚያሳዩት፣ ሕይወት ከጽንሰት ተነስቶ ወደመድረሻው ሞት ላፍታ እንኳ መቆም ወይም ማረፍ ሳይችሉ በተመጠነ ፍጥነት የሚገሰግሱበት የአንድ አቅጣጫ ጉዞ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ጉዞ፣ ሞትና ሕይወት በአንድ አካል ላይ ተዳብለው ተሳፍረው በውስኗ የጊዜ ምህዋር ላይ ይሽከረከራሉ፡፡

ሰው ከእናቱ ማሕጸን ሲወለድ ተረግዞ፣

በሞት ጎዳና ላይ ይጀምራል ጉዞ፡፡ እንዳሉ ከበደ (1994፣70) ፡፡

ይህ በተቃርኖ ውስጥ የሚገኝ የሕይወትና ሞት ደባል ጉዞ፣ በዓለማዊ እይታ ነፍስ ከስጋ ስትለይ (አፈር ወደአፈር ሲመለስ) የሚቋጭ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ *ሥጋ* ወደአፈር ነፍስ ወደአስገኚዋ እግዚአብሔር መመለሳቸው የሕይወትን ጉዞ ወደመነሻ ያደርገዋል፡፡ *ሥጋ* ወደአፈር፣ ነፍስ ወደእግዚአብሔር ከተመለሱ በኋላ እስከፍርድ ቀን ድረስ *ሥጋ* ከአፈር፣ ነፍስ ከሞት ተዳብለው ይቆያሉ፡፡ በፍርድ ቀን *ሥጋ* ከአፈር ተፋትታ ከነፍስ ጋር እንደገና በመዋሃድ፣ እንደሚች *ሥራ* በጽድቅ ከሞት ተፋትታ ዘላለማዊ ሕይወትን ስትቀዳጅ፣ በኩነኔ ከሞት ተጋብታ ዘላለማዊ ፍዳን ትገፍታለች ተብሎ እንደሚታመን ለመረዳት ተችሏል፡፡

ይህ ሀይማኖታዊ አመለካከት፣ በተጠኚው ማሕበረሰብ ሕይወትና ሞት ምድራዊና ሰማያዊ ተብለው በሁለት እንዲከፈሉ አድርጓቸዋል፡፡ ምድራዊ ሞትና ሕይወት ተራና ጊዜያዊ ተደርገው ሲወሰዱ፣ የወዲያኛው ዓለም ሞትና ሕይወት ግን ዘላለማዊ ተደርገው ስለሚታዩ ክብደት ይሰጣቸዋል፡፡ ምክንቱም የዚህኛው ዓለም ሕይወት የ*ሥጋ* ሲሆን፣ ሞቱም የ*ሥጋ* ብቻ ነው፡፡ በወዲያኛው ዓለም ግን ዘላለማዊ ሞቱም ሆነ ሕይወቱ የነፍስ ጭምር ነው፡፡

የዘላለማዊዩ ዓለም ሞት (የነፍስ ከእግዚአብሔር መለየት) አስፈሪነትና ሕይወቱ (የነፍስ ከእግዚአብሔር ጋር መኖር) ተናፋቂነት፣ ተጠኚው ማሕበረሰብ፣ በአንድ በኩል ምድራዊ ሞት ሲከሰትና ሕይወት ስትጎመዝዝ በቀላሉ እንዲያየውና ለከፋ ስነልቡናዊ ቀውስ እንዳይጋለጥ በማድረግ፣ በሌላ በኩል፣ በመልካም ባሕርያት እንዲታነጽ፣ ሠላሙ እንዲጠበቅና ተዛዝኖ እንዲኖር በማበረታታት፣ ምድራዊ ሕይወቱ እንዲሰምር በማድረግ የጎላ ሚና የሚጫወት

መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ዞሮዞሮ፣ ሞት ለሕይወት ትርጉም መስጫ ብቻ ሳይሆን ለስምረቱም ቅመም ሁኖ ተገኝቷል፡፡ የሚከተሉት ግኝቶችም የጥናቱ ውጤት ሁነው ተመዝግበዋል፡፡

1. ተጠኚው ማሕበረሰብ ከሚያከናውናቸው የለቅሶ ሥርዓቶች ውስጥ፣ የሬሳ ማሰናዳቱ፣ መገነዙና በተለይ የሀዘን አገላለጽ ልማዱ፣ ከእስራኤላውያን የሀዘን አገላለጽ ልማድ ጋር በብዙ መልኩ የሚመሳሰል ሁኖ ተገኝቷል፡፡ የእስራኤላውያን በማህበራዊ ግንኙነትና በስደት ምክንያት ወደኢትዮጵያ መግባትና ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ ለረዥም ጊዜ በጉርብትና መኖር፣ እንዲሁም ከሀዲስ ኪዳን በፊት በኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን እምነት ተንሰራፍቶ መቆየት፣ ለልማዶቹ መወራረስ የራሳቸውን አስተዋጽዖ እንዳደረጉ ለመረዳት ተችሏል፡፡

2. የተጠኚው ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ቀደም ሲል በተደረጉት ጥናቶች የሚታወቁት፣ በሙሾ፣ በፉከራና በቀረርቶ ዘውጎች ነበር፡፡ በዚህ ጥናት የወየታ ቃል-ግጥም ዘር መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ ይህ የቃል-ግጥም ዘር ለሚከወንላቸውም ሆነ ለከዋኞቹ ጾታና እድሜ የማይለይ ሲሆን፣ በከዋኝና ታዳሚ መስተጋብርና በክወና ከሙሾ፣ ከቀረርቶና ከፉከራ የተለየና ራሱን የቻለ ዘውግ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

3. በዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የተካሄዱ የተለያዩ ጥናቶች፣ የሙሾ ቃል-ግጥም ክወና በሴቶች እንደሚካሄድ ያስረዳሉ፡፡ ይህ ጥናት በተካሄደባቸው ስፍራዎች በጊዜ ሂደት ሴቶች ከሙሾ ክወና መውጣታቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከሁሉም የጥናቱ አካባቢዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች እስከ1930ዎቹ አካባቢ ሴቶች ሙሾ ያወርዱ እንደነበር ያስረዳሉ፡፡ ከተጠቀሰው ጊዜ በኋላ በወንዶች እንደተተኩና በአሁኑ ጊዜ ሴቶች ሙሾ በማውረድም ሆነ በመቀበል እንደማይሳተፉ ተረጋግጧል፡፡ ሴቶች ከዚህ ዘውግ ክወና በወንዶች እንዲገፉ ካደረጓቸው ውስጥ፣ በሕይወት ያለን ሰው ስም በስህተት ጠርተው በማስለቀሳቸው የደረሰባቸው ተግሳጽ አንዱ መሆኑ በመረጃ አቀባዮቹ ተጠቅሷል፡፡ ያ ወቅት የጠላት ወረራ የተካሄደበት ከመሆኑ አኳያ፣ በግፍ ለተገደሉት ቁጭቱ፣ ጀብዱ ለሰሩት ሙገሳው፣ ከሙሾ ይልቅ ለቀረርቶና ፉከራ መመቸቱና

ክወናዎቹም በወንዶች የሚቀርቡ መሆናቸው፣ ሴቶችን ከክወና ሳያስወጧቸው እንዳልቀሩ ለመገመት ይቻላል፡፡

4. እንደሙሾ ክወናዎቹ በከዋኞቹ በኩል ባይሆንም፣ በፉከራና ቀረርቶ ቃል-ግጥም ክወናዎችም፣ ቀደም ሲል ይከወንላቸው ከነበሩት የማሕበረሰብ ክፍሎች አኳያ፣ ለውጥ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ ተጠኚው ማሕበረሰብ ቀደም ባለው ጊዜ፣ ጦር ሜዳ ለዋሉ፣ በግብርና ሥራቸው ለተመሰከረላቸው፣ በአዳኝነታቸው ለታወቁ፣ ተሟግተው ለረቱና በመልካም አስተዳደራቸው ለተመሰገኑ፣ ለጀግንነት ያበቋቸው መሳሪያዎች በአካል ተይዘው ወይም በስም እየተጠሩ በለቅሷቸው ላይ ይፎከርላቸው እንደነበር መረጃ አቀባዮቹ ይገልጻሉ፡፡ ቀደም ሲል ሚችን ባልዋለበት አውሎና የሌለውን ማሕበራዊ ደረጃ ሰጥቶ መፎከር እንደነውር የሚቆጠር ብቻ ሳይሆን፣ ከክወናው ላይ ፊት ለፊት ተቃውሞ የሚያስሰነዝር ውግዝ ተግባር ነበር፡፡

   በአሁኑ ሰዓት ለማንኛውም ሰው ያለሥራውና ያለማሕበራዊ ደረጃው እየተፎከረ እንደሆነና ወጣቶች በስፋት ወደክወናው በመግባት የቃል-ግጥም ዘርፉን እያጠናከሩት እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ለዚህ ለውጥ፣ በፊውዳሉ ሥርዓት የተለያየ ማዕረግ ተሰጥቷቸው የነበሩ ሰዎች በወታደራዊው አስተዳደር ዘመን፣ በአንድ በኩል እንደወንጀለኛ እንዲቆጠሩና ክብራቸው ዝቅ እንዲል መደረጉ፣ በሌላ በኩል የሰው ልጅ እኩልነት መታወጁ አንዱ ሲሆን፣ የእነዚህ ሰዎችም ሆነ በጣሊያን ወረራ ወቅት የተዋጉ አርበኞች በቁጥር እየተመናመኑ መሄድ ሌላኛው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለሁሉም ያለ ገደብ መፎከር እንደነውር ካለመታየቱ በተጨማሪ፣ ፉከራ ጥሩ ድምጽ ባለውም ሆነ በሌለው ሊከወን መቻሉ፣ ለታዋቂ ከዋኞች ክብር የሚሰጣቸውና ጠቀም ያለ ገንዘብ የሚከፈላቸው መሆኑ፣ ለዘውጉ እየተጠናከረ መምጣት በምክንያትነት ይጠቀሳሉ፡፡

5. ከቃል-ግጥም ክወናዎቹ በተጨማሪ፣ በለቅሶ ሥርዓቱ ላይ በጊዜ ሂደት ከታዩት ለውጦች ውስጥ፣ የቀጠሮ ለቅሶ ቦታ ለውጥ ይጠቀሳል፡፡ እስከአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት መጨረሻ፣ የቀጠሮ ለቅሶ ሚች በሚኖርበት አካባቢ በተመሳሳይ ሁኔታ ይፈጸም እንደነበርና ከደርግ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በላይ ጋይንትና በፎገራ ወረዳዎች በገበያ ዳርቻዎች የሚካሄድበት ሥርዓት መፈጠሩን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ባሕሉ ከላይ ጋይንት

አጎራባች ወረዳ ከመቂት መወረሱንና፣ እንደማርገኛ ለቅሶ የእዝን አቅርቦትን የግድ የማይል መሆኑ፣ የተፈጥሮ አደጋ በተደጋጋሚ በሚከሰትባቸውና በአንጻራዊነት የኑሮ ውድነት አይሎ በሚታይባቸው በእነዚህ ወረዳዎች ተመራጭ ሁኖ መስፋፋቱን ለመረዳት ተችሏል፡፡

6. በተጠኚው ማሕበረሰብ የለቅሶ ሥረዓት ክወና፣ ከማሕበረሰብ እስከቤተሰብ ድረስ ያለውን ትስስር ማጠናከሪያና እንዳይላላ ማጥበቂያ ገመድ በመሆን እንደሚያገለግል ለመረዳት ተችሏል፡፡ ሞት የሰው ልጅ የጋራ እጣፈንታ መሆኑ፣ የቋሚን አጠቃላይ ስነምግባር በማረቅ ሕይወትን መስመር የማስያዝና ተዛዝኖና ተረዳድቶ ለመኖር የሚያስችሉ መልካም ባህርያት እንዲዳብሩ የማገዝ ሚና ይጫወታል፡፡ መተዋወቂያ፣ መጠያየቂያ፣ ቀደም ሲል በአባቶች የነበረውን የመረዳዳት ባህል እየተረከ ማስተማሪያ፣ ግንኙነትን ማጠናከሪያና ባህልን ማስተላለፊያ ሆኖ እንደሚገለግልም ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

7. የሁሉም የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ክወና ተቀዳሚ ተግባርም፣ ቋሚዎች ለሟቾች የተሰማቸውን ጥልቅ ሀዘን ለመግለጫነት፣ ለብሶት መተንፈሻነትና የለቅሶ ሥርዓቱን ለማድመቂነት እንደሆነ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ የጀግኖች፣ የታታሪ ሰራተኞችና የተለያዩ ባለሙያዎች ጠንካራ ጎኖች እየተነሱ ታሪካቸው ለተተኪው ትውልድ የሚተላለፍባቸው ብቻ ሳይሆኑ፣ ተተኪው ትውልድ በመልካም አርያነት እንደተነሱት ቀዳሚዎቹ እንዲሆን የማነሳሳት ሚና እንደሚጫዎቱም መረጃ አቀባዮቹ ይገልጻሉ፡፡ ሀዘንንና ብሶት ስለሚተነፈስባቸው ታምቆ ቢቀር በጤና ላይ ሊከተል ከሚችለው ችግርና ሠላም ማጣት የመታደግ፣ ሥነልቡናዊ ጠቀሜታ ያላቸው መሆኑንም ለመረዳት ተችሏል፡፡

8. የመታሰቢያ ሥርዓቶቹም፣ በሕያዋንና በሙታን መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖር፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚከወነው ባሕላዊ ልማድ ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፍና በቋሚዎቹ መካከል መተሳሰብ እንዲፈጠር በማድረግ ሥነልቡናዊ፣ ባሕላዊና ማሕበራዊ ጠቀሜታ ያላቸው መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በለቅሶ ሥርዓቶቹ ክወና ላይ በጊዜ ሂደት ከተከሰቱ ለውጦች በተጨማሪ፣ ውሃ፣ ውሃ ያልነካው የከፈን ጨርቅ፣ ሰሌን፣ የሬሳ ሰባት ቦታ ላይ መገነዝ፣ ሬሳ ሲወጣ የሸክላ መሰበር፣ የግንዘት ወይም የዑደት ጊዜ መብራቶች፣ የሬሳ በጓዳ መውጣት፣ ሰባቱ የፍትሃት ጸሎቶችና ሬሳ ከመቀበሩ በፊት በቤተክርስቲያን እንዲሰግድ መደረግ፣ ትዕምርታዊ ትርጉም ካላቸው በሥርዓቱ ውስጥ ከሚፈጸሙ ድርጊቶችና ሥርዓት ማስፈጸሚያዎች መካከል ጉልሆቹ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

## 8.2. ይሁንታ

በደብረታቦር ዙሪያ ወረዳ ከ1990ዎቹ መጨረሻ ዓመታት ጀምሮ ተግባራዊ እየተደረገ ያለውና በሌሎች ወረዳዎችም እንደሚቀጥል ፍንጭ የታየበት በለቅሶ ሥርዓቶቹ ላይ የተጣለው ክልከላ፣ በጊዜ እጥረት ምክንያት ሥርዓቶቹ እንዲታጠሩ ማድረጉና ተላልፎ በተገኘ ላይ የሚጣለው ቅጣት፣ ከገንዘብ ከእድር እስከመባረር ጠንከር ያለ መሆኑ፣ ከፍ ሲል በተገለጹት የሥርዓቶቹ ክወናዎች በጎ ጎኖች ላይ የሚያሳድረው ጫና ቀላል እንዳልሆነ አስተውያለሁ፡፡

የማሕበረሰቡን የመረዳዳት ባሕል ማጠናከር፣ ሀዘንን ማቅለል፣ ታሪክን ማስተላለፍና ወጣቱ ትውልድ የቀዳሚዎቹን ፈለግ እንዲከተል ማነሳሳት፣ ከሥርዓቶቹ በጎ ጎኖች ውስጥ ቢጠቀሱም፣ ከአቅም በላይ ለተገካር ወጭ ማውጣት፣ሀዘንን ለመግለጽ በአካል ላይ ጉዳት ማድረስ፣ በየጊዜው ወደሀዘንተኞች ቤት እየሄዱ መላቀስ፣ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሥነልቡናዊ ችግሮች ከሚያስከትሉት ውስጥ ይገኛሉ፡፡

ስለሆነም የለቅሶ ሥርዓቶቹንም ሆነ ቃል-ግጥሞቹን ክወናዎች በጥቅል በአጉል ባህልነት ፈርጆ ማዕቀብ ከመጣል፣ መወገድና መቀጠል ያለባቸውን በጥናት መለየት ተገቢነት ይኖረዋልና የሚመለከታቸው አካላት አሁንም ትኩረት ቢሰጡ መልካም ይሆናል፡፡

የምርምር ሥራዎችን ተወልዶ ባደጉበት ባሕልና በማያውቁት እንግዳ ባሕል ላይ በማካሄድ ዙሪያ የሁለቱንም ጠንካራና ደካማ ጎኖች እየጠቀሱ የሚካሄዱ ክርክሮች መኖራቸው ይታወቃል፡፡ ክርክሮቹ የሚካሄዱት በአመዛኙ በምዕራባውያኑ መሆኑ፣ የአፍሪካውያኑን ልዩ ልዩ ማሕበረሰቦች መረጃ የመስጠት ባህልና የተቋማትን የገንዘብ አቅም ግምት ውስጥ ያስገባ አይመስለኝም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በጥናት ሰበብ በጉያ የሚያዙ ድብቅ ዓላማዎችና በሁሉም መስክ ‹‹እኛ ያልነው ይሁን››

የሚሉ አካዳሚያዊ የቅኝ ግዛት አስተሳሰቦች፣ የራስን ባሕል ማጥናትን ብዙም በአዎንታዊ ጎኑ እንደማያዩት ለመገመት አይከብድም፡፡

ከዚህ ጥናት ተደጋጋሚ የመስክ ጉዞዎች በተግባር ያገኘሁት ልምድ ግን፣ የአንድን ማሕበረሰብ ባህል በጥልቀት ለማጥናት፣ በሚያውቁት ባሕል ብቻ ሳይሆን፣ በሚታወቁበት አካባቢ ማካሄድ ጉልህ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ነው፡፡ ቁልፍ መረጃ አቀባዩ ቀኝ ጌታ ዜናዊ ‹‹የወዳጄ ወንድም ሁነህብኝ እንጂ፣ እንደሌላውማ ብትሆን በቀደም ነካ ነካ አድርጌ እሸሕኝ አልነበር›› ፣ ሲሉ የተናገሩት፣ መተዋወቅ መረጃ አቀባዩ ላይ ለሚያሳድረው በጎ ተጽዕኖ ጥሩ ማስረጃ የሚሆን ይመስለኛል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ተጠያቂዎች አንዳንዴ ትኩረት ሳይሰጡ፣ በጣም አልፎ አልፎ ሆን ብለው ሊያልፏቸው የነበሩ ቁምነገሮችን እንዳይዘሉ በማድረግና በትዕምርቶች መካከል የሚገኙ ተቀራራቢነቶችን አገናኝቶ ለማየት በማስቻል፣ የሚያውቁት ባሕል ላይ ጥናት ማካሄዱ ጠቃሚ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡

ስለሆነም የአጥኚውን ማንነትና ፍላጎት ሳያውቅ በብዙ ጥርጣሬ ተሞልቶ በ‹‹ልገላገል›› ስሜት ከሚገኝ መረጃ ለመዳን፣ ማንነት በሚታወቅበትና ‹‹ለክፉ አይሰጠኝም›› የሚል አመኔታ በሚጣልበት አካባቢ ጥናትን ማካሄድ፣ የተሻለ ውጤት ለማግኘት የሚያግዝ ስለሚመስል ተመራማሪዎች ለዚህ ትኩረት ቢሰጡ መልካም ይሆናል፡፡

## 8.3. ትዝብቶች

በለቅሶ ሥርዓቶቹና በቃል-ግጥም ክወናዎቹ ላይ በሀይማኖትም ሆነ በአስተዳደር አካላት በተለያየ ጊዜ ክልከላዎች መደረጋቸው፣ የሀይማኖት አባቶችና የአስተዳደር አካላት በአሉታዊ መልኩ እንደሚያዩዋቸው ይጠቁማል፡፡ ተጠኚው ማሕበረሰብ በእነዚህ ክልከላዎች ሳይገደብ እየከወናቸው ዛሬ ላይ ደርሷል፡፡

ዘመናዊ ሕግ ከመረቀቁ በፊት ቢያንስ ለሰባት መቶ ዓመታት (ከ1270-1966) በኢትዮጵያ የነገሱትን ነገስታት ሥልጣን ይወስን በነበረውና እንደሕገ መንግሥት ሆኖ ያገለግል በነበረው በ‹‹ክብረ ነገስት›› እና ቢያንስ ከአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በመንግሥት ደረጃ፤ በአዋጅ፤ እንዲሁም በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት፣ በስብከት፤ በለቅሶ ሥርዓቶቹ ላይ ክልከላ ተጥሎ፣ ሕዝቡ ያለማቋረጥ የሚተገብራቸው ለምን ይሆን? የሚለው ጥያቄ ከትዝብቱ መንጭቷል (ሀይማኖት፣ መንግሥታትና

ተጠኚዎቹ ሳይደማመጡ እንዴት አብረው ሊኖሩ እንደቻሉ ብቻ ሳይሆን አብሮ ያኖራቸው ጉዳይም ሊመረመር የሚገባው ይመስለኛል)፡፡

ከለቅሶ ሥርዓቶቹ እስከቃል-ግጥም ክወናዎቹ ቀደም ሲል ይፈጸሙ በነበሩትና አሁን እየተፈጸሙ ባሉት መካከል በርካታ ለውጦች መኖራቸውን በገለጻው ክፍል የቀረቡት መረጃዎች አሳይተዋል፡፡ ምን ምን ለውጦች ተካሄዱ ብቻ ሳይሆን፣ ለምን ተካሄዱ? የሚለው ጥያቄ ከዚህ ጥናት ተወልዷል፡፡

ከእነዚህ ከመረጃዎቹ ትንተና ከመነጩት ጥያቄዎች በተጨማሪ፣ የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ የሚያንጸባርቋቸው ማሕበረ-ባሕላዊ አንድምታዎቻቸውም ሆነ ቅርጾቻቸው (በተለይ ኪነጥበባዊ ለዛቸው) አልተመረመረም፡፡ በሙሾ ክወናው እርግዶና በቤተክርስቲያን ወረብ ሽብሸባዎቹ መካከል የጎሉ ተመሳስሎዎችን ታዝቤያለሁ፡፡ በከልካዮችና በተከልካዮች በሚፈጸሙ በእነዚህ ፍጹም የተለያየ ዓላማ ባላቸው ክወናዎች መካከል መመሳሰል እንዴት ሊመጣ ቻለ? ማንኛቸው ከማንኛቸው ምን ወስደው ይሆን? የሚሉ መልስ የሚሹ ጥያቄዎች አቃጭለዋል፡፡ ስለዚህ ፍላጎቱ ያላቸው (ርዕስ ለመምረጥ የተቸገሩ አላልኩም)፣ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስና ክፍተቶቹን ለመሙላት ጥናት ለማካሄድ ቢነሱ፣ የካበተ መረጃ የሚያገኙ መሆናቸውን ሳልጠቁም አላልፍም፡፡

## ዋቢዎች

ሀብታሙ አቃናው። ‹‹ሞተን ተነሳን የሚሉ ሰዎች የሌላ ዓለም ጉዞ ተረኮች።›› ኤም.ኤ ዲማጽ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2003። (ያልታተመ)።

መላከ ሰላም ዳኛቸውና ሌሎችም። ሃይማኖት የለየንን መቃብር አንድ አያደርገንም። አዲስ አበባ፣ ትንሳዔ ዘጉባዔ ማተሚ ቤት፣ 1986።

መልከ ጼዴቅ (አባ)። ትምህርተ ክርስትና 2ኛ መጽሐፍ። አዲስ አባባ፣ ትንሳዔ ማተሚያ ድርጅት፣ 1984።

ሙሉነህ መንግሥቱ። ‹‹ዘይቤያዊ አነጋገሮች በአማርኛ ሥነ ግጥም ውስጥ።›› ቢ.ኤ ዲማጽ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1973። (ያልታተመ)።

መጽሐፈ ግንዘት። አዲስ አበባ፣ ገብረሥላሴ ብርሃኑ ማተሚ ቤት፣ 1997።

ማተቤ አያሌው። ‹‹የአማርኛ ልቅሶና ዘፈን ግጥሞች ከጎንደር ክፍለ ሀገር።›› ቢ.ኤ ዲማጽ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1972። (ያልታተመ)።

ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል። የአባቶች ቅርስ። አዲስ አበባ፣ ነጻነት ማተሚያ ቤት፣ 1943።

----------። የኢትዮጵያ ባሕል ጥናት ቡልጋ። ለቀ.ኃ.ሥ ዩኒቨርሲቲ የጥናት ኢንስቲቲዩት የቀረበ ማስታወሻ፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚ ቤት፣ 1960።

---------። ዝክረ ነገር። አዲስ አበባ፣ ነጻነት ማተሚያ ቤት፣ 1942።

ሞገስ ሚካኤል። ‹‹በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ሥነ ሥርዓት፣ በሥርዓቱ ላይ የሚካሄድ የቀረርቶና የፉከራ ክዋኔ።›› ኤም.ኤ ዲማጽ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2002። (ያልታተመ)።

ሽመልስ አክሊሉ። ‹‹የቋሪት ወረዳ የለቅሶ ሥነሥርዓትና የለቅሶ ግጥሞች ይዘት

ትንተና፡፡›› ቢ.ኤ ዲግሪ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1997፡፡ (ያልታተመ)፡፡

በሪሁን መንግሥቱ፡፡ ‹‹የሙሾ፣ የወየታና የፉከራ ግጥሞች ክዋኔና የይዘት ትንተና በደብረ ታቦር ከተማ፡፡›› ኤም.ኤ ዲግሪ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2004፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ባልከው ቸርነት፡፡ ‹‹የመንዝ የለቅሶ ግጥሞች ጥናት፡፡›› ቢ.ኤ ዲግሪ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1974፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ብርሀኑ መኮንን፡፡ ‹‹የአማርኛ የሙሾ ግጥሞች ጠባይ ይዘትና የዘይቤ አጠቃቀም፡፡›› ኤም.ኤ ዲግሪ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1973፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ተክለጻድቅ መኩሪያ፡፡ <u>የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ</u>፡፡ 5ኛ እትም፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀ. ኃ. ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1965፡፡

ታደሰ መንግሥቱ፡፡ ‹‹የጎጃም የለቅሶ ግጥም፡፡›› ቢ.ኤ ዲግሪ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1963፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ፡፡ <u>በይነ-ዲሲፒሊናዊ የሥነጽሑፍ ንባብ</u>፡፡ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 2001፡፡

ንጉሴ አክሊሉ፡፡ ‹‹ለጀግኖች ለቅሶ የሚደረደሩ ግጥሞች (በምንጃርና ሸንኮራ አካባቢ)፡፡›› ቢ.ኤ ዲግሪ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1974፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፡፡ <u>የለቅሶ ዜማ ግጥም</u>፡፡ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት፣ 1910፡፡

አባይነህ ካሴ፡፡ <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አንደኛ መጽሐፍ</u>፡፡ አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት፣ 1994፡፡

አንተነህ አወቀ፡፡ ‹‹የአማርኛ ሥነቃል፡፡›› <u>የአማራ ሕዝብ ባሕልና ቋንቋ</u>፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባሕልና ቱሪዝም ቢሮ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ

ድርጅት፣ 2001፣ ገጽ፣ 105-140።

ከሳቴ ብርሃን ተሰማ። አዲስ የዐማርኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ

ቤት፣ 1951።

ከበደ ሚካኤል። የቅኔ ውበት። አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፣ 1994።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ። መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ መዝገበ ቃላት ሐዲስ። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ

ማተሚያ ቤት፣ 1948።

ወርቁ ማንደፍሮ። ‹‹በሊቦ ከምከም ወረዳ የለቅሶ ሥነስርዓትና የሙሾ ግጥሞች።›› ኤም.ኤ ዲግሪ፣

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1987። (ያልታተመ)።

ወርቃየሁ አረጋ። ‹‹የአዊ ሕብረተሰብ ሴንቲ (የለቅሶ ሥርዓት) እና የአውኚ ዚንዚምኚ (የሙሾ)
ግጥሞች ይዘት ትንተና።›› ቢ.ኤ ዲግሪ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1995። (ያልታተመ)።

ዋጋው ሀይሉ። ‹‹የአማራ ባሕል ገጽታዎች።›› የአማራ ሕዝብ ባሕልና ቋንቋ፣ በአማራ ህዝብ

ክልላዊ መንግሥት የባሕልና ቱሪዝም ቢሮ፣ ብርሃንና ሠላም ማተሚያ ድርጅት፣ 2001፣

ገጽ፣ 1-104።

ዘሪሁን አስፋው። የሥነጽሑፍ መሰረታውያን። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1992።

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የ2004 ዓ.ም የሕዝብ

ብዛት መረጃ በነጠላና በእድሜ ክፍፍል። ከደቡብ ጎንደር ዞን የተቀናጀ ልማት እቅድ ዋና

ሥራ ሂደት፣ ገንዘብና ኢኮኖሚ መምሪያ፣ 2004።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር። የብሉይና የሀዲስ ኪዳን መጸህፍት። አዲስ አበባ፣

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ተግሳጽ ዘ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፡፡ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን፣1983፡፡

የኢትዮጵ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፡፡ አማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1993፡፡

የኢትዮጵ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፡፡ ክብረ ነገስት ግዕዝና አማርኛ፡፡ ተርጓሚ፣ ስርግው ገላው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣1994፡፡

የደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር የባሕልና ቱሪዝም መምሪያ፡፡ ‹‹የደብረታቦር ከተማ አመሰራረት፡፡›› አካባቢውን ለማስተዋወቅ የቀረበ መረጃ፣ ዓመተ ምህረት የለውም)፣ ያልታተመ፡፡

ደቡብ ጎንደር ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ የተዘጋጀ ዓመታዊ መጽሔት፣ 2002፡፡

ደስታ ተክለወልድ፡፡ ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣1962፡፡

ጌቴ ገላዬ፡፡ ‹‹ከ1983 የመንግሥት ለውጥ በኋላ የምሥራቅ ጎጃም ገበሬዎች የገጠሚቸው ፖለቲካዊ ግጥሞች፡፡›› Ethiopian Studies at the End of the Second Millennium: Proceeding of the XIV$^{th}$ International conference of Ethiopian studies, vol.3. Eds. Baye Yimam et al., Addis Ababa: Addis Ababa University (2002: 1907-1935.

ጌጡ ታደሰ:: ‹‹ክዋኔ በጎንደር ከተማ የለቅሶ ሥነ ሥርዓት::›› ቢ.ኤ ዲግሪ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1989፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ጎርጎርዮስ (አባ):: የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ:: 3ኛ እትም፣ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሐዋርያዊ ድርጅት፣ 1991፡፡

ፈለቀ ታደሰ፡፡ ‹‹እምነት-ነክ ክብረ በዓላት፣ ባህላዊ ክንውኖችና የልማት አንድምታቸው፡፡››

ባሕልና ልማት በኢትዮጵያ፤ በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የውይይት መድረክ ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች። አርታኢ፣ ሺፈራው በቀለ፣ አዲ አበባ፣ ኤዲፐስ አሳታሚ፣ 2004፣ ገጽ፣139-158።

ፈቃደ አዘዘ። ሰሚ ያጡ ድምጾች። አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት፣ 1996።

-----------። ‹‹አፋዊ ኪነተ ቃል።›› የኢትዮጵያ ቋንዎችና ሥነጽሑፍ መጽሔት። ቁጥር 2፣ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 1984።

-----------። የሥነ ቃል መምሪያ። አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ **1991**።

ፍትሀ ነገሥት ንባብና ትርጓሜው። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሠላም ማተሚያ ቤት፣ 1958።

Abbink, Jon. "The Final Rite: Burial Among the Me'en of South-West Ethiopia." Procedings of The National Confrence of Ethiopian Studies. Addis Ababa: Addis Ababa University (1990): 65-76.

Aborampah, Osei-Mensah. "Women's Roles in the Mourning Rituals of the Akan of Ghana." Ethnology, Vol. 38, No. 3 (1999 ): 257-271. 28 July 2011 <http://www.jstor.org/stable/3773817>.

Aklilu, Habte. "Harer Funeral Custom." Addis Ababa University Ethnological Society Bulletin Vol. I, No. 2 (2002): 16-24.

Alembi, Ezikiel. "The Construction of the Abanyole Perceptions on Death Through Oral Funeral Poetry." Doctoral Dissertation defended at the University of Helsinki, Finland 2002, 29 October 2012, http//ethesis/helsinki. fi/julkaisut/hum/kultt/ vk/ alembi/theconst.pdf.

Andargachew, Tesfaye. "The Funeral Customs of the Kottu of Harar." Addis Ababa University Ethnological Society Bulletin No. 7 (2002): 216-219.

Babalola, S.A. The Content and Form of Yoruba Ijala. London: Oxford University Press, 1966.

Bamia, Aida Adib. The Graying of the Raven: Cultural and Sociopoletical Significance of Algerian Folk Poetry. Egypt: The American University in Cairo Press, 2001.

Bauman, Richard. Ed., Folklore, Cultural Performances, and Popular Entertainments. New York: Oxford University press, 1992.

................ Story, Performance, and Event: Contextual Studies of Oral Narrative. Cambridge: Cambridge University Press, 1986.

Ben-Amos, Dan. "Toward a Definition of Folklore in Context." In Toward New Perspectives in Folklore, ed. Anlerico Paredes and Richard Bauman, Austin: University of Texas Press, 1972: 3-15.

Bernard, Russell H. Research Methods in Anthropology: Quantitative and Qualitative Approachs 4th ed. Lanhum: AltaMira Press, 2006.

Berehanu Gebeyehu. "mušo as a socio-political Discourse among the Amhara" In Baye Yimam, et al (eds). Ethiopian Studies at the End of the Second Millennium: Proceeding of the XIV$^{th}$ International conference of Ethiopian studies. Addis Ababa University. Addis Ababa, vol.3, (2002): 1907-1935.

Bloch, Maurice. "Introduction: Death and the Concept of a Person." eds., S.Cedrroth, C. Corlin, and J. Lindstrom. On the Meaning of Death: Essays on Mortuary Rituals and EschatologicalBeliefs. Stockholm: Acta Universities, 1988: 9-11.

Brookman-Amissah, Joseph. "Akan Proverbs about Death." Anthropos. Bd. 81, H. 1./3." (1986): 75-85. 28 July 2011 <http://www.jstor.org/stable/40462026>.

Bryman, Alan. ed., Ethnography. Vol.I, New Delhi: Sage Publication, 2001.

Carr, Deborah and Sara M. Moorman ."Social Relations and Aging." Handbook of Sociology of Aging. Eds.Richard A. Settersten, Jr. Jacqueline L. Angel. New York: Springer Science+Business Media, LLC, 2011:145-159.

Ca´tedra, Marı´a. "Kinds of Death and the House." Death, Mourning, and Burial: A Cross-Cultural Reader. ed., Antonius C. G. M. Robben. Blackwell Publishing Ltd., 2008: 77-90.

Cederroth, S. "pouring water and Eating Food: On the Symbolism of Death in a Sasak Community on Lombok, Indonesia." On the Meaning of Death: Essays on Mortuary Rituals and Eschatological Beliefs. eds., Corlin C. S. Cedrroth and J. Lindstrom. Stockholm: Acta Universities, 1988: 39-62.

Cohen, Luis, Lawrence Manion, and Keith Morrison.eds., Research Methods in Education. Six ed. London: Roteledge Publication, 2007.

Creswell, John W. Qualitiative Inquery and Researcg Design: Chossing Among Five Approachs. London: Sage Pubications , 2002.

Daniel, Kasomo. "An analysis of the rites of passage and their relation to christianity." International Journal of Sociology and Anthropology Vol. 1(8) (December,2009): 156-166. 21 Feberuary 2014 <http://www.academicjournals.org/ijsa>.

Davies, Charlotte Aull. Reflexive Ethnpgraphy: a Guide to Researching Selves and Others. London: Routledge, 1999.

Denscombe, Martyn. The Good Research Guide for Small-Scale Social Research Projects 3rd Ed. England: Open University Press, 2007.

Dorson, Richard M. Folklore and Folklife: An Introduction. Chikago: the University of Chikago, 1972.

Falk, Catherine. "'If You Have Good Knowledge, Close It Well Tight':Concealed and Framed Meaning in the Funeral Music of the Hmong qeej." British Journal of Ethnomusicology, Vol. 12, No. 2 (2003):1-33. 04 September 2012 <http://www.jstor.org/stable/30030310>.

—. "Hmong Instructions to the Dead:What the Mouth Organ Qeej Says (Part One)." Asian Folklore Studies, Vol. 63, No. 1 (2004):1-29. 04 September 2012 <http://www.jstor.org/stable/30030335>.

Fasika Belete. "The Death Customs Among the Amharas of Shewa." Addis Ababa University Ethnological Society Bulletin. No. 1, Vol. 1 (1953):204-211.

Fekade, Azeze. "The State of Oral literature Research in Ethiopia: Retrospect and Prospect." Journal of Ethiopian Studies. (2001): 43-86.

Finnegan, Ruth. Oral Literature in Africa. Nairobi: Oxford University Press, 1970.

------. Oral Poetry: its Nature, Significance and Social Context, Cambridge: Cambridge University Press, 1977.

-------. Oral Traditions and Verbal Arts: A Guide to Research Practices. London: Routledge, 1992.

Fishbane, Simcha. "Jewish Mourning Rites - a process of Resocialization. "Anthropologica. Vol. 31, No. 1 (1989):65-84. 10 August 2011 <http://www.jstor.org/stable/25605529>.

Geest, Sjaak van der. "Between Death and Funeral: Mortuaries and the Exploitation of

Liminality in Kwahu, Ghana. "Africa: Journal of the International African Institute, Vol. 76 No. 4 (2006):485-501. 18 March 2011 <http://www.jstor.org/stable/40027295>.

Gennep, Arnold Van. The Rites of Passgae. London: Houtledge & Kegan Paul, (1960 (1908).

Given, Lasa M. The Sage Encyclopedia of Qualitative Research Methods. London: Sage Publications, Inc., 2008.

Goldbart, Juliet, and David Hustler. "Ethnography." Research Methodsin the Social Sciens. Eds. Bridget Somekh and Cathy Lewin. London: Sage Publication, 2005: 16-23.

Golden, Clara, and Deborah Sabbagh. "Reflecting Upon Etic and Emic Perspectives on Distributive Justice." Springer Science+Business Media. (2007): pp. 372-587.

Goody, Jack. "Death and the Interpretation of Culture: A Bibliographic Overview." American Quarterly, Vol. 26, No. 5, Special Issue: Death in America (Dec, 1974): 448-455. 11 April 2011 <http://www.jstor.org/stable/2711884>.

Gufler, Herman. ""Crying the Death." Rituals of Death among the Yamba (Cameroon)." Anthropos. Bd. 95, H. 2 (2000):349-36. 28 July 2011 <http://www.jstor.org/stable/40465946>.

Hammersley, Martyn, and Paul Atkinson. Ethnography: Principles in practice third ed., New York: Taylor & Francis e-Library, 2007.

Hampton, Barbara L. "Music and Ritual Symbolism in the Ga Funeral." Yearbook for Traditional Music, Vol. 14 (1982): 75-1105.

Helfrich, Hede. "Beyond the Dilemma of Cross-Cultural Psychology: Resolving the Tension between Etic and Emic Approaches." Culture & Psychology vol. 5 No. 2 (1999): 131–153.

Hill, Jeff, and Peggy Daniels. Life Events and Rites of Passage: the Customs and Symbols of Major Life-Cycle Milestones, Including,Cultural Secular, and Religious Traditions Observed in the United States. Omnigraphics, Inc., 2008.

Hoare, Karen J. "Using an emic and etic ethnographic technique in a grounded theory study of information use by practice nurses in New Zealand." Journal of Research in Nursing 1–12 (2012):1-12.

Hustler, David and Juliet Goldbart. "Ethnography. " In Research methods in the Social Sciences. Eds., Briget Somekh and Cathy Leein. London: SAGE Publications Ltd, 2005:16-23.

Jaccard, James, and Jacob Jacoby . Theory Construction and Model-Building Skills: a Practical Guide for Social Scientists. New York: The Gilford Press, 2010.

Jackson, Bruce. Fieldwork. Urbana: University of Illions Press, 1986.

Kapchan, Deborah A. "Common Ground: Keywords for the Study of Expressive Culture." Journal of American Folklore, Vol. 108, No. 430 (1995): 479-508.

Krüger, Simone. Ethnography in the Performing Arts: A Student Guide. Liverpool: The higher Palantine Education Dance, Drama Academy and Music. 2008.

Laungani, Pittun, and Bill Young. "Conclusions I: Implications for practice and policy." Death and Bereavement Across Cultures. Eds., Colin Murray Parkes, Pittu Laungani and Bill Young. London: Routledge, 1997: 218-232.

Levine, Ellen. "Jewish views and customs on death." Death and Bereavement Across Cultures. eds., Parkes, Colin M., Pittu Laungani, and Bill Young London: Taylor & Francis e-Library, 2004: 98-130.

Lloyd-Evans, Sally. "Focus Group." Doing development Research. Eds., Vandana Desai, and Robert B. Potter. London: Sage Publication, 2006: 153-162.

Luper, Steven. The Philosophy of Death. New York: Cambridge University Press, 2009.

Mallon, Berenda. Daying, Death and Grief. Los Angeles: Sage, 2008.

Marczyk, Geoffrey, David De Matteo and David Festinger. Essentials of Research Design and Methodology. eds. Alan S. Kaufman, and Nadeen L. Kaufman. New Jersey: John Wiley & Sons, Inc., 2005.

Marshall, Douglas A. "Behavior, Belonging, and Belief: A Theory of Ritual Practice." Sociological Theory, Vol. 20, No. 3. (Nov., 2002): 360-380. 28 July 2011 <http://www.jstor.org/stable/3108616>.

Mareye Tefera. "A Thematic Analysis of the Oral Poetry of the People of Fogra." MA thesis. Addis Ababa University, 2008. (Unpublished).

Meeks, G. Blair. Standing in the Circle of Grief: Prayers and Liturgies for Death and Dying. Nashville: Abingdon Press, 2002.

Megebaru Eysayas. "A Thematic Analysis of Funeral Dirges in West Gojajam." MA thesis. Addis Ababa University, (2009). (unpublished)

Moore, Gerald. "The Image of Death In African Poetry." Journal of the International African Institute. Vol. 38 No., 1. (Jan 1968):57-70. 24 March 2011 < http://www.jstor.org/stable/1157339>.

Morris, Ian. Death Ritual and Social Structure in Classical Antiquity 3rd ed. New York: Cambridge University Press, 1992.

Murchison, M. Julian. Ethnography Esseentials: Designing, Conductinig, and Presenting Your Research. San Francisco: Jossey-Bass, 2010.

Nega, Tessema. "The Death Custom in the Provience of Tigray." Addis Ababa University Ethnological Society Bulletin, No. 5 (2002):108-115.

Nketia, J. H. Funeral Dirges of the Akan People. James Townsend and Sons Ltd, 1955.

Ogede, Ode S. "Context, Form and Poetic Expression in Igede Funeral Dirges." Africa: Journal of the International African Institute, Vol. 65, No. 1 (1995): 79-96. 04 September 2012 < http://www.jstor.org/stable/1160908>.

Okpewho, Isiodore. African Oral Literature: Background, Character and Continuty. Bloomington: Indiana University Press, 1992.

Pankhurst, Richard. "The History of Dabra Tabor (Ethiopia)." Bulletin of the School of Oriental and African Studies, University of London, Vol. 40, No. 2 (1977): 235-236.

Parkes, M. Colin, Pittu Laungani and Bill Young. Eds., Death and Bereavment Across Cultures. New York: Routledge, 1997.

Parkes, M. Colin. "Conclusions II: Attachments and losses in cross-cultural perspective." Death and Bereavement Across Cultures. Eds. Colin Murray Parkes, Pittu Laungani and Bill Young. London: Rotlage, 1997: 233- 255.

Pojman, Louis P. Life and Death: Grappling with the Moral Dilemmias of Our Time. London: Jones and Bartlett Publishers , 1992.

Pritchard, Maureen. "Creativity and Sorrow in Kyrgyzstan." Journal of Folklore Research, Vol. 48, No. 2 ( May/August 2011): 167-196. 29 December 2011.

<http://www.jstor.org/stable/10.2979/jfolkrese.48.2.167>.

Rodabough, Tillman. "The Evolution of the Legal Defenition of Death". Handboo of Death and Dying. ed. Clifton D. Byrant. London: Sage Publications Inc, 2003: 284-291.

Roth, Andrew L. ""Men Wearing Masks": Issues of Description in the Analysis of Ritual." Sociological Theory, Vol. 13, No. 3 (Nov., 1995): 301-327. 27 Auguest 2012 http://www.jstor.org/stable/223300.

Samuel Adal. "The Development of Modern Amharic Poetry (1950-1980)". MA Thesis. Addis Ababa University, 1994. (unpublished).

Sanka Confidence, B.A "The Sisaala Dirge: A Critical Analysis." Doctoral Dissertation defended at the University of Kwame Nkrumah, 2010. 11 January 2011 <https://www.google.com/>.

Savage, Jan. "Ethnographic Evidence:The Value of Applied Ethnography in Healthcare." Journal of Research in Nursing (2006): 383-393. 16 February 2012 < http://jrn.sagepub.com/content/11/5/383>.

Sims, Martha C., and Martine Stephens. Living Folklore: An Introduction to the Study of People and Their Tradition. Logan: Utah State University Press, 2005.

Staal, Frits. "The Meaninglessness of Ritual." Numen, Vol. 26, Fasc. 1 (Jun., 1979): 2-22. 01 December 2011 <http://www.jstor.org/stable/3269623>.

Stuart, Kevin and Hu Jun. "Death and Funerals among the Minhe Tu (Monguor)." Asian Folklore Studies, Vol. 51, No. 1 (1992): 67-87. 10 February 2012 <http://www.jstor.org/stable/1178422>.

Tavakoli, Hossein. A Dictionary of Research Methodology and Statistics in Applied Linguistics. Tehran: Rahnama Press, 2012.

The 2007 Population and Housing Census of Ethiopia Result for Amhara Region. Federal Democratic Republic of Ethiopia Population Census Commission Central Stastical Agency. Addis Ababa, 2007.

Titon, Jeff Todd. "Common Ground: Common Ground Keywords for the Study o Expressive Culture." The Journal of American Folklore. (1995): 432-448. 21 May 2010 <http://links.jstor.org/sici?>.

Toher, Mark. "Euripides' "Supplices" and the Social Function of Funeral Ritual." Hermes, 129. Bd., H. 3 (2001 ): 332-343. 16 March 2012 <http://www.jstor.org/stable/4477442>.

Tolbert, Elizabeth. "Women Cry with Words: Symbolization of Affect in the Karelian Lament." Yearbook for Traditional Music, Vol. 22 (1990): 80-105. 21 September 2012 <http://www.jstor.org/stable/767933>.

Tolken, Baree. The Dynamics of Folklore. Logon: Utah State University Press, 1996.

Untiedt, Kenneth L. "The Lore of Death." Death Lore:Texsas Rituals, Superstitions, and Legends of the hereafter. Ed., Kenneth L. Untiedt.Texas: University of North Texas Press, 2008: 1-14.

Vernon, Glenn M. Sociology of Death: An Analysis of Death Related Behavior. New York: The Ronald Press Company, 1970.

Whitehead, Tony L. Basic Classical Ethnographic Research Methods. Maryland: July, 2005.

Wilce, James M. Craying Shame: Metaculture, Modernity, and the Exaggeerated Death of

Lament. A John Wiley & Sons, Ltd., Publication, 2009.

Young, Bill and Danai Papadatou. "Childhood death and bereavement across cultures ." Death and BereavementAcros Cultures. Eds. Bill Young, Colin Murray Parkes, and Pittu Laungani. London: Taylor & Francis e-Library, 2004: 190-205.

Yoder, Lonnie. "The Funeral Meal: A Significant Funerary Ritual." Journal of Religion and Health Vol. 25, No. 2 (1986): 149-160. 10 August 2011 <http://www.jstor.org/stable/27505870>.

# የአባሪዎች ማውጫ


አባሪ 1 ........ 1

የመረጃ ምደባ ........ 1

ሀ.የደብረታቦር ከተማና አካባቢው ታሪካዊ ዳራ ........ 1

ለ. የሞት ምንነት ........ 8

1. የቀብር ሥርዓትና የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ክወና ........ 15

1.1. የቀብር ሥርዓት ክወና ........ 15

1.1. ሀ. ከቀብር ሥርዐት ጋር የተያያዙ ልማዶች ........ 15

1.1.ለ. የአቀባበር አይነቶች ........ 16

1.1.ሐ. የሕጻናት አቀባበር ........ 17

1.1.መ. ለቅሶ አለመድረስ ........ 18

1.1.1. በዕለት ለቅሶ እስከ ቀብር ድረስ የሚፈጸሙ ሀይማኖታዊና ዓለማዊ ሥርዓቶች ........ 21

1.1.1.1. በዕለት ለቅሶ እስከቀብር ድረስ የሚከወኑ ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች ክወና ........ 21

1.1.1.1.1. ግንዘትና ከፈን ........ 21

1.1.1.1.2. የፍትሀት ጸሎት ........ 30

1.1.1.2. በዕለት ለቅሶ አስከቀብር ድረስ የሚከናወኑ ዓለማዊ ሥርዓቶች ክወና ........ 39

1.1.1.2.1. የሟች ዜና ረፍት ይፋ አደራረግ ሥርዓት ........ 39

1.1.1.2.2.የሬሳ አወጣጥ ........ 41

1.1.2. በቀጠሮ ለቅሶ እስከቀብር ድረስ የሚከናወኑ ሀይማኖታዊና ዓለማዊ ሥርዓቶች ........ 43

1.1.2.1. በቀጠሮ ለቅሶ እስከቀብር ድረስ የሚከናወኑ ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች ክወና ........ 43

1.1.2.2. በቀጠሮ ለቅሶ እስከቀብር ድረስ የሚከናወኑ ዓለማዊ ሥርዓቶች ........ 44

1.1.2.3.በምሥል የሚለቀስ የቀጠሮ ለቅሶ ........ 51

1.1.3. በመርዶ ለቅሶ የሚከናወኑ ሀይማኖታዊና ዓለማዊ ሥርዓቶች ክወና ........ 53

1.1.3.1. በመርዶ ለቅሶ የሚከናወኑ ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች ........ 53

1.1.3.2. በመርዶ ለቅሶ የሚከናወኑ ዓለማዊ ሥርዓቶች ክወና ........ 54

1.2. የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ክወና ........ 57

1.2.1. የተጠኚው ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ድረሳ ........ 57

1.2.2.የተጠኚው ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች አካባቢያዊ ምደባ ........ 66

1.2.2.1. ወየታ ........ 66

1.2.2.2. ሙሾ ........................................................ 68

1.2.2.3. ቀረርቶና ፉከራ ........................................................ 73

1.2.3. የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ክወና ........................................................ 74

1.2.3.1. የወየታ ክወና ........................................................ 74

1.2.3.2. የሙሾ ክወና ........................................................ 75

1.2.3.3. የቀረርቶና ፉከራ ክወና ........................................................ 78

1.3. የሀዘን አገላለጽ ልማድ ........................................................ 101

1.3.1. በአካል ላይ የሚፈጸሙ ........................................................ 103

1.3.2. በአለባበስ የሚገለጹ የሀዘን ልማዶች ........................................................ 105

1.3.3. ሌሎች የሀዘን መግለጫ ልማዶች ........................................................ 108

1.4.የመታሰቢያ ሥርዓቶች ........................................................ 110

1.4.1. የሥንብት ሥርዓት ........................................................ 110

1.4.2. የእዝን አቀራረብ ሥርዓት ........................................................ 112

1.4.3. የቀናቀንና የተዝካር ሥርዓት ........................................................ 113

1.4.3.1. ከሰልስት እስከሙት ዓመታት ያሉት የቃናቀን ሥርዓቶች ........................................................ 113

1.4.3.2. የተዝካር ሥርዓት ........................................................ 118

1.4.3.2.1.የቁም ተዝካር ........................................................ 118

1.4.3.2.2. ከሞት በኋላ የሚወጣ ተዝካር ........................................................ 120

1.4.4. ሞት በሥጋ ዝምድናና በማሕበራዊ ትስስር ላይ የሚስከትለው ውጤት የተገለጸባቸው ... 122

ቃል-ግጥሞች ........................................................ 122

1.4.4.1. የእናት ሞት በልጆች ላይ ........................................................ 122

1.4.4.2. የአባት ሞት በልጆች ላይ ........................................................ 125

1.4.4.3. የልጅ ሞት በወላጆች ላይ ........................................................ 125

1.4.4.4.የእህት ሞት በወንድምና እህት ላይ ........................................................ 126

**1.4.4.5.**የወንድም ሞት በእህትና ወንድም ላይ ........................................................ 127

1.4.4.6.የሽማግሌ ሞት በማሕበረሰቡ ላይ ........................................................ 128

1.4.4.7.የጀግና ሞት በማሕበረሰቡ ላይ ........................................................ 128

1. እንዴት ጀግና ይሙት በእንቢያ የሚደፋ፣ ........................................................ 128

**5.** በለቅሶ ቃል-ግጥሞች ዘር የተመደቡ ተጨማሪ አባሪዎች ........................................................ 129

**5.1.**ወየታ የወል ........................................................ 129

5.2. የሙሾ ቃል-ግጥሞች ........................................................................ 143
5.2.1. ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ ዋየ ........................................................................ 143
5.2.2. ዋየ ዋይ ወየሁ ........................................................................ 145
5.2.3. አወየሁ ዋይ ዋይ /ወየሁ ........................................................................ 146
5.2.4.አየ/ዋ ተለየነ/ አየ ያለው ማነው ........................................................................ 147
5.3. ቀረርቶና ፉከራ ........................................................................ 151
5.3. 1. ቀረርቶ ........................................................................ 151
5.3.2. ፉከራ ........................................................................ 154
5.3.2.1. ፉከራ ለጀግና ........................................................................ 154
5.3.2.2. ለተሚጋች ........................................................................ 160
5.3.2.3. ለገበሬ ........................................................................ 165
አባሪ 2 ........................................................................ 172
የመረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል ........................................................................ 172
አባሪ 3 ........................................................................ 175
መረጃዎቹ የተሰበሰቡባቸው የለቅሶ ሥርዓቶች ........................................................................ 175
አባሪ 4 ........................................................................ 176
የውይይት መነሻ ጥያቄዎች ........................................................................ 176
አባሪ 5 ........................................................................ 181
ተጨማሪ ፎቶዎች ........................................................................ 181

## አባሪ 1

## የመረጃ ምደባ

**ሀ.የደብረታቦር ከተማና አካባቢው ታሪካዊ ዳራ**

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ ግሩም ሀይሉ (አባ.2፣ቁ.6)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 5/09/2004

*ጥያቄ፣ ስለ ደብረታቦር ከተማ አቆራቆር ቢነግሩኝ*

1. የደብረታቦር ከተማ የተቆረቆችው በአጼ ሰይፈ አርዕድ ዘመነ መንግሥት (በ1327) ነው፡፡ ከተማዋ 667 ዓመት ሆኗታል፡፡ ደብረታቦር የሚለውን ስም የሰጡት ግን አፄ (ሳልሳዊ) ገብረ መስቀል ናቸው፡፡ ከጣና መጥተው ተራራው ላይ 3 ቀን አድረው ‹‹ይህ እየሩሳሌም ያለውን የደብረ ታቦር ተራራ ይመስላል›› ብለው ስያሜውን ሰጥተውታል፡፡ ከጎንደር ይቀድማል፡፡ ከዚያ ወደ ዙራንባ ሄዱ፡፡ ነገስታት እየተፈራረቁባት ቆይተዋል፡፡ አሁን ወደ ኋላ አጼ ቴዎድሮስ፣ ከሳቸው ቀጥሎ አጼ ዮሐንስ ነግሰውበታል፡፡

ጥያቄ፣ *ከተማው መጀመሪያ የተቆረቆረው የት አካባቢ ነበር?*

2. እየሱስ ነው የተቆረቆረ፡፡ ከዚያ ወርዶ በራስ ጉግሳ ጊዜ ሥላሴ አካባቢ ተመሰረተ፡፡ ከዚያ አውራጃ ሆኖ ራስ ካሳ ተሾሙ፡፡ ልጃቸውን ተክተው ሄዱ፡፡ በኋላ ጠላት መጣ፡፡ ጠላት ሲወጣ እንደገና በአውራጃ ደረጃ ተቋቋመ፡፡ ደርግ ሲገባም አውራጃ እንደሆነ ቀጥሎ በ1980 ዓ.ም ደቡብ ጎንደር ዞን ተባለ፡፡

*ጥያቄ፣ የከተማ የዱሮ ስም ማን ይባላል?*

‹‹ጁራ›› የሚሉ አሉ፡፡ ይኸ ከዚያው እየሱስ ግርጌ በስተሰሜን ያለ ቦታ መጠሪያ እንጂ የከተማው መጠሪያ አይደለም፡፡ የከተማው ስም ሳልሳዊ ገብረ መስቀል ያወጡለት ጥንትም ደብረታቦር ነው፡፡

*ጥያቄ፣ ከተማውን ራስ ጉግሳ መሰረቱት የሚል ነገር አለ እንዴት ያዩታል?*

3. ራስ ጉግሳ የንግስት ዘውዲቱ ባል ለገዥነት መጡ እንጂ ከተማውን አልቆረቆሩም፡፡ የመጀመሪያው ጉግሳ (መረሳ) እዚህ ነግሰዋል፡፡ ሁለተኛው ራስ ጉግሳ ወሌ ከአጼ ኃይለ ሥላሴ ጦር ጋር እኔ እነግስ እኔ እነግስ አንችም ላይ ተዋግተው ሞተዋል፡፡ አፄ

ቴዎድሮስ ከጎንደር መጥተው ጭርቆስ ላይ ካረፉ በኋላ ወደ መድኃኒያለም መጥተው ከዚያ ቤተ መንግስታቸውን በመቆርቆር በዘመናዊ መልክ ሲያስተዳድሩ ቆይተዋል፡፡ መድኃኒያለምን ካስሰሩ በኋላ ከግርጌው ቤተ መንግስታቸውን ለመስራት የሰበሰቡት ድንጋይ ዛሬም አለ፡፡ አንዳንዶች ‹‹ወደ መቅደላ ሲሄዱ የተከተላቸውን ሰራዊት ለማወቅ ያስቀመጡት ነው›› ይላሉ፤ ይህ ልክ አይደለም፡፡ ዘመቻ ሲሄዱ እያንዳንዱ ሰራዊት ድንጋይ እንዲያስቀምጥና ሲመለሱ እንዲያነሳና ሌላ ቦታ ላይ እንዲያስቀምጥ ያደረጉት ክምር ድንጋይ ላይ ነው፡፡ ከዚያ ሳይነሳ የቀረውን ድንጋይ በመቁጠር የሞተ ጦራቸውን ተረድተውበታል፡፡

4. ከአጼ ቴዎድሮስ ተከትለው አጼ ዮሐንስ ሲነግሱ ቤተ መንግስታቸውን ሰመራ ላይ መስርተው አስተዳድረዋል፡፡ ከዚያ በኋላ መንግስቱ ከዚህ ተነስቶ ወደ ሸዋ ሄዷል፡፡ አልነገሱበትም እንጂ አጼ ሱስንዮስም በዚህ ሀገር መጥተዋል፡፡

5. የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ሲወድቅ አዲስ አበባ ላይ ያለውን ንቅናቄ የተመለከተው ግራዝማች አድማሱ በላይ፣ ያካባቢውን በተለይ የጋይንትን ገበሬ በማንቀሳቀስ በደርግ ሰራዊት ላይ ጦርነት ከፍቶ ጊዜያዊ ድል አግኝቶ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ የነበረው አውራጃ ገዥ መቶ አለቃ ጋሻው ይባል ነበር፡፡ ከጎንደር የመጣ ጦር የበላይነቱን ወስዶ አሸነፈው፡፡ ይኸ ጦርነት ለከተማው ውድቀት ምክንያት ሆኗል፡፡ ለገበሬው ጦር ምግብ በማቅረብ፣ በኋላ የደርግ ጦር ሲገባ አንዳንድ ሰዎችን በመጥፎ አይን በማየት፣ ጦርነቱ ስለተካሄደበት ሀብት ንብረት በመውደሙ ጉዳት አስከትሏል፡፡

6. ከደርግም በኋላ ኢሕአፓዎች በመና መቀጠዋ አኛ አድርገው መጥተው ውጊያ በመክፈት ከተማዋን ተቆጣጥረው ነበር፡፡ ደርግ ሀይል አሰባስቦ በመምጣቱ እነሱ ወደኋላ ወደክምር ድንጋይ አፈገፈጉ፡፡ እነደገና ሀይላቸውን አጠናክረው መጥተው ሰራዊቱን በመደምሰስ ከተማውን ያዙ ወደታችም ወረዱ፡፡ ከዚያ በኋላ ደርግ መመለስ አልቻለም፡፡ በዚሁ ቀጥለው ባሕርዳርንና በኋላም ሀገሪቱን መቆጣጠር ቻሉ፡፡ ይኸው ነው ታሪኩ፡፡

*ጥያቄ፣ የማሕበረሰቡ ግንኙነት በሀዘንና በደስታ ምን ይመስላል?*

7. ማህበረሰቡ በሀዘን በደስታው አብሮ ይበላል፤ ይጠጣል፡፡ የዚህ ሀገር ለቅሶ ከሌሎቹ የተለየ ነው፡፡ የሚለየው ሙሾ የሚባል አለ፡፡ እሱ በጣም ያስደስታል፡፡ ሰዎቹ ሰባትም ስምንትም ዘጠኝ አስር ይሆኑና በሁለት ጎራ ይከፈላሉ፡፡ ከዚያ የሚገጥሙት ግጥም አለ፡፡ ውዝወዘዜም አለው እሱን በአንድ ላይ እያሉ እሱን ሲጨርሱ ደግሞ ሌሎቹ ያቀርባሉ፡፡ እንዲህ እያለ ይቀጥላል፡፡ ሲጨርሱ ተለያየነን ይሉና ወደ ቀብር ይሄዳል፡፡ ካህናቱ ባርከው ይቀበርና ወደ ሟች ቤት ይኬዳል፡፡ በአንዳንድ አገር ጥሬ ነው፡፡ ከዚህ ግን እዝኑ እንጀራ ነው፡፡

*ጥያቄ፣ በዱሮውና በአሁኑ የለቅሶ ስርዓት መካከል ምን ምን ልዩነቶችን ታዝበዋል?*

8. እኔ ሳውቀው ጀምሮ ልዩነት የለውም፡፡ ከጥንት የነበረው አሁንም አለ፡፡ ደብረታቦርን ኢህአዴግ ተቆጣጥሮት በነበረ ጊዜ ወደ ባህር ዳር የሸሹት ሰዎች ሲያለቅሱ ሰው እየወጣ ያያቸው ነበር፡፡ ለቅሶ ልዩ ስለ ነበር ይህኑ ለማየት ሰዎች ይሰበሰቡ ነበር፡፡

*ጥያቄ፣ ሙሾ የሚወረድላቸው፣ ቀረርቶ የሚቅራራላቸውና የሚፈከርላቸው እነማን ናቸው?*

9. በጠላት ወረራ ጊዜ ጀግንነት ለፈጸሙ ይደረጋል፡፡ በቅሎ ቀሚስ ለብሶ ይዘጋጃል፡፡ ፈካሪ መሳሪያ ይዞ ከዚያ ላይ ይወጣና ቁጭ ብድግ እያለ ይፎክራል፡፡ ይኸ የሚደረግላቸው ለጀግኖችና ባስተዳደርም ለታወቁ ሰዎች ነው፡፡ ለተራው ግን ሲፎከር ‹‹ከዚህ ገዳይ›› ስለሚባልና ሟች ያንን ስለማያሟላ ማፈር ይመጣል፡፡ ሙሾ ዝም ብሎ ሊወጣለት ይችላል፡፡ ታዋቂ ከሆነ ባንዲራም ይያዝለታል፡፡

*ጥያቄ፣ የሙሾ፣ ቀረርቶና ፉከራ ለቋሚና ለሟች ምን ጥቅም ይኖረዋል?*

10. መችም ሞት አይቀርም፡፡ አንድ ሰው ሙሾ ሲወረድለት ታሪኩ ይታወቃል፡፡ እንደገናም ባህል ነው፡፡ ጥቅሙ ባሕሉን ማስተላለፉ ነው፡፡ መሰናበቻም ስለሆነ ጥሩ ነው፡፡

*ጥያቄ፣ ጥሩ ፎካሪ የሚባሉት እንዴት አይነት ናቸው?*

11. ጥሩ የሚባሉት በድምጻቸው ነው፡፡ አንዳንዶች አሉ በግጥማቸው ጥሩ ናቸው፡፡ አንዳንዶች ተገዝተው መጥተው ይፎክራሉ፡፡ መተዳደሪያቸው ነው፡፡

*ጥያቄ፣ ጀግና ፎካሪ የሚባል የሚያውቁት አለ?*

12. ታክለ ኀበዝ ነው፡፡ በየወረዳው እየተጠራ ይሄዳል፡፡ የሟቹን ታሪክ አጋጥሞ ከፍ አድርጎ ያቀርበዋል፡፡ በጣም ከፍ አድርጎ ስለሚያቀርበው ምግብ ይበላል፣ ይጠጣል፣ ገንዘብ ይከፈለዋል፡፡ ሲንደቀደቅ ነው የሚውል፡፡ በዚህ እሱ የታወቀ ነው፡፡

*ጥያቄ፣ የሟች ዜና ረፍት የሚነገረው እንዴት ነው?*

13. ቀደም ሲል ይለፈፋል፡፡ የሟች መኖሪያና መቀበሪያ ቦታ ተነግሮ ጥሩንባ እየተነፋ ይለፈፋል፡፡ እድር በቅርብ ነው የመጣ፡፡ ራቅ ያለ ቦታ ላለ ሰው ደግሞ ይላካል፡፡ አሁን የሚከፈለው ለፋፊ አለ፡፡

*ጥያቄ፣ ስንት አይነት ለቅሶ አለ?*

14. የእለት ለቅሶ አለ፡፡ ሌላው የመርዶ ለቅሶ ነው፡፡ የመርዶ ለቅሶ ከቤትም ከቤተክርስቲያንም ሊካሄድ ይችላል፡፡ ግቢው የሚጠበው ከሆነ ከቤተክርስቲያን ተገኝቶ ሰውን እየተቀበለ ያሰናብታል፡፡ ሙሾና ፉከራ ግን የለውም፡፡ በከተማው የለም እንጅ በገጠሩ የቀጠሮ ለቅሶም አለ፡፡

*ጥያቄ፣ ለቅሶ ደራሽና ሀዘንተኞች ትከሻ ለተከሻ የሚገናኙትስ ለምንድን ነው?*

15. ይኸ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከጎንደር መጣ የሚባል ባህል ነው፡፡ በፊት አልነበረም፡፡ የዱሮው ሲገናኙ ፊቱን በእጁ ነካ ነካ ነበር የሚያደርግ፡፡ይኸ ያሁኑ ከሀያና ከአስራ አምስት ዓመት ወዲህ የመጣ ነው፡፡ አሁን እንዲያውም በለቅሶ አስተባባሪዎችና በካህናት እየተከለከለ ነው፡፡ ሀዘንተኛው እያንዳንዱ ሰው በመጣና በተገናኘው ቁጥር እንደአዲስ እያለቀሰ ስለሚቀበል አድካሚ በመሆኑ ጎጅ ሆኖ በመገኘቱ እየቀረ ነው፡፡

**የመረጃ አቀባይ** ***ሥም***፣ *ቀኝ ጌታ መዓዛ ንጋቱ* (አባ.2፣ቁ.5)

***ቃለመጠይቅ*** **የተደረገበት ቀን**፣ እ.አ.አ. 6/09/2004

*ጥያቄ፣ ደብረ ታቦር ከተማ መቼና በማን ተቆረቆረ?*

1. ስለ ደብረታቦር ከተማ አቆራቆር ሁለት አይነት መረጃዎችን አንብቤያለሁ፡፡ ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ በ1332 ተቆረቆረች ሲሉ፣ ሊቀ ጠበብት አክሊሉ ብርሀን በ1327 ተቆረቆረች ይላሉ፡፡ የአምደ ጽዮን ልጅ አጼ ሰይፈ አርዕድ በ1336 ዓ.ም ኢየሱስ ተራራ ላይ ከነሰራዊታቸው ሰፈሩ፡፡ ይህ ከብራና መጻሕፍት ላይ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ መጀመሪያ

ከሰሜን ሸዋ እንደመጡ ሰራዊታቸው ሰፍሮ የነበር ይፋግ ነው። ወባ ስላስቸገራቸው ተራሮች መድሃኒያለምን አድርገው ወደ ላይ ወደ ደጋው ወጡ። በዚያም ግሩም የሆነ የስንዴ አዝመራ አዩ። ገበሬውም እሸት ቆርጦ ሰጣቸው። እየሱስ ከሰፈሩ በኋላ ያንን አስታውሰው አካባቢውን አሁን እስኪከለከል ድረስ ስንዴ ሲያስገብሩት ኖረዋል።

2. አጼ ሰይፈ አርዕድ እየሱስ ላይ ሰራዊታቸውን ይዘው ጊዜያዊ ሰፈር መሰረቱ። ቦታው ስላማረ ሕዝቡን አስፈቅደው እየሱስ ቤተክርስቲያንን ተክለው 284 ጋሻ መሬት መደቡለት። ሰይፈ አርዕድ እየሱስን ተክሎ ለልጁ ለሰርጸ ሚካኤል እንዲያስተዳድር ሰጥቶ እሱ ወደ ሸዋ ተመለሰ። ለቤተ ክርስቲያን የገበረ ለመንግስት አይገብርም ነበር። እንዲህ አይነቱ ቀፈፋ ይባላል። ከእብናት አሞራ ገደልና ቡሮ መደብ፣ ጉና ጉናና ደብረሲና ማርም ለእየሱስ ይገብሩ ነበር። በአጼ ሰይፈ አርዕድ ጊዜ የቤተክርስቲያኑን ንብረት አይጥ እንዳታወድመው ለሚከላከሉ ድመቶች የድመት የመሬት ስሪት ነበራት። ቱሚ ላይ አንድ ጋሻ መሬት ነበራት።

*ጥያቄ፣ የደብረ ታቦር የጥንት ስም ማን ይባላል?*

3. የአካባቢው የተለያዩ የጎጥ መጠሪያዎች ነበሩ። ራስ ጉግሳ የአካባቢውን አስተዳደር ከመሬት ስሪት ሲያወጡ ሰየሙት የሚለው የተሳሳተ ነው። ከዚህ የነበሩ አለቃ ታደሰ የሚባሉ ታሪክ አዋቂ ሲናገሩ እንደሰማሁት፣ የውጭ ሰዎች ጣና ሀይቅ ላይ ሆነው ወደ ላይ ተራራውን በማየት ‹‹ይኸ የእየሩሳሌምን የታቦር ተራራ ይመስላል›› በማለታቸው ስያሜውን እንዳገኘ የሚናገሩ አሉ። እኔ እንደሚመስለኝ ግን በዘመኑ የነበሩት ሊቃውንት ተሰባስበው ከተራራው አቀማመጥ በመነሳት የሰየሙት ነው። ጁራ የሚለው መጠሪያ ዛሬ ጎንደር በር የሚባለው አካባቢ መጠሪ እንጂ የከተማዋ ስም አልነበረም።

4. ወደ ኋላ ከመጡት ራስ ጉግሳ ትልቁ፣ ቤተክርስቲያኑ እንዲጠናከር አድርገዋል። አጼ ሱስንዮስ አሪንጎ ላይ ቤተመንግስት አሰርተው ነበር። በሕልማቸው ጎ የሚል ፊደል ስለታያቸው እሱን እየተከተሉ ቤተ መንግስታቸውን ጎርጎራ፣ ጎመንጌ፣ እያሉ መጨረሻ ላይ ጎንደር ሰሩ።

5. እነ እሹቴ ሀይሉ የሚባሉ የዚህ ሀገር ሀይለኞች ነበሩ። ግብር ይቀነስልን ብለው ለተክለ ጊዮርጊስ አመለከቱ። መኳንንቶቻቸውን ሰብስበው ‹‹እንዴት እናድርግ?›› ሲሉ ‹‹እነሱ ከማን ስለሚበልጡ ነው አይቀነስም›› አሏቸው። እነእሹቴ ሀይሉ አንገዛም አሉና አመጹ። ከንጉሱ ባለሟልም ራስ ጉግሳን በሚስጥር ተገናኝተው ‹‹እኛ እርስዎን ልናነግስ ነው፤ ለተክለ ጊዮርጊስ አንገዛም›› አሏቸው። እሳቸውም ‹‹እሺ›› ብለው ወደ ጎንደር ከተመለሱ በኋላ ‹‹እናቴ ታማለችና የጁ ደርሼ ልምጣ›› ብለው በማታለል ንጉሱን አስፈቅደው ወደ የጁ ሄዱ። ከዚያም እንደደረሱ ‹‹በጌምድር አንግሶኛል እንናንተስ ምን ትላላችሁ?›› ቢሏቸው ‹‹አንግሰነዎታል አሏቸው።›› ተመልሰው መጥተው አንድ አንድ እያሉ ባለሟሎቻቸውን አስከዱባቸውና ንጉሱ ያለጦርነት ተሸንፈው ገዳም ገቡ። ትልቁ ጉግሳ ነግሰው ማስተዳደር ጀመሩ። ፍጻሜ መንግስት ተክለ ጊዮርጊስ ተባሉ። የትግራይም የራሳቸውን መርጠው ኢትዮጵያ ለ68 ዓመታት ያለ ንጉስ በመሳፍንት ተከፋፍላ ኖረች። ከትልቁ ዓሊ እስከትንሹ ዓሊ መናገሻው ደብረ ታቦር ነው።

6. አጼ ቴዎድሮስ ራስ ዓሊን ድል አድርገው ዘመነ መሳፍንትን በማስወገድ የዘውድ አገዛዝን እንደጋና መለሱ። 15 ዓመታት በጦርንት ከላይ ከታች እንዳሉ ኖሩ። መጀመሪያ ቤተ መንግስታቸውን ዛሬ መድኃኒዓለም ካለበት ላይ ለመስራት አስበው ነበር። በሕልማቸው አንድ ትልቅ እንግዳ መጥተውባቸው ‹‹ይቀመጡ›› ሲሏቸው ‹‹መቀመጫየን አንተ ይዘህብኛል›› ስላሏቸው ወደ ታች እልፍ ብለው ሰሩት። ጋፋት ላይ ያሰሩትን መድፍ ሰኞ ገበያ ላይ ከነይግለጡ ቤት አካባቢ ነው የሞከሩት። ፈረንጁ ‹‹ይተኩሱት›› ቢላቸው ‹‹መጀመሪያ አንተ ተኩሰህ አሳየኝ›› አሉት። ሲተኮስ ወደ ኋላ ሸንቶ አደጋ አድርሶ ነበር ይባላል። እሳቸው ሲወድቁ አጼ ተክለ ጊዮርጊስ ተተኩ። ላስቴ ናቸው። እንግሊዞች እቃውን የሚረከብ ሰው መርጣችሁ ስጡን ቢሉ እሳቸው ተመረጡ። የላስታ ሰው በዚያ ይዞዎት ይሄዳል ብሎ ስላስፈራራቸው ሳሄዱ ቀሩ። እቃውን የሚረከብ ሲጠፋ የእንግሊዝ መንግስት ወዳገሩ ጫነው። እሳቸው ሶስት ዓመት እንደገዙ አጼ ዮሐንስ መጡ። አጼ ዮሐንስ ጤፍ በስልቻ አድርገው ‹‹ጦሬ ይህን ያህል ነውና አይሆንልህም›› ብለው ቢልኩባቸው፣ ጤፉን ቆልተው ‹‹እንደዚህ ቆልቸ እመልስሃለሁ›› አሏቸው። ገጠሙና አጼ ተክለ ጊዮርጊስ ተሸነፉ።

አሁን ጊዜ ሰጥቶት ከላስታ ቢወጣ፣

ከጥንት አይደለም ወይ ከትግሬ የወጣ፡፡ ተብሎ ተገጠመ፡፡

7. አጼ ዮሐንስ እንደመጡ መጀመሪያ ሰፍረው የነበር ወይብላ ማርያም ነው፡፡ ሌሊት ጉንዳን መጥቶ ሰራዊቱን ሲያስቸግር በማደሩ ለቀው ወደ ሕሩይ ሄዱ፡፡ ቦታውንም ሰመርናሃ አሉት፡፡ በገዕዝ ‹‹ወደድናት›› ማለት ነው፡፡ ቤተ መንግሥታቸውን ከዚህ መሰረቱ፡፡ ከፖለቲካ ሰውነት ኃይማኖተኝነታቸው ያይል ነበር፡፡ እነምኒልክን በቤታቸው አሽከር ሆነው ነው ያሳደጓቸው፡፡ በዚያ አፍላነት ተሰምቷቸው ጉብ ጉብ ሲሉ ለምኒልክ ሸዋን፣ ለተክለ ኃይማኖት ጎጃምን እንዲያስተዳድሩ ሰጧቸው፡፡ እኔ እነግስ እኔ እነግስ እርስ በርስ ገጠሙና ንጉሥ ምኒልክ ንጉሥ ተክለ ሀይማኖትን ማረኳቸው፡፡ ድርቡሽ በጎንደር ሲመጣ አጼ ምኒልክ የንጉሱን ደካማ ጎን ያውቁ ስለነበር ጸጉሩን የገመደ ባሕታዊ ልከው ‹‹ወደ ሸዋ የዘመትክ እንደሁ ድል ታደርጋለህ፣ ነብስህ ግን ትኮነናለች፡፡ ወደ መተማ የዘመትክ እንደሁ መንግስትህ አጭር ነው መንገስተ ሰማያት ግን ትገባለህ›› ብሎ እንዲነግራቸው አደረጉ ይባላል፡፡ እሳቸውም ሀማኖተኛ ነበሩና ወደ መተማ ዘምተው ተሰው፡፡ በዚህ ጊዜ ምኒልክ ንግሥናውን ጠቅልለው ያዙት፡፡ የንግሥና ቦታ ከደብረ ታቦር ወደ ሸዋ የሄደው በዚህ ዘመንንና ምክንያት ነው፡፡

8. ራስ ጉግሳ ወሌና ብጡል ወሌ (የጣይቱ አባት) ወንድማማቾች ናቸው፡፡ ጣይቱ አጼ ምኒልክን አግብታ የእንጀራ ልጇን ዘውዲቱን ለአጎቷ ለራስ ጉግሳ ወሌ ዳረችላቸው፡፡ አጼ ምኒልክ ሲታመሙ መኳንንቱን ሰብስበው ‹‹ንግሥናውን ከእኔ እንዳታወጡ ››ብለው አስምለዋቸው ነበር፡፡ እሳቸው ሲያርፉ በመሃላው መሰረት ልጅ እያሱ ነገሱ፡፡ ልጅነት አሸንፏቸው አልሆን ሲል ንግስት ዘውዲቱ እንዲነግሱ ታዘዘና ከባላቸው ለይተው ከደብረታቦር አስመጥተው ለይስሙላ ‹‹ንግሥት›› ካሉ በኂላ ‹‹እንግዲህ እርስዎ ለሁለት ባል አይገዙም፡፡ ዘውድ ባል ነው ሌላ ባል አያስፈልገዎም›› ብለው ከባላቸው ለዩዋቸው፡፡ አልጋ ወረሽ ተፈሪ ይህን ሁሉ እያቀነባበሩ የማስተዳደር ስራውን የሚሰሩት እሳቸው ነበሩ፡፡ ራስ ጉግሳ ጦራቸውን ይዘው አንችም ላይ ከአልጋ ወረሽ ተፈሪ፣ ከራስ ሙሉጌታና ከደጃች ክፈተው ጋር ተዋግተው ተሰው፡፡ አያሌው ብሩ የሚባሉ ሰሜነኛ ዘመዳቸው እንዳያግዟቸው ‹‹እሱ ከተሸነፈ የእሱን ግዛት ላንተ እንሰጥሃለን›› ብለው ቃል

ገብተውላቸው ስለነበር፣ ራስ ጉግሳን ከድተው አላገዟቸውም። ጉግሳ ከሞቱ በኋላ ‹‹ግዛት ስጡኝ›› ቢሉ ‹‹ለዘመዱ ያልሆነ ለኛ አይሆንም›› ብለው ከዷቸው። በዚህን ጊዜ፦

አያሌው ሞኙ፣

ሰው አማኙ ሰው አማኙ። ተብሎ ተዘፈነ።

ራስ ሙሉጌታ ትግራይ ላይ ሁነው ሲያስተዳድሩ የጣሊያን ወራሪ መጣባቸው።

ሰራዊታቸውን ይዘው በየጁ አድርገው ሲሸሹ፣ ‹‹የጉግሳ ባለደም መጣልህ›› ብለው አሳደው ገደሏቸው።

አባ ደልድል ጉግሳ አንችም ቢንገላታ፣

የጁን አገኘ አሉ ራስ ሙሉጌታ። ተብሎ ተገጠመ።

**ለ. የሞት ምንነት**

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣ ቀኝ ጌታ ዜናዊ ስቡሕ (አባ.2፣ቁ.1)**

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣ እ.ኢ.አ. 6/09/2004**

*ጥያቄ፣ ሞት በቤተክርስቲያን ምንድን ነው?*

1. ሞት ማለት የነብስና ስጋ መለየት ነው። እንግዲህ ትልቁ ነገር ሞት ማለት መለየት ነው። ሞት ሶስት አይነት ነው። በቤተክርስቲያናችን ትርጓሜ መለየት ሶስት ነው። አንደኛው ሞተ ሕሊና ይባላል። የሰውን ልዥ እግዚአብሔር ሲፈጥር ንጹህ አድርጎ፣ በነጻ ልቡና፣ ነጻ ነፍስ፣ ነጻ ስጋ ሰጥቶ ንጹህ አድርጎ ነው የፈጠረው። ሥጋውም ልቡናውም ንጹህ ነበር፤ እጸ በለስን ሳይበላ። ‹‹ያችን እጸ በለስ የበላህ እንደሆነ የሞት ሞት ትሞታለህ›› ተብሎ ተነገረው። በኋላ ትእዛዝ አፍርሶ ያችነን ህማም ያለባትን ሞት ያለባትን መርዝ የሆነች እንጨት በላ እጸ በለስን። እሷን እንደበላ ሶስት ሞት ሞተ። ሞት ማለት መለየት ነው። ነግሮታል ‹‹ከእኔ ትለያለህ፤ ገሃነመ እሳት ትወርዳለህ። አንደኛው ሞት ከእግዚአብሔር መለየት ነው። በላ ከእግዚአብሔር ተለየ። እለቱን አልሞተም እኮ። ከሱ ጋር የነበረውን ክብር አጣ፤ ወደምድር ወረደ፤ ተለየ። አሁን ይኽ እንግዲህ ሞተ ሕሊና ነው። ሞተ ህሊና የሚባለው ክፉ የሚያሰራ ነው። ከእግዚአብሔር

የተለየ ቁሞ ይሄዳል እንጂ ሞተ ሕሊና ነው፡፡ የክፉ ሀሳብ ተገዥ ከሆነ ከእግዚአብሔር ተለይቷልና ሙቷል፡፡

2. ሁለተኛውና ሞተ ነፍስ የሚባለው ደሞ፣ ነፍስ ከእግዚአብሔር ተለይቶ ገሃነመ እሳት ወደ ዲያብሎስ መውረዱ ሲሆን የሥጋ ሞት የነፍስና ሥጋ መለያየት ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ያለቸው ነፍስ ሕያው ትባላለች፡፡ ሲጠቃለል ሞተ ህሊና በአካል ቁሞ በመጥፎ ሥራ ምክንያት ከእግዚአብሔር መለየት ነው፡፡ ሞተ ሥጋ የሥጋና ነፍስ መለያየት ነው፡፡ ሞተ ነፍስ የነፍስ ከእግዚአብሔር መለየት ነው፡፡ ነፍስ ከፍርድ ቀን በኋላ ገሃነመ እሳት የምትገባ ቢሆንም ከፍርድ ቀን በፊትም መቀመጫዋ ሲኦል ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር አይገናኝም ተለየ ማለት ነው፡፡

ጥያቄ፣ ሞት እንዴት መጣ፣ ማን አመጣው? (ራሳቸው ጠየቁ)

3. እግዚአብሔር አልፈጠረም ሞትን፡፡ ሞትን የፈጠረ የሰው ልዥ ነው፡፡ ህማመ ሞትን የፈጠረ የሰው ልዥ ነው፡፡ ተነግሮታል ህጉ፡፡ ‹‹ይህችን ህግ ብትጥስ ትሞታለህ፤ ትታመማለህ›› ተብሏል፡፡ ነገር ግን አታድርግ የተባለውን በላና በራሱ ጎትቶ አመጣት፡፡ መጻህፍት ስላሉ መነሻ እነሱን እናያለን፡፡ (ማስታወሻ ልወስድ ስሞክር ሳናነብ መጻፍ እንደሌለብኝ ተቃወሙ፡፡ መጽሐፍ ቅዱሱን ቁጥሩንና ምዕራፉን ነግረው እንዳነብ ሰጡኝ፡፡)

> እግዚአብሔር ሞትን አልፈጠረምና ነዋሪ ይሆን ዘንድ ፍጥረትን ፈጥሯልና፣ የሰዎች ጥፋት ደስ አያሰኘውም በእጃችሁ ሥራ ሞትን አታምጡ፣ የሰውም መፈጠር ልድኅነት ነውና በእነርሱ ዘንድ ሁሉን የሚያጠፉ የሞት መርዝ ሀጢያት አልነበረምና ሕይወት የማታልፍ ስለሆነች፤ ለመቃብርም በዚህ ዓለም ግዛት አልነበረምና እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ግን በቃል ጠሩት፤ ባልንጀራም አደረጉት፤ በዚህም ጠፉ፡፡ የእርሱ ወገን መሆን ይገባቸዋልና ከእርሱ ጋራ መሃላን ተማማሉ (ጥበ.ሰሎ.1፣13-17)፡፡

4. ስለተማማሉ እስከመጨረሻው አይለያዩም፡፡ እግዚአብሔር ሞትን አልፈጠረም፡፡ ‹‹ይህችን እንዳትነኩ›› የተባሉትን አፍርሰው ህማምን፣ ሞትን ፈጠሩ፡፡ እግዚአብሔር መቃብርን አልፈጠረም፡፡ እንግዲህ ይኸ እግዘአብሔር መጀመሪያ ሞትን አለመፍጠሩንና የሰው

ልኹ በገዛ ራሱ ሞትንና ሕማምን፣ደዌን ማምጣቱን ያሳያል። (ቀጠሉና ይህን አንብብ ብለው ሰጡኝ።) ሞት ወደ ዓለም እንዴት መጣ?

‹‹እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፡- ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስተውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና›› (ዘፍ.2.16)።

‹‹ሔዋን የሰይጥጣንን ተንኮል ሳታውቅ ምክሩን ተቀብላ አዳም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንዲተላለፍና ከሀጢያት ላይ እንዲወድቅ አደረገችው›› ዘፍ.3፣1-4)።

እግዚአብሔርም በአዳምና በሔዋን ሥራ ተቆጥቶ ረገማቸው፤ ሞተ ሥጋና ሞተ ነፍስ ፈረደባቸው›› (ዘፍ.3፣19፤ኩፋ.423)። ‹‹እስካሁን የመጣንበትን ስለሚያሳይ ይችን አንብብ››

5. ‹‹ከገነት አስወጥቶ ወደዝች ምድር ወደምድረ ፋይዳ አባረራቸው (ዘፍ.3፣22)። አዳምና ሔዋን ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው ዘራቸውና ትውልዳቸው ሁሉ በዚህ ፍርድ መሰረት በሞተ ሥጋ ወደመቃብር በሞተ ነፍስ ወደ ሲኦል መውረድ ግዴታ ሆነባቸው። አምስት ሺህ አምስት መቶ ዓመት፣ ዘመነ ፍዳ ተፈጽሞ አምላክ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ፣ ተሰቅሎ ሞቶ ተነስቶ ዓለሙን በደሙ እስኪያድነው ድረስ ሞት የበደሉትንም ሆነ ያልበደሉትን ባንድነት ገዝቷቸዋል።››

6. ሞተ ነፍስ ነው። በሲኦል የነበሩትን ማለት ነው። እነሙሴም እነ አብርሃምም ከዚያው ገሀነም ነው የነበሩ። ክፉ ብትሰራም በጎ ብትሰራም አንድ ላይ ማለት ነው። በኋላ በክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ፣ ሞተ ነፍስ ቢጠፋም ሞተ ሥጋ አልቀረም። ሞተ ነፍስም ቢሆን ከአዳም በተወረሰው የዘረ ሐጢያት መተላለፉ ቀረ እንጂ፣ እያንዳንዱ ሰው በፈጸመው በደል፣ በሰራው ሀጢያት በንስሃ ካልታደሰ ሞተ ነፍስ ያገኘዋል (ሮሜ.5፣18፤ቆላ.1፣21፤ሉቃ.15፣11-25፤1 ጴጥ.3፣19) በዚህ አይነት ሞተ ስጋም ሆነ ሞተ ነፍስ ሰው የእግዚአብሔርን ሕግ በማፍረሱ፣ ትዕዛዙን በመጣሱ ራሱ ጎትቶ ያመጣው ጣጣ እንጂ፣ እግዚአብሔር የባህሪው አድርጎ ለሰው አልፈጠረበትም ነበር።

ሞት በሰው ልጅ በደል ምክንያት ወደ ዓለም መምጣቱን የሚገልጹ የተለያዩ መረጃዎችን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንዳነብ ከጋበዙኝ በኋላ የሚከተለውን ለሞት ብያኔ የሚሰጥ መረጃ ከእነ መላከ ሰላም ዳኛቸውና ሌሎችም (1986፣10-11) አስነበቡኝ።

7. በመሰረቱ ሞት ስንል ምን ማለታችን ነው? ሞት ስንል በመጀመሪያ የምናየው፣ የነፍስንና የስጋን መለየት ነው። ሰው ሞተ በመንልበት ጊዜ ሕያውና ተንቀሳቃሽ አድርጋው በውስጡ የምትኖር ሕያውት ነፍስ ከስጋው ተለይች ማለታችን ነው።

   ሕያውት ነፍስ ከሥጋ በምትለይበት ጊዜ ደም በመላ ሕዋሳት የመዘዋወር ሥራውን ያቋርጣል። በደመነፍስ የሚንቀሳቀሰው ሰውነትም ሥራውን ያቆማል። ‹‹ነፍስ በደም ታድራለች›› ተብሎ ተጽፎአልና (ዘፍ.9፣4፤ ዘሌ.17፣11፤ መቴ. 27፣50)።

ኸዚህ ላይ እስቲ በእናንተ ደመ ነፍስ ማለት ምን ማለት ነው? ደመንፍስ የእንስሳት ነው የሰውም አለው? (ጠየቁኝ። ስውተፈተፍ ተመልክተው መልሱን ራሳቸው እንደሚከተለው ሰጡ)።

8. ደመ ነፊስ የሥጋ ባህሪ ነው። አራት ባህርያተ ሥጋን አዋህዶ ሲያበቃ ደመነፍስነን አሳደረበት። በደመነፍስ ሕያውት ነፍስ አላደረችበትም። ሕያውት ነፍስ የምትባለው የማትሞት፣ የማትፈረስ፣ ዘላለም የምትኖር፣ አዋቂ፣ ተናጋሪ፣ልብ የምታደርግ ናትኝ። ደመነፍስ የሥጋ ባህሪ ነው። የሰው ልዥ በደመነፍሱ መብላት፣ መጠጣት፣ መተኛት ፣መነሳት፣ ይኸ የደመነፍስ ነው። ደመነፍስ የምትኖረው በደም ነው። ዘር የምንዘራ የምንራባ በደመነፍስ ነው። በነፍስ መራባት የለም። ነፍስ ደግሞ የምታድረው በደም ነው። ይህች ደመነፍስ ደሙ ወጥቶ ወጥቶ ሲያበቃ ተና ነው የምትጠፋው። ነፍስ ግን ሕያውት ናትና ወደ ፈጣሪዋ ነው የምትሄደው። ደመ ነፍስ ሰውየው ከሞተ ደሙ መዛወር ካቆመ በኋላ የለችም።

ከመላከ ሰላም ዳኛቸውና ሌሎችም (ጥቁም ስራ፣11) የሚከተለውን እንዳነብ ጋበዙኝ።

   በሀጢያት ምክንያት የሚመጣ ሞት፣ በሞተ ስጋ ብቻ የሚወሰን አይደለም። ሞተ ነፍስንም ያስከትላል። ይኸውም ሁለተኛ ሞት ማለት ነው። ሁለተኛ ሞት የተባለውም የነፍስ ከእግዚአብሔር መለየትና ዘለዓለማዊ የሆነ ኩነኔ ገሀነምን መቀበል ነው።

ስለሆነም ሞተ ነፍስ እንደሞተ ሥጋ ሁሉን አያጠቃልልም። ሞተነፍስ የሚፈረደው በክርስቶስ በማያምኑ፤ ሕጉን በማይጠብቁ ትዕዛዙን በማይፈጽሙና ንስሃ በማይገቡ ሰዎች ብቻ ነው።

‹ዳሩ ግን የማይፈሩና የማያምኑ፣ ሰውነታቸውን የሚያሳድፉ፤ነፍሰ ገዳዮች የሚሰስኑ፣ ሥራይ የሚያደርጉ፤ ጣዖት የሚያመልኩ፣ ሐሰት የሚናገሩ ቅጣታቸው በእሳትና በዲን ጉድጓድ ይሆናል። ይኸውም ሁለተኛ ሞት ነው› (ራዕ. 21፣3፤20፣140።)

በቅዱሳት መጻሕፍት የታዘዘውን አለመፈጸምና የሥነምግባር ጉድለትም ሞተ ነፍስን እንደሚያመጣ በቅዱስ ወንጌል ተጽፎአል (ማቴ.20፣22)።

በቅዱሳት መጻሕፍት የታዘዘውን አለመፈጸምና የሥነ ምግባር ጉድለትም ሞተ ነፍስን እንደሚመጣ በቅዱስ ወንጌል ተጽፎአል (ማቴ፣ 23፣ 25-41)።

ሞት ከሞተ ሥጋና ሞተ ነፍስ ሌላም የሰውን ልጅ ስነምግባር በተመለከተ የተለያየ ትርጉም አለው። በሀይማኖት ጸንተው በፍቅረ እግዚአብሔር በፍቅረ ቢጽ የማይኖሩ፣ መልካሙን ነገር አውቀው የማይሰሩና በሀጢያት መንገድ የሚጓዙ ሁሉ በሕይወት እያሉ ሙታነ ሕሊና ይባላሉ (ማቴ.20፣22)።

9. ‹‹ሙታን ሙታናቸውን ይቀብራሉ›› ይላል። አሁን በእኛ ሀይማኖት ሬሳ ሬሳን ይቀብረዋል? (ጠየቁኝ)። ይኸ ምንድን ነው ሙታነ ሕሊና ነው። ‹‹ተከተለኝ›› ሲለው ‹‹አይ አባቴን ልቅበር›› አለው። ‹‹ተዋቸው ሙታን ሙታንን ይቅበሯቸው›› አለው። ሙታነ ህሊና ሙታነ ሥጋን ይቅበሯቸው ማለቱ ነው።

የሞት ትርጉሙ መለየት መሆኑ ታውቋል። ስለሆነም ታላላቅ የሀይማኖት አባቶችና መንፈሳውያን ሰዎች የወዲሁን ዓለም በወዲኛው ዓለም ለውጠው የጽድቅ ወራሾች ለመሆን ዓለምንና በዓለም ያለውን ሁሉ ትተው እግዚአብሔርን ለማገልገል ሰውን በጸሎታቸው ለመርዳት ይወስናሉ። እንደነዚህ ያሉት ደጋግ ሰዎች ከዓለም ሥራ መለየታቸውን ለመግለጽ ራሳቸውን እንደሞተ አድርገው ይቆጥራሉ። ይህን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹ዓለም በእኔ ዘንድ የሞተች ናት፣ እኔም በዓለም ዘንድ የሞትኩ ነኝ›

በማለት አረጋግጦታል (ገላ.6.14)፡፡ በሌላ በኩል መጽሐፍ ‹ለሀጢያት ሬሳ ሁኑ›፣ ‹ለጽድቅ ህያው ሁኑ› ይላል፡፡

10. የሞተ ሥጋና ሞተ ነፍስ ሁኔታ ከዚህ በላይ በአጭሩ የተዘረዘረውን ሁኖ ሳለ የሰው ልጆች ቀደም ሲል በኃጢያታቸው ሞትን ወደ ዓለም ማጣታቸው አልበቃ ብሎ በዘመናችንም ሞትን በተለያየ መልኩ በራሳቸው ላይ ሲያመጡ ይገኛሉ፡፡ይኸውም፣ ጽንስን በማስወረድ፣ የራሳቸውንም የልጆችንም ሕይወት ያጠፋሉ፡፡ በመታነቅ፣ መርዝ በመጠጣትና በተለያዩ ድርጊቶች ሕይወታቸውን ያሳልፋሉ፤ ከዚህም ሁሉ ጋር ሰዎች በተፈጥሮ ሕማምና ጦርነትን ከመሰለ በሰውነታቸው ላይ በሚደርስ አደጋ ሲሰቃዩ በራሳቸው ወይም በሌላው ሕይወታቸው እንዲያልፍ የሚያደረጉም አሉ፡፡ ይህም ሁሉ በቅዱሳት መጻሕፍት የተከለከለና በቤተክርስቲያን የተወገዘ ነው፤ በዚህ አይነት አሟሟት ሕይወታቸውን የሚያጠፉ ሁሉ በሀይማኖት ትምህርት ተቀባይነት የላቸውም፡፡ በሞቱም ጊዜ በህግና በሥርዓት ኖረው በክብር ለሞቱ ሰዎች የሚፈጸመው የቤተክርስቲያን ጸሎተ ፍትሃት ሌላውም ስርዓት ሁሉ አይፈጸምላቸውም (2 ሳሙ.1፣1-10፤ማቴ. 27-30)፡፡

11. ሳኦል ንጉሱ እብራውያን ቢከቡትኝ ከገዛ ሰይፉ ላይ ወድቆ ሙቷል፡፡ ይሁዳ ታንቆ ነው የሞተ፡፡ እንደዚህ የሚያደርጉ ማለት ነው፡፡ አሁን ጥይት ጠጥቶ ታንቆ ምን ብሎ ለሚሞት ቤተክርስቲን ፍትሃት አታደርግም፡፡

ታንቆም ይሁን በሌላ ምክንያት ሕይወትን ማጥፋትን ቤተክርስቲያን በጣም በጣም ታወግዛለይ፡፡ በራስ ፍላጎት ልሙት ብሎ መሞትን ቤተክርስቲን ትከለክላለች፡፡ ታስተምራለች፤ ሕግ ጥሶ ሲሞት ወደፍትሃት አይወሰድም፡፡ ክልከላማ ከሌለ ጦም ባደረ ጊዜ ሁሉም ያልቃልኝ፡፡

*ጥያቄ፣ ይህን ለመከላከል ነው?*

12. ለዚህ ብቻ አይደለም፡፡ አሁን እርስዎ ቤተ አለዎት እንበል፡፡ ደክመው የሰሩት፡፡ አንድ ሰው መጥቶ ቢያፈርሰው ምን ይላሉ? ያልሰራውን ሲያፈርስ ቢሆን በጉልበት ባይሆን

በህግ መጠየቅ አለ፡፡ ያልሰራውን የሰው ቤት ማፍረስ ወንጀል ነው አይደለም? ወንጀል ነው፡፡ (መጽሐፍ ቅዱሱን እንዳነብ ሰጡኝ)

‹‹ማንም የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ቅዱስ ነውና ያውም እናንተ ናችሁ» (1ቆ.3፤17)፡፡ ሟች እኮ ያንን ሰውነት አልፈጠረውም፡፡ ያልሰራውን? የሰራው እኮ እግዚአብሔር ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ማደሪያ ያልሰራውን ሰውነቱን ቢያፈርስ ወንጀል ነው፡፡ ባለቤቱ ቤቱን አፍርሶ ቢፈልግ ሊያድሰው፣ ቢፈልግ ሊያበሰብሰው ይችላል፡፡

13. አፈር ወደ አፈር ሳይመለስ ነፍስም ወደ ሰጠው እግዚአብሔር ሳይመለስ፡፡ ነፍስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ናት፡፡ በንና ተንና አትጠፋም፡፡ ሁሉም ወደመነሻው ነው የሚሄድ፡፡ አሁን ውሃ ከየት ነው የሚመጣ በደመና ተቋጥሮ ከውቅያኖስ ነው፡፡ እናንተ ተን ትሉታላችሁ፡፡ አምጥቶ ያዘንበዋል፡፡ ያ ዝናብ ወንዝ ይፈጥርና ሌት ተቀን ተጉዞ ወደውቅኖስ ይገባል፡፡ መነሻው ውቅያኖስ ነበር መድረሻውም ውቅኖስ ሆነ፡፡ የሰው ልዥም መነሻ አፈር ነው፡፡ የሥጋው መነሻ አፈር ነው፡፡ ነፍሱ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ናትኝ፡፡ ሁላቸውም ወደመነሻቸው ነው የሚሄዱ፡፡ ይኸ ምንድን ነው ሁሉም ወደመነሻው ነው የሚሄድ ለማለት ነው፡፡

***የመረጃ አቀባይ ሥም መሪጌታ ክፍለማርያም አለነ (አባ.2፤ቁ.2)***

***ቃለመጠይቅ የተደረገሯት ቀን 21/06/05***

*ጥያቄ፣ ሞት ምንድን ነው በቤተክርስቲያን?*

1. ሞት ሲባል ረፍት ማለት ነው፡፡ የጻድቅ ሰው ሞቱ በእግዚአብሔር ፊት ረፍትና በጎነት ነው፡፡ በዚህ ዓለም ውጣ ውረድ አለ፡፡ በዚህ ዓለም ጨለማ አለ፡፡ መብላት መጠጣት የድካም ውጤት ነው፡፡ ከዚህ በኋላ መራብ ወደሌለበት፣ ድካም ወደሌለበት፣ መጠማት ወደሌለበት መራቆት ወደሌለበት፣ ደስተኛ ወደሚኮንበት ወደብርሃን ዓለም ነው የሚሄደው፡፡ ስለዚህ ከዚህ ዓለም ያለውን ድካም መላቀቂያ ስለሆነ እረፍት ነው፡፡ በቤተክርስቲያን ሥርዓት የነብስ ከስጋ መለየት እረፍት እንጂ ሞት አይባልም፡፡

*ጥያቄ፤በቤተክርስቲያን ስንት አይነት ሞቶች አሉ?*

2. ሞት የሚለው ሰው ቁሞ እየሄደ ይሞታል። ሞት የሚባለው ይህ ነው። ለምሳሌ ሉቃ.15፣15 ላይ አንድ ባለጸጋ ነበር፤ ሁለት ልጆች ነበሩት፤ የመጀመሪው አባቱን አገልጋይ ነበር። ሁለተኛው አባቱን አይታዘዝም። ለአባቱ «ያለኝን ሁሉ ስጠኝና ወደፈለገኝ መሄድ አለብኝ» ብሎ ጥያቄ አቀረበለት። አባቱም የሚከፍለውን ነገር ከፍሎ ሰጠው። ገንዘቡን ወስዶ ይህ ዓለም ባፈራው ነገር ጨረሰና ሎልነት ገባ። ሎልነት ሲገባ እሪያዎችን እንዲጠብቅ ነው የተደረገ። እንደቤተክርስቲያን ሥርዓት እሪያ አይጠበቅም አይበላም። አህዛቦች ግን እያረቡ ይበሏቸዋል። እሪያዎቹ አሰር እየበሉ ሲሄዱ እሱም ለመብላት ቢፈልግም እነሱ እየቀደሙ ይበሉበት ነበር። በኋላ «ከአባቴ ቤት እኮ ብዙ ነገር አለ፤ ተመልሼ ብሄድ ልጄ እንደማይለኝ እርግጠኛ ነኝ፤ ነገርግን ከገበሬዎቹ እንደ አንዱ ይቆጥረኛል፤ ተመልሼ ሂጄ የሰማይ አባቴን በድያለሁ አንተንም በድያለሁ ብየ እንደልጅህ ባትቆጥረኝም እንደገበሬዎችህ ቁጠረኝ እለዋለሁ» ብሎ ሄደ። አባትየው ሲያየው ግን ምንድን ነው ያለ «ሙቶ የነበረው ልጄ ድኗልና ኑ ሰንጋ ይታረድለትና በደስታ እንኑር። ደስ ይበላችሁ ሙቶ የነበረው ልጄ ዳነ» አለ። ልጁን ግን በአካል ነው ያገኘው። «ሙቶ የነበረው ዳነ» ማለት በሀጢያት ላይ የነበረው ወደዚህ ተመለሰ ማለት ነው።

3. ወደወርቁ ስንገባ አባት (ባለቤት) የተባለው ክርስቶስ ነው። ትልቁ ልጅ የተባለው ጻድቃን ናቸው። ሚቹ ልጅ የተባለው ሀጥአን ናቸው። ሀጥኡ ንስሃ ሲገባ ክርስቶስ ምን ያህል ደስ እንደሚለው በዚህ ይታያል። ስለዚህ ሞት የሚባለው በአካል እየተራመዱ እግዚአብሔርን ረስቶ ለሰይጣን መገዛት ነው። ከዚህ በኋላ ደግሞ ወደሲኦል መውረድ ሞት ይባላል። መጠሪያውም የሞት ሞት ነው። እንዲህ የተባለበትም አንዱ ሞት በዚህ ዓለም ሀጢያት ሲሰራ ሞት ነው ብለናል፤ ሁለተኛው ሞት ነፍስ ከስጋ መለየት ነው፤ እሱ እረፍት ተብሏል፣ ወደሲኦል መውረድ ግን ከእግዚአብሔር ቤት መውጣት ነው። እንግዲህ የእግዚአብሔር ቤት የምንለው ብርሃን የማይለየው ምንጊዜም ብርሃን የሆነ የማይደከምበት፣ የማይራብበት፣ እማይጠማበት፣ በጎ ነገር ያለበት፣ ምንጊዜም «ቅዱስ ቅዱስ» እየተባለ የሚኖርበት ቦታ ነው ያ። መላዕክትን መስሎ መኖር ማለት ነው። ይህን መስሎ መኖር ሲቻል ከመቀመቅ ሲኦል ገብቶ ምንጊዜም ጨለማ ከሆነው ቦታ

ላይ ወርዶ ከዚያ በላይ ደግሞ በሚያሰቃይ የዲያቢሎስ ተገዥ ሁኖ መኖር ይህ ሞት ነው። ይህን የሞት ሞት ይሉታል።

**1. የቀብር ሥርዓትና የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ክወና**

**1.1. የቀብር ሥርዓት ክወና**

**1.1. ሀ. ከቀበር ሥርዐት ጋር የተያያዙ ልማዶች**

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** ቀኝ ጌታ ዜናዊ ስቡሕ (አባ.2፣ቁ.1)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 10/09/2004

*ጥያቄ፣ መቃብር ከመቆፈሩ በፊት ይባረካል፣ ሬሳ ከመግባቱ በፊትም እንደዚሁ። ይሕ የሚደረግ ለምንድን ነው?*

1. ቤተመቅደስም ቢሆን ምንም ቢሆን መጀመሪያ ቡራኬ ያስፈልገዋል። ያ የተባረከ ቤት እንዲሆን ነው። ለሚች መቃብሩ ቤቱ ነው። ያ የተባረከ እንዲሆንለት ይባረካል። የተባረከ ቤት እንዲሆንለት።

*ጥያቄ፣ ከተቆፈረ በኋላም ካህን ሳይባርክ አይቀበርም?*

2. ያማ ከመጽሐፉ ላይ አለ። ባርኮ ሲያበቃ አፈር ይመልስበታል። የተጸለየበት ጠበልና እምነት በሽተኞች እንፈወስበታለን። አሁንም ይኸ የተጸለየበት መድሃኒት ነው ማለት ነው እንደ እምነት። አፈር መመለሱ ግን አፈር ነህና ወደ መሬት ግባ ለማለት ነው።

*ጥያቄ፣ የሬሳው ወደ ምስራቅ መዞርስ ተምሳሌቱ ምንድን ነው?*

1. ጌታችን ያረገው ወደ ምስራቅ ዞሮ ነው። የሚመጣም በምስራቅ ነው። ገነት ያለችም በምስራቅ ነው።

*ጥያቄ፣ እሬሳ ሲቀበርስ በቀኙ ነው፣ በግራው፣ ተንጋሎ ነው ወይስ ተደፍቶ?*

2. እንዲህ እንዳለ ነው (ከራሳቸው ገለል ብለው በመንጋለል አይነት) ራሱ ወደ ምዕራብ እግሩ ወደ ምስራቅ ሆኖ። ወደ ምስራቅ ዞሮ ነው። እኛም ጸሎት የምንጸልየው ወደ ምስራቅ አይደለ እንደዚያው ነው።

*ጥያቄ፣ እንዲያ ተደርጎ መቀበሩ የምን ተምሳሌት ነው?*

ኢየሱስ የሚመጣው በምስራቅ ስለሆነ ለመቀበል ነው፡፤ ዛሬ የምንጸልየው ከምዕራብ ወደ ምስራቅ ዞረን አይደል እንደዚያ ብለው ይጠብቃሉ፡፡

1.1.ለ. የአቀባበር አይነቶች

**መረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ አያሌው ተሾመ (አባ.2፣ቁ.22)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 09/05/2006

*ጥያቄ፣ በዚህ አካባቢ ሬሳ የምትቀብሩት እንዴት አድርጋችሁ ነው?*

1. ቀብር በሁለት ምንገድ ይካሄዳል፡፡ አንደኛው ድመም (ከሟች ሬሳ ላይ አፈር እንዳያርፍ የሚከላከል ድንጋይ ከላይ መቃብሩ ወደ ጎን ተቦርቡሮ እየተስተካከለ የሚዘጋበት ነው፡፡)

   ወረዳ ቀብር (ጉድጓዶ እንደተቆፈረ ሬሳ ይገባና የሚመለሰው አፈር በቀጥታ ያርፍበታል)

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ ሀይሌ ዘውዴ (አባ.2፣ቁ.37)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 11/05/2006

ጥያቄ፣ በዚህ አካባቢ ሰው ሲቀበር አፈር እንዴት ተደርጎ ነው የሚመለሰው?

1. እህ ወረዳ ቀብር ተሆነ ዝም ብሎ መመለስ ነው፡፡ ድመም ተሆነ ደሞ ድንጋ ተላዩ ላይ ከተደረደረ በኂላ ነው አፈር የሚመለስ፡፡

ጥያቄ፣ እንዲህ አይነቱ አቀባበር የቆየ ነው በቅርብ የመጣ?

የቆየ ነው፡፡ ኸፊትም አለ፡፡

ጥያቄ፣ ለስምንድን ነው በድመም የሚቀበር?

2. እሬሳውን አፈር እንዳይነካው፡፡ እንዳይደበድበው ነው፡፡

ጥያቄ፣ *ለማንኛውም ሰው ይደረጋል ወይስ ለተለዩ ነው?*

3. አየ እንግዲህ እንደየሰው ነው፡፡ ሴትም ብትሆን ወንድም ቢሆን አሁን ካገር ሰው የሚወደው ሰው አለ አይደል፣ ስለዚያ ሰው ተባብሮ ድንጋውን በዳገት ፈንቅሎ አምጥቶ ድመም አድርጎ ደርድሮ አፈር እንዳይነካው ያደርጋል፡፡

ጥያቄ፣ እንዲህ የሚደረገው ለቋሚ ነው ወይስ ለነፍስ ነው?

4. ለሚቱ ለዕለት ኸላዩ ላይ እንዳይወድቅበት ነው፡፡ ኋላ ቋሚው ሰው ወርዶ ሲደበድበው እንዳያይ እንዳይሰማ ነው፡፡

ጥያቄ፣ አንዳንድ ሰዎች «በድመም ሳይሆን ወረዳ ቅበሩኝ» ብለው እንደሚናዘዙ ሰምቻለሁ፡፡ ለምንድን ይመስለዎታል?

አየ ለነብሳቸው ነው፡፡ ጌታ የቀመሰውን ለመቅመስ ነው፡፡

**1.1.ሐ. የሕጻናት አቀባበር**

***የመረጃ አቀባይ ሥም፣*** አያሌው ተሾመ (አባ.2፣ቁ.22)

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣*** እ.ኢ.አ. 09/05/2006

1. ሕጻናት ሲሞቱ አቀባበራቸው በሶስት መንገድ ይካሄዳል፡፡ ጠበል ያልተረጨ ከሆነ (አስር ቀን ካልሞላው) በዚያው በቤት ጥግ ይቀበራል፡፡ ጠበል ከተረጨ ግን ወደቤተክርስቲያን ተወስዶ በቅጥሩ በውጭ በኩል ጠጋ ተደርጎ ይቀበራል፡፡ ክርስትና ከተነሳ እንደማንኛውም ክርስቲያን ቤተክርስቲያን ቅጥር ውስጥ ይቀበራል፡፡

***የመረጃ አቀባይ ሥም፣*** ሀይሌ ረታ (አባ.2፣ቁ.37)

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣*** እ.ኢ.አ. 10/05/2006

1. አስር ቀን ሞልቶት ጠበል ከተረጨ ክርስትናም ባይነሳ ያው ቄስ በደገመው ጠበል ስለተረጨ የክርስቲያንነት ምልክት አለው፡፡ ጠበል ካልተረጨው ስለሚሻል ወደ ቤተክርስቲያን ተወስዶ በእድሞው በስተውጭ ይቀበራል፡፡ አስር ቀን ካልሞላውና ጠበል ካልተረጨ ግን በዚያው በቤቱ አካባቢ ነው የሚቀበር፡፡ ምክንያቱም ክርስቲያን አልሆነም፡፡ በሁለቱም ለቅሶ የለም፡፡ ሁለት ሦስት ሰው ወስዶ ነው ሸጉጥ አድርጎት የሚመጣ፡፡ ክርስትና ከተነሳ ግን ማንኛውም ክርስቲያን በሚቀበርበት ቦታ ይቀበራል፡፡

ለአካባቢው ሰው ለቅሶው የሚነገር ሲሆን እናት አባት፣ እህት ወንድም ያለቅሳል። ሙሾ አይኖርም። ፍታትም አይኖርም።

**የመረጃ አቀባይ *ሥም*፣ *መሪጌታ* ክፍለማርያም አለነ (አባ.2፣ቀ.2)**

***ቃለመጠይቅ* የተደረገበት ቀን፣ እ.ኢ.አ. 19/05/2006**

ጥያቄ፣ ሕጻናት ጠበል ሳይረጩ ከሞቱ በቤት አካባቢና ክርስተና ካልተነሱ ደግሞ ከቤተክርስቲያን ውጭ የመቅበር ልማድ አለ። ቤተክርስቲያን ይህን እንዴት ታየዋለች?

ይኽ ልማድ እንጂ በቤተክርስቲያን የሚፈቀድ አይደለም። እንኳን በሥርዓት ተወልዶ ለሞተ በማሕጸን ውስጥ የመቆያ ጊዜውን ሳያጠናቅቅ ቢጨነገፍ እንኳን አካል ያለው ከሆነ መቀበር ያለበት በቤተክርስቲያን እንጂ የትም ቦታ አይጣልም። የክርስቲያን ልዥ በመሆኑም ለሕጻናት እንደሚደረገው አንድ ፍትሃት ሊፈታ ይገባል። በየቤቱ ጥግና ከቤተክርስቲያን ውጪ መቅበር የቤተክርስቲያን ሥርዓት አይደለም።

1.1.መ. ለቅሶ አለመድረስ

***የመረጃ አቀባይ ሥም*፣** አያሌው ተሾመ (አባ.2 ቀ.22)

***ቃለመጠይቅ* የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 09/05/2006

*ጥያቄ፣ከአንድ ሰው ለቅሶ አለመድረስ ተጎጅን ምን ይሰማዋል?*

1. ያኮራርፋል። አንተ ወንድሜ ነህ እኔ ስሞት መጥቶ ‹‹አየ ጉድ›› ካላለህ ሆድ ያስቀይማል። ‹‹ከእኛ ለቅሶ ሳይመጡ የቀሩ ምን አባታቸው ሁነው ነው?›› ይባላል። ያስከፋል። ‹‹እንዴት ያለ ወንድም ሲሞት መጥቶ ከደጃችን ያልደረሰ ምን ጠብ አለን? ምንድን ነው የጠፋነው? ያስብላል፤ያቀያይማል። ከዚህ የኳሳ ከየኳሳ ማዶ ጎጃም ድረስ እንኽዳለን ጉልበት ያለን ሰዎች። አንደኛ ወገኞቸን ነው። ሁለተኛ ከዚህ ዓለም ሲለይ ወንድሞቻችን ቅር ይላቸዋል። ከዚህ አገርም ደግሞ ትናንት በዕለቱ ቢቀር ዛሬ ማልዳ ከቀብሩ መድረስ አለበት። ዛሬ ቢቀር በቀጠሮው ቀን መድረስ አለበተ። በቀጠሮው እንኳን ሳይችል ቢቀር ከቤት መጥቶ ይደርሳል። ያቀያይማላ።

*ጥያቄ፣ ከዚህ አገር ከገበያ ላይ ለቅሶ አለ?*

2. አየ ጋይንት ላይ አለ። ከዚህ የቅዳሜ ለቅሶ ነውር ነው። ነገ ቅዳሜ ገበያ ነው። ለቅሶ ላድርግ ካለ በዕለት ቀብር ነው ለቅሶ ይደረጋል። የዕለት ቀብር ከሆነ፡ ቀጠሮ ቅዳሜ ገበያ አይደረግም። አሁን ዛሬ ሰው ይሞትና ነገ ቅዳሜ አይደል፣ ‹‹አይ አይሆንልህም አንተ ወይ ክረምቱ ይገባና ዝም ብለህ የዕለት ቅጠረው›› ይባላል። እንድታላቅሱኝ እያለ ይጠራል። ሲጠራ ደሞ ‹‹እከሌ ተጎድቷልና አላቅሱን ተብላችኋል›› ተብሎ ነው የሚጠራ። ገበያ ያልቸገረው መጥቶ ያላቅሳል እንጂ ከገበያ ላይ ለቅሶ የለም።

***የመረጃ አቀባይ ሥም*፣** ቀኝ ጌታ ዜናዊ ስቡህ (አባ.2 ቁ.1)

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን*፣** እ.ኢ.አ. 10/09/2004

ጥያቄ፣ በዚህ አካባቢ ከለቅሶ አለመድረስ ምን ስሜት ይፈጥራል?

1. በአካባቢያችን ከአንድ ሰው ለቅሶ አለመድረስ ከጉዳተኛው ጋር በአጋጣሚ በተገናኙ ጊዜ በጣም ያሳፍራል። እኔ በችግር ምክንያት በዕለት ከለቅሶ ሳልደርስ ቀርቼ ‹‹ነገ ዛሬ›› ስል የተጎዳውን ሰው እንደማገኝት የሚያሳፍረኝ ነገር የለም። በተለይ አቀረብሽ ከሆነ መግቢያ ነው የሚጠፋ። ለተጎዳውም ሰው ከዚህ የበለጠ ቂም የሚይዝበት ነገር የለም። መከራ ለሁሉም ስለማይቀር የተጎዳው ሰው ቂም በሆዱ ቋጥሮ ቆይቶ ብድሩን ይመልሳል እንጂ ‹‹እንዲህ አደረክኝ ወይም በደልከኝ›› ብሎ አይወቅስም።

2. እንዲያውም ወደቆማ አየር የሚነዳ ኩኒናር ልዥ የነበረው በደርግ ጊዜ ኤርትራ ሂዶ ሲዋጋ ጀቱ ተምትቶ ልገፍ ሙቶ ሩቅ ላሉት ዘመዶቹ ጥናው ይደርሳል። ቀደም ሲል ኩብኩባ (ታዳጊ) ልገፍ ከሞተበት ዘመዱ ለካ የኩኒናሩ አባት ሳይደርስ በመቅረቱ ተቀይሟል። ዘመዶቹ እያዘኑ ወደለቅሶው ለባብሰው ሲወጡ እሱ ላሞቹን ያግጣል። አንዱ ወንድሙ ‹‹ያያ እገሌ ልዥ እኮ ኩኒናሩ ነው የሞተ እልቅሶ እንህድ እንጂ›› ቢለው ‹‹ለእኔም ልገፍ ኩኒናሬ ነው›› ብሎ በመቀየሙ ብድር እየመለሰ መሆኑን ነገረው ብለው አጫውተውኛል። እንዲኸው ነው ብድር ምለሳ።

***የመረጃ አቀባይ ሥም*፣** ደጀን አመኑ (አባ.2 ቁ.17)

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን*፣** እ.ኢ.አ. 15/06/2005

ABABA UNIVERSITY LIBRARIES P. O. BOX 1176 ADDIS ABABA, ETHIOPIA

1. ስማዳና ጋይንት በለቅሶ አደራረስ ይለያያል፡፡ ስማዳ እኔ በነበርኩበት ጊዜ ተወልጄ ያደኩት ከዚያው ነው፡፡ ስማዳ ሰው ከገበያ ላይ ለቅሶ ደረሰ ማለት እንደበደል ነው የሚቆጠረው፡፡ እንኳን ከገበያ ላይ ይቅርና ሚቹ ከተቀበረበት ቤተክርስቲያን ላይ ራሱ ደራሹ ሰውየ የሚመጣበት አይታወቅም ለሽምግልና ይምጣ ለሌላ ጉዳይ ይምጣ አይታወቅም ከቀናቀኑ ውጭ ከዚያ ቢገናኘው ከቤት መጥቶ ካልደረሰ እንደንቀት እንጂ እንደደረሰው አይቆጠርም፡፡

2. ደሞ ጋይንት ላይ የሚበረታታው ነገር ቢኖር የትም ቦታ ላይ ማስተዛዘን ይቻላል፡፡ ታች ጋይንትም ሰርቻለሁ ላይ ጋይንትም እየሰራሁ ነው ሀዘንተኞቹ የሚቀመጡበት ቦታ አለ፡፡ ሀዘንተኞች ቅዳሜ ቀን ወይም በገበያ ቀን ሂደው ቁጭ ነው፡፡ ‹‹መጥተውልናል›› እያለ ሰው በቅርበት እየደረሰ ገበያውን እየገበየ ይሄዳል፡፡ ይኸን ጥሩ ነገር አይቻለሁ፡፡

3. ስማዳ ላይ ግን የስማዳ ዋና ከተማ አለ፣ ሌሎችም ገበያዎች አሉ እነ የኳሳ አሉ፡፡ ከእነዚህ ገበያዎች ላይ አጋጣሚ በመንገድ የሀዘን ለብሶ ስለሚሄድ ከገጠመው ‹‹ምን ሆንክ?›› ይለዋል፡፡ ወይም ሴትዮዋ የሞተበት ቤተሰብ አዘን ለብሶ ይወጣል፡፡ የሰማም ያልሰማም ከለቅሶው ያልተገኘ አካል ‹‹ምን ሆንክ? ብሎ ይጠይቃል፡፡ ጠይቆ ‹‹ እንዲያው ተጎዳሀ ›› ምናምን ይላል ድንገት ስላገኘው፡፡ ግን እንደጠየቀው አይቆጠርም፡፡ ሲያየው ‹‹ሳይጠይቀኝ ቀረ ወይም ሳትጠይቀኝ ቀረች›› እንዳይባል ትጠይቃለች እንጂ፣ አስባ በሳልስት ወይም በሳምን ከቤት መሄድ አለባት፡፡ ስማዳ ላይ ይኸ የተለየ ባሕሪ ነው፡፡ ከቤት ካልመጣ ወይም በቀጠሮው ካልመጣ የተለየ ነገር አለ አስቸጋሪ ነው፡፡

4. ትንሽ እንደዚህ የሚመሳሰለው ምንድን ነው፣ የሚች ቤተሰብ የሀዘን ልብስ እንደለበሱ ሰሞን ሌላ ሰው ከሞተ ለቅሶ ላይ ማለት ነው ኸዚያ ለቅሶ ላይ የራሳቸው አስመስለው ነው ለባብሰው የሚወጡ የሀዘን ልብሱን፣ የለቅሶ መድረሻ አጋጣሚ ያች ናት፡፡ ከቤት ውጭ መድረሻ አጋጣሚ ያ ነው፡፡ በቀረ አስከሬን ከተቀበረበት ቤተክርስቲያን ወይ በሳልስት ወይ በሰላሳው ወይ ባርባው፣ ወይ በሰማንያው ሚች በሚፈታበት እለት ስራየ ተብሎ ተሂዶ እዚያ ይደረሳል፡፡ ከዚያ ውጭ ከገበያ ላይ አይደረስም፡፡ ታች ጋይንትና ነፋስ መውጫ ወይም ላይ ጋይንት ላይ ከገበያ መድረስ አይቻለሁ፡፡

*ጥያቄ፣ አሁን ከዚህ ከገበያው ላይ የለቅሶው ሥርዓት እየተከናወነ ነው የሚገናኙት ወይስ ቁጭ ካሉበት ነው ሂደው የሚገናኙ?*

5. ተጎጅ ክፍል ቁጭ ብለዋል፤የሚደርስ ሰው ሶስትም ሁለትም እየሆነ ነው የሚሄድ። ደመቅ ያለ ነገር ከሆነ ብድግ ብለው ይቀበሉታል። አንድና ሁለት ሰው ከሆነ ቁጭ ብለው ይቀበሉታል፤ ያ ሰውየም ‹‹ፊቱን በጋቢው ጫፍ ግራና ቀኝ ነካ ነካ አድርጎ በጎን ሂዶ ቁጭ ይላል። እየዞሩ ማልቀስና ፉከራ ምናምን የለም። ከተገናኘና ትንሽ ከጎናቸው ቁጭ ብሎ ከቆየ በኋላ ‹‹ተጎዳህ፣ ተጎዳሽ እግዜር ያስችላችሁ›› ብሎ ተነስቶ ጭልጥ ነው።

**1.1.1. በዕለት ለቅሶ እስከ ቀብር ድረስ የሚፈጸሙ ሀይማኖታዊና ዓለማዊ ሥርዓቶች**

**1.1.1.1. በዕለት ለቅሶ እስከቀብር ድረስ የሚከወኑ ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች ክወና**

**1.1.1.1.1. ግንዘትና ከፈን**

***የመረጃ አቀባይ ሥም፣*** ቀኝ ጌታ ዜናዊ ስቡሕ (አባ.2፣ቁ.1)

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣*** እ.ኢ.አ. 6/09/2004

*ጥያቄ፣ አንድ ሰው እንደሞተ ወዲያውኑ ምን ምን ይደረጋል?*

1. ሰው ሲሞት ይወራጫል። አፉም አ... እንዳለ ይቀራል። ከከረረ በኋለ እሽ ስለማይል ወዲያውኑ በትኩሱ አፉን መዝጋት ዐይኑ ፍጥጥ እንዳይል ማጋጠም እጆችንም ማስተካከል ያስፈልጋል። ቆይ እንግዲህ ኸዚህ ላይ እንጫወትና ሬሳ ሸሽ፣ ልጋግ አለ፤ ሽንት አለ፤ ነፍስ ስትወጣ ሰገራ ይወጣል፣ ጭንቀት ስላለ። እንግዲህ ንጽህና አጣ ማለት ነው። እኛ ኦሪትን የተቀብልነ ክርስቶስ ሲወለድ አንድ ሺህ ዘመን ሲቀረው ነው። ማንም ማንም ሳያውቀው ሌላው ሀገር ኢትዮጵያና ኢየሩሳሌም ብቻ ናቸው ኦሪትን የተቀበሉ። ከዚህም አያይዞ እስራኤላውያን በምኒልክ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል። ማሰናዳቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። ትውፊት ቅብብሎሽ ነው። ቀኖና ሥርዓት ነው። ዶግማ ሀይማኖት ነው። ከያዕይቆብ ጀምሮ እየተቀባበልነው የመጣ ነው። ሕዝቡ በኦሪቱ ስለለመደው አብዛኛው የሰሜኑ ክፍል በዚያው እንዳለ ነው የያዘው። በኦሪት ያለ ነው። በእነሱ ዘመን ሬሳ የነካ እስከ ሰባት ቀን ርኩስ ነው። እኛ ግን ያንን ርኩስነት ክርስቶስ

ስላጠፋው ተጠምቀን ደሙን ጠጥተን ስጋውን በልተን ስላለን ትንሳኤ ዘለክብር ያለን ስለሆነ እንዲውም ይሳሙት ይላል።

*ጥያቄ፣ አካል ከተስተካከለ በኋላ ምን ይደረጋል?*

2. በንጹህ ውሃ በቅጠልና በምናምን አድርገው ያጥቡታል። ቆሻሻውን ለማንጻት። የምዕመናኑ ማጣቢያ ለንጽህና ነው። ለግንዘት እንዲበቃ ግን በተጸለየበት ውሃ ይታጠባል። ይህ ዝምብሎ ሳይሆን ከጥንት ከሀዋርያት ዘመን ተያይዞ የመጣ ነው። (መጽሐፍ ቅዱሳቸውን አቀበሉኝና የሐዋ.9፣38 እንዳነብ አዘዙኝ)፡፤

«በኢዮጴም ጣቢታ የሚሉአት አንዲት ደቀ መዝሙር ነበረች፤ ትርጓሜውም ዶርቃ ማለት ነው፤ እርስዋም መልካም ነገር የሞላባት ምጽዋትም የምታደርግ ነበረች። በዚያም ወራት ታመመችና ሞተች፤አጥበውም በሰገነት አኖሩአት።» ይኸ ህጥበት በሀዋርት ጊዜ የነበረ መሆኑን ያሳያል።

*ጥያቄ፣ ሬሳው ከታጠበ በኋላ ምን ይደረጋል?*

3. ሬሳው ከተሰናዳ ንጽሕናውን እንዲጠብቅ ከታጠበ፣ እንዳይሸት ወይም የመልካም ምግባር ምሳሌ የሆነውም ሽቶ ተርከፍክፎ ከተዘጋጀ በኋላ፣ በአዲስ ጨርቅ ይገነዛል። ግንዘት እንደየማይረጉ ይለያያል። ቄስ ልብሱን አያወልቅም። «መስቀሌን ተሸክሞ ያልተከተለኝ ሊያገለግለኝ አይችልም» ባለው መሰረት፣ እጆቹንም በትዕምርተ መስቀል አጣምሮ ነው የሚገነዘ። መግነዙ ከላይ አስከታች ድረስ ሰባት ነው የሚሆን። በሶስት ክር ይገነዛል። አስራ ሁለት መብራት ይበራለታል።

*ጥያቄ፣ ሰባት በቤተክርስቲን ምንን ያመለክታል?*

4. ሰባትማ ብዙ ነው ትርጉሙ። ሰባት መላክ አለ። ሰባት በእብራውያን ፍጹም ማብቂያ ነው። እሁድ ጀምሮ ቅዳሜ በሰባተኛው ቀን አይደል ያረፈ. ፍጹም ማለት ነው። ዓለምን ስድስት ቀን ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን አረፈባት አይደል ማብቂያ ማለት ነው። አንድ ሱባኤ ሲባል ደሞ ያው ሰባት ቀን ነው። ሰው ማለት ምንድን ነው? ሰባት ነገር ያለው ማለት ነው። ሰባት ባህርያት። ከዚያ በላይ የለውም።

5. መነኩሴ ሲገነዝ እንዲህ አድርጎ ነው (እጆቻቸውን ከአይኖቻቸው ላይ ጭነው አሳዩኝ)፡፡ «የዚህን ዓለም ነገር አልሰራሁትም አላየሁትም›› ለማለት ነው፡፡ መብራቱና መግነዙ ለቄሱ እንደተደረገው ነው፡፡

ዲያቆን ሲሆን ሲላላኩ መኖራቸውን ለማሳየት የሚገነዙት እንዲህ አድርገው ነው (የእጆቻቸውን ክንዶች ከቀበቷቸው መዋያ ላይ አድርገው ወደ ትከሻዎቻቸው በማጠፍ አሳዩኝ)፡፡ የሚበራለት መብራት ሰባት ሲሆን ክሩም ሁለት ነው፡፡

ሕዝባዊ ሲሆን አውራ ጣቶቹ ተገጥመው ታስረው እጆቹ ከብልቱ ላይ እንዲያርፉ ይደረጋል፡፡ ብዙ ተባዙ ብለህ የሰጠኸንን ሰርተንበታል ለማለት ነው፡፡ በድኑ የሚታሰረው ባንድ ክር ሲሆን የሚበራው መብራት አራት ነው፡፡ ይኸ ሁሉ ትውፊት እንግዲህ መጻፍ ቅዱሳዊ እንጂ ዝም ብሎ የመጣ አይደለም፡፡ ለምሳሌ ግንዘትን (የሐ.11፣ 43፡44) ብናይ አሁን የሚደረገው ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረበት ዘመን ተግባራዊ ሲያደረግ የነበረው ነው፡፡ ይህንንም ብሎ በታላቅ ድምጽ፤- «አልኣዛር ሆይ ወደ ውጭ ና ብሎ ጮኸ፡፡ የሞተውም እጆቹና እግሮቹ በመግነዝ እንደተገነዙ ወጣ፤ ፊቱም በጨርቅ እንደተጠመጠመ ነበረ፡፡» ኢየሱስ ክርስቶስ የተገነዘውና የተቀበረውም በዚሁ መንገድ ነው፡፡

*ጥያቄ፣ መከፈኛ ጨርቁስ ምንድን ነው?*

6. ኢየሱስ ክርስቶስ ከተልባ እግር በተሰራ የተለየ ጨርቅ ነው የተከፈኑ፡፡ አንዲት ያልገባችኝና ጠይቄ ያልተረዳኋት ያገራችን ሰው በሰሌን ነው የሚቀበር፡፡ አንዳንዱ በገቦንዲም ይቀበራል፡፡ እነዚህ ሁለቱ ምንድን እንደሆኑ እነዚህን አላወቅኋቸውም፡፡ በጨርቅ መከፈኑ ግን ከኢየሱስ ክርስቶስ የመጣ ነው፡፡ በእኛም ባገራችን ሰሌን በላይ ይደረግ እንጂ ጨርቅ ከውስጥ ተደርጎ ይከፈናል፡፡ መነሻው ካባቶቻችን የመጣው ከእስራኤል አይደል? ከዚያ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ እንዲያው የሰሌኑ ግን በሆሳዕና ሰሌን በእጃችን እንይዛለን፡፡ ያ ሰሌን አብርሃም ይስሃቅን፣ ይስሃቅ ያዕቆብን፣ በወለዱ ጊዜ እስራኤል ከግብጽ በወጡ ጊዜ ዮዲት ሆሎፎርኒስን ገድላ እስራኤልን ነጻ ባወጣች ጊዜ ሰሌን እየያዙ አመስግነዋል የደስታ፡፡ ይኸ ግን መቃብሩ ስለሆነ አላገኘሁትም፡፡

ለእንግዲኸው እጠይቃለሁ፡፡ መቼስ አዋቂ መባል መከራ አይደል፡፡ (ሳቅ) መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ገልጠው አንድ ቦታ ላይ በእጃቸው አመልክተው እንዳነበው አቀበሉኝ) የእስራኤል ባህላቸው ያው ከጥንት ጀምሮ አስቲ አንብበው እሱም ሂዶ የጌታችንን ስጋ ወሰደ፡፡ ቀድሞ በሌሊት ወደ ጌታችን ኢየሱስ ሂዶ የነበረው ኒቆዲሞስ መጣ፡፡ ቀድቶም የሚቀቡበት መቶ ወቄት የከርቤና የዘይት ሽቱ ቅልቅል አመጣ፡፡ እንደ አይሁድ አገናነዝ ስርዓትም የጌታችን የእየሱስ ስጋ ወስደው ከሽቱ ጋር በበፍታ (በፍታ የሚባለው ግምጃ ነው፡፡ በትሃ የመሰለ ነጭ ልብስ) ገነዙት፡፡ በዚህም በተሰቀለበት ቦታ የአትክልት ስፍራ ነበር፡፡ (አስቆሙኝ የሚፈለገው በፍታው ነው) ከኢየሱስ መቃብር አግኝተውታል፡፡ እንግዲህ ከዚያ የተያያዘ አይሁድ ሲያደርጉት የነበረው ተያይዞ የመጣ ልማድ ነው፡፡ እንግዲህ እኛ መነሻችን ከዚያው ነው፡፡ ይህን በሰሌንና በቁረንጮ የሚደረገውን አላገኘሁትም፡፡

*ጥያቄ፣ ልብሱ ውሃ ያልነካው አዲስ አቡጀዲ ወይም ከፈትል የተሰራ ልብስ መሆኑስ ከምን ጋር የተያያዘ ነው?*

7. ጌታችን የተከፈነው ማንም ባልተጠቀመበት ነው፡፡ በአዲስ የመገነዙ ነገር ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በገጠር ግን በተጠቀሙበት ጋቢያቸውም ይከፍኗቸዋል፡፡ አሁን ደግሞ ለምሳሌ ካህናት የለበሱትን ልብሳቸውን ሳያወልቁ ነው የሚቀበሩ፡፡ ሱሪያቸውንና እጀ ጠባባቸውን እንደለበሱ ነው የሚቀበሩ ይላል፡፡ (የቤተ ክህነቱን) ካህን ራቁቱን አይታይም፡፡ ታሞ ለበሽታ ሊመረመር ካልሆነ በስተቀር ሰውነቱ አይገለጥም፡፡ ለምእመናኑም ቢሆን ሬሳ ክቡር ስለሆነ ንጽህና ያለው ነገር ቢደረግለት ጥሩ ነው፡፡ ንጹህ መልበሱ ስለዚህ ነው፡፡
8. ወደ ዝርዝሩ እንግባና ሬሳ እንዴት ነው የሚሰናዳው?

**የመረጃ አቀባይ ሥም**፣ አቶ ገበያው ዓለሜ (አባ.2፣ቁ.11)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን**፣ እ.ኢ.አ. 6/09/2004

*ጥያቄ፣ በዚህ አካባቢ አንድ ሰው ነፍሱ እንዴት ነው የምታሰናዱት?*

1. ሬሳ የሚዘጋጀው ወዲያው እንደሞተ ነው፡፡ ዐይኑ እንደፈጠጠ አፉ እንደተከፈተ እንዳይቀር ዐይኑ እንዲህ እንዲህ ይደረጋል (በእጆቻቸው ያላይኛውን የአይናቸውን ሽፋን

ወደ ታች በማልበስ አፉን ከንፈርና ከንፈራቸውን በእጆቻቸው እያገናኙ) የእጆቹ አውራ ጣቶች ይታሰራሉ (የእጆቻቸውን መዳፎች በማነካካት አውራ ጣቶቻቸውን አስተካክለው እያሳዩ)፣ ከታች የእግር አውራ ጣቶችም ይታሰራሉ። ተዘርግቶ ተንጋሎ ይቀመጣል። ከውጭ የሚገባ ሰው እንዳያየው በጋቢም ሆነ በሌላ ነገር መጋረጃ ከለል ይደረጋል። ከዚያ በውሃ ይታጠብና መከፈኛ አቡጀዴም ከሆነ ወይም ሰሌንም ከሆነ ሬሳው ተጠቅልሎ ከሰባት ላይ ይታሰራል። ከዚያ ሳጥን ካለ ከሳጥን ይከተታል።

***የመረጃ አቀባይ ሥም*፣ አቶ ትዕዛዙ አያሌው (አባ.2፣ቁ.20)**

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን*፣ እ.ኢ.አ. 7/06/2005**

*ጥያቄ፣ በዚህ አካባቢ እሬሳ እንዴት ነው የሚሰናዳው?*

1. ነፍስ እንደወጣ በአካባቢው ካለ የቅርብ ሰው፣ ሲንፈራገጥ የተዛቡ እጆቹንና እግሮቹን ቀጥ እንዲሉ ያደረጋል። ሽታጠፉ ይገርና አይዘረጋም። እንዲያ ሲሆን ቋሚ ያሰደባል። «ከዋኝ የለለው» ያስብላል። ዐይኖቹ የፈጠጡት ይከደናሉ። አፉ የተከፈተው ግጥም እንዲል ይደረጋል። ከዚያ ወዲያ እንደሞተበት ሰሀት ለቀብር የሚደርስ ተሆነ ወዲያው በዕለት እኚ በቅጠል እየታሸ ይታጠባል። የሚያድር ተሆነ ሊከፈን ሲል ነው የሚታጠብ። የነብስ አባት ደርሶ ተሆነ ወይም ባካባቢው ያለ ቄስ ጦለት ባደረሰበት ጠበል እርጫ እርጫ ይደረግና በአዲስ ልብስ ተጠቅልሎ ሽሳባት ቦታ ላይ በክር እየታሰረ ይከፈናል። ሰው እንዳያየው ይጋረድና እስቲወጣ ድረስ ይለቀሳል።

***የመረጃ አቀባይ ሥም*፣ አቶ ጸጋዬ ጀንበሬ (አባ.2፣ቁ.19)**

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን*፣ እ.ኢ.አ. 10/09/2004**

*ጥያቄ፣በደብረታቦር ዙሪያ አንድ ሰው ነፍሱ እንደወጣ እንዴት ነው የሚሰናዳው?*

1.ብላታ ቀዲሙ እንደገለጹት መጀመሪያ እጅና እግሮቹ ቀጥ ብለው ይታሰራሉ። ከዚያ በኋላ ይታጠባል። የሚታጠበው እንዴት ነው መቸም የሰው ልጅ ሕይወቱ ካለፈ በኋላ የመበላሸት ጸባይ ይመጣል። ስለዚህ ደንበኛ ከፋኞች ይገባሉ ውሃ ተሙቆ በደንብ ታጥቦ ነው ወደ ሰሌን የሚገባው። ንጽህናውን ለመጠበቅ ነው። ለምሳሌ እኔ እራሴ ባለሙያ ነኝ። በአካባቢየ ሰው ከሞተ እገባለሁ፤ እከፍናለሁ፤ አሳናዳለሁ። አንዳንድ ሰወች አሉ። እያወቁም

ሰውነታቸው ይሰቀቃል፡፡ እኔ ግን የኛው አካል ወገናችን እስከሆነ ድረስ ምንም አይሰማኝም፤ የምጠራጠር ከሆነ ግላብ እጠቀማለሁ፡፡ እና እጥባት የመጣው ከዚህ ነው፡፡ ካደረ ሰው ፍርስ ነው፡፡ ካህናትንም ያሳቅቃል፣ ካካባቢም ላለ ሰው እንደሚያሳቅቅ ሁሉ ለዚያ ነው የሚታጠበው፡፡

**የመረጃ አቀባይ** ***ሥም***፣ አባ አቸነፍ እንግዳ (አባ.2 ቁ.12)

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን***፣ እ.ኢ.አ. 29/09/2004

*ጥያቄ፣ አንድ ሰው ነበሱ ሲወጣ መጀመሪያ ምንድን ነው የሚደረገው?*

1. አባ አቸነፍ፣ በመጀመሪያ ነብሱ ሲወጣ አውራ ጣትና አውራ ጣቶቹ የእግሮቹ ይታሰራሉ፡፡ ቀጥሎ የእጆቹ ይታሰራሉ፡፡ ይኽ ተደርጎ የነብስ አባት ይደርሳል፡፡ ነብሱ ሳይወጣ በፊት ደርሶ እንደሁ እሱ ያስረዋል፡፡ ነብሱ ከወጣ ከደረሰ እኛ አስረን እንጠራዋለን ይመጣል፡፡ ከዚያ ወዲያ መከፈኛ ጨርቅና ነጣላ ይገዛል፡፡ ከሰሌኗ ላይ ያች ትኀዘኀዛለይ በዚያ ይከፈናል፡፡ ወዲያ ነብሱ እንደ ወጣ ለሰው ፊት እንዲቀርብ ሰውነቱ የሰነበተው እንዲያ ያለው ይተጣጠባል፡፡ ሰውነቱ ለውጦ እንደሆ እንዳይሸት ነው የሚታጠብ፡፡ በኂላ ቄስ ሲከፍን በቅጠል እንደገና ያጥበዋል፡፡ እኔ ከደረስኩ መጀመሪያ አዘንተኛው ሙልጭ አርጎ ያጥበዋል፡፡ ሳያጥብ አያቆይም፡፡ እሚከፍነው ግን ቄስ ነው፡፡

**የመረጃ አቀባይ** ***ሥም***፣ አቶ አራጋው ታረቀኝ (አባ.2 ቁ.32)

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን***፣ እ.ኢ.አ. 05/09/2004

*ጥያቄ፣ በዚህ አካባቢ ሰው ነፍሱ ሲወጣ እንዴት ነው የምታማውቱት?*

1. ያው ሰው ሲደክም ትልቅ ከሆነ ልገሮቹ ይሰበሳበሉ፡፡ እህት ወንድም እንደዚሁ ቁርጠኛ ዘመድ ተሰባስቦ ለአዝን የሚሆን እህል ውሃ ያሰናዳል፡፡ ነብስ ሲወጣ በሰል ያሉ ሰወይ ይቀሩና ሌላውን ወደውጭ አስወጥተው መጋረጃ ይጋረድና እጅና እግሩ እንዳይዛነፍ ቀጥ አርገው አውራ ጣቶቹን ያስራሉ፡፡ አፉንም አፍንጫውንም ይጠራርጋሉ፡፡ አይኖቹንና አፉን ይገጥማሉ፡፡ ከዚያ የዕለት ውሃ እያፈሰሱ በዝግጣ ቅጠል እያሹ ያጥቡታል፡፡ ቆሻሻ ነገር ስለማይጠፋ እሱን ለማስወገድ ነው፡፡ ኸዚያ ወዲያ በአዲስ ጨርቅ ይጠቀለልና በላዩ ላይ ሰሌን ወይም ገንዲ ተደርቦ በቱቻ ገመድ ኸሰባት ቦታ ላይ ይገነዛል፡፡

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣ መሪጌታ ክፍለማርያም አለነ (አባ.2፣ቁ.2)**

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣ እ.ኢ.አ. 14/05/2006**

*ጥያቄ፣ የግንዘት ሥርዓት እንዴት ነው የሚከናወን?*

የግንዘት ሥርዓት እንደየማእረጉ በአራት ክፍል የሚፈጸም ነው፡፡

*ጥያቄ፣ በአራቱ ክፍሎች እንዴት እንደሆነ እስቲ ያብራሩልኝ?*

1. ግነዛ ላይ ሲገነዙ አራቱም ራሳቸውን የቻሉ ሥርዓቶች አሏቸው፡፡ የመነኮሳት ወይም የባህታውያን ከሆነ በጣቶቻቸው አይናቸውን ሸፍነው በአውራ ጣቶቻቸው ጆሮዎቻቸውን ይሸፍናሉ፡፡ ይህ ማለት በአይናችን የዚህን ዓለም ነገር አላየንበትም፣ በጆሯችን ደግሞ የዚህ ዓለም በነገር አልሰማንበትም የማለት ምሳሌ ነው፡፡ ይህ ይሁንና አሁን የእነዚህ ጸሎት በውስጥ ሥርዓት ላይ የካህናቱ ወይም የሊቃውንቱ በሥርዓት ላይ የምናደርገው አለ፡፡ ለሊቃውንተ ከሆነ ቅኔ ይደረጋል አሁን፡፡ ይኸ ውዳሴ ያሬድ የደረሰው የብቃት ማሳያ ነው፡፡ ቅኔ ሲደረግ አርአያም ተቁሞ ነው፡፡ ነቢያት ይቆማል፡፡ በዚህ ማህል እየገባ ለካህናት ብቻ የሚደረግ ይሆናል፡፡ ከካህናት መካከል መነኮሳት፣ ባሕታውያን ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ዲቆናትም ቢኖሩ በዚህ መልኩ ይሆናሉ፡፡

2. ሕዝባዊ ከሆነ ግን ቅድም ባልነው በመዋሲትና በቅዳሴው ሥርዓት ይውላል ከዚያ በኋላ ሥርዓቱ ይፈጸማል፡፡ ለአራቱ የማሕበረሰብ ክፍል ቢሆን ዘጠኙ ኪዳኖች ቋሚዎች ናቸው፡፡ በዘጠኙ ኪዳኖች መካከልም የሚገቡ ነገሮች አሉ፡፡ ወካይበ ናስተበቁ ልዩ ነው ራሱን የቻለ ሥርዓት ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች ለሁሉም ይገባሉ፡፡ ምስባክ በሰባቱ ምዕራፎች ሁሉ የሚሰበክ ነው፡፡ ከሰባቱ ምስባክ ተሰብኮ ዘጠኙ ኪዳን ባይደርስ ሶስቱ ኪዳን ቢደርስ ጸሎቱን አያጎድለውም፡፡

*ጥያቄ፣ ካህናት ሲገነዙስ እንዴት ነው?*

3. ካህናት ሲገነዙ እጃቸውን ትምህርተ መስቀል አድርገው ነው፡፡ ይህ በዓለም እግዚአብሔር በሰጣቸው ስልጣን ወንጌለ መንግስትን ሰብከው ህብረተሰቡን አስተምረው ክርስቶስ የተሰቀለበትን መስቀል በእጃቸው ይዘው ቡራኬ ላይ መኖራቸውን ሲያመለክት

እጃቸወንት በትዕምርተ መስቀል ላይ ያደርጋሉ። ዲቆናት ሲገነዙ ደግሞ እጃቸውን ትክሻቸው ላይ ይጥላሉ አንገታቸው ላይ ያርፋል። ይህ መላእክት በተለየ አንቀጽ ላይ የእግዚአብሄር መልዕክተኞች እንደሆኑ እናገኛለን። ዲያቆናት ደግሞ የቤተክርስቲያን ተልዕኮ ፈጻሚ ቀዳሚ ዲያቆናት ናቸው። ቄሱ የሚልካቸው ዲያቆናትን ነው ። መምህሩ የሚልካቸው እነሱን ነው። ከዚያም ወርደው ታላቁን ምስጢር የሚሰውት ዲያቆናት ናቸው። ይህ መላካቸውን ሲያመለክት የመላዕክት ምሳሌ ናቸው ሲል እጃቸውን ወደላይ አድርገው ይገነዛሉ።

4. ሕዝባውያን እጃቸው ከሃፍረተ ሥጋቸው ላይ ነው የሚሆነው። እነሱ ደግሞ «በዚህ ዓለም አንተ በሰጠኸን አካል ሰርተናል፣ ይህን ዓለም አይተንበታል አሁን ደግሞ ይህን ዓለም ትተን ወደ አንተ መጥተናል» ሲሉ አካላቸውን ሸፍነው ወይም ደግሞ አዳም ከገነት በወጣ ጊዜ መጀመሪያ ራቁት መሆኑን ሲያውቅ በዕጸ በለስ ነው ሀፍረ ሥጋውን የሸፈነ። ይህ ማለት ፈጣሪውን ሲያይ ነው። ሟች ደግሞ አሁን በዚህ ዓለም ይኑር እንጂ ወደ ፈጣሪው እየሄደ ነው። በሚቀርብበት ጊዜ አስቸጋሪ ስለሆነ ወይም የአዳም ልዥ ስለሆነ እሱን ሸፍኖ ይቀርባል። የአራቱ ማሕበራዊ ቡድኖች ግንዘታቸው ይኸ ነው።

*ጥያቄ፣ አንድ ሰው ከመገነዙ በፊት ይታጠባል። ማነው የሚያጥበው፣ እንዴት ነው የሚታጠበው፣ የመታጠቡስ ምክንት ምንድን ነው?*

5. መታጠቡ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ነው። ቅዱስ ጴጥሮስ ጣቢታ የምትባል አገልጋይ ነበረች። ለእናቶች ውሃ እየቀዳች፣ ለአባቶች እየፈተለች እያገለገለች የነበረች ብላቴና ናት። በዚህ ላይ እንዳለች አረፈች። ስታርፍ እነዚህ ሰዎች ታገለግላቸው የነበሩት ተሰባስበው ጴጥሮስ የቅድስና አገልጋይ በመሆኑ ሙታንንና ድውያንን እየፈወሰ ገቢረ ተአምራት ማድረጉን ያዩ ሰዎች ሄደው «ይህች እየረዳችን የነበረች ብላቴና አርፋለች የሚሆነን አድርግ» ነው ያሉት። ወደእሱ ሲሄዱ ግን መጀመሪያ አጥበዋት ሸፍነዋት ነበር። ሄደና ይህች ብላቴና የእናንተ አገልጋይ መሆኗ ግልጽ ነው። እግዚአብሔር ደግሞ ቸር ነው። እናንተ ወደ ውጭ ውጡ አለ። ካስወጣ በኂላ ተንበርክኮ ጸለየ። ጸሎቱን ከፈጸመ በኂላ በአግዚአብሔር ስም ተነሽ አላት። ተነሳች ወስዶ ሰጣቸው።

6. ይህ ማለት መጀመሪያ ሰዎቹ አጥበዋታል ሥርዓት መሆኑ በዚህ ይታወቃል። ካጠቧት በኋላ ሽፈኗት ገነዟት ማለት ነው። ከገነዙ በኋላ ማንን ጠሩ ጴጥሮስን ጠሩ። ካህናት አስፈለጉ ማለት ነው። እንደኛ ሥርዓት ደግሞ መጀመሪያ በጣር ላይ ላለ ሕብረተሰብ መጀመሪያ ካህኑ ይጠራል። በትራሱ ተቀምጦ የሚያስፈልገውን ነገር ይጠይቃል። ስሥጋ ወደሙ የሚበቃ ከሆነ በጣር ላይ ቢሆንም ይቀበላል። ሰውየው ሲሞት ካህኑ ጸሎት ባደረሰበት ውሃ (ፀበል) ነው መታጠብ ያለበት። ከዚያ ይገነዛል። ግንዘቱ የሚካሄደው ሰው ካልጠፋ በቀር በወንዶች ነው። ሴት ምስጢር ስለማትችል አትገንዝም። ካህናት ስልጣን ስላላቸው ማንኛውንም ሰው መገነዝ ሲችሉ፣ መነኮሳትን የሚገንዙ መነኮሳት ናቸው። ሕዝባዊ መነኩሴንና ካህንን አይገንዝም። ስልጣን ስለሌለው

*ጥያቄ፣ ሬሳ ጸሎት በተደረሰበት ጸበል መጠመቁ ምን ያደርግለታል፤ ተምሳሌቱ ምንድን ነው?*

7. አሁን የካህናት ጸሎት ቅዱስ ያዕቆብ በሐዋ.5፣15 ላይ ተጽፏል። የታመመ ሰው ቢኖር የቤተክርስቲያን ካህናትን ይጥራ፣ ቀሳውስት መጥተው ይጸልዩለት፣ የቤተክርስቲን ጸሎት ድውይን ይፈውሳልና። ይህ ማለት አሁን ነብሱ ከስጋው ከተለየች በኋላ ሰውየውን ይፈውሰዋል ማለት አይደለም። ነገር ግን ይህ ሰው ቁስል ሆኖበታል። በሰባቱ በአስራሁለቱ የሚጸለይለት ኃጢያቱ እንዲወገድለት ነው። የፈወሱት የቤተክርስቲያን አገልጋዮች ናቸው። ያ ጸሎት ደግሞ ድውዩን ይፈውሰዋል። ፈውሱ በስጋ ብቻ ሳይሆን በነፍሱም ድውይነት ካለበት ድውይነቱን ያርቀዋል ማለት ነው። ለዚያ ነው በጸበል መታጠቡ። ከዚህ በኋላ መግነዝ ነው።

*ጥያቄ፣ግንዘቱ እንዴት ነው?*

8. መጀመሪያ የመነኮሳት ክብረ ልብሳቸውን ቆባቸው እንዳለ ይገነዙ ይላል። ይህ አሁን ቆባቸው አይውለቅ ያለበት ምክንቱ አክሊላቸው ዘውዳቸው፣ ምልክታቸው፣ መለዮአቸው ነው። ለክርስቶስ ምልክትነታቸው ይጠፋዋል ማለት አይደለም። ግን ይህ ክብራቸው በዓለም ብቻ ሳይሆን እስከ መቃብር ድረስ አብሯቸው እንደወረደ ለማጠየቅ ነው። የደፉት አክሊለ እሾህ ነው። የጀመረው ተራ ሰው ሳይሆን ባለቤቱ በዕለተ አርብ ነው

አክሊለ እሾሁን የደፋው፡፡ ስለሆነም እስከ መቃብር ድረስ አብሯቸው ዘልቋል፡፡ የዚህ ዓለም የሆነውን ነገር ይተውታል ቀሪ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ በአዲስ ልብስ ተገንዘው ወደ መቃብር ይወርዳሉ፡፡ ይህ ዓለም ጨለማና ብርሃን የሚፈራረቁበት ነው፡፡ ከዚህ በኋላ የሚሄዱበት ግን አዲስ ዓለም ነው፡፡ ያ ማለት ገነት ማለት ነው፡፡ እኛ እኮ አዲስ ዓመተ ምህርት ስናከብር አዲስ የባሕል ልብስ ለብሰን ነው የምናከብር፡፡ ወደ አዲስ ዓለም ወደ ብርሃን ዓለም እየሄደ ስለሆነ ቤትክርስቲያን አዲስ ልብስ አልብሳ ትሸኛቸዋለች፡፡ ውሃ ያልነካው ልብስ ማለት ያለም ነገር ያልነካው ማለት ነው፡፡

*ጥያቄ፣ ሕዝባዊ የምንለው ልብሱን አውልቆ በአዲስ ልብስ ነው፡፡ ካህናቱስ?*

9. ካሕናት መስቀላቸው አለ፡፡ በዚህ ዓለም ስናያቸው እና ከስጋና ከደም ጋር የተዋሃዱ ወይም ከሰባቱ ባህርያት ጋር ያሉ ናቸው፡፡ ለየት የሚያደርጋቸው ረቂቅ ስልጣናቸውና መስቀላቸው ነው፡፡ እግዚአብሔር የሰጣቸው ስልጣን ረቂቅ ነው፡፡ የስልጣናቸው ምልክት ሁኖ በግልጽ የምናየው በእጃቸው በያዙት መስቀል ነው፡፡ ያ ስልጣን ደግሞ ከተራ ሰው ሳይሆን የተሰጣቸው ከባለቤቱ ነው፡፡ መጀመሪያ ለጴጥሮስ ከዚያ ሲወርድ ሲዋረድ ከአሁኑ ደርሷል፡፡ ከዚህ ዓለም ወጥታችሁ ሕዝበ ክርስቲያንን አስተምራችሁ፣ ሰብካችሁ የእኔ አድርጋችኋል፡፡ አሁን ደግሞ ወደ እኔ ስትመጡ መስቀላችሁን ይዛችኋል፡፡ መስቀሌን ያልያዘ ለእኔ ሊሆን አይገባም ይላል እራሱ፡፡ መስቀል በቃሉ የምናየው ምልክት ማለት ይሁን እንጂ፣ ውስጠ ሚስጢሩ መከራ ማለት ነው፡፡ መጀመሪያ በእጃቸው ትእምርተ መስቀል ያደርጋሉ፡፡ ይህ አንድ ምልክታቸው ነው፡፡ ሁለተኛም ደግሞ ያን መስቀላቸውን ይዘው ይሄዳሉ፡፡

*ጥያቄ፣ ልብሳቸውን ያወልቃሉ?*

ልብሳቸው ይወልቃል፡፡ የቤተክርስቲን ካባቸው ክብራቸው እንዳለ ይቀበራሉ፡፡ ተራ ልብሳቸው ግን ይወልቃል፡፡ ልብሱ መለዮአቸው ነው፡፡

### 1.1.1.1.2. የፍትሀት ጸሎት

**የመረጃ አቀባይ *ሥም*፣ ቀኝ ጌታ ዜናዊ ስቡሕ (አባ.2፣ቁ.1)**
**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣ እ.ኢ.አ. 6/09/2004**

1. ጸሎተ ፍትሃት ለሀጢያተኞች ሀጢያታቸው እንዲታጠብላቸው ያደርጋል፡፡ ለእነዚህ ደግሞ ለደጋጎቹ ከክብር ላይ ክብር እንዲጨምሩ፣ ኮከብ እንደሆኑ ጨረቃ እንዲሆኑ፣ ጨረቃ እንደሆኑ ፀሀይ እንዲሆኑ ከክብር ላይ ክብር ይጨምርላቸዋል፡፡ እኛ ‹‹ማራቸው ማራቸው›› እያልነ ወደፈጣሪ ጸሎት እናቀርባለን፡፡ እነሱ ደሞ በአጸደ ነፍስ ሁነው ሲያበቁ ‹‹በሀጢያት እንዳሉ እንዳትጠራቸው፤ ለንስሃ አብቃቸው፤ ለሥጋ ወደሙ አልበቁ እንደሁ ለሥጋ ወደሙ እንዲበቁ፤‹‹በህጻንነታቸው አትቅሰፋቸው›› እያሉ ተዝካራቸውን ለሚያደርጉቱ፣ መታሰቢቸውን ለሚያደርጉቱ ህያዋን ይለምኑላቸዋል፡፡ (መጽሐፍ ቅዱሳቸውን አቀበሉኝና ሄኖክ.12፣34 ን እንዳነብ አዘዙኝ)፡፡ ‹‹በነዚህ ወራቶች በሰማይ የሚኖሩ ጻድቃን ባንድ ቃል ሁነው ተባብረው ያመሰግናሉ፤ ለሰው ፈጽመው ይለምናሉ፤ ፈጣሪያቸውንም ፈጽመው ያመሰግናሉ፡፡››

*ጥያቄ፣ ፍትሃት የሚፈታው ከስንት ዓመት በላይ ላለ ነው?*

2. እንግዲህ ከሰባት ዓመት በላይ ላሉ ነው፡፡ ሕጻናትም ቢሆኑ መቃብራቸው ይባረክላቸዋል፡፡ ነገር ግን ፍትሃቱ ከሰባት ዓመት በላይ ነው፡፡ የሕጻናት ፍታት የሚባል አለ ከ7-20 ዓመት ላሉት፡፡ የወጣት ፍታት አለ፡፡ ከዚያ በላይ የጎልማሳና የሽማግሌዎች ፍታት አለ፡፡

*ጥያቄ፣ከሰባት ዓመት በታች ያሉ ሕጻናት የማይፈቱት ለምንድን ነው?*

3. ዓዕምሯቸው ገና አልበሰለም ለኃጢያትም አልተጋለጡም፡፡ ሕጻን ስለሆኑ ኃጢያት የለባቸውም ንጹህ ናቸው፡፡
4. በሌላ በኩል ራሳቸውን ለሚያጠፉ ሰዎች የፍትሃት ጸሎት እንዳይደረግላቸው ቤተክርስቲያን ደንግጋለች፡፡ ዱሮ የሰው ልጅ ሞትን አመጣ፡፡ ዛሬም የሰው ልጆች ሞትን በተለያየ መንገድ ጎትተው ያመጣሉ፡፡

ይኸውም ጽንስን በማስወረድ፣ የራሳቸውንም የልጆችንም ሕይወት ያጠፋሉ፡፡

በመታነቅ፣ መርዝ በመጠጣትና በተለያዩ ድርጊቶች ሕይወታቸውን ያሳልፋሉ፤ ከዚህም ሁሉ ጋር ሰዎች በተፈጥሮ ሕማምና ጦርነትን ከመሰለ በሰውነታቸው ላይ በሚደርስ አደጋ ሲሰቃዩ በራሳቸው ወይም በሌላው ሕይወታቸው

እንዲያልፍ የሚያደረጉም አሉ። ይህም ሁሉ በቅዱሳት መጻሕፍት የተከለከለና በቤተክርስቲያን የተወገዘ ነው፤ በዚህ አይነት አሟሟት ሕይወታቸውን የሚያጠፉ ሁሉ በሀይማኖት ትምህርት ተቀባይነት የላቸውም። በሞቱም ጊዜ በህግና በሥርዓት ኖረው በክብር ለሞቱ ሰዎች የሚፈጸመው የቤተክርስቲያን ጸሎተ ፍትሃት ሌላውም ስርዓት ሁሉ አይፈጸምላቸውም (2 ሳሙ.1፣1-10፤ማቴ. 27-30)።

5. ሳኦል ንጉሱ፣ እብራውያን ቢከቡትኝ ከገዛ ሰይፉ ላይ ወድቆ ሙቷል። ይሁዳ ታንቆ ነው የሞተ። እንደዚህ የሚያደርጉ ማለት ነው። አሁን ጥይት ጠጥቶ ታንቆ ምን ብሎ ለሚሞት ቤተክርስቲን ፍትሃት አታደርግም። ታንቆም ይሁን በሌላ ምክንያት ሕይወትን ማጥፋትን ቤተክርስቲያን በጣም በጣም ታወግዛለይ። በራስ ፍላጎት ልሙት ብሎ መሞትን ቤተክርስቲያን ትከለክላለች። ታስተምራለች፤ ሕግ ጥሶ ሲሞት ወደፍትሃት አይወሰድም። ክልከላማ ከሌለ ጦም ባደረ ጊዜ ሁሉም ያልቃልኝ።

*ጥያቄ፣ ይህን ለመከላከል ነው?*

6. ለዚህ ብቻ አይደለም። አሁን እርስዎ ቤተ አለዎት እንበል። ደክመው የሰሩት። አንድ ሰው መጥቶ ቢያፈርሰው ምን ይላሉ? ያልሰራውን ሲያፈርስ ቢሆን በጉልበት ባይሆን በህግ መጠየቅ አለ። ያልሰራውን የሰው ቤት ማፍረስ ወንጀል ነው አይደለም? ወንጀል ነው። (መጽሐፍ ቅዱሱን እንዳነብ ሰጡኝ) «ማንም የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ቅዱስ ነውና ያውም እናንተ ናችሁ» (1ቆ.3፣17)። ሚች እኮ ያንን ሰውነት አልፈጠረውም። ያልሰራውን? የሰራው እኮ እግዚአብሔር ነው። የእግዚአብሔርን ማደሪያ ያልሰራውን ሰውነቱን ቢያስፈርስ ወንጀል ነው። ባለቤቱ ቤቱን አፍርሶ ቢፈልግ ሲያድሰው፣ ቢፈልግ ሲያበሰብሰው ይችላል።

*ጥያቄ፣ ካሕናት የፍትሃት ጸሎቱን ሲያከናውኑ አሰላለፋቸው ምን እንደሚመስል ቢገልጹልኝ?*

7. ሬሳው የሚጓዘው እግሩ ቀድሞ ነው። በፍትሃት ጊዜም ካህኑ በምዕራብ (ራስጌ) ቁሞ ፊቱን ወደ ምስራቅ ይዞራል። ዳቆኑ በምስራቅ (በእግር) ቁሞ ፊቱን ወደ ምዕራብ ይመልሳል። ንፍቁ ቄስ በደቡብ ቁሞ ፊቱን ወደ ሰሜን ሲመልስ፣ ንፍቅ ዳቆኑ ደግሞ በሰሜን ቁሞ ፊቱን ወደ ደቡብ መልሶ ነው የሚጸልይ። ሬሳው ራሱ ወደ ምዕራብ እግሩ ወደ ምስራቅ ዞሮ በአልጋው ላይ ተንጋሎ ይቀመጣል። ያው ስርዓቱ እንደ ቤተ መቅደሱ እንደቅዳሴው ስርዓት ነው።

**የመረጃ አቀባይ *ሥም*፣** *ደጀን አመኑ* (አባ.2፣ቁ.17)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 15/06/2005

*ጥያቄ፣ የፍትሃት ጸሎት ለሁሉም ሰው በተመሳሳይ ሁኔታ ይካሄዳል?*

1. ካህናቱ የሚሰበሰቡትና ለቅሶውን የሚያደምቁት ካህን ሲሞት፣ ለቤተክርስቲያን አስተዋጽኦ ያደረገ ታዋቂ ሰው ሲሞት፣ ወገን ያለው ታዋቂ ሰው ሲሞት፣ ግብረ ሰላም ያበላ ሰው ሲሞት ነው። ፍትሃቱ ለማንኛውም ሰው ይካሄዳል። ለእንደነዚህ አይነት ሰዎች ግን ለየት ያለ ነው። የኔቢጤ ድሃ ሲሞት በሰዓቱ ተገኝቶ ፍትሃቱን ያለማካሄድና ጠደፍ ጠደፍ የማድረግ ነገር ይታያል። ግብረ ሰላም የሚያበሉ ሰዎች ለነብሳቸው ብለው ቢሆንም እግረ መንገዱን ለፍትሃትና ለቅሶ ድምቀት ይሰጣል።

**የመረጃ አቀባይ *ሥም*፣** *መሪጌታ ክፍለማርያም አለነ* (አባ.2፣ቁ.17)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 21/06/2005

*ጥያቄ፣ ፍትሃት ለሁሉም ሰው እኩል ነው የሚፈጸመው?*

1. ይለያያል፤ እንደሁኔታው ሙሉና ግማሽ ፍትሀሃት ይኖራል።

*ጥያቄ፣ ሙሉ ፍትሃት የሚፈታው ለማን ነው?*

2. ሙሉ ፍትሃት የሚፈታ የዕለት ሞት ሲሆን ለምሳሌ ዛሬ አንድ ሰዓት ያለፈ ከሆነ ከአንድ ሰአት ጀምሮ ነፍስ አባትየው ይመጣል፤ መጀመሪያ ግንዘቱ ላይ እንዳየነው ጸዓተ ነብስ አንብቦ፣ ወንጌለ ዮሀንስ አንብቦ፣ አትናቴዎስ ደግሞ ለሕብረተሰቡ ይሰጣል። ያ ማለት ጸበል ነው በዚያ ጸበል ሬሳው ይታጠባል።

3. ይህ የሚሆነው የነፍስ አባትየው ነፍስ ስትወጣ ሲኖር ነው፡፡ ወዲያውኑ የቤተክርስቲያን አገልጋዮች ካህናትና ዲያቆናት መጥተው ቤተሰብ አስወጥተው ያን የታጠበና የተገነዘ ሬሳ ከመሃል አጋድመው የመጽሐፍ ስሙን ጠይቀው ሰዓታት ይቆማሉ፡፡ ሰዓታቱ እስከከንጋቱ 10 ሰዓት ወይም 11 ሰዓት ሊደርስ ይችላል ያ ከተጠናቀቀ በኋላ በአቡነ ዘበሰማያት አስረው ወደቤተክርስቲያን ይሄዱና የአስከሬኑን ልብስ ወይም ልብሰ ተክህኖውን፣ መስቀሉን፣ ከበሮ፣ ጸናጽል፣ አስፈላጊ የሆነውን ነገር ሁሉ ይዘው ይመጣሉ፡፡

4. ይህ እንደየ አካባቢው ይለያያል፡፡ ለምሳሌ ደቡብ ጎንደር ካህናቱ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው መስቀል ይይዛሉ፣ መሪጌታውና ዲያቆናቱ ጸናጽል፣ ከበሮ ይይዛሉ፡፡ ካህናቱ ከቤት ገብተው ከውስጥ የሚያስፈልገውን ሥርዓት ሲፈጽሙ መዘምራኑ ወይም እንግዶቹ ከሁለተኛው መድረክ ላይ ወይም ከበሩ ላይ ሁነው መዋሲት ይመራሉ፤ እዝል ከድን (ድን ዘመን ዘመን አለው)፡፡ አሁን እኛ ያለንበት ዘመን፣ ዘመነ ልደት፣ ዘመነ አስተርዮ፣ ዘመነ ጥምቀት ይባላል ከልደት ጀምሮ ጾመ እስከሚገባ ያለው፡፡ በእነዚህ ዘመናት የያሬድ ድን የደረሰበት አለ፤ ከድን ውስጥ ድርሰቱ ሶስት አይነት ድርሰት አለው፡፡ ግዕዝ፣ እዝልና አራራይ፡፡ ከእዝሉ ላይ አንድ አንስተው ለእለቱና ለዘመኑ ያመቻል የሚሉትን ድን አውጥተው እዝል መርተው መዋሲት ይመራሉ፣ ያን ይጠረጥራሉ፡፡ ይኸ አሁን መቼ ላረፈ ነው ከምሽቱ አንድ ሰዓት ጀምሮ ላረፈ ነው፡፡ ሥርዓቱን ከቤት ጀምሮ ወደመቃብር እስከሚወርድበት ጊዜ ድረስ ሰባት ፍትሃት ፈትተው ጉድጓድ ያስገቡታል፡፡ ይህ ቋሚ ወይም ሙሉ ፍትሃት ይባላል፡፡

5. ከዚህ በላይ አንዳንድ ቦታ ላይ 12 ፍትሃት ይደረጋል፡፡ ይህ ቋሚ አይደለም አልፎ አልፎ የሚካሄድ ነው፡፡ ግን ደግሞ ይህ ስህተት ነው ማለት አይቻልም ስላለ፡፡ ምሳሌነቱን የምናገኘው ከወደሐዋርያት ነው፡፡ 12 የሚሆነው በአካባቢ ነው እንጂ በሚች ማንነት አይደለም፡፡ አሁን ለምሳሌ ጎጃሞች በ12 መዋሲት ይፈቱታል፡፡ 12 ስላደረጉት ሀጢያት ነው ማለት አንችልም፡፡ የ12 ሐዋርት ስለሚሆን ማዕረጋተ ቤተክርስቲያን ብዙ አይነት ምሳሌ ስላለው፡፡ ግን ብዙሃኑ ሕዝብ እየተቀበለ ያለው ሰባቱን ነው፡፡ የያሬድ ድርሰትም የሚመለከተው ሰባቱን ነው፡፡

6. ሌላው ሙሉ ፍትሃት የማይደረስለት ከሰዓት በኋላ ከሆነ ከጊዜ ጋር ነው። አንድ ፍትሃት ብቻ ይደረግለታል። ከሰባቱ ፍትሃቶች የመጀመሪያው ብቻ ተብሎ ሙሉ ቅዳሴው ይከናወናል። ለምሳሌ አሁን ክርስትና ሲነሳ ሙሉ ቅዳሴ ነው የሚደረግ። እንደዚህ ሁሉ ሙሉ ስርዓተ ቅዳሴ ተደርጎለት ይቀበራል። ሰዓት ሲያጥር ነው እንግዲህ ሰባት (ሙሉ ፍትሃት) የማይደረገው።

*ጥያቄ፣ ፍትሃት የሚደረግላቸውና የማይደረግላቸው አሉ? በእድሜ ልዩነትስ?*

7. የሃይማኖቱ ተከታይ ሁኖ የሚፈታና የማይፈታ አለ። ለምሳሌ የሀይማኖቱ ተከታይ ሁኖ ታንቆ የሞተ በሥርዓተ ቤተክርስቲያን አይፈታም። ለምን ያው ራሱን ስላጠፋ ነው። እስከ ሰባት ዓመት ያሉ ሕጻናት የኦርቶዶክስ ሀይማኖት ልጆች መሆናቸውን ለማሳወቅ አንድ ፍትሃት ይፈታሉ። የሚፈቱት ሀጢያት ስላለባቸው አይደለም። ታንቆ የሞተው ክርስቲያንነቱ እንዳለ ቢሆንም እሱ የእግዚአብሔር ሕንጻ ሁኖ ሳለ ራሱን ስላጠፋ ከፍትሃ ነገስቱ ላይ ስለተከለከለ አይፈታም።

*ጥያቄ፣ ሙሉ ፍትሃት የሚፈታበትና የማይፈታበት ሁኔታ አለ?*

8. ይኸ የሰዓት ጉዳይ ነው። ወደ ማታ የሞተ መቀበር አለበት። አንድም ሬሳ አጋድሞ እህል መብላት ስለሌለ ሲሆን፣ በሌላም በኩል ሚች መቅመስ ያለበትን አፈር መቅመስ ስላለበት ነው። 10 ሰአት ላይ ለሞተ ሰው ሰባቱን ፍትሃት ለማከናወን ሰዓቱ ስለማይበቃ የመጀመሪያውን ፍትሃት ፈትቶ ወደ መቃብር ይሄዳል። ይኸ የጊዜ ጉዳይ እንጂ የቤተክርስቲያን ሥርዓት ሁኖ አይደለም። የበቴተክርስቲያን ቋሚ ሥርዓቷ ያው ሰባት ፍትሃት ነው።

*ጥያቄ፣ ግብረ ሰላም ያላበሉ በአንዴ ተወስደው ይጣላሉ የሚል ስሞታ አለ። ይኸስ እንዴት ነው?*

9. ይኸም ቢሆን ስህተት ነው። እንደ ሥርዓት አንስተን አንነጋገርበትም። ‹‹ለእከሌ ይህን ያህል ፍታ፤ ለእከሌ ይህን ያህል ፍታ›› የሚል ነገር የለም። እንደ ማዕረግ ግን አራት አይነት ፍትሃት አለ። አንዱ የመነኮሳት ወይም የባሕታውያን፣ ሁለተኛው የካህናት፣

ሶስተኛው የሕዝብ፣ አራተኛው የዲያቆናት ነው። ከዚህ ውጭ «እገሌ ግብረ ሰላም ስላበላ በተለየ ይፈታለት» የሚል የለውም። ለሀብታምና ለድሃ የሚል ልዩነት ካለ ይኸ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን አይደለም። ምናልባት ግብረ ሰላም ያበሉ ሰዎች ለቤተክርስቲያን ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገውም ሊሆን ስለሚችል፣ እነዚህ ሰዎች ሲሞቱ በደንብ ካልተፈቱ ሌላውም ለመልካም ነገር አይነሳሳም በሚል ሀሳብ ልማዱን የሚያደርጉት ማህበረሰቦች አስበውት ሊሆን ይችላል። ግብረ ሰላም ስላበላ ከፍ ይበል አይባልም። መልካም ስላደረገ ግን ሌላውም ነገ እንደዚህ እንዲነሳሳ ከፍ ሊደረግለት ይችላል።

***የመረጃ አቀባይ ሥም፣*** **አቶ ወንዳያ ጓንጉል (አባ.2፣ቁ.15)**

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣*** **እ.ኢ.አ. 17/09/2004**

2. ትልቅ ሰው ከሆነ ያበላ ያጠጣ ወይም መነኩሴ ከሆነ የጉዞ ፍትሃት ይፈታል። አንዱ ከቤት በየመንገዱ አምስቱን መጨረሻ ላይ ሰባተኛውን አድርገው ፍትሀት ይፈታሉ። የጉዞ ፍትሃት ይባላል ይኸ። ሌላው ከሆነ ዝም ብሎ ቀጥታ ቄሶች ፊት ፊት ይመራሉ አዘንተኞቹ እየተከተሉ እያለቀሱ ማርገጃ የሚባል አለ የለቅሶ ቦታ ከዚያ ላይ አልቃሽ ይቆማል።

***የመረጃ አቀባይ ሥም፣*** **አቶ ጸጋየ ጀንበሬ (አባ.2፣ቁ.19)**

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣*** **እ.ኢ.አ. 10/09/2004**

1. አንደኛው ሬሳው ከቤት ከወጣ ቧላም በቀጥታ ወደ ቤተክርስቲያኑ አይሄድም። የጉዞ ፍትሃት የሚባል አለ። ካቀረብሽ መስክ ላይ እንዲያርፍ ይደረግና ሙሾም ይደረጋል ወየታም ይደረጋል። ፉከራ እሚያስፈልገው ከሆነም አንድ ጊዜ ይደረጋል። ያ ከተደረገ በኋላ ጉዞ ይደረጋል። ጎዞ የሚደረገው ሰባት ጊዜ ነው። ካህናቱ ሰባት ጊዜ ይፈታሉ ጨዋውም ሰባት ጊዜ የራሱን ያደርጋል።

### 1.1.1.2. በዕለት ለቅሶ አስከቀብር ድረስ የሚከናወኑ ዓለማዊ ሥርዓቶች ክወና

#### 1.1.1.2.1. የሟች ዜና ረፍት ይፋ አደራረግ ሥርዓት

***የመረጃ አቀባይ ሥም፣*** **አቶ ዋለ ጎበና (አባ.2፣ቁ.14)**

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣*** **እ.ኢ.አ. 10/09/2004**

*የአንድ ሰው ሞት ለቤተ ዘመድ ጥሪው የሚተላለፈው እንዴት ነው?*

1. በመሰረቱ በገጠር አንድ ሰው ሲሞት ተላልኮ ያድራል ሌሊት ሁለት ሶስት ሆኖ ይሄዳል፡፡ በገጠር በአንዳንድ አካባቢ ሲጠራ «ለእነ እከሌ ጥናውን አስይዛችሁልኝ ኑ» እየተባለ የቤተክርስቲያን ጥላ እየተያዘ ነው የሚመጣ፡፡ ካህኑ የቤተክርስቲያኑን ልብስ ለብሶ ከየአድባራቱ ይመጣል፡፡ በገጠር አፋፍ ላይ ሁነው ሲጠሩ ሰላምታ አይሰጡም፡፡ «ሰማኸኝ ወይ» ይለዋል «እህ» ይለዋል፡፡ «አቶ እከሌ ስለሞተ ጥና አስይዛችሁ እንድትመጡ ተብላችኋል» ብሎ ይነግረዋል፡፡ ጥሪው የሞትና የሌላ መሆኑ የሚታወቀው በሰላምታ መኖርና አለመኖር ነው፡፡ ለእነእከሌ ዘመዶች አድርስ ይለዋል፡፡ እንዲህ አሻግሮ እየተጠራራ ሩቅ ድረስ ይሄዳል፡፡ ከማዶ ሲጠራራ በመሃል ያለው ይሰማል፡፡ ይኸ ባህል አሁንም አለ፡፡ በዚህ በከተማ ግን ይለፈፋል፡፡

2. የሞተው ሕጻን ከሆነ፣ ታዋቂነት ከሌለው፣ ራቅ ያለቦታ ለሚኖር ዘመዱ የከተማ ሰው የሚያስጠራ ሲሆን ባጠቃላይ ሚች በአካባቢው ታዋቂ በማይሆንበት ጊዜ ለቅሶው የሚጠራ በሟች ስም ሳይሆን ታዋቂነት ባለው የቅርብ ሰው ነው፡፡ ሚስት በባሏ፣ ልጆች ባባታቸው፣ እናት አባት በልጆቻቸው፣ እህት ወንድም በወንድሞቻቸው፣ አቶ እከሌ ሚስቴ፣ ልጄ፣ ወንድሜ፣ እህቴ፣ አባቴ፣ እናቴ ተጎድታለችና አላቅሱኝ ብሎ ያስጠራል፡፡

***የመረጃ አቀባይ ሥም፣ መላሽ ወርቁ (አባ.2፣ቁ.21)***

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣*** **እ.ኢ.አ. 10/09/2004**

*ጥያቄ፣ ወደኋላ ልመልሰዎትና ሰው ሲሞት ለዘመድ መልክት እምታስተላልፉት እንዴት ነው?*

1. በየቦታው ሁለት ሁለት እየሆነ እንሰማራለን፡፡ ሟቹ በጊዜ ሙቶ ከሆነ ወደማታ በየአቅጣጫው ዘመድ ወደያለበት ጥና ጠሪዎች ይሰማራሉ፡፡ ውሃ ሙላትና ሌላ እክል የሚያደርስ አውሬ ከሌለ ለቅርብ ዘመዶች እየነገሩ ያልፋሉ፡፡ ከዘመድ ተጠግተው ያመሹና ደሮ ጩኸት ሲሆን ኸተራራ ላይ ቁመው ባሻጋሪ የሚያውቁትን ሰው ስም ይጠራሉ፡፡ «አቤት» ሲላቸው «ሰማኸኝ ወይ?» ይሉታል፡፡ ሰላምታ ሳይሰጡ እንዲህ ማለት ያው የመከራ ጥሪ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከሰማ «ሰምቻለሁ» ይላል፡፡ ካልሰማ

ይጠይቃል። ጥና ጠሪው ሚቹ የሚገኝበትን ደብር ጠቅሶ «እገሌ ተነድቷልና እንድታላቅሱን ተብላችኋል። ጥናውንም እስከ እንገሌ አስጠራ ተብለሃል» ይለዋል። በደንብ ካልሰማ «ምንድን ነው ያልከኝ?» ብሎ ይጠይቃል። ከሰማ «ሰምቻለሁ» ይላል። በመሃል ያለው ሰው በዚህ አጋጣሚ ለቅሶ መጠራቱን ይሰማል። ያኛውም በተራው አስጠራ እስከተባለበት አፋፍ ላይ ቁሞ ወደማዶ የሚያውቀውን ሰው ይጠራና ሰላምታ ሳይሰጥ ይነግረዋል። «እስከነ እገሌ አስጠራ ተብልሃል» ይለዋል። ያም ተቀብሎ ጠርቶ ያስጠራል። እንዲህ እያለ ዘመዱ እስካለበት ድረስ ይደርሳል። ስልክ ያለው ሰው ተፈልጎ ይደወላል። በገጠሩ የሚሰራበት ግን ካባቶቻችን የቆየው ጥና ጠሪ ነው።

***የመረጃ አቀባይ ሥም፣*** አባ አቸነፍ እንግዳ (አባ.2፣ቁ.12)

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣*** እ.ኢ.አ. 29/09/2004

*ጥያቄ፣ የሞት አደጋ ሲከሰት እንዴት ተደርጎ ነበር መልእክቱ የሚደርስ?*

1. ሁለት ጠሪ በፈረስ ይላካል። ፈረስ ከሌላቸው በግራቸው ህደው ባፋፉ ላይ ይጠራሉ። «እገሌ የተባለው ተነድቷልና አላቅሱኝ ተብላችኋል ጥናውን ይዛችሁል ኑ» ይላሉ። ጥና ማለት የቤተክርስቲያን ማጠኛ ማለት ነው። «ወደነ እገሌ አገርም አድርስ ተብለሃል።» ይለዋል። ወደ ሌላው አገር እንዲያሻግር። እንዲህ ነው አጠራሩ ክብት ያለው በክብት ክብት የሌለው በእግሩ። እንዲህ እያለ ከደብር ወደ ደብር ባራቱ ማይዘን ይተላለፋል። ሰው እየሰማ ይመጣል።

1.1.1.2.2.የሬሳ አወጣጥ

***የመረጃ አቀባይ ሥም፣*** አቶ ገበያው ዓለሜ (አባ.2፣ቁ.11)

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣*** እ.ኢ.አ. 17/09/2004

ጥያቄ፣ ሬሳው ገና ከቤት ሲወጣ ምን ምን ይደረጋል?

1. የተለያዩ ባህሎች አሉ። እንግዲህ ሬሳ ሲወጣ ትልቅ ሰው ሲሆን በግ ይታረዳል። በጉ ይታረድና «ሬሳው ደም እረግጦ ይውጣ» ይባላል። ደግሞ እሬሳው እየወጣ መቃውን ጨርሶ ሳይወጣ እንደ ድስት ያለ ወይም እንደ ቶፋ ያለ ሸክላ ይሰበራል። ዳግም እንዳይተካ እግሩን ደረቅ እንዲያደርገው ነው መሰል ባህሉ። እሚታረደው ላለው ሲሆን እሚሰበረው ግን ለሁሉም ይሰበራል። የሚታረደው በግ ለቄሶቹ ነው የሚሄድ። ያለው ከሆነማ

ለመኳንንቱም በሬውን ያርዳል፡፡ ቶፋው ወይም ድስቱ ግን ኳ ኳ ብሎ እንዲጮህ ሰውየው እንደተሰበረው ዳግም እንዳይተካ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ እንግዲህ ሚች ጥቅም የሌለው ነገር ነው አበቃ ማለት ነው፡፡ ሰባሪው የሚቆመው ከቤት ውጭ ነው፡፡ አስከሬኑ ወደ ውጭ ብቅ ሲል ያንን ይሰብራል፡፡ ሬሳው ርጥብ ረግጦ ይውጣ ተብሎ በግ የሚታረደውም ከመውጫ በሩ ላይ ነው፡፡ ዱሮ የተለያየ የሬሳ አወጣጥ አለ ይባል ነበር፡፡ የባለቤት ሬሳ በደንብ ለብሶ በዋናው በር ሲወጣ የአገልጋዮች በበር ሳይሆን በጓዳና በመስኮት ይወጣ ነበር፡፡ እንዲህ የሚደረገው አገልጋይ እንደቤተሰቡ አባል ሳይሆን እንደ ትርፍ ሰው ስለሚቆጠር ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት ግን ማንኛውም ሰው በዋናው በር ይውጣ በጓዳ አይውጣ የሚል ይዘናል፡፡ አስከሬኑ እንደወጣ ሀዘንተኛው ተክትሎ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

**የመረጃ አቀባይ *ሥም*፣ ቀኝ ጌታ ዜናዊ ስቡሕ (አባ.2፣ቁ.1)**

***ቃለመጠይቅ* የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. **10/09/2004**

*ጥያቄ፣ ሌላ አሁን እንዲያው ሬሳ ከቤት በየት ነው የሚወጣ? በበር ነው በመስኮት ወይስ ግድግዳ ተቀዶ?*

1. ይኸ እንዲያው ያምልኮት ነው፡፡ መውጣት ያለበት በበር ነው፡፡ ግን ሲወጣ እቃ እሚሰብሩት አለ ምን እሚሉት አለ (ቅላጼያቸው የጥላቻ ነው) ይኸ አምልኮተ ባዕድ ነው፡፡ ፍሬ የለውም፡፡ ለምን እንደሚያደርጉት አይገባኝም፡፡ ምናልባት ባላገሮቹ ፍሬ ፈርስኪም ቢሆን ምክንያት ይኖራቸው ይሆናል፡፡ አንዱ ሲያደርገው ሌላው እየተከተለ ልማድ ያደረጉት ይመስለኛል፡፡

*ጥያቄ፣ ሬሳ ሲጓዝ ከእግሩና ከራሱ ማን ይቀድማል?*

2. ሬሳው የሚጓዘው እግሩ ቀድሞ ነው፡፡ በፍትሃት ጊዜም ካህኑ በምዕራብ (ራስጌ) ቁሞ ፊቱን ወደ ምስራቅ ይዞራል፡፡ ዳቆኑ በምስራቅ (በእግር) ቁሞ ፊቱን ወደ ምዕራብ ይመልሳል፡፡ ንፍቁ ቄሱ በደቡብ ቁሞ ፊቱን ወደ ሰሜን ሲመልስ፣ ንፍቅ ዳቆኑ ደግሞ በሰሜን ቁሞ ፊቱን ወደ ደቡብ መልሶ ነው የሚጸልይ፡፡ ሬሳው ራሱ ወደ ምዕራብ እግሩ ወደ ምስራቅ ዞሮ በአልጋው ላይ ተንጋሎ ይቀመጣል፡፡ ያው ስርዓቱ እንደ ቤተ መቅደሱ እንደቅዳሴው ስርዓት ነው፡፡

*ጥያቄ፣ ሬሳ እግር ቀድሞ የሚሄድበት ተምሳሌት ይኖረዋል?*

3. እንግዲህ የዚህ ተምሳሌቱ ቅዳሴ ነው፡፡ ቄሶቹ ሲቀድሱ ከላይ በተገለጸው ሁኔታ ነው፡፡ እንደዚህ ሲጸለይ ያ ሙት የክርስቶስ ማደሪያ ነው፡፡ እነዚያም የሚጸልዩት የክርስቶስን ስጋ ወደሙ ለመለወጥ ነው፡፡ ሟችም የክርስቶስ ማደሪያ ስለሆነ በዚኸው አይነት ይጸለይለታል፡፡

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** ሊቀ ማዕምራን አማረ ጌጡ (አባ.2፣ቁ.1)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.አ.አ. 22/06/2005

*ጥያቄ፣ሬሳ ከቤት በየት በኩል ይወጣል፤ ሲወጣስ ምን ይደረጋል?*

1. አስከሬን የሚወጣው በበሩ ነው፡፡ ሲወጣ ግን በተለይ ደቡብ ጎንደር ውስጥ እንስራ ይሰበራል፡፡ ፎገራ ላይ ያየሁት ቅል ነው፡፡ አስከሬኑ ከቤት ውጪት ሲል በሀይል ተጥሎ ይሰበራል፡፡ እና ይህን ዝም ብየ ሳየው ሰው ጠይቄ መረጃ አላገኙሁም ሰው የተሰራው ከአፈር ነው ሽክላም አፈር ነው፡፡ ሰው ፈራሽ መሆኑን የሚያሳይና ለሞተው ሳይሆን በዙሪው ያሉት ትልቅ ትምህርት የሚቀስሙበት ነገር ነው ያለው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ እንደቤተክርስቲያን ጥሩ አይደለም እንጂ ልማድ ነው በግ ከበሩ ላይ ያርዳሉ፡፡ እንደቤተክርስቲን የበግ ደሞች መስዋእተ ኦሪት ናቸው፡፡ መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ አደባባይ ከተሰቀለ በኂላ እንዲህ መደረጉ በሀዲስ ነውር ነው እያልናቸው ነው ያለ፡፡ በጣም የሚገርመው ነገር ሬሳው ደሙን እረግጦ እንዲወጣ ብለው እንደዚህ ያደርጋሉ፡፡ ከዚህ በኂላ የበጉ ስጋ ሲፈታ ላደረው ካህን ምሳ ይሆናል፡፡ በአንድ በኩል ግብዣ ነው በአንድ በኩል ትንሽ ከበድ የሚል አምልኮት አለው፡፡

*ጥያቄ፣ ሬሳው ደም ረግጦ ይውጣ ማለታቸው ምን ያደርጋል ብለው ስለሚያስቡ ነው?*

2. «ሟቹ ቤቱ እርጥብ ነው፤ ያበላ ያጠጣ ነበርና የሱ በረከት ለእኛ እንዲተርፈን» ነው አምልኮቱ የሰው፡፡ የሀብታምነቱ ምልክት ነው፡፡ እገሌ እኮ አንድ በሬ፣ ሁለት በሬ፣ በግ ታርዶለታል ይባላል፡፡ ይህ ዝና በህበረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት አለው፡፡ ልምዱ ስለሆነ፡፡

1.1.2. በቀጠሮ ለቅሶ እስከቀብር ድረስ የሚከናወኑ ሀይማኖታዊና ዓለማዊ ሥርዓቶች

1.1.2.1. በቀጠሮ ለቅሶ እስከቀብር ድረስ የሚከናወኑ ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች ክወና

*የመረጃ አቀባይ ሥም፣ መሪጌታ ክፍለማርያም አስነ* (አባ.2. ቁ.2)

*ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣* እ.ኢ.አ. 21/06/2005

*ጥያቄ፣ በቀጠሮ ለቅሶ የሚከናወነው ሀይማኖታዊ ሥርዓት ከዕለቱ በምን ይለያል?*

1 ቅድም እንደገለጽኩት ሬሳ በሌለበት ከዚህ በላይ የተገለጹት ሰባት ፍትሃቶች በቀጠሮም ሆነ በመርዶ ለቅሶ አይደረጉም፡፡ በእነዚህ ለቅሶዎች ታዋቂ ሰው ከሆነና ተለፎ ሰው የሚሰባሰብ ከሆነ ካህናትም ተገኝተው አንድ ፍትሃት ብቻ በማርገጃ ያደርጋሉ እንጂ ሌላ የለውም፡፡ በዕለት ከሚደረጉት የሚቀሩት አንድ ብለን ከቤቱ እንነሳና በጉዞ ላይ እስከሰባት እናደርሳለን፡፡ በቀጠሮ ግን ከቤት አይኬድም፡፡ በቤተክርስቲያን ወይም በተቀበረበት ቦታ ተገኝተን አንድ ፍትሃት ብቻ እናደርጋለን፡፡

1.1.2.2. በቀጠሮ ለቅሶ እስከቀብር ድረስ የሚከናወኑ ዓለማዊ ሥርዓቶች

*የመረጃ አቀባይ ሥም፣* አቶ ተስፋው አራጌ (አባ.2፣ቁ.41)

*ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣* እ.ኢ.አ. 16/06/2005

1. ዱሮ በጋይንት ይህን የገበያ ዳር ለቅሶ አናውቀውም ነበር፡፡ ይኼ ልቅሶ ብቅ ያለው በወሎ ክፍለ ሀገር ነው፡፡ ከዚያ ሲመጣ ጋይንት ላይ ጨጨሆ ተጀመረ በቅዳሜ ቀን፡፡ ይኼ ለቅሶ እንዴት ነው በገበያ ላይ ሰው ሲሞት በማርገጃ ላይ ተገናኝቶ እንባውን ተካፍሎ ይሄዳል እንጂ እያልን ስነገረም ይኼው አሁን እንደምታየው ወደዚህም መጥቶ ስንት አመት አስቆጥሯል፡፡ ያው ይኼ የለቅሶ አይነት ያልደረሰው የሚደርስበት ነው፡፡ ባህል አይደለም፡፡

*ጥያቄ፣ መቼ እንደተጀመረ ጊዜውን ያስታውሱታል?*

2. አየ በዚያው በደርግ ነው የተጀመረ፡፡ ከ75 አካባቢ ጀምሮ ነው ወደኛ የገባ፡፡ ከዚያ በፊት አናውቀውም ነበር፡፡

*ጥያቄ፣ ምን ጥቅም ስላለው ይመስለወታል ሰው ሊለምደው የቻለው?*

3. ዘመድ ሙቶ ዘመድ ሳይደርስ ሲቀር ዘመድ አይባባልም፡፡ «ከመከራየ ሳይደርስ ቀረ ቢደክመው እንኳን በቅርቡ ከገበያ ቀጥረን እኔ ተጎድቼ ሳይደርሰኝ ቀረ ይባላል፡፡» ይኸ ደሞ የሚያቆራርጥ ነው፡፡ ሰው ተቆራርጦ እንዳይቀር ሥራ ሳያስፈታ መገናኛ መሆኑ አንድ ጥቅሙ ነው፡፡

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ ጥሩነህ ጎሹ (አባ.2፣ቁ.42)

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣*** እ.ኢ.አ. 16/06/2005

ጥያቄ፣ ይኸ አሁን የሚያዩት የገበያ ለቅሶ በዚህ አካባቢ የተለመደ ነው?

1. ባባቶቻችን እንዲህ ያለ ለቅሶ አልነበረም፡፡ አሁን ነው ከመቄት የመጣ፡፡ ከመቄት ከቀብር የቀረውን ዘመዳችን እየተንጠባጠበ ስላስቸገረነ ሰኞ ገበያ ላይ እናስናብተው በሚል መቄት ተጀመረ፡፡ ስንስቅ ስንስቅ ጋይንት ገባ፡፡ ዛሬ በዕለቱለት የቀረውን ሰው በቅዳሜ ቀን ነው የምናሰናብተው፡፡ በዚህ አካባቢ ይኸ ልማድ የተጀመረ ከደርግ ጠቀስ አድርጎ ነው፡፡ ይኸም ቢሆን አግሪት ላይ ነበር፡፡ ደርግ ገበያው ሁሉ ቅዳሜ ቀን ብቻ ይሁን ብሎ ካወጀና ይህ ገበያ ከተቋቋመ በኂላ ነው የተጀመረ፡፡ ወደ ሰማንያ አካባቢ ነው ተስፋፍቶ የተለመደ፡፡

ጥያቄ፣ ምን ጥቅም ያለው ይመስለዎታል?

2 ሕብረተሰቡ አፍሮ ሳይደርስ እንዳይቀር ያደርጋል፡፡ ሰው እንዳይቆራረጥ፡፡ ከቤት እንዳይሄድ ማስቸገር አለ፡፡ ገበያ መጥቶ እግር ምንገዱን ደርሶ ይመለሳል፡፡

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ ወንዳያ ዓንጉል (አባ.2፣ቁ.15)

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣*** እ.ኢ.አ. 17/09/2004

*ጥያቄ፣ በዚህ አካባቢ ስንት የለቅሶ አይነቶች አሉ?*

1. ሬሳ ሲኖርና ያበላ ያጠጣ ሲሆን ካህናት በጉዞ ፍትሃት ሌላው በለቅሶ የሚያጅበው ለቅሶ አለ፡፡ ይህ የዕለት ለቅሶ ይባላል፡፡ ሁለተኛው የዝግጅት ጊዜ ወስዶ ድግስ ኖሮት ሟች ከተቀበረ በኂላ ሩቅ ወዳሉት ዘመዶቹና ወገኖቹ መልዕክት ተልኮ በቀጠሮ ቀን የሚካሄድ የለቅሶ አይነት የቅጥር ለቅሶ የሚባለው ነው፡፡ ሶስተኛው ደግሞ አሁን ከቅርብ ጊዜ

ወዲህ የመጣ የግንኝት ለቅሶ የሚባል አለ፡፡ የሚያበላው የሌለው ድሃ የቆላና የደጋው ተገናኝቶ ፍትሃት በሌለበት ቅዳሜ ቀን ከገበያ ዳር የሚካሄድ ነው፡፡ አቀጣጠሩም በሚች ሰልስት ወይም በእሁድ ቀን እናንተ በሩቅ ያላችሁ ኑና በዚህ ቀን እንገናኝ ተብሎ ቀኑ ተቆርጦ ይነገራል፡፡ ይህን የሚያደርጉ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ያላቸው ማሕበረሰቦች ናቸው፡፡ ከቤታቸው ደግሰው ለማስተናገድ ስለማይችሉ በገበያ ለመመለስ ይህን ይጠቀማሉ፡፡

2. የቅጥር ለቅሶ የሚቀጠረው ያለው ሰው ይሆንና ድንገት ሳይታሰብ ሰው ለመጥራት በማይቻልበት በክረምት ሰዓት ያሰው ሲሞት በበጋ ለቅሶውን ለማድረግ ይቀጠራል፡፡፡ (አሁን አሁን እየቀረ ነው) ምክንያቱ ወጭ ይጠይቃል፡፡ ከተቀጠረ ጥሩ ጠላ፣ እርድ መኖር አለበት፡፡ ጠም ከሆነ የእንጀራ አቅርቦት መኖር አለበት፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች የቅጥር ለቅሶ እየቀረ ነው ያለ፡፡

*ጥያቄ፣ የቀጠሮ ለቅሶውን ነው ወደ ግንኝት ለቅሶ የቀየሩት?*

3. አወ ቅጥሩን ወደዚህ ቀይረውታል፡፡ ያለው ከቤቱ ሁኖ የመጣውን ይቀበላል፡፡ የሌለው «አየ ቡና አፍልቼ የመጣውን ሁሉ የምቀበልበት አቅም የለኝም ብሎ የቆላውም የደጋውም አንድ ቀን ከዚህ እንገናኝ» ብሎ ለቅሶውን ከባህል ውጭ በሆነ ነገር ከገበያ ላይ ያደርጋሉ፡፡ ከገበያ ላይ ለቅሶ ሲደረግ ምንድን ነው አልቃሾች የሚለብሱት ነገር አለ፡፡ አዘንተኞች ለምሳሌ ሴቷ ቀሚስ ትለብሳለች፣ ኮት ትለብሳለች፣ ሱሪ ትለብሳለች ባሏ ከሆነ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አጉል የመጣ አለ፡፡ ወጣቶች አባታቸው ሞቶ ሱሪ ይለብሳሉ፡፡ ከግንኝት ውሎ ተመልሶ ደግሞ ጨው ሊገዛ ገበያ ይገባል፡፡ ይህ ባህልን ማበላሸት ነው የሚል ሮሮ፣ ተቃውሞ አለ፡፡ አሁን እኛ ይህን ለማስቀረት እየፈለግን ነው ያለን፡፡ መገናኘቱ ጥሩ ነው፡፡ ብዙ ወጭ አያስወጣም፡፡ እሚገናኘው ከገበያ ዳር ነው በዚያው ይለያያል፡፡ በዚህ አንድ ጥሩ ጎን አለው፡፡

*ጥያቄ፣ የግንኝት ቀኑ ተቀጥሮ ነው ወይስ ሀዘንተኛው የሀዘን ልብስ ለብሶ ሲወጣ ሄደው ይገናኙታል?*

4. ተቀጥሮ ነው። እንዴት ነው ለምሳሌ ከዚህ ከከተማ ከሆነ የሞተው ሰውየው ተቆላ እንደ ደብረታቦር ካለ ሩቅ ቦታ ዘመድ ይኖረዋል። አሁን በስልክ ነው። በፊት ግን ሰው ተልኮ ስለነበር የሚጠራው ጥና ጠሪ ስለሌለ የታች ጋይንትን ዘመድ አልጠራነውም። በይህ ቀን እገሌ ሞቶ ተጎድተናልና ተገበያ ተገናኝተን እንድንላቀስ እርማችሁን አውጡ ብሎ ይልካል። በዚህ ሰዓት ከገበያ ይመጣሉ። እና የተላከበት ሰው ይመጣል ከገበያው ዳር ስለሚቀመጡ ሌላው ሰው አሻግሮ በማየት የማውቀው ሰው ይኖራል ብሎ ይገናኛል።

**የመረጃ አቀባይ *ሥም*፣** አቶ ገበያው ዓለሜ (አባ.2፣ቁ.11)

***ቃለመጠይቅ* የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 17/09/2004

*የትኛው የሕብረተሰብ ክፍል ነው የገበያ ላይ የቀጠሮ ለቅሶ የሚጠቀም?*

1. ይኸ ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ነው። አሁን ትናንት ከዚህ ከከተማው ሰው የሞተባቸው አሉ። የገጠሩን አልጠሩም። የገጠሮቹ ስላልመጡ በ25/09/04 ቅዳሜ ገበያ ድረስ እንገናኝ ብለው ይቀጥራሉ። የገጠሩ ሰው ደግሞ እኔ እናንተ መምጣት አልሆንላችሁ ብሎ እንደሁ ብሎ እዚያው ቅዳሜ ገበያ እንገናኝ ብሎ ቀጥሮ ይመጣል። ቅዳሜን የሚመርጡት ሥራ ላለመፍታትና ባህሉም እንዳይቀር ነው። ይህ ወጭ ይቀንሳል፣ የጉልበት ኪሳራ የለውም። አሁን የገጠሩ ሰው የከተማው ሰው ወደ እነሱ ሲሄድ ጠላ ጠምቆ እንጀራ አዘጋጅቶ የሚያበላው አጣ። ይኸ ግድ ስላስገደደው ከገበያ ተገኛኝቶ ገበያ የሚሰራም ይሰራል ሌላውም ወደ ጉዳዩ ይሄዳል።

*ጥያቄ፣ ከዚህ የሚዘጋጅ መስተንግዶ የለም? የሚበላ፣ የሚጠጣ?*

አይታጣም። እንዲያው አንዳንዶቹ ያላቸው ገዝተው ሊጋብዙ ይችላሉ። ግን ከዚያ ሰውም ሳንበላ ሳንጠጣ ብሎ አይጠብቅም አያማም። ግንኙነት ነው።

**የመረጃ አቀባይ *ሥም*፣** አቶ ምህረት ገረመው (አባ.2፣ቁ.18)

***ቃለመጠይቅ* የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 15/06/2005

1. የላይ ጋይንት የገበያ ላይ ለቅሶ መቄት ወረዳ ወሎ ውስጥ ነው የተጀመረው። ኸዚያ እሚያደርጉት ምንድነው፣ ዘመድ ኸዚያ ኸቀብሩ ላይ ይመካከሩና «ለዚህን ቀን ብለናል ዘመድ እንዳይለፋ ተላላኩልን» ይላሉ። አሁን ሄደው ገበያ ላይ ኸዚህም ኸዚም የተጎዳው

ቁጭ ይላል፡፡ ኸዚያ በኋላ ያ ገበያ የሄደ አንዱን አንዱ ይነግረዋል «እንዲህ ነው» ይለዋል፡፡ ሰው ሲሄድ መቁት ላይ ሁለት ብር ከኪሱ፣ ባገልግል እንጀራ ያለው በወጥ፣ የሌለው በጨው ሁለት እንጀራ ቀብቶ ይዞ ነው የሚወጣው ለቅሶ ደራሹ፡፡ ኸዚያ በኋላ ያንን ብር የሚሸክፍ አለ ይሸክፍ ይሸክፍና ሰዎቹ ኸዚያው እንደተቀመጡ ጠላ ሀለበት ይፈልጋሉ፡፡ ከተገኘበት ቤት ሀዘንተኞቹን ወስደው ያገልግል እንጀራቸውን ጨርቅ ላይ ዘርግተው ይበላሉ፡፡ ጠላቸውን ጠጥተው የተረፈውን ብር ለተጎዳው አካል «ለቡና ይሁንህ» ተብሎ ይሰጣል፡፡

2. ጉርብትና መቼም ችግር ነው ያንን ተሞክሮ ጋይንት ከዚያ ለመደ፡፡ አሁን ጋይንት ላይ ስናየው የብሪቱና የእንጀራይቱ ነገር ጋይንት ላይ የለችም፡፡ በአብዛኛው ግን ሰው ወደዚህ እየዞረ ነው፡፡ ስናየው ደግሞ በአብዛኛው ሰው ተጎጅ ነው፡፡ ሰው ለቅሶ ለመድረስ ከሩቅ ቦታ መጥቶ መቼም ሻይ ቡና ሳይል አይመለስም፡፡ ያስተዛዘነውን ሰው «ግባ» ለማለትና ለማስተናገድ ሰው አቅም አጣ፡፡ ይህንን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ነገር ነው፡፡ አቅምን ያገናዘበ ነገር ነው፡፡ «ኧህ ይኸነገር ሰው ቢመጣ አሁን እህል ውሃውስ መች» ይባላል፡፡ ስለዚህ «ኸገበያው ጠብቁ እንበላቸውና ሰውም እንዳይደክም እኛም በዚው እንሸኛቸው» እየተባለ የሚደረግ ሁኔታ ነው ያለው፡፡

**የመረጃ አቀባይ ሥም**፣ አበረ ከበበው (አባ.2፣ቁ.10)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን**፣ **እ.አ.አ. 25/09/2004**

*ጥያቄ፣ዛሬ ስትሮክርበት የዋልክበትን የለቅሶ አይነት ምን ብላችሁ ነው የምትጠሩት?*

1. የቅዳሜ የቀጠሮ ለቅሶ፣ የግንኙት ለቅሶ እንለዋለን፡፡

*ለቅሶው መኖሩን ሰው እንዴት ነው የሚሰማ?*

2. ሰውየው ሙቶ በተቀበረበት ቀን በሚቀጥለው ወይም በሁለተኛው ቅዳሜ ‹‹በዚህ ቀን እንድታላቅሱን፣ ላልሰማው አሰሙልን፤ ዘመዱ እንዳይለፋ›› ብለው ይናገራሉ፡፡ የሰማው ላልሰማው ይነግራል፣ ለባለቁርጥ መላክተኛ ይናገራል፡፡ እንደዕለት ሞት ጥሪ የለውም፡፡

*ጥያቄ፣ ካባት የቆየ ነው?*

3. አየ ሀባት የመጣ እንኳን አይደለም። በእኛ እድሜ ቢሆን ነው ተጀመረ ሲሉ የሰማኋቸው። ኸደርግ ውስጥ ነው ተጀመረ እሚባል። በዚያን ጊዜ እንዳሁኑ ቦታ ተከልሎለት ሳይሆን በጎንደሩና በባህርዳሩ መግቢያ ከምንገዱ ዳር አዘንተኞቹ ቁጭ እያሉ ሰው እየደረሰ ነበር የሚሄድ። ኸቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው ቦታ ተመድቦለት እንዳየኸው መዋል የጀመረው።

*ጥያቄ፣ ዛሬ እንዳየሁት በሁለቱም አቅጣጫ ከስድስት ያላነሱ የቀጠሮ ለቅሶዎች ውለዋል። ሰው የለመደው ይመስላል?*

4. እስታስርና ከዚያም በላይ የሚውልበት ቀን አለ። ብዙ ጥቅም ስላለው ሰው ወዶታል።

*ጥያቄ፣ ጥቅሙ ምንድን ነው?*

5. ለገበያ በመጣህበት ከሶስት ከአራት ለቅሶ በቁምህ ደርሰህ ወደገበያህ ትኸዳለህ። ተጎጆቹ ለመጣ ለኸደው ቡን ምን እያሉ አይቸገሩም። ባለቁርጥ ሳልሆነው ሁላ ሥራ ከመፍታት ያድናል። የተቀጠረበትን ቀን ጠብቆ ኸዚኸው መገናኘት ስለሚቻል። ይኸ ይኸ ጥቅም አለው።

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** ብርሃን አበበ (አባ.2፣ቁ.16)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 29/09/2004

*ጥያቄ፣ በዚህ አካባቢ ካሉት የለቅሶ አይነቶቹ አንዱ የቀጠሮ ለቅሶ መሆኑን ገልጻችሁልኛል። ምን መልክ እንዳለው እስኪ አብራሩልኝ*

1. በፊት በፊት የዕለት ቀብር በእዝን ይፈጸም ነበር። ይኸ በድንገት ስለሆነ ዝግጅት ስለሌለ ብዙ የሚባክኑ ነገሮች አልነበሩም። አሁን አሁን ግን ከተቀበረ በኋላ እንደገና ለማስለቀስ የመቃጠር ሁኔታ አለ። ከቀብር በኋላ ያልደረሰው ዘመድ እንዲደርስ በሚል ሀሳብ ይቀጠራል። አሁን አሁን ግን ከማን አንሼው ነው የሚበዛ። የቀን ጠላ የሚለው ነገር አሁን በጣም እየጎላ ነው የመጣ። በደርግ ጊዜ በሀይልም ቢሆን ለማስቀረት ጥረት ይደረግ ነበር። አሁን በማስተማር እንጂ የሕግ ማዕቀፍ ካለማግኘቱ የተነሳ ያላቅሙ አርዶ መደገስ አሁን በቃ በተለይ የቀን ጠላ የሚባለው ነገር ከማን አንሼ ሰርግም ላይ ፉከራም ላይ በቃ የሚች ቤተሰቦች ይሰደባሉ። በጠላ ካልተለቀሰ የትልልቅ ሰዎች ሌላ

ጊዜ በሰርግ ሲፎከር «የእናት አባቱን ለቅሶ እንኳን በጠላ ያላስለቀሰ» ተብሎ እንደ ክብርም እንደ ዝናም ስለሚቆጠር እንዳልሰደብ እየተባለ ዛሬ አሁን ያላቅም እየተደገሰ ይገኛል። ይኸ ከማን አንሸ ነው። ልገሮቻቸው በሰው ቤት ተቀጥረው እየሰሩ «ያባቴ ተስካር ሊወጣ ነው፤ የእናቴ ለቅሶ ሊለቀስ ነው ለቀን ጠላ» እየተባለ ካቅም በላይ እየተደገሰ ነው ያለ። ለሕዝቡ ትምህርት ቢሰጠውም እየተባባሰበት ነው ያለ። ከኛ ወረዳ እንደዚህ አይነት ነገር አለ።

*ጥያቄ፣ ይኸ ልማድ መቼ ነው የተጀመረው?*

2. ልማዱ በዚህ ጊዜ ነው የተጀመረ አይባልም። ዱሮም አለ። ግን አሁን አንዱ አንዱን እያየ ከማን አንሸ እነእገሌ ስላደረጉ እኛም እናድርግ፣ እነእከሌ አድርገው እኛ ሳናደርግ ብንቀር እንሰደባለን፣ ክብራችን ይዋረዳል፣ የሚለው ነገር አሁን ከጊዜ ወደጊዜ እየባሰበት ነው የመጣ። እኔ እንዲያውም የሚያሳዝነኝ የተማሩ የምንላቸው ከትልልቅ ከተማ ያሉ ባለሃብት የሚባሉት ይህን ነገር በመጥላት እየቀረቡት ሳይሆን እንዲያውም ገንዘብ እየላኩ እነሱ መጥተው ሳይቀብሩ «አደራ የእኔ እናትና አባት ከሌላው እንዳያንሱ» እያሉ ገንዘብ እየሰጡ እያስደገሱ ነው ያሉ። እና አሁን አንዱ አንዱን እያየ ልክ እንደ መልካም ተሞክሮ መጥፎ ተሞክሮ ወስዶ «እኔ ከማን አንሼ» በሚል ልማዱ ከዚህ 5 እና 6 ዓመት ወዲህ በጣም እየጎላ መጥቷል ለማለት ነው እንጂ ልማዱማ ዱሮም ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው። በጣም የተባባሰው በዚህ በ5 እና 6 ዓመት ውስጥ ነው።

*ጥያቄ፣ በቀጠሮና በእለት ለቅሶ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?*

3. በቀጠሮና በዕለት ለቅሶ መካከል ያለው ልዩነት ለምሳሌ አሁን ዛሬ ሰው ሞቶ ቀብሩ ነገ ቢሆን ከሩቅ ያለ ሰው አይገኝም። ወዲያው ከተለቀሰ ብዛት ያለው ሰው አይገኝም። ከዚያ በያገሩ ያለው ሁሉ በስልክ ተጠራርቶ እንዲጠራቀም ነው የቀጠሮ ለቅሶ ያስፈለገው። የቀጠሮ ለቅሶ ብዙ ወጭ ያስወጣል። እንዲውም በዕለቱ ለቅሶ የቀጠሮ ለቅሶ አድርጉ ተብሎ ይመከርና ለምንድን ነው እንዲህ የሚደረገው በትኩሱ ወዲያ ካልተቀጠረ ለሚመጣው ደራሽ ሁሉ ሁልጊዜ ቡና ይቀጠቀጣል። ከወጭ አንጻር። በቀጠሮ ለቀሶ ከሆነ አንድ ጊዜ ተቀጥሮ ሰው ይመጣል አለቀ። በዘንድሮው ዓመት ጥይት መተኮስ

ተከልክሏል። ለአንድ ጥይት 50 ብር ይቀጣል። እስካሁን ድረስ ግን ለቅሶ የመሳሪያ መፈተሻ ነበር።

*ጥያቄ፣ በዚህ አካባቢ የዕለት ለቅሶ ሲሆንና የቀጠሮ ለቅሶ ሲሆን በመስተንግዶ በኩል ምን ምን ልዩነቶች ይታያሉ?*

4. በቀጠሮ ለቅሶ ይደገሳል። ሁለት እድር ሶስት እድር ይኖረዋል። ያን እድር ለቀጠሮ ለቅሶ ያስቀምጠዋል። እንጀራው ጠላው ይመጣና ተደግሶ ሀዘንተኛው እንዲስተናገድ ይደረጋል። የዕለት ለቅሶ እንደሆነ የዚያን ሰዓት እንዲመጣ ይደረጋል ብዙም አይደለም። የቀጠሮ ለቅሶ ነው ተዘጋጅቶ የሚመጣና ዘመዱም አድሮ እንዲሄድ የሚደረገው።

5. ሟች በሁለት መንገድ የሚናዘዘው አለ። አንዳንዱ ለቅሶየን ከዕለት በኋላ ቀጥራችሁ ዘመድ አዝማድ ሳይቀር በሥርዓት ማስለቀስ አለባችሁ፣ ሀውልት መስራት አለበት ይላል። ለቅሶዬ በሥርዓት ይካሄድልኝ ይላል። አሁን ለምሳሌ የኔ አያት ያለው ምንድን ነው «ዕለት በሞትኩባት ዕለት ብቻ ነው መለቀስ ያለበት እንጂ ቀጠሮ ምንም አያስፈልግም፣ ሀውልት ሳይሆን የምታደርጉልኝ ግድግዳ ቤት ሰርታችሁ ቆርቆሮም ይሁን ሳር እንደምትችሉት ጸሎት እንዲካሄድበት መሆን አለበት» ብሎ ነው የተናዘዘው። እና ስለዚህ ቋሚ ብቻ ሳይሆን የሟችም ኑዛዜ ይወስነዋል። ማድረግና አለማድረጉ የሚወሰነው ያው ባቅም የቤተሰቡ ጉዳይ ነው። ያው በዚህ መልኩም የሚያደርጉ አሉ። አሁን አያስፈልግም ቢባል ከማን አንሼ ከብቶቻቸውን ሸጠው ያደረጉ ሰዎች እኔ አውቃለሁ። ሌላው ደግሞ በአዲስ አበባና በአሜሪካ ባላየው ሞት የሚሰደው ገንዘብ አሁን ከዚህ አንጎት የሚባል ቦታ አለ ብሩ ከአሜሪካ ተልኮ በማን አንሸ ከዚህ ተደግሶ የቀጠሮ ለቅሶ ተካሂዷል። እና ከማን አንሼ በሚለው ደራ እየተገባባ ነው እንጂ የቀጠሮ ለቅሶ እንዲያደርግ የሚያስገድደው የለም። ለቀጠሮ ለቅሶ መኖር ዋና ዋና ነገሮች ተብለው የሚታሰቡት፡-

1ኛ ለለቅሶው ድምቀት ነው። ለቅሶው በደንብ መድመቅ አለበት።

2ኛ. በድጋሚ ሰው መጥቶ ሀዘንተኞቹን እንዳያስለቅሳቸው በአንድ ላይ ለመሸኘት ነው፡፡ ከቦታው ርቀት አንጻር በወረዳው 80 ኪ.ሎ ሜትር እንዲያውም ከዚያ በላይ ባለ ርቀት ዘመድ ስለሚኖር ባንድ ላይ መጥተው እርማቸውን እንዲያወጡ ይታሰባል ማለት ነው፡፡

3ኛ ከማን አንሼ አንቺ ያባትሽን ለቅሶ እንኳን አላስለቀስሽም ተብሎ ስለሚያሰድብ ከማን አንሼ ያው ያለውን ከብት ሽጦ መደገስ ይጠበቅበታል፡፡ በምድር ያማረበት በሰማይም ያምርበታል የሚል ከንቱ ብሂል አለ እሱን በማስተጋባት ማለት ነው፡፡

**1.1.2.3.በምሥል የሚለቀስ የቀጠሮ ለቅሶ**

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ ኃይሌ ዘውዴ (አበ.2 ቁ.37)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 11/05/2006

*ጥያቄ፣ የምስልለ ለቅሶ ባለበት ውለው ያውቃሉ?*

አወ ውያለሁ፡፡

*ጥያቄ፣ ምስሉን እንዴት አድርገው ነው ለቅሶው ላይ የሚያውሉት?*

1. ዱሮ ሀልጋ እንደተኛ ነበር የሚመሰል፡፡ አልጋው ለብሶ እንደሬሳው ነበር፡፡ አሁን እንደገና ሀልጋው ላይ ቁጭ አድርጎ ጥምጣሙ ምናምኑ ባርኔጣው ተደረገ ዝናሩን አስታጠቀ ሰውየውን ያለ አስመስሎ መቼም ኩታውን አለበሰ እንደዚያ ያለ አለ ዛሬ፡፡ ደሞ በቁሙ የሚመስሉ መጡ፡፡ ሰውየው እንደቆመ አድርገው፡፡ ሽድንኳኑ ፊት ላይ ሰውየው እንደቆመ አድርገው ይመስሉታል፡፡

*ጥያቄ፣ የሚመስሉት ለምንድን ነው?*

2. ምስሉ ሰውየውን እየመሰለው ሰው እንዲያለቅስ፡፡ እንግዲህ ሰውየው ከተቀበረ ቆየት ካለ በኂላ የቀጠሮው ለቅሶ ስለሚካሄድ ሰው ምስሉን ሲያይ ሰውየውን እያስታወሰ እንዳዲስ እንዲያለቅስ ለማድረግ ነው፡፡

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ ደጀን አመኑ (አባ.2 ቁ.17)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 15/06/2005

*ጥያቄ፣ ሲለቀስበት የዋለውን ምስል መጨረሻ ላይ ምን ያደርጉታል?*

1. ምስሉ በዋለበት መልኩ በክብር በጎን መሳሪያ ታጣቂዎች አሉ፡፡ ታጅቦ ወደቤት ይመለሳል፡፡ መሳሪያ ታጥቀው ምስሉን በጎንና ጎን ቁመው የሚጠብቁ ሁለት ሰዎች አሉ፡፡ የሚጠብቁት ሟች የተከበረ መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ (ከፊውዳሉ ሥርዓት የተያያዘ ነው፡፡ ከአለቃና ምንዝር) ለሥራ የተቀጠሩ በፊት ሞሰብ፣ ገንቦ ተሸካሚዎች ይሳተፋሉ፡፡ (ባሪያዎች) የአባቴ ለቅሶ ሲለቀስ ተይ ብለን ብንከለክላትም አገልጋይ የነበረችው እናንተ እንቢ ብትሉ እኔ አልሰርዘውም ብላ በ1998 ዓ.ም ሞሰብ ተሸክማ ስትዞር ውላለች (ከአቶ አመኑ ለቅሶ)

*ጥያቄ፣ ምስሉን የሚሰራው ማን ነው?*

2. ምስሉን የሚሰራው በአካባቢው አጠራር ወጌሻ ይባላል፡፡ እንጨቱን፣ ሀረጉን፣ በደንብ አስሮ ከላይ ጀበናውን ዘቅዝቆ መቅጃውን አፍንጫ አስመስሎ ይሰረዋል፡፡ የሟች አፍንጫ ከፍ ያለ ከሆነ በእደ ጥበብ ባለሙያው ተስተካክሎ ይሰራል፡፡

*ጥያቄ. የምስሉ አለባበስ እንዴት ነው የሚወሰነው?*

3. ሰውየው በአደባባይ አዘውትሮ የሚለብሰው ልብስ፣ ባርኔጣ፣ ይለብሳል ምስሉ፡፡ ምንም ቀጠሮው ቢሰነብት ሰው ያንን በርቀት ሲያየው ሰውየውን አስታውሶ ያነባል፡፡ ሰውየው የሚያሳየው ባህሪ ነው በምስሉ ላይ የሚንጸባረቅ፡፡ ከዘራ፣ ጠበንጃ አያያዙ፣ አቋቋሙ ከዘራ ደገፍ ብሎ የሚቆም ከሆነ መሳሪያ ቆፍጠን ብሎ በእጁ ዘቅዝቆ የሚይዝ ከሆነ ብቻ እንደሚቹ ባሕሪ ምስሉም ያንኑ እንዲከተል ይደረጋል፡፡ አባቴ በቀኝ ተከሻው መሳሪያ ዘቅዝቆ ያነግት ነበር፡፡ ምስሉ እንደዚያ ተደርጎ ተሰራ፡፡ ዝናሩን የሚታጠቀው በኮቱ በስር ነበር፡፡ ምስሉም እንደዚያው ታጠቀ፡፡ በአጠቃላይ ሟች በአደባባይ የሚያዘወትረው አለባበስና ባህሪ እንዲንጸባረቅ ተደርጎ ምስሉ ይመሰላል፡፡ መጨረሻ ላይ ለቅሶው ካበቃ በኋላ ምስሉ በክብር ወደ ቤት ይወሰድና ከሚቀመጥበት (ሟች በሕይወት ሳለ) ቤት እንዲገባ ይደረጋል ፡፡ ከዚያ መጋረጃ ተጋርዶ ምስሉ ይፈረሳል፡፡ መጋረጃውን ያመጡት አንድም ወጌሾቹ ጥበቡን ሌላው እንዳይካፈላቸው ነው፡፡ (ክፍያዋ እንዳትቀር) ሌላው

በክብር ተጋርዶ በዚው ገብቶ ቀረ ለማለት ነው። እሚፈርሰው በዚያው ቀን ማታ ነው። ማታ ማታም ያንጎራጉራሉ። ጠላ እየተጠጣ በሞቅታ ይለቀሳል።

### 1.1.3. በመርዶ ለቅሶ የሚከናወኑ ሀይማኖታዊና ዓለማዊ ሥርዓቶች ክወና

#### 1.1.3.1. በመርዶ ለቅሶ የሚከናወኑ ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** *መሪጌታ* ክፍለማርያም አለነ (አባ.2 ቁ.2)

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣*** እ.ኢ.አ. 21/06/2005

*ጥያቄ፣ የመርዶና የቀጠሮ ለቅሶ ሲሆን የፍትሃት ሥርዓቱ ከዕለቱ በምን ይለያል?*

2. ለቀጠሮው አንድ ፍትሃት ብቻ ነው የሚደረግለት። በዕለት ከሚደረጉት የሚቀሩት አንድ ብለን ከቤቱ እንነሳና በጉዞ ላይ እስከሰባት እናደርሳለን። በቀጠሮ ግን ከቤት አይኬድም። በቤተክርስቲያን ወይም በተቀበረበት ቦታ ተገኝተን አንድ ፍትሃት ብቻ እናደርጋለን። ከዚያ በኋላ ትምህርት ካለ ትምህርት ይሰጣል። በነፍስ አባትየው አማካይነት።

*ጥያቄ፣ ቅኔ መዝረፍስ አለ ሽብሽባ?*

3. ይኖራል። ይኸ ቢኖርም ግን ሙሉ ፍታት ሊያደርገው አይችልም። ለምሳሌ አሁን ባገራችን የጥምቀት ታቦት ይወርዳል። በየመንገዱ እያረፈ ካህናት እያስረገጡ እያሸበሸቡ ይዘውት ይሄዳሉ። ይህ ምን ስለሆነ ነው ታቦት ስላለ። ታቦት ሳይኖር ግን ምናልባት የዓመት በዓል ቢሆን ከጀመረበት ጀምሮ ሲደክመው እንጂ ማቆሚያ የለውም። ቅኔ የተዘረፈለት ለምሳሌ ለቤተክርስቲያን አገልግሎ ሊሆን ይችላል። ቅኔው የሚያመለክተው ሰውየው በምን አይነት ሁኔታ እንዳረፈ፣ ምን አይነት ባህሪ እንዳለው የሚያመሰጥር እንደሆነ እንጂ ዝምብሎ ከሆነ ወራጅ ውሃ ቀጂ ይባላል። ምስጢር የለውም።

#### 1.1.3.2. በመርዶ ለቅሶ የሚከናወኑ ዓለማዊ ሥርዓቶች ክወና

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ አለምነው አሉላ (አባ.2፣ቁ.23)

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣*** እ.ኢ.አ. 10/09/2004

1. ከዕለት ለቅሶ ቀረብ የሚለው ከባድ ለቅሶ የመርዶ ለቅሶ ነው። ሀዘንተኛው ሳይሰማ በር ተንኳኩቶ ስለሚነገረው ክብደቱ ወደ ዕለት ለቅሶ ቀረብ ያለ ነው። ደብረታቦር ቅዳሜ ብቻ እንዲደረግ ተወስኗል። ተረጂዎቹ የማያስጠሩ ከሆነ ከዚው ከቤታቸው ጎረቤቱ

ተላቅሶ ድንኳናቸውን ጥለው የእድር አባላት ብቻ ተሳትፈውበት ይጠናቀቃል፡፡ ከማርገጃ ህደው እስከ ሁለት ሰዓት ቆይተው ሰውን አሰናብተው ሌላ ነገር ሙሾ ምናምን የለም ይጠናቀቃል፡፡ ሟች በጦር ሜዳ የሞተ ከሆነ፣ አገሩን ከመልቀቁ በፊት ታዋቂ ከነበረና ተረጆቹ ጎን ካላቸው ለቅሶው እንደ እለት ይለፈፋል፡፡ ሬሳ ካለመኖሩ በቀር እንደ እለት ለቅሶ በወየታና ሙሾ ይውላል፡፡ ደከም ያለ ከሆነ ከቤቱ ተላቅሶ ድንኳንም ሳይጣል ይቀራል፡፡ እድሩ ገንዘብ ይሰጣቸዋል፡፡

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ አራጋው ታረቀኝ (አባ.2 ቁ.32)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 05/010/2004

*ጥያቄ፣ የቀጠሮና የመርዶ ለቅሶ ሲሆን እንዴት ነው የምታደርጉት?*

1. የቀጠሮ ለቅሶ እኮ የሚደረግ እኂ ወስዶት እሬሳው ሳይገኝ ሲቀር ነው፡፡ ወይም በክረምት ትልቅ ሰው ይሞትና እሩቅ ላለው ዘመድ ለመንገር እንደነ እርብና አሙስ ወንዝ ያሉ ሀይለኛ ወንዞይ ስለሚከለክሉ፣ በክረምት ችግርም ስላለ እንግዳ ለማስተናገድ በመኸር ደመቅ አርጎ ለማስለቀስ ሲባል ያካባቢው ሰው ተላቅሶ ኸቀበረ በኂላ የሚካሄድ ነው፡፡ እሬሳ ስለማይኖር ኸዚያው ኸማርገጃ ህዶ መላቀስ ነው፡፡

2. የመርዶ የሚሆነው ደሞ እነጀራ ፍለጋ በሰው አገር የኸደ ሰው ይሞትና ዘመዱ እርም እንዳይበላ ተቆርቋሪ ጓደኛ የሥጋ ዘመድም ካለ እሱ ይመጣና ኸቁርጠኛ ሰው ጋር ሁኖ ነገሩን አመቻችቶ ወፍ ሳይንጫጫ ኸባለቁርጡ ቤት መጥቶ ስሙን እየጠራ ያለቅሳል፡፡ ኸዚያ ወዲያማ ያው ዱታ ነው፡፡ አዘኑ ሬሳ ከተያዘው አይለይም፡፡ ድንጋጤው አለ፡፡ እንዲውም ያሳስታማሚ በሰው አገር መቅረቱ ከሞቱ በላይ አንጀት ይቆርጣል፡፡ እንግዲህ እንዲህ የሚደረግ እልቅሶው በዚያው በመንደር የሚቀር ከሆነ ነው፡፡ ሟቹ ደህና ደህና ወንድም ካለው ግን ለጠንካራው ባለቁርጥ ይነገርና ይዘጋጃል፡፡ ደሮ ጨኸት ላይ አርድቶ ያስጠራል፡፡ እንደእለት እልቅሶ ሰው እዝኑን እየቋጠረ ይመጣል፡፡ በደንብ ይለቀስለታል፡፡ ታዋቂ ከሆነ ፉከራው ሙሾው በደንብ ነው የሚለቀስ፡፡ አሁን ይኸ መናጢ በሽታ ከመጣ ወዲህ እንጀራ ፍለጋ የሚወጡ ልገሮይ በወጡበት ቀሩ፤ እልቅሶው ሲበዛ ሰው ተሰላቸ በዚያው እርም እንዳይበላ ብቻ ባቀረብሽ ባቀረብሽ ሆነ፡፡

3. በፊት እኛም በከተማው እየኸድነ እናላቅስ ነበር፡፡ የከተማውም ባለቁርጥ ይመጣ ነበር፡፡ አሁን የከተማውም ኸዚያው ጎረቤት ለጎረቤት ተላቅሶ እድሩን ይቀበላል እንጂ ወደገጠሩ አይጠራም፡፡ ደንኳን ቢጥል እንኳን እንዲያው ባለቁረጥ ተላልኮ እስቲደርስ ነው እንጂ ወዲያው ነው የሚነቅል፡፡

4. ምንድን ነው እንግዲህ ያቅም ማጣት ጭምር ነው፡፡ ደሞ እንዲህ ሲባል አሁን በውትድርና ህዶ የሞተ በደንብ ተጠርቶ ነው የሚለቀስለት፡፡ ሙሾው በተለይ ፉከራ ጉድ ነው፡፡

*ጥያቄ፣ መርዶ የሚያረዳ እንዴት አይነት ሰው ነው?*

5. እሱማ የሚያረዳው ዘመድ ከሆነ ከተረጁ ቤት ለጥየቃ የኸደ መስሎ አድሮ ለሊት ላይ ስሙን እየጠራ በማልቀስ ያረዳል፡፡ ራቅ ራቅ ላለው ሰው ቀድሞ ስለሚናገር ሁሉም ደርሶ ይላቀሳል፡፡ ከፊራ ወይም ብዙ ቅርበት ከሌለው ባካበቢው ካለ ዘመድ ተጠግቶ አድሮ ከቀደም ብለው ህደው እየተላቀሱ ያረዳሉ፡፡ «ያርጅ አንጀት የለውም» ይባላል፡፡

6. በፊት በጦር ሜዳ ሲሞት ደሞ ቁርጠኛ ጓደኛ የሞተበትን ቦታ፣ ቀኑን አርጎ የቀበረው መሆኑን ገልጦ በደብዳቤ ይልካል፡፡ ያ የፊረደበት ቤተሰብ ሰላምታ መጣ ብሎ ሲያነብ ወይ ሲያስነብብ ይረዳል፡፡ ከሁሉው መጥፎ ይኸ ነው፡፡ ያለሰዛት ስለሚሆን ከባድ ነው፡፡ የአቶ መኮነን ልዥ በየርትራ የቀረውን ጓደኛው ልኮ ሰላምታ ሊሰሙ አስፍስፈው ሲጠብቁ ለካስ መርዶ ነው፡፡ ነብሱን ይማርና ቄስ ኪዴ ጎበዝ ነበር እኔ ደና ነኝ ብሎ የውሸቱን አንብቦ ለአጎቶቹ ነግሮ በሶስተኛው ቀን ለእናት አባት አረዷቸው፡፡ ፉከራና ቀረርቶ እንደዚያ ቀን አይቼ አላውቅም፡፡ አሁን በከተማውም ቅዳሜ ብቻ እስተሁለት ሰዛት ተባለ፡፡ በኛም የኑሮ ውድነቱ እያስቀረው ነው፡፡

**ከእሙሀይ አስናቀች አስማረ እና ወሪ/ት ዘውዴ ከበደ በ11/09/04 የተካሄደ ምልከታ**

1. ሚች ያረፉት በ96 ዓመታቸው ገጠር ውስጥ ሲሆን ከተማ የሚገኙ ወንድማቸው እርማቸውን እንዳይበሉ አርድተዋቸው ለቅሶው ተለፎ ስላሴ ቤተክርስቲን በ11/09/04 ዓ.ም ተካሄዷል፡፡ መለፊፉን ሰምቼ ወደ ቦታው ሄድኩ፡፡

2. ቤተክርስቲያን ማርገጃ ላይ አግዳሚ ወንበር ፊትና ኋላ ተደርድሮ ተቀምጧል፡፡ የእድር ተረኞች አሉ፡፡ ሀዘንተኞቹ እያለቀሱ ጥቂት ሰዎች አጅበዋቸው መጥተው ተቀመጡ፡፡ የእድር አባላቱና ሌላውም ሰው እየተንጠባጠበ እየመጣ ፊት ለፊት ቁሞ ከአንገቱ እየሰገደ ይቀመጣል፡፡ በርከት ብሎ ሲመጣ እየተነሱ ይቀበላሉ፡፡ አንዳንዱ በእጁ ትከሻቸውን እየነካ ሲገናኛቸው አንዳንዱ ፊት ለፊት ቁሞ ከታየ በኋላ ዘወር ብሎ ይቀመጣል፡፡

3. ከጎን ዘውዴ ከበደ የተባለች ወጣት ቤተሰቦች መርዶ ተነግሯቸው በተለይ እህቷና እናቷ እየጮሁ ይላቀሳሉ፡፡ በጣም አልፎ አልፎ ካልሆነ ሰው አይደርሳቸውም፡፡ እህቷ የነጠላዋን ጫፍ ከወገቧ ላይ አስራ ሌላኛውን ጫፍ ወደኋላ መልሳ ከአንገቷ ላይ አጣፍታ የአስተዳደግ ትዝታቸውን እያነሳች ከምር ታለቅሳለች፡፡ ፊቷን በጣም ነጭተዋለች፡፡ እናትና አባቷም በሰው አገር ስለመቅረቷ፣ ያለጠያቂ ሞትን ስለመጋፈጧ እያነሱ ካጎራባች መርዶ የተቀመጡትን ስሜት በሚነካ አኳኋን ያለቅሳሉ፡፡ ፎቶ ግራፏን ይዘዋል፡፡ ልጅቷ አረብ አገር ለስራ ሄዳ መርዶዋ በጓደኞቿ አማካይነት በደብዳቤ እንደመጣላቸው ለመረዳት ችያለሁ፡፡

4. የልጅቱ ሕጻንነት፣ የቤተሰቦቿ ጉስቁልናና አለቃቀሳቸው የበርካታ ከልታማ እህቶቻችንና ያልታደሉ ወላጆችን ወካይ ሁኖ የበርካቶችን ልብ ሰብሮ አስነባ፡፡ ከሁለቱም መርዶ የሚለቀሰው ተቀምጠው ደራሽ ሲመጣ እየተነሱ እየተቀበሉ እንጂ እየዞሩ አይደለም፡፡

5. የእሙሃይ አስናቀች መርዶ ላይ የእድር አባላት መምጣት መቅረታቸውን ቁጥጥር የሚያደርጉ ሰዎች አሉ፡፡ ብዙ ደራሽ ለቅሶ ለመድረስ ሳይሆን ቀሪ እንዳይባል ስሙን ለማስመዝገብ የመጣ በሚመስል ሁኔታ ከመቀመጡ ተነስቶ ይሄዳል፡፡ አንድ ሰዓት ተኩል ሲሆን የሚመጣው ሰው ቀነሰ፡፡ ሁለት ሰዓት ላይ ሀዘንተኞቹ ተነስተው ወደየቤታቸው በጥቂት ሰዎች ታጅበው ሄዱ፡፡ በአለባበስ ጥልፍ ቀሚስ ወደኋላ አዙሮ ከጀርባ መደረብ፣ ነጠላ መዘቅዘቅም ሆነ ቀኝ እጅ ማውጣት ከእለት ለቅሶ የተለየ ባይሆንም የሰው ቁጥር በጣም አነስተኛ ነበር፡፡ መረጃ አቀባዮቼ የመርዶ ለቅሶ በደብረታቦር ዙሪያ እየቀነሰ መሄዱን የነገሩኝን የለቅሶው ስሜት ያንጸባርቃል፡፡

6. ወደእሙሁይ አስናቀች ወንድም ቤት ሀዘንተኞቹን ከተከተሏቸው ጥቂት ለቀስተኞች ጋር አብሬ ሄድኩ፡፡ ግቢው ውስጥ ድንኳን ተጥሎ ተረኛ የእድር አባላት ሀዘንተኞቹንና አጅቦ የሄደውን ውስን ለቀስተኛ ተቀብለው እህል ውሃ ሲያስተናግዱ ተመለከትኩ፡፡

### 1.2. የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ክወና

#### 1.2.1. የተጠኚው ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ድረሳ

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ ሞላ አየሁ (አባ.2፣ቁ.1)

**ለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 5/10/2004

*ጥያቄ፣ ወደ ሙያው እንዴት ገባህ?*

1. ወንድሜ ፍቃዴ መንግስቱ እምንለው አውደልዳይ ነበር፡፡ እንደ ሽፍታም ከላይ ከታይ ይላል፡፡ አሁን ያን ሰው ከምከም ሀዶ ኋደኛ ይገድለዋል፡፡ ኋደኛ ሲገድለው ልቅሶው ፍከራ ተባለ፡፡ አሁን ከለቅሶው ስንሸድ በወዲያ በኩል ይፎክራሉ፡፡ ሲፎክሩ አሁን እኔ ኽዘፈኑም ከዳስ ፍከራም ወሽክ ወሽክ እላለሁ፡፡ አሁን የገዛ ዘመዶቼ ናቸው እኔ ነቅቼ ሶስት ብረት ይዘናል፡፡ አራተኛ እኔ አለሁ፡፡ ቦት ቦት አግብተናል መቼም ወታደር መስለናል፡፡ ተው ለባለ ፈንታ ተው ለባለ ፈንታ ተባለ፡፡ ሲባል ለኔ ሰጡኝ፡፡

   ሀይ ዘራፍ! ይላል ፍቃዴ መንግሥቱ፣<br>በሙጫነቱ ገና በማርዳው፣<br>ቤቱ እንደ ንጉሥ የተሰናዳው፣<br>ወረዳ አውራጃ የሚያውቀው ልጁ፣<br>እጁ ሳይሰራ ባጭር ቀረንጂ፡፡

ብየ ስገጥም ‹‹እረ ሞላ አየሁ አይ አጅሬ›› ተባለ፡፡ በዚያን ጊዜ ፉከራ ብርቅ ነው፡፡ አጭር አልበገን ናት ደሞ ብረቴ ሙጨ ጠጋየ ‹‹ምንሽሩን ልስጥህ›› ብሎ እንዲህ እንዲህ አለ፡፡ ኽይድ ‹‹ከዚያው ይታወቅ እንጂ እመሚ›› አልኩና ሳብ ባደርግ ቡግግግ አለች፡፡ ደሞ እነዚያ አንድ ባሪያ አብሮን አለ ውለታው ቸሬ ደረሂና እሱ እተኩሳለሁ ብሎ ለካ ሽክፎ ቀርቷል፡፡ እየው በዚያ የተነሳ ነው የተጀመረ፡፡

*ጥያቄ፣ ፍከራውን በዚያ ቀን ነው የጀመርከው?*

አወ

*ጥያቄ፣ ከዚያ በኋላስ እንዴት ነበር ግጥሞቹን የምትገጥማቸው?*

2. ከዚያ በኋላማ ስሊት ማምስልሰል ደግሞ ጓደኛ (ፎካሪ ) ይመጣብኛል ከዚያ ያ እንዳያጠቃኝ አጠቃ አልጠቃ ያለ መከራ። አባ ካሴ (በአካባቢው ታዋቂ የነበሩ አዛውንት ናቸው) የሞቱ ጊዜ ተክሌ (ፎካሪ) እኔ ሳላሰብኩትም አምላክህ አለ፣

«ገድብ ነው እንጂ አገረው የሚያውቀው አርበኛ እሚያውቀው፣
እንደ ሽለቆ ጠጅ እሚፈልቀው፣
ዛሬም ይሸታል ሀደባልቂ ቤት የገድብ ጠጅ፣
አሳላፊ አጥተው አይሰጡም እንጂ።»
ብየ ፎከርኩ። «ሰደበነ እኮ» ብሏል።
እሽ

ጫኔ ገበየሁ ‹‹አሳላፎቹ ነነ እንጂ አንተማ ያባትህ ጠጅ እየወረደ አይደል›› ብሎታል።
‹‹አይ ሰደቦናል። ያችን ሞላን እሚያጠቃልኝ ባገኝ እሽልመው ነበር›› ብሏል።

እሽ

3. ‹‹አይ ለሞላማ እኔ አይደለሁ እንጥሏን እምቆርጠው›› ሲል ኂላ አባ ካሴ ሙተው እንዲያው ሙሽራ ነኝ እኔም ዕጨብጥ እጨብጥ እያልኩ እውሽከሽካለሁ ገና ፎካሪም የለ ደንቆሮ ነው አገሩ። ኂላ ተክሌ ከልቅሶው ድርስ ስል፣
‹‹ያንዱነን ልቅሶ ሀንዱ ኸማልቀስ፣
መሞት ይሻላል እረ አፈር መልበስ።
ያንዱነን ልቅሶ ሀንዱ ኸመደብለቅ፣
መሞት ይሻላል እረ መታነቅ።›› ይላል።

እሽ

4. በዝች እንግዲህ ግጥሙም ያንሰኛል  መልዛ እህዳለሁ፣ ከምከም እሽዳለሁ፤ አሞራ ገደል እሽዳለሁ። እንግዲህ «አነዚያን አትጥራ» ነው። እንግዲህ አርበኞይ ተሆኑ ምን አገባኝ ብዬ አደባልቃለሁ።

እሽ

ይላክብኛል በቡኋላ የኔ ተራ ደረሰ።

እሽ

ፋርጣ በፈረስ ሊጠቀጥቀኝ፣

የርቡን ሞላ ስሜን ሳያውቀኝ።

ጥንትም የሞተ ወገናችን ነው፣

ዛሬም የሞተ ወገናችን ነው፣

የሚያላቅሰን ወገናችን ነው፣

ያን እያነሳን ብናለቅስበት ነውሩ ምንድን ነው? በል!

ለስሙ ሱሪ የማይችለው፣

ለደረቱ ኮት የማይችለው፣

ሊሰድበኝ መጣ ባለጌው ሰው፣

ምን ግንፍል ግንፍል እንደ ጫሀና

አሽርሻለሁ ዳግም በይና (ሳቅ)

እንግዲህ ለደረቱ ኮት ያልኩት እንድች ያለች ናት (ደረቱ ላይ ኮቱ ጠባብ መሆኑን በእጁ እያሳየ) የለውም። ደሞ ለጭኑ ሙታንታ ናት (ቁምጣ) እኔ ቡላሌ አርጌያለሁ። ሰው መጋጠማችን አውቋል ‹‹እንኳን እግዚሃር አወጣህ›› አለኝ።

*ጥያቄ፣ ግጥሙን እዚያው ላይ ገጥመህ ነው የመለስከው?*

5. እንግዲያ ተዚያው ላይ! እንግዲህ በፊትም ቀን ጎሰም አርጎኛል።

ባሁኑ ግዜ ለእናት አገሬ እየተባለ፣

ለእናቶቻችን ሳይፈከር፣

እናቶቻችን ትልቅ ትልቅ ሰው፣

አንጀት እንደ ልጥ የምታርሰው፣

ራብን በእህል የገደለችው፣

አመት አጥብታ ያሳደገችው፣

የሷነን ልፋት መንግስት አውቆታል፣

እኩልነትም ተፈቅዶላታል፡፡

እኩልነትን አልፈቅድም ላለ፣

ሁለት ወር ታስሮ ይቅርታ እንዲል፡፡ ብያለሁ፡፡

እሽ

‹‹ደሞ ሴትን ምን አገባት?›› ብሎ ቦጨቅ አረገኝ፡፡

እሽ

መቼስ የእንግዳ መጠባበቂያ ብዬ አምሰላስያለሁ፡፡ (ሳቅ)

*ጥያቄ፣ ወደ ፋከራ ተጠርተህ ነው የምትሄድ?*

6. እንዴ አወ መጥቶ ለምኖኝ ነው እንጂ፡፡

   *ጥያቄ፣ ያ ሰው መጥቶ ሲወስድህ ለዚያ ሰው ለመፎከር (ለግጥሙ) መነሻ የሚሆንህ ምኑ ነው?*

   ገበሬ ተሆነ ያንዱ ላንዱ ይሆናል፡፡ ብቻ ስሙ ነው እንጅ የሚለወጥ ያንዱ ላንዱ ይሆናል፡፡ ወታደር ተሆነ ያንዱ ላንዱ ይሆናል፡፡ ያንዱ መደብ ለብዙ ይሆናል፡፡ በዚያ ነው የምገጥመው፡፡

   አሁን ገበሬ

   ደህናው ገበሬ እውቀት ያለው

   ያለ ጥረጨው ሁሉን ዘራው

   ገበሬ ዓለሙ

   ካማጋው ብኸድ በሬና ላሙ

   ከቤት ብገባ ቅቤና ማሩ

   ኸገበሬ ቤት ብገባበት

   አቅርቦ ሰጠኝ እኔ እንዳልኩት

   እላለሁ፡፡ ይኸ እንግዲህ ለሕዝብ (ለብዙ) ይሆናል፡፡ ስሙ ብቻ ነው የሚቀየር፡፡ በዚህ ነው የምገጥመው፡፡

*ጥያቄ፣ ይህን አሁን ያልከውን ግጥም ገበሬ ከመሞቱ በፊት እንዴት አድርገህ ነው የምትገጥመው (የምታምሰለስለው)?*

7. በለሊት ነው፡፡ አነሳ እጥለዋለሁ፡፡ ለእያንዳንዱ እያምሰለሰልኩ ቁልፍ ቁልፍ አብጅቸለታለሁ፡፡ እንደዚህ ያለው ቢሞት እንደዚህ ነው ፍከራው፡፡ እንደዚህ ያለው ቢሞት እንደዚህ ነው ፍከራው እያልኩ አስቀድሜ በየክፍሉ አስቀምጥለታለሁ፡፡ ሰው አሁን ምን ግዜ ገጠምከው ይላል፡፡ ተፈጭቶ ተቦክቶ የተቀመጠ ነው፡፡ አሁን አስፈጭተህ ብታቦካው ላሁን እንጀራ ይሆናል; (ሳቅ)

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ ደሳለኝ ታየ (አባ.2፣ቁ.7)
**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 29/09/2004

*ጥያቄ፣ አሁን እርስዎ ለሰው ወየ ሲሉ፣ ሙሾ ሲያወጡ መነሻ የሚያደርጉት ምኑን ነው? ግልጽ እንዲሆንለዎት አሁን በቀደም ሙሾ ለወይዘሮ አጸዴ አውርደዋል፡፡ ዛሬ ላቶ ዋለ፡፡ በሁለቱ ለቅሶ ያወረዱት ሙሾ አንድ አይነት ነው?*

አይደለም፡፡

*ጥያቄ፣ የልዩነቱ መነሻ ምንድን ነው?*

1. አሁን ከእነዚህ ተለምኖ ነው፡፡ የሰው ድሃ ናቸው፡፡ የማርገጃ ድሃ መሆን

መች እንደዚህ ነበር የማርገጃ አውድማ፣

ረግ ረግ ይላል ወገን ያለውማ፡፡

ማልቀስ ለድሃ ነው ማልቀስ ለምስኪን ነው፣

ሀብታምማ ሰሲሞት አልቃሹ ብዙ ነው፡፡

አሁን ይኸ ራሱ ድሃ መቼም ድሃ ነው፡፡ ልቅሶውም አያምር ኑሮውም አያምር፡፡

‹‹ደሞም እንደ ኑሮሽ ልቅሶሽ መነመነ፣

ምን አረግሻለሁ እድልሽ ከሆነ፡፡›› ብሏል፡፡ የሌለው ሲኖርም ሲሞትም አያምርበትም፡፡ ይኸ ራሱ አንድ ነገር ነው፡፡

*ጥያቄ፣አሁን ወየ ለማለት ወይም ሙሾ ለማውረድ የሰዎቹን ታሪክ ታጠናላችሁ፣ ስራቸውን? አሁን አንድ ቦታ ሄደው ደርሰው ወየ ይላሉ ወይስ የሰውየውን ታሪክና ሥራ አጥንተው ነው?*

2. ሲፎክርም እኮ ፎካሪ አጥንቶ ‹‹ምንድን ስራ ነው በግብርናው ነው የሚፎክር በምንድን ነው በዘመቻው ነው፣ ነጋዴ ነው ወይንስ ምንድን ነው?›› ተብሎ ተጠንቶ ነው። ነጋድራስ ከሆነ ነጋድራስ ይባልለታል። ምንነቱን አውቆ እንጂ ዝም ተብሎ ተሂዶ ወየ አይባልም። ተጠንቶ ነው። ‹‹ከየት ነው? እንዴት ነው ኑሮው?›› ተብሎ ተጠይቆ ‹‹እዚህ እዚህ ነው›› ተብሎ ነው። እንዲያው ዝም ብሎ ‹‹ወየ በሉልኝ›› ወይም ‹‹እንዲህ በሉልኝ›› አይባልም። እኔ ወየ ብየበታለሁ እኮ።

   እንደማንም ብለህ ግባ ወደ አገርህ ልቀቅ የሰው ታቦት፣

   አውጥቶ እንዳይጥልህ ባላባቱ ሲሞት ብያለሁ። አሁን ለምሳሌ

   ኑሮን በሰው አገር ሞት ባገር ይደምቃል

   ያም መጥቶ ያም መጥቶ ከአንገት ላይ ይወድቃል። አለ። መተዋወቅ አስፈላጊ ነው። አሁን ለምሳሌ መቼም ሰው ‹‹ቅምስ ቅምስ አርገህ ወደ አገርህ እንጂ›› ያለው መጠጡ ይጠጣል። መብሉ ይበላል። ግን ‹‹ምን ያረግልሃል የሰው አገር ቢራ፣ የሰው አገር ጮማ የሰው አገር ጠጂ፣

   ቅምስ ቅምስ አርገህ ወደ አገርህ እንጂ›› ያለው ነው። አሁን ሁሉም የሚያምር ባገር ላይ ነው። ኑሮውም ይለያል። ምንድን ነው ተብሎ ምንነቱ።

*ጥያቄ፣ ሙሾአውራጅ ከሙሾ አውራ ስትገናኙ እንዴት ነው የምታደርጉ? እስቲ ገጠመኝዎትን ያጫውቱኝ*

3. አሁን የሙሾ ሁኔታ ያው እንደነገርኩህ አምስት አምስት ዙር ነው። መጀመሪያ ይኸ ይባላል። ኋላ ተከታው ነው። ከዚያ ላይ ደርሶ አይሰቀልም። ከታች ይባልና ይኸ በዚህ ቢመጣ ይኸ በዚህ ቢመጣ አንድ ሰሞን ይኸ በድርቡ ያለው ሙሾ መጣ። ኋላ እሱ ሲባል ያ የሞተው ሰውየና እኔ ብቻ። ማን ይበለው። ተቀባውስ ማነው? ኋላ እነዚያ ሰዎችና እኛ ገጠምነ። እሃ ተዋቅተን፣ ተዋቅተን ኋላ ያንን ሙሾ እኛ በውነትም አጠቃነ። ስናጠቃ ምን ይዞነ ይኸዳል ምን መጠጥ ነው የምትሉት ኸዚያ ገባነ እነዚያም ቢጠቁም መቼም አብረው መጥተዋል ሳቅ ጨዋታ ሆነ ማታ። መቼም ብዙ ነገር አለ

ይኸ ሙሾ አውጭ ሲገናኝ ረፍት ሲገኝ እነደዚህ ባለው ባል ጨዋታ ሞልቷል፡፡ ‹‹ግጠምልኝ አቶ እገሌ›› ብለውታል ‹‹አቤት፡፡›› ‹‹አንተ እኮ ፈጥረህ ነው የምትል ግጠምልኝ›› አለው፡፡

‹‹በምን?››

‹‹ለእኔ ብልት ወየ በልለት››

‹‹‹ብልቴ ሙቶብኛል ወየ በልልኝ› ብሎታል››

‹‹እሺ››

አሁን ያ ሰው መልከኛ ነበር ያየኸው እንደሁ የተቀሸረ መኳንንት ነው፡፡ ኋላ አብልቶ የሚያጠጣ ሀብታም ነው ፡፡

‹‹እሽ ልበልልህ?››

‹‹አወ››

‹‹እረ አይዋ እገሌ እረ አይዋ እገሌ፣ መልኩ የሰለሞን ቁመቱ ያንበሳ ቁመቱ ያንበሳ››

‹‹ሲለፋ ይኖራል ተሸክሞ ሬሳ›› አለው፡፡

4. ከዚያ አንች ሰውየ ዛሬ አለና ካሳ ቢራ አስመጣና ከዚህ ላይ አስደረደረና ‹‹ጠጣ ዝም ብለህ፡፡›› ኋላ እንደዚህ እየተጠጣ ገብስ ጥሬ ተደፍታለይ፡፡ ‹‹አሁን በዝች ገብስ የሚገጥም ማነው?›› አሁን ሀይለኛ ነው ያኛው፡፡ ‹እኔ አቶ እገሌ በዚህ እገጥማለሁ፤ ብቻ ወደ ነውርነቱ አትውሰዱብኝ እንጂ እኔ እገጥምበታለሁ›› አለ፡፡ ገጠመመበት፡፡

‹‹አየ እእእ እእእ አወይ እእእ እእእ፣

ጌሾው እእእ ይዳፋ እንጂ እእእ ምን ባለ ነው ገብሱ››

‹‹እህ››

‹‹እንግዲህ እስዎ ዝም ብለው ይፈሱ›› አለ፡፡ ሴትዮቱ ያስገጣሚው ውሽማው ነበረች፡፡

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ አበረ ክበበው (አባ.2፣ቁ.10)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 25/09/2004

*ጥያቄ፣ ወደሙያህ ልመልስህና የፎከርከውን ግጥም ከየት ተማርከው?*

1. (ሳቅ) ከማን እማረዋለሁ እራሴ ፈጥሬው ነው አንጂ፡፡ እንግዲህ መጠጥ እጠጣለሁ፡፡ እንዲህ ብየ ውየ ህጁ ከቤቴ ስተኛ ጠቅላላ ብርሃን ሆኖ ነው የሚታየኝ፡፡ ሌሊት እንዲህ አድርጎ ሲያሳድረኝ አንዱን ከአንዱ፣ አንዱን ከአንዱ ሳጣልፈው አድራለሁ፡፡ አንዱን ካንዱ እያደረኩ አሁን ስሞክር ስሞክር ትንሽ የሁለት ሶስት ጊዜ ሞከርኩ፡፡ የሶስት አራት ጊዜ ጨመርኩበት፡፡ አሁን ትንሽ እንደመጠጥ ያለ ከጠጣሁኝ ከበላየ ላይ ያለው በቃ አይታወቀኝም፡፡ ከደረሰም የማደርገውን አላውቅም፡፡ ዝም ብሎ መጥቶ ራሱ ግጥም ራሱ ግጥም ነው እንጂ ወይም ጽፌ ወይም አንብቤ ስሜን በፍጹም አልፈርመውም፡፡ እግዚአብሔርን ከወንድም መሃል ነበር የምነግርህ አሁን፡፡ ስሜን አልፈርምም፡፡ መጥቶ ጥልፍ ጥልፍ ይልልኛል፤ ዝም ብሎ ወጥ ሁኖ ይቀርብልኛል፤ ከበላየ ላይ ያለው ያሳካዋል፡፡ አሁን በግብርና ሙያ እፎክራለሁ፤ በዚህ በጀግኖችም፣ በመምሮችም፣ በዘማቾችም፣ በተለያየ ነገርም አንዳንዶቹ መቼም ትንሽ ቀለሞች ያስፈልጉኛል፡፡ ግን አንዳንዶች ‹‹ላንተ እስቲ ጻፍ እናስጽፍህ፤ ትንሽ እናስጽፍህ ደግሞ ጨምር ይሉኛል፡፡ ታዳያ አልገባኝ ብሎ ቀረ፡፡ ጽፈው የሰጡኝ ስለማላነበው አልገባኝ ብሎ ቀረ፡፡ ግን ራሱ እግዚአብሔር የፈጠረ ንጉሥ ግን በቃ እንዳየኸው ነው፡፡

ጥያቄ፣ አሁን ስትፎክርላቸው የቆየህላቸውን ሰው ታውቃቸዋለህ?

አላውቀውም፡፡

*ጥያቄ፣ ስራቸውንስ ጠይቀሃል?*

2. አወ አጎቱ የእኔን የአጎቴን ልዥ ነው ያገባ፡፡ ደግሞ ለዚያ አጎት ነው፡፡ የአባቱ ትንሽ ወንድም ነው፡፡ አሁን እንደዚህ አጎቴ ሙቷልና እንሂድ ብሎኝ ነው እንጅ ሰውየው ጥቁር ይሁን ቀይ ይሁን አላውቀውም፡፡

*ጥያቄ፣ የሰውየውን ታሪክ ነግሮሃል?*

ታሪኩን ነግሮኛል፡፡ አወ የቀደም አድራጎቱን የወንድሙን ‹‹እንዲህ እንዲህ ያርስ ነበር፣ እንዲህ ያል ሀብት ነበረው፤ እንዲህ እንዲህ አድርጓል፤ ልዥ ድሯል፤ እምርቷል፤ እንዲህ እንዲህ አድርጓል፡፡›› ብሎ ነገረኝ፡፡ በቃ አኔ ይህን እያነሳሁ ማንጠባረቅ ነው፡፡

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ ታከለ ንጋቱ (አባ.2፣ቁ.13)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** ኢ.ኢ.አ. 25/09/2004

*ጥያቄ፣ ግጥሙን እንዴት አድርገህ ነው ለሰዎቹ የምትገጥመው?*

1. መጀመሪያ የሰውየውን ታሪክ ምን ምን እንደሰራ እጠይቃለሁ፡፡ ይህን ይህን የሰራ ነው ይለኛል፡፡ ከዚያ እኔ ሂደቱን አቀነባብረዋለሁ፡፡

*ጥያቄ፣ ምን ጊዜ ነው የምታቀነባብረው ሌሊት ነው?*

2. እረ አይደለም ዝም ብየ ወዲያው የፈጠራ ችሎታ ነው፡፡ ከብት ይሸለማል ከዚያ ላይ እወጣለሁ፡፡ ከዚያ ግጥሙ ይመጣልኛል፡፡ ተፈጥሮ ነው አላጠናውም፡፡ ዝም ብሎ ይመጣል፡፡ እስካባቱ እስካያቱ እገጥምለታለሁ፡፡ በዘራቸው ሁሉ ይቀርባል፡፡ ምንም ችግር የለውም፡፡

   ደህናው ገበሬ የተሰናዳ፣
   ይሸኝ ነበር አያሌ እንግዳ፣
   እህል ይዛቃል በትልቅ አቅማዳ፡፡
   ክርክም ገበሬ የተዘጋጀ፣
   ምንም ሳይቸግረው እድሜውን ፈጀ፡፡
   (ይኸ የገበሬው ነው) የነጋዴው ደሞ
   ነጋዴን ሳንሳው እንደምን ልተው፣
   ብር እሚያከማች ድርቅ እማይታው፣
   ነግዶ በርግዶ ያቀናው ቤት፣
   ይጠጣ የለም ወይ ማር ተወተት፡፡

1.2.2.የተጠኚው ማሕበረሰብ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች አካባቢያዊ ምደባ

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ ብርሃን አበበ (አባ.2፣ቁ.16)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 29/09/2004

*ጥያቄ፣ በዚህ አካባቢ በለቅሶ ላይ የሚገጠሙትን ግጥሞች ምን ብላችሁ ትጠሯቸዋላችሁ?*

1. አልቃሽ ይፎክራል ያቅራራል፡፡

*ጥያቄ፣ ሌላ ምን አለ?*

1. ሌላ ሙሾና ወየታ ነው በቃ፡፡ ልክ እሱ እንዳለው አሁን ልክ ቀረርቶዎችና ፉከራ እሚባለው የሰውየውን እንትን ለማንጸባረቅ፣ ወይም ደግሞ ሀዘንተኞቹ እንዳይጎዱ ለማድረግ ነው፡፡ በቃ ምንም እማያውቅህም ቢሆን እንኳን ሰዎቹ በጣም እንዳይደክሙ አድሯል ደሞ ሊውል ነው እነዚህ አዘንተኞች እንዳይጎዱ ዝም ብሎ ባያውቀውም አልቃሽ እንኳን ባይገዛ እያንዳንዱ ሰው ያለቅሳል፡፡ ለምን «አይ የኛ ለቅሶማ ሰው የሌለው በመሆኑ እንዳይባል እንደዚህ አድርጋችሁ አውሉት» ይባላሉ፡፡ እና እኔ እንደማውቀው በዚህ አካባቢ ያለው፣ ሙሾ፣ ወየታና ያው ፍከራ ነው፡፡

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** *መሪጌታ* ስቡህ ዘላለም (አባ.2፣ቁ.4)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 10/09/2004

*ጥያቄ፣ እንናንተ ግጥም ነው እያቀረባችሁልኝ ያለ፡፡ እነዚህን ግጥሞች በተለያየ ዜማ የምታቀርቡባቸው ስማቸው ምን ምን እንደሚባል ብትጠቅሱልኝ፡፡*

1. በግጥም መልክ ሁኖ በዜማ የሚቀርበው እኔ እንደተረዳሁት ሶስት ነው፡፡ አንደኛው የወየታ ግጥም ነው፡፡ ከዚህ በአባባልና በዜማ የሚለየው ሁለተኛው ሙሾ ነው፡፡ ሶስተኛው ፉከራ ነው፡፡ ፉከራም የአባባልም የአገጣጠም ስልት አለው፡፡ እነዚህ ባቀራረብና በዜማ ይለያዩ እንጂ በግጥም ሙሾ የተባለው ወየታም ይሆናል፡፡

1.2.2.1. ወየታ

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ ደሳለኝ ታየ (አባ.2፣ቁ.7)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 29/09/2004

*ወደ ሌላ ጥያቄ ልመልሰዎትና የወየታው ግጥም አሁን ለሙሾ ይሆናል?*

1. አየ አይሆንም። የዜማው ስብር ብቻ ላያመጣው ይችላል። ያነን የሙሾው ሊያራዝም ይችላል ከስብሩ። ይኸኛው (ወየታው) ተሎ ሊሰብረው ይችላል። ወየ ሲባል አንድ ሰው ብቻ ድምጹን አሳምሮ ሲያንጎራጉር ሌላው ይቀበለዋል። ሙሾ አንድ ሰው ብቻውን አያወጣም። በወየታ አይረገድም። ሙሾ እንዳየኸው ያለ እርግዶ አይሆንም። ከዜማ ስብራቸውም በጣም ይለያያሉ። ወየታ ለሕጻኑም ለትልቁም ይባላል። ሙሾ ሳካለመጠን ላልደረሰ አይባልም።

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ ዋለ ጎበና (አባ.2፣ቁ.14 ክፍ. አን.)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 29/09/2004

*ጥያቄ፣ በሙሾና በወየታ መካከል ያለው ልዩነት ምን እንደሆነ እስቲ ይግለጹልኝ*

1. ሁለቱ ባቀራረብና በዜማ ይለያዩ እንጂ በግጥም ለሙሾ የተባለው ለወየታም ይሆናል። እሚለያዩ ባቀራረባቸው፣ በዜማቸው ስብርና በሚቀርቧቸው ሰዎች ነው።

*ጥያቄ፣ እስቲ አንዳን ግጥም ይውሰዱና በሁለቱ ዜማ ልዩነታቸውን ያሳዩኝ*

2. እንዴት አደራችሁ፣

   አሁንም ቅድምም፣

   ይህ የያዝነው ጊዜ፣

   አያስተማምንም። (ሙሾ ነው)

3. በይ እራቱን ስጭኝ፣

   በጊዜ ልብላው፣

   ከተኛ አይነሳም፣

   የዚህ ጊዜ ሰው። (ሙሾ ነው።)

4. በይ እራቱን ስጭኝ በጊዜ ልብላው፣

   ከተኛ አይነሳም የዚህ ጊዜ ሰው። (ወየታ ነው)።

5. እነዚህ ሀኪሞች በጣም ይለፋሉ፣

ቲቪ ነው ይላሉ፣ ጉበት ነው ይላሉ፣

አላዳኑም እንጂ ስም ማውጣት ያውቃሉ።

6. እንዴት አደራችሁ አሁንም ቅድም አሁንም ቅድምም።

ይህ የያዝነው ጊዜ አያስተማምንም (ወየታ ነው።)

(በወየታው ድምጻቸውን ዘለግ አድርገው ሲያንጎራጉሩ አንዱን ስንኝ ባንዴ ይሉታል። በሙሾው አንድን ስንኝ በሀረግ እየከፈሉ ሲያቀርቡት ዘሜማውም የተለየ ነው።)

1.2.2.2. ሙሾ

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ ወንዳያ ጓንጉል (አባ.2፣ ቁ.15)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 17/09/2004

*ጥያቄ፣ ሰዎች በቡድን ሁነው ግራ ቀኝ እየዘመሙ የሚያንጎራጉሩት ዜማ ምን ተብሎ ይጣራል?*

1. አልቃሽ ባለበት ይለቀሳል። ዱሮ ዱሮ ስንሰማ እርግዶና ሙሾ የሚባል ነበር። ሰው ክብ ሆኖ እርግዶ ይረገዳል። ትልልቅ ሰዎች ሁነው ያሞሸሙሻሉ። እንዲህ እንዲህ የሚል (ግራና ቀኝ ከትከሻቸው እየተወዛወዙ) ውዝዋዜ ችሎታ የነበራቸው ሙሾ ያወጣሉ። ዱሮ ይኸ ነው የነበረው። አዘንተኛው ውጭ ወጥቶ ሌላ ሰው እየተቀበለ እያለቀሰ ነው የሚቀመጠው።

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ ደሳለኝ ታየ (አባ.2፣ቁ.7)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 29/09/2004

2. እንደሰው ብዛት በዚህ ሶስትም፣ አራትም እስተ ዘጠኝ ሁነን እንቆማለን። በኛ ቁጥር ልክ በዚያም ይቆምና እያረገድነ አንዳችን ስናወርድ ሌላችን እየተቀበልነ የምናቀርበው ነው። የዜማው አመጣጥ ብዙ አይነት ነው ዜማው። አሁን፣

‹‹ዋየ እያሉ ሄዱ ወየሁ›› ይላል። ያኛውም ይቀበልና

‹‹ዋየ እእእ እያሉ ሄዱ ወየሁ›› ይላል። ‹‹እረ አወይ እረ አወይ ወየሁ ዋዋ›› እያለ እየሰበረው ይኸዳል። ሌላው እየተቀበለ በዚህ በዚህ በኩል የሚባለውን እየገጠመ እየገጠመ ነው የሚሄደው።

*ጥያቄ፣ አሁን ያሉልኝ ባጠቃላይ ምንድን ነው በአካባቢው አጠራር?*

3. በአካባቢው አጠራር ሙሾ ይባላል፡፡ ወየታ በዙረት ሙሾ በማስረገድ ነው፡፡ አላየሕም እንዲያውም ዛሬ ደህና አስረጋጆች እኮ ገብተው አባ አግማሴ ማለት ነው ዱሮ ሲያረግድ እኮ ዱሮ እንዲህ እንዲህ (አንዴ ወደ ግራ እንዴ ወደቀኝ ከወገብና ትከሻቸው እየተናጡ) ብድግ ቁጭ ከዚያ እንዲህ እንዲህ እንዲህ የዘለለ ጊዜ (አሁንም ወደ ቀኝና ወደ ግራ እየተናጡ) በቃ ያን ግዜ ገንፍሎ ይኸዳል፡፡

*ጥያቄ፣ እነሱ አስረጋጅ ነው የሚባሉ?*

4. አወ አስረጋጅ ነው የሚባሉ፡፡ ሕሩይ የዓለምነው መንግስቴ ለቅሶ ጊዜ እርሰዎ ሲያስረግዱ አይቸዎታለሁ፡፡ (አወ አባ አግማሴ ዘመዳችን ነው እንግዲህ) ሰው ይላል እንግዲህ፡፡ ከሙሾ ‹‹እነእገሌ እነገሌ ግቡ›› ብየ የሚያስረግደው የለም ብየ ነው ያኔ አስረጋጅ የሆንኩ፡፡

*ጥያቄ፣ ሁሉም ሙሾ ተመሳሳይ ነው?*

አይደለም ዜማዎቹ ማቅረቢያዎቹ ይለያያሉ፡፡

*ጥያቄ፣ ስንት ዜማ አለ?*

5. ወዳጅ ወዳጄ ፈረስክ እያሉኝ ልዘን ዋ፣ አንዱ ሲሆን ባለ ሁለት ድርብ ይባላል፡፡

*ጥያቄ፣ እስቲ አንድ ግጥም በዚህ ዜማ ይበሉልኝ?*

አውራጅ፣ አወይ ዋይ አወይ ዋይ አወየው ዋይ ዋይ

ተቀባይ፣ ወዳጅ ወዳጄ ፈረስክ እሉኝ ልዘን ዋ

አውራጅ፣ የሰንበት ቁርስና ያባት ዳረጎት

ተቀባይ፣ ወዳጅ ወዳጄ ፈረስክ እያሉኝ ልዘን ዋ

አውራጅ፣ አወይ ዋይ አወይ ዋይ አወየው ዋይ ዋይ

ተቀባይ፣ ወዳጅ ወዳጄ ፈረስክ እያሉኝ ልዘን ዋ

አውራጅ፣ ምን አነሰ ቢሉት አለው ረዶት

ተቀባይ፣ ወዳጅ ወዳጄ ፈረስክ እያሉኝ ልዘን ዋ

6. ሁለተኛው አይነት ዜማ ደሞ፡-

አውራጅ፣ እረ አወይ እረ አወይ አወየው ዋይ ዋይ (ይልና መስበሪያው ‹‹ዋየ ዋይ ወየሁ›› ነው)

ተቀባይ፣ ዋየ ዋይ ወየሁ

አውራጅ፣ ባዝን እዘኝ እንጂ

ተቀባይ፣ ዋየ ዋይ ወየሁ

አውራጅ፣ ባለቅስ ስትስቂ

ተቀባይ፣ ዋየ ዋይ ወየሁ

አውራጅ፣ አዘን ጥናቡግ ነው

ተቀባይ፣ ዋየ ዋይ ወየሁ

አውራጅ፣ ለሁሉም ዘላቂ

ተቀባይ፣ ዋየ ዋይ ወየሁ

*ጥያቄ፣ ይኸ ስሙ ምን ይባላል?*

ይኸ አንድ ዜማ ነው የሚባል። እንግዲህ ሁለት በል።

7. ሶስተኛው ደግሞ፡-

አውራጅ፣ ዋየ እያሉ ሄዱ ወየሁ ዋዋ/ዋየ ዋየ

ተቀባይ፣ ዋየ እያሉ ሄዱ ወየሁ ዋዋ

አውራጅ፣ በላሁ በላሁና ተኛውሁ እንደ በሬ

ተቀባይ፣ አየ እያሉ ኸዱ ወየሁ ዋ

አውራጅ፣ ያነን ያህል ጉድንድ ወየሁ ዋ

ተቀባይ፣ አየ እያሉ ኸዱ ወየሁ ዋ

አውራጅ፣ ጫን አፈር አኑሬ ወየሁ ዋ

ተቀባይ፣ አየ እያሉ ኸዱ ወየሁ ዋ

*ጥያቄ፣ይኸ ምን ይባላል?*

ይኸ ሶስተኛው ዜማ ነው። ይኸም እንደ ሁለተኛው ነጠላ ነው።

8. ይኸኛው ደሞ ‹‹አወየው ዋይ ዋይ ወየ/ሁ›› ይባላል፡፡

‹‹በዝችም አንድ ልግጠም?››

‹‹አወ››

‹‹እሽ››

አውራጅ፣እረ አወይ እረ አወይ አወየው ዋይ ዋይ፣

ተቀባይ፣ ወየሁ

አውራጅ፣ እረ አወይ እረ አወይ አወየው ዋይ ዋይ፣

ተቀባይ፣ ወየሁ

አውራጅ፣ እረ እንቢ አላኮራም ነው ወይ (ወደ ግጥሙ ሲገባ መሆኑን ጠቀዋሚ ነው)

አውራጅ፣ ባዝራይቱ ሙታለይ

ተቀባይ፣ ወየሁ

አውራጅ፣ የሠንጋው እናት

ተቀባይ፣ ወየሁ

አውራጅ፣ ላሚቱም ሙታለይ

ተቀባይ፣ ወየሁ

አውራጅ፣ የበሬው እናት

ተቀባይ፣ ወየሁ

አውራጅ፣ በሬውም ሞተ አሉ

ተቀባይ፣ ወየሁ

አውራጅ፣ የእንጀራው ማቶት

ተቀባይ፣ ወየሁ

አውራጅ፣ ሊቀር ነው መሰለኝ

ተቀባይ፣ ወየሁ

አውራጅ፣ በልቶ መጠጣት፡፡

ተቀባይ፣ ወየሁ

ይኸም ያው ነጠላ ነው፡፡

አቶ ትዛዙ ይኸ የሙሾ አይነት በጣም አስቸጋሪ መሆኑን ገልጸው በእያንዳንዱ የሙሾ ግጥም መጀመሪያ አውራጁ ‹‹አወየው ዋይ ዋይ›› ሲል ተቀባዮቹ ‹‹ወየሁ›› እንደሚሉና ‹‹እረ እንቢ አላኮራም ነው ወይ›› ሲል አዲስ ግጥም ሲጀምር መሆኑን ማሳወቂያ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

አውራጅና ተቀባይ በመነሻው ላይ የተለያየ ዜማ የሚያወርዱበት የሙሾ ንዑስ ክፍል ሁኖ ተገኝቷል፡፡

9. ‹‹አየ/ዋ ተለየነ/ አየ ያለው ማነው›› ደግሞ አምስተኛው ዜማ ነው፡፡‹‹ያዝናል ሆዴ››ም እንለዋለን፡፡

አውራጆች፣ አየ ተለየነ፣ (ከ5 ጊዜ ላላነሰ)

ለቀስተኛቀው፣ አየ ተለየነ፣ (እንደ አውራጆቹ)

መሪ፣ አየ ተለየነ፣ (ከሶስት ጊዜ ላላነሰ)

አውራጆችና ለቀስተኛ፣ አየ ተለየነ፣ (በመሪው ልክ)

መሪና አውራጅ፣ አየ ተለየነ፣

ተቀባይና ለቀስተኛ፣ አየ ተለየነ፣

አውራጅ፣ አየ ተለየነ፣

ተቀባይ፣ አየ ተለየነ፣

መሪ፣ በሰማይ የሚጸድቅ፣

መሪና አውራጅ፣ በሰማይ የሚጸድቅ፣

ተቀባይ፣ አየ ተለየነ፣

መሪ፣ በሰማይ ይጸድቃል፣

መሪና አውራጅ፣ በሰማይ ይጸድቃል፣

ተቀባይ፣ አየ ተየነ፣

መሪ፣ የሰንበትን አፈር፣

መሪ አውራጅ፣ የሰንበትን አፈር፣

ተቀባይ፣ አየ ተለየነ፣

መሪ፣ ማን አግኝቶት ያውቃል፣

መሪ አውራጅ፣ ማን አግኝቶት ያውቃል

ተቀባይ አየ ተለየነ

አንችም ዘመናይ ነሽ በሥራው መሞትሽ፣

በክረምት መሞትሽ በሀምሌ መሞትሽ፣

በበጋ አትሞችም ወይ

በባል አትሞችም ወይ እንደ ድህነትሽ፡፡

አየ ያዝናል ሆዴ

አውራጅ፣ አየ እእእ ያዝናል ሆዴ

ተቀባይ፣ አየ እእእ ያዝናል ሆዴ

አውራጅ፣ ወየ እእእ ያዝናል ሆዴ

ተቀባይ፣ አየ እእእ ያዝናል ሆዴ

አውራጅ፣ እንዲህ እንዲህ ብዬ

ተቀባይ፣ አየ ያዝናል ሆዴ

አውራጅ፣ ና ያልከኝ እንደሆን

ተቀባይ፣ አየ ያዝናል ሆዴ

አውራጅ፣ አንተ መጠይቅ ወዳጅ

ተቀባይ፣ አየ ያዝናል ሆዴ

አውራጅ፣ ምን እመልስ ይሆን

ተቀባይ፣ አየ ያዝናል ሆዴ

ጥያቄ፣ ሌላ አለ ከዚህ ውጭ?

የለም፡፡ እነዚህ አምስቱ ናቸው፡፡ የመጀመሪያውን ግን እንደነገርኩህ የሚችለው የለም፡፡ ድርብ ስለሆነ ለተቀባዩ ያስቸግራል፡፡

አምስተኛው የሙሾ ንዑስ ዜማ ‹‹ዋየ/አየ ተለየኑ›› ከሚለው ጋር ተመሳሳይ መሆኑን በክወና ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የአንድ ዜማ አማራጮች ሲሆኑ የሚቀርቡት በሙሾ መጨረሻ ነው፡፡

1.2.2.3. **ቀረርቶና ፉከራ**

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ ወንዳያ ጓንጉል (አባ.2፣ቁ.15)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 17/09/2004

*ጥያቄ በእናንተ የለቅሶ ሀዘን አሁን እንዴት ነው የሚቀርብ?*

1. የእኛማ ሽለላ ነው ቀረርቶ፡፡ ‹‹ኧረ አያ ቀኛዝማች፣ ግራዝማች እገሌ ወይም ወይዘሮ እገሊት›› እያለ አንድ ሰው ይገጥማል፡፡ ያ ሰው በሙያቸው ይገጥማል ይገጥማል ሌላው እየዞረ ያለቅሳል፡፡ ገጣሚው በሚች ሙያ ሲገጥም አልቃሹን ሲነካው ‹‹እውነት ነው አሁን የምትለው፤ እውነት ነው›› ይላል፡፡ እንዲህ ያለውን ቀረርቶ እንለዋለለን፡፡

1.2.3. **የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ክወና**
1.2.3.1. **የወየታ ክወና**

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** ወ.ሮ. ፈለቁ ከበደ (አባ2.፣ቁ፣31)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 13/05/2006

*ጥያቄ፣ አንቺ ወየ ስትይ ወንዶቹ የተለየ እድል ይሰጡሻል ወይስ እንደነሱ ተጋፍተሽ ነው እድል የምታገኚ?*

1. አፌን ከከፈትኩ አይቀሙኝም፡፡ በወዲያም ያሉት ‹‹ስጣት እንዳትቀማት›› ይላሉ፡፡ ያከብሩኛል፡፡ ሴት አፏን ስትከፍት በእፍረት ላይ ይመለሳሉ እያሉ ያከብሩናል፤ አይቀሙንም፡፡ ወንዱ ነው እስበሱ የሚጋፋ እንጂ፣ ሴት አፏን ስትከፍት አይቀሙም፡፡ ወንዶቹ ግን ሁሉም በድፍረት ስለሚነሱ የገፋ ይነጥቃል፡፡ ጥሩ ድምጽ ያለውና አሰማሙ ላይ ነቃ ያለው ይቀማል፡፡ ቢቀማም ጠብ የለውም፡፡ ‹‹ቆይ ፊንታህ ዙሮ ይመጣልሃል›› ይባላል፤ ዋንጫ ይሰጠዋል ተራው ሲደርስ ያወርዳል፡፡

*ጥያቄ፣ በዋንጫ የሚለቀስ ለምንድን ነው?*

2. የበላበትን የጠጣበትን ለማስታወስ ያህል ነው፡፡

*ጥያቄ፣ ወየ ሲባል ከሴቶች ውጭ አንድ ሰው የመድገም እድል ያገኛል?*

3. እኔን ‹‹ተዋት ስጣት፤ ስጣት፤ እያሉ እስከ ሶስት ጊዜ የምደግምበት አለ፡፡ እንዲያውም ሞራን ይሰጡኛል፡፡

*ጥያቄ፣ ይኸ እድል ለሌላውም ይሰጣል?*

4. አይሰጥም፡፡ አንድ ሰው ሊደግም ሲል ‹‹ይደርሰው ተው›› ይላሉ፡፡ እኔ ግን የመጨረሻውን አብረውኝ ሲደፉ ዙሬ እደርስባቸዋለሁ፡፡ ‹‹ተዋት ተዋት›› እያሉ እድሉን ይሰጡኛል፡፡ ወንዶች ያበረታታሉ፡፡

*ጥያቄ፣ እንዳንቺ ወየ የሚሉ ሴቶች አሉ?*

5. በስም አላውቃቸውም እንጂ አንዳንዴ ያጋጥመኛል፡፡ ግን በስብሩ ላይ አልመች እያለ አይደግሙም፡፡ ባይመችም፣ ‹‹ሰው ለዘመዱ የመሰለውን አልቅሶ መውጣት ይችላል›› እየተባለ አንዳንዶች አሉ፡፡

*ጥያቄ፣ በሌላ ጊዜ እነዚህን ሰዎች ታገኛቸዋለሽ?*

6. አየ አይገጥመኝም፡፡ አጣርቸ ‹‹እገሌ አለ›› የምለው የለኝም፡፡ አልፎ አልፎ ግን ወየ የሚሉ ሴቶች አሉ፡፡

1.2.3.2. **የሙሾ ክወና**

**የመረጃ አቀባይ *ሥም*፣** አቶ ታደለ ሲሳይ (አባ.2፣ቁ.38)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 10/05/2006

*ጥያቄ፣የለቅሶ ባሕላችን ብናይ ሙሾ እሚባለው ነገር እንዴት ያለ እንደሆነ እስቲ ያጫውቱኝ፡፡*

‹‹አይ ዱሮ ሙሾ በሴት ነበር የሚጠራ፡፡››

*‹‹ጥያቄ፣ደርሰውበታል እርስዎ?*

‹‹ሴት ሙሾ ሲጠራ?››

‹‹እህ››

‹‹ታዲያስ!››

*‹‹ጥያቄ፣እስቲ እንዴት እንደነበር ይንገሩኝ?››*

‹‹ሴት ነበር ሙሾ እሚያወጣ ወንድ ሙሾ አያወጣም ነበር፡፡››

*‹‹ጥያቄ፣ እንዴት እያሉ ነበር ሴቶቹ የሚያወጡት? እነሱ እንዴት ይቆሙ ነበር፣ ሌላውስ እንዴት ይቀበላቸዋል? እስቲ ትዝ የሚለውትን ይንገሩኝ፡፡››*

1. ሰው ሀራት ገጥ ይከፈላል፡፡ በዚህኛው ገጥ አለ፤ በዚያኛው ገጥ አለ፤ ሙሾ አርጋጂቱ ስታረግድ ያኛው ይቀባላል፡፡ እሷ ስታቆም ያ ሲመለስ ያ ያረግዳል፤ ያ ያረግዳል፡፡ እሷ ስታረግድ አብረው ያረግዳሉ፡፡ ትመለሳለይ፡፡ ሲመለሱ ያኛው ገጥ ያረግዳል፡፡ ይኸ ነው፡፡

*ጥያቄ፣ ስንት ሴቶች ነበሩ እንዲህ የሚያደርጉ?*

ሙሾ እሚጠሩት ሁለት ናቸው፡፡

*ጥያቄ፣ ፊት ለፊት እየተያዩ ነው ጎን ለጎን ቁመው?*

2. አንድ ላይ ቁመው ነው፡፡ ፊታቸውን ወደዚያ ዞረው ሲያረግዱ ፊት ለፊት ያለው ያረግዳል፡፡ ኸዚያ ደርሰው ወደዚህ ዞረው ሲያረግዱ ይኸኛው ይቀበላቸዋል፡፡ እንደዚያ ነበር፡፡

*ጥያቄ፣ ከእነዚህ ሴቶች ተቀብሎ ወንዱ መቼ ጀመረ? ይህን ያስታውሱታል?*

3. ወንድ የጀመረው በደርግ ጊዜ ነው፡፡

*ጥያቄ፣ በምን ምክንያት ከሴቶቹ ተቀብሎ የጀመረው ይመስለዎታል?*

4. እንግዲህ በምን ምክንያትማ ኸሙሾ ላይ ሴቷ ሙሾ ስትጠራ የሞተችውን ትታ ያልሞተችውን ጠርታ ነው፡፡ አሳሳተይ በሚለብል (በሚል) የሴት ልቦና ሁኖ ነው ልቧ ወደቤት ተበትኖ ነው በሚሊብል ነው፡፡ የሞተችውን ትታ ያለችውን በመጥራቷ ተስቆባት አፍራ ነው፡፡ በዚያ ነው ወንዱ የገባበት፡፡ ኸዚያ ወዲያ ወንድ ገባበት፡፡

*ጥያቄ፣ ሴቶቹ ሙሾ ሲጠሩ ምን ይይዙ ነበር?*

5. አታሞ ይዘው እንዲያው እንደዘፈን ያችን ትም ትም እያደረጉ ነበር የሚጠሩ፡፡ ዛሬ አታሞ ወንድ አይመታም፡፡ ዝም ብሎ ሙሾ መጥራት እንጂ አታሞ የቀረው በሴት ጊዜ ነው፡፡ እንዲያው አታሞ ቷም ቷም ሲል አካባቢው ‹‹አሃ ሙሾ ቆመ፣ ሙሾ ቆመ

እንህድ›› ይላል ዳተኛው፡፡ ‹‹ልቅሶ ቆመ እንህድ›› ይላል ዳተኛው፡፡ እንግዲህ ወንዱ ሴቶቹን የተካቸው የቆመችውን እንደሞተች አድርጋ በመጥራቷ ነው፡፡

ጥያቄ፣ አሁን የወንዶቹ አወጣጥ ሥርዓቱ ተቀይሯል?

ያው ነው፡፡ ሁለት ሁነው ይገባሉ፡፡ እነሱ ሲደክሙ ሁለት ይፈሰጋል እነዚያ ያርፋሉ እንደዚህ ነው፡፡

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ ጠና ገበያው (አባ.2፣ቁ.36)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 10/05/2006

*ጥያቄ፣ ሴቶች ሙሾ ሲያወርዱ ደርሰዋል?*

1. አወ አታሟቸውን ትም ትም እያደረጉ ሲያወርዱ ደረሽላሁ፡፡

*ጥያቄ፣ ዛሬ ሴቶቹ ሙሾ ያወርዳሉ?*

ዛሬ የሉም፡፡

*ጥያቄ፣ መቼ ነው ወንዶ የተቀበሏቸው?*

*ምን ሁነውስ ለቀቁ?*

2. ምን አውቃለሁ፡፡ የለቀቁበት ዘመኑ ከኃይለሥላሴ ነው፡፡ በደርግ አልነበሩም፡፡

*ጥያቄ፣ ሴቶቹ የለቀቁበትን አላወቁትም?*

3. እኸ ወንዱ ተሰለፈ፡፡ አቸነፋቸው (ሳቅ) ሙሾ በሴቶች ነበር፡፡ በኋላ ቅረርቶ ሆነ ፉከራ ሆነ በዚያ ተገፉ፡፡

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣**ብላታ ቀዲሙ ዓለሙ (አባ2.፣ቁ፣24)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 10/09/2004

*ጥያቄ፣እስቲ ስለሙሾ የሚደረገውን ቀደም ካለው ጊዜ ጀምራችሁ ግለጹልኝ?*

1. ዱሮ ከዚህ አጅባራችን ላይ ከበሮ እየመቱ ሴቶች ነበሩ የሚያለቅሱ፡፡ እድም እድም ድድም እያደረጉ አታሞ እየመቱ ሁለት ሴቶች ህሩይ ነበሩ እነሱ ነበሩ ሙሾ የሚያወጡ፡፡ሁለት ሁለት ሴቶች ከየ አገሩ ነበሩ፡፡ እኒያ ሴቶች ትንሽ ከበሮ ነበረቻቸው በዚህ ሁለቱ በዚያ ሁለቱ ይሆኑና ሙሾ ያወጣሉ፡፡ የከበሮው ምት እንደዜማው ነው፡፡

ከመሀል ሶስት ሶስት ወንዶች ገብተው እየተያዩ ያዳምጣሉ፡፡ ሌላው ቁሞ ያዳምጣል እንጅ ሙሾ አያወርድም ነበር፡፡

*ጥያቄ፣ ሴቶቹ ካባት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ነው ወይስ ከሌላ ቦታ መጥተው ነው ባህሉን ያሳስተዋወቁ?*

2. ካባት የመጣ ነው፡፡ በሙላው አገር ሁለት ሁለት ሴቶች ነበሩ፡፡ በኃይለ ሥላሴ ዘመን ቀረ፡፡ እነዚያ ሴቶች ከለቅሶ ቀሩ፡፡ ሲሞቱ ተተኪ ጠፋ፡፡

**የመረጃ አቀባይ ሥም**፣ሻምበል አብርሃም አሰገድ (አባ.2፣ቁ.26 አን.1.

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን**፣ እ.ኢ.አ. 29/09/2004

*ጥያቄ፣ ቅድም ሴት አልቃሽ ነበርች ብላችሁኛል፡፡ እንዴት እያሉ ነበር የሚያለቅሱ የዱሮዎቹ?*

1. የምታቀነቅነው አንዲት ናት፡፡ ታቀነቅንና ‹‹ዋ እያሉ ኸዱ›› ትለዋለይ ያ ተቀባው ‹‹አይ እያሉ እያዘኑ›› ይላል፡፡ እንደዚህ ነው፡፡ ያ ተቀባው ያበቃ ጊዜ እሷ ደሞ ታቀነቅናለይ፡፡ የሟችን ሙያን ትነገራለይ፡፡ ተቀባው ይቀበላል፡፡

2. መልካም ገበዝ አየሁ በዚያ ታይ በወንዙ፣

እከሌን ይመስላል በልጅግ አያያዙ፡፡

(ጠበንጃ አያያዙ) እያለይ ትገጥማለይ፡፡ ሌላው ‹‹ዋ እያሉ ኸዱ›› ሲል እሷ ‹‹አየየ›› ትላለይ፡፡

*ጥያቄ፣ አንድ ቦታ ላይ ቁመው ነው እየዞሩ?*

3. የምትዞርም አለይ፡፡ አንዳንድ የማይዞሩም አሉ፡፡ ከመሃል ላይ ቁመው፡፡ በቃ የግንባሯን ብቻ ትስባለይ፡፡ ያና ያ ተሳስቦ ይገናኛል፡፡ እንደዚያ እያለ አራቱ ማይዘን ነው የሚገናኝ፡፡ ሙሾው ደስ ይል ነበር፡፡

*ጥያቄ፣ ይኸ መቸ እንደቀረ ታስታውሳላችሁ?*

4. ይታወቃል፣ በጣም የገነነ ኸደርግ ወዲህ ነው፡፡ በኃይለ ሥላሴ ጊዜ ሴትም ሆነ ወንድም ሆነ ሙሾ አልተከለከለም ነበር፡፡ ደህና ይለቀስ ነበር፡፡

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣**አቶ ጺጋየ ጀንበሬ (አባ.2፣ቁ.19)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 10/09/2004

*ጥያቄ፣ በዚህ ዘመን ሴቷ ሙሾ ስታወርድ አጋጥሟችሁ ያውቃል?*

1. አባቴ እንዳሉት ቀደም ሲል እኔም ልዥ ሁኼ ሴቶች ሲያወጡ ደርሻለሁ፡፡ ከመሀል ሁነው ሲያወጡ ይቆዩና ደረታቸውን እየደቀደቁ ‹‹ውይ፣ ውይ) ይላሉ፡፡ ይህን ነገር የት አየሁት አዲስ አበባ፡፡ ከ56-64 አዲስ አበባ ኑሬያለሁ፡፡ ከዚያ ነው ደረት እየደቀደቁ ሴቶች ‹‹የት ትሄዳለሁ ዘመዶችህን ታስለቅሳለህ›› እየተባለ ሲያስለቅሱ ያየሁ፡፡ ከበሮ ይዘው ሲደበድቡ አውቃለሁ፡፡ ልዥ ሳለሁ ከዚህ ህሩይ ከምትባል ቦታ ላይ ሲያስለቅሱ አይቻለሁ፡፡ ከዚያ ወዲህ እየቀረ ነው የመጣ፡፡

1.2.3.3. **የቀረርቶና ፉከራ ክወና**

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ ታከለ ንጋቱ (አባ.2፣ቁ.13)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 8/10/2004

*ጥያቄ፣ ፉካራ የምታቀርቡት እንዴት ነው፣ ለማነው የምትፎክሩ?*

1. የሰውየውን ታሪክ ይነግሩናል፡፡ በወረቀት ጽፈውም ይሰጡናል፡፡ ያችን ወረቀት አነበብነ ከዚያ ‹‹የሰውየው ታሪክ ይኸ ነበር›› ስንል የነበረው ሰው እየተከተለ ‹‹እውነት ነው፣ እውነት ነው›› እያለ ምስክራችን ይሆናል፡፡ ‹‹እውነት ነው›› ካላለ ውሸት አለ ማለት ነው፡፡

‹‹ልክ ነው ያበላል ያጠጣል እንግዳ ይሸኛል፣ ለድሃ ያበድራል፣ የታረዘ ያለብሳል፣ የተራበ የተጠማ ያጠጣል›› እያለ ይቀበላል፡፡ እኛ ግጥማችን እናወርዳለን፡፡

*ጥያቄ፣ ሰው እውነት ነው እያለ ሲከተልህ ምን ይሰማሃል?*

2. እውነት ነው ሲልህ በጣም ደስ ይላል፡፡ ደሞ አንዳንዴ ያልሰራውን ሰው እንከበክበዋለን ሀምስክሩ ፊት፡፡ ይኸ ምስክር አልቦ ተሚጋች ማለት ነው፡፡ አሁን ምስክር አልቦ ተሚጋች ይረታል በከሰሰው?

ከዚያ ግን ገና ስንጀምር አቶ እገሌ ዛሬ ሽውክ የለውም ጥሩ ሥራ የሰራ ሰው ነው። እንዲያው እንዴት አድርጎ እንግዳ የሸኘ፣ ያበላ ያጠጣ፣ ድሃ የወደደ እንዲያው የመጨረሻ ድሃን ያከበረ ሲባል ‹‹እውነት ነው፣ እውነት ነው ያላበደረው የለም›› ይላሉ። ጀግናው ደግሞ ላገሩ የቆሰለው አለ አይደል ‹‹አርበኛ›› ስንል ‹‹እውነት ነው በረሃ ወርዶ የማይመለስ ከጦር ግንባሩ የማይመለስ እያለ›› ምስክሩ ያበረታታናል። ነጋዴም ሲሆን ‹‹እንኩ ዘር ሽምቱ ብሎ ለድሃ ያበድራል፣ ድሃ እሚረዳ ነው ዘመድ ይወዳል›› ይባላል። እንደገና እናቶቻችን ልጆቻቸውን ጥሩ አድርገው ከስርቆት ተከላክለው ጥሩ አድርገው አሳድገው በግብርናም ሆነ፣ በንግድም ሆነ፣ በትምህርትም ሆነ ሲያሳድጉ፣ በባልትናቸው ጥሩ እንግዳ የሚሸኙ ሲሆኑ በዚያው እንፎክራለን። በዚያን ጊዜ ‹‹እውነት እውነት ባዩ ምስክሩ ከበዛ የምንናገረው እውነት ነው ማለት ነው፤ በጣም ደስ ይለናል። ለተሚጋቹ ከፍርድ ቤት ስላሚያደርገው ነገር፣ ስለመልስ አሰጣጡ፣ ይግባኝ ብሎ ፍርድ ስለማግኘቱ ስትፎክር እውነት ይላል። ካልሆነ ግን ‹‹እምም እምም ይላል›› ይኸ እንግዲህ ችግር አለ ማለት ነው ቀዝቀዝ ያደርገናል።

***የመረጃ አቀባይ ሥም*፣** አቶ አበረ ክበበው (አባ.2፣ቁ.10)

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን*፣** እ.ኢ.አ. 25/09/2004

*ጥያቄ፣ አሁን አንተ ላንድ ሰው ልትፎክር ስትል ምኑን መነሻ አድርገህ ነው የምትገጥም?*

ዘማች ከሆነ በዘማችነቱ ገበሬ ከሆነ ልኸ የዳረ፣ ላም የወደረ፣ በቅሎ የጫነ እየተባለ ይፎከርለታል። አዳኝ ተኳሽ እየተባለ፣ ተሚጋቹ፣ ሴቷም ልኸ አስተዳደን፣ ሴትነቷ፣ እንግዳ ተቀባይነቷ እየተነሳ ይፎከራል። እንደሥራቸው።

1. ገበሬ ሁኖ ያላመረተ፣
   ነጋዴ ሁኖ ያላተረፈ፣
   ዘላን ሁኖ ላም ያልቀረተ፣
   ሸማኔ ሁኖ ጥበብ ያልሰራ፣
   ቄስ ተብሎ ቅኔ ያልመራ፣
   ዶክተር ነኝ ብሎ ያልመረመረ፣

*መመህር ነኝ ብሎ ያላስተማረ፣*

*ከዚህ ሁላ ውለት የለለው፣*

*የወደቀ እንጨት ምስጥ የበላው።*

*መነሻው በሙያቸው መስራት ያለባቸው ነው። ይኽ መነሻ ይሆንና*

2. *ዶሮ እሚያረባ ግርድ ለው ሰው ነው፣*

   *ሀጎታ አውጥቶ ግርዱን ሰጥቶ ነው፣*

   *ተባቱ ደሮ ደግሞ ሲሸጡት መቶ አስር ብር ነው፣*

   *ቡና ጥረጨው በዚህ መቻል ነው፣*

   *እህልን ማቅናት ችግር ማግባት ነው።*

   *እስቲ ወገኔ እንደማመጥ፣*

   *ዘማች ከሆነ ዘማች ልበለው፣*

   *ገበሬ እንደሆን በግብርናው ነው፣*

   *ያለ ቦታው ያለ ሥፍራው እንዳላውለው።*

***የመረጃ አቀባይ ሥም፣*** አቶ መላሽ ወርቁ (አባ.2፣ቁ.21)

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣*** እ.ኢ.አ. 24/06/2005

*ጥያቄ፣ እርስዎ ፎካሪ ነዎትና ለእንዴት አይነት ሰው ነው የምትፎክሩ?*

1. በየአገሩ ጠንካራ ሰዎይ አሉ። ኸጥንት አባቶቻችን ባርበኝነት፣ በኛ እድሜ ደሞ በውትድርና፣ በዘመቻ፣ በግብርና፣ በሙግት ስመ ጥሩ ለሆኑ ሰወይ ይፎከርላቸዋል። ለእነዚህ ሰወይ እንደ ሥራቸው በቅሎ ተሸልሞ፣ መሳሪያ ተይዞ አርበኛና ዘማች ሲሆን ሰለፍ ተይዞ ጃሎ ባዩ ሲደፋው እንደአቀረብሹ ፎካሪ ይገባል። እሱ ሲንደቀደቅ አብሮት የሚዞረውና አዘንተኛው በኛ በፎገራ ‹‹ይል ነበር!›› ይላል። ወዲህ ወደፋርጣ ‹‹እውነት!›› እያለ ይቀበላል። አንዱ ሲደናገረው ወይም ሲጨርስ አንዱ እየገባ አቧራውን ያጤሰዋል። ሚቹ ታዋቂ ከሆነና የኮራ ልዥ ወይም ወንድም ካለው ተገዝቶ የሚመጣ ፎካሪ ይኖራል ፉከራው በጣም ይደምቃል። ለሴቶይም በሙያቸው በሴትነት፣ በልዥ አስተዳደግ ይፎክርላቸዋል።

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ ሞላ አየሁ (አባ.2፣ቁ.21)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 05/10/2004

*ጥያቄ፣ ደስ የሚልህ ስለነማን ወይም ስለምን ስትፈክር ነው?*

ስላገራችን ሰው ነው ስለ እንትኑ? (መልሶ ጠየቀኝ)

*ጥያቄ፣ አንተ ስላገራችን አርበኞች ነው፣ ስለ ገበሬዎች ነው ስለነማን ስትፈክር ነው ሞቅ የሚልህ?*

ስላርበኛ ስፈክር ነው የሚሞቀኝ።

*ጥያቄ፣ ከእነሱ ጀምርና እሲቲ ለእነማን እነደፎከርክ በየክፍሉ ያስቀመጥከውን ትንሽ እናንብበው። እስቲ የእነሱን ከነታሪኩ ጋር እያዋዛህ አጫውተኝ።*

እሽ ቆይ ቀይ እሱን ዝጋውና ታሪኩን እነግርሃለሁ። (መቅረጸ ድምጹን ማለቱ ነው)

ይኸማ አይዘጋም። አብሮ ከነታሪኩ ነው የሚያዝ። ታሪኩ ለፉከራው የሚያግዝ የሚጠቅም ነገር አለው።

*እንደዚያ ነው? እሽ*

እሽ እንግዲህ ልጀምር ነው
እሽ ጀምር
(ሳቅ እንግዲህ ውል ነገር መጣ አይደል (ሌላ ሳቅ)
**ለአርበኞች (ለጀግና)**
1. አገሬ በየምድር አይወድም ጥቃት አይወድም ደራ፣
አድዋ ገጣሚ ኸጠላት ጋራ፣
በነ ናስማሰር በነ ውጅግራ።
ያድዋ ጦርነት አየ ክብደቱ፣
የመጡት መጡ የሞቱት ሞቱ።
እንኳን ጦር ሜዳ ሆነ ሞታችሁ፣
ጉንፋን ይገድላል ሲደርስ ቀናችሁ።

ከጦር ሜጋ ላይ የሞተውን ሰው፣
እኔም አልረሳው ከማስታወሻው፣
ይነገር በወግ ወንድነታቸው፣
ትግሬ ላይ ህደው ተጋጠሚቸው፣
በሰማይ አየር ቢነጉድባቸው፣
የእጅ መሳሪያ ቀለል ቢላቸው፣
ትተውት ዞሩ ወደ አገራቸው።
እነዚያም ወዲያ ተከተሏቸው፣
ከዚህ ሲደርሱ ተጋጠሚቸው።
በዚያ አምስት ዓመት በዚያ መከራ፣
አባቶቻችን፣ ወንድሞቻችን፣ ወገናቻችን ያስመሰግናል የሰሩት ሥራ።
በጥቁር አየር በማይታረር፣
በጋንቲራ አንጀት ሲታረስ፣
ሰው እንደ ጎታ አካሉ ሲፈርስ፣
እንደ ሸለቆ የሰው ደም ሲፈስ፣
ወይ የዚያን ጊዜ የተቃተሉ፣
ስም እንደ ማተብ አስረው የቀሩ።
የኛ አገር ጀግኖይ ወንድነታቸው፣
ድርቦታቦር ላይ ተጋጠሚቸው፣
ከወደ ጎንደር አባረሯቸው፣
ቁልቋል በር ደርሰው እነሱም ዞሩ ተጋጠሚቸው።
ገዳይ ቁልቋል በር አየሩ ሲነጉድ መኪናው ሲበር፣
ገዳይ ጎንደር በር ገዳይ ደጎማ፣
ጀግና ሲማርክ ፈሪ ሲቀማ።
ገዳይ ጎንደር፣
ጀግናና ጀግና ሲወዳደር፣
ሱዳን በካንኩ ሲሽከረከር፣
ጓደኛው ቁሞ ሲመሰክር፣

ሰው ያለቀኑ የማይሞት ቢሆን፣
አርጅቶ ሞተ ቆይቶ እስታሁን፡፡
ገዳይ ጎንደር ላይ ገዳይ ቸቸላ፣ ◉
መርተጌስ ሲዘነብ ቦንብ ሲፈላ፣
ቀለሁ ሲያድጥ እንደ ባቄላ፣
ምንሽር ሲመዘዝ እንደ ፡፡
አይፎከርም አይሞከርም ጎንደር ላልዋለ፡፡
ገዳይ እብናት ገዳይ ፋርጣ፣
አንበጣ መስሎ ፈረንጅ ሲመጣ፣
እየነጎደ አየር ሲመጣ፣
ፈሪ በቁሙ ነብሱ ሲወጣ፡፡
ገዳይ እብናት ገዳይ ቀይ አፈር፣
እንደ ባቄላ ጥይት ሲሰፈር፡፡
አየር በሰማይ ደማሚት ሲጥል፣
ሰው እንደ ቅጠል ሲል ዝንጥል ዝንጥል፣
ኸረ ያንን ቀን ዳግምስ አይጣል፡፡
አርበኛ አለቀ በላው መሬት፣
ማን ይቆም ይሆን የክፉ ለት፡፡
አርበኞች ደማቸው ፈሶ፣
አጥንታቸው ተከስክሶ ባቀኑት አገር፣
ከቤት የዋለው ትርጉም መናገር፡፡
ብኋል ሞላ አየሁ (ሳቅ)

2. ያጃነን ሥራ የእያዳን ሥራ ኸረ አይበል አይጣል፣
ሰው እንደ መንጠር በሳት ሲቃጠል፣
በሳት አይፈስም የሰው ደም፣
አትልኩም ወይ ወደ ሥዩም፡፡
እንደ ወገኔ ሳልንገበገብ፣
ታጥቆ ተነሳ ደስታ አባ ታገል፣

አሰየፋለሁ አለ ላገሬ፣
ፊረደ በላይ ግራዝማይ በሬ፡፡
መልዛን በሙሉ ሱሪ አስታጠቀው፣
አንጠበጠበው ተሾመ ላቀው፡፡
መቼ ይቻላል መልዞች ጠባቸው፣
ማልዳ ተጋጥመው በሁለት ሰዛ ሶስት መትረጌስ ወዲያው በኋቸው፡፡
አንዱ የደስታ፣ አንዱ የሥዩም አንዱ የለማ፣
ይኸነን ከያዝን የመጣው ይምጣ እንግዲህማ ፡፡(አሉ መልዞች)
አወ
የእብናቱን ጦር እንኳን ወገኑ የሰማው ሁሉ ተንገበገበ፣
ከበደ ደብሪቱ እብናት ሰፈር ተደበደበ፣
ቦጋለ መንግሥቱ እብናት ሰፈር ተደበደበ፡፡
በዚያ አረመኔ በዚያ ግምዴ፣
አታሎ አግብቶ ፊጃቸው እንዴ?
ይህን ሰማና ተቆጣ መልዛ፣
ጣሊን በኮዳ ውሃ ሲቀዳ፣
አናቱን አለው ከበደ እንግዳ፡፡
ጥይት ሊተኩስ ሲንገረገሽ፣
አናቱን አለው ሥዩም ነጋሽ፤
አናቱን አለው ደስታ ሽበሽ፡፡
የሦስቱን ልፋት መንግሥት ቢያውቀው፣
ኸዙፋኑ ላይ ሰቀላቸው፡፡
ለፍተው የቀሩ አሉ ሁለቱ፣
ለማ ዘለለው አቤ መንግሥቱ፡፡
አቤ መንግሥቱስ በሬን ተክቷል፣
በስተዚያስ በኩል አባተ ለማ፣
ልኽ ተክተዋል የለፉትማ፡፡
ፈረንጅ ተጨንቆ ተይዟል ቁንጣን፣

አገላገለው አቤ አባ ፈጣን፡፡

ያዜ አባ ፈጣን ሳስታ ቡግና ላይ ጨለማ እንኳ አይደል ወለል ባለው ቀን፣

አባሮ አነቀው ማንዳ (ባንዳ) ዘለቀን፡፡

ትግሬ በረሃ ውሃ ከለለው፣

ካንክ ማራኪ ለማ ዘለለው፡፡

ደህና መጥረቢያ ይባላል አፋ፣

የደህና ጎበዝ ቀኑም ቢረዝም ስሙም አይጠፋ፡፡

አለ፡፡ ይኸውልህ ይኸ ነው መልዛ (ሳቅ)

**ስገበሬ**

3. አቶ እገላቱ ንቡ ሲወጣ ይመስላል ዝናብ፣

ሸርፋው በታዛው ይመስላል ሰፈር፣

አሁን ይኸንን ሊበላው አፈር?

ወረዳ አውራጃ የሚያድርበት፣

ዋ ተዘጋ ወይ ያጅሬ ቤት፡፡

ደናው ገበሬ የተሰናዳው፣

ሀቤት ሲገቡ ጥሩ እሚቀዳው፣

ከኩላቡ ላይ መጫኛ አቅማዳው፣

ወይንም በርሻ ወይ በዘመቻ ስም የለለው፣

የወደቀ እንጨት ምስጥ የበላው፡፡

ተኳሽ አርበኛ አራሽ ገበሬ ቢወዳደሩ፣

ተኳሽ አርበኛ ይበልጣል ለለት፣

ሰውን ሰው ገዳይ እየተሳበ፡፡

ተኳሽ አርበኛ ሲፎክር ውሎ ኸገበሬ ቤት ካልበላ ማታ፣

ሩጦ አያመልጥ ተኩሶ አይመታ፡፡

እኔ ገበሬን እወደዋለሁ፣

ገንቦ አዘንብሎ አግቸዋለሁ፡፡

የገበሬ ሚስት የታደለችው፣

እያቀረበች ሁሉን ሰጠቸው፡፡ (ብኋል)

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** ዳምጤ ፈረደ (አባ.2፣ቁ.8)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 02/10/2004

1. በለሳ እንዴት አለህ? ያ ደጃማይ ሞላ፣ ያ ደጃይ በላቸው፣

መልዛ[1] እንደምን አለህ? ፍታራሪ ሥዩም፣

መቀጠዋ[2] እንዴነህ? ያ ያለው ከበደ፣ ያ ለማ ዘለለው ፣ያ ከበደ እንግዳ፣

አቶ ደስታ ሸበሽ፣ አይ አቶ ሽሙላ ቢያድጌ፣ ቄስ ረዳ ዋሴ፣

ጋይንት እንዴት አለህ? ላይ ጋይንት እነ ዳኘ ገሰሰ፣

ታይ ጋይንት እንዴነህ? ያ ደጃይ ብርሌ፣ ያ ደጃማይ ዳኘው፣

ስማዳ እንዴት አለህ? ያ ደጃይ ታደሰ፣

እስቴ እንደምን አለህ? አባ ዋጠው ገብሬ፣

ስምና[3] እንደምን አለህ? እረ አሞራው ውብነህ፣

ግራሪያ[4] እንዴት አለህ? የኔ አንዳርጌ ማረው፣

ጎጃም እንዴት አለህ? ያ በላይ ዘለቀ፣

እንግዲህ አገሬ ግብርህነን ብላ፣

አለቀ ይሉኛል ነጭ አምራቹ ሁላ።

ያማሴኑ ዳኛ የነጨ ገበሬ፣

ተፈታ መሰለኝ በየምድር አገሬ።

እርካሽ ነው አሉ መልዛ ሽመታው፣

ነጭ እያመረተ ሥዩም ገበሬው።

**ለተሚጋች**

**የመረጃው ምንጭ ሥም፣** አዱኛው መለሰ

**ፋርጣ ወረዳ ከግለሰብ በካሴት ተቀርጾ የተገኘ መረጃ** (08/09/2004)

**በ2001 ዓ.ም አትከና ጊዮርጊስ ለሞት ገላየ ክብረት ለተባለ ተሚጋች የተፎከረ**

**ቀረርቶ**

---

[1] ፋርጣ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ የቦታ ስም
[2] ፋርጣ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ የቦታ ስም
[3] ፋርጣ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ ቦታ ስም
[4] ፋርጣ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ የቦታ ስም

1. አባት ሳለ ቀሲል ይነሳል በአንድ እጅ፣
መግቢያ የታጣለት ይቸግራል እንጂ።

አባሙላት ቢያድጌ ክብረቴ፣ ባይለየኝ ክብረቴ፣ (ግጥም ነጋሪ አለ)
ኀዴ ክብረቴ እርቂሁን ሞላ እረ ወንድሞቼ፣
እረ አሰፋ እጅጉ እረ ቂሰስ ክብረቴ እረ ወዲያልኝ እረ ወዲያልኝ፣
እንዴነህ ገላየ፣ እንዴት ሰው ያጀላል እንዴት ሰው ያሞኛል
ጎንደር ከፍርድ ቤት ያለሁ ይመስለኛል።

**ቀረርቶ**

ልዥ በዜ ክብረቴ፣ እንዳለ ክብረቴ፣
ደረሰ ክብረቴ፣ ማለደ ክብረቴ፣
አገራችን ፋርጣ አትከናላይ ነበር የኩታ ጥለት የኩታ ጥለት፣
ገላየ ነበረ ላገሩ እዳይት ።

**ፉከራ**

ፎካሪ፣ገላየ ክብረቴ፣ ከመስሪያ ቤት ላይ ገዳይ በግራው፣
ተቀባይ፣እውነት! በየስንኞቹ መጨረሻ በዚሁ መንገድ ይቀበላሉ)
የሚያስቸግረው ለባላንጋራው።
እንደ መስታይት የሚፈልቀው፣
እንደ መስታይት የሚያሳየው፣
አቶ ገላየን አፈር በላው፤
የእንዳለን ወንድም የኮፍጣናው፣
የያዜን ወንድም የቦልካታው፣
የማልዴ ወንድም የዘንካታው፣
የበዜ ወንድም የበጥብጥ ወንድም፣
ባገሩ እንዳንተ ያል አይወለድም።
ለፍቅር ነው እንጂ ጠቡ እሚፈላ፣
መች ዘመድ ያደርጋል ጥላየ ሲጣላ።
አስቸጋሪ ነው ለባላንጋራ፣
እምቢ የሚለው ለባላንጋራ፣

ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADDIS ABABA, ETHIOPIA

ገዳይ በኮበ. አለ እንዳለ ክብረቴ፣
ጥጋብ ኃይለየሱስ ማለደ ክብረቴ፣
ገዳይ በኮበ. በትንሽቱ፣
በሞጥሟጣይቱ ባፈ ሹሊቱ፣
ሌባው ቀጣፊው በማይወዳቱ፣
ገሎ ይመጣል ያዜ አንድ የናቱ።
ኧረ በኮበ. ይል ነበር ገላየ ክብረቴ፣
የማለደ ወንድም፣
የኀይለየሱስ የቀኛች ወንድም፣
የዚያ መራኸሮም የበዜ ወንድም፣
የሀብታሙ የእንዳለ ወንድም፣
አየ ጉድ ብየ አይቀርም ሞት፣
አቶ ገላየን በላው መሬት፤
አቶ እንዳለንም በላው መሬት፤
የደጌን አባት፣ የለማን አባት፣ የይመኝ አባት በላህ መሬት፤
ዋ ክንብል ያርገኝ አይቀርም ሞት፣
ገላየ ክብረቴን በላው መሬት፤
ያንን ዘንካታ በላው መሬት።
ኧረ የነሱስ ለየት ያለ ነው፣
ኧረ የገሌስ ለየት ያለ ነው፣
ኧረ የእንዳለስ ለየት ያለ ነው፣
ኧረ የዘልቁስ ለየት ያለ ነው፣
ኧረ እናንተ ሆየ ልንገርህ አገሬ፣
ልንገርህ አሙስ ወንዝ ልንግረህ ፋርጣ፣
እንዴት አድርጋችሁ ተነጋገራችሁ፣
እንዴት አድርገው ነው ከመስሪያ ቤቱ ላይ ያስተናገዷችሁ?
ገላየ ክብረቴ አይ አረማመድ እግርና ባት፣
አየ ጉድ ሱሪ ባታ ሁለት፣

ገላየ የጋሻው አባት፣
የአለምነው አባት፣
ኸረ ገላየ የይመኝ አባት፣
ኸረ የጥላሁን አባት፣
የነካሴ አባት የካሴ እንዳለ፣
የካሴ ተፈሪ፣ የጥላሁን አስናቀ፣
የትልቆቹ አባት፣ የትልቆቹ አማት፣
ገላየ ክብረቴ፣
ማለየ ክብረቴ፣
ደረሰ ክብረቴ፣
በዛብህ ክብረቴ፣
ቀኛች ኃይለየሱስ ቢጋባም ተጓዶ፣
ደረሰ ክብረቴ የነ መንጌ አባት፣
የሰውነት አባት፣
አየኸው አገሬ፣
እሸቴ ክብረቴ፣
የነይመኝ አባት፣የነአማቹ አባት፣
ሲጋባም ተጓዶ፣
ሲታጭም ተጓዶ፣

ዛሬ እንዲህ ኸደ እንጂ በእግዜር እጅ ተገዶ።

**ለጎበዝ ገበሬ**

**የመረጃ አቀባይ ሥም**፣ አቶ ታከለ ንጋቱ (አባ.2፣ቁ.13)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን**፣ እ.ኢ.አ. 08/10/2004

1. ደህናው ገበሬ የተሰናዳ፣

ይሸኝ ነበር አያሌ እንግዳ፤
እህል ይዛቃል በትልቅ አቅማዳ።
ክርክም ገበሬ የተዘጋጀ፣

ምንም ሳይቸግረው እድሜውን ፈጀ፤
የባላባት ልጅ የተዘጋጀ።
አራሽ ገበሬ ቀይና ዋልካ፣
ችግር ያልነካው የባላባት ልጅ የተረጋጋ።
ከተወለደ እስቲሞት ድረስ፣
ችግር ከቤቱ ከደጁ ሳይደርስ፣
አጥቢት ሲወጣ ኩኩ ሲል ደሮ፣
በሮቹን ይዞ ወጥቷል ከጓሮ።
ጎህ ሲቀድ ወፍ ሲንጫጫ፣
በሮቹ ጠግበው ከደይ ቁመዋል፣
ቁርስ ሊበላ ከቤቱ ገብቷል፣
ሚስቱ ምን ጊዜ አዘጋጀችው፣
ወፉ ሲንጫጫ ቁርስ ሰጠችው።
ቁርሱን በላና ወርዶ ጠመደ፣
ሽሩ እንደ ማበል እየተናደ፣
ባገር በዘመድ የተወደደ።
እንዴት ያል ሀብታም ዛሬ ተለየ፣
ሰኔና ግንቦት ቀድሞ ሲበልግ፣
ሀምሌ ነሀሴ ምድሩ ሲፈልቅ፣
መስከሮም ወጥቶ ጥቅምት ሲዘልቅ፣
ከሂዳር ጋራ ስንታረቅ፣
እልም አይልም ሞቱ ቢዘልቅ።

**የመረጃ ምንጭ**፣ አቶ ደጀን አመኑ (አባ.2፣ቀ.17)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን**፣ እ.ኢ.አ. 17/09/2004

1. ፎካሪ፣ ብቻየን ዘልቄ ስሰማ ወሬ!፣

   ተቀባይ፣ እውነት (ፈካሪው በሚያቀርባቸው ስንኞች መጨረሻ ተቀባዩ እውነት ይላል)

   አመን ሽፈራው መልካም ገበሬ!፤

አገኝ በላቸው መልካም ገበሬ!

ጥሩ ገበሬ በጣም የሰራ!፣

የሚሰለፈው ሳይወጣ ጮራ!፣

ምርቱ እሚያህለው ትልቅ ተራራ!፣

አይመቀኝም የሰው አዝመራ!፣

ሞልቷል ከቤቱ ነጭ በጎተራ!፣

ቤቱ እሚጠምቀው ስዝና ቢራ!

ኧረ ይደገም የነ አመኑ ስም!፣

ኧረ ይደገም የነ ታዬ ስም!፣

ጠላው ጥሩ ነው አይደፈርስም!፣

ችግር ተበሩ ተጓሮ አይደርስም!

ችግርስ ቢሆን ኧረ ብሶት!፣

ከነታዬ ቤት ምን አልከስክሶት!?

ከአመኑስ ደጃፍ ምን አልከስክሶት!?

ከነታዬ ቤት ካባ ባህር ቤት ምን አልከስክሶት!?

ስራ እማይሰራ ደሞ ሰነፍ!፣

ይላል ተፍ ተፍ ተሱ ደጃፍ!

**የእንጉርጉሮ ቀረርቶ**

1. አለቁ እን ቦታው ክፍት አደረ ጀግኖቹም አለቁ፣

   አለቁ እን እእእ እረ እሪበል ወንዱ እእእ አየ ጉድ እእእ አመኑ አባ አበጋዝ፣

   እሽ (አመኑ አባ ደራ በለው!)

   እህ እእእ አየ ጉድ እእእ የኔው ነገር ወዲያ ወዲያ እኔን ይብላኝ፣

   ኧሽ!

   እህ አመኑ አባ በሃር እእእ የኛው ነገር ወዲያ፣

   አየ ጉድ አመኑ አባ በሃር እነ አምሳ አለቃ ታደሰ በላቸው፣

   አየ ጉድ እእ ወንድማማች በሬ አርሶ የታከተው፣

   እህትማማች ላም አልቦ የታከተው፣

   አየ ጉድ እን እእእ፣

ጥንድ ጥንድ ሙክት የሚገጠግጠው፣

ኧሀ!

ኑሮን እንዳመኑ አድርጎ ነው መተው አድርጎ ነው መተው።

እ ድ ድድ ድድ፣

2. የአባ በሀር ልጆች እእእ አመኑ አባ በሃር ወዲያ ወዲያ፣

በነጋ መሞት፣ በታደሰ መሞት በመኮንን መሞት፣

በዘውዳለም መሞት በማሪቱ መሞት ተቆርቁረው ሳለ ተቆርቁረው ሳለ፣

እህ፣

አየ ጉድ እእእ  አመኑ ሲሞት አንዳርጌ ምን አለ አገሩ ምን አለ።

እኸ!

አየ ጉድ እእእ እኔስ የገረመኝ የልገሮች ዝምታ ያገሩ ዝምታ፣

እእእ የነ አመኑ ቤት ገበያው ሲፈታ።

እእእ እእእ አመኑ አባ ሙላት እእእ አየ ጉድ አየጉድ አየ ጉድ አገሬ፣

(ግጥም ለአዝማሪ ነጋሪ ጀመረ)

አይ እእእ አገሩ እስተ ጋይንት እእእ አመኑ አባ ብሃር፣

እእእ አገሩ እስተጋይንት ከጅባ ደንበር ከጅባ ደንበር፣

እን እእእ አየ ጉድ አየጉድ አመኑ አባ ብሃር፣

ቤቱ ከጎድንዳው ኸገደሉ ስር፣

ጠበንጃው ምንሽር ሰውየው ነብር፣

ማነው ያለ ሠዓት በዛች የሚዞር ይል ነበር ወዲያ ወዲያ ወዲያ።

ያ ደሳለኝ ብሩ የበለሳው በሬ ግራዝማይ ተብሎ፣

ቀኛዝማች ተብሎ ግራ ዝማች ተብሎ የልቡ ባይደርስ፣

ያመርት አልነበረ በአንድ አውድማ መቶ አቅማዳ ገብስ፣

ተኝቶ ይመስላል እንደ በሬው አመን፣

ያምትኩ በላይ የነካሴ ወንድም፣

ተኝቷል መሰለኝ ያርማጭሆው በሬ የበለሳው በሬ፣

ካራውን አምጡ ይመተርበት፣

ገበታውን አምጡ ይፈትፈትበት፣

ማርና ሥጋውን የበላንበት።

በለሳ አርመጭሆ በሸንብራ ቆሎ የዘመተው፣

አመን እንዴት አደረከው።

አለቅልቁ ዋንጫ ብርሌውን አንሱ፣

ለካ ሙቶ ነው ወይ ልገሮቹ ሲደርሱ።

እነ ነጋ ቀሩ እነ አጅሬ ቀሩ ቀሩ ቀሩ ቀሩ፣

እነ አበራ ቀሩ አምሳ አለቃ ታዬ፣ እነ ቢተው ቀሩ፣

ያ ጅሬማ ልጆች የቢተውስ ልጆች፣ ያመኑማ ልጆች፣

የነነጋ ልጆች፣ የነ አጅሬ ልጆች፣ የመኮነን ልጅች፣ የዘውዴ ልጆች፣የነ ብሩ ልጆች፣

እንግዲህ እም እም ነው፣

እንገዲህ ኃይንት ታይ ኃይንት መመኪያችን ታዬ ቀርቷል በጠዋት፣

አገራችን ወዲያ ይማም አባ በሀር፣ ገስጥ አባ በሀር፣

እስቴ አፈረ ዋናት እንደ ውዶው ደንበር፣

ይማምስ ገነትስ ያንች ቤት መገናኛ ነበር።

እንኳን የወገንህ እንኳን የዘመዱ፣

እንቦንጭ እንቦጭ አለ የበሬውም ሆዱ፣

ምን ይበጀኝ ብሎ ገለባና ጭዱ።

ታደስ በላቸው አንተ ደህና ነህ ወይ?

በስተ ጨፋ በኩል ልዥ ዳርገው በለጠ፣

በስተ ሰዴም በኩል አባ ደራ አመኑ፣

እኒህ ጀግኖይ ናቸው፣

ወንዝ እሻገራለሁ ዛሬም በስማቸው።

ያባይ ውሃ ሞልቶ ሲመስል እንቆቆ፣

ርብ ውሃ ሞልቶ ሲመስል እንቆቆ፣

አመኑ ገባ አሉኝ ታደሰ በላቸው ገባው ባጭር ታጥቆ።

ኃይንት መውለድ እንጂ ማሳደግ አያውቅም፣

የበልጅግ እርሳስ የሚለቅም።

አመኑ አባ ብሃር ይማም አባ ብሃር የሰው ነገር ወዲያ፣

እንደ አፈረ ዋናት እንደ ውዶ ደንበር፣
ይማም ያንተስ ቤት ገስጥ ያንተስ ቤት መገናኛ ነበር።
ከነ መአኑ ቤትስ ከነይማም ቤትስ ከነነጋ ቤትስ ከነ ኪዶ ቤትስ፣
ካምሳ ለቃ ቤትስ ከታደሰ ቤትስ ታደሰ በላቸው፣
ከነ ፺ አለቃ ቤት ከነ ታደሰ ቤት ከላቀይ መስቀሉ፣
አማቹን ተጠርቶ ታላቅ ታናሽ ወድቆ፣
ከቀን አንዳንድ ቀን የማይጎልበቱ፣
ጠጅና ቢራ ይቀዳል ከቤቱ።
**ሌላ አዝማሪ ገባ**
አባ ሙላት በላይ አይቸው ምትኩ፣
አንድ ሲናገሩት ይመጣል እልኩ።
እንግዲህ ስማዳ እንግዲህ በየምድር በወይፈን ታረሰ፣
እንግዲህ ስማዳ የነ ታዶ ወንድም በወይፈን ታረሰ፣
አንድ በሬ ቢኖር ዛሬ ተጨረሰ።
እስተ ዛሬ ድረስ ፺ አለቃ ታዶ፣
አበበ በላቸው ታደሰ በላቸው፣
እንደተፈጠሩ ዘረ መልካም ናቸው።
በሬው ሶስት እቃ ነው ጎተራው የሞላ፣
አደባባይ ዘልቆ ሲያጠቃ ባላንጣ፣
እንደ ሰም አቅልጦ እንደ ጧፍ፣
የደካማውና የድሃው ጠበቃ።
አስጠምዶ በሬ ከሁዳዱ ላይ፣
የታደሰን ወንድም ሞተ አላችሁ ወይ?
በሮቹ ወይፋፍን ማስፈራሪያው ወኔ፣
በሮቹ ወይፋፍን እርሻው ዋህልድባ፣
ጅምሪቱ ማሬ እስቲ ላገሬ ሰው ልንገራችሁ አዋጅ፣
ለካ ሙታ ነው ወይ ቁንጅናዋን ሳትፈጅ።
እንዲህ ነው ወይ ለካ የእህት ቁም ነገሩ፣

ተሸቀዳደሙበት አፈር ለመሆኑ፡፡
አመን እንጀራው ቀርቦለት በግራው ይበላል፣
ምነዋ ቀኝ እጁ ካፈሩ ተቀብሯል፡፡
አመን አባ ሙላት በዘሩ የኮራው፣
ካደባባይ ዘልቆ ነገር የሚያብራራው፡፡
በየምድር አገሬ የወንድ አመል አመን፣
አየ ጉድን አገሬ እንግዲህ አይገኝ እንዳንት ያል ጀግና፣
በየምድር ተወልዶ ጎንደር የሚያስፈታ፡፡
ሰሜን አርማጭሆ መተማ ዮሐንስ፣
ቸር ይዋል በለሳ ደሞ ጥሩ ዋሻ፣
አመን ሰው መሰለኝ ያለም መጨረሻ፡፡
የወንድ አመል አመን ፱ አለቃ ታዬ አንበሳው በላቸው፣
አባ ብሃር ታዬ ታደሰ በላቸው አመኑ ሽፈራው፣
ሸከርካራ ብሩ ብሩ ሰው በላቸው፣
ኧረ እናንተ ሂዱ ግፍ አደባባይ፣
የበጌምድር ጌታ ሞተ አላችሁ ወይ?
በሮቹ ወይፋፍን እርሻው ወለሊማ፣
ከአውድማው ነው ወይ ከምርቱ ባይጠራ፣ (ዜማ ቀየረ)
አፈር አፈር አለኝ አመን ያንተ እንጀራ፡፡
እረ አመን አመን ሰው ሽፈራው፣
መጣልኝ ሽፈራው ሞተ ይላል እሳ፣
ጠላት ሰርጎ ገብቶ አገሩን ሊያጠፋ፡፡
እሱ አልነበረም ወይ የርሱ መግባቢያ፣
አንች ያመኑ ልዥ እስተዛሬ ድረስ ባል በባል ያጭሻል፣
ጌታውን ብሎ ነው አንችን የት ያውቅሻል፡፡
ስማዳ አገራችን ኩሽሌ አበቀለ፣
በጌምድር አገሬ ኩሻሌ አበቀለ፣
የሚመነጥረው የነ ታዬ ወንድም አንበሳው ነበረ፡፡

የወንድ አመል ማታ ሲሳክበት የሚደርሰው ማልዶ፣
ለካ ሙቶ ነው ወይ የጥቃቱ መንዶ፡፡
አፈሩን ሳኩት የበለሳው በሬ ያርማጭሆው በሬ፣
የግንብራው በሬ፣
አፈሩን ግለጡት በበላው ላይ ከራሱ ላይ፣
አይቀርም አመኑ የነካሴ ወንድም ጥቃት የመጣ ለት፡፡
መልኩም ወለላ ነው እንደ ሠለሞን፣
ግርማው እንደ አራስ ነበር፣
ወሎ እሚጠመደው ጎንደር እቃው ሲያድር፡፡
የሴቶቹ ወንድም የወንዶቹ ባል፣
ውሸቱን እንደሆን ይመስክር አገር፡፡
ባለፈው የሞተው ማስፈራሪያው አመን አንድ ሰው ነው ወይ አንድ ሰው ነው ወይ?
የዘመዱ ቆሌ አትሉትም ወይ፡፡

ለጦር ሜዳ ጀግና የተፎከረ

**የመረጃው ምንጭ፣** ስሙ ያልታወቀ (አባ.2፣ቁ)

**ፉከራው የተከወነበት ዕለት፣** እ.ኢ.አ. 09/10/2004

**ከበ፺ አለቃ ጌትነት ዘለቀ የቀጠሮ ፎገራ ወረዳ በክወናላ ላይ የተቀረጸ**

**ቀረርቶ**

አቅራሪ፣ ኧረ ወየው አይ ሻምበል ጌትነት፣
የኮረሙ ዘማች የውጋዴው ዘማች፣
ኧረ ወየው እናነተ እእእ ኧረ እናንተየ እእእ
ኧረ ወየእው እእእ
ተቀባይ፣ ተው! ተው! ተው!

ፎካሪ ገባ

1. ተንቆርጦ ተኳሽ እንደ ሴት ወይዘሮ፣
ከምድር በታች ይቀራል ብሎ፡፡

አይ ዘራፍ አለ አምሳለቃ!
ይል ነበር!
፺ አለቃ ጌትነት ዘራፍ አለኮ፣
ይል ነበር1
ዘራፍ አለኮ ልፎክርለት ትንሽ ፉከራ፣
ተቀባይ፣ ይል ነበር!
መቼም ይኸው ነው የጀግና ሥራ፣
ተቀባይ፣ ይል ነበር!
አጥንቱ ላፈር ስጋው ላሞራ።።
ኸነ ሂዳኑ ወዴት ደረሱ ልበለው እስቲ፣
ኸነ ዓለምነው ወዴት ደረሱ?
ኸረ እነቁሜ ወዴት ደረሱ ልበለው እስቲ፣
ኸረ እነ ምስጌ ወዴት ደረሱ?
ይመጡ ነበር በበልጅግ ጥይት እየተኮሱ።።
ኸረ ዘራፍ ሲል ብልጭ ብልጭ ቦንብ እንደ መብረቅ!
እንደ ነጎድጓድ ጥይቱ ሲፈልቅ።።
፺ አለቃ ጌቴ አየ ውጋዴን ላይ የኮረም ላይ፣
አየ አሰብ ላይ እንቢ አለኮ፣
ቦግ ቦግ ሲለወ ቦምብ እንደ መመብረቅ፣
እንደ ነጎድጓድ ጥይቱ ሲፈልቅ፣
አለ እኮ ዛርጢ ስሙን የማያውቅ።።
የሚውል እኮ ከዱር ከዋሻ፣
የሚያስበላ እኮ ጃርትና አሳማ፣
አፉ አይናገር ጆሮው አይሰማ፣
ጎትቶ አገባው ከጦር አውድማ አለኮ!
ያዘኝ ልያዝህ ቢባባልማ፣
ያስቀር አልነበር ባዶ ባድማ!
እንቢ አሻፈረኝ ፈሪ ለፈሪ አብረው ሲሄዱ አለ እኮ፣

ኧረ አሰብ ላይ፣ ኧረ ውጋዴ ላይ ኧረ ኮረም ላይ፣
ከሱማል ጋራ እንቢ አሻፈረኝ አለኮ፣
ተው አትውደደኝ፣
ተነስ ሲሉኝ እየነደደኝ።
ተኮሰኮሰ ልበለው እስቲ፣
ኧረግ ዘራፍ ኧረግ አሰብ ላይ ከሱማል ጋራ ተኮሰኮሰ፣
ነካው ፈረሱን፣
እንደ እሳት እራት የጠላው ነብሱን።
ዘራፍ ገዳይ ውጋዴ!
ገድሎ ሳይመጣ መስሎ ነጋዴ አለ እኮ።
ገዳይ አንችም ላይ!
ከሰቀለበት ከጎፈሬው ላይ።
ምሳና ቅጠል አይለብስም ገሳ፣
ጦር እማይፈራ የዱር አንበሳ።
ጠበንጃው ክላሽ ጥይቱ መቶ አለኮ፤
ጠላት ይገላል ከምሽግ ገብቶ።
ከምሽግ ምሽግ ምሽግ ተራምዶ፣
አነባባሪ የሬሳ ነዶ።
ኧረ ዘራፍ አለ!
ፈሪ ለፈሪ አየ ኮረም ላይ አብረው ሲሄዱ፣
ኧረ ለጌቴ አይ ለ፺ አለቃ አለኮ፣
በለው ግንባሩን በዚያው ይመመለስ፣
አይቀርምና ተሰርቶ መፍረስ።
ገዳይ በክላሽ በሁለት ጆሮ፣
እንዳይዛባ ክንዱን ገትሮ።
ገዳይ ባብራራው ባዲሱ ብረት፣
ውሃ በኮዳ የተሸጠ ለት አለኮ።
በዚያ ክልካላ፣

ቅጠሉ ረግፎ ድንጋው ሲባላ፡፡
ገዳይ በግንቦት፣
ሲል ከልታ ከልታ ወታድ እርቦት፡፡
ገዳይ በጥቅምት በዚያ ወለላ አለኮ፣
ጥይት ላኩ ባይ ሰማይ ሲጠራ፡፡
ሰማይ ሲጠራ ሲሆን መነጠር፣
፺ አለቃ ጌቴ የታመነው ጦር፡፡
ዘራፍ ገዳይ በለሳ!
እሬሳ ዘላይ እንደ ሳቢሳ፡፡
ገዳይ ጎንደር ከዚያ ከጭንጫው፣
እንደ ነብሰ ጡር ደፍቶ ባፍንጫው አለኮ፡፡
ቀረርቶ

2. ፺ አለቃ ጌቴ አየ ዘመዶቼ አየጉድን አየ ጉድ፣
አየ ጉድ አየ ጉድ እነገብረ መድን ጠጌ አንተ ወንድማለም፣
አየ ጉድን የባድመን ምሽግ እሳት ይዞረዋል፣
አየ ጉድን የውጋዴን ምሽግ እሳት ይዞረዋል ይዞረዋል፣
የትግሬውነን ምሽግ እሳት ይዞረዋል ይዞረዋል፣
የጦሩ ገበሬ ጌቴ ይባርከዋል፡፡
ግጥም እንዳለቀበት የገመተ ሌላ ፎካሪ ነጥቆት ገባ፡፡

3. ዘራፍ ዘራፍ ዘራፍ!
ወንዱ ጌትነት ባቀናው አገር፣
ሻምበል ጌትነት ባቀናው አገር፣
ሻምበል ምስጋነው ባቀናው አገር፣
ጉቦ በላበት የሴት ወታደር፡፡
ሀይ በል ግባ መቅደስ፣
ነጋዴም ነግድ በመኪና፣
ገበሬም እረስ በበሮችህ፣
እህል ብትበላ አማረብህ፡፡

ሀይ ዘራፍ ብሎ ዘራፍ ሲነሳ፣
ሻምበል ጌትነት የዱር አንበሳ፡፡
አስተጣጠቁ ያለው ከፍ ከፍ፣
ከጠባብ ቦታ የሚለው ከተፍ፡፡
ተወስዱ አይቀር ታልቀረ ምጡ፣
እንደ ጌትነት እንደረመጡ፡፡
ከዚህም አይደል ውጋዴ ምላሽ፣
ጠላቱን ገዳይ በጊዜ ድራሽ፡፡
አይወረወር የሳት አለሎ፣
አይቆረጠም የድንጋ ቆሎ፡፡
አስተጣጠቁ እንደ ወይዘሮ፣
ጠላት ሲመጣ ያፍቃል ዙሮ፡፡
ሻምበል ጌትነት ሻምበል ምስጋናው፣
ዘር አለባቸው እንደ ንስናሽ፣
ሀብታቸው ትልቅ እድሜያቸው ትንሽ፡፡
ዘር አለባቸው እንደ ቁምጥና፣
የሚወረውር ሰው እንደ ቁና፡፡
ሻምበል ጌትነት ዓይኑ እሚመስለው የንጋት ውርጭ፣
እንደደረሰ የሚፈነጭ፡፡
አይ አተኳኮስ ከታፋ አውርዶ፣
ካፋፍ ላይ ካለው ከላይ ከማዶ፣
አንክቶ ጣለው አንገቱን ጎርዶ፡፡
ታንክ በምድር አየር በሰማይ፣
የእህል ሰው ተለይ የጦር ሰው ተለይ፡፡
ብልጭ ብልጭ ሲል በምብ እንደ መብረቅ፣
እንደ ነጎድጓድ ሰማው ሲፈልቅ፣
አንደኛው ሲሮጥ አንደኛው ሲወድቅ፣
አይ የዛን ጊዜ ደርሶ ቢጠየቅ፣

ስንት ዛርጢ አለ ስሙን የማያውቅ፡፡

አይ ዘራፍ እንበለው እስቲ አንተ!

1.3. **የሀዘን አገላለጽ ልማድ**

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣ ቀኝ ጌታ ዜናዊ ስቡሕ (አባ.2፣ቁ.1)**

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 6/09/2004

*ጥያቄ፣ ቤተክረስቲያን ሀዘን በምን መንገድ ይገለጽ ትላለች?*

1. ሀዘንን በተመለከተ በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ቦታ ላይ ተገልጾ እንደሚገኝ ከነገሩኝ በኋላ (2 ሳሙ.12፣22-23) እንዳነብ አዘዙኝ፡፡

> ነቢዩ ዳዊት የወለደው ሕጻን በታመመ ጊዜ ከዙፋኑ ወርዶ ልብሰ መንግሥቱን ጥሎ ማቅ ለብሶ አመድ ነስንሶ አዘነ ጸለየም፡፡ ሆኖም የህጻኑ መሞት በእግዚአብሔር የተወሰነ ስለነበር በሞተ ጊዜ ሀዘኑን ተወ፡፡ ሕዝቡም ባህልና ልማድ እንደተለወጠ አይተው በጠየቁት ጊዜ «ሕጻኑ ሕያው ሳለ ይምርልኛል ሕጻኑም በሕይወት ይኖር እንደሆነ ማን ያውቃል? ብየ ጾምሁ፣ አለቀስሁ፡፡ አሁን ግን ሞቶአል፣ የምጾመውስ ለምንድን ነው? በውኑ እንግዲህ እመልሰው ዘንድ ይቻለኛል? እኔ ወደእርሱ እሄዳለሁ እንጂ እርሱ ወደእኔ አይመለስም» ብሎ መልሶላቸዋል፡፡

ይህ የተጻፈ ለሀዘንተኞች ነው፡፡ ሀዘንተኞች የሞተ እንደማይመለስ አውቀው እንዲጽናኑ ነው፡፡ ለቅሶ የቀቢጸ ተስፋ ነው፡፡ የአህዛብ ሥራ ነው፡፡ ክርስቲያኖች ወደ ፈጣሪያቸው ነው የሄዱ፡፡ ኋላም ደሞ በትንሳኤ ሙታን ይነሳሉ በክብር፡፡ ዘወሮ ማለት ነው ከገጠር ወደከተማ፡፡ ሰው ዘር ነው፡፡ ጳውሎስን ትንሳኤ ሙታን የለም ሲሉት «አንተ ሰነፍ ገበሬ አንተ የዘራኸው ዘር ካልበሰበሰ ይበቅላል?» አለው፡፡ ጤፍም ይሁን ምን ሲዘራ ሳይፈርስ አይበቅልም፡፡ መቃብር መዘራት ነው፡፡

2. ለሞተ ሰው ሀጢያታችሁን እያሰባችሁ እንደራሳችሁ አልቅሱ ነው፡፡ እንግዲህ ለቅሶ ነፍሱ ከስጋው በተለይበት ጊዜና ደሞ ከቤት ሲወጣ ታበላበት ታጠጣበት ከነበረው ቤትህ ወጥተህ ኸድክ ብሎ ወደመሬት ሲገባ ደሞ «ስጋህ ወደመሬት አፈር ነህ ነፍስህ ወደየት

ትገባ ይሆን?» እያሉ ያንን እያዘከሩ ማልቀስ እነዚህ ሶስቱ ግዴታ ናቸው፡፡ ከዚህ በተረፈ ግን እንዲው «አካኪ ዘራፍ!» እየተኩሱ ማለቀስ ያ ያህዛብ ስራ እንጂ የክርስቲያን ሥራ አይደለም፡፡

*ጥያቄ፣ ቤተክርስቲያን እንዲህ ብታስተምርም ህዝቡ ግን ይፈጽመዋል፡፡ ይኽ ነገር ከመጀመሪያ አመጣጡ ከየት ነው?*

3. ይኽ ከእምነት በፊት የነበረው ያህዛብ ሥራ ነው፡፡ ትምህርቱም ባብዛኛው ወንጌል ስላልተሰበከ ነው፡፡ ከግራኝ ወዲህ ነው ይኽ እንግዲህ፡፡ ከግራኝ በፊት ወንጌል ይሰበክ ነበር፡፡ የቀሳውስቱ ማዕረጋቸው ዝቅ ማለት የመጣ፣ ቢናገሩ መሰማት የለ እንዲህ ያለው ሁላ ከግራኝ ወዲህ የመጣ ነው፡፡ ስለዚህ ትምህርት በማነሱ ላይ ያህዛብ ሥራ እየተቀላቀለ እየተቀላቀለ ገባ፡፡ ሞተ ቀረ በሰበሰ ብለው ያምኑ የነበሩና ተስፋ የሌላቸው ሰዎች ሲያደርጉት የነበረው ነው፡፡ እንኳን ሌላ የክርስቲያን ብዙ ልማዶች አሉ፡፡ ያንን ጥሩውን ሥራ ወደአምልኮ ባይድ እየወሰዱ አሁን ይኽ ንፍሮ የሚባል (የግንቦት ልደታን መሆኑ ነው) የመስቀል እርድ (አድባር፣ ቆሌ) እንዳምልኮ ጣዖት የሚወስዱት አሉ፡፡ በመጽሐፉ መጀመሪያ የተሰራበትን ትተው ወደእነሱ ፍላጎት፡፡ ይኽ እንግዲህ የትምህርት ማነስ እንጂ የቤተክርስቲያን ሥርዓት አይደለም፡፡ ይኽ ሲደጋገም እንደባሕል ሁኖ ዋናው ሲረሳ ይኽ እየገነነ ይሄዳል፡፡

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** መሪጌታ ክፍለማርያም አለነ (አባ.2፣ቁ.2)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 21/06/2005)

*ጥያቄ፣ አንድ ሰው ሲሞት ሀዘን እንዴት ነው የሚገለጸው?*

1. እንደቤተ ክርስቲያን ከሆነ በሶስት መልኩ ልቅሶ እንደሚያስፈልግ ትገልጻለች፡፡ አንደኛው ነብሱ ከስጋው ስትለይ፡፡ ይህ ማለት ያዕቆብ አባቱ ሊቀ ካህናት ነው የነበረ፡፡ ከእናቱ ጋር ሁኖ በሶስት ዓመቱ ከእናቱ ጋር ሁኖ ወደ ቤተክርስቲያን ሄደ፡፡ ቅዳሴ ማገባደጃ ሁኖ ሥጋ ወደሙ ሲፈተት ብላቴናው ወደቤተምቅደስ ገባ፡፡ ሊቀጳጳሱ ይህንማ እንደ እዝራ ሱቱኤል መንፈሱ አነሳስቶ ነው ያመጣው ብሎ ሥጋ ወደሙን አቀበለው ይላል፡፡ ወዲወኑ ወጥቶ «እኔ ሶስት ነገሮች አስፈሩኝ» አለ፡፡ «ነብሴ ከሥጋየ ስትለይ፣ ከእግዚብሔር ፊት ስቀርብ፣ ቀጥየ ፍርድ ስሰማ አስፈሩኝ» አለ፡፡ በዘመኑ የነበሩ ካህናት

ይህን ሰምተው እግዚአብሔር በሕጻኑ አድሮ ሲገስጸን ነው ብለው አዘኑ፡፡ ወደለቅሶው እንመለስና ከዚህ ዓለም በነበረበት ሟች ሲለይ አንድ ለቅሶ፣ በዚህ ዓለም ከነበረበት ቤቱ ሲወጣ፣ ከዚህ ዓለም ከነበረበት ቦታ ለቆ ወደመቃብር ሲወርድ ይለቀስለታል፡፡ ከዚህ ወዲያ ያለውን የመታሰቢያ ለቅሶና ሌላውንም ቤተክርስቲያን አትደግፍም፡፡

1.3.1. በአካል ላይ የሚፈጸሙ

***የመረጃ አቀባይ ሥም***፣ አቶ ገበያው ዓለሜ (አባ.2፣ቀ.11)

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን***፣ እ.ኢ.አ. 17/09/2004

ከዚያ ከኃይለሥላሴ እንዲህ ወደ ኂላ ያለው ሥርዓት ፊቱን ካልነጨ «አለሰማም እንዴ መሞቱን እከሌ መሞቷን አላወቀም?» ይባላል፡፡ ፊቱን ካልነጨ አለቀሰ አይባልም፡፡ እንኳን ሴት የሆነው ወንዱ መንጨት አለበት፡፡ እንግዲህ የእኛ ባህላችን ፊት መንጨት ነው፡፡ በለቅሶው ቀን ድሪውን ማተቡን መስቀሉን አስቀምጦ ክር ያስራል፡፡ በኂላ ጠጉራቸውን ይላጫሉ፡፡ እስከ ሰባት ቀን ይላጫሉ፡፡ ማቅ ለምድ ደግሞ ሌላ ነገር ድሪቶ ለብሶ በገመድ ታጥቆ ነበር የሚያዝን፡፡ መደበኛ ልብሳቸውን አይለብሱም፡፡ ዛሬ መደበኛ ልብሱን ነው የሚለብስ፡፡

***የመረጃ አቀባይ ሥም***፣ አባ አቸነፍ እንግዳ (አባ.2 ቀ.12)

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን***፣ እ.ኢ.አ. 10/09/2004

*ጥያቄ፣ የቅርብ ዘመዶችስ ሀዘናቸውን እንዴት አድርገው ይገልጻሉ?*

1. ፊታቸውን ይነጫሉ፣ ፊታቸውን በመንጨት ግን ዛሬም ባላገሩ ይሞክራል፡፡ ጥናፋ በሚባል አገር ዘመዶች አሉነ እንዲያው ስንሄድ ፊታቸው ተጠብሶ ነው የምናገናቸው፡፡

*ጥያቄ፣ እንዲያ እሚያደርጉት ግን ለምንድን ነው?*

2. የድንጋጤ ሀዘን ነው፡፡ እንዲህ ያደርጋል የሚባል ነገር የለውም፡፡ የድንጋጤ ሀዘን የምር ማዘናቸውን ለማስታወቅ ነው፡፡ እነ እገሌ አይ እንዴት አድርገው አዝነዋል ፊታቸውን መች አስተርፈውታል፤ እነ እከሌማ የሞተባቸውም አይመስሉ መች ፊታቸውን ነክተውታል ይላል ተመልካች፡፡ ጠጉራቸውንም ይላጫሉ፡፡ ጥምጣም የመጣ አሁን አሁን ነው እንጂ አይጠመጥሙም ነበር፡፡ ጌጣቸውን ያወልቃሉ፡፡ ማተብ አትፈታም፡፡ ሌላው ጌጣጌጥ እርባን ምናምን ድሪ ይወጣል፡፡

***የመረጃ አቀባይ ሥም፣ መሪጌታ ክፍለማርያም አለነ (አባ.2 ቁ.2)***

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣ እ.አ.አ. 21/06/2005***

*ጥያቄ፣ ፊት መንጨት፣ ልብስን ገልብጦ መልበሱ ከምን ጋር የተያያዘ ነው?*

1. ልማዱ ከእስራኤል የመጣ ነው፡፡ እሥራኤል ስንል በምን ምክንያት ነው ስንል በተለይ በግብጽ ባርነት በነበሩበት ጊዜ የተለያየ የደረሰባቸው በደል አለ፡፡ ለምሳሌ ራሄል ጭቃ ስትረግጥ መንትያ ልጇ ከጭቃው ላይ ወደቀ፡፡ «እረ እንዲህ ሆንክ» ብላ ለጭቃ አስረጋጩ ስትነግረው «የሰው ደም ጭቃውን ያጠብቀዋልና እርገጭው» ብሏት ረገጠችው፡፡ በዚህ ምክንያት እንባዋን ወደሰማይ ረጭታ አለቀሰች፡፡ ፊቷንም ነጨች፣ ማቅ ለበሰች፡፡ ይህን ሀዘን እንደሰረገላ አድርጎ እግዚአብሔር የእሥራኤልን ጸሎታቸውን ሰማ ይላል፡፡ ትንቢተ ኤርምያስ 31፣13 ይህ ችግራቸውን፣ ሀዘናቸውን የሚገልጹት ባለባበሳቸው እንደሆነ ያሳያል፡፡ በኋላም ያዕቆብ ለራሄል መጀመሪያ ላይ እንዳለቀሰላት ይገልጻል፣ ለሙሴ ደግሞ 30 ቀን ሁሉ እንዳለቀሱለት ይገልጻል፡፡ ይህ የሀዘን ምልክት ነው፡፡ «ይህ ያምር የነበረው ልብሳችን በቤተሰባችን ሀዘን የሱ ሞት ሀዘናችን ነው»ሲሉ ይገልጹ ነበር በኦሪት ጊዜ፡፡ ያ ሁሉ ግን የባርነት ምልክት ነው፡፡ አሁን በሀዲሱ ነብስ ከስጋው ከተለየ እረፍት ነው የሚያስፈልገው በሶስት ጊዜ ማልቀስ እንጂ ከዚያ ውጭ ያለው አያስፈልግም፡፡ በመታሰቢያነት ያገለግላል፤ ፊት መንጨት ግን ምን ላይ ነው ጥቅሙ? ሽቶውን ያደረጉት እኮ ለመታሰቢነት ነው፡፡

2. ልማዱ ከእስራኤል አለ፡፡ እስራኤል ፊታቸውን ነጭተው የሚያለቅሱት ችግር፣ መከራ ሲኦል ስላለ ነው፡፡ አሁን ግን በሀዲስ ተወግዷል፡፡ ቤተክርስቲያን የምታምነው ገነት እንደሚገባ ነው፡፡ የገነት ባለቤት ከሆነ ደግሞ ሟች ከሀዘን ወደ ደስታ እየሄደ ነው እንጂ እየሞተ አይደለም፡፡ ለዚህ ሀዘንን ቤተክርስቲያን አትደግፊውም፡፡ በሥርዓት የሆነውን ግን ስለወዳጅነት ወይም ስለ ዝምድና አብሮ ስለመኖር ከቤት ሲወጣ ስለመታሰቢያ «ይቅር በለው» ተብሎ ቀደም ሲል በተገለጸው መሰረት ይለቀሳል፡፡ በስቅለት እለት እነማርያም መግደላዊት ጥቁር ለብሰው ነበር፡፡ በሰሙነ ሕማማት ከሰኞ እስከ ሀሙስ ልብስ ተገልብጦ ነው የሚለበሰው፡፡ ዓርብ ግን በትክክል ይለበሳል፡፡ ችግሩ ሁሉ ስለተወገደ፡፡ አሁን ይህ የሀዘን ልብስ የሚለብሱት ከዚህ ጋር በተያያዘ ነው፡፡ ሲያለቅሱ

እኮ እንዲውም «እናንተ ለራሳችሁ አልቅሱ» እያለ እኮ ባለቤቱ ክርስቶስ ተናግሯል። እሱ ሀጢያትም ምንም የለበትም፤ እኛን ስለማዳን ነው የመጣ። «ስለራሳችሁ አልቅሱ» አወ ልክ ነው። ጥቁር ሲለብሱ የምናየው መነሻው እስራኤልና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። ፊታቸውን የሚነጩት ከዚያ ባህል ጋር አያይዘው ነው። እኛ ግን አሁን ከመከራ ነጻ ስለወጣን እዳ ስለሌለብን ይህን ማድረግ አይገባም።

### 1.3.2. በአለባበስ የሚገ̥ለጹ የሀዘን ልማዶች

o

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አባ አቸነፍ እንግዳ (አባ.2 ቁ.12)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 10/09/2004

*ጥያቄ፣ የሟች የቅርብ ዘመዶች እስከ ስንት ቀን ነው የሀዘን ልብስ የሚለብሱት?*

እስከ ሶስት አራት ቀን ሀዘንተኛ ሁነው ይለብሳሉ።

*ጥያቄ፣ ከዚያ በኂላስ?*

1. ኸዚ ወዲያማ ሌላ ለቅሶ ባለ ቀን ያነኑ ያዘን ልብሳቸውን ለብሰው ይሄዳሉ። በጣም አዘን የተሰማቸው ሰዎች ኸረ እስተ ብዙ ቀን ሲቆዩ አያለሁ። ያንን ያዘን ልብስ ለብሰው እንዲያው የሰው ለቅሶ አድማቂወይ ናቸው።

*ጥያቄ፣ የራሳቸው ልብስ ላይስ አለባበሱ ላይ ለውጥ የሚያደርጉት ነገር አለ?*

2. ዛሬ ቀብረው ከሆነ ከነገ ወዲያ በሰልስቱ ይታጠባል። ያ ሬሳው ለብሶት የነበረው፣ የሟቹ ልብስ ይታጠብና ለምጹዋት የሚሄደው ይሄዳል። ለምጹዋት ሳይታጠብ አይሄድም። እንደዚያ ነው የሚያደርጉ። ጥቁር ልብስ ይለብሱ ነበር ዱሮ። ዛሬማ አዳዲስ ልብስ ባይኖረው እንኳን ተውሶ ይወጣል። እንደ ሰው ነው። አንዳንዲቱ ቶሎ ታስራለይ። እስከ አርባው ሴት ከሆነች እስከ ሰማንው ይቆያል። አንዳንዱ የምር የሚያዝን እስከ ብዙ ጊዜ ይቆያል። ከዚያ ወዲያ እርባናቸውንም ሆነ ድሪያቸውን መልሰው ያስራሉ። ባሏ የሞተባት ሴት የባሏን ሱሪ ከትከሻዋ ላይ ዘቅዝቃ ትለብሳለች። ኮቱንም ትደርባለች። መለያዋ ይኸ ነው። ይህን የምታደርግ የሟች ሚስት ናት።

*ጥያቄ፣ እህት ወንድሞችስ?*

እህት ኮት፣ ሸሚዝ ይለብሳሉ፡፡

*ጥያቄ፣ በዚህ አካባቢ ስንት አይነት ለቅሶዎች አሉ?*

3. በፊት ጊዜ አንድ ሰው ያስታምማል፡፡ በሞተበት ጊዜ ... ማቅ ይገለብጣል፣ በርኖሱን ገልብጦ ይለብሳል፡፡ ዝቅ ያሉት ድሆች አጎዛ ይለብሳሉ፡፡ አጎዛ ፣ ድሪቶ ይታጠቃሉ፡፡ ፊታቸውን ይነጫሉ፡፡ እንደዚህ ነበር ኋላ አስከ ሰባት ቀን አዘን ያደርጋሉ፡፡ በቤታቸው ህዝቡም ያስተዛዝናቸዋል፡፡... ያዘን ምልክቱ ዱሮ ይኸ ነው፡፡ አሁን ግን ተለውጧል፡፡ በጌጥ ነው የሚለቀሰው እንጂ ባጎዛ በድሪቶ አይለቀስም፡፡ ዛሬ ባበባ ጨርቅ ነው ለቅሶ የሚዋል፡፡

   ቤተሰብ ሲሞት በፊት ... ማቅ መገልበጥ፣ ወጮ መልበስ አለ፤ ይኸ አለ በጥንቱ ጊዜ፡፡ አሁን ግን ተለውጧል፡፡ አሁን መርዶ ፊት አይነጭም፤ ራስ አይላጩም፤ ጨርቅ አይጣልም፤ አጎዛ አይለበስም፤ በርኖስ አይገለበጥም፡፡ ዛሬ በመልካም ልብስ ነው የሚያለቅስ፡፡ ካቦርቱን ለብሶ እየተጀነነ ነጭ ኩታውን ለብሶ መዋል፡፡ ይኸ ነው፡፡

***የመረጃ አቀባይ ሥም***፣ **አቶ ጸጋየ ጀንበሬ (አባ.2 ቁ.23)**

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን***፣ **እ.አ.አ. 10/09/2004**

*ጥያቄ፣ ሰዎች ወደ ለቅሶ ሲሄዱ እንዴት ነው የሚለብሱት?*

1. ማንኛውም ሰው ዝምድና ባይኖረውም ለቅሶ ሲሄድ፣ ሴቶች ነጠላቸውን ከቤት ጀምሮ ዘቅዝቀው ለብሰው ይሄዳሉ፡፡ ከቀብር በኂላ ከቤት እስኪገቡም አይገለብጡም፡፡ ወንዶች ግን ሊገናኙ ሲሉ ቀኝ እጃቸውን ቢያወጡም ከተገናኙ በኂላ አስተካክለው ይለብሳሉ፡፡ ሀዘንተኛ ሴቶች ወደቤት የሚመለሱት በዚያው አለባበሳቸው ሲሆን ወንዶቹ ግን ከለቅሶው ቦታ ዘወር ካሉ በኂላ አስተካክለው ይለብሳሉ፡፡ ለሀዘንተኞቹ ደሞ መለያ ምልክቶች አሉ፡፡ ሴቶቹ ኩታቸውን ዘቅዝቀው ወገባቸውን ያስራሉ፡፡ እንደቀረቤታቸው ጎረቤትም ቢሆን ሚቿ ሴት ከሆነች ቀሚስ ከጀርባቸው ላይ ደርበው ይለብሳሉ፡፡ ወንድ ከሆነ ኮት ይለብሳሉ፡፡ ባሏ የሞተባት ሴት ኮቱን ደርባ ሱሪውን ዘቅዝቃ ከተከሸዋ ላይ ታደረጋለች፡፡ ባሏ የሞተባት ሴት ወዳጅ ወይም ጓደኛ ደግሞ ኮት ይደርባሉ፡፡ ሌሎች

ወንዶች ደግሞ ልጅም ሆነ ወንድም ኩታቸውን በወርዱ አጣጥፈው ከአንገታቸው ላይ ይጠመጥሙታል።

*ጥያቄ፣ የሟች የቅርብ ቤተሰቦች የምንላቸው በደብረታቦር ሀዘናቸውን እንዴት ነው የሚገልጹ? እስከመቼ ምን ያደርጋሉ? ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ ያለውን እያነሳችሁ ብንወያይ።*

2. የሀዘን ቆብም ሆነ ዘቅዝቆ መልበስ ከጥንት ጀምሮ የመጣው እስከ አርባ ቀን ድረስ ነው። አንዳንዶች ከዚያም አልፈው ይሄዳሉ። እንደ ሕግ ልምድ የሚቆጠረው ግን እስከአርባ ቀን ብቻ ነው። «ዐይኑ ሳይፈስ የመከራ ጨርቅ እንዴት እጥላለሁ? ቆብ እንዴት አወልቃለሁ?» የሚሉ አሉ። አንዳንዶቹ አሁን በገጠር የምናየው ወንድማቸው ከሞተ ሱሪ እየለበሱ ነው። ደብረ ሲና በሚባል አገር ሄጄ ይህን አይቼ «ሱሪ ባሏ የሞተባት ሴት ትልበስ እንጂ እንዴት ነው እናንተ የምትለብሱ እግዚአብሔርን እያስቀያማችሁ ነው»፣ ብያቸው አንዳንዶቹ እነንዲውም አሁን የኜን ነገር ይዘው እየከለከሉ እያስተው ነው። አንዳንዶች ሞክረው አስትተናቸዋል።

***የመረጃ አቀባይ ሥም፣*** አቶ አለምነው አሉላ (አባ.2፣ቁ.23)

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣*** እ.ኢ.አ. **10/09/2004**

1. እንግዲህ ባህል ነው። ሴት ባሏ ሞቶባት ከዓመት በፊት የሀዘን ልብሷን ከመልበስ ፊቷን ከማነስቀል አትመለስም። ሌላው እህትም ሆነች ወንድም ጥቁር ለብሰው ያዝናሉ። በተለይ በገጠር ታጥቀው (ሴቶች በነጠላቸው ጫፍ ወገባቸውን አስረው ጫፉን ወደ ላይ በመመለስ አንገታቸው ላይ ያስሩታል፣ ጸጉራቸውን በጥቁር ሻሽ ይሸፍናሉ) የሚያዝኑት ይረግ (ተስካር) ሳይወጣ (ለወንድ በ40 ለሴት በ80) ሀዘናቸውን አይተውም። የሌለውና ይረግ የማያወጣ ቢሆንም ሀዘናቸውን እስከ አርባ ቀን አይተውም። በአካባቢው ሌላ ሰው በሞተ ጊዜ የባሏን ኮት ሳትደርብ፣ ሱሪውን ሳትዘቀዝቅ ለቅሶ የምትሄድ ሴት የለችም። ይህ አስከ መንፈቅና አመት ድረስ ይቀጥላል። ከባሏ ለቅሶ ያልደረሰ ሰው ይህን ምልክት አይቶ በዚህ አጋጣሚ ለቅሶ ሊደርስ ይችላል። የሀዘን ምልክታቸውን እስከ ዓመት ድረስ አይጥሉም።

***የመረጃ አቀባይ ሥም፣*** አቶ ገበያው ዓለሜ (አባ.2፣ቁ.11)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣ እ.ኢ.አ. 17/09/2004**

*ጥያቄ፣ ሀዘንተኞቹ አለባበስ ምን ይመስላል?*

1. አለባበስ ዝብርቅርቅ ያለ ነው። ከደርግ ወዲህ ነው የመጣው ሱሪ እሚለበሰው ለሚስት ነበር። ሚስት ካለች እንኳ እናቲቱ አትለብስም። ያን ዛሬ ቀለበት እንደሚባለው ሽምቀቅ ወይም ደግሞ ከሱሪው ከኂላ ላይ ቀለበት አስሮ ነው ይደረግ የነበረው። የቃል ኪዳን የሀይማኖት መለያ ነው የነበረው። የጽናቷ፣ የሰማንያ ሚስት የመሆንዋ። ዛሬ አንድ ወንድ ሲሞት ልጅነሽ፣ ወንድመነሽ አጎትም ሱሪ ነው። ወንድ ወንዱ። ሱሪ እንዴት ሚስት የምትለብሰውን ወንዶች የምትለብሱ ባሕላችን ያላመጣውን አውልቅ ብለን እየገፈፍን ነው።

*ጥያቄ፣ ሴቶቹስ ምን ይለብሳሉ?*

*2.* ዱሮ እንግዲህ ኮት ሰውየው ኮት አለው ብዙ ልብስ አለው ሴቶች ከደጁ ጀምረው ነው እየለበሱ የሚወጡ። ለዚያ ለሰውየው ክብር። ኮትም ቢሆን ወንዱ ሲለብስ ነውር ነው፣ ሱሪ መልበስም ነውር ነው። ሴት ስትሞት ደግሞ ሰውየው ቀሚስ ለብሶ። «እንዴት የሴት ቀሚስ ትለብሳለህ?» ተብሎ ይተቻል። ሴት ስትሞት ሴቷ የሴቷን ልብስ ልትለብስ ትችላለች። ወንድ ግን ወንድሙ ቢሞት አባቱ ቢሞት ያለ ሚስት ሱሪ መልበስ አይፈቀድም። ሴት ስትሞትም ያለልኳና ጓደኛዋ በቀር ቀሚስ የሚለብስ የለም። ኮት የሚለብሱት ሴቶቹ ወንድማቸው የሞተ ስለመሆኑ ነው። አምስት እህቶች ቢኖሩት አምስት ኮት ይለብሳሉ። ትልቁ ስህተት ያለው ከምን ላይ ነው ሱሪና ቀሚስ መልበስ። ሴት ልጅ ስትሞት ወንድ ልጅ ቀሚስ እንዴት ይለብሳል፣ ወንድ ልጅ ሲሞት ወንድ ልጅ እንዴት ሱሪ ይለብሳል? ነውር ነው።

1.3.3. **ሌሎች የሀዘን መግለጫ ልማዶች**

**የመረጃ አቀባይ *ሥም*፣** አቶ ወንዳያ ጓንጉል (አባ.2፣ቁ.15)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣ እ.ኢ.አ. 17/09/2004**

*ጥያቄ፣ ሌላ ካመጋገብ ካተኛኝ ጋር የሚያያዝ የሀዘን መግለጫ ልማድ አለ?*

1. አለ፡፡ እንደ ሰወቹ ቢለያይም ከ15 እስከ አርባ ቀን ለሚሆን ካልጋ አይተኛም፡፡ ብርድ ልብስ አይለበስም ከወለወሉ ላይ ነው የሚተኛ፡፡ እንኳን አዘንተኞቹ የአካባቢውም ሰው ቢሆን እነሱን እያስተዛዘነ ከወለል ላይ ነው የሚተኛ፡፡ ለቅሶ ደራሹን ከወለል ላይ ተቀምጠው ይቀባላሉ፡፡ ቴሌቪዝን፣ ሬዲዮ አይከፈትም ተሸፍኖ ነው የሚቀመጥ፡፡ ነብስ ያላወቁ ልገሮች እንዳይከፍቱት፡፡ ደስታ ወዳለበት ቦታ አይሄዱም፡፡ ቅቤም አይቀቡም፡፡ ጠጉራቸውን አይሰሩም፡፡

**የመረጃ አቀባይ *ሥም*፣** አቶ አለምነው አሉላ (አባ.2፣ቁ.23)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 10/09/2004

*ጥያቄ፣ ካለባበስና ባካላቸው ላይ ከሚደርሱት ሌላ ሀዘናቸውን የሚገልጹበት ልማድ ካለ ብትገልጹልኝ፡፡*

1. ደስታ ወዳለበት ቦታ አይሄዱም፡፡ በማሕበራዊ ህይወት ተገደው ቢሄዱም ሲዘፈን አያጨበጭቡም፡፡ የሚያግዙት ነገር ከሌለ ዘፈን ሲጀመር ሲል ወደቤታቸው ይሄዳሉ፡፡ እንዲውም የሚገርመው አሁን ባላቸው ሲሞትባቸው ሴቶቹ ዓለሜ ከሱ ጋር ተቀብሯል ብለው በማተባቸው እንደጠኑ ቀርበው መልክሰው እያየናቸው ነው፡፡ ልገሮቻቸውን ሽክፊው ስለሚያሳድጉም ሕብረተሰቡ ያከብራቸዋል፡፡

**የመረጃ አቀባይ *ሥም*፣** አቶ ታደለ ሲሳይ (አባ.2፣ቁ.38)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 10/05/2006

*ጥያቄ፣ ሀዘን የደረሰባቸው ሰዎች ፊታቸውን ከመንጨትና ጥቁር ከመልበስ ውጪ ሀዘናቸውን በምን ይገልጻሉ?*

1. ባልጋ አይተኙም፡፡ በቆራጣ ቁረንጮ ነው ኸመሬት ላይ እሚተኛ፡፡ ወደሰርግ ቢሄዱም አይዘፍኑም፤ አይደልቁም፡፡ የተጎዳ ሰው ዘፈን የለ፣ ጭብጨባ የለ፣ ድለቃ የለ ዝም ብሎ ቁጭ ነው፡፡ እስተ ስድስት ወር ድረስ እንደፍቅራቸው ኸዚያም በላይ ሲቆዩ ይችላሉ ቅቤ አይቀቡም፡፡

**የመረጃ አቀባይ *ሥም*፣** አባ አቸነፍ እንግዳ (አባ.2፣ቁ.12)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣ እ.ኢ.አ. 29/09/2004**

*ጥያቄ፣ ማቅ ከመልበስ ፊትን ከመንጨት፣ ጸጉርን ከመላጨት ውጪ የሚያወቁትን የሀዘን መግለጫ እስቲ ያጫውቱኝ፡፡*

1. ሴቶች ቅቤ አይቀቡም፡፡ እሚተኙም በቆራጣ ሰሌን ነው፡፡ ማተባቸውን አያስሩም፡፡ ብዞቹ ከፍቅር እንዲህ ቢያረጉም የሟች ዘመድ ያፍሩናል፤ ጎረቤት ምን ይለናል? እያሉ አርባና ሰማንያ ከወጣ በኂላ እንኳን በሉንታ እሚቀጥሉ አሉ፡፡ ቄሶችም ይገስጣሉ፣ የቀርብ የሚባል ሰውም ተው/ተይ ብሎ ያስተዋል እንጂ ሰውነትን ማጎሳቆል አለ፡፡

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣ አቶ ጸጋየ ጀንበሬ (አባ.2፣ቁ.19)**

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣ እ.ኢ.አ. 10/09/2004**

*ጥያቄ፣ የሟች የቅርብ ቤተሰቦች የምንላቸው ራሳቸውን አጎሰቁለው የሚቆዩት ለምን ያህል ጊዜ ነው?*

1. የሀዘን ቀብም ሆነ ዘቅዝቆ መልበስ ከጥንት ጀምሮ የመጣው እስከአርባ ቀን ድረስ ነው፡፡ አንዳንዶች ከዚያም አልፈው ይሄዳሉ፡፡ እንደሕግ ልምድ የሚቆጠረው ግን እስከአርባ ቀን ብቻ ነው፡፡ ዐይኑ ሳይፈስ የመከራ ጨርቅ እንዴት እጥላለሁ? ቀብ እንዴት አወልቃለሁ? የሚሉ አሉ፡፡ ተዝካር ሳይወጣላቸው ቢጥሉ ሰው በጥሩ አይን አያያቸውም፡፡

### 1.4.የመታሰቢያ ሥርዓቶች

#### 1.4.1. የሥንብት ሥርዓት

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣ ቀኝ ጌታ ዜናዊ ስቡሕ (አባ.2፣ቁ.1)**

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣ እ.ኢ.አ. 6/09/2004**

*ጥያቄ፣ አፈር ተመልሶ ሲያበቃ ካህናት ምንድን ነው የሚጸልዩት?*

ማሰናበቻ ጸሎት ነው፡፡

*ጥያቄ፣ የማሰናበቻ ጸሎቱ ምንድን ነው?*

1. ጸሎተ ቡራኬ አባ ሳሙኤል ይነበብና ይሰናበታል። እንግዲህ ፍትሃቱ ሲያበቃ ወደ ቤተክርስቲያን ይሄዳል። ቤተክርስቲያን እንድትቀበለው ይጸለያል። ያ ሬሳውን ቤተክርስቲያን እንድትቀበለው ማድረጊያ ነው። ከቀብር በኋላ የሚደረገው ጸሎት ደግሞ የመሰናበቻ ነው። እንግዲህ የመለያየት ነው። ሟችን መንግስተ ሰማያት ያግባህ ቋሚዎቹን ያጥናችሁ ተብሎ መለያ (መሰነባበቻ) ነው።

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** ሻምበል አብርሃም አሰገድ (አባ.2፣ቁ.26)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 29/09/2004

*ጥያቄ፣ ማርገጃ ከደረሰ በኋላ ካህናት ምን ያደርጋሉ ሌላው ጨዋውስ ምን ያደርጋል?*

1. ቀብረው ሲመለሱ ቃለ እግዚአብሔር ኑዛዜ ይሰጣሉ። እግዚአብሔር ይፍታህ ይላሉ፣ ልቅሶው ይፈታል ከዚያ ወዲያ። ባለመከራው ረፉልን ልስ አርገናል ይላል።

*ጥያቄ፣ ሲለያዩ እንዴት ብለው ነው የሚለያዩት?*

2. ያርፋል ሂዱ። እዝኑን እየበላ «እግዚሃር ያስችላችሁ፣ የመከራ ዳርቻ ራድርግላችሁ» እያለ ይሄዳል።

*ጥያቄ፣ ሀዘንተኞቹ ምን ይላሉ?*

እግዚሃር ያስችላችሁ ሲላቸው «እሱን ያስችለው» ይላሉ። እንደዚህ ነው።

*ጥያቄ፣ እግዚአብሔር ያስችላችሁ የሚሏቸው እንዴት ሁነው ነው?*

3. አንዳንዱ «እግዚሀር ያስችልህ ብሎ»ሀዶ ይነካል። የማይነካም አለ ሰገድ ብሎ የሚሰናበት።

*ጥያቄ፣ እንዲህ ማለታቸው ከምን ጋር የተያያዘ ነው? የምታውቁውት ነገር አለ?*

«ለመከራው መጥኖ ይስጥህ። አታልቅስ» ማለት ነው እንጂ ሌላ ምን አለ።

«እግዚአብሔር ያስችላችሁ» ማለት «ተውት እንግዲህ ሙቷል አታልቅሱ» ማለት ነው።

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ ወንዳያ ጓንጉል (አባ.2፣ቁ.15)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣ እ.ኢ.አ. 29/09/2004**

*ጥያቄ፣ የስንብት ሥርዓት እንዴት ነው የሚካሄደው?*

1. ሥርዓተ ቀብር ይፈጸማል። ሥርዓተ ቀብር በሚፈጸምበት ሰዓት ጸሎት ይደረጋል፤ ያው ተቀምጦ ተነስቶ ወደቤት ይኬዳል፤ ልክ ከቤት እንደተገባ እህል አለ (ነብስ ይማር) ይባላል «ነብስ ይማር» እንዲል ሰው «ነብስ ይማር በሉ» ይባላል። እያንዳንዱ ሰው «ነብስ ይማር» ማለት አለበት። ቁጭ ብሎ በልቶ «ነብስ ይማር»ብሎ ይሄዳል። ሲሄድ አዘንተኛውን ጉልበቱን በእጁ ነክቶ «እኔ የእገሌ ልጅ ነኝ አውቀኸኛል ወይ?» ይላል። የሚተዋወቁ ከሆነ «በል ተጎዳህ ሌላ ቀን መጥተን እናስተዛዝንሃለን እግዚአብሔር ያጥናህ እግዚአብሔር ያስችልህ» ብሎ ይሄዳል። ያኛው ሰውየም «ቸር ያምጣላችሁ፣ እሱን/እሷን ያስችለው/ያስችላት» ይላል።

   ተሰናባቹ ጉልበቱን በመንካት «እግዚአብሔር ያጥናህ» ይላል። ይህን የሚያደርግበት ምክንያት ለቅሶው ላይ መዋሉን ለማሳወቅ ነው። ዝም ብሎ በልቶ ጠጥቶ አይሄድም። ልክ ከምግብ እንደተነሳ «ሳልሰናበት አልሄድም» ብሎ ሀዘንተኞቹ ወደተቀመጡበት ሂዶ «እግዚአብሔር ያጥናህ፣ ያስችልህ» ብሎ ይሄዳል። ያኛው ሰውየም (ሀዘንተኛው) እሱን ያጽናው ይላል። ሌላውም እንዲህ እያለ ይሄዳል።

1.4.2. የእዝን አቀራረብ ሥርዓት

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣ ቀኝ ጌታ ዜናዊ ስቡሕ (አባ.2፣ቁ.1)**

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣ እ.ኢ.አ. 6/09/2004**

*ጥያቄ፣ እህል ውሃውስ (እዝኑ) ምንድን ነው?*

1. ከደጋ ከቆላ ተሰባስቦ ሲያለቅስ የዋለው ሰው አርፎ እንባ አድርቁን ቀምሶ ተሰናብቶ እንዲሄድ ለማድረግ ነው እንጂ ሌላ የተያያዘ ነገር የለውም። እንግዲህ ይኸ እንዳገሩ ባህል ነው። እኩሌታው እንጀራ ያደርጋል። እኩሌታው ደግሞ ባቄላውን አሹቅ ያደርጋል። ደገኛው ደግሞ ገብሱን ያደርጋል። እኩሌታው ጠላ ጠምቆ ያደርጋል። እኩሌታው ደግሞ ውሃ ቀድቶ ያቀርባል።

*ጥያቄ፣ የነብስ ስንቅ የሚባል አለ እሱስ ምንድን ነው?*

2. የነብስ ስንቅ ጸሎት እንደሆነ እንጂ ሌላ ምን አለ፡፡

*ጥያቄ፣ ለሟች ተብሎ ከሬሳው ጋር የሚሄድ እህል ውሃ የለም?*

3. በዚህ አካባቢ እንዲህ እሚባል ነገር የለም፡፡ በበለሳና በዚያ እህል ውሃ ተይዞ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይኬዳል፡፡ ያ ግን ሲለፉ ለዋሉት ተብሎ እንጂ ከሟች ጋር ግንኙነት የለውም፡፡ ሙት አይበላ ምን ያደርግለታል፡፡

**1.4.3. የቀናቀንና የተዝካር ሥርዓት**

**1.4.3.1. ከሰልስት እስከሙት ዓመታት ያሉት የቃናቀን ሥርዓቶች**

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አባ አቸነፍ እንግዳ (አባ.2፣ቁ.12)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 29/09/2004

*ጥያቄ፣ ወደ መታሰቢያ ሥርዓቱ ልመልሳችሁና አንድ ሰው ከሞተ በኋላ በስንት ስንት ቀን ምን ምን ነው የሚደረግለት?*

1. በሳልስት፣ ሰባት፣አስራ ሁለት፣ ሰላሳ፣ አርባ፣ ሰማንያ፣ መንፈቅ ዓመት ይከበራል፡፡ በእያንዳንዱ ቀን አከባበር ምን ምን ነው የሚደረገው? በሳልስቱ የተቻለውን እንጀራና ጠላ ቅዳሴ ለቁሶቹ፡፡ በሰባቱም በአስራ ሁለቱም እንደዚያው፣ በሰላሳውም እንደዚው፣ ታገኝ ባርባው ይታረዳል፡፡ እርዱ የሚካሄደው ከቤተክርስቲን ሲሆን የሚታረደው ነገር ከበግ እስከ ከብት እንደ ሀብቱ ይለያያል፡፡ የሚታረደው ከመቃብሩ ላይ ነው ደሙ እንዲፈስበት፡፡ የሴት በሰማንያዋ ነው የሚታረድላት፡፡

*ጥያቄ፣ ይኽ ስለምን እንደሆነ የምታውቁት ነገር አለ?*

2. አናውቀውም፡፡ ስለቆየነ ዝም ብለን ማድረግ እንጂ ምን እንደሆነ አናውቀውም፡፡ ካህናቱ ይኖራሉ፤ ዘመዱም ይመጣና ለቅሶ ይካሄዳል፡፡ አርባው ወይም ሰማንያው ሲወጣ ተቀጥሮ ነው፡፡ የሚሄደውም ይሄዳል የሚያድረውም ያድራል፡፡ እዛዲያ ለሚያድረው ሰው ተብሎ ይደገሳል፡፡ ጠዋት ላይ ከመቃብሩ ላይ ተላቅሰው ይሸኛኛሉ፡፡ በመንፈቅ

ከታሪደም ለካህናት ብቻ ነው። አንዳንድ ሰዎች ባመታት ያርዳሉ። ለቅሶው እምብዛም ነው። ያው አዳር ነው ከዚያ ወዲያ ወደየቤቱ ነው።

***የመረጃ አቀባይ ሥም፣ መሪጌታ ክፍለማርያም አስነ (አባ.2፣ቁ.2)***

***ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣*** **እ.ኢ.አ. 21/06/2005**

*ጥያቄ፣ የመታሰቢያው ዓላማ ምንድን ነው?*

1. መታሰቢያ ከዕለት ይጀምራል። በዕለት እስራኤል ሽቱ ይቀቡ ነበር። ይህም አሁን ለምሳሌ እነማርያም መግደላዊት ከመቃብሩ ሽቱ ሊቀቡ ሲሄዱ ማርቆስ 16 ማቱ 28 ሉቃ 23 ዮሐ. 25 አካባቢ አለ። እነዚህ ሰዎች ሽቱ ሊቀቡ ሄዱ ማለት እስራኤል በእለቱ ሽቱ ይቀቡ ነበር። ከዚህ ልማድ በመነሳት ነው እነዚህ ሽቱ ለመቀባት የሄዱ። ይህ ሽቱ የሚቀባ ሥጋው ነው መቃብሩ። የመቃብሩ መቀባት ለነብስ የሚያደርግላት የለም። ለነብስ የሚያደርግላት መታሰቢያ ሲኖር ነው። ይህ ማለት የሚቀባው ሽቱ ወደ መስዋዕትነት ተቀይሮ ሲቀደስለት ምጽዋት ሲሰጥለት፣ የሰውየው ንብረት ለነደያን ሲመጸወትለት ከእግዚአብሔር ያሳስብለታል። እግዚአብሔር ሰጪም ተቀባይም ነው። በሀብታሞች ላይ አድሮ ሕሊናቸውን አራርቶ ለድሆች እንዲመጸውቱ ያደርጋል። በእኔ ቢጤዎች አድሮ ደግሞ ሀብታሙ የሰጠውን ስጦታ ይቀበላል። ስለዚህ እግዚአብሔር ሰጭም ተቀባይም ነው ማለት ነው።

2. «በዚህ መልኩ የዚህ ሰው ገንዘብ ሲመጸወትለት በነብሱ ይማራል እንጂ፣ ሽቱ ቢቀባለት ተስፋ አይኖረውም» ብለው ይህን ሥርዓት በፍትሃ ነገስት ላይ ቀየሩት ማለት ነው። ሐዋርያት «ለነፍስ፣ መዓዛ ነፍስ ነው እንጂ መአዛ ሥጋ ምን ይረባል?» ብለው «መስዋዕት ሰውለት፤ ዳዊት ድገሙለት፤ ምጽዋት መጽውቱለት፤» ብለዋልና ስለዚህ ነው ይላል። ሽቱው ቀርቶ መታሰቢያው ይደረግለት አሉ። በዚህ መልኩ ቤተክርስቲያን የሐዋርያትን ሥርዓት ይዛ ዛሬ በእለት ይመጸወትለታል፣ በሰለስት፣ በሰባት፣ በዘጠኝ፣ በአስራ ሁለት፣ በአስራ አራት፣ በሰላሳ በአርባ፣ በስድሳ፣ በሰማንያ፣ በመንፈቅ፣ በዓመት ይላል። ነገር ግን፣ በሰለስት ቢቀር ሶስት ጊዜ ሶስት ዘጠኝ ነው በሶስት ከተሰዋለት በዘጠኝ አይሰዋለትም። በሰባት ከተሰዋለት በስራ አራት አይሰዋለትም። አስራ ሁለትና ዕለት የወል ነው። ከዚያ በሰላሳ ባይሰዋለት በስድሳ ይሰዋለታል። በአርባ ባይሰዋለት

በሰማንያ ይሰዋለታል። እንደገና ዙረን በሶስት፣ በሰባት በአስራ ሁለት ቋሚ ይሆንና በአርባ ለወንድ በሰማንያ ለሴት አድርጋ ቤተክርስቲያን እንደህብረሰተቡ ይታሰባል።

*ጥያቄ፣ የእያንዳንዱ ትርጉም ምንድን ነው?*

3. በሰልስት የሚሰዋለት ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሶስት መአልት ሶስት ሌሊት ከመቃብር አድሮ የተነሳው በሶስተኛው ቀን ነው። ከተነሳ በኂላ ከ120 ቤተሰቡ ጋር ሁኖ ምንድን ነው ያደረገ «የሚበላ ነገር አላችሁ ወይ» (ሉ.ቃ. 24፣25) አካባቢ. «ሠላም ለእናንተ ይሁን» አላቸውና «የሚበላ ነገር አላችሁ ወይ?» ከዚያ ተገናኙ። እሱ መሆኑን አላወቁምና ደነገጡ፣ ፈሩ ይላል ምትሃት መስሏቸው። «ለምን ትደነግጣላችሁ ምትሃት እኮ አይበላም አይጠጣም፣ አይጨበጥም አይዳሰስም፣ እኔ እንደሆንኩ እዩኝ» አለ። እጁን ዘረጋ አዩ። ከተረዱ በኂላ «የሚበላ ነገር አላችሁ?» አላቸው። «ትንሽ ማርና ትንሽ አሳ አለች» አሉት። ያች ቀረበችና እሱም በላ እነሱንም አበላቸው። ይህ ምንድን ነው አሁን እሱ ተነስቶ ነው። ይህ የትንሳኤ ዘጉባኤ ምልክት ነው። ወደእኛ ስንመለስ ግን አሁን የእኛ ነብስ ረቂቅ ናት አትመገብም፤ ነግር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚያ ቤት እንደተገኘ ሁሉ እነዚህ ነብሳት ደግሞ ከዚያ ከተቀበሩበት ቦታ ላይ ይገኛሉ። ሲገኙ ከተቆረበላቸው፣ ከተቀደሰላቸው፣ «ዘራችሁን ያርባላችሁ» ብለው መርቀው ይሄዳሉ። ለምን ሙታን በሕይወተ ሥጋ ላሉት ይለምናሉ፤ በሕይወተ ሥጋ ያሉት ደግሞ ለሙታን ይለምናሉ። በዚህ መልኩ በሶስተናው ቀን መታሰቢያ ያደርጋሉ፤ ያቺ የመጣቺው ነብስ መርቃ አመስግና ትሄዳለች። መነሻው ግን ማነው? ኢየስስ ክርስቶስ ነው።

*ጥያቄ፣ ሰባተኛውስ?*

4. ሰባተኛው ሰባቱ ምስጢራት ናቸው። «አንተ ከሰባቱ ነገራት የተፈጠርክ ሕብረተሰብ በዚህ ዓለም ኑረሃል ከሰባቱ ዕለታት አንድ ቀን ሀጢያት ሰርተህ ቢሆን ይቅር በለው» ብለው መታሰቢያ ለማድረግ ከገንዘቡ አንስተው ይመጸውቱለታል። ቅዳሴም ቢሆን ምጽዋትም ቢሆን መታሰቢያነቱ ለእግዚአብሔር ነው።

*ጥያቄ፣ አስራ ሁለቱስ?*

5. አስራ ሁለቱ የአስራ ሁለቱ ሀዋርያት ምሳሌ ሲሆን፣ ይህ ዓለም ጸንቶ ያለው በአስራሁለቱ ሀዋርያት ትምህርት ነው። በወንጌል ማለት ነው። ስለዚህ በ12 ሐዋርያት ትምህርት ሳያውቅ ቀርቶ ሀጢያት ሰርቶ ተሳስቶ እንደሆነ የእዳ በደል አታድርግበት ሲባል መስዋዕት ይሰዋለታል። ወይም ደግሞ መንግሥተ ሰማያት ሰባት በር አላት ይባላል። ለምን ባለቤቱን ጠየቁት (ማቴ.19፣26) አካባቢ ጴጥሮስ «እኛ ሁሉንም ነገር ትተን ተከተልንህ ምን እናገኝ ይሆን?» አለው። «እምታገኙትማ እውነት እላችኋለሁ የሰው ልጅ በክብር በሚገለጽበት ጊዜ እናንተ ደግሞ በአስራሁለት ወንበር ተቀምጣችሁ በአስራሁለቱ ነገደ እሥራኤል ላይ ትፈርዳላችሁ» አለው። ይህ በክብር ዙፋን ላይ ያስቀመጣቸው ሥልጣን በዚህ ዓለም ሳሉ ያስተማሩት ትምህርት ነው። ስለዚህ በዚህ ባስተማራችሁት ትምህርት በር ሁኖ ነብሳትን ታስተምራላችሁ ማለት ነው። ስለዚህ መንግሥተ ሰማያት መግቢያ አስውራ ሁለት በር አላት። በዚያ እንዲገባ በእራሁለተኛው ዕለት ይከበርለታል።

*ጥያቄ፣ ሰላሳውስ?*

6. በሰላሳ አስራኤል መስዋዕት ይሰው ነበር። አስራኤልን ከግብጽ ባርነት ያወጣቸው ሙሴ ነው። በናበው ታራራ አሪት ዘዳግም፣ 34፣16 እዚህ ላይ «ለሙሴ ሰላሳ ቀን አለቀሱለት» ይላል። ወደ እግዚአብሔር ለመኑለት። «ከግብጽ ባርነት ያወጣኸን ከባዱን ባሕር ባሕረ ኤርትራን ከፍለህ ያሻገርከን አንተ ከእኛ ተለየህ» ብለው ሰላሳ ቀን አለቀሱለት። በሰላሳኛው ቀን መስዋዕት ሰውለትና ልቅሷቸውን አቆሙ። አንዱ የዚህ ምሳሌ ነው። ሌላው ደግሞ አዳም ሲፈጠር የ30 ዓመት ጎልማሳ ሁኖ ነው። ከዚህ በኋላ ክርስቶስ በየዮርዳኖስ የተጠመቀው በሳለሳ ዓመቱ ነው። በሰላሳ ዓመቱ ተጠምቆ በሰላሳ ዓመቱ ከሞት የወደቀውን ጎልማሳ አዳነው። ስለዚህ «አንተ አዳኝ ቸር ነህ። በሰላሳ ዓመትህ ተጠምቀህ እንዳዳንከን ሁሉ ይህን ነብስም ይቅር በለው» ተብሎ ነው በሰላሳ ቀን የሚሰዋለት።

*ጥያቄ፣አርባስ?*

7. አርባም እንዲሁ «እስራኤል ሙታቸውን ሽቱ ይቀቡ ነበር» ይላል፡፡ አርባ ቀን እኛ የምነሰዋበት እነዚህ ሕብረተሰቦች ሐጢያት ሰርተው አስቀይመውህ ከሆነ ይቅር በላቸው በማለት ነው፡፡

8. ከዚህ ጋር ተያይዞ በአርባ ቀን ተዝካር ያደርጋሉ፡፡ ወንድ ልጅ ከአብረካ መንፈቅዱስ ከማሕጸነ ዮርዳኖስ የሚወለደው በአርባ ቀን ነው፡፡ ሴቶች በአርባ ቀን አይወለዱም በሰማንያ ነው፡፡ ሴቶች በተፈጥሮ ጉዳይ ወንድ የወለደች እናት ከደሚ የምትነጻ በሰላሳ አምስት ቀኗ ነው ይላል፡፡ ሴት የወለደች በስድሳ አምስት ቀኗ፡፡ ከዚህ በኂላ ያሉት ለአርባና ለሰማንያ ቀናት መንጫ ናቸው፡፡ እና በአርባ ቀኑ ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማሕጸነ ዮርዳኖስ በቤተክርስቲያን ይወለዳል፡፡ በዚህ መንገድ የተወለደ ሕብረተሰብ «ያንተ ልጅ ከሆነ በኂላ በዚህ ዓለም ሲኖር ሀጢያት ቢሰራ ይቅር በለው» በሚል የተቻለውን በአርባ ቀንም ይሁን በሰማንያ ቀንም ይሁን ተዝካር ይወጣል፡፡ የሰው ልጅ ሁለቴ ይወለዳል፡፡ የመጀመሪያው ከጨለማው ወደ ብርሃን ሲወጣ፣ ሁለተኛው ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማሕጸነ ዮርዳኖስ የክርስቶስን ስጋና ደም ሲቀበል ዳግም ልደት ይወለዳል፡፡

*ጥያቄ፣ መንፈቅስ እንዴት ነው?*

9. በዚህ ጊዜ ውስጥ ሀጢያት ሰርቶ እንደሆነ ይቅር በለው ለማለት ነው መስዋዕት የሚቀርብለት፡፡ እንደገና ደግሞ የጸሐይ ዑደት የሚጨርስ በዓመት ነው ይላል፡፡ አንድ ዓመት 365/6 ቀናት ይሆናል፡፡ አራቱ ዘመናት ቢቀያየሩም እነዚህ ቀናት ያው ናቸው፡፡ በእነዚህ ዕለታት ይህ ሕብረተሰብ ሀጢያት ሰርቶ ከሆነ ይቅር በለው ሀጢት አታድርግበት፣ በማለት መታሰቢያ ይደረግለታል፡፡ መነሻቸው ግን አሁንም እስራኤል ናቸው፡፡

10. ከዚህ በኂላ ደግሞ መፈጸሚያ የሚባል አለ፡፡ በሰባት፣ በአስራ አራት፣ በሀያ አንድ፣ በሃያ ስምንት በሰላሳ አመስት፣ በአርባ ሁለት በአርባ ዘጠኝ ዓመት አለ፡፡ አርባ ዘጠኝ ዓመት ሰባት ጊዜ ሰባት ስለሆነ አንድ ሙሉ ሱባኤ ይባላል፡፡ እንግዲህ እንደ ሰውየው አቅም ነው፡፡ ሰባት ዓመት ላይ ሊቆም ይችላል፡፡ ካለው «የእናቴ አጽም ይመርቀኛል፣ ነብሷ ይመርቀኛል» ብሎ ካመነበት ጸጋ ያገኝበታል እስከእድሜ ልክ ሊያካሂድ ይችላል፡፡

ከሌለው ሳያነሳ ሊቀር ይችላል። ሳያነሳ ከቀረ ከዚህ ላይ መጽሐፉ ግን እስከአስራ አራትና እስከ ሃያ አንድ ዓመት ነብሳት ተመልሰው እዚህ ቦታ ላይ እንደሚመጡ ያመለክታል። መታሰቢያ ከተደረገላቸው ደስ ብሏቸው ይሄዳሉ።

11. ባሮክ እንዳየው ዛፍ በቅሎ ክንፍና ክንፉ እስከአድማስ ድረስ ፍሬ አፍርቶ አዕዋፍ ሲመገቡት ከታች እንደማር እንደወተት ያለ የሚወጣ ፈልቆላቸው ሕጻናት ሲጠጡ አየ። ነቅቶ ተመልሶ ተኛ። ዛፉ ደርቆ ፍሬው ረግፎ አዕዋፍ ሲጮሁ ምንጩ ደርቆ ሕጻናቱ ሲያለቅሱ አየ። መልአኩን «ተርጉምልኝ» አለው። «ዛፉ የቁርባኑ፣ የፍትሃቱ፣ አዕዋፍ የነፍሳቱ፣ ፍሬው በመስዋዕቱ፣ በፍታቱ፣ በምጽዋቱ የሚገኙት ክብር ነው» አለው። ምሳሌው ማለት ነው። «ሕጻናት የሕያዋን፣ ምንጩ ሕያዋን በመስዋእቱ በፍታቱ የሚያገኙት ክብር ነው።» መስዋእት የሰውላቸው፣ ቁርባን ያስቀረቡላቸው እንደሆነ ሙታን ባረፉበት ቀን በየዓመቱ ይመጣሉ። «ብድር ከፋይ ልጅ አይንሳችሁ፤ ከርስታችሁ ከጉልታችሁ አይንቀላችሁ» ብለው መርቀው ክብር አግኝተው ይሄዳሉ። ሕያዋኑም ክብር አግኝተው ይቀራሉ። ደርቆ ማየትህ መስዋዕት ያልሰዋላቸው፣ ቁርባን ያላስቀረቡላቸው እንደሆነ «ብድር ከፋይ ልዥ ይንሳችሁ፤ ከርስታችሁ ከጉልታችሁ ይንቀላችሁ» ብለው ተራግመው ክብር አጥተው ይሄዳሉ ሕያዋኑም ይቀሰፋሉ።

ብሎ ተርጉሞለታል።

12. አሁን ነብሳት ባረፉበት ቀን በየዓመቱ ይመጣሉ። ሱባኤው አርባ ዘጠኙ ካለቀ በኋላ ግን አይመጡም። እስከ 21 ዓመት ጊዜ ግን ይመጣሉ። በሌላ መልኩ ደግሞ «የሟቹ ገንዘብ እስካለቀ ድረስ መታሰቢያው ይደረግለት» ይላል። እስከ 21 ግን ገንዘቡ ሳያልቅ ይችላል። መሬት ይኖረዋል ገንዘቡ ነው። ለዚህ ነው «ከርስታችሁ ከጉልታችሁ አያናውጣችሁ» የሚባለው።

*ጥያቄ፣ መታሰቢው ለነብስ ጸሎት ማድረግ ነው። ደግሶ ማብላቱ ግን ከምጽዋት ጋር አይገናኝም። ይህ እንዴት ነው?*

13. አብሮ መብላቱ ምጽዋቱን ሊግድብ አይችልም። ችግሩ ግን የሚጠሩት እነማን ናቸው? የሚለው ነው። እየሰከሩና ሌላ ነገር እያደረጉ መሄድ ይኸ ሥርዓት ነው አይደለም።

ነገር ግን በስርዓት መጥቶ የሚገባውን በስርዓት አድርጎ ዘመድ አዝማዱ ተገናኝቶ ጸሎት አድርጎ መሄድ ከእስራኤል ጋር የተያያዘ ነው፡፡ እስራኤልም እራሱ ያዕቆብ ለራሄል አድርጎላታል፡፡ በአንድ ላይ ሁኖ በአርባውም በመንፈቁም በዓመቱም በሰባት ዓመቱም ተገናኝቶ በልቶ «ነብስ ይማር» ብሎ መሄድ ከእስራኤል የመጣ ነው፡፡

**1.4.3.2. የተዝካር ሥርዓት**

**1.4.3.2.1.የቁም ተዝካር**

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** እሙሀይ ያየሽ ወርቅ ካሳ (አባ.2፣ቁ.43)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 09/05/2006

ሰኔ 15/97 ለሞቱ ባላቸው ከራሳቸው ጋር አራት በሬ አርደው በ4/05/06 ተዝካራቸውን ያወጡ ናቸው፡፡

*ጥያቄ፣ የቁም ተዝካር ባለጉዳዩ በሕይወት እያለ የሚያወጣው ነው፡፡ ለምንድን ነው የሚያወጣ?*

1. ተዝካሩን ለነፍሳቸው ብለው ማውጣታቸውን ይገልጻሉ፡፡ «የቁም ተዝካር ያወጣሁት ልጆቼ እንዳይጣሉ፣ ገንዘብ አጥቶ አንዱ ይሸሽና እንዳይጣሉ እራሴ አወጣሁ፡፡»ይላሉ፡፡ ልጆቻቸውም ተዝካር ክብርና የአባት ቅርስ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

   የቁም ተዝካር ያወጣ ሰው ቢሞት መስቀል ይቆማል እንጂ ሌላ ነገር አይኖርም፡፡ ተዝካር በዚህ ጊዜ ይውጣ ተብሎ አይወሰንም፡፡ በተሟላና በተሳካ ጊዜ ይወጣል፡፡

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ ሀይሌ ዘውዱ (አባ.2፣ቁ.37)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 11/05/2006

*ጥያቄ፣ የቁም ተዝካር የሚወጣላት ሰው ምንድን ነው የሚያደርገው?*

1. ምንም አያደርግም ተምግብ መከልከል ብቻ ነው፡፡ ለራሱ የተደገሰውን እንጀራ ጠላ አይቀምስም፡፡ ለብቻው አንዲት የሆነች ፍየል ታርዳለት ያችን ነው የሚበላ፡፡ እሚቀመጥም ተነጥሎ ነው፡፡ እሚውልም ተገንዞ ነው፡፡ ኸዚያ ወዲያ ተዝካር አይበላም፡፡ የራሱንም ሆነ የሌላ ሰው ተዝካር አይበላም፡፡

*ጥያቄ፣ ለምንድን ነው የማይበላ?*

2. እንጃ፡፡ ምን ሞተ አበቃ አይደል፡፡ ምን አለው ኸዚያ ወዲያ፡፡

*ጥያቄ፣ ብዙ ሰው የቁም ተዝካር ያወጣል?*

3. አወ አለፍ አለፍ መችም ያወጣል፡፡

*ጥያቄ፣ ሰዎች የቁም ተዝካር የሚያወጡ ለምንድን ነው?*

4. እኸ ሀብት ያልቃል፣ ቤተሰብ ይጣላል ምናምን ችግር አለ አይደል በሕዝብ ላይ ያ እንዳይሆን ራሱ ቁሞ በሀብቱ እዳ መንዳውን ጠቅሎ ወደልኸ እንዳይተላለፍ «ቢተርፍ ይጠይቅ ባይተርፍ የራሱ ጉዳይ» ብሎ እዳውን ለመጨረስ ነው፡፡ ይኸ ነው ብልሃቱ፡፡

1.4.3.2.2. ከሞት በኋላ የሚወጣ ተዝካር

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** ሊቀ ማዕምራን አማረ ጌጡ (አባ.2፣ቁ.3)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 22/06/2005

*ጥያቄ፣ተዝካር ያለወጣን ሰው ማሕበረሰቡ እንዴት ያየዋል?*

1. ማሕበረሰቡ ዝቅ አድርጎ ያየዋል፡፡ አሁን እኛ እሱን ለማስቀረት ነው እየሰራን ያለነው፡፡ አንድ በሬ ብቻ ያለው ሰው እሱን እንዲያርድ አይገደድም፡፡ ምዕመኑ እርስ በርሱ ይሰዳደባል፡፡ ከሌላ ተዝካር ሂዶ ቢገኝ «አንተ አውጥተህ ብላ» እስከመባል ድረስ፡፡ ተዝካር ሳያወጣ ከሰው ተዝካር ሂዶ «ከዚህ አካባቢ ወጥ አልቋል ቢል» አንዱ ባላጌ ብድግ ብሎ «የራስክን አውጥተህ ብላ» ብሎ ይሰድበዋል፡፡ ሰው ያቅሙን ይመጸውታል ያስቀድሳል እንጂ እንደደግስ ቤተክርስቲያን አትመክርም፤ አትቀበለውምም፡፡

**የመረጃ አቀባይ ሥም፣** አቶ ግዛቸው ደምሴ (አባ.2፣ቁ.35)

**ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣** እ.ኢ.አ. 09/06/2005

*ጥያቄ፣ የአባትክን ተዝካር ሰፋ ባለ ድግስ አውጥህ ዳስ ላይ እያለህ ነው ያገኘሁህ፡፡ እስቲ ስለተዝካር ያለህን አመለካከትና የወላጆችህን በማውጣትህ የተሰማህን ስሜት ግለጽልኝ፡፡*

1. አባት ማንም ሳይረዳው ማንም ሳያረግለት ለፍቶ ነው ባገራችን የሚያሳድገን፡፡ እኛ ለዚህ በቅተን ወደ ሥራ ዓለም ስንሄድ ችሎታችን ስናውቀው የእናትን ድካም የአባትን ድካም እንዴት መመለስ እንዳለብህ ገንዘብክን አሰባስበህ እውቀትህን ተጠቅመህ «ይህን ከዚህ

ከማጠፋው፣ ከዚህ ቦታ ባውለው ከዚህ ቦታ ባውለው ስም ያስጠራል ቅርስ ነው የሚኖር ለዘላለም ላይምሮየም እርካታ» ብለህ የምታስበው ነገር አለ። የአባቴን ሀውልት የዛሬ ሶስት ዓመት ነው የሰራሁት። ብዙ ልፋት ነበረው ከነወንድሞቼ። ይህ ሁሉ ግን እንዲሆን የሚያደርገው ባሕሉ አይምሮህን ስለሚያስገድድህ ነው። አዕምሮህን ያስጨንቅሃል። «የአባቱን ስም አላስጠራሁም፣ የወንድምን ስም አላስጠራሁም፣ የእናቴን ስም አላስጠራሁም፣ መቼም ከቻልኩ ለሀገሬ፣ ለወገኔ፣ ለሰፈሬ የማደርገው ነገር ይኖረኛል ብለህ ታስባለህ። አብዛኛውን የባህል ጉዳይ አለ። በቤተክርስቲያን በጎረቤት፣ በውቂያ፣ በትምህርት ቤት በዘመድ አዝማድ ስትገናኝ የእነ እከሌ እኮ አልተነሳም፣ የእነእገሌ ተዝካር አልወጣም እሚባል ነገር አለ። እሱ ነው የሚያስገድድህ። ውለታቸውን መመለስ አለብኝ በቃ። ሌላ ምንም አይነት ትርጉም የለውም።
ብድር ልመልስ ነው። እኔም ሰርቼ ሰርቼ ከዚህ ዓለም ስለይ ልዥ ካለ ያወጣዋል። ልዥ ከሌለኝ የእኔ ወንድም አዝማድ ያወጠዋል።

*ጥያቄ፣ ዘመዱ እንዲህ ተገናኝቶ አንተም ከዚያ መጥተህ ስትጫወቱ ምን ተሰማህ?*

2. በጣም ነው ደስ ያለኝ። ተገናኝተው ሲሳሳሙ፣ አብረው ሲበሉ ሲጫወቱ አያቶቻቸውን ሲቆጥሩ ብዙ ነገሮችን ሲነጋገሩ በጣም ደስ ይለኛል። ያለፈ ታሪካቸውን የ60 ዓመት ያወራሉ፤ የ50 ዓመት ያወራሉ፤ የእገሌ ልዥ ናት፣ የእገሌ ልዥ ነው፣ የእገሌ ዘመድ ነው፣ እንዳትጋቡ በጣም ቅርብ ነው። ሶስት ቤት ነን፣ አራት ቤት ነን እያሉ ብዙ የሚጫወቱት ነገር አለ። ይኸ ምነድን ነው ቅርስ ጥበቃ ነው። ባህል ጥበቃ ነው። ካልተሰባሰበ በምን ይጫወታሉ? በስልክ አይገናኙ። መገናኛቸው ሰርግ፣ ክርስተናና ተዝካር ነች። ተፈላልገው የሚገናኙበት ስለሆነ፣ የሚተሳሰቡበት ስለሆነ ቅርስ ነው።

3. ከሚገርምህ አንዲት እህቴ ሁለት ወልዳ ተፋተው ነበር። እሷ ተጠርታ መጣች። እሱን ባንጠራውም ጉዳዩ እንደተዘጋጀ ሲሰማ ይመለከተኛል ብሎ መጣ። ምግቡ እየተዘጋጀ ከዚያው አብሮ ቆየ። እኔ አላውቀውም። «ከዝች ልዥ ጋር በማይረባ ነገር ተጣልተን እባካችሁ ሽምግሉኝ አስታርቁኝ ቤቱን ልመስርት። ከሳኛለች በቤተዘመድ ይታይልኝና ክሱ እንዲዘጋና ኑሯችን እንድንመሰርት» ብሎ ሲያቀርብ ሽማግሌ መርጠን መስማማታቸውን ወረዳ ሂደው እንዲናገሩ ያደረግንበት ሁኔታ አለ። ሰዎቹን ጉንብስ

አዋርደን አስማምተን አብረን ላክናቸው። ለየብቻ መጥተው ልገሮቻቸውን አብረው ይዘው ተመለሱ። ከመገናኘት ፍቅር ይታደሳል። ይቅር መባባል ይመጣል እልሃለሁ።

*የመረጃ አቀባይ ሥም*፣ አባ አቸነፍ እንግዳ (አባ.2፣ቁ.12)

*ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን*፣ እ.ኢ.አ. 29/09/2004

1. ከዚህ ሌላ ተዝካር የሚባል አለ። ይኸ የሚወጣው ቤተሰብ በሆነለት ጊዜ ነው። ድግሱ በሬ ይታረዳል፣ ጠላ ይጠመቃል። ዘመድ ይጠራል። ማታ የሚመጣው እንግዳ ይሸኛል፣ ቄሶቹ በልተው ጠጥተው ሲፈቱ ያድራሉ። ማለዳ ላይ ያገኟትን ቅራሪ ቀማምሰው ቁርስም አድርገው ወደየቤታቸው ይሄዳሉ።

*ጥያቄ፣ ተስካር የሚወጣው ለምንድን ነው?*

3. አንድ ሰው ተዝካር ሳይወጣለት ከቀረ ቤተሰቡ ስለሚነወር በዛችም አነሰችም ተስካር ሳይወጣለት የሚቀር የለም። በዘፈኑም በምኑም ይሰደባል። ባገራችን የእናት አባቱን ተዝካር ያላወጣ የእሱ አይወጣለትም። ተዝካር ሳይወጣለት ሲቀር «እከሌ ልዥ አልወለደም ሳይፈታ ቀረ» ይባላል። ለዝና ነው።

### 1.4.4. ሞት በሥጋ ዝምድናና በማሕበራዊ ትስስር ላይ የሚስከትለው ውጤት የተገለጸባቸው ቃል-ግጥሞች

#### 1.4.4.1. የእናት ሞት በልጆች ላይ

1. በዚያም በዚያም ዘልቃ እናት ትጠራለች፣
   ና ብላ ነው እንጅ ሌላ ምን ትላለች።
2. መካን አለመኛ በኖረች ዘላለም፣
   ኧረ እናቴ እናቴ የሚላት ልጅ የለም።
3. ተንጫጩ ልጆቹ ያንጫጫባታቸው፣
   የእናት ገቢያ የለው እንዳንገዛላቸው።
4. እናቴ ደህና ሁኝ በቀስተ ዳመና፣
   እንግዲህ በምድር አትገኝምና።
5. እናትን ቀበሯት በነጠላ ሸማ፣

እራብ ይሸሽ ነበር ድምጿን እየሰማ፡፡

6. እናት ሞተች አሉ እናት የትኛይቱ፣

ከደረቷ ወተት ከእጅ ማር ያላቱ፡፡

7. ከቤት እቃሽ ሁሉ ገበታሽ ይድረሰኝ፣

እየፈተፈተ እንዳንቺ እንዲያጎርሰኝ፡፡

8. አንቺ ፍት ፍት  ፍት እኔ ጉርስ ጉርስ ጉርስ፣

ወዴት ትሄጃለሽ ወንፈሌን ሳልመልስ፡፡

9. እናቱ አፈር ሆና ካይኔ ገብታብኝ፣

እያደር እያደር ቆረቆረችኝ፡፡

10. ኧረ እማየ እማየ ይላሉ ልጆችሽ፣

ቀና ብለሽ እይ አይጨክን ልብሽ፡፡

11. ከቶ ለዚህ ነበር ልጁ መወለዱ፣

ንሱ አሳድጉልኝ ብሎ ለመሄዱ፡፡

12. ኧረ እናት ኧረ እናት ኧረ እናት ቻይቱ፣

13. እንደኪዳነምህረት ምህረት ለማኝቱ፤

የማይናገረው በላሽ ወየ መሬቱ፡፡

14. እናት አውድማናት የተለቀለቀ፣

ብትሰጠው ብተሰጠው አትልም አለቀ፡፡

15. የሞሰብ እንጀራ ዝንብ እየወረረው፣

ያነን ይበላዋል አየ እናት የሌለው፡፡

16.. የሰማይ አሞራ ወርደሽ ተናገሪ፣

እናት የሌለው ሰው የለውም መካሪ፡፡

17. እስኪ ልሂድና ሞሰብሽን ልዳሰው፣

ሳይጋግር አይሄድም ልጅ የወለደሰው፡፡

18.. ይብላኝ ለሞተ ሰው ልጅስ ያድጋል በጁ፣

እንደ አሮጌ ገሳ ወድቆ በየደጁ።

19. ታምሜ ተኝቼ ሆዴን ባማክረው፣

ትኩስ እንጀራ አለኝ እናት የጋገረው።

20. ኧረ እናት ስትሞት እንዲህም አልነበር፣

በስር ምንጣፍ ሆኖ እርሷን በላይ ነበር።

21. እናት አለሚቱ ካንች ከተለየሁ የበላሁት ምሣ፣

በከንቱ መሳሳት ጐን የማያነሣ።

22. እንኳን ስታበላ ቀዳ ስታለብስ፣

እናት አለም ሲሏት ታገባለች ነብስ።

23. እንዴት እናት ትሙት፣

እንዴት ወተት ትሙት፣

እንዴት ፍትፍት ትሙት ሌላ ሰው ይመስል፣

ቆርጣ የምትጥለው እራብ ካራ ሲስል።

24. እናት ከየት ውላ ከየትስ አደረች፣

እስከ ማታ ድረስ ከገበያው ነበረች።

25. እንሂድ እንጓዝ እንሂድ ምናኔ፣

እናት የሚሰራ ብናገኝ ሸማኔ።

26. እናትማ ስትሞት አብሮ ነው መሞት፣

እርግፍ እያረጉ ምስጥ እንዳይበላት።

27. እናት ደገላናት ዝሆን የማይጥሰው፣

የልጁን ገመና አትገልጠም ለሰው።

28. እናት አንድ ሆና ለሰው አስቸገረች፣

እንደ አጎት እንደ አክስት ሁለት ሶስት በሆነች።

29. በጠፍጣፋ ድንጋይ ከተዘጋ በሩ፣

እናት ወት ተገኝታ እንደ ወፍ ቢበሩ።

30. ጀንበር ትገኛለች ማታ ገብታ ጠዋት፣

እናት አትገኝም አፈር ከበላት፡፡

31. እናት አውድማ ናት የተለቀለቀ፣

ብትሰጠው ብትሰጠው አትልም አለቀ፡፡

32. እርጎውን ቅጅና ድቁስ ጨምሪበት፣

መቼም ያንች ነገር ይበቃል የለበት፡፡

33. እናት አንድ ባላ እናት ሁለት ባላ እናት ሶስት ባላ፣

የልጆቿን ቤት ጎደሎውን ሁሉ ሁልጊዜ እምትሞላ፡፡

34. እናትስ አትሙት ትኑር አጎንብሳ፣

እራት ታበላለች ከተኛ ቀስቅሳ፡፡

35. እናት ሞተች አሉኝ እናት የትኛይቱ፣

ከደረቷ ወተት የሚፈልቅባቱ፡፡

36. እንዴት ጥሩ ነበር የእናት ጎረቤት፣

ተበድሮ በልቶ የለኝም ማለት፡፡

37. የሚኖር በሆነ እናትን በጎታ፣

ቁንጥር እያረጉ የቸገረ ለታ፡፡

38. እናቴ ሞትሽብኝ ዋ በላሽ መሬቱ፣

እንደ ዋናተኛ ቀን አሻጋሪይቱ፡፡

39. አንጀቴን አንጀቴ ሲበላው አደረ፣

እናት የሌለው ልጅ እያንጎራጎረ፡፡

40. እናት የሌላችሁ ተነሱ ከጭሱ፣

ማን ይሰጣችኋል ጋግረው ሳይጨርሱ፡፡

41. እናት ሞተች አሉ እኔ ልሙትላት፣

የምትለው ለልጅ እሷን እየራባት፡፡

42. እራቤ በሆዴ በቅሎ ዘረዘረ፣

እናቴ ብትኖር ታጭደው ነበረ፡፡

43. የእናቴን ቀኝ እጇን ስቀሉት ከማገር፣

ልጆቿ ሲያለቅሱ እንዲወርድ ሲጋገር፡፡

44. ከእንግዲህስ ወዲያ መውለድ ይቅርብኝ፣

ያለ እናት መታረስ መቸም አያምርብኝ፡፡

45. አንች ሆነሽ ዋርካ እኛ ሆነን ወፍ፣

አሁን ምን አለበት ከጥላሽ ብናርፍ፡፡

46. እናት የለለው ልዥ ከደጃፍ ያመሻል፣

ጅብ ይበላውና ይፈረድብሻል፡፡

47. እናቴ መብራቱን አጠፋሽው ወይ?

ታጋሽ መብራቱን እናታለምየ አጠፋሽው ወይ?

ሳላሰናዳበት የቤቴን ጉዳይ፡፡

48. በትልቁ ሰጥታ በትልቁ ስትደግም፣

እጇ እማይሳሳባት አይኗ እማይገመግም፡፡

49. እንኳን ግባ ብላ ቀድታ ስታጠጣ፣

እንኳን ግባ ብላ በጇ ስታበላ በጇ ስታጎርስ፣

ቀድሞ መድሃኒት ናት በጇ ስትዳስስ፡፡

50. እሴት ልዥ መች አለሽ እሴት በኖረ፣

ማተብሽም ድሪሽም ከማገሩ ቀረ፡፡

51. እናታለም እየ እመጣልሻለሁ፣

የከፋኝን ሁላ አጫውትሻለሁ፡፡

52. እናታለም እየ እግዜሩን ለምነሽ ተመለሽልኝ፣

ከባዶው ባድማ ኸስሚዛው ነኝ፡፡

1.4.4.2. **የአባት ሞት በልጆች ላይ**

1. ከባልሽ ተጣልተሽ ዱላ ቢዋልብሽ፣

በሉ አባቴን ጥሩ ማለቱ ቀረብሽ፡፡

2. መብላቱም ይቅርብኝ አፈሩን ልብላው፣
   መጠጡም ይቅርብኝ ደሙን ልጠጣው፣
   ከደጃፍ ቁጭ ብለህ ድምጽህን ልስማው፡፡
3. አባት የለለው ልጅ ትል የወጋው ቀጋ፣
   ሁል ጊዜ ይኖራል ጉት እንደተወጋ፡፡
4. እስቲ ጠይቁልኝ ወንዙን ሳይሻገር፣
   እንዴት ብሎ ሄደ የልጆቹን ነገር፡፡
5. አደባባይ ውየ የሚዋሰኝ ባጣ፣
   ምድር ምድር አየሁ ቆፍሬ ላወጣ፡፡
6. ድንጋይ ቢወረውር ወረወርኩኝ ኩበት፣
   አባት የሌለው ሰው የለውም አንደበት፡፡
7. አባት እየሞተ ልጅ እየተተካ ይላልኝ ሰው ሆየ፣
   አገር ሽረኛ ነው ተቀማጭ ካላየ፡፡
   አባቴ ብቅ በል ከፈሰሱ ድረስ፣
   የከፋኝን ሁሉ ነግሬህ ልመለስ፡፡
8. አንጀቴን አንጀቴ ሲበላው አደረ፣
   አባት የሌለው ልጅ እያንጎራጎረ፡፡
9. ማነው የከፈነው ጣቱን ሳኩልን፣
   ልጆቹ ተጉላላን ጉርሻ ቀርቶብን፡፡
10. አባቴስ ሞተብኝ ልፍተል መቀነት፣
    ዋስና ጠበቃ የምገዛበት፡፡
11. ቢያለቅስ ቢተክን ምንም ቢከፋው፣
    ልጅ አድማጭ የለውም አባት ከሌለው፡፡
12. አባት ያለውማ ነገሩን ከተተው፣
    በስተኋላው ሆኖ እያመለከተው፡፡
13. ከጎረቤት ሀብታም የአባት ድሃ ይሻል፣

የሚሰጠው ቢያጣ ሲመክር ያመሻል፡፡

14. ሲይዙት ቀላል ነው አባትና ብር፣
 እየቆየ እኮ ነው የሚቆረቁር፡፡
15. ከአደባባይ ቆሜ ይለኛል ድንግርግር፣
 ለካስ አባት ኖሯል የልብ የሚያናግር፡፡
16. አባት የሌለው ሰው ንብ የሌለው ቀፎ፣
 ዘላለም ይኖራል ውቃቢው ተገፎ፡፡
17. እቴ የናቴ ልጅ ልንገርሽ መላውን፣
 ባል ገረድ ያደርጋል አባት የሌለውን፡፡
18. እንኳን ወየ ማለት አላውቅም መናገር፣
 ቢጨንቀኝ ነው እንጂ ያባትየ ነገር፡፡
19. የዛሬው በጋ አልፎ ለሚመጣው በጋ፣
 ልጆችህ በሰው ቤት ሚስትህ በሰው አልጋ፡፡
20. ያጅሬ ዘመዶች ልጅም ይሁን እንጃ፣ ወንድም ይሁን እንጃ እህትም ትሁን እንጃ፣
 ሲያለቅሱ አረፈዱ ከበጉ ማረጃ፡፡
21. አባቴም አልልህ ጠላቴ ጠላቴ፣

ጥለኸኝ የሄድከው ሳይጠና ጉልበቴ፡፡

22. እረግ አባትየ አንደዜ ተነሳ፣
 ጥቃት መጥቶ መጥቶ ከደጃፌ ቆሟል፣
 እስቲ ተነሳና አነጋግርልኝ፣
 እስትመጣ ድረስ ሰው እንዳይደፍረኝ፡፡

#### 1.4.4.3. የልጅ ሞት በወላጆች ላይ

1. ከቶ ለምንድነው ልጅ አንጀት መብላቱ፣
 ባድማው ሁኖ አይደል የበቀለበቱ፡፡

2. ኧረ ቀስ ኧረ ቀሰ ምን ያስቸኩልሀል፣
   እንዳይመሽብህም ማልደህ ተነስተሃል፡፡
3. አንተ ላይ ዳመና አንተ ላይ ሰማይ፣
   እናት ተቀምጦ ልጅ ይሞታል ወይ?
4. ባለጌው ባለጌው እየተወለደ፣
   እናትና አባቱን እየጣለ ሄደ፡፡
5. አስፈረድኩኝ ስትል ይፈረድብሃል፣
   አሮጌ እናትህን ጅብ ይበላብሀል፡፡
6. የዚያን ሚች ላሞች በመድን ሽጧቸው፣
   ልጅ አላደረሰ ማልዶ የሚያልባቸው፡፡
7. የአጅሬማ እሬሳ በጉድጓዱ ሞላ፣
   የእናቱን አባቱን አንጀት እየበላ፡፡
8. ጫማውን ልብሱን ብሎ እንደ ማስቸገር፣
   ሰኔል ለብሳ ሄደች አወይ የልጅ ነገር፡፡
9. ምን ያል ክፉ ልጅ ነው ለሥራው ምቀኛ፣
   እንጀራውን ከአፈር ጎዝጉዞ የተኛ፡፡
10. እንኳንስ ለአንድኛው ከቀየው ሲጠፉ፣
    ልጅ አንጀት ይበላል አንገቱን ሲደፉ፡፡
11. ልጅ አለም ልጅ አለም ልጅ አለም ነበረ፣
    ላሳደገማ ሰው ወልዶ ላልቀበረ፡፡
12. እንዴት ጥሩ ነበር ይህ ልጅ የሚሉቱ፣
    አንዱን ወደ አተላው አንዱን ወደ ከብቱ፡፡
13. ሁል ጊዜ በገረድ እንደ ዘመናይ፣
    ወልዶ ማዘዝማ ቀርቶ የለም ወይ፡፡
14. አርቀው ቢቀብሩት መች ይቀራል ልጅ፣
    ተመልሶ መጥቶ ሆድ ይበላል እንጂ፡፡

15.ወይም አልተሰደድኩ ወይ አልሞትኩላቸው፣
ለባልንጀሮቼ ምቀኛ ሆንኳቸው፡፡
16.ክብት ያላችሁ ሰዎች ሰብስቡ እባካችሁ፣
እንደኔ  ልጅ በቅሎ እንዳይጠፋባችሁ፡፡
17.ልጅ አይደል ይላሉ እንደ ቀላል እቃ፣
ልጅ አድጎ አይደለም ወይ የሚሆን ጠበቃ፡፡
18.እምቢ አለኝ ምጣዱ እያነኳኮረ፣
የልጅ እንጨት ለምዶ የተሰባበረ፡፡
19.በኋላ ሂዱ እንጂ ለምነው በፊቱ፣
እንደ ልጅነትህ እንደናትነቱ፡፡
20.እስቲ ደብተሮችህ እስቲ እርሳሶችህ፣
እስቲ ደብተሮችህ እስቲ መጻፎችህ፣
አሳይብሃለሁ ለባልንጀሮችህ፡፡
21.ወትሮ ነበር እንጂ አባት አለመሆን፣
ቀድሞ ነበር እንጂ እናት አለመሆን፣
ሲርበው ያስለቅሳል እንኳን አፈር ሲሆን፡፡
22.በል ተሎ ተሎ ህድ ግዜው መሽቶብሃል፣
እንዲህ ያል መቀጨት ምን ያደርግልሃል፡፡
23.ቤሳ ምላጭ ይዘህ ከሆዴ ገብተህ፣

እረ ተው አንጀቴን ትቆርጠኛለህ፡፡

1.4.4.4.**የእህት ሞት በወንድምና እህት ላይ**

1. አንች ፍትፍት ፍትፍት እኔ ጉርስ ጉርስ፣
   ወዴት ትሄጃለሽ ብድሬን ሳልመልስ፡፡
2. እህቴ የናቴ ልጅ ቆይኝ ከመንገዱ፣
   የራበኝ ድሃ ነኝ እያሉሽ ይሄዱ፡፡
3. በማጀት ግቢና እስኪ በይ ጉድ ጉድ፣

የለሽም መሰለኝ አየ ጉድ አየ ጉድ።

4. እባክሽ እህቴ ራቤን ተቆጭው፣
   አንችን ይፈራሻል ስትገላምጭው።
5. እንግዲህ አልመጣም እግሬን አያደርሰኝ፣
   ዱሮም ሆዴ ነበር የሚያመላልሰኝ።
6. ና ብላ ተብዬ ስጀነን ስቆጣ፣
   ና ጠጣ ተብየ ስጀነን ስቆጣ፣
   እንግዲህ አርፍ የለ የሚጠራኝ ሳጣ።
7. ኮትኩተሽ ኮትኩተሽ እንደ በርበሬ ፍል፣
   ወዴት ትሄጃለሽ ብድርሽን ሳልከፍል።
8. ለላይኛው ጌታ አጋፋሪ ማነው?
   አንዲት ናት እህቴ ተውልኝ አንድ ሰው።
9. እቴ የእናቴ ልጅ የሰጠሽኝ ጠላ፣
   ምን ቅጠል አለበት አንጀት የሚበላ።
10. አየ ጉድ እህቴ ሞሰቧ ጎድጓዳ፣
    የራበው ታውቃለች ጎኑ የተጎዳ።
11. እራቡ በሆዴ ጎጆ ሰራ እንደሰው፣
    ይህን ያለ እህቴ ማነው የሚያፈርሰው።
12. ምነው ባፋፉ ላይ ምነው በመሬቱ፣
    አይሳሳም ወይ ቆንጆ ለሰራ አካላቱ።
13. ተዋት አትቅበሯት ጣሏት ከመንገዱ፣
    የማናት ሙሽራ እያሏት ይሂዱ።

### 1.4.4.5.የወንድም ሞት በእህትና ወንድም ላይ

1. ወንድም ተገንዞ ሲወጣ ተራራ፣
   የዚህ ጊዜ አይደለ ጠላት የሚኮራ።
2. ባቅፈው ደነዘዘኝ ምላሴን እንደእግር፣

ለካስ ወንድም ኖሯል የልብ የሚያናግር፡፡

3. አንጎራጉሩብኝ እንጉርጉሮ አልወድም፣

በድንገት የወጣ አለኝና ወንድም፡፡

4. እስኪ ሰፌድ ስጡኝ አፈሩን ላንፍሰው፣

ምሁሩ ወንድሜ ያነን ሁሉ ቀለም ከምን አደረሰው?

5. እህልም ይበላል ባቄላ መሳይ፣

ልብስም ይለበሳል ነጠላ መሳይ፣

እኔስ የምቀና ወንድም ያለው ሳይ፡፡

6. ኧረ ወንድም አለም ድረስ ከኃላየ፣

አካሌ ሳይቆስል ሳይደማ ገላየ፡፡

7. ወንድም አልኩሽ እንጂ ሲወድቁ የሚወድቅ ሲደሙ እሚደማ፣

ባድማ መቸ አጣሁ እየበላ የሚያማ፡፡

8. እንኳን ባለ ሱሪ ባለ ጋሻ ወንድም፣

ለሴት አንድ እንጀራ ቢጠፋት አትወድም፡፡

9. በየስሚዛው ስር ሽጉጦ ጉልበቱን፣

የማን ነሽ ዋስ የለሽ አስባላት እህቱን፡፡

10. አንት የወንድም ዋሾ አንተ ቃል አባይ፣

አብረን እንከርማለን አላልከኝም ወይ፡፡

11. እንባን ጠለል አርጎ አይንን ቅርዝዝ አርጎ ቢነግሩት ለወንድም፣

አይጨክንም ነበር በውድም በግድም፡፡

12. ጥቃት ባላንጋራ ሊያወጣው ዐይኔን፣

አንተ ጮራ ሁነህ መከልከያ ሁን፡፡

13. መቼ ለዚህ በቅቶ መቼውን ሊረሳ፣

ጠላት መጣ ቢሉት አሁን በተነሳ፡፡

14. ጀግና ነኝ አላልከኝ የታል ጀግንነቱ?

እንግዲያ ክር አይደል የታሰርክበቱ፡፡

15. ሁለት ተናግሬ ሶስተኛ ሳልደግም፣
‹‹ተይ ነገር አበዛሽ›› ይላል የሰው ወንድም፡፡
16. ትልቅ ፈረስ ታስሮ ከቤቱ ድምድም፣
ባጭር በቅሎ ሄደ የኔማ ወንድም፡፡
17. ትናንትና ማታ ሰከክ ብየ ሞቼ፣

ሁለት ወንድማማች ሲጫወቱ አይቼ፡፡
18. ሁለት ወንድማማች ባንድ ይወለድና፣
አንዱ ይሞትና ሲቀር አንዱ ብቻ፣
ይሆናል ገበጣ ያገር መጫዎቻ፡፡
19. እረ እነ እገሌ አየ ወንድሞቼ መታሰር ነው እንጂ ከንድን አብርትቶ፣
ተውሶ እሚያስፈታ ወንድም ወት ተገንቶ፡፡

20. ሰኞ ስትታሰር ማክሰኞ እሚደርሰው፣
አንድ ሰው ሞተ ብሎ ይለኛል ሰው፡፡
21. ጥቃት መቶ መቶ ከደጃፌ ቁሟል፣
አባ ነብሩ ወንዱ እንቅልፉን ተኝቷል፡፡
ተነሳ ወንድሜ አንገራግርልኝ፣
እስክመጣ ድረስ ሰው እንዳይደፍረኝ፡፡

**1.4.4.6.የሽማግሌ ሞት በማሕበረሰቡ ላይ**

1. ያነን ማዶ ዋርካ ማነው የቆረጠው?
እንግዲህ እሾህ ነው የሚያቆጠቁጠው፡፡
2. አገሬስ ዘንድሮ ጉዳ ሁናአል ላሙ፣
ወዴት ሂዶ ይሆን ያ ቀንዳም ቀንዳሙ፡፡
3. ያገሬ መኳኳንንት ቀንድ ቀንዱ ወለቀ፣
ጎዳ ጎዳው ቀርቶ ተደካድኮ አለቀ፡፡

4. ያነን ትልቅ ዋርካ ማነው የቆረጠው ሥሩን ምሶ ምሶ፣
   የሰው የለሽ አገር ለማለት ነው እጅ ህዝብን አስለቅሶ፡፡
5. አገራችን እስቴ አገራችን ቆማ አንዳቤት በሙሉ ጉዳ ሆኗል ላሙ፣
   ወደ የት ደረሰ ያቀንዳም ቀንዳሙ፡፡
6. ታላላቁ ሞተ ያገር ከለላው፣
   ሲቸግር የሚሰጥ ሲርብ የሚያበላው፡፡
7. እዘኑ እባካችሁ አልቅሱ እባካችሁ፣
   ትልቅ ሰው ካገሩ ሲጠፋ እያያችሁ፡፡
8. ትላልቁ አለቀ ዋርካና ባንባው፣
   ቀረ ኩሽሽሌው ሲያልፉ እሚወጋው፡፡
9. ሰው ሲጣላ አስታራቂ ማነው?
   እንግዲህ ወዲያ ብላ ተባላ ነው፡፡

1.4.4.7.የጀግና ሞት በማሕበረሰቡ ላይ

1. እንዴት ጀግና ይሙት በእንቢያ የሚደፋ፣
   ባልቴት ተቀምጦ ወለል የሚያለፋ፡፡
2. ደህና ጎበዝ ሲሞት ይስቃል ጅሉ ሰው፣
   የታገተ ጥጃ የማያስመልሰው፡፡
3. ፀሐይም ጠለቀች ጨረቃን ተክታ፣
   አሁን ምን ይሆናል ያለ ጀግና ቦታ፡፡
4. ደህና ጉበዝና የጉመን ዘር ፍሬ ሁለቱ አንድ ናቸው፣
   ዘራቸው አይጠፋም ከዚያው ከቦታቸው፡፡
5. አገሬ ስማዳን ነፋስ ወዘወዘው፣
   ለካ አጅሬ ኖሯል ገድቦ የያዘው፡፡
6. ደህና ጎበዝ ሲሞት ይስቃል ሞኝ ሰው፣
   አገሩ ሲወረር ደንበሩን ሲያፈርሰው፡፡

7. የሚያጉረመርመው እንደ አራስ ነብር፣

   ወርዶ የሚጋርደው ከጫካው ከዱር፣

   አየ ጉድ አጅሬን በላው ወይ አፈር፡፡

8. ጀግና ጎበዝ ሲሞት ምንድን ነው ማርከሻው፣

   አያድርስ ነው እንጅ እስከመጨረሻው፡፡

9. አፋፉ ዘልቂ ወደ ታች ብጣራ ሴቶቹ ወይ አሉኝ፣

   ሴቶቹ ወይ አሉኝ ወምዶቹ በሙሉ አልቀዋል መሰለኝ፡፡

10. እረ እንኳን ዘመተ የልቡ ደረሰ፣
    ጉንፋንም ይገላል ቀኑ ከደረሰ፡፡
11. ሲሄድ በፊታቸው ምናሉ ልጆቹ፣

    እኛ እንፈራው ነበር እንኳን ጠላቶቹ፡፡

## 5. በለቅሶ ቃል-ግጥሞች ዘር የተመደቡ ተጨማሪ አባሪዎች

### 5.1.ወየታ የወል

1. ተቀማጭ ገምጋሚ ቋሚ ተገምጋሚ፣

   ቆይ አገኝሻለሁ ከመሀል ስትቆሚ፡፡

2. አባቱ፣ እናቱ፣ ወንድሙ፣ እህቱ ለሞተ አላቃሹ ነኝ፣

   እንደኔ እንደ ራሴ እየመሰለኝ፡፡

3. እናላቅሰው እንጂ እገሌን እናላቅሰው በተራ በተራ፣

   ያገሩን አላቃሽ ሲያገኘው መከራ፡፡

4. በዳር በዳር ብኸድ እግሬን እግሬን ጎረበጠው፣

   እስቲ ለእገሌ ስል መሃሉን ልርገጠው፡፡

5. እባካችሁ ሰዎች ይህንን መከራ እንተጋገዘው፣

   አዙሮ ይጥላል ብቻውን ለያዘው፡፡

6. አልቅሱ እንላቀስ ለቅሶ ወንፊል ነው፣

   ዛሬ የኛ ቢሆን ነገ የናንተ ነው፡፡

7. አልቅሱ እናልቅስ ነግ ለኔ ብላችሁ፣
   በኔ የደረሰ አይድረስባችሁ።
8. እኔ ልብስ ቢሉኝ እኔ ልብስ ብዬ፣
   ለሰው ሰው ነው ልብሱ እረ እናንተ ሆዬ።
9. ማዘን ለለቅሶ ነው መርዳት ለመከራ፣
   እንዲህ እየዞረ ለሚያደርሰው ተራ።
10. ያያ እንቶኔ ቤቱን አሞራ አፈራረሰው፣

    አይገለግልም ወይ አብሮ የበላ ሰው።
11. እንኳን አበላኸው እንኳን አጠጣኸው አልከው ግባግባ፣
    መፈታቱ አይቀርም ቤትና ገበያ።
12. ከበላሁ ከጠጣሁ ሀጃየ ከሞላ፣
    ምን የእናት ልጅ ቢሆን ስጋው አይበላ።
13. በል እንባየ ውረድ ከመሬት ድረስ፣
    ይሁዳን መሆን ነው በልቶ አለማልቀስ።
14. እግሬ ቢንቀጠቀጥ አይኔ ሰው ቢፈራ፣
    እንዴት አደርጋለሁ ዝልሴ ነውና ጮማየ ነውና።
15. መላቀስ ነው እንጅ የመከራለት፣
    የሚበላ አይጠፋም ቁመው ከዋሉት።
16. እናንተ ገናኞች እጁን አትሰሩት እኔ እዋሰዋለሁ፣
    ፍትፍቱን ጮማውን እየፈተፈተ በልቸበታለሁ።
17. እኔ ላልቅስ እንጂ ማን ያልቅስ እላለሁ፣
    መደብ ተደግፌ የጠጣሁት ሳለሁ።
18. እንደ እጀራው ቢሆን እንደ መፈትፈቱ፣
    እንደ ጠላው ቢሆን እንደ መጠጣቱ፣
    እገባ ነበረ ከገባህበቱ።

19. የጮማ የፍትፍቱን ቤት አሞራ አፈረሰው፣
አይከለክልምወይ አብሮ የበላ ሰው፡፡
20. ስጡኝ እሱን ዋንጫ እንባ እሞላዋለሁ፣
በሞቴ እየተባልኩ ጠጥቸበታለሁ፡፡
21. መልካም ተለቀሰ እሱም ተቀበረ፣
የዚያ ወጣት ወገን መብላት መጠጣቱ መጫወቱ ቀረ፡፡
22. በዚያ ጥቁር ዋንጫ ምነው ባልጠጣሁኝ፣
እየገነፈለ ባይኔ ወረደብኝ፡፡
23. ጮማየ ጮማየ ይላል ጎረቤቱ፣
ዝልሌ ዝልሌ ይላል ጎረቤቱ፣
ሥጋየ ሥጋየ ይላል ጎረቤቱ፣
በሥጋ ነው ወይ የተሰራ ቤቱ፡፡
24. በል እንባየ ውረድ በዋንጫው ሙላልኝ በጠጣሁበቱ፣
እኔም ነገ እነዳንተ ለምሆነው ከንቱ፡፡
25. ላይለቀስ ነወይ ወትሮ ላበላ ሰው፣
ላይለቀስ ነወይ ወትሮ ላጠጣ ሰው፣
እጁ ወንፊት ሆኖ ሰጥቶ ለጨረሰው፡፡
26. የሰው ጥሩ ጠላ ጠጥቼ ጠጥቼ ወት እረሳዋለሁ፣
በራሴ አዘንብየ በዓይኔ እቀዳዋለሁ፡፡
27. አላለቅስም ብየ ብቀር ወደ ኋላ፣
ገፋ ገፋ አረገኝ የጠጣሁት ጠላ፡፡
28. ጠላሽ ማሽላ ነው እንጀራሽ ነጭ ጤፍ ሞሰብሽ ጎድጓዳ፣
ዋንጫሽ ባለ ጎሚ ዋንጫሽ ባለ ጎሚ፣
አገሩ ምን አለ አንች ስትታሚ፡፡
29. የነቅቤው መንደር የእነርጎየው መንደር ሁለተዜ ጠፋኝ፣

ወትሮም እየሰከርኩ ዛሬም እየከፋኝ፡፡

30. ካንተ ቤት ባልበላ ከእህትህ ከእህትህ በልቼ፣

ልርገብገበው እንጂ ከመሃል ገብቼ፡፡

31. ቀዘቀዘ ቤቱ ሰፊው አዳራሹ፣

ያሳለፍንበቱ ሠርግና ምላሹ፡፡

32. የሰኔው ገበሬ የሀምሌው ጎልጓይ፣

ጅራፍክን ጠቅለህ መሄድህ ነወይ?

33. በሮችህ ተጠምደው ከበሰላው ላይ፣

አንዱን ዘር ጥለህው መሄድህ ነው ወይ?

34. ያ የሰኔው አራሽ የሃምሌው ጕልጓይ፣

እህሉን ሳትሸክፍ መሄድህ ነወይ?

35. የድሀ ኑሮና የባቄላ መጅ፣

ክልትምትም ክልትምትም ክልትምትም ነው እንጅ፡፡

36. አሁን ምን ሊሆን ነው ገንዘብ መያዝ በእጅ፣

የዳቢሎስ እራት ለመሆን ነው እንጂ፡፡

37. የተራበን ሁሉ የሚያበላውን፣

አፈር በላው አሉ አባ ባሕርን፡፡

38. አልቅሱ እናልቅስ ዛሬስ ድሀ ሙቷል፣

ሁልግዜ ያበላን ያጠጣ ይሞታል፡፡

39. የኒያ ላሞች ጌታ የኒያ በጕች ጌታ፣

እንዴት ሽርተት ሽርተት ከአፈር ላይ ምኝታ፡፡

40. ምነው በቆዩልን ካባ እንደለበሱ፣

ምነው በቆዩልን ጋቢ እንደለበሱ፣

ያገሬን መኳንንት ፊጃቸው ቀሚሱ፡፡

41. ምን አደርግሃለሁ እድልህ ከሆነ፣

እንደ ኑሮህ ሁሉ ለቅሶህ መነመነ፡፡

42. እባክሽ ቀኒቱ ቶሎ ቶሎ እለፊ፣

አግኝቶ ያጣ ሰው ይመስላል ቀጣፊ፡፡

43. የሰኞው ባለ ጠጅ የማክሰኞ ድሃ፣

ታሞ የተኛ ዕለት አላገኝም ውሃ፡፡

44. ለምን ትኴዳለህ መስለህ የተቆጣ፣

ነውር መሰለህ ወይ ያገኘ ሰው ቢያጣ፡፡

45. ማልቀስ ለድሃ ነው ማልቀስ ለምስኪን ነው፣

ሀብታምማ ሰሲሞት አልቃሹ ብዙ ነው፡፡

46. መልካም ጥሩ ጠላ የዋለ ያደረ፣

ከናባ እገሌ ቤት ይጠመቅ ነበረ፡፡

47. ማግኘትና ማጣት መቱነን ቁሞ፣

ማጣት አሳዘነኝ የሚያሳፍረው፡፡

48. ጸሀይ በስተምስራቅ ስትወጣ እያያችሁ፣

ሰዎች አትሞኙ ቀን አለ ብላችሁ፡፡

49. በስምንተኛው ሺህ እዘኑ በጠና፣

ነፍስ አሰኝቶ ሊፈጀን ነውና፡፡

50. እናንተ ቅበሩ እኛም እንቀብራለን፣

ቀን የወጣለታ እናስለቅሳለን፡፡

51. ምን ያለ ጊዜ ነው ውቃቢ የራቀው፣

እገሌ አቶ እገሌን ከአፈር ደባለቀው፡፡

52. የዘንድሮው ወራት የሳት የገለባ፣

የታመመው አይድን የወጣው አይገባ፡፡

53. ጊዜ መሀንዲስ ነው ያድሳል ያፈርሳል፣

አንዱ ሲያሸበርቅ አንዱ አፈር ይለብሳል፡፡

54. ጊዜው ነው መሰለኝ ከፍቶ የመረረ፣
ደጅ ወጥቶ መመለስ ታሞ መዳን ቀረ።

55. የዛሬ ዘመን ልጅ የገባነው እዳ፣
ለቅሶ ወንፊል ሆነ እንደ ጤፍ አጨዳ።

56. እኩሉም ይስቃል እኩሉም ያለቅሳል፣
ዓለም ልትቀበር ጉድጓዱ ተምሷል።

57. ትናንት ጦም ገደፍኩኝ እንጀራ ባዋዜ፣
እንዲህ ቶሎ ብሎ ለሚደርሰው ጊዜ።

58. እሱማ ምን ይበል እኛ ቅጥ ብናጣ፣
የስምንተኛው ሺ በቀጠሮው መጣ።

59. ይህ ስምንተኛው ሺ ምንጊዜ ደረሰ፣
እየጎሼ ያድራል እየደፈረሰ።

60. ወትሮ ነበር እንጅ ሰው አልሆንም ማለት፣
አዳምና ሔዋን የተፈጠሩለት።

61. አየ ጉድ አየ ጉድ የዚህ አለም ነገር፣
ትንሽ ሳይኖርበት ወደ አፈር መቀየር።

62. እራሴን ብላጨው እንጼት አማረብኝ፣
ሰው ሆኖ መፈጠር ምነው በቀረብኝ።

63. የኔማ ዘመዶች ፀጉራቸው ማማሩ፣
ወዲያው ለመቆረጥ ምነው ባልተሰሩ።

64. ምነው ቀርቶ ቢሆን ሰው ሆኖ መፈጠር፣
ተመልሶ ጭቃ አፈር መሆን ላይቀር።

65. ሰው መሆን ሰው መሆን እኔስ አሰለቸኝ፣
ኸላይ ቤት አልሰራሁ ከታይ አልተመቸኝ።

66. በሬው ደንበር አይግጥ አፉ ሰው አይነካ፣

ኧረግ አቶ እከሌ ሙተህን ነው ለካ።

67. ጅሉ ሰው ሞኙ ሰው ይጣላል ከመንጋው፣

በመከራው ሌሊት አብሮ ከሚያነጋው።

68. ቁም ነገር ቢያበዛ ቢወድ ዝምታ፣

ያውቅበት ነበረ ሳቅና ጭዋታ።

69. አስረዋት ነው መሰል በቁቻ ገመድ፣

መቸ ትቀር ነበረ በእርሷ ሰው መውደድ።

70. ክፋ ሰው አይሞትም ተተክሎ እንደዋንዛ፣

ብሩክ ሰው አይቆይም ሠላምታ እያበዛ።

71. እንዲህ እንደዋዛ ለሚቀረው ሀገር፣

ሰው ከዘመዱ ጋር ክፉ መነጋገር።

72. የነገረ ሰሪ የለውም ወረታ፣

በሰማይ ኩነኔ በምድር ሽልታ።

73. ምድሩን ምድር በላው ትንሽ እህቱን፣

ይቅር መንተግዚሀር የማታውቀውን።

74. እንዳማረ ኸደ እንደ ለሰለሰ፣

ክፉ ሲናገሩት በጎ እየመለሰ።

75. እስቲ ጠይቁልኝ ወነዝዙን ሳትሻገር ጎረቤቶቿን፣

አንድ ቀን ክፉ ቃል ተናግራ እንደሆን።

76. አንተም ደህና ሰው ነህ ከደህና ያድርስህ፣

አይደለህ የእግት ከብት በዋስ አልመልስህ።

77. አታልቃሻ ይለኛል ያልተባሰ ሰው፣

አንጀቱ አይደለም ወይ የተበጠሰው።

78. ሣልበላ ሳልጠጣ ብሎ ከማለት፣

ዝም ብሎ ማልቀስ ነው ካገር ሰው ሲሞት።

79. እናላቅሰው እንጂ በተራ በተራ፣
ቢጐዳ አይደለም ወይ ማልደ የተጣራ፡፡

80. እንላቀስ እንጂ የባሰው ለባሰው፣
ያልባሰው ሰውማ ሳቁም አያደርሰው፡፡

81. ሲታረዝ አልብሶ ሲጠማ አጠጥቶ ሲራብ ላበላ ሰው፣
ተለይቶ ሲሄድ አያስለቅስም ወይ እንባ እንዴት ይነሰው፡፡

82. እንባም ጉዳይ ነው ወይ በፊት በፊት የሚፈሰው፣
አይገኝም እንጂ አዝኖ እሚመልሰው፡፡

83. አለቅሳለሁ እንጂ ዋይ ለልስ ዋይ ለልስ፣
ሲጀምር ያለቅሳል እንኳን ሰው ሲጨርስ፡፡

84. ኸረ አያ እገሌ አለቅስልሃለሁ ያሉትን ይበሉ፣
ሀስጋ ዝምድና ሆድ ይበልጣል አሉ፡፡

85. አንተ ያጅሬ ልዥ ልርዳህ በወየታ ልርዳህ በምላሴ፣
አባት እንዳልሰጥህ የለኝም ለራሴ፡፡

86. ሸንጎ መሀል ሲቀርብ እንደበተ መልካም፣
አሸንፎ ይወጣል ጥቃትን አያውቅም፡፡

87. ገንቦው አለቀሰ ወደ ማጀት ዙሮ፣
እንዳንች ያል እመቤት አላገኝም ብሎ፡፡

88. እስቲ ጭርቆስ ልሂድ የኔ ገላው ደስታ ቃልህ ወት ደረሰ፣
ያ በላቸው ቢያድጌ ቃልህ ወት ደረሰ፣
ሰላምኮ ልምጣ የኔ አያሌው ነጋሽ ቃልህ ወት ደረሰ፣
ያ መኮንን ቢያድጌ ቃለህ ወት ደረሰ፣
ያ ሰብስብ መኮንን ቃልህ ወት ደረሰ፣
ምስጋናው ካሳሁን ቃልህ ወት ደረሰ፣
ቀደም አርጎ አይደለ አፈር የለበሰ፣

89. አወይ እገሌ ጠጉርህ ይታየኛል ጥርስህ ይታየኛል፣
እንደነበርክ አርጎ ማን ይሰራልኛል፡፡

90. አጅሬን ሳነሳው ሆዴ ይላወሳል፣
እንዲህ ስል እንዲህ ስል የኔም ቀን ይደርሳል፡፡
91. ኸረ ተው ታረቁ ኸረ ተፋቀሩ፣
ወደገነት መግቢያው እንዲከፈት በሩ፡፡
92. ቢያለቅሱት እንባ ነው፣
ቢጠጡትም ደም ነው፣
ከቶ ወዳጅ ሲሞት መለያው ምን ድነው?
93. እስቲ ልነሳና አገሩን ልወሰው፣
ከሁሉም ከሁሉም ጥቃት ክፉ ሰው ነው፡፡
94. ከጭራ ይቀጥናል የሲኦል መንገዱ፣
ከዚህ ተለቃልቆ ታጥበውት ካልሄዱ፡፡
95. መቆም አይቀረንም ከስላሴ ፊት፣
መንገዱን ሳናበጅ ሣንሰራ ቤት፡፡
96. የላይኛው መንደር ተራማጅ ነው አሉ፣
የመጣልን የለም ከሰደድነው ሁሉ፡፡
97. ምድር ሳንቃ ሁኖ የሚከፈት ቢሆን፣
አይቻች በመጣሁ ተሽሏት እንደሆን፡፡
98. ከበተስኪያን ጓሮ መሆንሽን አውቃለሁ፣
የሙት ወዳጅ የለው ዝም ብየሽ አልፋለሁ፡፡
99. እስከምንገናኝ በማያልፍ ቤታችን፣
እረፍቱን ይስጠዎት ቸሩ ፈጣሪችን፡፡
100. እልክልሀለሁ ለጎፈሬህ ሚዶ፣
አልበላው እንደሆን አፈሩ ተንዶ፡፡
101. አሳር ነው መከራ የላይ ቤት መንገዱ፣
ከዚህ ተለቃልቀው ታጥበውት ካልሄዱ፡፡

102. አፈር ላፈር ሄደሽ መሬት ለመሬት፣
ከከሲ.ታ ጋራ ሁኚ ጎረቤት፡፡

103. ከፍ በይ ወደ ላይ ወደሰገነቱ፣
የዚህ ዓለም ኑሮ ቢቀር ምናባቱ፡፡

104. ኸረ እነ እገሌ ከማርገጃው ሁነን እየጠራናቸው፣
አቤትም አላሉ አፈሩ በልቷቸው፡፡

105. አንተ በጉልበትህ ልኸር አሳድግበት ዘመድ ጥቀምበት፣
አፈርና ድንጋ አትሸከምበት፡፡

106. ያሁን ጊዜ ወጣት እድሜው አጭር ነው፣
ገና በእሸቱ ነው የሚታጨደው፣
ይህንን እያዩ አያዝነም ወይ ሰው፡፡

107. ገና ሳያፈራ ወጣት ከታጨደ፣
አዬ ጉድ የሰው ዘር እየጠፋ ሄደ፡፡

108. ዝናብ ዘነቦ፣ዘንቦ ሰማዬ ሳይጠራ፣
ቡቃያው አረረ ገና ሳያፈራ፡፡

109. ምን ዝናብ ቢዘንብ ቡቃያው ቢያምር፣
እንደ አበባ እኮ ነው አሮ የሚቀር፡፡

110. እንደዚህ ላለው ነው ማልቀስ የሚገባ፣
እወጣ እወጣ ሲል ጮርቃው ሲቀነባ፡፡

111. አየ ጉድ ያ ወጣት የወፎች አባት፣
እንደ ተልባ አበባ የቀረ በጧት፡፡

112. ምን ያለ ጉበዝ ነው መንገድ ያላወቀ፣
ገና ሲንጠለጠል ሲወጣ ወደቀ፡፡

113. ሞቱንስ ሙተው ከማን ትበልጣለህ፣
ባጭር አቀራርህ ታሳዝነኝአለህ፡፡

ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADDIS ABABA, ETHIOPIA

114. ሞትማ ብትሞት ከማን ትበልጣለህ፣

እንዴው ለልጆችህ ባጭር ለቀረኸው ታሳዝነኛለህ።

115. አየ እከሌ እኔማ አድርጌህ የዘላለም ኗሪ፣

ለካስ ብርሌ ነህ ተሎ ተሰባሪ።

116. ወንዶችም እንሂድ ሴቶችም እንውጣ፣

ከዚያው ቀሪ ሰው ነው ሸኝተን እንምጣ።

117. የሞተ ሰው ሳለ የሚበሰብሰው፣

ምን ያስቸኩለዋል ቀብሮ እሚመለሰው።

118. ማዘን ለሞተ ሰው ማልቀስ ለሞተ ሰው፣

እስከወዲያው ድረስ ለማይመለሰው።

119. ደሞ ለንባው ነው ወይ በፊት በፊት ለሚፈሰው፣
አይገኝም እንጂ እንዳንተ ያለ ሰው።

120. እኔስ ከሰወቹ ቦታው አሳዘነኝ፣

ያሳማ መዋያ ሲሆን ነው መሰለኝ።

121. ከኛውስ ባድማ ሙጃ ከወረሰው፣

እንዴት ተፈልጐ ይጠፍል አንድ ሰው።

122. አሁን ምን ያረጋል የሰው አገር ነጭ፣

ጉርስ ጉርስ  አርጎ ወደ አገር ነው እንጅ።

123. አፈር አበድሩን በቁና ሰፍራችሁ፣

አገሩ ሲገባ ይመልስላችሁ።

124. ኧረ ያሳዝናል በጣም ያሳዝናል፣

ሰውየው ከሞተ ቦታው ምን ይሆናል።

125. የአንበሳውን ቦታ አሻግሬ ባየው፣

ድንጋይ ብቻ ቀርቷል የማይናገረው።

126. ምን ያደርግልሃል የሰው አገር ጠጅ፣

ምን ያደርግልሻል የሰው አገር ጠጅ፣

ቅምስ ቅምስ አርጎ ወደአገር ነው እንጂ።

127. ኑሮ በሰው አገር ሞት ባገር ይደምቃል፣

ያም መቶ ያም መቶ ከአንገት ላይ ይወድቃል።

128. አንተ በሰው አገር አገርክን ለሌላ፣

ከሰው የበለጠ እንጀራ ላትበላ።

129. ውሸት አይምሰልህ የልግም የልግም፣

ተው አገርክን ሳግባህ ሳዘግም ሳዘግም።

130. ይኸ ሸዋ ማለት አጋም ነው ወይ ቀጋ፣

በዚያው አስቀረችው የእንጀራውን ዋጋ።

131. የሰው አገር አፈር በእንጨት የተማሰው፣

እንኳን አከላቱን እግሩን አላለበሰው።

132. በሰው አገር መሞት ወይ አሳር ወይ አሳር፣

ሰሌን አገኙልሽ ጠቀለሉሽ በሳር።

133. ቀባሪስ አይጠፋም ዳኛ ካለ ካገር፣

እኔን የጨነቀኝ ያስታማሚው ነገር።

134. ተጨንቃ ተጠባ ቄሶች ቀረቡና ቃሏን ሲቀበሉ፣

እናቴና አገሬ ብላ ነበር አሉ።

135. እየመለመልኝ እየሰደድናቸው፣

በነጋ በጠባ ይመጣል መርዷቸው።

136. እንጀራ ፈላጊ ቢሄድ አይታክተው፣

እስቲ መውደቂያውን ቁሜ ልመልከተው።

137. ኸረ እናንተ ሆየ ነገር ተበላሽ፣

እንጀራ ፈላጊው ሳይመለስ መሸ።

138. እንደማንም ብለህ ግባ ወደአገርህ ልቀቅ የሰው ታቦት፣

አውጥቶ እንዳይጥልህ ባላባቱ ሲሞት።

139. አምላክ በዚህ ነገር አይጠረጠርም፣

የከፍው ሰው ሙቶ ደስ ያለው አይቀርም፡፡

140. እንደ እግዚያብሄር ክፋ እንደ መሬት ሆዳም፣

ሌባ እንኳን ከበረት እራስ ላም አይነዳም፡፡

141. ኸረ ጉድ ነው እንጅ ሌላ ምን ይላል ሰው፣

የላይኛው ጌታ ፊቱን ካልመለሰው፡፡

142. አሁን ምን ሁኖት ነው አጥንቱ ቢበስል፣

ኋላ ሌላ ጌታ ያለበት ይመስል፡፡

143. በቃ መጣሁልህ የፈለከው እቃ፣

ተቀበል አምላኬ ሁንለት ጠበቃ፡፡

144. ለላይኛው ጌታ አጋፋሪ ማነው?

አንዲት ናት እህቴ ተውልኝ አንድ ሰው፡፡

145. መሬት ተረገጥኩሽ መልሼ መልሼ፣

እታረቅሻለሁ ሙሉ አካሌን ክሼ፡፡

146. ይከፈት በነበር ምድር እንደ ሳንቃ፣

የሆዴን አውጥቸ ልምረገው በጭቃ፡፡

147. ኸረ ኸኛና ምድር ታረቅን በመላ፣

ዛሬ እኛ እየበላን ኋላ እርሷ ልትበላ፡፡

148. እጀ አመድ አፋሽ ነው ምድር አማኝ አሉ፣

ያን ሁሉ መኳንንት ያን ሁሉ ወይዘሮ ያንን ሁሉ ቆንጆ ሰጥቸው በሙሉ፡፡

149. ምድርን አልወዳትም ዘመዴነን ሁላ ስጥቃ በልታለይ፣

ደሞ ለዛሬውም እኔኑ ታያለይ፡፡

ይህን ሁሉ በልታ አላት አንድ ካሳ፣

እህል ታበቅላለይ ሁሉን የሚያስረሳ፡፡

150. እግዜር በገደለው እንደ አባት አደሩ፣

ገደል ባየሁ ቁጥር ከማጉራጉሩ፡፡

156. እረ እናቴ ማርያም ጽድሽ በሰበሰ፣
አራሲቱ መጣች ጡቷ እየፈሰሰ።
157. አንች የማርያም አራስ አይችልም ወገቡ፣
ደገፍ ብለሽ ቆይኝ ከደጀ ሰላሙ።
158. አሁን ማን አለና እንደመሬት ሆዳም፣
ሌባ እንኳን መርምሮ እመጫት አይነካም።
159. ፍትፍት ያለሽ ፍትፍት ደሮ ያለሽ ደሮ፣
አራስ ተኝታለች ከበተስኪያን ጓሮ።
160. በጭብጥ ሽንብራ ይታደናል አውሬ፣
እንደዚህ ከመሞት ያድንህ ወገኔ።
161. ኸረግ አያ እከሊት እኔ አለኝ መድሃኒት፣
እህልና ውሃ እንቅልፍና ሌሊት።

162. ባለቤት ያለውስ ክዳን አለበሰ፣
ወ/ሮ እገሊት የአንችስ ቤት ፈረሰ።
163. በምን ግድግዳ ኑሯል የተሰራ ቤቱ፣
አገሬ አገሬ ይላል ህዝቡ ጎረቤቱ።
164. አልከፈት አለ ጠበቀና ደጁ፣
ባልና ሚስቶቹ ዘግተውት ቢሄዱ።
165. እኔን የገረመኝ የልገሮቹ ዝምታ፣

መገናኛቸው ቤታቸው ሲፈታ።
166. ከአያ እገሌ አልተላከም ወይ፣
እንዲህ ሲል ይቀራል ቤትና ሲሳይ።
167. ባልና ሚስቲቱ እንዲያ ሲዋደዱ፣
አልፊያለሁ እለፍ ብለው አብረው ሄዱ።
168. የጋሽ እገሌ ዋንጫ የጠጣንበቱ መዳብ የት ደረሰ፣
በኛ ነው መሰለኝ ቤቱ የፈረሰ።

169. ያንን ሁላ ቅቤ የቀዳሽበቱ፣
ምናለ እንትናየ ባይዘጋ ቤቱ፡፡
170. የደጋው ዘመድ የቆላው ዘመድ እዚያው ባለህ ባለህ፣
እገሊት ሙታለይ ወየት ትገባለህ፡፡
171. ተማሰ መሰለኝ ደረሰ ጉድጓዱ፣
መለየት አይቀርም ምንም ቢዋደዱ፡፡
172. ሄዱ ተማምለው ተማምለው፣
ልዥ ያሳደገ ሰው ውሻ ይሁን ብለው፡፡
173. ከሳ መነመነ ቀጠነ እንደ ሰበዝ፣
ገና ባሻጋሪ የሚያስፈራው ኀበዝ፡፡
174. እምሽክ ድቅቅ አለ እንደኑግ አገዳ፣
እንግዲህ እገሌ ጉልበቱም አይረዳ፡፡
175. ኧረ አየዋ እገሌ እንዲህ ታሞ ታሞ መሞትም አይበጅ፣
‹እንዲህ ብየ ተረፍኩ› ማለት ነበር እንጂ፡፡

## 5.2. የሙሾ ቃል-ግጥሞች

### 5.2.1. ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ ዋየ

አውራጆች፣ ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ ዋየ፣ (ከ5 ጊዜ ላላነሰ)
ለቀስተኛቀው፣ ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ ዋየ፣ (እንደ አውራጆቹ)
መሪ፣ ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ ዋየ (ከሶስት ጊዜ ላላነሰ)
አውራጆችና ለቀስተኛ፣ ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ (በመሪው ልክ)
መሪና አውራጅ፣ ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ ዋየ፣
ተቀባይና ለቀስተኛ፣ ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ ዋየ፣
አውራጅ፣ ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ ዋየ
ተቀባይ፣ ዋየ ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ ዋየ፣
መሪ፣ ማነው የከፈተው፣

መሪና አውራጅ፣ ማነው የከፈተው፣

ተቀባይ፣ ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ ዋየ፣

መሪ፣ የላሙን በረት፣

መሪና አውራጅ፣ የላሙን በረት፣

ተቀባይ፣ ዋየ እሉ ሄዱ ዋየ ዋየ፣

መሪ፣ ዓለምነው መንግሥቱ፣

መሪና አውራጅ፣ ዓለምነው መንግሥቱ፣

ተቀባይ፣ ዋየ እያሉ ሄዱ ዋየ ዋየ፣

መሪ፣ ተራው ደርሶበት፣

መሪና አውራጅ፣ ተራው ደርሶበት፣

ተቀባይ፣ ዋየ እሉ ሄዱ ዋየ ዋየ፣

2. በተራ በተራ በተራ ከሆነ መንገድ፣
እኛም እንመጣለን በሉ እናንተም ህዱ።

3. ክምር ከማሪና እግዜር አንድ ናቸው፣
መልሰው ሲያፈርሱት አወይ ድካማቸው።

4. እዘኑ እባካችሁ አልቅሱ እባካችሁ፣
ትልቅ ሰው ካገሩ ሲጠፋ እያያችሁ።

5. ደረሰ መሰለኝ መጣ ጉድጓድ ማሹ፣
እንግዲህ መቅረት ነው አየ ሰው ብላሹ።

5. ኸጤፍ ከዳገሳ ይዘሯል ቀናንሶ፣
ኸወደቀ ወዲያ ይቀራል በስብሶ።

7. በጎባባ ሞፈር በሰፊ ድግር፣
ሲገፋው ይውላል አፈሩን አፈር።

8. የበኸር ልኸርና ትልቅ አዳራሽ፣
ይህ ሁሉ ቀሪ ነው እንደ ሰው ፈራሽ።

9. አልቅሱ እንላቀስ እርዱ እንረዳዳ፣

ለቅሶ ተራ የለው እንደ ጤፍ አጨዳ።

10. ባለቅሰው ባለቅሰው እንባየም አለቀ ተቆረጠ አንጀቴ፣

አንተም ወዳ ፈርህ እኔም ወደ ቤቴ።

11. አገሬ አሳዘነኝ ምስራቅ አሳዘነኝ ደቡብ አሳዘነኝ፣

ፊቱን የተነጨ አይሁድ መሰለኝ።

12. ባዝን እዘኝ እንጂ ባለቅስ ትስቂ፣

አዘን ጥናቡግ ነው ለሁሉም ዘላቂ።

12. በላሁ በላሁና ተኛሁ እንደ በሬ፣

ያነን ያክል ጉድጓድ ጫን አፈር አኑሬ።

### 5.2.2. ዋየ ዋይ ወየሁ

አውራጆች፣ ዋየ ዋይ ወየሁ፣ (ከ5 ጊዜ ላላነሰ)

ለቀስተኛቀው፣ ዋየ ዋይ ወየሁ፣ (እንደ አውራጆቹ)

መሪ፣ ዋየ ዋይ ወየሁ (ከሶስት ጊዜ ላላነሰ)

አውራጆችና ለቀስተኛ፣ ዋየ ዋይ ወየሁ (በመሪው ልክ)

መሪና አውራጅ፣ ዋየ ዋይ ወየሁ፣

ተቀባይና ለቀስተኛ፣ ዋየ ዋይ ወየሁ፣

አውራጅ፣ዋየ ዋይ ወየሁ

ተቀባይ፣ ዋየ ዋይ ወየሁ፣

መሪ፣ አባይ ዙሪያው ገደል፣

መሪ አውራጅ፣ አባይ ዙሪያው ገድል፣

ተቀባይ፣ ዋየ ዋይ ወየሁ፣

መሪ፣ መጠምጠሚያው ዘንዶ፣

መሪ አውራጅ፣ መጠምጠሚያው ዘንዶ፣

ተቀባይ፣ ዋየ ዋይ ወየሁ፣

መሪ፣ ማን ይችለው ይሆን፣

መሪ አውራጅ፣ ማን ይችለው ይሆን፣

ተቀባይ፣ ዋየ ዋይ ወየሁ፣

መሪ፣ ይህን ቀን ተራምዶ፣

መሪ አውራጅ፣ ይህን ቀን ተራምዶ፣

ተቀባይ ዋየ ዋይ ወየሁ።

15. እሱማ ምን ይበል እኛ ቅጥ ብናጣ፣

የስምንተኛው ሺ. በቀጠሮው መጣ። (ወየታም ላይ አለ)

16. ይህ ስምንተኛው ሺ. ምንጊዜ ደረሰ?

እየጎሼ ያድራል እየደፈረሰ። (ወየታም ላይ አለ)

17. አልቅስ አልቅስ አለኝ አይኔም አላበለ፣

ይህ ያያዝነው ዘመን ሄደ ዘነበለ።

18. የእናቴ ልዥ ይላል ወንድማለም ይላል የማይገኘውን፣

እኛ ለፍተን ለፍተን ደክመን የተውነውን።

### 5.2.3. አወየሁ ዋይ ዋይ /ወየሁ

አውራጆች፣ አወየሁ ዋይ ዋይ፣ (ከ5 ጊዜ ላላነሰ)

ለቀስተኛቀው፣ ወየሁ፣ (እንደ አውራጆቹ)

አውራጆች፣ ኧረ እንቢ. አላኮራም ነው ወይ?

ለቀስተኛው፣ ወየሁ

መሪ፣ አወየሁ ዋይ ዋይ፣ (ከሶስት ጊዜ ላላነሰ)

አውራጆችና ለቀስተኛ፣ ወየሁ፣ (በመሪው ልክ)

መሪና አውራጅ፣ ኧረ እንቢ. አላኮራም ነው ወይ?

ተቀባይና ለቀስተኛ፣ ወየሁ፣

መሪ፣ ተነሱ እንላቀስ፣

መሪና ተቀባይ፣ ተነሱ እንላቀስ፣

ተቀባይ፣ ወየሁ፣

መሪ፣ ምን ያስቀምጥሃል፣

መሪና አውራጅ፣ ምን ያስቀምጥሃል፣

ተቀባይ፣ ወየሁ፣

መሪ፣ የጨበጠ እንደሆን፣

መሪና አውራጅ፣ የጨበጠ እንደሆን፣

ተቀባይ፣ ወየሁ፣

መሪ፣ ያቅለበልብሃል፣

መሪና አውራጅ፣ ያቅለበልብሃል፣

ተቀባይ፣ ወየሁ

መሪ፣ አወየሁ ዋይ ዋይ

መሪና፣ አውራጅ፣ አወየሁ ዋይ ዋይ

ተቀባይ፣ ወየሁ፣

መሪ፣ ኧረ እንቢ አላኮራም ነው ወይ

መሪና አውራጅ፣ኧረ እንቢ አላኮራም ነው ወይ

ተቀባይ፣ ወየሁ፣ (በእያንዳንዱ ግጥም መጨረሻ ይኸ አዝማች ይደጋገማል)

19. ኸተያዙ ወዲያ ቂስ ጥሩ ማለት፣

ያልተደላደለ የሽብር ጭነት።

20. ኑማ ኑማ ብለህ ባታስቸኩለነ፣

እንመጣልሃለን ሌላም ቤት የለነ።

21. የሥላሴ ወስኮ ወይራ ነው ማነቂያው፣

ወጋኝ እያለ ነው የሰው ልዥ ማለቂያው።

22. በእንዲህ ባለው ግዜ አይተኙም ይነቋል፣

ክፉ ክፉ ጠሪ በየ አፋፉ ዘልቋል።

22. ወልዱ ወልደ እግዚአብሔር፣

ኸሰራኸው ሥራ አንድ አበር የለህም፣

የተጣላህ ለታ ገላጋይ የለህም።

24. ኤድስ ነው ይላሉ ኤድስ ከየት መጣ?

ቲቪ ነው ይላሉ ቲቪ ከየት መጣ?

ወባ ነው ይላሉ ወባ ከየት መጣ?

ዱላ እኮ አይፈልግም እግዚአብሔር ሲቆጣ።

25. የሰንበት ቁርስና ያባት ዳረጎት፣

ምን አነሰ ቢሉት አለው ረዴት።

5.2.4. **አየ/ዋ ተለየነ/ አየ ያለው ማነው**

አውራጆች፣ አየ ተለየነ፣ (ከ5 ጊዜ ላላነሰ)

ለቀስተኞቀው፣ አየ ተለየነ፣ (እንደ አውራጆቹ)

መሪ፣ አየ ተለየነ፣ (ከሶስት ጊዜ ላላነሰ)

አውራጆችና ለቀስተኛ፣ አየ ተለየነ፣ (በመሪው ልክ)

መሪና አውራጅ፣ አየ ተለየነ፣

ተቀባይና ለቀስተኛ፣ አየ ተለየነ፣

አውራጅ፣ አየ ተለየነ፣

ተቀባይ፣ አየ ተለየነ፣

መሪ፣ በሰማይ የሚጸድቅ፣

መሪና አውራጅ፣ በሰማይ የሚጸድቅ፣

ተቀባይ፣ አየ ተለየነ፣

መሪ፣ በምድር ይጸድቃል፣

መሪና አውራጅ፣ በምድር ይጸድቃል፣

ተቀባይ፣ አየ ተየነ፣

መሪ፣ የሰንበትን አፈር፣

መሪ አውራጅ፣ የሰንበትን አፈር፣

ተቀባይ፣ አየ ተለየን፣

መሪ፣ ማን አግኝቶት ያውቃል፣

መሪ አውራጅ፣ ማን አግኝቶት ያውቃል።

ተቀባይ፣ አየ ተለየን፣

26. አንችም ዘመናይ ነሽ በሥራው መሞትሽ፣

በክረምት መሞትሽ በህምሌ መሞትሽ፣

በበጋ አትሞችም ወይ

በባል አትሞችም ወይ እንደ ድህነትሽ።

27. ደሞም እንደ ኑሮሽ ልቅሶሽ መነመነ

ምን አረግሻለሁ እድልሽ ከሆነ

አየ ያለው ማነው

አውራጆች፣ አየ ያለው ማነው (ከ5 ጊዜ ላላነሰ)

ለቀስተኛቀው፣ አየ ያለው ማነው፣ (እንደ አውራጆቹ)

መሪ፣ አየ ያለው ማነው (ከሶስት ጊዜ ላላነሰ)

አውራጆችና ለቀስተኛ፣ አየ ያለው ማነው (በመሪው ልክ)

መሪና አውራጅ፣ አየ ያለው ማነው፣

ተቀባይና ለቀስተኛ፣ አየ ያለው ማነው፣

አውራጅ፣ አየ ያለው ማነው፣

ተቀባይ፣ አየ ያለው ማነው፣

መሪ፣እንዴት አደራችሁ፣

መሪ አውራጅ፣ እንዴት አደራችሁ፣

ተቀባይ፣ አየ ያለው ማነው፣

መሪ፣ አሁንም ቅድምም፣

መሪ አውራጅ፣አሁንም ቅድምም፣

ተቀባይ፣ አየ ያለው ማነው፣

መሪ፣ ይህ የያዝነው ጊዜ፣

መሪ አውራጅ፣ ይህ የያዝነው ጊዜ፣

ተቀባይ፣ አየ ያለው ማነው፣

መሪ፣ አያስተማምንም፣

መሪ አውራጅ፣ አያስተማምንም።

ተቀባይ፣ አየ ያለው ማነው፣

28.ጭድ እንዳየ በሬ ደም እንዳየ ውሻ፣

ተስካር እንዳየ ቄስ ሰደቃ እነዳየ ስላም፣

29. ንብርብር ንብርብር አሉብኝ፣

በኋላየ የሚቆም ሰው አጥተውብኝ።

30. እናትን ለፍትፍት አባትን ለኩራት ኸሰጠኸኝማ ፣

እህትን ለእንጎቻ ኸሰጠኸኝማ፣

አባትን ለሸንጎ ኸሰጠኸኝማ፣

ወንድምን ለጥቃት ኸሰጠኸኝማ፣

ልኸየን ለመታዘዝ ኸሰጠኸኝማ፣

በሬውን ለእንጀራ ኸሰጠኸኝማ፣

ላሚቱን ለወተት ኸሰጠኸኝማ፣

እንኳን ላንጎራጉር ድምጼ ባልተሰማ።

**መውጫ**

31. ኸበተስኪያን ጓሮ አንድ እግር ጥጥ አለች

ለልብስ አትሰቡ አፈራለሁ አለች።

መሪ፣ኸበተስኪያን ጓሮ

መሪና አውራጅ፣ ኸበተስኪያን ጓሮ፣

ተቀባይ፣ አየ ያለው ነው፣

መሪ፣ አንድ እግር ጥጥ አለች፣

መሪና አውራጅ፣ አንድ እግር ጥጥ አለች፣

ተቀባይ፣ አየ ለው ማነው፣

መሪ፣ ለልብስ አትሰቡ፣

መሪና አውራጅ፣ ለልብስ አትሰቡ፣

ተቀባይ፣ አየ ለው ማነው፣

መሪ፣ አፈራለሁ አለች፣

መሪና አውራጅ፣አፈራለሁ አለች።

ተቀባይ፣ አየ ያለው ማነው፣

መሪና አውራጅ፣ አየ ያለው ማነው፣

ተቀባይ፣ አየ ያለው ማነው፣

መሪ፣ ዝናቡ ዘነበ

መሪ፣ አውራጅና ተቀባይ፣ ዝናቡ ዘነበ፣ (የነበረው ቡድን ከአውራጆቹ ጋር ይደረባል

ተቀባይ፣ አየ ተለየን (ለቀስተኛው የመቀበል ሚናውን ብቻውን ይወጣል)

መሪ፣ ማርና ወተት፣

መሪና አውራጅ፣ ማርና ወተት፣

ተቀባይ፣ አየ ተለየን፣

መሪ፣ዘር ሲቆላ ዋለ፣

መሪና አውራጅ፣ ዘር ሲቆላ ዋለ፣

ተቀባይ፣ አየ ተለየን፣

መሪ፣ ኸጌትየው ቤት፣

መሪና አውራጅ፣ ኸጌትየው ቤት፣

ተቀባይ፣ አየ ተለየን፣

መሪና አውራጅ፣ አየ ተለየን፣

ተቀባይ፣ አየ ተለየነ፣

መሪና አውራጅ፣ አየ ተለየነ፣ (ከ5 ጊዜ ላላነሰ)

ተቀባይ፣ አየ ተለየነ፣ (በአውራጆቹ ልክ)

ፍጻሜ ይሆናል

### 5.3. ቀረርቶና ፉከራ

#### 5.3. 1. ቀረርቶ

1. አባ ሙላት ገሌ፣
   አባ ገርግር ደረሰ አባ ገርግር፣ ቦጋለ አባ ገርግር፣
   ኸረ ኃይለየሱስ አብየ ወረዳህ አብየ፣
   አንት ጌቴ ደረሴ፣ ለማ ደረሴ፣
   አሰፋ ገላየ ኸረ መገኔውና አባ ሙላት ገቤ፣
   የእነ አጅሬ ወንድም፣
   ሲያታልል ነው እንጂ ሲነኩት አይወድም፣
   እረ መራኸ።
2. ኸረ ... ኸረ ... ኸረ ... ወዲያልኝ፣
   አባሙላት ሸሞንሟናየ ጌቴ፣
   ደረሴ አባ ብሃር፣
   ኸረ ወዲያልኝ ኸረ ወዲያልኝ፣
   ኸረ እርቂሁን ሞላ ኸረ አስራቴ ሞላ፣
   ሸሞንሟናው ገሌ ገላየ ክብረቴ፣
   ኸረ ወዲያልኝ ጌትነት ደረሴ ገበየሁ አባ ብሃር፣
   ሲያጉረመርም ያድራል አውራው በበረት፣
   ሞልቶ የሚያገሳው ንቡ ሀማጀት፣
   ያጎዛው የዋንጫው የገንቦው ብዛት፣
   ሸሞንሟናው ገቤ በላው ወይ መሬት?
3. ኸረ ወዮላቸው በየፍርድ ቤቱ በየመስሪያ ቤቱ፣
   በየፍርድ ቤቱ የተነገረኝ አንሶኛል ወሬ፣

ጌቴ ነበር አሉኝ ያገሩ ቆሌ፡፡

4. ኸረ አገሬ ፋርጣ በወይፈን ታረሰ፣

በጥጃ ታረሰ፣

አንድ በሬ ነበር ዛሬ ተጨረሰ፡፡

5. ብላታ ደባልቄ ሁለተዜ ሙተህ አንድ ጊዜ ተነሳ፣

ባገር ሽማግሌ እንከፍላለን ከሳ፡፡

6. እንግዲህ ወረዳ እንግዲህ አውራጃ ዘንጋዳህን ብላ፣

እየሞተ አለቀ ነጭ አምራቹ ሁሳ፡፡

7. አየ ጉድ አየ ዘመዶቼ፣

አምሳ አለቃ ጌቴ አየ ዘመዶቹ አየጉድን አየ ጉድ፣

አየ ጉድ አየ ጉድ እነገብረ መድን ጠጌ አንተ ወንድማለም፣

አየ ጉድን የባድመን ምሽግ እሳት ይዞረዋል፣

አየ ጉድን የውጋዴን ምሽግ እሳት ይዞረዋል ይዞረዋል፣

የትግሬውነን ምሽግ እሳት ይዞረዋል ይዞረዋል፣

የጦሩ ገበሬ ጌቴ ይባርከዋል፡፡

8. አፈር አፈር አለኝ አመን ያንተ እንጀራ፣

ኸረ አመን አመን ሰው ሽፈራው፣

መጣልኝ ሽፈራው ሞተ ይላል እሳ፣

ጠላት ሰርጎ ገብቶ አገሩን ሊያጠፋ፡፡

እሱ አልነበረም ወይ የርሱ መግባቢያ፣

አንች ያመነ ልኸ እስተዛሬ ድረስ ባል በባል ያጭሻል፣

ጌታውን ብሎ ነው አንችን የት ያውቅሻል፡፡

9.ስማዳ አገራችን ኩሽሌ አበቀለ፣

በጌምድር አገሬ ኩሻሌ አበቀለ፣

የሚመነጥረው የነታዬ ወንድም አንበሳው ነበረ፡፡

የወንድ አመል ማታ ሲላክበት የሚደርሰው ማልዶ፣

ለካ ሙቶ ነው ወይ የጥቃቱ መንዶ፣

አፈሩን ለኩት የበለሳው በሬ ያርማጭሆው በሬ፣

የግንብራው በሬ፣

አፈሩን ግለጡት በበላው ላይ ከራሱ ላይ፣

አይቀርም አመኑ የነካሴ ወንድም ጥቃት የመጣ ለት፣

መልኩም ወለላ ነው እንደ ሠለሞን፣

ግርማው ተፈሪ ነው እንደ አራስ ነበር፣

ወሎ እሚጠመደው ጎንደር እቃው ሲያድር።

የሴቶቹ ወንድም የወንዶቹ ባል፣

ውሽቱን እንደሆን ይመስክር አገር።

ባለፈው የሞተው ማስፈራሪያው አመን፣

አንድ ሰው ነው ወይ አንድ ሰው ነው ወይ?

የዘመዱ ቆሌ አትሉትም ወይ።

9. አባት ሳለ ቀሊል ይነሳል በአንድ እጅ፣

መግቢያ የታጣለት ይቸግራል እንጂ።

10. አባሙላት ቢያድጌ ክብረቴ፣ ባይለየኝ ክብረቴ፣

ጓዴ ክብረቴ እርቂሁን ሞላ እረ ወንድሞቼ፣

እረ አሰፋ እጅጉ፣ እረ ቂስ ክብረቴ፣ እረ ወዲያልኝ እረ ወዲያልኝ፣

እንዴነህ ገላየ፣ እነዴት ሰው ያጅላል እንዴት ሰው ያሞኛል፣

ጎንደር ከፍርድ ቤት ያለህ ይመስለኛል።

11. ገላየ ክብረቴ፣ ልዥ በዜ ክብረቴ፣ እንዳለ ክብረቴ፣

ደረሰ ክብረቴ፣ ማለደ ክብረቴ፣

አገራችን ፋርጣ አትከናላይ ነበር የኩታ ጥለት የኩታ ጥለት፣

ገላየ ነበረ ላገሩ እዳይት ።

12. ከበርሃው ወርዶ ቢያውለበልበው፣

አርገብግቦ ነዳው ንብ እንደበላው።

13. አየ እኔን ዋክንብል ያድርገኝ፣

አባ ነብሮ ገቤ አባውቃው ገቤ የእነእንዳለ ወንድም የነበዜ ወንድም፣

ኸረ ጌታው ገቤ በልቆርጣጣው ናማ፣

የደባልቂም አባት፣ የነጋሻው አባት፣

የውለታው አባት፣ የነአወቀም አባት፣
አየ ጉድ ቆፍጣኔ ናልኝማ የመስሪያ ቤቱ ቂስ፣
አየ ጉድ እናንተ ገላየ ባንተ እግር፣
ገላየ ባንተ እግር ማነው የሚተካ፣
ጌታየ ነበረ እሱም አፈረ ነካ፡፡

5.3.2. ፉከራ

5.3.2.1. ፉከራ ለጀግና

1. ፎካሪ፣ ሀይ ዘራፍ ይል ነበር ጀግናው አንበሉ!
ተቀባይ፣ እውነት ነው!
ጀግናው አንበሉ ብለው ሲጣሩ፣
ተቀባይ፣ እውነት ነው! (በየስንኙ መካከል በዚሁ መንገድ ይቀበላሉ)
በየተራራው በየሸንተሩ፡፡
እሳት የበላው ሲመስል ዛፉ፣
ዘራፍ! ዘራፍ! ተወግሌ!
የሚፎገላው ጦር ያየ ግዜ፡፡
ምነው አመኑ ጠቆረ ፊቱ?
ጠላት በሳንጃ ያረደበቱ፡፡
ፍየሉ ጥቁር እንደጆቢራ፣
የተጠመደው በቀኝ በግራ፣
ምሎ የገባው ከጠላት ጋራ፡፡
ጠላት ሲመጣ መስሎ ተረተር፣
በክላሽ ጥይት የሚያንፈራፍር፡፡
በክላሽ ጥይት ቢለው ደረቱን፣
አልተመለሰም አልዞረም ፊቱን፡፡
አጥቢያው ዝቅ ሲል ጉጉት ማደሮ፣
በክላሽ ገዳይ በሁለት ጀሮ፡፡
ደሞ ለዝና ደሞ ለወሬ፣
አባሮ ገዳይ ከሰው ቀበሌ፡፡

መተኮስና መግደል የብቻ፣
ጠላት ዘቅዛቂ እንደስልቻ፡፡
አየር በሰማይ ሲብለቀለቅ፣
ታንክ በምድር ሲደባለቅ፣
ቦንብ ሲፈነዳ እንደ መብረቅ፣
የክላሽ ጥይት ኮከብ ሲመስል፣
የም ፎርቲ ጥይት ኮከብ ሲመስል፣
ከምሽግ ምሽግ ምሽግ አዳሪ፣
እንደቂስ ጥምጣም ዝናር ተርታሪ፣
ለወገኖቹ ተከራካሪ፣
እንዳይለወስ ተዚያው ገታሪ፡፡
2. ባምስቱ ዘመን በለው ያለለት፣
ፈሪ እንደጊደር የተለየ ለት፡፡
ታጠቅ ወታደር ታጠቅ ሚኒሻ፣
ሰው እንዳይ ነካው ያባትክን ጋሻ፡፡
ያባቱን ጋሻ ያላሰቀለ፣
በግራ ክንዱ ያንጠለጠለ፡፡
መንታ እያወጣ ሲፈስ ደሙ፣
አብሶ ገዳይ በመሃረሙ፡፡
3. ይወጋ ብለን ታሪክ ካወጋን፣
ዛሬ እኮ ነው የተለያየን፡፡
አመኑ ወድቆ እንዴት ይረሳ፣
ሽፈራው ወድቆ እንዴት ይረሳ፣
አበራ ይማም እንዴት ይረሳ፣
አገር ሲወረር አልጋ ሲናጋ፣
አመኑ ነበር ወርዶ እሚዋጋ ያገሩ ጠጋ፣
ማርኮ እሚመጣው ቆላና ደጋ፡፡
ሰውየው ብርቱ ጠበንጃው ክላሽ፣

አንደዝጌ ሰላሳ ጎራሽ፣
የጠላት ግንባር በጥይት ከስካሽ፣
የተወረረ አገር አስመላሽ።
ጀግናው ሲቆጣ እሱን አትንኩ፣
ይነግር የለም ወይ አመን ሽፈራው የጠጋው መልኩ፣
4. ገና በለጋ በልጅነቱ፣
ማርኮ ይመጣል በዋለበቱ።
ከመሳሪያውም መርጦ ይይዛል፣
ከምንሽሩም መርጦ ይገዛል፣
ደሞ ከጥይት መርጦ ይገዛል፣
ገዳይ በለሳ ገዳይ ቋሊሳ፣
ኢዲሀባ ጓዙን ሲያነሳ።
ምርቱን ሲያነሳ ኢዲሀባ፣
ጀግና በለው ሲል ጠላት ሲባባ።
ጠላት ሲባባ ሲገባ ገደል፣
ለጀግናው ሁሉ ጥይት ሲታደል።
እረ የዛን ለት ደፋር ማን ነበር?
እነመኳንንት አብረው ነበሩ፣
አመኑ ሲገል በምንሽሩ፣
ጀንበሩ ሲገል በዲሞፍተሩ፣
እነዚህ ሁሉ አብረው ነበሩ።
አመን ሽፈራው ገዳይ የዛን ለት፣
ሰማይ ተቀዶ ሲቃጠል መሬት።
አመኑ ነበር የጦሩ አለቃ፣
አመን ሽፈራው ወጣት አሧሪ፣
እራስ የሚሄድ ምንሽር ገሪ፣
እራሱን አይቶ እግር ሰባሪ፣
በቀጋ ብትር ወንዝ አሻጋሪ፣

የክርስቲያን ልዥ ዝክር ዘካሪ።

6. ሀይ ዘራፍ አቶ እከሌ!

እጥፍጥፍ ብሎ የሚተኩሰው፣
ሰው እንዳገዳ የሚዘልሰው፣
አይ አባይ ማዶ በረሃ ወንዱን ያየው ሰው።
ደፋር ሲያመራ ፈሪ ሲጨነቅ፣
እንደነጎድጓድ ጥይቱ ሲፈልቅ፣
ሀጠላቱ ጋር የሚደባለቅ።
እረ ያ ጀግና ወርዶ ጦር ሜዳ፣
ከጠላቱ አንገት ደም እየቀዳ፣
ማን ይነካዋል ያገሬን ልጅ፣
ደም እንደውሃ ይወርዳል እንጂ።
ከጎጃም ወዲያ ይባላል ከፋ፣
ይነሳል ወንዱ አገር ሲከፋ።
በምንሸር ገዳይ በሚደነፋው፣
በጎንደሬ ገዳይ ባፈ ድምድም፣
በሳንጃ ገዳይ በተቀላቀል፣
ከሰውነቱ ሲፈስ ደሙ፣
አብሶ ገዳይ በመሀረሙ።

7. በክትክታ ነው ደርሶ እሚጥሰው፣

በዱላ ነበር ደርሶ እሚጠብሰው።
ሳቅ ሳቅ ይለዋል ጠብ ያየ ጊዜ፣
ሙጫው ተጋዳይ ጌቴ ደረሴ፣
ወየት ደረሰ ለማ ደረሴ?
ሳቅ ሳቅ ይለዋል ጠብ ያየ ጊዜ፣
ያ ጎርዛዛ ጌቴ ደረሴ፣
ያ ጎርዛዛ ለማ ደረሴ፣
የወንዶቹ ባል በዜ ነው አሉ፣

የምንሽር ጌጥ በዜ ነው አሉ፣
ልዥ ተሸልሟል ባተኳኮሱ በምክትሉ፡፡
ዘራፍ ጌቴ ደረሴ!
አናት የኸደ ምንሽር ገሪ፣
እግር የቀረ እርሳስ መርማሪ፣
አነጣጥሮ ተኳሽ ራስ አብራሪ፣
ዝቅ አርጎ ተኳሽ ጉልበት ሰባሪ፣
አማክሎ ተኳሽ ጉበት መታሪ፣
በዜ ክብረት የወንዱ መሪ፣
አልሞ ተኳስ ጉልበት ሰባሪ፣
ከመሃል ገብቶ የዙሪ ዙሪ፣
በዜ ወርቁ የጦሩ መሪ፡፡
በሁለት ጥይት ካልዘመተ፣
ለማ አለ ደረሴ ሞተ፣
ደረሴ ስንል ጌትነት ሞተ፣
ጌትነት ስንል እንዳለ ሞተ፣
እንዳለ ስንል በዛብህ ሞተ፣
በዛብህ ስንል ገላየ ሞተ፣
ደና መጥረቢያ ይባላል አፉ፣
በሬ ካለበት ወይፈን አይጠፋ፣
እያስዘለለ በእንቢያ እሚደፋ፡፡
እረ ደረሴ ክብረቴ፣
እረ ገላየ ክብረቴ፣
ዝናው መጣብኝ እኔስ ከቤቴ፣
ልገፍ ምሁር ነው ያቶ ክብረቴ፣
ቤቱ ሙሉ ነው ያቶ ክብረቴ፣
ቤቱ ጻዳ ነው ያቶ ክብረቴ፣
ይኸ ሁሉ ተንዶ መጥቷል ከፊቴ፣

እዘውት ጠፉ አይ መከራየ፣
አጎቴ እኮ ነው ጓንጉል ገላየ፡፡
ይደርስ ነበር ጠብ ሲጎመራ፣
ያ ጎረዝራዛ እርቂሁን ሞላ፡፡
ጌቴ አልነበረ የወንድ አረቂ፣
ለማ ደረጀ የወንድ አረቂ፣
አሰሰስ ገሰሱን አትደብልቂ፣
የክብረቴ ዘር ብለሽ ጠይቂ፡፡
አየ ሙስና ጥርስና ከንፈር፣
ገላየ ክብረት ሊበላው አፈር፡፡
እንዲህ ገላየ የጋሻው አባት፣
እንዲህ ያለምነው አባት፣
እረ የውቤም አባት፣
ገንቦ አዘንብሎ ጠጅ የሚያጠጣ፣
መጣበት ዛሬ የሞት እጣ፡፡
አይነካው የለ መናጢ ሞት፣
ያገሩን አውራ በላው መሬት፡፡
እረ ገላየ ክብረት፣
አውራጃው ገብቶብኝ እንቧ የሚለው፣
እረ ገላየን ምኑ ገደለው?
ገላየ ክብረት የበሮቹ ዘር፣
እረ ያባይ ጣና ዘር፣
ገላየ ነበር የወንዶቹ አውራ፣
ይደርስ ነበር ጦር ሲጎመራ፡፡
ገላየ ክብረት የወንዶቹ ባል፣
እንዳለ ክብረት የወንዶቹ ባል፣
ጦር መጣ ሲሉት ወርዶ ያፈጣል፣
አሰፋ በክላሽ ግንባር ይፈልጣል፣

ጠላት ሲመጣ ጋልቦ እንደደራሽ፣
አንገት አንገቱን በበልጅግ በጣሽ፣
ቢመለከተው፣
ገላየ ክብረት ባፉ ከተተው፣
እንደመዳኒት ባፍንጫው ጋተው፣
እጁ በምላጭ የመነመነው፣
ተኩሶ ሳተ የሚለው ማነው፣
ተኩሶ ማሳት ፍጹም ነውር ነው፣
የክብሬ ወገን ይሆት ታሪክ ነው፡፡
‹‹አይቀርም መሻር›› ይል ነበር ደረሴ ክብረት፣
የወንዶቹ አባት የወንዶች አርዓያ፣
የአበረ አባት አቶ ገላየ፣
የሙክቱ ባል አቶ ገላየ፣

5.3.2.2. ለተሚጋች

1. ዘራፍ ገላየ ክብረት፣
እሪ በል አገር እሪ በል ወንዙ፣
ገላየ ክብረቴ ወድቋል ጎበዙ፡፡
መስሪያ ቤት ገብቶ አይ አጣጣፉ፣
ጠላት በይግባኝ ይደፋል ባፉ፡፡
ይዞት ነው እንጂ ይህ መናጢ ሞት፣
ይቀርን ነበር የሙግቱለት፣
አገዳደሉ አሉ በላይኛው ቤት፣
የወንዶቹ አውራ ደረሴ ክብረት፣
የወንዶቹ ባል በዛብህ ክብረት፣
ሀብታሙ ወድቋል እንዳለ ክብረት፣
የሥራየ ባል ገላየ ክብረት፡፡
ደና አደራችሁ በጎቹ አንሰዋል፣
ገላየ መጥቷል ይበጥሰዋል፣

በዜ ከመጣ ይበጥሰዋል፣
መጥቷል ደረሴ ይበጥሰዋል፣
እንዳለ መጥቷል ይበጥሰዋል።
በብዙ ወንጀል መክረውበት፣
እንኳን ዘረ ቢስ አይፈራም ሞት፣
ያደገው በጹፍ በወረቀት፣
ውስቱ እኮ ነው ቤተ መንግሥት፣
በዜ ወደቀ በላው መሬት፣
ገላየ ሙቶ በላው መሬት፣
ደረሴ ሙቶ በላው መሬት፣
እንዳለ ሙቶ በላው መሬት።
እስቲ ኸደብሩ በሬ ቁጠሩ፣
እስቲ በደብሩ ወንድ ቁጠሩ፣
በዜ ክብረት የት ኸደ ነብሩ?
ገላየ ክብረት ወት ኸደ ነብሩ?
እንዳለ ክብረት ወት ኸደ ነብሩ?
ደረሴ ክብረት ወት ኸደ ነብሩ?
ጌቴ ደረሴ ወት ኸደ ነብሩ?
እንኳን ደረሴ ክብረት ደርቋል ባሀሩ።
በደብረታቦር የረታበቱ፣
በአዲስ አበባ የረታበቱ፣
በጎንደር ሀዶ የረታበቱ፣
በክልል ገብቶ የረታበቱ፣
ውሳኔ አገኘ ዛሬ ከቤቱ፣
ከውሳኔው ላይ ከወረቀቱ፣
ገላየ ክብረት ይላል ባናቱ፣
እንዳለ ክብረት ይላል ባናቱ፣
ደረሴ ክብረት ይላል ባናቱ።

ደረሴ ክብረት የወንዶቹ ባል፣
ገላየ ክብረት የወንዶቹ ባል፣
በዜ ክብረት የወንዶቹ ባል፣
እንዳለ ክብረት የወንዶቹ ባል፣
ኸፍርድ ቤቱ ያጉረመርማል፣
የተቸነፈው በዚያ እሪ ይላል፣
ማመልከቻማ ሙላው ያገባል፣
እንዳለ ክብረት ምነው ቢወለድ፣
አቶ ክብረቴ ምነው ቢወለድ፣
እንኳን አትከና የሆነ አገሬ፣
የክብረቴ ዘር ለጥቆ በሬ፡፡
ህግን የሚያሰናዳው፣
ለጥቆ ልገዞ የወንድ ዓመል ነው፣
በይግባኝ ህዶ የሚወቃ ነው፣
በይግባኝ ህዶ ሞግቶ ረትቶ፣
ርስቱን ሁሉ ኮልኩሎ አውጥቶ፣
ለሚያርስ ወጣት ኮልኩሎ ሰጥቶ፣
ያስችለው ነበር ገላየ ከቤት አምጥቶ፣
ደረሴ ክብረት ከቤት ተኝቶ፣
ይለው ነበር እንዳለ ክብረት ከቤት ተኝቶ፣
እንዳለ ክብረት የከሰሰው ሰው፣
በዜ ክብረት የከሰሰው ሰው፣
ገላየ ክብረት የከሰሰው ሰው፣
ደረሴ ክብረት የከሰሰው ሰው፣
ማለደ ደሞ የከሰሰው ሰው፣
ለማ ደረሴ የከሰሰው ሰው፣
‹‹አስታርቁኝ›› አለ መጥሪያው ሳይደርሰው፡፡
ጌቴ ደረሴ የከሰሰው ሰው፣

ይዝረጠረጣል ጉልበት ሳያንሰው።

ባላንጋሮቹ በዚህ አለፉ፣

አስተካክለው መልስ እማይጽፉ፣

ገላየ ሲወድቅ እነሱም ጠፉ።

እረ ገላየ ክብረት፣

የሰው ሁላ ሙክቱ፣

ወይም ሀብቱ፣

ወይም ጉልበቱ፣

ወይ አንደበቱ፣

ወይ ወደማታ ወይንም ማልዶ፣

የነዚህን የተወለደው ሙላው ምሁር ነው፣

እየቆጠረ እሚያስረዳ ነው፣

መሬት አንስቶ እሚሸለም ነው፣

እሚፎከረው እንደዚህ ላለነው፣

እረ የጌቴ ዘራቸው ሁሉ የሚያኮራ ነው።

6. አቶ እገላቴ ሞተወይ እርግጥ፣

በነጭ ወረቀት ከመስሪያ ቤት ላይ የሚያስደነግጥ።

በኮቢ ገዳይ በምላስ አፍራሽ፣

ባላጋራውን ከመስሪያ ቤት ላይ ቅጠል አስበጣሽ።

አሁን ማን አለ እንዳንት ያል ጀግና ሰርቶ የሞተ፣

በባላጋራው የተጫወተ።

7. ባለፈው መንግሥት ባለፈው ዳኛ፣

ወርሳነ ነበር ምድርን አፈኛ።

እረግ አፈኛ ዛሬ እንደወትሮው አለን መስሎሻል፣

ደሮ ተእንቁላል ወስደሽ በልተሻል፣

መንደር ለመንደር ምን ያዞርሻል።

8. አግማሴ መኮንን ያንበሳ ለማዳ፣

ታስሮ ይፎግራል በበየምድር እዳ፡፡

አግማሴ መኮንን የብረት ምሰሶ፣

የሰሜንን አስራት ሰደደው መልሶ፡፡

ደራና ፎገራ፣ እብናት ከምከም፣ግራሪያና ውዶ፣ መና መቀጣዋ፣

እብናት አሙስ ወንዝ፣ ጋይንትና ፋርጣ አገሬ ምናለ?

የነ አግማሴ ሱሪ ከመከታው ዋለ፡፡

አግማሴ አባ ግጠም፣

ከአውራጃው ፍርድ ቤት ብዙውን ሲወቃ፣

ከወረዳው ፍርድ ቤት ብዙውን ሲወቃ፣

ያገር ምርት ሁኖ ጎንደር ኸገቢያው ላይ ሰሜንን ይወቃል፣

እረ አገሬ ፋርጣ እርምህነን አውጣ፣

አግማሴ አባ ውቃው ተመልሶ አይመጣ፡፡

ጠንከኛው ሰሜን ይቅበጠበጣል፣

አግማሴ ደርሶ አስራት ያወጣል፡፡

ከመጣ ወዲያ በጣም ችግር ነው፣

እዚያው እያለህ መከራከር ነው፡፡

እረ አገሬ ፋርጣ ጠሀው መታው፣

አግማሴ መኮነን ተሰብሮ ጥላው፡፡

አየጉድ ልሳኑ አየ ጉድ አንደበት፣

ከናግማሴ ቦታ ወታደር ገባበት፡፡

እባክህ ወታደር ከገባህም አይቀር ቁርስህነን ብላ ቡናህን ጠጣ አታንገላታኝ፣

አግማሴ ሙቶብኝ ጠበቃም የለኝ፡፡

የሰሜን ገበሬ በሰፊው ትለም፣

‹‹ይኸ ነው ደንበሩ›› የሚልህ የለም፡፡

አግማሴ ነበረ ነበር በድንገት፣

ድንጋይ ተተንተርሷል፣

ያፈር ልጓም ነርሷል፡፡

አግማሴ አባ ግጠም እሰይ የምስራች አልሞተም ደህና ነው፣

አገሩ ተጠቅቶ ላባ ጠቅል ሀይሌ ሲናገር ህዶ ነው።

ባለቅስ ባለቅስ እንባየ ደረቀ፣

አልቀናውም መሰል እንደወጣ ቀረ።

እስቲ ላነሳሳው ኋላ ኋላውን፣

አግማሴ አባ ግጠም፣ ዓለሙ መኮንን፣ ከጨጨሆ በታይ ፍርቃ በመለስ፣

እረ አገሬ ፋርጣ ስላሙን ነው አሉ፣

ማተቡማ ሙቷል ጌታነህ ዓለሙ።

ጌታነህ[5] ዓለሙን ታቦቱን ቀብራችሁ፣

የልደት የጥምቀት ምን ታወርዳላችሁ?

የበርሜሉን ጠላ ባነሳው ቀለለኝ፣

እርጎውን በዋንጫ ባነሳው ቀለለኝ፣

አግማሴ መኮነን ሙተሃል መሰለኝ።

5.3.2.3. ለገበሬ

1. መጠጫው ዋንጫ መጥለቂያው ፋጋ፣

እንዴት ያለ ቤት ዛሬ ተዘጋ።

ባለ በሬ ነው፣ ባለ ፍየል ነው ባለ ሙክት፣

ባለ ጋቢ ነው ባለ ኮበት፣

ከቤቱ ደሞ ሚስቱ ያላት እውቀት፣

የእቃው ጥራት፣

የምታውቅበት ማብላት ማጠጣት፣

አለንጋ በመሰለ ጣት፣

የተዋበች ናት ባለ ውቅራት፣

በክፉ ቀን በችግር ወራት እስከመስከረም፣

ከደባልቄ ቤት የማይደርስ የለም፣

ይሳለሙታል ያጅሬን ቤት፣

አይደል በተስኪያን አይደል ታቦት፣

---

[5] ጌታነህ ዓለሙ ያገሪቱ ተጠሪ የነበሩ ያግማሴ ወንድም ናቸው

ቅቤና ማሩን አይተውበት።
የቆንጆይቱ ባል የዛች ከብከቦ፣
ታቀርብ ነበር ንጥር በካቦ።
እረ ደባልቄ እንዴት ላርግህ፣
አይደለሁ እግዜር በጀ አልሰራህ።

2. ምን ጫማ ቢያደርጉ፣ ምን ካቦርት ቢለብሱ፣ ምን ባየር ቢጓዙ፣
ገበሬ አይደለም ወይ የራብ መድሃኒቱ፣
አምራቹ ገበሬ ለምን ትሞታለህ፣
ሲጠማ አጠጥተህ ሲርብ ታበላለህ፣
ደግሞም ለቸገረው ዘር ታበድራለህ።
ከበላሁ ከጠጣሁ እንቅልፍ ይወስደኛል፣
ካልበላሁ ካልጠጣሁ ንዳድ እንደ ያዘው ያንቀጠቅጠኛል።
እህል መድሃኒቱ ወየት ህደህ ነበር፣
በየፈረፈሩ ሰው ሲቀበር።
እህል እናታችን እህል አባታችን፣
እህልማ ቢቀር ታየ ጉልበታችን።

3. አሰሙ ፈንታ በሬው አስራ አምስት ላሙ ቁጥሩ እንጃ፣
እስቲ ልጠይቅ ተጎረቤት፣
ስንት ኑሯልኝ የሚጠግት?
ግሬራው ብዙ ላሙ ወተታም፣
አሰሙ ፈንታ ሞንሟና ሀብታም።
በመጋኛ ነው መኪና ነድተው፣
አሰሙ ፈንታ ያን ሁሉ ሽርፋ[6] ወት አደረሰው፣
ወት አደረሰው ወዴት ጣለው?

---

[6] ጎተራ

ድሃ በክረምት እንዳይበላው፡፡
ሀብታሙ ደሞ ዘር እንዳይለውጥ፣
አይ አጨካከን አይ አቆራረጥ፣
እንዴት ያለ ሰው ዛሬ አመለጠ፡፡

4.. አቶ እገላቱ ንቡ ሲወጣ ይመስላል ዝናብ፣
ሸርፋው በታዛው ይመስላል ሰፈር፣
አሁን ይኸንን ሲበላው አፈር?
ወረዳ አውራጃ የሚያድርበት፣
ዋ ተዘጋ ወይ ያጅሬ ቤት፡፡
ደናው ገበሬ የተሰናዳው፣
ሀቤት ሲገቡ ጥሩ እሚቀዳው፣
ከኩላቡ ላይ መጫኛ አቅማዳው፣
ወይንም በርሻ ወይ በዘመቻ ስም የለለው፣
የወደቀ እንጨት ምስጥ የበላው፡፡
ተኳሽ አርበኛ አራሽ ገበሬ ቢወዳደሩ፣
ተኳሽ አርበኛ ይበልጣል ለለት፣
ሰውን ሰው ገዳይ እየተሳበ፣
ተኳሽ አርበኛ ሲፎክር ውሎ ኸገበሬ ቤት ካልበላ ማታ፣
ሩጦ አያመልጥ ተኩሶ አይመታ፡፡
እኔ ገበሬን እወደዋለሁ፣
ገንቦ አዘንብሎ አግቸዋለሁ፡፡
የገበሬ ሚስት የታደለችው፣
እያቀረበች ሁሉን ሰጠቸው፡፡

5. የተገዛ እቃ ይባላል አዲስ፣
አቶ እገላቱ የርሻው መሀንዲስ፣
ደሞ በሸርፋው ያስመሰከረ፣

ደሞ በበሬው ያስመሰከረ፣
እሁድ ቅዳሜን ባል ያከበረ፣
እነሚካኤልን እነብርኤልን ዝክር የዘከረ፣
እንዲህ ያለ ሰው ተፈርዶለታል እንዲፈከር፡፡
ሲኸድ በዝናር እንክልት የለው፣
እህል በማለቅ አሳብ የለለው፣
ምኝታው ፍራሽ ተባይ የለለው፣
እንዴት ያል ሀብታም አፈሩ በላው፡፡
አውራው ተበረት እየደነፋ፣
ላሙ ታማጋው መስሎ ሳቢሳ፣
እንዴት ያለ ሰው ዛሬ የጠፋ፡፡
6. መልካም ገበሬ በላይ ምትኩ፣
እንደስሙ የጸጋው ልኩ፡፡
አምሳ ክንድ ጨርቅ ደርቦ ለባሽ፣
ከሰፊ ማሳ በሶስት አሳራሽ፣
በብዙ አህያ ምርት አመላላሽ፣
አግብቶ ጋባዥ ከሰፊ አዳራሽ፡፡
አሰትም አይደል ያውቃል ስማዳ፣
ቀንዳም ቀንዳሙን ሙክት ሲነዳ፣
ጋሻየ በላይ መልካም ኮራህ፣
አመን ሽፈራው መልካም ኮራህ፣
የነአመን እናት መልካም ኮራሽ፣
ላገር የሚሆን ወንድ ወልደሽ፣
አመን ሽፈራው ዛሬ ይጋብዘን፣
ይምጣ ገበሬ ይብላ ይሰብሰብ፣
ጭልፋ እየያዘ ሞሰብ ለሞሰብ፡፡
የኛማ አመን መልካም አሳቢ፣
ከሰፊ አዳራሽ ወገን ሰብሳቢ፣

ከሰፊ አውድማ ምርት አራጋቢ።
የነአመኑ እናት አንች አትፍረሽ፣
ሸማኔ አይደለሁ እኔ አልሰራሽ፣
ያባ ባህር እናት አንች አትፍረሽ፣
እመቤቲቱ እንች አትፍረሽ፣
ተነግሮ አያልቅም ያ ታሪክሽ።
የጋይንቶች ዘር የቅልብልቦቹ፣
የርጥቦቹ ዘር የለምለሞቹ፣
አመኑ ቀርቶባቸው ይኸው ያለቅሳሉ ሰዎቹ።
ገዳይ በጮማ ደረቱን መትቶ፣
በቅቤ ገዳይ ትን አሰኝቶ፣
መስጠት ሳይገደው ደሞ ተክቶ፣
አዳነው እንጂ አመን ሽፈራው እርጎ አጠጥቶ።
አመን ምሽፈራው የገብሬል ምስል፣
በላይ ምትኩ የገብሬል ምስል፣
ውብ ይወለዳል ምክር ይመስል።
እንዳይቆጣ ሕጉን አትንኩ፣
መልካም ገበሬ በላይ ምትኩ፤
እንደሰሎሞን እረ አመን ሽፈራው የጠዳው መልኩ።
በየኸደበት የማያረዳው፣
እንደሰሎሞን መልኩ የጸዳው።
አገሬ ፍጀት አለብኝ ወሬ፣
አመን ሽፈራው መልካም ገበሬ።
ትጉ ገበሬ በጣም የኮራ፣
ይሰለፍ ነበር ሲጠልቅ ጮራ።
ማንቆርቆሪያ ያዙ ዋንጫ አሳልፉ፣
ዝም አትበሉ አጎዛ አንጥፉ።
ከናት አባቱ ዝናው የቆየ፣

ከነሽፈራው ዝናው የቆየ፣
ከነበላቸው ዝናው የቆየ፣
ደሳለኝ ብሩ ዝናው የቆየ፣
ሲሰጡ እንጂ ሲነጥቁ ያላየ።
ያልጎደለበት የሰጠው ቤቱ፣
አልፎ እሚጠቅመው ለጎረቤቱ።
የግድግዳው ልክ ጠረዙ ብዙ፣
የትልቅ ሰው ዘር ወገኑ ብዙ፣
ያልጎደለበት ጠጅና ብርዙ።
የሀብቱ ጌታ የተንቦላካ፣
አመን ሽፈራው ዘፋፉ ዋርካ፣
የተጠጋውን ሰው የማያስነካ፣
ህዶ ቢጠምደው ካደረው ዋልካ።
አላመረተም እረ ሶስት ጫን?
አላመረተም እረ አራት ጫን?
እናገራለሁ አፌን ሞልቼ፣
አፌን ሞልቼ እረ ልናገር፣
ምርቱ ነጭ ነው በሬውም ዘገር፣
ደሞ ይፈርሳል የሆነው ነገር፣
ሀሰቴን እንደሁ ይመስክር አገር።

# አባሪ 2

## የመረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

| ተ.ቁ | ሥም | ዕድሜ | ወረዳ | የት/ደረጃ | ሥራ | በማሕበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ኃላፊነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቀኝጌታ ዜናዊ ስቡዕ | 76 | ደብረ ታቦር ዙሪያ | የቤተክህነት | ቤተ ክህነት | የወረዳ ቤተ ክህነት ትምህርትና ስልጠና |
| 2 | መሪጌታ ክ/ማርያም አስነ | 33 | ፋርጣ | የመጻህፍት ትርጓሜ መምህር | የቤ/ክ ሰራተኛ | የአብነት ትምህርት መምህርና ቤተክህነት አገልጋይ |
| 3 | ሊቀ ማዕምራን አማረ ጌጡ | 55 | ፎገራ | የቤተክህነት | የመንግስት ሰራተኛ | የወረዳ ቤተክህነት አስተዳዳሪ |
| 4 | መሪጌታ ስቡህ ዘላለም | 45 | ደብረታቦር ዙሪያ | የቤተ ክህነት ትምህርት | ወረዳ ቤተክህነት | የእድሮች ህብረት ሊቀመንበር |
| 5 | ቀኝ ጌታ መዐዛ ንጋቱ | 82 | ደብረ ታቦር ዙሪ | ሰርቲፊኬት | ጡረተኛ | ያገር ሽማግሌና የቤተክህነት አገልጋይ |
| 6 | ግሩም ሀይሉ | 74 | ደብረታቦር ዙሪያ | ሕግ ዲፕሎማ | ጠበቃ | ያገር ሽማግሌ |
| 7 | ደሳለኝ ታየ | 62 | ደብረታቦር ዙሪያ | የቤተ ክህነት | ገበሬ | ሙሾ አውጭና ወየ ባይ |
| 8 | ዳምጤ ፈረደ | 86 | ፋርጣ | ያልተማረ | ገበሬ | ወየ ባይና ሙሾ አውጭ |
| 9 | ሞላ አየሁ | 76 | ፋርጣ | ያልተማረ | ገበሬ | ፎካሪ |
| 10 | አበረ ክበበው | 32 | ፎገራ | ያልተማረ | ገበሬ | ፎካሪ |
| 11 | ገበያው ዓለሜ | 70 | ላይ ጋይንት | 8ኛ | ገበሬ | የጀግኖች አርበኞች ማሕበር ሊቀመንበር |
| 12 | አባ አቸነፍ እንግዳ | 90 | ስማዳ | 6ኛ | ገበሬ | ያገር ሽማግሌ |
| 13 | ታከለ ንጋቱ | 52 | ፋርጣ | መሰረተ ትምህርት | ገበሬ | ፎካሪ |
| 14 | ዋለ ጎበና | 60 | ደብረ ታቦር ዙሪያ | 8ኛ ክፍል | ነጋዴ | ወየ ባይ፣ ሙሾ አውጭና ለቅሶ አስተባባሪ |
| 15 | ወንዳየ ጓንጉል | 65 | ላይ ጋይንት | | ነጋዴ | የጀግኖች አርበኞች ማሕበር ጸሀፊ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 16 | ብርሃን አበበ | 32 | ስማዳ | 12 | የመንግሥት ሠራተኛ | የመ.ኮ.ጽ.ቪ.ዲዮ ካሜራ ባለሙያ |
| 17 | ደጀን አመኑ | 32 | ላይ ጋይንት | 12+4 | የመንግሥት ሰራተኛ | የመ.ኮ.ሥራ ሂደት ቡድን መሪ |
| 18 | ምህረት ገረመው | 42 | ላይ ጋይነት | 12 | የመንግሥት ሰራተኛ | የመ.ኮ. የቪ.ዲዮ ካሜራ ባለሙያ |
| 19 | አቶ ጸጋየ ጀንበሬ | 70 | ደብረታቦር ዙሪያ | 6 | አናጺ | የእድር ገናኝ |
| 20 | አቶ ትእዛዙ አያሌው | 45 | ፎገራ | መሰረተ ትምህርት | ገበሬ | ወየ ባይና ሙሾ አውጭ |
| 21 | አቶ መላሽ ወርቁ | 49 | ፎገራ | 6 | ገበሬ | ፎካሪ |
| 22 | አያሌው ተሾመ | 73 | ስማዳ | ያልተማሩ | ግብርና | ያገር ሽማግሌ |
| 23 | ዓለምነው አሉላ | 77 | ደብረታቦር ዙሪያ | 12 | ጡረታ | ያገር ሽማግሌና የለቅሶ አስተባባሪ |
| 24 | ብላታ ቀዲሙ ዓለሙ | 80 | ደብረታቦር ዙሪያ | 12 | ጡረታ | ያገር ሽማግሌና ለቅሶ አስተባባሪ |
| 25 | አባ አቤ ገበያው | 82 | ስማዳ | ማንበብ መጻፍ የሚችሉ | ግብርና | ያገር ሽማግሌ |
| 26 | ሻምበል አብርሃም አሰገድ | 84 | ስማዳ | 6ኛ | ጡረተኛ | ያገር ሽማግሌ |
| 27 | ተስፋየ ባየ | 36 | ፎገራ | 12+2 | የመንግስት ሰራተኛ | የመ.ኮ.ጽ.ቤ ቪ.ዲዮ ካሜራ ባለሙያ |
| 28 | ሲሳይ ታደገ | 37 | ስማዳ | 12 | የመንግስት ሰራተኛ | የመ.ኮ.ጽ.ቪ.ዲዮ ካሜራ ባለሙያ |
| 29 | አበበ በዛ | 50 | ደብረታቦር ዙሪያ | 12 | የዞን ባሕልና ቱሪዝም የካሜራ ባለሙያ | የእድር ሊቀመንበርና ለቅሶ አስተባባሪ |
| 30 | ኃይለየሱስ መኩተ | 62 | ፎገራ | 8 | ነጋዴ | ያገር ሽማግሌ |
| 31 | ወ.ሮ ፈለቁ ከበደ | 47 | ደብረታቦር ዙሪያ | 4 | የቤት እመቤት | ወየ ባይ |
| 32 | አራጋው ታረቀኝ | 84 | ፋርጣ | መሰረተ ትምህርት | ገበሬ | ሙሾ አውጭና ለቀሶ አስተባባሪ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 33 | አቶ ፊቃዱ ንጋቱ | 44 | ፋርጣ | መሰረተ ትምህርት | ገበሬ | ወየ ባይ |
| 34 | ቀኝ ጌታ ጌትነት እጅጉ | 60 | ደብረታቦር ዙሪያ | የቤተ ክህነት ትምህርት | ወረዳ ቤተክህነት | የእድር ሊቀመንበር |
| 35 | ግዛቸው ደምሴ | 35 | ስማዳ | 12 ክፍል | ንግድ | |
| 36 | ጠና ገበያው | 84 | ስማዳ | ›› | ግብርና | ያገር ሽማግሌ |
| 37 | ሀይሌ ዘውዱ | 78 | ስማዳ | ያልተማሩ | ግብርና | ያገር ሽማግሌ |
| 38 | ታደለ ሲሳይ | 78 | ስማዳ | ›› | ግብርና | ያገር ሽማግሌ |
| 39 | ካሣው አራጌ | 68 | ፎገራ | ያልተማሩ | ግብርና | ያገር ሽማግሌ |
| 40 | ያረጋል ጌታሁን | 84 | ስማዳ | ማንበብና መጻፍ | ግብርና | ያገር ሽማግሌ |
| 41 | ተሳፋው አራጌ | 72 | ላይ ጋይንት | ያልተማረ | ግብርና | ያገር ሽማግሌ |
| 42 | ጥሩነህ ጎሹ | 81 | ላይ ጋይንት | ያልተማረ | ግብርና | ያገር ሽማግሌ |

# አባሪ 3

## መረጃዎቹ የተሰበሰቡባቸው የለቅሶ ሥርዓቶች

| የሟች ሥም | ወረዳ | የለቅሶ አይነት |
|---|---|---|
| አዛለች ቸኮለ | ፋርጣ | 8/09/04 የዕለት |
| አለምነው መንግሥቱ | ፋርጣ | 14/09/04 የዕለት |
| ቀነኒብሽ | ደብረታቦር ዙሪያ | 22/09/04 የዕለት |
| ደባልቄ ገበየሁ | ፎገራ | 25/09/04 ቀጠሮ |
| መኮንን ድንቁ (ሕጻኑ) | ፎገራ | 18/09/04 የዕለት |
| አጸዱ ስመኝ | ደብረታቦር ዙሪያ | 27/09/04 የዕለት |
| ዋለ ቸኮል | ፋርጣ | 29/09/04 ቀጠሮ |
| ሕይወት አድማሱ | ደብረታቦር ዙሪያ | 06/10/04 የዕለት |
| ጸሐይ እንግዳየሁ | ደብረታቦር ዙሪያ | 8/09/04 የዕለት |
| አየነው አብተው | ላይ ጋይንት | 18/10/04 የዕለት |
| አመኑ ሽፈራው | ስማዳ | 18/04/98 ቀጠሮ |
| ጌትነት ዘለቀ | ፎገራ | 09/10/04 ቀጠሮ |
| ሳለም ሉላየ | ስማዳ | 04/05/06 ቀጠሮ |
| አስረስ ጥሩነህ | ላይ ጋይንት | 11/05/06 የዕለት |
| አንችናሉ ከበደ | ደብረታቦር ዙሪያ | 01/10/04 የዕለት |
| መላኩ ፈጠነ | ደብረ ታቦር ዙሪያ | 4/09/04/ ቀጠሮ |
| አስናቀች የማታ | ደብረታቦር ዙሪያ | 11/09/04 መርዶ |
| ዘውዱ ከበደ | ደብረታቦር ዙሪያ | 11/09/04 መርዶ |
| አማረ አቸነፍ | ስማዳ | 23/2/2003 የዕለት |
| ገላየ መኮንን | ፋርጣ | 2001 የዕለት |
| በላይ ተካ | ስማዳ | 2004 ቀጠሮ |
| መለስ ዜናዊ | ስማዳ | ነሐሴ 23/2004 ቀጠሮ |

## አባሪ 4

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡት ጥያቄዎች ተለይተው ለተጠቀሱት ቡድኖች ለመነሻ እንዲሆኑ (ጠያቂው በውይይት ወቅት የሚያነሳቸውን ርእሰ ጉዳዮች) ለማመልከት እንዲያግዙት የተነደፉ ናቸው። መረጃዎቹ ሲሰበሰቡ ከቀብር ሥርዓት፣ ከሀዘን አገላለጽ ልማድ፣ ከመታሰቢያ ሥርዓቶችና ሞት በቤተሰብና በማህበረሰቡ ላይ በሚስከትላቸው ውጤቶች ዙሪያ ከጥያቄና መልስ ይልቅ በጨዋታ በተዋዙ ውይይቶች ተጠያቂዎቹ ነጻ ሆነው የተነሳውን ርዕሰ ጉዳይ ከተለያየ አቅጣጫ እያዩ በሚመልሱበትና መረጃ ሰብሳቢውም ይህንኑ ተከትሎ ጥያቄዎችን እያነሳ የተፈለገው ቁምነገር በሚዳሰስበት እንጂ፤ የተዘረዘሩትን መነሻዎች አንድ በአንድ እየጠየቀ መረጃዎቹ አልተሰበሰቡም።

### ሀ.ለቤተክርስቲያን አባቶች

1. በቤተ ክርስቲያን ሞት ምንድነው? (እንዴት ይገለጻል) ምስል ይኖረዋል?
2. ሰው ሲሞት ምን ምን ተግባራት በቅደም ተከተል ይከናወናሉ?
3. የግንዘት ሥርዓት እንዴት ይከናወናል?
   - 3.1. የተለያዩ የግንዘት ሥርዓቶች አሉ?
   - 3.2. ካሉ የሚለያዩበት ምክንያት ምንድን ነው?
   - 3.3. እነዚህ የግንዘት ሥርዓቶች በመጽሀፈ ግንዘት ከተጠቀሰው ጋር አብረው ይሄዳሉ?
   - 3.4. ትዕምርታዊ ፍቾቻቸውስ ምንድን ናቸው?
4. የጉዞ ፍትሃት የሚደረገው ለምንድን ነው? ሀይማኖታዊ መሰረት አለው?
   - 4.1. ስንቴ ነው የሚደረገው?
   - 4.2. በእያንዳንዱ ፍትሃት የሚደረገው ጸሎት ምን ምን ተብሎ ይጠራል?
   - 4.3. በመካከላቸው ያለው ልዩነቱ ምንድን ነው?
5. አስከሬን ቤተክርስቲያን እንዲዞርና እንዲሳለም የሚደረገው ለምንድን ነው?
6. የአስከሬን አቀባበርን በተመለከተ (ተንጋሎ፣ በጎን፤ አቅጣጫ፣ምስራቅ፣ሰሜን) የቤተክርስቲን ሕግ ምን ይላል፣ (እንዲህ የሚቀበረውስ ለምንድን ነው?)

7. ቤተክርስቲያን ስሙታን ምን ምን መታሰቢያዎች መደረግ አለባቸው ትላለች?

   7.1. የእያንዳንዱ መታሰቢያ ትርጉምስ ምንድን ነው?

   7.2. መታሰቢያ እንዳይደረግላቸው የሚከለከሉ አሉ? ካሉ ለምን?

8. ቤተክርስቲያን በለቅሶ ላይ የሙሾዎችንና የፉከራዎችን መከወን እንዴት ትመለከታቸዋለች?

9. ቤተክርስቲያን ስለሀዘን አገላለጽ የደነገገችው ሕግ አላት?

   9.1. ካላት የሟች ቤተሰቦችና የቅርብ ዘመዶች ሀዘናቸውን እስከመቼ በምን መንገድ መግለጽ አለባቸው ትላለች?

   9.2. ደረት በመድቃት፣ ፊት በመቧጠጥ፣ ጸጉር በመንጨት፣ ጥቁር በመልበስ የሚገለጹ ሀዘኖችን እንዴት ትመለከታቸዋለች?

10. ቤተክርስቲያን ከሞት በኋላ ነፍስ ወደየት ትሄዳለች ብላ ታስተምራለች?

11. እንዴት እንደምትንዝስ ይታወቃል?

12. ፍጻሜዋስ ምን ይሆናል?

13. አንድ ሰው በወጉና በሥርዓቱ ባይቀበር

   13.1. በራሱ ላይ ምን ይከሰታል?

   13.2. በዘመዶቹና በአካባቢው ላይስ?

14. ሬሳ ወደቀብር ሲወሰድ ሲል ከቤት የሚወጣው በየት ነው? ወደቤተክርስቲያን ሲወሰድስ እግሩ ነው ራሱ የሚቀድም? ለምንድነው እንደዚያ የሚሆነው?

15. ሬሳ ከተቀበረ በኋላ የሟች የቅርብ ቤተሰቦች መቃብሩ ላይ አፈር ጨብጠው እንዲመልሱ የሚደረገው ለምንድን ነው?

16. ከቀብር በኋላ አልቃሽ ወደሟች ቤት ተመልሶ የሚበላው እዝን ምን ሀይማኖታዊ ትርጉም አለው?

17. ሬሳን በውሃ የሚታጠበውና ውሃ ባልነካው ጨርቅ የሚገነዘው ልምንድን ነው?

18. መብራት የሚበራው ለምንድን ነው?

19. የመብራቶቹ ቁጥር ለማንኛውም ሟች ተመሳሳይ ነው ወይስ ይለያያል?

ለ. ለሙሾ አውራጆችና ፎካሪዎች

ሀ. ግለሰባዊ መረጃ

ሥም ---------------------- ጾታ -------------------- እድሜ --------------- ቀበሌ -------------------

በሙያው የቆዩባቸው ዓመታት --------------------------- ሌላ ተጨማሪ ችሎታ ----------------

ለ. ጥያቄዎች

1. ሙያውን እንዴት ተማሩት?
2. ሙሾ ከማውጣትዎ በፊት ምን ምን ዝግጅት ያደርጋሉ?
3. ሙሾ ወደሚያወርዱበት ለቅሶ ሰዎች ጋብዘወዎት ነው የሚሄዱ ወይስ በራስዎት ነው?
4. አንዳንዶቹ ሙሾዎች ተደጋጋሚ ሲሆኑ አንዳንዶቹ አዳዲስ ናቸው፡፡ አዲስ ሙሾ ለመፍጠር መነሻ የሚሆነዎ ምንድን ነው ?
5. በሙሾ አውራጆች መሃል ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል?
    5.1. በመተባበር
    5.2. በመወዳደር
6. ሙሾ ላወረዱበት ክፍያ ይሰጠዎታል? ከተከፈለዎት በቅድሚያ ነው ወይስ ከጨረሱ በኂላ?
7. የሙሾ ግጥሙን የሚገጥሙት ከምን በመነሳት ነው?
8. በሙያዎት ሕብረተሰቡ ለእርስዎ ያለው ከበሬታ ምን ይመስላል?
9. በየለቅሶው አዳዲስ ሙሾ ነው የሚያወጡ ወይስ ቀደም ያለውን ነው የሚደጋግሙት
10. ከዛሬ 15 እና 20 ዓመት በፊት በነበረውና በአሁኑ ሙሾ መካከል ያለውን ልዩነት እስኪ ይግለጹልኝ፡፡
11. በአንድ ለቅሶ ላይ የሙሾ መወረድ ምን ጥቅም ያለው ይመስለዎታል?
12. አሁን ከሚያዩት በመነሳት የሙሾ ባህል ምን የሚሆን ይመስለዎታል?
13. ወጣቶች ወደ ሙያው እንዴት ነው የሚገቡ/ እንዴት ይለምዱታል/?
14. ወደዘህ ሙያ ባልገባሁ የሚያሰኝ ጸጸት አጋጥሞዎት ያውቃል?
15. ሙሾ በማውረድዎ ምን ጥቅም አግኝተዋል?



አቶ ደሳለኝ ታየ፣ በሙሾ ክወና ታዋቂና ስለቃል-ግጥሙ ጠለቅ ያለ እውቀት ያላቸው ቁልፍ መረጃ አቀባይ



አቶ ገበያው ዓለሜ በቀኝ በኩል እና አቶ ወንዳያ ጓንጉል ስለ አካባቢው የለቅሶ ሥርዓትና ታሪካዊ ሂደቱ ሰፊ እውቀት ያላቸው መረጃ አቀባዮች



ስለደብረታቦር ከተማ ታሪክ አዋቂው አቶ ግሩም ሀይሉ



*በግራ በኩል ስለአካባቢው የለቅሶ ሥርዓት አዋቂው አቶ አራጋው ታረቀኝ በቀኝ በኩል በተለይ ከታሪክ ጋር አያይዘው በመፎከር ጠወዳዳሪ እንደሌላቸው የተመሰከረላቸውና (ቁልፍ መረጃ አቀባዩ) አቶ ሞላ አየሁ*



*ታከለ ንጋቱ፣ ከዞኑ አልፎ ወደአጎራባች ዞኖችም በመሄድ በፉከራና ወየታ ችሎታው እየተከፈለው የሚያስለቅስና በዚህ ጥናት ቁልፍ መረጃ አቀባይ*

16.የሚች የቅርብ ቤተሰቦችና ዘመዶች ለሚች ሙሾ በመወረዱ ምን ጥቅም የሚያገኙ ይመስለዎታል?

17.ሙሾ የሚወረደው ለእነማን ነው? የማይወረደውስ?

18.ጎበዝ ሙሾ አውራጅ ወይም ፎካሪ የሚባለው እንዴት ዓይነት ሰው ነው?

19.በሙሾ፣ በወየታ እና በፉከራ መካከል ምን ልዩነት አለ? (አከዋወናቸውን መጠየቅ)

ሐ. ባሕሉን ጠንቅቀው ለሚያውቁ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች

በዚህ አካባቢ በለቅሶ ላይ የሚቀርቡ ግጥሞች ምን ምን ተብለው ይጠራሉ?

1. አንድ ሰው ሲሞት በቅድም ተከተል የሚከናወኑ ተግባራት፡-
   ሀ. ሬሳ በማሰናዳት፣ መከፈን
   ለ. ለቤተ ዘመድና የአካባቢው ሰው ጥሪውን በማስተላለፍ
   ሐ. የማታና የሌሊት ለቅሶ ምን እንደሚመስሉና በእነማን ምን ምን ተግባርት እንደሚከናወኑ፣
2. የሬሳ ከቤት አወጣጥና ጉዞ
   ሀ. እንዴት (በየት በኩል) እንደሚወጣ
   ለ. ሬሳው ሲወጣ ምን ምን ልማዳዊ ድርጊቶች እንደሚፈጸሙ
   ሐ. ከቤት እስከማርገኛ ጨዋ/ካህናት ምን እንደሚያደርጉ
   መ.በማርገኛ እና በቤተክርስቲያን ምን እንደሚደረግና ቀብሩ እንዴት እንደሚፈጸም
   ሠ. ለቀስተኛው ሀዘንተኞቹን እንዴት እንደሚያሰናበታቸው/ ሀዘንተኞቹ ወደቤት እንዴት እንደሚመለሱ
   ረ. እዝን በማንና እንዴት እንደሚቀርብ
3. የሚች የቅርብ ዘመዶች ሀዘን አገላላጽ በአለባበስና በአካል ላይ በሚፈጸሙ
   ሀ. በለቅሶ ቀን
   ለ. ከለቅሶ ቀን በኋላ (እስከ ሰልስት፣አርባ፣መንፈቅ፣ዓመት)
4. ለሚች የሚደረጉ መታሰቢያዎች አፈጻጸምና የሚቀርብ መስተንግዶ
   ሀ. ሰልስት፣ሰባት፣ አሰራሁለት ሰላሳ፣ አርባ
   ለ. ተዝካር፣ መንፈቅ ዓመታት
5. በለቅሶ ላይ የሚቀርቡ ግጥሞች አይነትና ክዋኔ በእነማን፣ ለእነማን፣ የትና መቼ እንደሚቀርቡ

ሀ. የሙሾ አቀራረብ (አቅራቢው ምን ሲያደርግ ተቀባዩ ምን እንደሚል፣ እንዴት ተጀምሮ እንደሚያልቅ)

ለ. የወየታ አቀራረብ (ወየ ባዩ ምን ሲል ተቀባዩ ምን እንደሚል፣ አጀማመር አጨራረሱ)

ሐ. የፉከራ አቀራረብ (ፎካሪው ምን ሲል ተቀባዩ ምን ይላል እንዴት ተጀምሮ ያልቃል)

(እነዚህ የሚቀርቡላቸው እንማን እንደሆኑ፣ የማይቀርቡላቸው፣ የሚቀርቡበት ቦታና ጊዜ)

6. የለቅሶ ስርዓት መከናወንና በዜማዊ ግጥሞች መታጀቡ፡-

ሀ. ለሟች ምን ጥቅም እንዳለው

ለ. ለሟች ቤተሰብና ቤተዘመድ ምን እንደሚጠቅም

ሐ. በለቅሶው ለሚውለው ሰው ምን እንደሚጠቅም

7. በለቅሷቸው ላይ ሙሾ ፉከራና ቀረርቶ የሚደረግላቸው እንዴት ላሉ ሰዎች ነው?

8. ኅበዝ ፎካሪ ወይም ወየ ባይ የሚባለው እንዴት አይነት ሰው ነው?

9. በለቅሶ ላይ ሰዎች ከሀዘንተኞቹ ጋር ሲገናኙ ትከሻ ለተከሻ የሚነካኩት ለምንድን ነው?

10. ወየ ሲባል ዋንጫ፤ ሲቅራራና ሲፎከር ጠበንጃ፤ የሚያዘው ለምንድን ነው?

11. ሙሾ ወይም ፉከራ ለቋሚና ለሟች ምን ጥቅም አለው?

በቀጠሮ፣በመርዶና በክትኩስ ለቅሶ መካከል ምን ምን ልዩነቶች ይታያሉ?

አባሪ አምስት

ተጨማሪ ፎቶዎች



*ቀኝ ጌታ ዜናዊ ስቡህ፣ ከሀይማኖት ጋር ለተያያዙ የለቅሶ ሥርዓቶች የጠለቀ እውቀት ያላቸውና ቁልፍ መረጃ አቀባይ*



*መሪጌታ ክፍለማርያም አለነ፣ ከ[illegible]ት ሥርኣት ጋር ሀይማኖታዊ ማብራሪያ መስጠት ጀምረ በዚሁ ዙሪያ የተጻፈውን ረቂቅ አንብበው አስተያየት በመስጠት ያገዙ ቁልፍ መረጃ አቀባይ*



የሟች ባለቤት ከፊት የባላቸውን ሲሪ ከኋላ ልጆቻቸው ኮታቸውን ደርበው በለቅሶው ላይ ሀዘናቸውን ሲገልጹ



የሟች ሚስት በቀኝ በኩል ሱሪያቸውን፣ ልጃቸው በግራ በኩል ማቅ ለብሰው ሀዘናቸውን ሲገልጹ



የሟች የቅርብ ቤተሰቦችና ጓደኞች የሀዘን አለባበስ (ለሴት)



የሀዘንተኞቹ አለባበስ ለሁሉም



መሾ አውራጆቹ እያረገዱ ሲጠጋጉ



ካህናቱ አስከሬኑን እየፈቱ ጸሎት ሲያደርሱ



ከቤተክርስቲያን ሬሳው እንዲሰግድ ሲደረግ



አባ ዳምጤ ፈረደ፣ በሙሾና በወየታ ቃል-ግጥም

ከዋኝነታቸው ታዋቂ የሆኑት ቁልፍ መረጃ አቀባይ

## ማረጋገጫ (Declaration)

የለቅሶ ሥርዓት ክወና በደቡብ ጎንደር ዞን፤ በሚል ርእስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት በፎክሎር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት፣ ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ሥራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢ የሆኑና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ሕጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ሥም ........[illegible]........ ፊርማ ........[signature]........ ቀን ........[illegible] 2007



*በቀኝ በኩል አባ አቤ ገቢያውና በግራ በኩል ሻምበል አብርሃም አሰገድ ስለለቅሶ ስርዓቱም ሆነ ቃል-ግጥም ክወናዎቹ ሰፊ ማብራሪያ የሰጡ መረጃ አቀባዮች*

## ማረጋገጫ (Declaration)

የለቅሶ ሥርዓት ክወና በደቡብ ጎንደር ዞን፤ በሚል ርእስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት በፎክሎር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት፣ ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ሥራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢ የሆኑና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ሕጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ሥም...................................................... ፊርማ ........................ ቀን.............................